# ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት



# ሕይወቴና
# የኢትዮጵያ እርምጃ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ሕይወቴና
# የኢትዮጵያ እርምጃ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

1ኛ መጽሐፍ

ኢንግላንድ ባዝ 1929 ዓ. ም.

መጽሐፉን በድጋሚ ለማሳተም

መብቱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ነው

መጀመሪያ እትም 1965 ዓ.ም ።

ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀዳማዊ ፣ ኃይለ ሥላሴ ፣

ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።



# መቅድም

በጭንጫና በጠነከረ መሠረት ላይ የታነጸን ቤት ፣ ዝናብ ቢዘንብ ፡ ጐርፍም ቢጐርፍ ፡ ነፋስም ቢነፍስ ፡ ገፍተው ሊጥሉት አይችሉም። የእኔንም የሕይወት ታሪክ አንዳንድ ሰዎች ባለማወቅና በመሳሳት ፡ ወይም በምቀኝነት ፡ እውነት አስመስለው ጽፈው ፣ ሌሎችን እንዲመስላቸው ለማድረግ ቢፈትኑ ፣ የውነተኛውን ነገር ከስፍራው ሊያናውጹት አይችሉም ።

የሕይወቴን ዜና ለመጻፍ ምክንያትና ጊዜ ባገኘሁበት በዚህ ሰዓት ፣ ከጽሕፈት አስቀድሜ ጸሎቴን እንደሚከተለው ለፈጣሪዬ አቅርቤ ወደፊት እቀጥላለሁ።

አቤቱ ድካም የሌለብህ ኃያል ፡ ኀልፈት የሌለብህ ዘለዓለማዊ ሆይ ፡የምትሠራውን ሥራህንና ፍርድህን በማድነቅ ከመወሰን በቀር ፍጡር መርምሮ ሊደርስበት አይችልም።

በዚህ ባለፈውና ባሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተራው ሰው አንሥቶ እስከ ንጉሥ ነገሥቱ ፣ ለጊዜው በኀዘን ባሕር እንዲሰጥም ፡ የኢጣልያ ሕዝብ እስከ ንጉሥ ለጊዜው በደስታ ባሕር እንዲዋኝ ያደረግህበትን ምክንያት ፣ አንተ ብቻ ታውቀዋለህ እንጂ ፍጡር ተመራምሮ ለማወቅ የማይችለው ረቂቅ ምስጢር ነው ።

በአርአያህና በምሳሌህ ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ፡ ነፍሱን ከሥጋው እስከምትለይበት ቀን ድረስ ካንተ የሚለምነውን ሁሉ ፣ አይደረግልኝም ብሎ ተስፋ የሚቆርጥ ስለሌለ ፡ ኢትዮጵያም ነፃነቷ እንደጠፋና በባዕድ ገዥ እጅ እንደ ወደቀች እንዳትቀር፣ሕዝቦችዋም የባዕድ ገዥን በመፍራት አፋቸው እንደ ተዘጋ ፡ በቀላል ቀንበርና በደስታ ወደ ሥልጣኔ የሚመራቸውን ኢትዮጵያዊ ገዢያቸውን በማጣት ልባቸው እንደተጨነቀ እንዳይኖሩ የቸርነትህን ሥራ ሠርተህ ታድናቸው ዘንድ እንለምንሃለን ።

አቤቱ የስደተኞች አገር ፣ የዕውሮች ብርሃን ሆይ ፡ እውነትና ፍርድ ዙፋኖችህ ናቸው። ስለ ነፃነታችን ካገራችን በግፍ ወጥተን የተሰደድነውን እኛንም ተቀበለን። እንደዚህም ብለን እንለምንሃለን። ስለ ብዙ ምሕረትህ ነው እንጂ ፣ ስለ ጽድቃችን አይደለም ።

አሁንም ከ13 ዓመት ዕድሜዬ ጀምሮ እስከዚህ ዘመን እኔን መሣሪያ አድርገህ በሠራኸው መሠረት ፣ ዜና ሕይወቴን ለመጻፍ አስቤ ጀምሬአለሁና ፣ ለፍጻሜው ፈቃድህ እንዲሆን እለምንሃለሁ። ይህንንም ለመጻፍ ያሰብሁበት ምክንያት ምንም ካንተ የተሰወረ ባይሆን ፣ በዚህ ጽሑፍ ላይ ልገልጸው ይገባኛል ።

አንደኛ ፣ አንተ በፈቀድኸው አድርገህ በምትሠራው ሥራ ሁሉ ስምህ እንዲመሰገንበት ነው።

ሁለተኛ ፣ ሰውን በዚህ ዓለም ላለው ክብር ባለጠጋና ከሌሎችም ፍጥረቶች በላይ አድርገህ ስትሾመው ፣ በቸርነትህና በለጋስነትህ ብቻ እንጂ ያለዋጋ መሆኑእንዲታወቅ ነው።

ሦስተኛ ፣ በዚህ ታሪክ ውስጥ የሌላ ሰው ስም በሚጠራበት መስመር ሁሉ በማዳላት ወይም በመጥላት ሳይሆን በስሕተት ከሚሆነው በቀር እውነቱን ብቻ ለመጻፍ ልባችንን ዳኛ ማድረጋችንን አንተ ታውቃለህ ።

አራተኛ ፣ ምንም በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተጻፈ ባይኖር ፣እንደ አሰብሁት ለመጻፍ እንድችል ብታደርገኝ ወደ ፊት የሚነሡት ወገኖቻችንና ወንድሞቻችን «ያለ እኔ ምንም ለመሥራት አትችሉም» ያልከውን ቃል ተመልክተው ባንተ እርዳታ ብቻ ሥራ መሥራት እንዲችሉ ልባቸው እንዲረዳው ነወ

አምስተኛ ፣ ሰው በደስታም በመከራም ጊዜ ቢሆን ያንተ መሣሪያ መሆኑን አምኖ በራሱ ቆራጥነትና ትጉህነት ሥራውን ካልሠራ በሌላ ሰው ፈቃድ ብቻ የሚሠራ ሆኖ አላፊነቱ የማይቀርለት ስለሆነ ፣ በተፈጥሮና በትምህርት ባገኘው መሥራት የሚገባው መሆኑን እንዲያውቀው ነው።

ስድስተኛ፣ ማናቸውም ሥራ ቢሆን በጊዜና በዕድሜ ይፈጸማል እንጂ፣ በምኞት ሊፈጸም የማይቻል መሆኑን ሰው ሁሉ እንዲያውቀውና እንዲረዳው ነው።

ለዚህ ሁሉ ሙሉ ፈቃድህ እንዲሆን እለምንሃለሁ ።

# መግቢያ

ማናቸውንም ሥራ ቢሆን ሰው ይጀምራል እንጂ እግዚአብሔር ካላገዘውና ካልረዳው ሊፈጽም አይችልም። እስከሚቻለውም ሠርቶ የጀመረውን ሥራ ሳይፈጽም ቢቀር ፣ ሰነፍ ተብሎ አይታማም። እንደዚሁ እኛም ከንግሥተ ሳባና ከሰሎሞን ዘር በመወለዳችን የኢትዮጵያን መንግሥት በፊትም በእንደራሴነት በኋላም በንጉሠ ነገሥትነት አደራ ከተቀበልንበት ከ1909 ዓ. ም. ጀምሮ እስካሁን ያገሩን ውስጥ ሥራ በየጥቂቱ ለማሻሻል። የምዕራባውያንንም የሥልጣኔ ሥራ ባገር ውስጥ አስገብተን ሕዝባችን ወደ ትልቅ ደረጃ የሚደርስበትን በሚቻለን ሁሉ ጀምረናልና ሕሊናችን አይወቅሰንም።

በየጥቂቱ ማለት ሕፃንን ልጅ በማባበልና በማስለመድ ካልሆነ በቀር በእጁ የያዘውን ነጥቆ ቢወስዱበት ደስ አይለውም። በማሳየትና በማቅመስም ካልሆነ ማናቸውንም ምግብ ቢሰጡት ሊመገበው አይፈቅድም። ጥርስም እስቲያበቅል ወተት ወይም ሌላ ለስላሳ ምግብ ካልመገቡት፥ዳቦ ወይም ሥጋ ቢያቀርቡለት ሊመገበው አይችልም ።

እንደዚሁም በትምህርት ቤት ሳይማርና በሮውም የዕውቀትን ነገር ሳይሰማ በዓይኑም ሳይመለከትና ሳይመረምር በልማድ ብቻ የሚኖረውን ሕዝብ ብዙ ዘመን የኖረበትን ልማዱን በትምህርት አስለቅቆ አዲስ ልማድ እንዲቀበል ለማድረግ በመቸኩልና በጭካኔ ሥራ ሳይሆን በትዕግሥትና በትምህርት በየጥቂቱ በቀን ብዛት ማስለመድ ያስፈልጋል ማለት ነው።

በ1901 ዓ.ም ዐፄ ምኒልክ ታመው ከቤት ስለ ዋሉ ፡ ከዚያም ወዲህ የልጅ ኢያሱ እንደራሴ ራስ ቢትወደድ ተሰማ በተሎ ስላረፉ ፣ ስድስት ዓመት ያህል መንግሥቱን ለመምራት ሥልጣን የተቀበሉት ልጅ ኢያሱ አላፊነቱን ለመሸከም ስለ አልቻሉ፣ በ1909 ዓ. ም. አላፊነቱን በተቀበልሁ ጊዙ ፣ስድስት ዓመት ሙሉ የተበላሸውን ለማቅናት ፡ ያልተጀመረውንም ሥራ እንዲጀመር ለማድረግና አዲሱን ሥልጣኔ ለማግባት ፡ አሳቤና ይልቁንም አርጉውን ልምድ ለሚወደው ሕዝብ አጋዥ ስለ ነበረው ፡ በሁለት ብረት መካከል እንዳለ እንጨት አጣብቀውኝ የተቻለኝን እየሠራሁ ጊዜውን አሳለፍሁ። በመዝናናት ሰውነትን ደስ የሚያሰኝ ሥራ በመሥራት የማሳልፈው ጊዜ ጥቂት ነበር። ከተጀመረው ካገሩ ውስጥ ሥራ ያቃናሁትና አዲስ የሠራሁት ፡ ከውጭ አገርም የሥልጣኔ ሥራ ባገር ውስጥ እንዲገባ ያደረግሁት ወደ ፊት በየተራው ተጽፎ ይገኛል ።

በዚህም ላይ ለአዲሱ ሥራችን መሰናከል የሚሆን በውስጥ ወይም በውጭ ሰዎች የሚወራ አንዳንድ የውስጥና የውጭ ችግር በየጊዜው ይደርስብን ነበርና ፣ ሽብር እንዳይሆንና የሰው ደም እንዳይፈስ ፡ በጐሣ መለያየትን እንዳያስከትል ሥራውን ሁሉ በትዕግሥት መሥራት የሚያስፈልግ ሆነ። የጠላታችን ወጥመድ ባገር ውስጥ ሽብር ለመጠቀም መሆኑን ገና የመንግሥቱን ሥራ ሳልይዝ አውተው ነበር።

ይልቁንም ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስተሳሰርና ለማጽናት ፣ ሕገ መንግሥትን በማቆማችን ፡ የወንዶችና የሴቶች ልጆች ትምህርት ቤት በመክፈታችን ፡ የሕዝባችን ፡ ጤና የሚጠበቅበትን ሆስፒታል በመሥራታችን ፣ ሌላውንም አገራችን ኢትዮጵያ በታሪክ ብቻ ሳይሆን በሥራ ነፃነቷን የምታጸናበትን ሥራ በያይነቱ በመጀመራችን ፡ የጠላት ልብ በቅንዓት መሸበሩን በሚሠራብን ፖለቲካ ስለ ተረዳነው ፡ በሕዝባችን መካከል መለያየት እንዳይሆን ስንጠነቀቅ ማናቸውንም የግዴታ ነገር በሕዝባችን ላይ አስጨንቀን ለመሥራት አልፈቀድንም።

ይህንንም ሁሉ የጥንቃቄ ሥራ እየሠራን ፡ ሕዝባችንን ወደ ሥልጣኔ መንገድ ለመምራት ስንጀምር፣ ጠላታችን በግፍ ተነሣቶ አዲሱን መሣሪያ የያዙ ብዙ ወታደሮችና ብዙ የጦር አይሮፕላኖች ፡ ብዙ ታንኮች ወደ አገራችን ልኮ ፡ የመንግሥታትንም ቃል ኪዳን አፍርሶ ፣ በመትረየስና በመድፍ በጥራቱም በብዛቱም ከእኛ መሣሪያ ብዙ ጊዜ በሚበልጥ ባዲሱ የጦር መሣሪያ ስለ ወጋን ፡ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አቤቱታ እያቀረብን ልባችን ሳይሸበር ፣ የጦር ሠራዊታችንን ልብ እያጽናናን ፣ በጥንካሬ ብንመክትና ብንከላከል ትልቅ ጉዳት ለማድረግ የሚችለውን በኢንተርናሽናል ሕግ የተከለከለውን ልዩ ልዩ የሆነ መርዝና የጋዝ ጢስ ስለ አፈሰሰብን ፡ ብዙ ቦምብም ስለ ጣለብን

፣ በቦምብና በመትረየስ የቆሰሉት ፣ በመርዝ የታፈኑት እንዳይታከሙና እንዳይድኑ ፡ የዓለምን የቀይ መስቀል ማኅበር ሐኪሞችን ከነመድኀኒቱ በቦምብ ስለ ደበደባቸው ፣ እኛም ስለ ነፃነታችን በጦርነት ውስጥ እንደ አንድ ወታደር ተዋግተን ፡ እንደ ጦር አለቃ አሰልፈን ፡ ለመሣሪያ መግዣ የብድር ገንዘብ እንኳ ባለማግኘታችን ምክንያት ከጥቂት አዲስ መሣሪያ በቀር ለመከላከያ የሚበቃ መሣሪያ ስለሌለን ፣ ከአርባ ዓመት በፊት በነበረ አሮጌ መሣሪያ እስከሚቻለን ከተከላከልን በኋላ በማያሳፍር አኳኋን ፣ ለጊዜው ድል ሆነን ወደ አዲስ አበባ የተመለስንበት ፣ ከአዲስ አበባም ወደ ውጭ አገር የወጣንበት ምክንያትና ሌላውም ይህን የመሰለው ሁሉ ወደ ፊት በየስፍራው ተጽፎ ይገኛል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ተወላጆች የሆኑ ሁሉ አገራችን ኢትዮጵያ ለነፃነቷ የሚያሠጋ አደጋ ስለ ወደቀባት ፣ ያለፈውን ከሥሩ ጀምረው መርምረው ለወደፊቱ ነፃነቷ እንዳይጠፋ እንደሚቻላቸው ከመሥራት ሳያቋርጡ እንዲኖሩ ፡ የኢትዮጵያም ተወላጆች ባይሆኑ ግፍን የሚጠሉና እውነቱን ፍርድ የሚወዱ ሰዎች ሁሉ ፡ ሕዝባውያን በምክራቸው ፣ ካህናት በጸሎታቸው ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት እርዳታቸውን እንዳያጓድሉ በአደራና በልመና እናሳስባቸዋለን።

እንግላንድ ባስ። የካቲት 1929 ዓ, ም. ተጻፈ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ማውጫ

መቅድም ........ 4

መግቢያ ........ 5

ምዕራፍ 1 ........ 12

የሕፃንነቴ ታሪክ ደጃዝማችነት እስከ ተሾምሁበት (በ1884 -- 1898 ዓ. ም.) ........ 12

ምዕራፍ 2 ........ 15

ደጃዝማችነት ከተሾምሁበት እስከ አባቴ ዕረፍት (1898 ዓ. ም.) ........ 15

ምዕራፍ 3 ........ 17

ከልዑል አባቴ ዕረፍት በኋላ የሐረርን ግዛት እስከ ተሾምሁበት ዘመን (1898 – 1902 ዓ. ም.) ........ 17

ምዕራፍ 4 ........ 21

ሐረርንና የአውራጃዋን ግዛት ስለ መሾሜ ፡ (1902 ዓ. ም.) ........ 21

ምዕራፍ 5 ........ 28

የጋብቻ ሥርዓት ከፈጸምሁበት ጀምሮ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እስከ ሆንሁበት ዘመን ድረስ። (1903 -- 1909 ዓ. ም.) ........ 28

ምዕራፍ 6 ........ 29

በልጅ ኢያሱና በእኔ መካከል መቀያየም ስለተጀመረበት ምክንያት ።........ 29

ምዕራፍ 7 ........ 31

ልጅ ኢያሱ ከተሻሩበት ከመስከረም 17 ቀን 1909 ዓ. ም. አንሥቶ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ዘውድ እስከ ጫኑበት እስከ የካቲት 4 ቀን 1909 ዓ. ም. ........ 31

ምዕራፍ 8 ........ 38

የንግሥት ዘውዲቱ የዘውድ በዓል ከተደረገበት አንሥቶ ልጅ ኢያሱ ወሎ ላይ ድል ሆነው እስከ ሸኹ ድረስ ።. 38

ምዕራፍ 9 ........ 40

ሚኒስትሮች ስለ መሻራቸውና በአዲስ አበባ የቸነፈር (ግሪፕ) በሽታ ስለ መግባቱ ። ........ 40

ምዕራፍ 10 ........ 41

ልጅ ኢያሱ ትግሬ ላይ ተገኝተው ስለ መያዛቸው ።........ 41

ምዕራፍ 11 ........ 42

በንግሥት ዘውዲቱና በእኔ መካከል እየገቡ ለመንግሥቱ ሥራ መሰናከል ሆነው ስለ ነበሩ ሰዎች ። ........ 42

ምዕራፍ 12 ........ 44

ያገሩን ውስጥ ሥራ በደንብና ባዋጅ ስለ ማሻሻልና የውጭ አገር ሥልጣኔ በኢትዮጵያ እንዲገባ ስለ ማድረግ ። ........ 44

ምዕራፍ 13 .......... 52
ኢትዮጵያ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ ስለ ማድረጋችን ። .......... 52
ምዕራፍ 14 .......... 53
ባሮች ነፃ እንዲወጡ ስለ ማድረጋችንና የነፃነታቸውም ነገር በያመቱ እየተሻሻለ ስለ መሔዱ ። .......... 53
ምዕራፍ 15 .......... 55
አውሮጳን ለመጐብኘት ስለ ተደረገልን የክብር ጥሪ ። .......... 55
ምዕራፍ 16 .......... 61
ከእስክንድርያ ወደ ፓሪስ ስለ መሔዳችን ። .......... 61
ምዕራፍ 17 .......... 64
ከፓሪስ ወደ ብሩክሴል ስለ መሔዳችን ።.......... 64
ምዕራፍ 18 .......... 67
ከፓሪስ ወደ ሮማ ስለ መሔዳችን ። .......... 67
ምዕራፍ 19 .......... 75
ከፓሪስ ወደ ሎንዶን ። .......... 75
ምዕራፍ 20 .......... 81
ከፓሪስ ወደ ግሪክ ከተማ ወደ አቴና ።.......... 81
ምዕራፍ 21 .......... 85
ከአቴና ወደ አገራችን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ።.......... 85
ምዕራፍ 22 .......... 88
የእንግሊዝ መንግሥት የጣናን ባሕር ሲገድብ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ከኤርትራ ወሰን ጀምሮ በኢትዮጵያ መሃል ለመሃል አቋርጦ እስከ ኢጣልያ ሱማሌ የምድር ባቡር ሲሠራ ለመረዳዳት ስለ መዋዋላቸው ።.......... 88
ምዕራፍ 23 .......... 102
ስለ አሰብ ባሕር ወደብና ስለ መንገድ ሥራ ፡ ስለወዳጅነትም ፣ ከኢጣልያ ጋራ ስለ መዋዋላችን ። .......... 102
ምዕራፍ 24 .......... 105
አልጋ ወራሽነትንና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነትን ሳንለቅ የንጉሥነት ማዕርግ ስለ መቀበላችን ። .......... 105
ምፅራፍ 25 .......... 112
ኢጣልያኖች ራስ ጉግሣ ወሌ እንዲሸፍቱ ስለማድረጋቸው ። .......... 112
ምዕራፍ 26 .......... 116
የቤተ ክህነት ሥራ እየተሻሻለና እየታደሰ እንዲሔድ ስለማሰባችንና ስለ መጀመራችን ። .......... 116

ምዕራፍ 27 ........ 118
ከኢትዮጵያ መምህራን ተመርጠው ጳጳሳት እንዲሾሙ ስለ ማድረጋችን ። ........ 118
ምዕራፍ 28 ........ 120
የንጉሥ ነገሥት ዘውድ ስለ መቀዳጀታችን ። ........ 120
ምዕራፍ 29 ........ 126
ሕገ መንግሥት ስለ ማቆማችን ። ........ 126
ምዕራፍ 30 ........ 130
የሕገ መንግሥትን ትርጓሜ ስለ ማስረዳት ። ........ 130
ምዕራፍ 31 ........ 140
ኢጣልያኖች በራስ ኃይሉ በኩል የተንኰል ፕሮፓጋንዳ ሠርተው ልጅ ኢያሱ ከሚጠበቁበት ከፍቼ አምልጠው እንዲወጡ ስለ ማድረጋቸው ። ........ 140
ምዕራፍ 32 ........ 143
የስዊድን አልጋ ወራሽ ልዑል ጉስታፍ አዶልፍ ሊጐበኙን ስለ መምጣታቸውና በክብር ስለ መቀበላችን ። ... 143
ምዕራፍ 33 ........ 145
የቀይ መስቀል ማኅበር ስለ ማቆማችን ። ........ 145
ምዕራፍ 34 ........ 150
ኢጣልያ በግፍ መነሣትዋን በየጊዜው ስለ ማስታወቃችን ። ........ 150
ምዕራፍ 35 ........ 157
የክተት ዐዋጅ ስለ መንገራችን ። ........ 157
ምዕራፍ 36 ........ 164
የደቡብን የጦር ሠራዊት ስለ ማደራጀት ። ........ 164
ምዕራፍ 37 ........ 168
ስለ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ክዳት ። ........ 168
ምዕራፍ 38 ........ 171
ወደ ደሴ ስለ መሔዳችን ። ........ 171
ምዕራፍ 39 ........ 176
በደሴ ሳለን ጀኔራል ዲቦኖ ተሽሮ ማሬሻል ባዶሊዮ መሾሙን ስለ መስማታችን ። ........ 176
ምዕራፍ 40 ........ 178
የጦር ሠፈራችን ገና በደሴ ሳለ በራስ ደስታ ግምባር የጦሩን መፈታት ስለ መስማታችን ። ........ 178

ምዕራፍ 41 ....179
ተጨማሪ ጦር ለማደርጀት ዐዋጅ ስለ ማድረጋችን ። ....179
ምዕራፍ 42 ....181
ከደሴ ወደ ኮረም ስለ መጓዛችን ። ....181
ምዕራፍ 43 ....183
በሽሬና በተምቤን የነበረው የጦር ሠራዊታችን እየቀናው ስለ መሔዱ ። ....183
ምዕራፍ 44 ....189
ከኮረም ወደ ማይጨው የጦር ግንባር ስለ መሔዳችን ። ....189
ምዕራፍ 45 ....198
የማይጨው ጦርነት ። ....198
ምዕራፍ 46 ....201
ወደ አዲስ አበባ ስለ መመለስ ። ....201
ምዕራፍ 47 ....204
ከአዲስ አበባ ወደ ውጭ አገር ለመሔድ በምክር ስለ መቆረጡና ስለ መሔዳችን ። ....204
ምዕራፍ 48 ....206
ከጅቡቲ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መሔዳችን ። ....206
ምዕራፍ 49 ....211
ከኢየሩሳሌም ወደ ሎንዶን ስለ መሔዳችን ። ....211
ምዕራፍ 50 ....213
ከሎንዶን ወደ ጄኔብ ሔደን ከመንግሥታት ማኅበር ፍርድ ስለ መጠየቃችን ። ....213



በልጅነት ዘመን።

# ምዕራፍ 1

## <u>የሕፃንነቴ ታሪክ ደጃዝማችነት እስከ ተሾምሁበት (ከ1884 -- 1898 ዓ. ም.)</u>

አባቴ ልዑል ራስ መኰንን የታላቁ የሸዋ ንጉሥ የሣህለ ሥላሴ ልጅ የልዕልት ተናኘ ወርቅ ልጅ ናቸው። አባታቸውም የዶባና የመንዝ ባላባት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ወልደ መለኮት ናቸው። በ1844 ዓ. ም. ግንቦት 1 ቀን ጐላ ወረዳ ደረፎ ማርያም በሚባል ስፍራ ተወለዱ። 14 ዓመት ያህል ካባታቸው ጋራ ቆይተው ያጎታቸው የንጉሥ ኃይለ መለኮት ልጅ ዳግማዊ ምኒልክ ገና የሸዋ ንጉሥ ሆነው ሳሉ ፡ አባታቸው ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ወስደው ይህ ልጅ ከአክስትዎ የወለድሁት ነውና ከርስዎ ጋራ በቤተ መንግሥትዎ ይደግልኝ ብለው ሰጧቸውና አጋጣሚ ሁኖ ከዝምድናው በቀር ልዩ ባለሟል አደረጉዋቸው ።

ከዚህም በኋላ በያንዳንድ ሥራ ላይ እየሾሙ ብዙ ጊዘ ፈትነው ለመንግሥታቸው ሥራ ታማኝና ትጉህ መሆናቸውን ዐፄ ምኒልክ ስለ ተረዱት የ24 ዓመት ዕድሜ ሳሉ በ1868 ዓ. ም. የባላምባራስነት ማዕርግ ሾሚቸው። በዚሁም ዘመን የሕግ ሚስታቸውን ወይዘር የሺ እመቤትን (የእኔን እናት) አገቡ።

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በ1879 ዓ. ም. ገና ንጉሥ ሲባሉ ፣ ወደ ሐረር ዘምተው ጥንት የኢትዮጵያ ግዛት የነበረውን የሐረርጌን ግዛት መልሰው በወሰዱት ጊዜ ፣ አባቴ በጦርነት ጀግና ፡ የወታደሮችም ወዳጅና መሪ መሆናቸው ስለ ታወቀላቸው ፣ ለሐረርና ለአውራጃዋ ገዥና የጦር አለቃ ሆነው ደጃዝማች ተብለው ተሾሙ። እንዲሁ ደግሞ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብላው ከተቀቡ በኋላ በ1882 ዓመተ ምሕረት በሚያዝያ ወር የራስነት ማዕርግ ሾሚቸው ።

አባቴ ወደ ሐረር በዘመቱ ጊዜ እንደ ክርስቲያን ሥርዓት በቃል ኪዳን ያገቧቸውን ሚስታቸውን የእኔን እናት ወይዘሮ የሺ እመቤትን በዘመቻው ጊዜ በሸዋ ትተዋቸው ዘምተው ነበር። ጦርነቱ ተጨርሶ አገሩ ሰላም ለመሆን ሲጀምር ወደ ሐረር እንዲመጡ አደረጉ።

በሐረርም ያልቀናውን የውጋዴንን አገር አቀኑ። የጊዜውን የጦር እቅድ እያስተማሩ ለባላገሩ የከበደበትን ግብር እያቃለሉ ኖሩ ።

እኔም በሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ. ም. በዘመነ ዮሐንስ ኤጀርሳ ጐሮ (ሐረር) ተወለድሁ። ያባቴ እኅት የወይዘሮ እኅተ ማርያም ልጅ ወይዘሮ መዝለቂያ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህን አግብተው ይኖሩ ነበር። እኔ በተወለድሁ ባራተኛው ወር ዛሬ ራስ ያልነውን እምሩን ወልደው ነበርና መንታ ሆነው እንደ ተወለዱ ልጆች ሁለታችንም በአንድነት አደግን። ዕድሜያችንም ሰባት ዓመት ሲሆን ልዩ አስተማሪ አምጥተውልን በቤታችን ትምህርት ጀመርን። በተወለድን በዐሥር ዓመት ፡ ትምህርት በጀመርን በ3ኛው ዓመት ባማርኛና በግእዝ ማንበብና መጻፍ ዐወቅን። አስተዳደጋችን ግን እንደ ተራ ሰዎች ልጆች ነበር እንጂ በዚያ ዘመን እንደ ነበሩ የነገሥታት ልጆች በመቀማጠል አልነበረም። እናቴ ወይዘሮ የሺ እመቤት ገና የሰላሳ ዓመት ዕድሜ ሳሉ በ1886 ዓመተ ምሕረት መጋቢት 6 ቀን ዐርፈው፣ሐረር በጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። ይህንንም ሁሉ በኋላ ዘመን ከአሳዳጊዎቼ እየሰማሁ የተረዳሁት ነው።

አባቴ ልዑል ራስ መኰንን በግዛት አገራቸው በሐረር ከሚኖሩበት ይልቅ በአዲስ አበባና በሌላው የኢትዮጵያ አውራጆች ለዘመቻ የሚጓዙበት ወራት ይበዛ ነበር። ወደ ውጭ አገሮችም የመንግሥት መልክተኛ እየሆኑ ሔደዋል።

አባቴ ካደረጓቸው ጉዞዎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው ። ፡ በ1881 ዓ. ም. ወደ ኢጣልያ ተልከው ሔደዋል። በ1888 ዓ. ም. በአላጌ ዘመቻ ጊዜ ራስ ወሌን ፡ራስ ሚካኤልን ፡ ራስ መንገሻ አቲከምን ፡ ራስ አሉላን ፡ደጃች ወልዴን

፡ ፊታውራሪ ገበየሁን ፥ ፊታውራሪ ተክሌን ፡ ሊቀመኳስ አድነውን ፡ ቀኛዝማች ታፈሰን ይዘው ቀዳሚና ጠቅላይ የጦር አዛዥ ሆነው አዝምተዋል። በ1890 ዓ. ም. በኢትዮጵያ ምዕራብ በሱዳን ወሰን በኩል የዐረብ አገር ወደሚባለው ዘምተዋል። ይኸውም ዛሬ ቤኒ ሸንጉል የሚባለው አገር ነው።

በ1891 ዓ. ም. የትግሬው ገዥ ራስ መንገሻ በዐፄ ምኒልክ ላይ ሸፈቱ ስለ ተባለ ወደ ትግሬ ተልከው ራስ መንገሻን ከዐፄ ምኒልክ ጋር አስታርቀዋል። ወዲያውምያገሩን ጸጥታ ለመጠበቅ ሐረርጌን እንደ ያዙ ሁለት ዓመት ያህል በትግሬ ተሾመው ቆይተው ተመለሱ። በ1894 ዓ. ም. ለግርማዊ ኤድዋርድ 7ኛ የዘውድ በዓል ወደ እንግሊዝ አገር ተልከዋል። በዚህም ሁሉ ላይ ዛሬ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚባለውን ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ የሚያገናኘውን ጉዳይ ሁሉ የሚሠሩትና የሚጨርሱት እርሳቸው ነበሩና በፖስታ ተላልኮ በስልክ ተነጋግሮ ለማይፈጸመው ለየትልቁ ጉዳይ ሁሉ ከዐፄ ምኒልክ ጋር ለመመካከር እየተጠሩ በየዓመቱ ወደ አዲስ አበባ ይመላለሱ ነበር። መንገዱም እንደ ዛሬው በምድር ባቡር ስላልነበረ በጐዞ ከሐረር እስከ አዲስ አበባ አንድ ወር ያስሔድ ነበር።

አባቴ ሁለት ጊዜ ወደ አውሮጳ መጥተው የአውሮጳን ሕዝብ ሥልጣኔ ስለ አዩ ወደ ኢትዮጵያም ከሚመጡት ከአንዳንድ የውጭ ሰዎች ጋር በመነጋገር ትምህርት የሚገኝ መሆኑን ስለ ተረዱት ፤እኔ የውጭ አገር ቋንቋ እንድማርላቸው አጥብቀው ይመኙ ነበር። በዚህም አሳብና ምኞት ሳሉ በሐረር ከተማቸው ውስጥ አንድ ሆስፒታል አሠርተው ዶክቶር ቢታልያ የሚባለውን ሐኪም ከፈረንሳይ ቅኝ አገር የጉዋዶሎፕ ሰው ቀጥረው አምጥተው ነበርና እርሱ በሽተኞችን ከማከም በሚተርፈው ሰዓት በቀን አንዳንድ ሰዓት የፈረንሳይ ቋንቋ እንዲያስተምረን አደረጉና ትምህርታችንን ጀመርን።

አባቴ በአውሮጳ ያዩትን የሥልጣኔ ሥራ በግዛታቸው ለመጀመርና ሕዝቡን ለማስለመድ ብርቱ ምኞት ነበራቸው። በሐረር ከተማቸው መጀመርያ ሆስፒታል ማቆማቸውም ስለዚሁ ነበር። ይኸውም ሆስፒታል አባቴ ከሞቱ ከ1 ዓመት በኋላ የፈረንሳዊ መንግሥት ከዳግማዊ ምኒልክ በ50ሺ ፍራንክ በሚከተለው ውል የገዛው ነው።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ዳግማዊ ምሂልክ ሥዩመ እግዚአብሔር

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከደጃዝማች ይልማ እንዴት ሰንብተሃል። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። ሐረርጌ ራስ መኰንን አሠርቶት የነበረውን የበሽተኛ መታመሚያ የሆስፒታል ቤት የፈረንሳዊ መንግሥት ሐኪም አስመጥቶ ያገራችንን ሕመምተኛ ሊያስታምምልን በኢትዮጵያ ልዩ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ምንስቴር ሙሴ ክሎቢኮብስኪ ስለ ፈረንሳዊ መንግሥት ሬፑብሊክ ሆኖ ገዝቶታልና ያንኑ የሆስፒታሉን ቤት የቦታውን ንድፉንና መጠኑን ለክተህ የሆኛውን ወረቀት አጽፈህ ለሐረርጌው ለፈረንሳዊ መንግሥት ቆንስል ለሙሴ ናጀር እንድታረካክብ ይሁን።

ሐምሌ 29 ቀን 1899 ዓመተ ምሕረት ኣዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

አባቴ በቶሎ የፈረንሳይ ቋንቋ እንዳውቅላቸው ቸኩለው ነበርና ዶክተር ቢታልያ በቀን አንዳንድ ሰዓት ብቻ የሚያስተምረን ወደ ፍጻሜ እንደማያደርሰን ስለ ተረዱት በሐረር ከተማ ውስጥ ካሉት ከአባ እንድርያስ ጋራ ተነጋግረው በዚያው በሚሲዮናቸው ቤት እየተማረ ያደገውን አባ ሳሙኤል የሚባለውን ኢትዮጵያዊ አመጡልንና እርሱ በትጋትና በጥንቃቄ ያስተምረን ጀመር። ስለሆነም ከዶክተር ቢታልያ በቀን አንዳንድ ሰዓት መማራችንን አልተውንም ነበር።

አባ ሳሙኤል የሚባለው አስተማሪያችን የአለቃ ወልደ ካህን ልጅ ነው። ወልደ ካህን ማለት የኢጣልያ ሚሲዮን አባ ማስያስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት የገቡ ናቸው። ልጃቸው አባ ሳሙኤልም በካቶሊክ ሚሲዮን

ቤት ገብቶ የተማረበት ምክንያት ስለዚህ ነው። አባ ሳሙኤል ትልቅ ዕውቀት ያለው ፡ ለመማርም ለማስተማርም የሚተጋ ፡ በደግነትና በትሕትና ከማንም ሰው ዕውቀትን እንደ ንብ የሚቀሥም ፡ በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ የተጠመደ ፡ የነፍሱን እንጂ የሥጋውን ጥቅም ለማግኘት የማይጥር ደግ ሰው ነበር። ይህንንም ማለቴ ዐሥር ዓመት ያህል አብረን በመኖራችን በጣም ስለ ዐወቅሁት ነው ።

በዚህ መጽሐፍ በመቅድሙ እንደ ተመለከተው ከ13 ዓመት ዕድሜዬ ጀምሮ ያለውን የሥራዬን መታሰቢያ እጽፋለሁ ማለቱ ከዚያ አስቀድሞ የሠራሁት ሥራ ሁሉ በሞግዚቴ መሪነትና አመልካችነት ነው። ከ13 ዓመት ዕድሜዬ ወዲህ ግን ምንም እንኳ የሥጋዬ ኃይል ባይበረታ ፣የነፍስ ዕውቀቴ ኃይል እየበረታ ለመሔድ በመጀመሩና የዚህ ዓለም የመግቢያው በር በመከፈቱ ምክንያት ሞግዚቱ ሳያዘኝ እኔ በፈቃዴ ይህ ሥራ ሌላውን ሰው ያስቀይማል ፤ይህ ሥራ ግን ደስ ያሰኛል ፡ ይህ ጉዳት ነው ፡ ይህ ግን ጥቅም ነው ፡ እያልሁ ክፉና በጎ እየለየሁ ለመሥራት የዓለም መግቢያውን መስላል ለመውጣት የጀመርሁበት ዘመን ስለሆነ ነው።

በልዑል አባቴና በእኔ መካከል ያለው ፍቅር በጣም ልዩ ነበርና እስካሁን ይሰማኛል። በምሠራውም ሥራና ታዛዥ በመሆኔ ዘወትር ይመርቁኝ ነበር። መኳንንቶቻቸውና ሠራዋዊቶቻቸውም አባቴ በኔ ላይ ያላቸውን ፍቅር በማድነቅ ስለ ተመለከቱ እነሱም ከማክበር ጋራ ይወዱኝ ነበር ።

ልዑል አባቴ በተመቻቸው ሰዓት ሁሉ ጸሎት በመጸለይ ፡ ገንዘባቸውን ለተቸገሩ ድሆችና ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ፣ የታዘዘውን የክርስቲያን ሥርዓት እንደተቻላቸው ለመፈጸም ሲተጉ እመለከት ነበር። እኔም ሳድግ እንደርሳቸው ለማድረግ መንፈሳዊ ምኞት እንዲያድርብኝ ራሴን ለመግዛት ይመራኝ ነበር። የልዑል አባቴ ኑሮ ከዚህ በላይ እንደ ተጻፈው መሆኑን ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ወገን የማያውቅ የለም። በዚህ ዘመን ከነበሩት ትልልቆች ሰዎች ፣ ይህ መጽሐፍ እስከ ተጻፈበት ዘመን አንዳንዶቹ በሕይወተ ሥጋ ይገኛሉና የማጋነን እንዳልሆነ ሁሉም የሚያውቀው ነው። አባቴም ዝንባሌዬ ሁሉ ወደ ትምህርት እንደ ሆነ ስለ ተመለከቱ በፍቅራቸው መጠን ደግሞ ደስታቸው እየበዛ ይሔድ ነበር።

# ምዕራፍ 2

## ደጃዝማችነት ከተሾምሁበት እስከ አባቴ ዕረፍት (1898 ዓ. ም.)

አባቴ ስለ ፍቅራቸው ጽናት አድጌ ለማዕርግ የምደርስበትን ዘመን ሲጠባበቁ ነበርና በተወለድሁ በ13 ዓመት ከ3 ወር ጥቅምት 21 ቀን 1898 ዓ. ም. ጋራ ሙለታ በሚባለው በትልቁ አውራጃ ደጃዝማች ብለው ሾሙኝ። ይህም ደጃዝማችነት እንደ አገራችን ልማድ ለማዕርጉ ብቻ ነበር። በችሎት ተቀምጦ ለመፍረድና ያገር ግዛቱን ለማስተዳደር ፡ የጦር ሠራዊት ለማሰለፍ ግን ዕድሜዬ አይፈቅድልኝም ነበርና ለሥራው ሁሉ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ፊታውራሪ ቆለጭ የሚባሉትን ዋና ታማኝ አሽከራቸውን ሞግዚትና እንደራሴ አድርገው ሰጡኝ።

የደጃዝማችነት ማዕርግ በተሾምሁበትም ቀን ፣ መኳንንቶቻቸውንና ሠራዊታቸውን ሰብስበው ፣ በታላቁ አዳራሽ ውስጥ አስተዋወቁኝ። ከዚህም በኋላ እርሳቸው ወደ አሉበት ወደ እልፍኝ አዳራሽ ገብቼ ፣ይህን የደጃዝማችነት ማዕርግ ስለ ሰጡኝ ጫማ ስሜ ባጠገባቸው ተቀመጥሁ። ወዲያውም መኳንንቱና የጦር አለቆቹ ሁሉ እንደ ገና እየተጠሩ ገብተው በፊታቸው በቆሙ ጊዜ ፣ ልዑል አባቴ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ። «ሁላችሁም ያሳደግኋችሁና የምወዳችሁ አሽከሮቼ ናችሁና ፣ ልጄን ተፈሪን ከእግዚአብሔር ጋራ አደራ ብያችኋለሁ። አደራም የምላችሁ ፣ ላይናችሁ እንዳ ትጠሉት ነው እንጂ ዕድሉ በፈጣሪው እጅ ነው» አሏቸው። መኳንንቱና ሠራዊቱም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ጌታችን ይህን የመሰለ የአደራ ቃል መናገራቸው በሞት የምንለይበት ጊዜ መድረሱን ዐውቀው እንደ መሰናበት ይመስላል እያሉ እንባቸውን ያፈስሱ ጀመር ።

እኔም አባቴ ይህን የደጃዝማችነት ማዕርግ ስለ ሰጡኝ ደስ ብሎኝ ሳለሁ ዳግም ይህን የመሰለ ልብ የሚሰብር ቃል ለመኳንንቶቻቸው በመናገራቸው ደስታዬ ከኀዘን ጋራ ተቀላቀለብኝ። አባቴ ግን ለእኔ የሚያስቡት አሳብ በረዢሙ እንጂ ባጭሩ አልነበረምና ይህን ትልቅ ማዕርግ ሲሰጡኝ ፣ በኑሮም ለብቻዬ የተለየ ቤት እንዳገኝ አስበው አስቀድመው አሰናድተው ኖሮ ፡ በተሾምሁ ማግስት ቤቱንም ለየሥራውም ክፍል ሁሉ የሚያስፈልጉትን ሹሞች አስረከቡት ብለው አዘዙልኝ ።

ከዚህም በኋላ ያባቴ መኳንንቶች ሁሉ ቀድሞም በማክበር ይወዱኝ ነበርና አሁን ደጃዝማች ተብዬ ስለ ተሾምሁ፣ የተለየ ኑሮም ስለ ተደረገልኝ የበለጠ የማክበር ፍቅራቸውን እየገለጡ አሳዩኝ። ምንም ዕድሜዬ ባይፈቅድልኝ እንኳ ፣ የደጃዝማችነት ማዕርግ ስለ ተሾምሁ ታላላቁ መኳንንቶች ለጉዳይም ለግብዣም በኦፌሴል ወደ አባቴ ሲገቡ አብሬ እየገባሁ እንድቀመጥ ተፈቀደልኝ። በንግግርና ለተጠየቅሁት ምላሽ በመስጠቴ ፡ ንግግራቸውንና ምክራቸውንም በጥንቃቄ በመስማቱ ፣ የፅድሜዬ ትንሽነት የሚያስከትለውን ማናቸውንም ሥራ ከመሥራት በመጠንቀቁየልዑል አባቴና ፡የመኳንንቱ ደስታ በጣም ይሰማኛል።

ከዚያም ጀምሮ እስካሁን በሕይወተ ሥጋ ያሉት የአባቴ መኳንንቶች ያን ጊዜ ደጃዝማች ተብለህ ስትሾም እንደዚህ ብለህ ተናግረህ ነበር ፣ እንደዚህ ተብላህ ተጠይቀህ ፣እንደዚህ መልሰህ ነበር እያሉ ያለፈውን ነገር እያነሱ ሲነግሩኝ በጣም ትዝ እያለኝ ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ ።

አባቴ ፡ ባለቤታቸው የእኔ እናት ወይዘሮ የሺ እመቤት ካረፉ በኋላ ፣ ብቻቸውን ስለ ሆኑ ፣ የምግባቸውን ጊዜ ችላ እያሉ ያሳልፉት ነበርና የምግብ ጊዜ ደረሰ ብሎ ደፍሮ የሚናገር ስለሌለ ፡ እኔ ወደ እልፍኛቸው እየገባሁ የምግብ ጊዜ ደርሷልና እባክዎ ግብር እንዲገባ ፈቃድዎ ይሁን እያልሁ በፍርሃት ስለምናቸው ፣ እኔን ደስ ለማሰኘት ሲሉ በቶሎ ግብር አግቡ ብለው እያዘዙ እርሳቸውም መኳንንቱም ፡ ሲጋበዙ በማየቱ በልጅነት መንፈሴ ለልቤ የኩራት ደስታ ይሰማው ነበር። አባቴም ይህን በማድረጉ ይመርቁኝ ነበር ።

ለልዑል አባቴ የመወደድና የመፈራት ዕድል ነበራቸው ፣ ጥፋት ከተገኘበት ማንም ትልቅ ባለማዕርግ ሰው ቢሆን ፣ እንደ ጥፋቱ መጠን ቅጣት ይፈርዱበታል እንጂ ዝም አይሉትም ነበርና ይፈሯቸዋል። ከጥቂት ቀን በኋላ ግን ቅጣት

የፈረዱበት ትልቅ ባለማዕርግ የሆነ እንደሆነ ፣ ሰጋውን ፡ ማሩን ፡ ቅቤውን ፣ ተራ ሰው የሆነ እንደሆነ ፣ ሙክቱን ፣ ማርና ቅቤ መግዣውን ብሩን እስከ ቤቱ እየላኩ ደስ ያሰኙታል እንጂ ቅጣት በፈረዱበት ሰው ላይ የመጨረሻ ጭካኔ ነገር የለባቸውም ነበርና በዚህ ይወደቸዋል። ከዚህም በቀር ምንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ፍጹምና ንጹሕ ባይሆን በሚቻለው ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ዋና አሳባቸው ስለ ሆነ ፣ ለተቸገሩ ሰዎች ገንዘብ መርዳትን ፡ ዐፄ ምኒልክ የተጣሏቸውን ሰዎች ማስታረቅን ፡የመንግሥት ሥራ ከሚሠሩበት በሚተርፈው ሰዓት ጸሎት መጸለይን ፡ በየገደማቱ ላሉት መነኩሳትና በየአድባራቱ ላሉት ካህናት በችግራቸው መርዳትን ፡ይኸኸን ሁሉ የሚሠሩት ለይስሙላ ሳይሆን እግዚአብሔርን ደስ አሰኛለሁ በማለት ነበር። መልካም የበጎ ሥራ ምሳሌ ነበሩ ።

# ምዕራፍ 3

## ከልዑል አባቴ ዕረፍት በኋላ የሐረርን ግዛት እስከ ተሾምሁበት ዘመን (1898 – 1902 ዓ. ም.)

በዚህ ዓለም በሚኖር ሰው ላይ መቸም ቢሆን ደስታና ኀዘን በየተራ ሲፈራረቁበት ይኖራሉ እንጂ በደስታ ወይም በኀዘን ብቻ ዘመኑን ወይም ቀኑን የሚጨርስ አይገኝምና እንደዚያ እየሳሱ በመናፈቅ የሚወዱኝ አባቴ በብርቱ ስለ ታመሙ አሳቤ ሁሉ በመጨነቅ ባሕር ይዋኝ ጀመር።

ልዑል አባቴ በ1898 ዓ. ም. ወደ አዲስ አበባ ለመውጣት በጥር 4 ቀን ከከተማቸው ከሐረር ተነሡ። በዚህም ጊዜ ጥቂት አሟቸው ነበር ። በጥር 9 ቀን ቡርቃ በሚባለው ወንዝ ሰፈር አድርገው የጥምቀትን በዓል አክብረው ከዋሉ በኋላም ሕመሙ ስለ ጸናባቸው ወደ ኋላ ተመልሰው ቁልቢ ከሚባለው ከሁለተኛው ከተማቸው ገብተው በሐኪም ይታከሙ ጀመር። በዚህም ጊዜ አባቴ እኔን ለማየት ናፍቀው ስለ አስጠሩኝ ወደ ቁልቢ ወጣሁ። አኳኋናቸውንም ለማየት ወደ ተኙበት ቤት ስገባ ባጠገባቸው ቆሜ ያዩኝ እንደ ሆነ ስለ በሽታቸው ጽናት ባንደበታቸው መናገር ሲያቅታቸው ባይናቸው እየጠቀሱ ተቀመጥ ይሉኝ ነበር። እኔም ካጠገባቸው አለመለየቱ ፈቃዳቸው መሆኑን ስለ ተረዳሁት ቀኑን ሁሉ ባጠገባቸው እየተቀመጥሁ እውል ነበር።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ሥልጣን የተቆረጠውን የሞት ፍርድ ሰዓት ያንድ አባትና ልጅ ፍቅር ይቅርና የብዙ ሰውም ፍቅር ቢሆን ሊያስተላልፈው አይችልምና በመጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ. ም. ቁልቢ ላይ ዐርፈው በሐረር እርሳቸው በተከሉት በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

ከዚህም በኋላ ያባቴ መኳንንቶችና ሠራዊቱ በሙሉ ተሰብስበው ባንድ ወገን አባቴ በሕይወት ሳሉ ልጄን ተፈሪን አደራ ብያችኋለሁ ስላልዋቸው ፣ በሁለተኛውም ወገን አባቴ ለዐፄ ምኒልክ ታማኝ ሆነው መንግሥታቸውን በትጋት ሲያገለግሉ መኖራቸውን ስለ ዐወቁ፣ያባቱን ግዛት ሐረርጌን ሳይሰጡት አይቀርም በማለት ተስፋ አድርገው የአርባቸውን ተዝካር አውጥተን ወደ አዲስ አበባ እንወጣለን ብለው መክረው ከጨረሱ በኋላ ፣ የራስ መኰንን ያርባ ልቅሶ የሚለቀሰው አዲስ አበባ በእኔ ፊት ነውና ከልጁ ከተፈሪ ጋር በቶሎ እንድትመጡ የሚል የዐፄ ምኒልክ ደብዳቤ ለመኳንንቱ ደረሰላቸው።

አባቴ በሕይወት ሳሉ ለዐፄ ምኒልክ ገጸ በረከት እልከዋለሁ ብለው አሰናድተው በተለይ ያስቀመጡት ዕቃ ነበርና ያን ይዘን በሚያዝያ 3 ቀን ከሐረር ተነሥተን ወደ አዲስ አበባ ተጓዝን። በጕዞውም ላይ ብዙ ሰዎች ስለ ሞቱብን በኀዘን ላይ ኀዘን ሆነብን። ምክንያቱም የበልግ ዝናብ ስለ ዘነበና ስለ ሠራዊቱም ብዛት በሰፈራችን የበረሃ በሽታ ስለ ገባ ነበር። በሚያዝያ 19 ቀን አዲስ አበባ ደረስን።

ዐፄ ምኒልክም ያባቱን ተዝካር በሚያበሉበት በሰፊ ሜዳ ላይ ድንኳን እንደ ዳስ እየተሰፋ እንዲተከል አዘው ነበርና በዚያ መኳንንቱና ሠራዊቱ እንዲሰበሰብ አድርገው ፤ከኛ ወገን መጭው፤ከነዚያም ወገን ተቀባዩ እየተላቀሰ በትልቅ ኀዘን ከዐፄ ምኒልክ ጋራ ተገናኘን ።

በአርባውም ቀን ሚያዝያ 22 ቀን ሰኞ በአዲስ አበባና በዙሪያውም ያሉት የየገዳማቱና የየአድባራቱ ካህናት ለክርስቲያን የሚገባውን የፍታት ጸሎት ሲጨርሱ ሁሉም ወደ ተሰናዳው ድንኳን መጥተው ትልቅ ግብዣ ተደርጎላቸው ዋሉ። ራሶችና ደጃዝማቾች እኩሉ የሥጋ ዘመዶቻቸው ፤ እኩሉም አብሮ አደጎቻቸው ስለ ሆኑ በየድንኳኑ ክፍል እየገቡና እየቆሙ የምግብ ነገር እንዳይጓደል ይመለከቱ ነበር። ለነዳያንም ከምግብ በቀር ብዙ የገንዘብ ምጽዋት ተሰጠ።

በማግስቱም እንደ ሀገራችን ልማድ ሰው በሞተ በአርባ ቀኑ ተዝካሩ በተበላ ማግስት እንደ ሞተበት ቀን ያህል ሆኖ ይለቀሳልና በሰፊ ሜዳ ላይ ትልቅ ድንኳን ተተክሎ መኳንንቱና ሠራዊቱ ተሰብስቦ ፡ ራሳቸው ዐፄ ምኒልክ በመካከል ተቀምጠው ያባቴ የማዕርግ ልብሳቸውና የራስ ወርቃቸው ፡ ኒሻኖቻቸውና የጦር መሣሪያቸው ተይዞ ፈረስና በቅሎዋቸው በወርቅ ዕቃ ተጭነው በሠራዊቱ መካከል እየተመላለሱና እየታዩ የሚያስደንቅ ልቅሶ ተለቀሰላቸው። ከአልቃሾቹም መካከል አንዱ እንዲህ ብሎ የልቅሶ ግጥም ገጠመላቸው።

ስልከኛው ሲያረዳ ነገር ተሳሳተው፡

መኮንን አይደለም ድኃ ነው የሞተው ፣

በአዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ይህን የመሰለ ልቅሶና ኀዘን ለማንም ተደርጎ አያውቅም ይባላል። የዚህም የልቅሶው አደራረግ ከተፈጸመ በኋላ ፡ የተሰበሰበው ሠራዊት በየቤቱ እንዲሔድ አጋፋሪዎች አስታወቁትና እየተነሣ ሔደ። ነገር ግን ከእኔ ጋራ ከሐረር የመጣው ያባቴ ሠራዊት ዝም ብሎ ቀርቶ ነበርና ሠራዊቱ ሁሉ ሲሔድ እናንተ ለምን ቀራችሁ ተብለው ቢጠየቁ ፣ የጌታችንን ልጅ ደጃዝማች ተፈሪን አጅበን ወደ ሰፈር እንድንሔድ ነው ብለው ተናገሩ። ጃንሆይም ይህን ሰምተው ከአባቴ ሠራዊት ጋራ ወደ ሰፈር እንድሔድ ፈቀዱልኝና ስንሔድ ከአዲስ አበባም ያባቴ ወዳጆች የሆኑት እስከ ሰፈር ለመሸኘት ተከትለውኝ ስለ መጡ ፣ የአጀቡ ብዛት ከልክ ያለፈ በመሆኑ መንገድ አላፊው ሁሉ እየቆመ ያደንቅ ነበር። ይህም በመደረጉ ያባቴ ሠራዊት ይቅርና ሌሎች በአዲስ አበባ የሚኖሩት የአባቴ ወዳጆች ፡ ጃንሆይ ደጃዝማች ተፈሪን ከአባቴ ሠራዊት ጋራ ወደ ሰፈር እንዲሔድ መፍቀዳቸው የሐረርን ግዛት ሊሰጡት ቢያስቡ ይሆናል እያሉ እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ የሰሙ ሰዎች ነገሩኝ ።

ነገር ግን አባቴ ፡ ወይዘሮ የሺ እመቤትን የእኔን እናት ከማግባታቸው በፊት የወለዷቸው ታላቅ ወንድሜ ደጃዝማች ይልማ ፣ የእቴጌ ጣይቱን የእኅት ልጅ ወይዘሮ አሰለፈችን አግብተው ነበር። በዚህም ምክንያት እቴጌ ጣይቱ ወገኖቻቸውን ሁሉ አስነሥተው ፣ ታላቅ ልጅ ሳለ ታናሽ ልጅ ያባቱን ግዛት አይሾምም እያሉ የሐረር ግዛት ለደጃዝማች ይልማ እንዲሆን ይደክማሉ እየተባለ ሲወራ ሰንብቶ ነበርና የሐረር ግዛት ለእኔ እንዲሆን የሚያመለክቱ እጅግ ብዙ ሰዎች ተነሡ።

ነገር ግን ባንድ ወገን እቴጉ ጣይቱ ለደጃዝማች ይልማ ይስጡልኝ እያሉ ዐፄ ምኒልክን ስለ አስቸገሩ በሁለተኛውም ወገን እኔ የሐረር ገዥ የምሆንበት እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ ስላልደረሰ ፣ ለደጃዝማች ይልማ ይሁን በማለት ነገሩ ተቆረጠ። ያባቴ ሠራዊትና ወዳጆቻቸውም ለእኔ እንዲሆን ያሰቡበት ምክንያት አብሮ በመኖር እኔን ስለ ለመዱ ፡ አባቴም ገና በሕይወት ሳሉ ልጄን ተፈሪን አደራ ብያችኋለሁ ስለ አልዋቸው ነበር።

የሐረር ግዛት ለወንድሜ ለደጃዝማች ይልማ እንዲሰጥ ነገሩ ከተቆረጠ በኋላ በአባቴ ሠራዊት መካከል እንደ ተቀመጥሁ ዐዋጁ የተነገረ እንደሆነ ለእኔም ለሠራዊቱም ቅር የሚያሰኝ መሆኑ የታሰበ ይመስላል ፡ ለዐዋጁ ስምንት ቀን ሲቀረው ከሰፈር ተጠርቼ በቤተ መንግሥቱ ግቢ በተሰናዳልኝ ድንኳን እንድቀመጥ ተደረገ። ከመኳንንቱም በፍቅር ወደኔ የሚያደሉትን ለአባቴም በጣም ታማኝ የነበሩትን ደጃዝማች አባ ታቦርንና ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህን (አሁን ደጃዝማች የተባለውን) ለጊዜው በቁጣና በግዞት አስመስለው እናንተ እዚህ አዲስ አበባ ደጅ ጠኚዎች ሆናችሁ ተቀመጡ ብለው አዘዙዋቸው። ምክንያቱም ደጃዝማች አባ ታቦርና ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ የሐረር ግዛት ለእኔ እንዲሆን በጣም ያስቡ ነበርና አሁን ተመልሰው ወደ ሐረር የወረዱ እንደሆነ በየምክንያቱ ደጃዝማች ይልማን እንዳያስቸግሩ ተብሎ በእቴጌ› ጣይቱ በኩል የተመከረ ነው ተብሎ ተወራ።

ከስምንት ቀን በኋላም በግንቦት 2 ቀን ሐረርን የራስ መኰንንን ግዛት ለደጃዝማች ይልማ ፡ ሰላሌን የራስ ዳርጌን ግዛት ለደጃዝማች ተፈሪ ሰጥቻለሁ የሚል የጃንሆይ ዐዋጅ ስለ ተነገረ ፣ ያባቴ ሠራዊት በሙሉ አዘነ። ከዚህም መካከል ጌታችን ራስ መኰንን አደራ ብለው የሰጡንን ልጃቸውን ደጃዝማች ተፈሪን ትተን ከደጃዝማች ይልማ ጋራ አንወርድም እያሉ ትዳራቸውን እየተዉ ወደ እኔ እየመጡ የተቀመጡ ብዙ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ የሚታወሱኝ

ፊታውራሪ ቆለጭ ፣ ልጅ ወልደ ሥላሴ (በኋላ ደጃዝማች) አቶ ደነቀ ጉበዜ ፣ ልጅ ዓለማየሁ ጉሹ ፣ (ፊታውራሪ) ቀኛዝማች ወልደ ማርያም ዓባይነህ አቶ ሰብስቤ (በጅሮንድ) አቶ ኃይሌ ወልደ ሩፋኤል (ጸሐፊ ትእዛዝ) ቀኛዝማች ድፋባቸው ፣ አቶ ተፈራ በለው ፣ ቀኛዝማች ገብረ ወልድ ፤አቶ ዋቄ (ዶጃዝማች) ቀኛዝማች ደርቤ ናቸው።

የሰላሌንም ግዛት በተሾምሁበት ወራት የደብረ ሊባኖስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ እንደገና ታድሶ እንዲሠራ ስለ ታዘዘ ፣ መሠረቱ ሲቆፈር ጽሑፍ ያለበት በጣም ስስ የሆነ የወርቅ ቁርጥራጭና ቀለበት ተገኝቶ ነበርና በዚያው ሥራውን የሚሠራው የእኔ እንደራሴ ልኮልኝ በእኔ እጅ ለጃንሆይ ስለ ቀረበ ፣ ይህ ትልቅ ዕድል ሆኖ ተቆጠረልኝ። እንደ ሀገሩ ልማድ ወደ ሰላሌ ግዛት ሔጄ ከአሽከሮቹ ጋራ እንድቀመጥ ጃንሆይ ፈቅደውልኝ ነበር። ነገር ግን እኔ ከጃንሆይ መለየት ስላልፈለግሁ በሰላሌ ግዛት እንደራሴዬ እንዲቀመጥ ተደርጎ ፡ እኔ አዲስ አበባ ጧት ባንድ ሰዓት ወደ ቤተ መንግሥት እየገባሁ ፡ ማታ በሁለት ሰዓት ወደ ቤቴ እየተመለስሁ 8 ወር ሙሉ ደጅ ጠናሁ።

በዚህም ወራት ዐፄ ምኒልክ ለኢትዮጵያ ልጆች የውጭ አገር ቋንቋ መማሪያ የትምህርት ቤት ከፍተው ከምስር አገር አስተማሪዎች አስመጥተው ነበርና ልጅ ኢያሱንና ልጅ ብሩን ልጅ ጌታቸውንም ፣ ሌሎችንም የትልልቆች መኳንንቶች ልጆች እየመረጡ ወደ ትምህርት ቤት ሲያስገቡ ፣ እኔን ትተውኝ ነበርና ትልቅ ኀዘን ሆነብኝ። ከጥቂት ቀን በኋላ ግን ትምህርት ለመማር ፈቃዴ መሆኑን ገልጬ ብነግራቸው አገረ ገዥሆነሃልና እንደ መኳንንት ሆኖ መኖርን የምትመርጥ መስሎኝ ነው እንጂ ፣ መማር ከፈቀድህ እየሔድህ ተማር ብለው ፈቀዱልኝና ትምህርቱን ጀመርሁ። ነገር ግን በሐረር ሳለሁ የፈረንሳይ ቋንቋ ተምሬ ነበርና ፡ አሁን አዲስ አበባ ከጀመሩት ጋራ ለመማር የማይመች ስለሆነ በተለየ ለብቻችን ሰዓት ወስነው ያስተምሩን ጀመር። አብረን እንማር የነበርነውም ልጅ እምሩ (ራስ) አቶ አስፋው በንቲ ፣ ልጅ ዘውዴ ጉበና (ፊታውራሪ) ናቸው። ሰላሌንም ተሾሜ አንድ ዓመት ያህል ከቆየሁ በኋላ ባሶ የሚባለውን ግዛት ተሾምሁ።

ወንድሜ ደጃዝማች ይልማ ሐረርጌን ተሾመው አንድዓመት ከአምስት ወር ያህል ከገዙ በኋላ በመስከረም 29 ቀን 1900 ዓ. ም. ሐረር ላይ መሞታ ቸው ተሰማና የኀዘን መርዶ በስልክ ወደ አዲስ አበባ ተላልፎልን ተረድተን ትልቅ ኀዘን ተደረገ። ከዚህም በኋላ የሐረርጌን ግዛት ለደጃዝማች ተፈሪ ሊሰጡት ነው እየተባለ እንደገና በየሰው አፍ ይነገር ጀመር። ነገር ግን ከዚህ ቀድሞ እንደ ተናገርሁት የሐረር ገዥ ለመሆን እግዚአብሔር የወሰነልኝ ጊዜው አልደረሰም ነበርና በመጋቢት 27 ቀን 1900 ዓመተ ምሕረት የሐረር ግዛት ለደጃዝማች ባልቻ ተሰጠና ለእኔም ከሲዳሞ ግዛት ግማሹን ሰጡኝ። ስለዚህም ትምህርቱን ትቼ ከሠራዊቱ ጋራ ወደ ሲዳሞ ግዛቱ ለመሔድና አገዛዙን ለማደላደል ታዘዝሁ። በሐረር ከነበሩትም ከአባቴ ሠራዊት ሦስት ሺ ተቆጥረው ወደ እኔእንዲመጡ ተደረገ።

ወደ ሲዳሞ መሔዴ የተቆረጠ ነገር በሆነ ጊዜ በግዞት ስም የቆዩት ደጃዝማች አባ ታቦርና ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ ከኔ ጋራ እንዲሔዱ ተፈቀደልኝ። ወዲያውም ደጃዝማች አባ ታቦር ለሥራው ሁሉ ትጉህና ብርቱ በቃላቸውም ሐሰት የሌለባቸው እውነተኛ ነበሩና ለእኔ መልካም ዕድል ሆነልኝ። በሲዳሞ ግዛቴም በነበርሁበት ዘመን ሁሉ ለውጭው ሥራ ደጃዝማች አባታቦር ፣ ለውስጡ ሥራ የእናቱ እናት አያቱ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ አላፊ እየሆኑ ስለ ሠሩልኝ ፣ ማናቸውም ችግር አላገኘኝም ነበርና በፍጹም የደስታዬ ወራት ያንጊዜ ነበር። እንደ ሀገሩ ልማድ አገረ ገዥ በችሎት እየተቀመጠ መፍረድ የሚገባ መሆኑን እያወቅሁ ከዚህ ቀድሞ የዕድሜዬን ማነስ እያየሁ በችሎት ተቀምጬ ለመፍረድ አልደፈርሁም ነበር። አሁን የሲዳሞን ግዛት ከተሾምሁ ወዲህ ግን ዓርብና ረቡዕ በችሎት እየተቀመጥሁ መፍረድ ጀመርሁ።

ከአባቴ ሠራዊት ወደ እኔ የመጡትን የራሴን የቀድሞ አሽከሮቼን ፡አዲስ አበባም ከወጣሁ በኋላ አዲስ የገቡልኝን ከሦስት መደብ ከፍዬ ለሁሉም እንደ ደረጃቸው አደላድዬ ትዳራቸውን በመስጠቱ በጣም ደስ ብሎኝ አንድ ዓሥት ያህል እንደ ቆየሁ ፣ በ1901 ዓመተ ምሕረት ጃንሆይ በብርቱ ታመዋል ማለትን ብሰማ ወደ አዲስ አበባ ልምጣ ስል

ፈቃድ ጠየቅሁ ። እንድትመጣ የሚል የጃንሆይ ደብዳቤም ስለ ደረሰልኝ በየአውራጃው ያሉት ሹሞቼ ሥራቸውን ሁሉ በትጋት እንዲሠሩና አገሩንም በጥንቃቄ እንዲጠብቁ አዝ በሚያዝያ ወር ወደ አዲስ አበባ መጣሁ።

ጃንሆይ ዐፄ ምኒልክ በብርቱ ስለ ታመሙ ወደ አደባባይ ወጥተው ለሠራዊቱ ከመታየት በቀር ዋና ሥራ ለመሥራት ብርታት አልነበራቸውምና ትልቁም ትንሹም በጣም ተጨንቆ ነበር። በመንግሥቱም ሥራ ሁሉ ባለሙሉ ሥልጣን ሆነው የሚያዙበት እቴጌ ጣይቱ ነበሩ። በዚሁም ምክንያት ሰላም ጠፍቶ ሁከት እንዲነሣ የሚጥሩ ብዙ ሰዎች በቤተ መንግሥቱ ግቢ ይታዩ ነበር። በዚሁም ሁሉ ደግሞ እቴጉ ጣይቱ ባለሙሉ ሥልጣን ሆነው የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ በመሥራታቸው የቀኑ ሰዎች ሥልጣናቸውን ለመውሰድና ከቤተ መንግሥቱ ለማስወጣት ሜራ ጀምረውባቸው ነበር። እኔም ወደ ራው እንድገባላቸው ቢጠይቁኝ ፡ በራቸው ውስጥ ለመግባት አልፈቅድም ስላልኋቸው ረኞቹ ሁሉ በመጥላት ዓይን ያዩኝ ጀመር። እቴጌ ጣይቱም ወደ ሜራው ለመግባት እምቢ ማለቱን ሰምተው ለጃንሆይ ነግረዋቸው ኖሮ ሁለቱም በጣም ደስ አላቸው።

ጃንሆይ ምንም እንኳ በብርቱ ቢታመሙ በዚያ ጊዜ አእምሮዋቸው ትክክል ነበረ። ይሁን እንጂ ጭረኞችን ለመቆጣትና ለመምከር የተመቸ ጊዜ አላገኙም ነበር። እኔም ወደ ራው አልገባም ማለቱን ፣ እነዚያው ሜረኞቹ ደጃዝማች ተፈሪ ወደ ሜራው ግባ ብንለው እምቢ አለ ብለው ምስጢሩን አወጡትእንጂ እኔ ለእቴጌጉም ለሌላ ሰውም ቢሆን እምቢ አልሁ ብዬ አልተናገርሁም። እቴጌም የነገሩን እርግጥነት ለማወቅ ብለው እየመላለሱ ቢጠይቁኝ ወደ ሜራው ግባ ብሎ የጠየቀኝ ሰው የለም በማለት ጸናሁ። ስለዚህም ምስጢሩን ባለማውጣቱቴ በጣም ደስ እንዳላቸው ገልጠው «እርግጡን አውቄዋለሁ ፣ አንተ ምስጢሩን አለማውጣትህ ታላቅ ቁም ነገረኛ ብትሆን ነው» አሉኝ።

ይህ የሜራው ነገር የተጀመረው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው እየተባለ መወራቱን እቴጌ ጣይቱ ስለ ሰሙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲዘጋ አድርገው ለጊዜው ጭራቸውን አፈረሱባቸው። ዳግም ባለፈው ዓመት ለመንግሥት ሥራ አማካሪነት ፡ ለሐኪምነት፣ ለአስተማሪነት ሦስት ጀርመኖች ተቀጥረው መጥተው ለየሥራቸው ከሚኒስትሮች ጋራ እየተገናኙ ይሠሩ ነበርና፡እቴጌ ጣይቱ ሚኒስትሮች በርሳቸው ላይ እንዲያሜሩ ምክር የሰጡ እነዚያ ጀርመኖች ይሆናሉ የማለት ጥርጣሬ ስለ ገባቸው አንዳንድ ምክንያት እየፈለጉ ሥራቸውን እንዲለቁ አደረጉ ይባል ነበር።

በዚህም ዓመት በትግሬ የእንደርታ ገዥ ደጃዝማች አብርሃ ስለ ሸፈቱ ራስ አባተ ገና ዋግ ሹም ተብለው ሳሉ ደጃዝማች አብርሃን በመስከረም መጨረሻ 1902 ዓ. ም. ወግተው ድል ባደረጉ ጊዜ ፡ ሌሎች የትግሬ ገዢዎች ለደጃዝማች አብርሃ ወይም ለራስ አባተ ሳይረዱ ዝም ብለው ያዩ ነበር ተብሎ ተወራ። ፡

ዐፄ ምኒልክም በሽታቸው ፡ ሕዋሳት ሁሉ እንዳይንቀሳቀሱና ሥራቸውን እንዳይሠሩ የሚከለክል ፓራሊዝ የሚባል ኖሮ ፣ በ1902 ዓ. ም. በጥቅምት 17 ቀን በ9 ሰዓት ሌሊት በድንገት መንቀሳቀስም መናገርም አቃታቸውና መኳንንቱም ሠራዊቱም ይህን በሰሙ ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ግቢ በከተማውም ትልቅ ኀዘን ተደረገ። ቢሆንም ከጥቂት ቀን በኋላ የሚለቃቸውና የሚድኑ ይመስል ነበር እንጂ ብዙ ዓመት የሚቆዩና ለሞት የሚያደርሳቸው ነው ተብሎ አልታሰበም ነበር።

# ምዕራፍ 4

## ሐረርንና የአውራጃዋን ግዛት ስለ መሾሜ ፡ (1902 ዓ. ም.)

ከዚህም በኋላ የሐረርጌ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ባልቻ በታኅሣሥ ወር ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ነበርና እርሳቸው ገና አዲስ አበባ ሳይገቡ የሐረርጌን ግዛት ለደጃዝማች ተፈሪ ሊሰጡት ነው እየተባለ በሕዝቡ አፍ ይወራ ጀመር። ደጃዝማች ባልቻምገና በመንገድ ሳሉ ይህንኑ ሰምተው ኖሮ አዲስ አበባ እንደገቡ ወዲያው ባማላጅም በገንዘብም የሐረርን ግዛት ለማስቀረት ይጣጣሩ ጀመር። እኔ ግን መቸም እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ እንደሆነ አይቀርብኝም በማለት ሌላውን የዕለት ሥራዬን እየሠራሁ እጠባበቅ ነበር።

ከዚህም በኋላ አንድ ቀን በድንገት ራስ ቢትወደድ ተሰማና ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ባንድነት ሆነው አስጠርተው፣«ምንም ዕድሜህ ልጅ ቢሆን ፣ ሥራህ ሁሉ ያዋቂ መሆኑን በሲዳሞ አገዛዝህ ስለ አሳየህ ፣ አሁንም ያባትህ ግዛት የነበረውን ሐረርጌን እቴጌ ሰጥተውሃል» ብለው ነገሩኝ ። እኔም የሐረር ገዥ በመሆኔ ትልቅ አላፊነት እንዳለብኝ ዐውቃለሁና እናንተ እየረዳችሁኝ ፣ አገዛዙን አደላድላለሁ ብዬ እጅ ነሣሁ። ዐዋጁም በየካቲት 24 ቀን 1902 ዓ. ም. በአደባባይ ተነግሮልኝ ወደ ቤቴ ስወጣ የሕዝቡ ደስታ ከልክ ያለፈ ሆኖ ይታይ ነበር። በሐረርም የቆንስላ ቤት ያላቸው የዲፕሎማቲክ ሰዎች ወደ ቤቱ እየመጡ የደስታዬ ተካፋይ መሆናቸውን እያስታወቁ ሐረርን እንደ አባትዎ በመልካም አገዛዝ እንዲገዙ ተስፋ እናደርጋለን እያሉ ተናገሩ።

ወደ ግዛቴ ወደ ሐረር እስክወርድ ድረስም ያባቴ ታማኝ የነበሩ ፊታውራሪ ገብሬ (በኋላ ደጃዝማች የተባሉ) እንደራሴ ሆነው አገሩን እየጠበቁ እንዲቆዩ ትእዛዝ አስተላለፍሁ። ለሐረርም መንገዴ ስሰናዳ ራስ ቢትወደድ ተሰማ እንደገና በእቴጌ ጣይቱ ላይ ውስጥ ለውስጥ ሤራ ማስነሣታቸው በድንገት ተወራ። ለሤራውም መሪ የሆኑት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ስለ ሆኑ ዋና ረዳቶች የነበሩት ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ፣ ፊታውራሪ ወሰኔ (በኋላ ደጃዝማች የተባሉ) ደጃዝማች ብርቄ ፣ ደጃዝማች መርድ ነበሩ። ደጃዝማች ደምስም (በኋላ ራስ የተባሉት) ከግዛታቸው ተሽረው ተቀምጠው ነበርና በግልጥ ሳይሆን ውስጥ ውስጡን ይጐተጕቱ ነበር ይባላል ።

እኔ የሐረርን ግዛት ከተሾምሁ ከጥቂት ቀን በኋላ መኳንንቱ ሁሉ በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ ቤት ተሰብስበው በእቴጌ ጣይቱ ላይ ልዩ ልዩ የሆነ ወንጀል ተናግረው ከእንግዲህ ወዲህ እቴጌ ጣይቱ በቤተ መንግሥት እያስታመሙ ይቀመጡ እንጂ በመንግሥት ሥራ ውስጥ እንዲገቡ አንፈቅድም ብለው አሳባቸውን ገልጠው አማከሩዋቸው። ነገር ግን የእቴገ. ጣይቱ ወገናቸው ብዙ ነበርና ነገሩን ለመቁረጥ ስለ አስቸገረ በውዝፍ ቆየ። ። እቴጌ ጣይቱ ፈቃደ ብርቱና አገዛዝ ዐዋቂ ነበሩ። እኔም በዚያ ወራት የእቴጌ ጣይቱን እቴጌነት አክባሪ ነበርሁ። የሐረርንም ግዛት የተሾምሁት በእርሳቸው እርዳታ ስለ ሆነ መኳንንቱ ነገሩን ገልጠው ለመንገር አልደፈሩኝም ነበር።

እስከ 13 ቀን ነገሩ ሳይቆረጥ በውዝፍ ከቆየ በኋላ እንደገና በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት ጉባኤ ይደረግ ተባለና በመጋቢት 11 ቀን ሁላችንም እየተጠራን ሔድን። ራስ ቢትወደድ ተሰማም በነገሩ እንዳልገቡ ለመምሰል እንደ መኳንንቱ ተጠርተው መጡ። ከዚህም በኋላ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አፈ ጉባኤ ሆነው እቴጌ ጣይቱ በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ይልቁንም በሹም ሽሩ ደስ አላለንም። የደጃዝማች ተፈሪ ብቻ ባባታቸው ግዛት በሐረር መሾማቸው መልካም ነውና የርሳቸው ብቻ ይጽና እንጂ የተቀረው ሹም ሽር ይፍረስ። ለወደፊቱም በመንግሥት ሥራ ውስጥ አይግቡብን ብለው ተናገሩና ሁሉም ባንድ ቃል የደጃዝማች ተፈሪ ሹመት ይርጋ ብለናል ፤የቀረው ሹም ሽር መፍረሱ መልካም ነው ብለው ነገሩ በዚህ ተጨረሰ።

በማግስቱ መጋቢት 12 ቀን ሁሉም ባንድነት ሆነው ወደ ቤተ መንግሥት ገብተው በእቴጌ ጣይቱ ፊት ቀርበው የእኛ አሳብ እቴጌ በቤተ መንግሥት ተቀምጠው ጃንሆይን እንዲያስታምሙልን ፣ የመንግሥቱን ሥራ ግን ለእንደራሴው ለራስ ቢትወደድ ተሰማ እንዲለቁለት ነው ብለው ተናግረው ሲጨርሱ ፣ እቴጌ ጣይቱ ፊታቸውን ወደ ራስ ቢትወደድ ተሰማ አዙረው «ይህን ነገር ሁሉ ያሰብከውና ያደረግከው አንተ መሆንህን እያወቅህ ለምን



በሕፃንነት ዘመን ከግራ ወደ ቀኝ ማሚቴ ብሩ፣ ልጅ ተፈሪ(ቀ.ኃ.ሥ) ተፈራ በለው(ቀኛዝ) ልክ እምሩ(ልዑል ራስ)

በሌላ ሰው ታመካኛለህ ሁሉንም ነገር በእርግጥ ሰምቼዋለሁ እኔን የሚያሳዝነኝ በተንኩል መሥራትህ ነው እንጂ ሥራውንማ ገና አስቀድሞ እኔ ጃንሆይን አስታምማለሁ የመንግሥቱ ሥራ ይቅርብኝ ብዬ ብነግርህ ራስ መንገሻ አቲከምን አማላጅ ልከህ የመንግሥቱን ሥራ እርስዎ እየሠሩ ካላስለመዱን ፤እኛ ምኑን እናውቀዋለን ፣ ሥራውን ልተው ማለትዎማ ቢበላሽ ምን ቸገረኝ ለማለት ነው ፣የምኒልክን ውለታ መመለስ እንግዲህ ወዲህ በሚሠሩት ሥራ ነው ብትለኝ፡ሥርቹ የምጠቅምከሆነ በሚቻለኝ እረዳለሁ አላልኩህምን። ደግሞስ ላንተ ሳላማክርህ ምን የሠራሁት ሥራ አለ ፣ በልእስቲ ይህን ይህን አልሰማሁም አላወቅሁትም ብለህ ገልጠህ ተናገር » ብለው በሦስት ነገር አሳፈርዋቸው። ይኸውም 1ኛ : ራውን ውስጥ ለውስጥ ማስነሣታቸውን ፣ 2ኛ : የመንግሥቱን ሥራ እርስዎ ይሥሩ ብለው አማላጅ መላካቸውን ፣3ኛ : ሳያስታውቁና ሳያማክሩ አለመሥራታቸውን በማስረዳት ነው።

ከዚህ በኋላ ራስ ቢትወደድ ተሰማም ሌሎችም መኳንንቶች በነገሩ ስለአፈሩ ይማሩን እያሉ አጉነበሱ። እቱጌ ጣይቱ ግን በነገሩ በጣም ስለ አዘኑ እያለቀሱ ዝም ከማለት በቀር ስለ ምሕረቱ ነገር ምንም ምላሽ አልሰጡም ። ቢሆንም ነገሩ በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት እንደ ተቆረጠው የመንግሥቱ ሥራ በሙሉ በራስ ቢትወደድ ተሰማ እጅ ተዛወረና ይሠራ ጀመር ።

እኔም ወደ ግዛቴ ወደ ሐረር ከመውረድ የቆየሁት በዚህ ምክንያት ይመስለኝ ነበርና የዚህ ነገር ከተጨረሰ ልውረድ ብዬ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ ፈቃድ ብጠይቅ ቆይ ተባልሁ። ቆይ የተባልሁበትም ምክንያት ፣ «ሕልም እናያለን የሚሉ መነኩሳት ፣ ደጃዝማች ተፈሪ ወደ ሐረር የወረደ እንደሆነ ለልጅ ኢያሱ መንግሥት በጣም የሚያስፈራው ይሆናል ብለው ስለ ነገርዋቸው ነው» እየተባለ ውጭ ውጭውን ይወራ ጀመር። ወዲያውም ራስ ቢትወደድ ተሰማ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በሆኑ በአራተኛው ቀን የልጅ ኢያሱ ባላንጣ ነው ብለው ፊታውራሪ ታዬ ጉልላቴን አስረውት ነበርና በእኔም በኩል ለጊዜው ሥጋት ሆኖብኝ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር የፈቀደውን : ሰው ሊያስቀረው አይችልምና የራስ ቢትወደድ ተሰማ አሳብ ልጅ ኢያሱንና እኔን ቃል ኪዳን ለማጋባትና በሥራቸው መሰናከል የሚሆን ነገር እንዳይገኝ ለማድረግ ኖሮ እኔንና ያባቴን ትልልቆች መኳንንቶች ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወደ አቡነ ማቴዎስ ቤት ወስደው ሁላችንም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ቃል እየማልንና እየተገዘትን ቃል ኪዳን ገባን ።

1ኛ. እኔ በተንኩል በባላንጣነት የልጅ ኢያሱን አልጋቸውን እንዳልፈልግ።
2ኛ. መኳንንቶቼም የልጅ ኢያሱን አልጋ ለመውሰድ ክፉ ምክር እንዳይመክሩኝ።
3ኛ. ልጅ ኢያሱ እኔን በባላንጣነት ዓይን አይተው ከአባቴ ግዛት ከሐረር እንዳይሽሩኝ።
4ኛ. ራስ ተሰማም ለልጅ ኢያሱ የተንኰልና የክፋት ምክር መክረው ከሐረር ግዛት እንዳይሽሩኝ በባላንጣነቴም እንዳያጠፉኝ ነው።

ከዚህም በኋላ ወደ ሐረር እንድወርድ ስለ ተፈቀደልኝ በየቤታቸው ሔጄ ለመሰናበት የሚገባቸውን ትልልቆቹን ባለማዕርጎች እየሔድሁ ተሰናበትሁ። እቴጌ ጣይቱን ለመሰናበት ምንም እንኳ ጊዜው በጣም የሚያሰጋ ቢሆን ሳልሰናበት ብሔድ ሕሊናዬ ይወቅሰኛል በማለት ወደ ቤተ መንሥት ገብቼ ተሰናብቼ ጉዞዬን ጀመርሁ።

በዚያ ዘመን ከአዲስ አበባ እስከ ድሬዳዋ የምድር ባቡር ገና አልተሠራም ነበርና በጣም የሚያደክም ጉዞ ሆነብኝ። ወደ ሚያዝያ መጨረሻም ሐረር ደረስን። በሐረርም ያለው እንደራሴዬ ብዙ ድግስ ደግሶ ወደ ሐረር የምንገባበትን ቀን ሲጠባበቅ ነበርና እንደ አጋጣሚ እኔ ሐረር በምገባበት ቀን የእንግሊዝ ንጉሥ ግርማዊ ኤድዋርድ 7ኛ በ28 ሚያዝያ 1902 ዓ ም ማረፋቸው ስለተሰማ የታሰበው የክብር አቀባበል እንዲቀር አድርገን ሰንደቅ ዓላማው በግማሽ እንዲሰቀል አዘዝንና የኀዘኑ ተካፋይ መሆናችንን ሐረር ላለው የእንግሊዝ ቆንሲል አስታወቅን። የተለየ ኀዘን ያደረግነውም ግርማዊ ኤድዋርድ 7ኛ የእንግሊዝ ንጉሥ የህንድ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውድ በጫኑ ጊዜ አባቴ ልዑል ራስ መኮንን ከዐፄ ምኒልክ ዋና መልክተኛ ሆነው ተልከው ሔደው ነበርና በዚያ ጊዜ በእንግሊዝ ቤተ መንግሥት የተደረገላቸውን የክብር አቀባበል ይነግሩኝ ነበር። ደግሞ ለዘውዱ በዓል አባቴ ሎንዶን እንደ ደረሱ ግርማዊ ኤድዋርድ በድንገት ታመው የዘውዱ በዓል ቀን መተላለፋን ቢሰሙ «ሎንዶን ድረስ መጥቼ ንጉሥን ትልቅ

አደጋ አግኝቷቸው የዘውዱ በዓል መከበሩ ቀርቶ ወደ ሀገሬ ብመለስ ዕድለ ቢስ እባላለሁና አደራህን አምላኬ አድንልኝ» ብለው ባገራችን በኢትዮጵያ እንደሚ ደረገው ልማድ ወደ ዌስት ሚኒስቴር አቤ ሔደው ለቤተ ክርስቲያኑ ትልቅ የወርቅ መስቀል ስለት አድርገው መስጠታቸውን ነግረውኝ ነበርና ይህን የመሰለ መገናኛ መኖሩን ስለማውቅ ነው። ይህንም የወርቅ መስቀል በ1916 ዓመተ ምሕረት ሎንዶንን ለመጐብኘት ግርማዊ ጆርጅ 5ኛ የክብር ጥሪ አድርገውልኝ በመጣሁ ጊዜ የካንተርባሪ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ራይት ሆነራብል ራንደል ቶማስ ዳቢድሰን ዌስት ሚኒስቱር አቤን ሲያሳዩኝ አባትዎ ልዑል ራስ መኰንን ስለ ግርማዊ ኤድዋርድ ሕመም ተስለው የሰጡት ነው ብለው አሳይተውኛል።

ከሰባት ቀንም በኋላ የክብር አቀባበሉ ሥራ ሁሉ በደስታ ተፈጸመና ያገሩን ማስተዳደር ሥራ ጀመርን። አንድ ትልቅ አውራጃ ማስተዳደር ምን መሆኑን ያገር ግዛት አላፊነት ያለባቸው ሰዎች ብቻ ያውቁታል ፡ያስተዳደሩ ነገር ከተጻፈ በኋላ ለሚያነበው ሰው የሥራው ድካም አይሰማውም ። እንዲያውም ተርታ ነገር መስሎ ይታየው ይሆናል። እኔ ግን ከሌሎቹ አገረ ገዢዎች የተለየ በጣም የሚያደክም ከባድ ሸክም ነበረብኝ ፣ ይኸውም ከዚህቀጥሎ ያለው ነው።

1ኛ. በአባቴ ጊዜ ባላገሩም ወታደሩም ሌላ ገዥ አያውቅም ነበርና እርሳቸውን ብቻ እንደ ጌታም እንደ አባትም አድርጎ አንድ ልብ ሆኖ ይኖር ነበር። አባቴ ካረፉ ወዲህ ግን ደጃዝማች ይልማና ደጃዝማች ባልቻ ስለተሾሙበት አመሉን ለውጦ ነበርና አሁን እንደ አባቴ ጊዜ ባላገሩንም ወታደሩንም አስማምቶና ደስ አሰኝቶ መግዛት የሚቻልበትን ዘዴ ማደራጀት ነበረብኝ።

2ኛ. ወንድሜ ደጃዝማች ይልማ ሐረርን ከተሾሙ በኋላ በቶሎ ስለዐረፉ ደጃዝማች ባልቻ የሐረር ገዥ ሆነው ሲሾሙ ከአባቴ የጦር ሠራዊት መካከል ለእኔ 3ሺህ ተሰጥቶኝ ፡3ቱ ሺህ ደግሞ በልጅ ኢያሱ ሠራዊት ስም ወደ ወሊጋ ሔዶ ነበርና አሁን እንደገና ወደ እኔ ሲመለስ ማደሪያውን ማደላደል ነበረብኝ።

3ኛ. ከደጃዝማች ይልማና ከደጃዝማች ባልቻ አሽከሮች ከእኔ ጋራ መኖርን ወደው በሐረር የቀሩ ብዙ ነበሩና ለነዚህም ማደሪያ መስጠት ነበረብኝ።

4ኛ. ከውጭ አገር ሰዎች ጋራ በሚያገናኘው ሥራ ሁሉ ዐፄ ምኒልክ ከፈረንሳዊ መንግሥት ጋራ በ1900 ዓ. ም. የተዋዋሉትን የክሎቢኮቢስኪ ውል የሚባለውን እየጠየቅሁ ኢትዮጵያ የተሸከመችውን ይህን የውል ቀንበር መሥራት ነበረብኝ።

የሐረርን ግዛት በመሾሜ የደስታዬ ተካፋይ ለመሆን በያውራጃው ከሚኖሩት ከመኳንንቱና ከወታደሩ ከባላገሩም ትልልቆቹ ተሰብስበው መጥተው ነበርና ስለ ሀገሩ አስተዳደር የምንሠራውን ሁሉ ወደ ፊት እናስታውቃችኋለን ብለን አሰናበትናቸው። ያገሩንም ማስተዳደሪያ ሥራ ለመጀመር ቁርጥ አሳብ አደረግን ።

በዚያ ዘመን የማስተዳደሪያ ደንብ የሚባለው ሠራዊቱን ለጊዜው ደስ የማያሰኘው መሆኑን ልባችን ተረድቶት ነበር። ቢሆንም በቀን ብዛት ሳይለመድ አይቀርምና ለመንግሥት ጥቅም የሚሆነውን መሥራት ያሻል በማለት በአሳባችን ገፋንበት። ለሥራውም እንዲረዳን በማለት ከእኛ አስቀድሞ የነበሩ ገዥዎች ይሠሩበት የነበረውን መዝገብ በሙሉ ለማግኘት ብንፈልግ ፣ ከአባቴ ከልዑል ራስ መኰንንና ከወንድሜ ከደጃዝማች ይልማ መዝገቦች ጥቂቶች ብቻ ሲገኙ ፣ በሙሉ ለማግኘት አልተቻለም። ስለዚህ በሐረር ብዙ ዘመን ከኖሩት ከመኳንንቱና ከባላገሩም ወገን ሽማግሌዎቹን እየፈለግን መጠየቅ ግድሆነብን ።

ይልቁንም በጣም አስቸጋሪ ሆኖብን የነበረው የጦር አለቆችና ጭፍሮች አኗኗር ነገር ነው። ያለቃው ማደሪያ ባንድ አውራጃ ሆኖ ፡ የጭፍራው ማደሪያ በሌላ አውራጃ ስለ ሆነ ፣ በዘመቻ ጊዜ ብቻ ይገናኛሉ እንጂ ለዘወትር በመተያየትና በመተዛዘዝ አይተዋወቁም ነበር። እነዚያንም ከየማደሪያቸው ላይ አፋልሶ አለቃና ጭፍራ ባንድ አውራጃ እንዲኖሩ ካልሆነና በመተያየት ፣ በመተዛዘዝም ካልተላመዱ በዘመቻ ጊዜ ብቻ መገናኘታቸው ሥነሥርዓት የማይሰጥ ትልቅ ጉዳት መሆኑን ስለ ተረዳነው ለማደላደል እንዲመቸን አስቀድሞ የሠራዊቱን ቀኑጥር፤

የማደሪያውንም ልክ ማወቅ የሚያስፈልገን ሆነ። ስለዚህ የሐረርን አውራጃዎች እየዞሩ ግብር ለመክፈል የሚችሉትን ባላገሮች ቆጥረው በፍጥነት የሚያስታውቁትን ሰዎች በያውራጃው እንዲሔዱ አዘዝን። እነዚህንም ባላገሮች ለመቁጠር የታዘዙት ሰዎች በ3 ወር ውስጥ ሥራቸውን ጨርሰው ስለ ተመለሱ ፣ ግብር ለመክፈል የሚችሉ ባላገሮች 70ሺ መሆናቸውን በመዝገባቸው ጽፈው አቀረቡልን።

ከዚህም በኋላ የሐረርን ግዛት በ12 ታላላቅ አውራጃዎች እንዲከፈል አደረግን። ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው። ጨርጨር ፣ ቆሪ ፣ ወበራ ፣ ሜታ ፣ አንያ ፣ የሐረር ዙሪያ ፣ ጋራ ሙለታ ፣ አፍረን ቀሎ ፣ጃርሶ ፣ ጅጅጋ ፣ ውጋዴን ፣ ኢሳና ጐርጐራ ነው።

በነዚህ በትልልቅ አውራጃዎችም ላይ አንዳንድ ጠቅላላ አበጋዝ እየሾምን በውስጡ አለቃና ጭፍራ በየደረጃው እንዲደላደል አደረግን። ገባርም፡ ወታደርም ፡ አለቃም ፡ ስሙ በመዝገብ እየተጻፈ አለቃና ጭፍራ ሳይለያይ ባንድነት እንዲኖር በማናቸውም ምክንያት በተጠራ ጊዜ ባንድነት እንዲገኝ ሆነ። በየወረዳው የዳኝነት ቤቶች እንዲቆሙና ለየወረዳው አላፊ እንዲሆኑ ተደረገ። የቤተ ክህነትን ማስተዳደሪያ ብቻ እንደ አሳባችን ለመፈጸም ጊዜው አልፈቀደልንም ነበርና ለጊዜው እንደ ጥንቱ እንዲቆይ ተውነው ።

አባቴ ልዑል ራስ መኰንን ከሞቱ በኋላ የሐረር ገዥዎች በመለዋወጣቸው ምክንያት ካቆሙት ከአገዛዙ ደንብ ብዙው ስለ ፈረሰ ፡ አበጋዙና ደሚናው ፡ ገራዳውም ባላገሩን በትክክል ስላልጠበቁት ባላገሩ ያገዛዝ ቀንበር እንደ ከበደው ልባችን ስለ ተረዳው ፣ ለዚህ የሚሻለውን ነገር መፈለግ ጀመርን። አበጋዝ ማለት ያውራጃው እንደራሴ ነው። ደሚናም ማለት በወረዳው ባሉት ሕዝቦችና በመልከኛው መካከል ሆኖ ባላገሩ ግብሩን በጊዜው እንዲሰጥ ፣ መልከኛውም ባላገሩን በግብርም በሌላም ነገር እንዳይጐዳው እንደ ተቆጣጣሪሆኖ የሚሠራ ነው፣ ፡ ምናልባት አንዳንዱ ደሚና ከ20 እስከ 300 ባላገሮች ያዝዛል። ገራዳ ማለትም ከደሚናው በታች ሆኖ የሚያዝዝና የሚሠራ ሹም ነው። ይኸውም ቱርኮች ሐረርን ለጥቂት ዘመን (ዐሥር ዓመትያህል) ይዘውት በነበሩ ጊዜ ተለምዶ እስካሁን የቆየ ነው።

አባቴ አቁመውት የነበረው ያገዛዝ ደንብ ከሞቱ በኋላ እየፈረሰ በመሐዱ ምክንያት አንዳንድ አስገባሪዎች ባላገሩን በመሬቱ በሚከፍለው የማር ግብር ሲቸግረው በማሩ ፋንታ እስከ 12 ብር ይቀበሉት ነበር። ሌላም ይህን የመሰለ ለባላገሩ ጉዳት የሚሆን ሥራ ለመሥራት ጀምረው ነበርና አበጋዞቹንና መልከኞቹን ብቻ ባላገሩን ባገዛዝ አትጉዱት ብለን አዘዝናቸው። ነገር ግን ባላገሩ ይኸንኑ ትእዛዝ ባዋጅ ካልሰማው ይህን የመሰለውን ግብር አልከፍልም ብሎ ለመከራከር እንደማይችል ስለ ተረዳነው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ባዋጅ አስታወቅነው።

## ዐዋጅ

አበጋዝ የሆንህ ፣ በእንደራሴነት በምትገዛው አገር ሌባና ቀማኛ ጠብቅ ፡በአገሌ ግዛት ሰው ተቀማ የሚሉ የሰማሁ እንደሆነ የሚከፍለው አበጋዙ ነው። ጌታ የሌለህ ፡ ሥራ ፈት ፣ላበጋዝ በሰጠሁት ከተማ ገብተህ ተቀመጥ እንጂ ባገር ቤት ሆነህ ባላገሩን አታውክ። በየአበጋዝነትህ ያለው መንገድ ተበላሽቶ ወጪ ወራጅ ፣ ነጋዴ እንዳያስቸግር መንገድህን ሥራ። በሰንበት ሥራ ከዚህ ቀድሞ ክልክል ነው ፣ አሁንም በሰንበት ስትሠራ የተገኘህ ትቀጣለህ። የማር ግብር ያለብህና ማር ያለህ ሰው ልኩን ላበጋዝህ ሰጥቼልሃለሁና በዚያው ልክ ማርህን አግባ። ማር የሌለህ ግን ስለ ማሩ ገራዳ አራት በር ፡ ሸበታ ሦስት ብር ፡ ጭሰኛ ሁለት ብር ፡ አረኛ አንድ ብር ስጥ። ነገር ግን ማር ያለህ ብር እሰጣለሁ ብለህ ማርህን ስትሸጥ የተገኘህ እንደሆነ ማሩን በእጥፍ ትከፍላለህ። ገራዳም ሆነህ እንደ ሸበታ ትክክል የምትገብር ፡ ማርህንም እንደ ሸበታ ሦስት ብር አውጣ። ገራዳ ፣ ሸበታ ፣ ጭሰኛ ፣ እረኛ ካልተቸገርህ በቀር ግብርህ ማር ነውና ቀፎህን ስቀል። መልከኛም የማር እሸት አትንካ ፣ ወደ ፊትም ለሚሠራው ሥራ ሁሉ እንደ ጥንቱ

ደሚናህን ይዘህ ሥራ። ከዚህም ቀድሞ «ካገር ወደ አገር ተዛወርህ እንጂ አዲስ አገር አላወጣህምና ኮቤ ባሳ አትብላ» ብዬ ባዋጅ ነግሬህ ነበር። አሁን ግን ከባላገሩ ላይ ትቀበላለህ ማለትን ሰምቻለሁና ይህን ከዐዋጅ በላይ የተቀበልኸውን ገንዘብ ለባላገሩ መልስ። ወደፊትም አበጋዝና ደሚና ከተደነባለት በላይ አልፎ መልከኛ የባላገሩን ገንዘብ እንዳይወስድበት ጠብቁ። ባላገሩ አልፎ የተበላበትን ገንዘብ ለናንተ ነግሮዋችሁ ሳትመልሱለት ቀርታችሁ ሥራውን ፈትቶ ወደኔ መጥቶ የጮኸ እንደ ሆነ ጥፋቱ የእናንተ ነውና ገንዘቡን እናንተ ከፍላችሁ እናንተ ከዚያ ከወሰደበት ሰው ላይ ትቀበላላችሁ። ባላገርም ለአበጋዝና ለደሚናህ ሳትነግር ወደኔ አትምጣ። ለሦስቱ ዓመት በዓል ለመስቀል ፣ ለገና ፣ ለፋሲካ ስለ ሙከት ሁለት ሁለት ብር ተቀበል እንጂ ከዚህ በላይ አትቀበል ።

ሐምሌ 13 ቀን 1905 ዓ. ም. ሐረር ፣

ዐዋጁም ከተነገረ በኋላ አበጋዞችና መልከኞች ምንም እንኳ ለጊዜው ደስ ባይላቸው ከጥቂት ወራት በኋላ ያስተዳደሩን ደንብ እየለመዱት ጥቅሙንም እያገኙት ስለ ሔዱ ፡ ባላገሮችም ያገዛዙና የግብሩ ቀንበር ስለ ቀለላቸው ሁሉም ልባቸውን አሳርፈው ሥራቸውን ይሠሩ ጀመር።

# ምዕራፍ 5

## የጋብቻ ሥርዓት ከፈጸምሁበት ጀምሮ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እስከ ሆንሁበት ዘመን ድረስ። (1903 -- 1909 ዓ. ም.)

የሐረርና ያውራጃው ሁሉ ገዥ ሆኘ የባላገሩንና የወታደሩን ኑሮ ፡ ያገዛዙንና ሌላውንም ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን ሁሉ ያለ ዕንቅፋት እየሠራሁ አንድ ዓመት ያህል ከቆየሁ በኋላ ዕድሜዬ 20 ዓመት ሲሆን ፡ በራሴና በዘመዶቼ ፈቃድ የንጉሥ ሚካኤልን የልጅ ልጅ ዛሬ እቴጌ የተባለችውን ወይ ዘሮ መነንን እንዳገባ ነገሩ ተቆረጠና በሐምሌ 23 ቀን 1903 ዓመተ ምሕረት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተጋባን ።

እርስዋም ጠባይዋ ከደግነት በቀር ክፋትና ማስቀየም የሌለባት ናት ። ባንድ ወገንም ወላድ በመሆንዋ ከተጋባንበት ዘመን ጀምሮ ደስታውንም ኀዘኑንም ባንድነት እየተካፈልን ኖረናል ።

ደስታውንም ኀዘኑንም ባንድነት እየተካፈልን ኖረናል ከተባለው ውስጥ ሳልጽፈው ለመቅረት የማይቻለኝ አንደኛው ትልቁ ኀዘን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው። የወይዘሮ መነን ታናሽ ወንድም ራስ ኃይለ ማርያም በ1907 ዓ. ም. ስለ ዐረፈ ፣ሐረር ላይ ተረድተን ነበር። እናታቸው ወይዘሮ ስኂን ከወሎወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ስለ ወንድሟ ዕረፍት ባንድነት ለመላቀስ ወይዘሮ መነን ወደ አዲስ አበባ እንድትወጣ ነገሩ ተቆርጦ ነበርና በግንቦት 30 ቀን ሰኞ ከሐረር ተነሣች። እኛም እስከ ሐረማያ ሸኝተናት ለመመለስ ስለ ፈለግን በሐረማያ ባሕር ዳር ሰፈር ሆኖ ነበር።

ከዚህም አስቀድሞ በሐረርና በድሬዳዋ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ወደ ሐረማያ ባሕር እየገቡ የሚናፈሱበት ጀልባ ነበርና በ9 ሰዓት ከድንኳን ወጥተን ወደ ባሕሩ ሔድን። ከእኛ ጋራ በጀልባ ገብተው በባሕሩ የሚናፈሱ ዐሥር ሰዎች ተቆጥረው ነበር። በጀልባው ከገባን በኋላ መሃል ለመሃል አቋርጠን ወደ ማዶ ተሻገርን። በወዲያኛውም ዳር ጥቂት ከቆየን በኋላ ወደ ሰፈራችን ለመመለስ እንደገና በጀልባው ውስጥ ገባን ። ነገር ግን ጀልባው ያረጀ ኖሮ በባሕሩ መካከል ስንደርስ ተቀደደና ውሃው ይገባ ጀመር ።

በጀልባውም ውስጥ ያሉት ሰዎች ውሃውን በየባርኔጣቸው እያፈሱ ቢያፈሱት የማያልቅ ሆነ። ጀልባውም መቀደዱንና በውስጡ ሆነን ለመሻገር የማይቻል መሆኑን ከተረዳነው በኋላ ሁላችንም ከነጀልባው ሰጥመን የጭንቅ ዋና እንዋኝ ጀመር። ነገር ግን ባሕሩ ሰፊ ነበርና ዋኝቶ ለመሻገር የማይቻል ስለ ሆነ አባ ተስፋ ፡ቀኛዝማች ገብረ ወልድ አቶ አየለ ሥዩም ፡ኪዳነ ማርያም ማንያዘዋል ፡ አሰምሬ ፡ አባ ሳሙኤል ፡ ጳውሎስ እነዚህ ሰባቱ ሰዎች እየደከሙ ሰጠሙ። እኔና ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ግን ገና ብቅ ጥልቅ እንል ነበር። እኔን የደጃች አብርሃ አሽከር ረዳኝ። በባሕሩ ዳር ቆመው የሚያዩት መኳንንቱም ሠራዊቱም ጀልባው መሰበሩን ስሉተረዱት ዋና የሚያውቁት ሁሉ በባሕሩ ላይ እየተወረወሩ ስለ ደረሱልን በጭንቅ ከሞት ተርፈን ወጣን። ስለ ወጣንም ነፍሳችን ብቻ ከሥጋችን አልተለየችም እንጂ ሰውን ለይተን ለማወቅና ለመነጋገር አንችልም ነበር።

በዚያም ጊዜ እንደ አጋጣሚ ዶክቶር ዘርቦስ የሚባሉት በፊት የግሪክ ሐኪም የነበሩት ፣ በዚያው ስለ ተገኙ የሚቻለውን ያህል በመድኀኒት አከሙኝና ፣ጥቂት በጥቂት እያልሁ የሰውን መልክ ለይቼ ለማወቅ ቻልሁ።

በማግስቱ ባልጋ ተሸክመው ወደ አማሬሳ ፣ ከአማሬሳ ወደ ሐረር አወረዱኝና በ12ኛው ቀን በጣም በጎ ሆኜ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ወጥቼ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረብሁ ።

ወይዘሮ መነንም በዚሁ በእኔ አደጋ ምክንያት ደንግጣ የአዲስ አበባ መንገዷን ትታ ወደ ሐረር ተመለሰች።

# ምዕራፍ 6

## በልጅ ኢያሱና በእኔ መካከል መቀያየም ስለተጀመረበት ምክንያት ።

የሐረርን ግዛት ከተሾምሁና ወይዘሮ መነንን ካገባሁ በኋላ ዓመት ያህል ደስ ብሎኝ ኖርሁ። ከዚያ በኋላ ግን ይህ ዓለም መቸም ደስታና ኀዘን የሚፈራረቁበት ስለ ሆነ ፣ ደስታዬ ወደ ኀዘን እየተለወጠ ይሔድ ጀመር። ምክንያቱም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

የልጅ ኢያሱ ሞግዚትና የመንግሥቱ እንደራሴ የነበሩት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ከሞቱ በኋላ ለልጅ ኢያሱ ሌላ ሞግዚት ስላልተደረገላቸው በማናቸውም ሁሉ ግንኙነታቸውንና ምክራቸውን ሁሉ የየራሳቸውን የዕለት ጥቅም ከሚፈልጉ ከተርታ ሰዎች ጋራ ስለ አደረጉ ፣ ትልልቁ መኳንንቶችና ሚኒስትሮች እየተቀየሙ ልባቸውን አርቀውባቸው ነበር።

አማካሪዎች ያደረጓቸው እነዚያም ተርታ ሰዎች ፣ ካንዳንድ የውጭ አገር ነጋዴዎች ጋራ እየተሻረኩ እንደዚህ የመሰሰ ዕቃ ከውጭ አገር እናስመጣለን ፡ እንደዚህ ያለ ዕቃ ወደ ውጭ አገር እንሰዳለንና ቀረጡን ይማሩን እያሉ በማታለል የፈቃድ ወረቀት ከመቀበል በቀር ይህን ቢሠሩ መንግሥትዎ ይጐዳል ፡ ይህን ቢሠሩ መንግሥትዎ ይጠቀማል ፡ይህን መጥፎ ሥራ ቢሠሩ ሕዝቡ ይቀየማል ብለው የሚመክሯቸው ፣ እጅግ ያነሱ እውነትን የሚፈልጉ ብቻ ነበሩ።

በዚህም ላይ ደግሞ በወሎ ተወላጅነታቸው በኩል ከነቢዩ ከመሐመድ እወለዳለሁ እያሉ ወደ ኋላ እስከ 40 ትውልድ እየቆጠሩ ከእስላሞች ጋራ በሃይማኖት የመገናኛና የመቃረቢያ ሥራ ሲሠሩ ፣ ይህ ነገር በመንግሥትዎም በራስዎም ጉዳት የሚያመጣ ነውና ይቅርብዎ ብሎ ለመምከር የሞከረ ቢኖርም አልተቀበሉትም። የቤተ መንግሥቱ የጦር መሣሪያና ሌላውም ማለፊያ ዕቃ ሁሉ ወደንጉሥ ሚካኤል እንዲሔድ ያደርጉ ጀመር።

ይህንንም ሁሉ በማድረጋቸው ሕዝቡ በሙሉ መቀየሙን እያወቁ ባንድ ስፍራ ሆነው ነገሩን በመጠባበቅ ፋንታ ፣ ሰውን በመግደል የቀናውን አገር ዱና እያደረጉ ለመደሰት ሲሉ አንድ ጊዜ ወደ ጊሚራ ፡ አንድ ጊዜ ወደ ወሎ ፡ አንድ ጊዜ ወደ አዳል መሬት ፡ አንድ ጊዜ ወደ ሐረር ፡ መዞር አበዙ። የብዙ ሕዝብ ደም ፈሰሰ። ዞረውም ሲመለሱ መኳንንቱም ሚኒስትሮቹም መከረውና ተቆጥተው አሳባቸውን ወደ መልካም ለመመለስ አለመቻላቸውን ባዩ ጊዜ ሁሉም ተስፋ ቆረጡ።

በዐፄ ምኒልክ ዘመን የነበሩት የትልልቁ መኳንንቶች ክብራቸው ተዋርዶ ማዕርጋቸው የጠፋ እንደሆነ ትንሹን በሹመት ለማሳደግ ይመችዎታል ፡ ትንንሾቹም እርስዎን ብቻ በማክበር እንዲወዱዎ እርግጥ ይሆናልና በእነርሱ ኃይል የወደዱትን ለመሥራትና ጠላትዎን ለማጥፋት ይችላሉ እያሉ ስለ መከሩዋቸውና እውነት ስለ መሰላቸው ይህንኑ ለማድረግ ይጣጣሩጀመር።

በኔም ላይ በ1907 ዓ. ም. ራሳቸው ወደ ሐረር መጥተው ከጦር ሠራዊቱ አለቆችና ከባላገሮችም ትልልቁን እየጠሩ ደጃዝማች ተፈሪ የበደላችሁ በደል እንዳለ ንገሩኝ እያሉ በቆይታ እየጠየቁና እያነጋገሩ ሲመክሩብኝ ሰንብተው ተመለሱ። ይኸም ከተጠየቁት ሰዎች ቃል የሰማሁት ነው።

ከዚህም በኋላ በግንቦት ወር 1908 ዓ. ም. እኔን ወደ አዲስ አበባ አስጠርተውኝ ነበርና ሁለት ወር ያህል ባንድነት እንደቆየን ፣ ለእኔ ሳያስታውቁኝ በሐምሌ 21 ቀን ከአዲስ አበባ ሌሊት ተነሡተው አቃቂ ላይ በባቡር ተሳፍረው ወደ ሐረር መውረዳቸውን በማግሥቱ ሰማሁ።

ወደ ሐረርም መውረዳቸውን እርግጡን ካወቅሁት በኋላ ምንም እርሳቸው ሳያስታውቁኝ ቢወርዱ ፣ የሐረር ግዛት ስሙ የኔ ነውና ፡ ሳያስታውቁኝ በመውረዳቸው የተቀየምሁ እንዳይመስል ብዬ «በሐረር የሚሰነብቱ እንደሆነ

ወደዚያው ልምጣ ፣ ወደ አዲስ አበባም ቢመለሱ ባንድነት እመለ ሳለሁ» የሚል ደብዳቤ ጽፌ ዘለቀ ከለላ በሚባል አሽከሬ እጅ ብልክላቸው «ወደ ሐረር የመጣሁበትን ምክንያት ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ እንዲያስ ታውቅህ ነግሬው ነበር ፣ አሁንም ወደ ሐረር መጥተህ ከኔ ጋራ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ሠራዊትህ ብዙ ስለ ሆነ ፣ የባቡር ኪሣራ ይበዛብሃልና እዚያው ቆይ። ብዙ ቀን የምሰነብት የሆነ እንደ ሆነ ግን እልክብሃለሁ» የሚል በሐምሌ 28 ቀን 1908 ዓ. ም. የተጻፈ ደብዳቤ ላኩልኝ።

በሐረርም ከተማ በገቡ ጊዜ የሐረርን ግዛት ከደጃዝማች ተፈሪ ወስደው ለራስዎ ያድርጉት እያሉ በመካከላችን እየገቡ ይመክሩ የነበሩ ክፉ ሰዎች ፣ አሁን ልጅ ኢያሱን ለብቻቸው ስላገኙዋቸው ቀድሞ የጀመሩት ምክር እንዲፈጸም ይጐተጉቱ ጀመር። ስለዚህም በነሐሴ 7 ቀን 1908 ዓ. ም. እንደራሴዬን ፊታውራሪ ገብሬን ጠርተው ከመንግሥት የቁጥር ጭፍራ በቀር ፣ በደጃዝማች ተፈሪ አሽከሮች እጅ ያለው የማደሪያ አገር ሁሉ እንዲያዝ ይሁን ብለው አዝዘው ወዲያውም የሐረርን ግዛት ለራሴ አድርጌ ለደጃዝማች ተፈሪ የከፋን ግዛት ሰጥቼዋለሁና እንድትነግሩት ይሁን የሚል ቃል በቴሌግራም ለቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ አሳልፈው ኖሮ ፣ የልጅ ኢያሱ ቃል ነውና በቶሎ ወደ ከፋ እንዲሔዱ ብሎ አስታወቀኝ።

ቀጥሎም ሐረርን ለእኔ የግል ግዛት አደረግሁት ፡ ከፋና ማጂን በግዛት፡ ጐራ ፈርዳን በበላይነት ሰጥቼሃለሁ ፣ የሚል በነሐሴ 10 ቀን 1908 ዓ. ም. የተጻፈ ደብዳቤ በቀጥታ ለእኔ ላኩልኝ ።

በአዲስ አበባም ያለው ትልቁም ትንሹም ይህን በሰማ ጊዜ ፣ የሐረርን ግዛት ከደጃዝማች ተፈሪ መውሰዳቸው ወደ እስላም ሃይማኖት ገብተዋልና ለእስላሙ እንዲቀርባቸው ነው እንጂ ለግዛት ብለው አይደለም እያለ በግልጥ ያወራ ነበር።

በትልቁ የዓለም ጦርነት ጊዜ አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች የኢትዮጵያ አዋሳኞች የሆኑትን እንግሊዝንና ፈረንሳይን ፣ ኢጣልያንንም በጦር ኃይል ለመርዳት ባትችሉ እንኳ ምግብ በሚሆን በሥንቅ ነገር ብትረዱ መልካም ነው ፣ እያሉ አሳባቸውን ቢያቀርቡላቸው አልሰሙም። በዚህ ፋንታ የጦር የቃል ኪዳን ጓደኞቹን ለመቃወም በኢትዮጵያ ዙሪያ ካሉት ሕዝቦች ከአዳሎችም ከሱማሌዎችም በምስጢር መላላክ ጀምረው ነበርና ይህንኑ የተላላኩትን የምስጢር ደብዳቤ አዲስ አበባ ያሉት የሦስቱ መንግሥቶች እንደራሴዎች ስላገኙት በኦፊሴል ቀርበው ለቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ አቀረቡ ተባለ።

የኢትዮጵያ መኳንንት ይህን ሁሉ ምክንያት ካገኙ በኋላ ፣ ልጅ ኢያሱን መሻር የሚያስፈልግ መሆኑን ተረድተው ነበርና ለምክሩ ባንድነት እንዳይሰበሰቡ ምስጢራቸው የሚገለጥባቸው ስለ መሰላቸው ፣የታመኑ ተላላኪ አሽከሮችን እየመረጡ በነርሱ አማካይነት ይላላኩ ጀመር። አንዳንዶቹ ግን ሌሊት በስውር ቦታ እየተገናኙ ቃል ለቃል እየተነጋገሩ ይለያዩ ነበር ። አንዳንዶቹ ደግሞ ልጅ ኢያሱ ሲሻሩ የሚተካውን አስቀድሞ አስታውቁን እያሉ ይጠይቁ ነበርና የዐፄ ምኒልክን ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱን አንግሠን የልዑል ራስ መኰንንን ልጅ ደጃዝማች ተፈሪን አልጋ ወራሽና የመንግሥቱ እንደራሴ እናደርጋለን እያሉ ሲነግሩዋቸው ፣ ደስ እያላቸው አሳባቸውን ስለ ተቀበልዋቸው ልጅ ኢያሱ መሻራቸው መልካም ነው የሚለው ወገን እየበዛ ይሔድ ጀመር።

እኔንም በምክሩ ውስጥ እንድገባ ቢጠይቁኝ ፡ከዚህ ቀደም ያባቴን ግዛት ሐረርጌን ተሾሜ ስወርድ ፣ ራስ ቢትወደድ ተሰማ ሁለታችንንም ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወደ አቡነ ማቴዎስ ቤት ወስደው ፣ ልጅ ኢያሱ እኔን ከሐረርጉ ግዛቴ ላይሽሩኝ ፣ እኔም በተንኰል አልጋቸውን ላልፈልግ በመሐላና በግዝት ቃል ኪዳን አግብተውን ነበር። አሁን ግን ልጅ ኢያሱ የመሐላውንና የግዝቱን ቃል ኪዳን አፍርሰው ፡ ከሐረርጉ ግዛቱ ሽረውኛልና በእኔ ወገን ይህ የሚበቃ ምስክር ነው። አሁን ደግሞ ወደ እስላም ሃይማኖት መግባታቸ ውን እናንተ ካስረዳችሁኝ ከናንተ የምለይበት ነገር የለም አልኳቸውና ወደፊት ለሕዝቡ ማስረጃ እንዲሆን የጻፉትን ሁሉ እያነበቡ አስረዱኝ።

# ምዕራፍ 7

## ልጅ ኢያሱ ከተሻሩበት ከመስከረም 17 ቀን 1909 ዓ. ም. አንሥቶ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ዘውድ እስከ ጫኑበት እስከ የካቲት 4 ቀን 1909 ዓ. ም.

ልጅ ኢያሱ በድሬዳዋና በሐረር በጅጅጋም ከተሞች እየተመላለሱ አዳሎችንና ሱማሌዎችን እየሰበሰቡ ሽልማት እየሸለሙ ፣ መሣሪያ እየሰጡ በሃይማኖት ወገናችሁ ነኝ እያሉ እየሰበኩ ተቀምጠው ሳሉ ፣ እስላሞች ክርስቲያንም እስላምም አይደሉ እያሉ ሲያሽሟጥጡ ይሰማ ነበር። በመስከረም 17 ቀን 1909 ዓመተ ምሕረት በትልቁ የመስቀል በዓል ቀን መኳንንቱ ከነሥራዊቱሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ከነካህናቱ ፡ በቤተ መንግሥቱ ግቢ በተዘጋጀው ስፍራ እንዲሰበሰቡ ተደረገና ሁሉም እየመጡ በየማዕርጋቸው በተቀመጡ ጊዜ ፣ ተዘጋጅቶ የቆየው የልጅ ኢያሱ ወንጀል ከዚህ ቀጥሎያለው ተነበበ።

«አባቶቻችን ስለ ሃይማኖታቸው ከእስላሞች ጋራ እየተዋጉ ደማቸውን እያፈሰሱ እስካሁን ጠብቀው ያቆዩንን የክርስቲያን ሃይማኖት ፣ ልጅ ኢያሱ በእስላም ሃይማኖት ለውጠው በመካከላችን ሁከት አስነሥተው ፣ እኛን እርስ በርሳችን ለማፋጀት ወደ እስላም ሃይማኖት ተለውጠዋልና ከእንግዲህ ወዲህ ለርሳቸው አንገዛም ፣ በክርስቲያን ንጉሥ ዙፋን ላይ የእስላም ንጉሥ አናስቀምጥበትም ፣ ወደ እስላም ሃይማኖት ለመለወጣቸው ብዙ ማስረጃ አለን።

1ኛ፣ ቁራን ይፈቅድልኛል ብለው አራት ሚስት አግብተዋል። ከነዚሁም አንዲቱ የጅማ ባላባት ያባ ጅፋር ልጅ ናት ፡ ሁለተኛይቱ የሐረር ባላባት የሐጅ አብዱላሂ ልጅ ናት ፡ ሦስተኛዋ የአዳል ባላባት የአቡበከር ልጅ ናት ፡ አራተኛዋ ግን አባቷ ደጃች ጆቴ ክርስትና ተነሥቶ ልጁንም ክርስትና አስነሥቶ ፣ በክርስትና ስሟ አስካለ ማርያም እየተባለች ስትኖር ፡ በኋላ እሳቸው አስልመው ሞሚና ብለው የእስላም ሴት ስም ያወጡላት የደጃች ጆቴ ልጅናት።

2ኛ፣ በመንግሥቱ ገንዘብ በጅጅጋ መስጊድ እያሠሩ ለእስላሞች ሰጥተዋል።

3ኛ ፡ በዚያ ዘመን ለውጭ አገር ቆንሲል በአዲስ አበባ ለሚኖረው ለመሐዘር ቤ የረመዳን በዓል ሲያከብር የመስቀል ምልክት በሚደረግበት ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ተብሎ በሜጸፍበት በኢትዮጵያ ባንዲራችን ላይ ላኢላ ሂይለላ መሐመድ ረሱል አላህ የሚል ቃል አስጽፈው ልከውለታል።

4ኛ ፡ የሱማሌ እስላም ግልድም እያገለደሙ ፡ የእስላም ጥምጥም እየጠመጠሙ ፡የእስላም መቁጠሪያ እየያዙ ፡ በመስጊድ ሲሰግዱ ታይተዋል ።

5ኛ ፡ ቁራኑን ባማርኛ ፊደል አስገልብጠው እያነበቡ ሲጸልዩ ታይተዋል።

6ኛ ፡ በልዩ ዘበኞቻቸው ቆብ ላይ ላኢላ ሂይለላ የሚል ምልክት አስጠልፈዋል።

7ኛ ፡ በሐረር ልዑል ራስ መኰንን ቤተ ክርስቲያን ሠርተው በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ያለውን ቦታ ለእስላሞች ለውጡን እየሰጡ ለካህናት መኖሪያ ባደረጉት በ32 ዓመት ካህናቱን እያስነሡ ለእስላሞች መልሰውላቸዋል።

8ኛ፣ ሴት ልጅ ቢወልዱ የእስላም ሃይማኖት እየተማረች እንድታድግ ብለው ለእስላሚቱ ለመዳም ሐናፊ አሳድጊልኝ ብለው ሰጥተዋታል ።

9ኛ ፡ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ተያይዞ የመጣውን የዳግማዊ ምኒል ክን ትውልድ ንቀው ከነቢዩ ከመሐመድ ወገን እወለዳለሁ እያሉ ትልልቆቹን የእስላም ሼሆች እየሰበሰቡ ትውልዳቸውን እየቆጠሩ ሲያስረዱ ይውላሉ።

10ኛ፣ አልጋውን ያወረሱዋቸው ትልቁ ንጉሣችን ዐፄ ምኒልክ በሞቱበት ቀን ልቅሶ እንደ ማልቀስና እንደ ማስለቀስ በፈረስ ተቀምጠው ጃን ሜዳ ወጥተው ጉግስ ሲጫወቱ ውለዋል። ሬሳቸውም በማዕርግ እንዳይቀበር ከልክለው እስካሁን ተቀምጧል። ሌላም ይህን የመሰለ ብዙ ማስረጃ አለን።



ከቀኝ ወደ ግራ ልዑል መኰንን፣ ልዕልት ፀሐይ፣ ልዕልት ወለተ ገብርኤል፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ራስ ደስታ፣ ልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ ግርማዊት እቴጌ መነን፣ ልዑል አልጋ ወራሽ፣ ልዕልት ዘነበ ወርቅ፣ በእቴጌ ግራና ቀኝ ሕፃናቱ ዓይድዓ ደስታና አምኃ ደስታ።



ከግራ ወደ ቀኝ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ(ንጉሥ) ፣ ንጉሥ ሚካኤል፣ ልጅ ኢያሱ



ዳግማዊ ምኒልክ ባሉበት ከቆሙት ውስጥ ራስ ጉግሣ ወሌ፣ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ደጃች ተፈሪ(ቀ.ኃ.ሥ) ደጃች ናደው፣ ደጃች ብሩ፣ ቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴ መገኖ፣ በጅሮንድ ዘለቀ መታፈሪያ

ስለዚህ እርሳቸውን ሽረን የዐፄ ምኒልክን ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱን አንግሠናል። የልዑል ራስ መኰንንን ልጅ ደጃዝማች ተፈሪን ራስ ብለን አልጋ ወራሽና የመንግሥቱ እንደራሴ አድርገናል ። »

ይህ ቃል ተነቦ ሲጨረስ በዚያ የተሰበሰበው ሁሉ ባንድ ቃል ሆኖ ወደን ተቀብለናልና ይበጅ ያድርግ ብሎ ተናገረ። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ፡ «ልጅ ኢያሱ የክርስቲያንን ሃይማኖት ነቅፎ ወደ እስላም ሃይማኖት ስለ ገባ አውግዘነዋል እናንተም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጸንታችሁ የመንግሥታችሁን ነፃነት እየጠበቃችሁ ከመኖር በቀር እንግዲህ ልጅ ኢያሱን የተከተላችሁና ለርሱ የተገዛችሁ እንደሆነ ውጉዛን ናችሁ» ብለው የመጨረሻ ቃል ተናገሩ።

ከዚያም በኋላ ዙፋኑና ዘውዱ ለንግሥት ዘውዲቱ ፡ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነቱ ለእኔ መሆኑ በዐዋጅ ተነገረና የዐዋጁ ቃል በሙሉ ኢትዮጵያ ላሉት ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለየአገረ ገዥዎቹም ሁሉ በስልክ አለፈላቸው።

ንጉሥ ሚካኤል ከእስላምነት ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት ከተመለሱ 40 ዓመት ያህል ስለ ሆነ ልጃቸው ወደ እስላም ሃይማኖት በመግባታቸው ማዘናቸውን ከመኳንንቱ ላንዳንዱ ይናገሩ ነበርና አሁን በልጃቸው መሻር ከእኛ ጋራ ሳይተባበሩ አይቀሩም በማለት የዐዋጁ ቃል አለፈላቸው።

ልጅ ኢያሱም በሐረር ከተማ ሳሉ የርሳቸውን መሻር ፣ የንግሥት ዘውዲቱን መንገሥ ፡ የእኔን አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆን በሰሙ ጊዜ ሱማሌዎቹንና አዳሎቹን ሰብስበው በከተማው ሽብር እንዲነሣ አደረጉና ክርስቲያኑና እስላሙ ወገን ለይቶ ስለ ተጋደለ ፣ ከሁለቱም ወገን 300 ያህል ሰዎች ሞቱ። ደጃዝማች ባልቻና አሁን ራስ የተባለው ቀኛዝማች እምሩ ለጊዜው በዚያው በሐረር ስለ ተገኙ ተይዘው ነበርና ደጃዝማች ባልቻን ከእኔ እንዳትለይ ብለው አስምለው ለቀቋቸው። ቀኛዝማች እምሩን ግን አስረው አስቀመጡት።

በሐረርም የነበሩት የእኔ መኳንንቶችና አሽከሮች ሁሉ ከጥቂቶች በቀር ከልጅ ኢያሱ እየከዱ ቀርሳ ወደሚባለው አውራጃ እየወጡ ተሰልፈው ይጠባበቁ ጀመር። ቀኛዝማች እምሩም ከታሰረበት አምልጦ ወጣ።

ከዚህም በኋላ ወደ እሳቸው የሆነውን ፡ከቁጥር ጦር ጭፍራ ሰብስበው ዶጃዝማች ጉግሣ አልዩ የሚባለውን የጦር አበጋዝ አድርገው ፣ ወደ አዋሽ መስደዳቸው ስለ ተሰማ ፣ ደጃዝማች አያሌው ብሩን የጦር አበጋዝ አድርገን ፡ ደጃች ኃይለ ማርያም ለማን ፡ ደጃች አድማሱ ብሩን ፡ ልጅ አበበ ዳምጠውን ፡ ልጅ ደስታ ዳምጠውን ፡ ፊታውራሪ መኩሪያ ገርማሜን ፡ ሌሎችንም የቁጥር ወታደሮች ጨምረን ልከን ነበርና ፡ ምኤሶ በሚባለው ጣቢያ ላይ ተጋጥመው በመስከረም 23 ቀን ደጃዝማች ጉግሣ አልዩን ድል አደረጉት። እርሱ ራሱ ግን በባቡር አምልጦ ድሬዳዋ ገባ።

ልጅ ኢያሱም በሐረርና ባውራጃዋ ሁሉ ያለው ክርስቲያኑ ፡ እስላሙም እንደ ከዳቸው ባዩ ጊዜ ወደ ድሬዳዋ ወርደው በግምጃ ቤት ከተገኘው ገንዘብ የሚችሉትን ያህል ይዘው ፡ የማይችሉትን በሙሴ ኤድልቢ እጅ ወደ ጅቡቲ ልከው ወደ አባታቸው ግዛት ወደ ወሎ ለመሔድ በአዳል በረሃተጓዙ።

ንጉሥ ሚካኤል ግን ልጅዎ ወደ እስላም ሃይማኖት ስለ ገቡ እሳቸውን ሽረን ንግሥትዘውዲቱን አንግሠን ፤ልዑል ተፈሪ መኰንንን አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ አድርገናል የሚል የስልክ ቃል ተላልፎላቸው ነበርና ያንን ባዩ ጊዜ ቢሆንስ ልጄን እኔ መክሬና ተቆጥቼ በክርስቲያን ሃይማኖት እንዲጸና አደርገው ነበር እንጂ አያቱ ዐፄ ምኒልክ የሰጡትን አልጋ ሲወስዱበት ዝም ብዬ አላይም ብለው የጦር ሠራዊታቸውን በዐዋጅ አስከትተው ወደ ሸዋ መገሥገሣቸው ተሰማና መሳፍንቱና መኳንንቱ ሚኒስትሮችም ባንድነት ሆነው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጽፈው ላኩላቸው።

ይድረስ ከንጉሥ ሜካኤል። ዘሥልጣኑ ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ ንጉሠ ጽዮን።

ልጅዎ ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽ ከሆኑ ጀምሮ እስከ ዛሬ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ የልጅነት ሥራ እንደ ሆነ ንጉሥም ያውቁታል። እኛም መክረን ተቆጥተን እናሳድጋለን ብለን ብናስብ ፣ ባንድ ስፍራ የማይቀመጡ ስለ ሆነብን ጊዜ አላገኘንም። አንዳንድ ጊዜም እያገኘን ብንመክራቸው አልተቀበሉንም። እኛም ምናልባት ከነገ ሣልስት የመንግሥታቸውን ጥቅም ፣የራሳቸውን ማዕርግና ክብር እያወቁ ይህን የልጅነት ሥራቸውን ይተዉት ይሆናል በማለት ሰውነታቸው እንዳይሰቀቅ ታግሠን ብንጠብቃቸው የልጅነት ሥራ መሥራታቸው አልበቃ ብሏቸው፣ ከአብርሃ ወአጽብሓ ፡ ከከሣቴ ብርሃን ሰላማ ጀምሮ አንድ ሺ. 600 ዓመት ያህል በክርስትናዋ ጸንታ በምትኖረው ባገራችን በኢትዮጵያ የእስላም ሃይማኖት ለማቆም ይጣጣሩ ጀመር።

ባለፈው ዓመት ወደ ወሎ በመጡ ጊዜ ከእስላሞች ጋራ ሲሠሩት የከረሙትን ሥራ ሁሉ ንጉሥ ራስዎ ያውቁታል። ደግሞም ለንጉሥ ሳይሆንልዎ ቢቀር ነው እንጂ የልጅ ኢያሱ ልብ ከክርስቲያን ሃይማኖት መናወጡን አይተው እባክህ ልጄ ይህን አሳብህን ተው እያሉ መምከርዎንና መቆጣትዎን ሰምተናል። አሁንም ለእኛ ሳያስታውቁን በስውር ወደ ሐረር ወርደው ከእስላሞች ጋራ የሠሩትን ሥራ ሁሉ የሚያስረዱ ፎቶግራፋቸውን ከዚህ ደብዳቤ ጋራ ልከንልዎታል።

ይህንንም ሁሉ ታግሠን ሁላችንም ባንድነት ሆነን ሊቀ ጳጳሱንና እጨጌውን ጨምረን ለማናቸውም ቢሆን ለዕንቁጣጣሽ (ላዲሱ ዓመት) ወደ አዲስ አበባ ይምጡልን ብለን ደብዳቤ ጽፈን ብንልክላቸው ሳይመጡ ቀሩ። እንደዚህም አድርገን መጨነቃችን የክርስቲያን ሃይማኖት እንዳትጠፋ ፡ በዚህም ምክንያት የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስስ አገራችንም ለባዕድ እንዳታልፍ ብለን ነውና ንጉሥም በዚህ ነገር በጣም ያስቡበት። ሕዝቡም የዚህን ነገር እርግጡን ሳያገኘው እንዳልተነሣ የታወቀ ነው። ይልቁንም በንጉሥ ሚካኤል ልጅ በልጅ ኢያሱ ምክንያት በኢትዮጵያ የክርስቲያን ሃይማኖት ጠፋ ፡ የእስላም ሃይማኖት ሰፋ ተብሎ በታሪክ ተጽፎ ለኋላ ትውልድ መቆየቱ አይቀርምና የርስዎም ስም አብሮ መጥፋቱን እናሳስብዎታለን።

ይህንም ሁሉ ለንጉሥ መጻፋችን ዐፄ ምኒልክን እኛንም ሁሉ እንዲወዱ ለክርስቲያንም ሃይማኖት እንዲቆረቆሩ እናውቃለንና አሳብዎ ከአሳባችን ሳይለይ ባንድነት ለሃይማኖታችንና ለመንግሥታችን ጥቅም የሚሆን እንድንሠራ በማለት ነው እንጂ በተለየ ንጉሥ እንዲቀየሙ ልጅ ኢያሱ እንዲጐዱ ብለን ያደረግነው አይደለም ።

ንጉሥ ሚካኤል ይህ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ምንም ቢሆን አልመለስም ብለው ወደ ፊት መገሥገሣቸውን መልክተኞቻችን በስልክ ስላስታወቁን ለጊዜው በአዲስ አበባ የተገኘውን የጦር ሠራዊት በራስ ሉል ሰገድ አበጋዝነት አድርገን አስቀድመን ሰደናቸው ነበርና ቶራ መስክ ከሚባለው ከሸዋ አውራጃ ሲደርሱ ከንጉሥ ሚካኤል የጦር ፊታውራሪ ጋራ በድንገት ተጋጥመው በጥቅምት 7 ቀን ማክሰኞ ራስ ሉል ሰገድና ደጃች ተሰማ ገዝሙ ሊቀ መኳስ አበበ አጥናፍ ሰገድ ፡ ፊታውራሪ ዘውዴ ጐበና ፡ አሳላፊ አቤ ፡ ቀኛዝማች ድልነሣሁ ፡ አሳላፊ ድልነሜ ፡ አቶ ሸዋዬ ሌሎችም የጦር አለቆች በጦርነቱ ውስጥ መሞታቸውን በስልክ ሰማን ።

ከዚያም በፊት የጦር ሚኒስትራችን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በጥቅምት 3 ቀን ከአዲስ አበባ ተነሥተው ተጉዘው ኮረማሽ ሲደርሱ ፣ በኮረማሽ ካለው የጦር መሣሪያ ለየወታደሩ ሲያካፍሉ እንዲሰነብቱ አድርገን ነበርና እኛ በጥቅምት 9 ቀን ተነሣን። ከያውራጃውም የሚመጣው የጦር ሠራዊት እንደተቻለ በግሥጋሤ እንዲደርስ ለሠራዊቱ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በዐዋጅ አስታወቅነው።

# ያዋጅ ቃል ።

## «ያገሬ የኢትዮጵያ ሰው ስማ

ልጅ ኢያሱ ከዐፄ ምኒልክ ፈቃድ ወጥተው ክፉ ሥራ እንዳይሠሩ የረገሟቸውን እርግማን ጥሰው የእስላም ትውልዳቸውን እየቆጠሩ ከእስላሞች ጋራ በመስጊድ እየሰገዱ ወደ እስላም ሃይማኖት መግባታቸውን በግልጥ ስለአሳዩ ማስተዳደርም ስላልቻሉ እርሳቸውን ሽረን ንግሥት ዘውዲቱን በአባታቸው አልጋ አስቀምጠን አነገሥን።

ንጉሥ ሚካኤልም የልጃቸውን መስለም ያውቃሉና ከእኛ ጋራ ሆነው ለክርስቲያን ሃይማኖት ደማቸውን ያፈስሳሉ እያልን ስናስብ እንዲያውም ለእስላም ንጉሥ ካልተገዛችሁ ብለው ሊወጉን ከወሎ በግሥጋሤ መጥተዋልና ወንድ ልጅ የሆንህ ተከተለኝ ። »

ይህንም ዐዋጅ ካናገርን በኋላ ወደ ፊት ገሠገሥን። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሰው እርስ በርሱ ደም መፋሰሱ በጣም የሚያሳዝን ስለ ሆነ ከደብረ ሊባኖስና ከዝቋላ ገዳማት ፡ ከየአድባራቱም ሁሉ መነኩሳትና መምህራን እየተመረጡ መጥተው መስቀል እየያዙ ንጉሥ ሚካኤል ጦርነት ሳያደርጉ ወደ ወሎ እንዲመለሱ እንዲለምኗቸው አደረግሁ። ንጉሥ ሚካኤል ግን እንኳን ሊመለሱና ለማስታረቅ የተላኩትን መነኩሳት እየያዙ አሰርዋቸው የሚል የስልክ ቃል ስለ መጣልን ለመዋጋት ቁርጥ አሳብ ማድረጋቸው የታወቀና የተገለጠ መሆኑን ተረዳነው።

በጥቅምት 15 ቀን ከኮረማሽ ተነሡተን ተጉዘን ነበርና በጥቅምት 16 ቀን ሰገሌ በሚባለው በጠራ ወረዳ ሜዳ የእኛና የንጉሥ ሚካኤል ሰፈር ግንባር ለግንባር ተያይቶ አደረ ።

በጥቅምት 17 ቀን ዓርብ ከሌሊቱ በ ሰዓት ጀምረው የጦር አለቆቻቸውን በቀኝና በግራ አሰልፈው እርሳቸው በማሃል ሆነው መጥተው ጧት ሲነጋ ቃፊር ሆነው ባደሩት በመድፈኞቻችን ላይ አደጋ ጥለው ተኩስ ጀመሩ። ከዚህም በኋላ የጦር ሚኒስትራችን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በግንባርራስ ካሣ በንጉሥ ሚካኤል ጀርባ ፡ የቀሩት ራሶችና ደጃዝማቾች በቀኝና በግራ እንዲሰለፉ አድርገን ፡ እኛ ለጦር ሠራዊቱ ሁሉ ደጀን ሆነን ተጋጠምናቸው።

ከጧቱም ጀምሮ 5 ሰዓት ያህል እንደ ተዋጋን የሸዋ የጦር ሠራዊት ፍየል እንዳየ ነብር ፡ ላም እንዳየ አንበሳ እየዘለለ ጐራዴውን እየመዘዘ እጅ ለእጅ ተያይዞ በሰልፉ ውስጥ በገባ ጊዜ ንጉሥ ሚካኤል ድል ሆነው ተማረኩ። ከሠራዊታቸውም የሞተው ሞቶ ፡ የተማረከው ተማርኮ የተረፈው እየሸሸ ወደ ወሎ ተመለሰ።

ልጅ ኢያሱም በአዳል መሬት ዞረው ለጦርነቱ ለመድረስ ሲገሠግሥ አንኮበር በደረሱ ጊዜ ንጉሥ ሚካኤል ድል መሆናቸውን ሰምተው ወደ ኋላቸው ተመልሰው በአዳል መሬት ዞረው ወደ ወሎ መሬትገቡ።

ንጉሥ ሚካኤል ግን ምንም ተማረኩ ቢባል ለስሙ ያህል ነው እንጂ ማናቸውም የውርደት ነገር እንዳያገኛቸው ለክብራቸው የሚገባውን ሁሉ አድርገንላቸው ነበር። ለሌሎቹም ምርኮኞች ከወሎ ጋራ ሌላ ጠብ እንደሌለን ሁላችንም ያንዲት የኢትዮጵያ ተወላጆች መሆናችንን እያስረዳን ከተለቀቁ በኋላ ባዋጅ ወደ ሀገራቸው ወደ ወሎ እንዲመለሱ አደረግን ።

የድሉንም ነገር በስልክ ወደ አዲስ አበባ ስላስታወቅን ከንግሥት ዘውዲቱ ጀምሮ የከተማው ሕዝብ በሙሉ ታላቅ ደስታ አደረገ። ወደ አዲስ አበባም በተመለስን ጊዜ በጥቅምት 23 ቀን ኀሙስ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ በጃን ሜዳ በትልቁ አጅባር ድንኳን ሆነው የከተማው ሕዝብ በሙሉ ተሰብስቦ በታላቅ ሰልፍ በእልልታና በደስታ ተቀበሉን። ።

# ምዕራፍ 8

## የንግሥት ዘውዲቱ የዘውድ በዓል ከተደረገበት አንሥቶ ልጅ ኢያሱ ወሎ ላይ ድል ሆነው እስከ ሸሹ ድረስ ።

የንግሥት ዘውዲቱ የዘውድ በዓል በየካቲት 4 ቀን 1909 ዓመተ ምሕረት እንዲሆን ነገሩ በምክር ቤት ስለ ተጨረሰ ለዘውዱ በዓል አከባበር የሚያስፈልገው ሁሉ እንዲሰናዳ ለየሹሞቹ ሁሉ ትእዛዝ ማሳለፍ ጀመርን ።

ለዘውዱም በዓል የበጌምድሩና የስሜኑ ገዥ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፡የሰላሌና የቦረና የደራው ገዥ ራስ ካሣ ፡ የጎጃሙ ገዥ ራስ ኃይሉ ፡ የትግሬው ገዥ ራስ ሥዩም ፡ ሌሎችም የትልልቅ አውራጆች ገዥዎች ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተላከባቸው። እነዚህን ለመጥራት በዚያ ጊዜ የነበረው የፖለቲካ ዳመና ከባድ ነበር።

ከውጭ አገርም በኢትዮጵያ አዋሳኝ ያሉት የእንግሊዝ ሱዳንና የእንግሊዝ ሱማሌ ገዥዎች ፡ የፈረንሳይ ሱማሌ አገረ ገዥ እንዲመጡ የክብር ጥሪ ተላከላቸው።

እነዚህም የተጠሩት ሁሉ በመጡ ጊዜ በየካቲት 4 ቀን በዕለተ እሑድ በትልቁ ደብር በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ ጫኑ።

ከዚህም በኋላ እንደ ሥርዓተ ንግሥ ሕግ ፣ ንግሥት ዘውዲቱ በአባታቸው ዙፋን ተቀምጠው መንገሣቸውን ፣ እኔም አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆኔ በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ በተሰበሰበው ፊት እንደገና በዐዋጅ ተነገረ።

ከስምንት ቀን በኋላም በየካቲት 11 ቀን ራስ ወልደ ጊዮርጊስ በንግሥት ዘውዲቱ እጅ ዘውድ ተጭኖላቸው የጎንደር ንጉሥ ተባሉ። ስለ ንጉሥነታቸውም የትግሬ ግዛት በበላይነት ተጨመረላቸው።


ያገሩንም ሹም ሽር እንደገና እያደላደልን ፡ ለራስ ወሌ የቀድሞ ግዛታቸውን የጁን ፤ለልጃቸው ለራስ ጉግሣ ሳይንትን ፡ ለራስ አባተ የንጉሥ ሚካኤል ግዛት የነበረውን ሰባት ቤት ወሎን ሰጠናቸው።

ልጅ ኢያሱም የተደረገውን ሹም ሽር በሰሙ ጊዜ ከመቅደላ ወርደው ወደ የጁ ሲገሠግሡ ከራስ ወሌ ልጅ ከደጃዝማች አመዴ ጋራ ተጋጥመው ኖሮ ድል አድርገው ማረኩት የሚል ወሬ ስለ ደረሰልን ፡ እንግዲህ ልጅ ኢያሱ ካልተያዙ ሰላምና ጸጥታ አለመገኘቱን ዐውቀን በጦር ሚኒስትራችን በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አበጋዝነት ብዙ የጦር ሠራዊት ወደ ወሎ ሒዶ ልጅ ኢያሱን እየተፈላለጉ እንዲይዙ አደረግን ።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስም ወሎ በደረሱ ጊዜ ልጅ ኢያሱ ወዲያና ወዲህ እየተዛወሩ የጦር ሠራዊት መሰብሰባቸውን ሰምተው የደሴን ከተማ ይዘው ይጠብቋቸው ጀመር ። -ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋራ ካሉት የጦር አለቆች ዋኖቹ ራስ አባተና ራስ ካሣ ነበሩ። ከነዚህም ጋራ ፡ ደጃዝማች ከበደ ተሰማና ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ለማ ፡ ደጃዝማች መኩሪያ ገርማሜ ሌሎችምየጦር አበጋዞች ነበሩ።

ልጅ ኢያሱም ብዙ የጦር ሠራዊት ከሰበሰቡ በኋላ ያባታቸውን የጦር አበጋዞች ራስ ይመርን ዋና ጠቅላይ የጦር አበጋዝ ፡ ፊታውራሪ ሥራህ ብዙን ምክትል የጦር አበጋዝ አድርገው በነሐሴ 21 ቀን 1909 ዓመተ ምሕረት በማለዳ አደጋ ጥለው ጦርነት ገጠሙና ብርቱ ውጊያ ሆነ። ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስም ከካባቸው ሳይወጡ ጠንክረው ስለ መከቱ ድል አደረጉና ራስ ይመር ተማረከ። ፊታውራሪ ሥራህ ብዙ ግን በጦርነቱ ውስጥ ሞተ። ልጅ ኢያሱም የራስ ይመርን መማረክ ፡ የሥራህ ብዙን መሞት በሰሙ ጊዜ ጥቂት ራሳቸውን ሆነው በፈረስ ጋልበው አመለጡና ወደ ባላገር ገቡ። ይኸውም የድሉ ነገር ዕለቱን በስልክ ተላከና በአዲስ አበባ ከተማ ትልቅ ደስታ ተደረገ። ነገር ግን ይህ ዓለም ደስታና ኀዘን የተቀላቀለበት ስለ ሆነ ፣ ራስ አባተ ታመው ሰንብተው ሳሉ በጦርነቱ ቀን በድንኳን ተኝቼ

አልውልም ብለው ተነሡተው ሲዋጉ ውለው ነበርና በዚሁ ምክንያት በሽታው ስለ ጠነከረባቸው ፣ ጥቅምት 6 ቀን 1910 ዓመተ ምሕረት ዐረፉ። መርዶዋቸውም ደረሰልንና ትልቅ ኀዘን ሆነብን። ሬሳቸውም ወደ ደብረ ሊባኖስ እንዲመጣ አድርገን እኛው ራሳችን ወርደን በታላቅ ክብር አስቀበርናቸው። ለመታሰቢያም እንዲሆን ጐራዴያቸውን ከሬሳቸው ጋራ እንዲቀበር አደረግን ።



# ምዕራፍ 9

## ሚኒስትሮች ስለ መሻራቸውና በአዲስ አበባ የቸነፈር (ግሪፕ) በሽታ ስለ መግባቱ ።

ሚኒስትሮች ከተሾሙ ዐሥር ዓመት ያህል ሆኗቸው ነበር ። ። ቢሆንም የመንግሥቱን ሥራ በትክክል ለመሥራት ባለመትጋታቸውና ሥራው ሁሉ እየተበላሸ በመሔዱ ሕዝቡ ሁሉ በጣም ስለ ተናደደ ፣ ባንድነት በሜራ ተነሡቶ ሚኒስትሮች ይለወጡልን ብሎ አመለከተ። እኛም ሚኒስትሮችን ለመሾምና ለመሻር የሕዝብ ሥልጣን በመግባቱ ነገሩ ከዚህ ቀድሞ ያልተለመደ ስለሆነ አይሻሩም በማለት እስከሚቻለን ተከራከረንላቸው ነበር። ነገሩን ለማብረድ ስንል ለጊዜው ሚኒስትሮች እንዲነሡ አደረግን። አዲሶችም ሚኒስትሮች እስቲመረጡና እስቲሾሙ ሥራው ሁሉ በእኛ አላፊነት ብቻ ይሥራ ነበርና ብዙ ድካም ሆኖብን ነበር።

ከዚህም በኋላ ከኅዳር 1 ቀን ጀምሮ እስከ ኅዳር 30 ቀን በአዲስ አበባና በሌላውም በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ የቸነፈር (የግሪፕ) በሽታ ተነሡቶ ነበርና በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከዐሥር ሺ የሚበዙ ሰዎች ሞቱ። እኔ ግን በብርቱ ከታመምሁ በኋላ በእግዚአብሔርቸርነት ከሞት ተረፍሁ ።

በአውሮጳ ተቀስቅሶ የነበረው ትልቁ ጦርነት በዚህ ዓመት አልቆ በፈረንሳይና በእንግሊዝ ፣ በኢጣልያና በሌሎችም መንግሥታት የጦር ጓደኝነት ጀርመንና ቱርክ ድል ሆነው ነበር። እኛም ለጎረቤቶቻችን ሥንቅ በማቀበል እንኳ እንዳንረዳ ልጅ ኢያሱ በዚያ ጊዜ አልፈቀዱም ነበርና ምንም ገለልተኛ ሆነን ብንቆይ ድል አድራጊዎቹ ጎረቤቶቻችን ስለ ሆኑ ለቁስለኞች እርዳታ ገንዘብ እየጨመርን እንኳን ደስ አላችሁ የሚሉ መልክተኞች ለመላክ ቁርጥ አሳብ አድርገን ፡ ለዚሁም ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሰዎች ተመረጡ።

- ወደ ፈረንሳይ መንግሥት ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል በሻህ ዋና ሆነው፣ በውስጣቸው ደጃዝማች ሽበሺ. በያንና ነጋድራስ ዘውገ ።
- ወደ እንግሊዝና ወደ አሜሪካ ዩናይትድ እስቴት ፡ ደጃዝማች ናደው ዋና ሆነው በውስጣቸው አቶ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና ከንቲባ ገብሩ።
- ወደ ኢጣልያ መንግሥት ደጃዝማች ጌታቸው አባተ ዋና ሆኖ ፣ በውስጡ ፊታውራሪ መንገሻ ውቤና አዛዥ ደገፌ ናቸው።

እነዚህም በሚያዝያ ወር ከአዲስ አበባ ሔደው የተላኩበትን ጉዳይ እየፈጸሙ ተመለሱ።

# ምዕራፍ 10

## ልጅ ኢያሱ ትግሬ ላይ ተገኝተው ስለ መያዛቸው ።

ልጅ ኢያሱ ደሴ ላይ ከጦር ሚኒስትራችን ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋራ ተዋግተው ድል ሆነው አምልጠው ነበርና ወደ አውሳ በረሃ ገብተው ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ ሁለት ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ከበረሃው ወጥተው ቅብፅያ ወደሚባለው ስፍራ መግባታቸው ተሰማ ።

የትግሬው ገዥ ራስ ሥዩምም ለጊዜው አስታርቃለሁ ብለው ሞክረው ነበር ። ። ነገር ግን የመንግሥትና የዘውድ ነገር አንተ ይቅርብህ እገሌ ይውሰደው ለማለት በጣም የሚያስቸግር ስለ ሆነ ፣ የዕርቁን ነገር ትተው ከግዛታቸው ወጥተው እንዲሔዱ አደረጓቸው። ከዚህም በኋላ ከራስ ሥዩም ግዛት ወጥተው በራስ ጉግሣ አርአያ ግዛት ገብተው ኖሮ ፣ ይህን በሰማን ጊዜ ፈልገው እንዲይዙ ብለን ወደ ራስ ጉግሣ ትእዛዝ አሳለፍን ።

ራስ ጉግሣም መፈለጉን እፈልጋለሁ ፣ ነገር ግን ከራስ ሥዩም ጋራ የምስጢር ንግግር እንዳላቸው ፡ ምናልባት መጥተው ነጥቀው እንዳይወስዷቸው እፈራለሁና ዘበኛ የሚሆኑ ሰዎች ይምጡልኝ ብለው ስለ አመለከቱ ፡በኋላ ራስ የተባለው ልጅ ደስታ ዳምጠው የውስጥ ዘበኛ ፡ ደጃዝማች ጌታቸውና ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ፊታውራሪ ዋቄ ፡ ደጃች ወሰኔትርፌ፡ደጃች ወልደ ሥላሴ ፡ ከራስ ጉግሣ ጋራ የውጭ ዘበኞች ሆነው ልጅ ኢያሱን ይዘው እንዲመጡ ወደ ትግሬ ሰደድናቸው።

እኛም ደሴ ላይ ሆነን ፣ የቀኙንም የግራውንም ለማዳመጥ በሚያዝያ 27 ቀን 1913 ዓመተ ምሕረት የአዳም ኅሙስ ዕለት ከአዲስ አበባ ተነሡተን ወደ ደሴ ተጓዝን። የጎጃሙ ገዥ ራስ ኃይሉም ተጠርተው ነበርና ደሴ ላይ በሰልፍ ገብተው ተገናኙን። ራስ ጉግሣም ልጅ ኢያሱን ፈልገው መያዛቸውን ስላስታወቁን ፣ በቶሎ ይዘው ወደ ደሴ እንዲመጡ ትእዛዝ አሳልፈንላቸው ነበርና አምጥተው አስረከቡ። ፡

ራስ ሥዩምም ተጠርተው መጥተው ነበርና ልጅ ኢያሱን ሳይዙ በመሰደዳቸው መቀጫ እንዲሆንባቸው ፣ የአድዋ ግዛታቸውን ሽረን ለደጃዝምች ገብረ ሥላሴ ሰጠንባቸው። ራስ ጉግሣም ልጅ ኢያሱን ይዘው ስለ አመጡ፣ በቀድሞ ግዛታቸው ላይ ሌላ ግዛት ጨምረን ሰጥተን ፣ ሹም ሽሩን አደላድለን ፡ ራስ ኃይሉም ወደ ጎጃም እንዲመለሱ አሰናብተን ፡ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰን በሐምሌ 12 ቀን ገባን። ልጅ ኢያሱንም ወደ ሰላሌ ከተማ ወደ ፍቼ ልከን በታማኞችን በራስ ካሣ እጅ እየተጠበቁ እንዲቀመጡ አደረግን።

ልጅ ኢያሱ ከተሻሩበት ከ1909 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ አራት ዓመት ሳይያዙ ስለ ቆዩ ፣ አንዳንድ ወስላቶች ሁከት ለማድረግ አላረፉም ነበር። ልጅ ኢያሱ ከተያዙ ወዲህ ግን ሰላምና ጸጥታ እየሆነ በመሔዱ ላገሩ ትልቅ ጥቅም ሆነ።

# ምዕራፍ 11

## በንግሥት ዘውዲቱና በእኔ መካከል እየገቡ ለመንግሥቱ ሥራ መሰናከል ሆነው ስለ ነበሩ ሰዎች ።

በንግሥት ዘውዲቱና በአባቴ በልዑል ራስ መኰንን መካከል ከዝምድናቸውም በላይ የመተማመንና የመተሳሰብ ወዳጅነት ነበራቸውና እኔንም ባባቴ ዓይን እያዩኝ በጣም የእናት ያህል ያስቡልኝ ነበር። በዚህም ላይ ደግሞ ልጅ ኢያሱ ሁለታችንንም ለማሳዘንና ለማስቀየም ሲሉ አንድ ዓይነት ግፍ ሠርተውብን ነበር። ንግሥት ዘውዲቱን ባባታቸው ከተማ በአዲስ አበባ እንዳይቀመጡ በግድ አስወጥተው ወደ ፋሌ ሰደው እንደ እስር ሆነው እንዲ ቀመጡ አድርገው ነበር። እኔንም ባባቴ ከተማ በሐረር ፡ ወይም በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ እንዳልቀመጥ በሹመት አስመስለው በግድ ወደ ከፋ እንድሔድ አዘውኝ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ልጅ ኢያሱ እንዲሻሩ ንግሥት ዘውዲቱ ለኢትዮጵያ ዘውድና ዙፋን ፡ እኔ ለኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለመሆን እንድንመረጥ ስላደረገን ይህንኑ እያደነቅን በፍቅርና በመስማማት ተቀምጠን ነበር።

ከዚህም ቀድሞ በመስከረም 17 ቀን 1909 ዓመተ ምሕረት መኳንንቱ ከነሠራዊቱ ጳጳሱና እጨጌው ከነካህናቱ ባንድነት ተሰብስበውና መክረው ንግሥትን ለዘውዱና ለዙፋኑ ፡ እኔን ላልጋ ወራሽነትና ለባለ ሙሉሥልጣን እንደራሴነት ሲመርጡ ፡ ስለ ኑሮዋችንና ስለ ሥራችንም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደንብ ወስነውልን ነበር ።

1ኛ. ንግሥት ፣ የዘውዱንና የዙፋኑን ክብር ይዘው ንግሥተ ነገሥታት እየተባሉ እንዲኖሩ።
2ኛ. እኔ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ተብዬ በዚህ ላይ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነቱን ይዤ ፣ የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ በሙሉ እንድሠራ።
3ኛ. የጦር አለቆችን እኔ እየመረጥሁ እንድሾምና እንድሽር።
4ኛ. በችሎት እየተቀመጥሁ ዳኞች የፈረዱትን የሲቢልና የወንጀል ይግባኙን ሁሉ እንድፈርድ።
5ኛ. ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ የሚያገናኘውን ማንኛውንም ጉዳይ ሁሉ እኔ እየተነጋገርሁ እንድጨርስ ነበር።

ይህንም በደንብ ተወስኖ የተሰጠንን ሥራ በመስማማት እየሠራን አንድ ናመት ያህል ከቆየን በኋላ ፣ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች በመካከላችን ገብተው አንድነታችንን ለማጥፋትና ለመለያየት ይሞክሩ ጀመር። ዋና ማስረጃም እያደረጉ ለንግሥት የነገሮቸው ሹም ሽሩና ሌላውም የመንግሥቱ ሥራ ሁሉ በአልጋ ወራሹ እጅ ከሆነ ፣ ንግሥትን የሚፈራና የሚያከብር አንድም ሰው አይገኝምና የጦር አለቆችንና ሚኒስትሮችን በመሾም ፣ ያገር ግዛትን በማደላደልና ርስት በመትከል ፣ ገንዘብም በመስጠት ፣ ይህን በመሰለው ሁሉ የንግሥት ሥልጣን እንዲገባበት ያስፈልጋል እያሉ ነበር። ዳኞች የሆኑትም የፈረዱት ፍርድ በይግባኝ ወደ እኔ እየቀረበ ከተመረመረ በኋላ እንዳይገለበጥባቸው ለማድረግ ስለ ፈለጉ፣ ለንግሥት ክብር እያስመሰሉ ንግሥት በችሎት ቢቀመጡ መልካም ነው ይሏቸው ነበር። ያሮጌው ልምድ እንዳይለወጥና ተማሪ ቤት እንዳይስፋፋ በማለት ነው።

ከዚህ በቀር እኔ ለመንግሥቱ ክብር ፡ ለሕዝቡ ሀብትና በረከት ይሆናል እያልሁ የምሠራውን ሁሉ ፡ ወደ ክፉ እየተረጐሙና እያስመሰሉ ይነግሯቸው ነበር። ለምሳሌ፡-

1ኛ. በኢትዮጵያ ያለው ማዕድን ተቀብሮ ከሚኖር እየወጣ ቢሠራበት ለመንግሥቱም ለሕዝቡም ትልቅ ጥቅም ይሰጣል ብዬ ባዬር ለሚባል ላንድ ለፈረንሳይ ኩባንያ ውል ብሰጥ በአገራችን ላይ ጉዳት እንዳደረስንበት አድርገው አወሩ።

2ኛ. አይሮፕላን ወደ ሀገራችን የገባ እንደ ሆነ ያገርን ጸጥታ የሚያጠፉትን አንዳንድ ወስላቶች ማባረሪያና ማስፈራሪያ ይሆናል ፤ ፖስታና ሰውም በያውራጃው ያመላልሳል ብዬ ከፈረንሳይ አገር ተገዝቶ አይሮፕላን እንዲመጣ ባደርግ የንግሥትን ወገን ሁሉ በአይሮፕላን ፈጅቶ ዘውዳቸውንና ዙፋናቸውን በኃይል ሊወስድባቸው ነው ብለው አወሩ። ይልቁንም ባርያ ነፃ ለማውጣት ታላቅ ችግር አግኝቶኝ ነበር።

ንግሥት ግን እነዚህ በመካከላችን እየገቡ እያስመሰሉ የሚነግሩዋቸው ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም እንጂ ለመንግሥት ጥቅም አለመሆኑን ሳይመረምሩ አንዳንድ ጊዜ የነሱን አሳብ ይከተሉ ነበርና የመንግሥቱን ሥራ እንደ አሳቤ ለመሥራት ብዙ ችግር ሆኖብኝ ነበር። ቢሆንም ትልልቆቹ መኳንንቶች ፣ይልቁንም ራስ ካሣ ባንዳንድ ሰዎች የተንኰል ምክር የመንግሥቱ ሥራ በመሰናከሉና ከሥልጣኔ ወደ ኋላ በመቅረታችን እያዘኑ ንግሥትና እኔ በመጀመሪያ ስንመረጥ እንደተሰጠን ደንብ የመንግሥቱን ሥራ ብንሠራ የሚጠቅም መሆኑን እያስረዱ ለንግሥት ይነግሩዋቸው ነበርና ሌሎች ከሚመክርዋቸው ብዙውን ችላ እያሉ ይተዉት ነበር።



# ምዕራፍ 12

## ያገሩን ውስጥ ሥራ በደንብና ባዋጅ ስለ ማሻሻልና የውጭ አገር ሥልጣኔ በኢትዮጵያ እንዲገባ ስለ ማድረግ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆንበት ከ1909 ዓመተ ምሕረት መስከረም 17 ቀን ጀምሮ አሁን ኢጣልያ በሠራችብን የግፍ ሥራ ይህ ትልቁ አደጋ እስከ ደረሰብን እስከ 1928 ዓመተ ምሕረት በሚቻለን ሁሉ ለመንግሥቱ ክብር ለሕዝቡ ሀብት የሚሰጥ የመሰለንን ሁሉ ከትግል ጋር ከመሥራት አላቋረጥንም። ምንም እንኳ ለሥራው ሁሉ ሚኒስትሮች ብንሾም አላፊነቱ በኛ ላይ ስለ ሆነ ትልቅ አሳብና ድካም ነበረብን።

በዚህም ላይ ደግሞ ከጥንት ጀምሮ እንደ ቆየው እንደ ኢትዮጵያ ነገሥታት ልማድ በየሳምንቱ ሁለት ቀን ረቡዕና ዓርብ በችሎት እየተቀመጥን የይግባኝ ፍርድ መፍረድ ዋና ሥራችን ነበርና የዕረፍት ጊዜ አልነበረንም ።

በየዕለቱ ከሠራነው ከትንንሹ ሥራና በቀን ብዛት ከዘነጋነው በቀር አሁን ትዝ የሚለን ዋና ዋናው ሥራ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

1ኛ. ከ1909 ዓመተ ምሕረት አስቀድሞ ለመንግሥቱ ሥራ ሁሉ ሚኒስትሮች ተሾመው ነበር። ነገር ግን ለሥራቸው ሁሉ በጽሕፈት የሆነ የውስጥ ደንብ አልተሰጣቸውም ነበርና ፡ በቂ የመሥሪያ ቤትም ስላልነበራቸው የሚኒስትርነታቸውን ሥራ አንዳንድ ጊዜ የሚሠሩት በየመኖርያ ቤታቸው ነበር። ግን ከ1913 ዓ. ም. ጀምሮ ለየሥራቸው ሁሉ የሚሆነውን ደንብና መጽሐፍ ከአውሮጳ እያስመጣንና እየሰጠን ለያንዳንዱም ሚኒስትሮች የመሥርያ ቤት እንዲሠራ እያደረግን ለሥራቸውም አንዳንድ የውጭ አገር አማካሪ እየቀጠርን ስለ ሰጠናቸው የመንግሥቱ ሥራ እየተቃና ሔዷል።

2ኛ. በፍርድ ቤቱ አኳኋን ሁሉ በትክክል አይሠራም ነበር ፣ ከ1914 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን ለየፍርድ ቤቱ ሁሉ በጽሕፈት የሆነ ደንብና መጽሐፍ ስለ ሰጠን በጣም እየተሻሻለ ሔዷል። ይልቁንም ከብዙ ዘመን ጀምሮ ተለምዶ በፍትሐ ነገሥት ተጽፎ የኖረውን እጅና እግር የመቁረጥን ይህን የመሳሰለውን የጭካኔ ቅጣት እንዲቀር በማድረጋችን ሕዝባችን ሁሉ ደስ ብሎታል።

3ኛ. ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ስለ ቅጣት የቆየው ልማድ አንድ ሰው የወንጀል ሥራ የሠራ እንደሆነ ፣ መቀጫው በገንዘብ ቢሆን ገንዘቡን ለማሳነስና ለማብዛት ፡ በእስራትም ቢሆን የእስራቱን ቀን ለማሳጠርና ለማስረዘም ዳኛው እንደ ወደደ ለማድረግ ሥልጣን ነበረው እንጂ ፡ በገንዘብም በእስራትም ቢሆን የተወሰነ ቅጣት አልነበረም። እንዲያውም ዳኛው በፍርዱ ወዳጁን ለመጥቀም ፡ ጠላቱን ለመጉዳት ቢያስብ የሚከለክለው ሕግ ስላልነበረ ፡ ሁለት ሰዎች አንድ ወንጀል ሠርተው ቢያዙ ፡ ዳኛው ከፈቀደ አንዱን ቀጥቶ አንዱን ያለ ቅጣት ሊለቀው ይችል ነበር።

ከ1923 ዓመት ምህረት ጀምሮ ኻ ወንጀል የሚሆነው ሥራ ሁሉ በዝርዝር ተጽፎ ይህን ወንጀል የሠራ ይህን ያህል ገንዘብ ይከፈል ፡ ይህን ያህል ቀን ይታሰር የሚል የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ ስለ አቆምን ዳኛው ወዳጁን ለመጥቀም ጠላቱን ለመጉዳት እንደ ወደደ ማስከፈሉና እንደ ወደደ ማሰር መፍታቱ እንዲቀር አድርገናል። ፍርድ ክብር ያለው መንገድ ይዟል።

ደግሞ ነፍሰ ገዳይ መግደሉን በቃሉ አምኖ ወይም ምስክሮች መስክረውበት እንዲሞት ከተፈረደበት በኋላ ለባለ ደሙ ተላልፎ ተሰጥቶ ባለ ደሙ ሕዝቡ ሁሉ በተሰበሰቡበት ስፍራ በወደደው መሣርያ እንደ ፈቃዱ እየደበደበ ጣሩን እያበዛ ይገድለው ነበር።

አሁን ግን ነፍሰ ገዳይ የሚሞትበት ልዩ ቤት አሠርተን ማንም ሰው ሳያይ የመንግሥት ባለወግ ብቻ ልዩ ማነጣጠሪያ ባለው ጠመንጃ ተኲሶ ያለጣር እንዲገድለው አድርገናል ።

4ኛ. ያገር ውስጥ ሰዎችና የውጭ አገር ሰዎች ሲጣሉ ክርክሩ በተቃና አኳኋን እንዲፈጸም በማለት ፣ ከ1913 ዓ. ም. ጀምሮ ልዩ የዳኝነት ቤት እንዲቆም አድርገን ፡ ሕግ ዐዋቂ ዳኛ ሾምን። ለዳኛውም ሕግና የሚያውቅ አማካሪ የውጭ አገር ሰው እየቀጠርን ስለ ሰጠነው የፍርዱ ነገር በጣም ተሻሽሏል። ለዚሁም ሥራ የተቀጠሩት አማካሪ የስዊስ አገር ተወላጅ ሙሴ ኦቤርሶን ነበሩ። ይህ ከባድና ያገርን ክብር የሚነካ ውል ሁናቴ የፈረንሳዊው መልክተኛ ሙሴ ክሎቢኮብስኪ ካፄ ምኒልክ ጋራ በ1900 ዓ.ም. በተዋዋለው ነበር።

5ኛ. በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ማተሚያ መኪና እንደሚበቃ ያህል ስለአልነበረ መጽሐፍ ሁሉ የሚጻፈው በእጅ ነበርና ሕዝቡ ሁሉ መጽሐፍ ለማግኘትና ለማንበብ ብዙ ችግር ነበረበት። ምክንያቱም በእጅ የሚጻፈው መጽሐፍ ለሁሉ ሊያዳርስ ስላልተቻለና ዋጋውም ብዙ ስለ ሆነ ነው።

ከ1914 ዓ. ም. ጀምሮ በልዩ ገንዘባችን ሁለት የመጽሐፍ ማተሚያ መኪና ገዝተን ስለ አቆምን ብዙ መጻሕፍት በግእዝና ባማርኛ በትርጓሜም ስለታተሙ ሕዝቡ ሁሉ በጥቂት ዋጋ እየገዛ በማንበቡ ብዙ ጥቅም አግኝቷል። ደግሞ ብርሃንና ሰላም የተባለ የሳምንት ጋዜጣና ከሣቴ ብርሃን የተባለ የወር ጋዜጣ በነዚሁ ማተሚያዎች ይታተማሉ። የማተሚያ ቤቱንም ገቢ ለቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ርስት አድርገን ሰጠነው። በመንግሥትም ገንዘብ ሌላ የማተሚያ መኪና እንዲቆም ፈቅደን ለመርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት ተሰጥቶ ብዙ መጻሕፍትና ለየሚኒስቴር ቤቱ ሥራ የሚሆነው ካርኔና ይህን የመሰለው ሁሉ ይታተማል። አእምሮ የሚባለውም ጋዜጣ በሳምንት አንድ ጊዜ በዚሁ ማተሚያ ይታተማል።

6ኛ. 6ኛ ፡ ከ1915 ዓመተ ምሕረት አስቀድሞ የብድር ደንብ አልነበረምና ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በመቶው ሀያ እስከ ሠላሳም ወለድ ገንዘብ እያበደሩ ባለ ዕዳው የሚከፍለው ገንዘብ ሲያጣ በዳኛ እየተከሰሰ እጁ ላበደረው አልፎ እየተሰጠ ዕዳውን እስቲከፍል ይታሰር ነበር።

ከ1915 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን ወለድ ከ መቶ 9 እንዲሆን እንጂ ከዚያ በላይ ወለድ የተቀበለ መቀጫ እንዲከፍል አድርገናል። ተበዳሪውም የሚከፍለው ገንዘብ የሌለው እንደ ሆነ በሐራጅ የሚሸጥ ከብትም ርስትም እንደሌለው ተመርምሮ ከታወቀ በኋላ እጁ ለአበደረው አልፎ እንዳይሰጥ በ1916 ዓ. ም. በደንብ ከልክለናል ።

7ኛ. በአዲስ አበባና በሌሎቹም በዋና በዋና ከተሞች በየቤቱ የጋዝና የሞራ የሰም (የጧፍ) መብራት ይበራ ነበር እንጂ የኤሌክትሪክ መብራት አልነበረም።

በ1909 ዓ. ም. በመጠኑ ተጀምሮ የነበረው አገልግሎት ከ1915 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ በቤተ መንግሥቱና በሚኒስትሮቹም መሥሪያ ቤት፡ በየመኳንንቱም ቤትና በትልቁ በልዑል ራስ መኰንን መንገድ ዳር ዳር ሁሉ በየትልልቁም ቤተ ክርስቲያን በሐረርና በድሬዳዋ ከተሞች በደሴም በደብረ ማርቆስም የመንግሥት ቤቶች የበለጠ የኤሌክትሪክ መብራት እንዲበራ ሆኗል።

8ኛ. ቀድሞ የውጭ አገር የነገሥታት ልጆችና መሳፍንት ወደ ኢትዮጵያ አይመጡም ነበር።

ከ1916 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን ባገሩ የውጭ አገር ሥልጣኔ እንዲገባ ስላደረግን የውጭ አገር ነገሥታት ልጆችና መሳፍንት ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ጐብኝተው ተመልሰዋል። ከነዚሁም ዋነኞቹ የእንግሊዝ ንጉሥ የግርማዊ ጆርጅ 5ኛ ልጅ ዱክ ኦፍ ግሎስተር ፡ የስዊድን መንግሥት አልጋ ወራሽ ጉስታፍ አዶልፍ ፡ የኢጣልያ ንጉሥ የግርማዊ ቢክቶር አማኑኤል አጎት ዱክ ዴዝአብሩዝ ፡ የሳቧይ ፕሪንስ ደኡዲኒ ናቸው ።

9ኛ. ከ1915 ዓመት አስቀድሞ ካንድ አውቶሞቢል በቀር በኢትዮጵያ አውቶሞቢልና ካሚዮን በብዛት አልነበረምና ከንጉሡ ነገሥቱ ጀምሮ መኳንንቱም ሕዝቡም የሚሔዱት በፈረስ ወይም በበቅሎ ስለሆነ ፡

የንግድ ዕቃና ይህንም የመሰለው የሚመላለሰው በአጋሰስ እየተጫነ ስለ ሆነ ፡ ወደ ታሰበው ስፍራ ለመድረስ ብዙ ጊዜ ያስፈልግ ነበር።





በልጅ ኢያሱ ዘመን ከልጅ ኢያሱ በቀኝ በኩል ዳጃዝማች ተፈሪ (ቀ.ኃ.ሥ) በግራ ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል

ከ1915 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን ብዙ አውቶሞቢልና ሞቶር ቢስክሊት ቢስኪሎችም ብዙ ካሚዮንም እንዲገባ ስላደረግን ማናቸውም ሥራ ሁሉ እየተፋጠነ የሚሔድሆኗል።

10ኛ. እስከ 1915 ዓመተ ምሕረት የሰሎሞንና የኢትዮጵያ ኮከብ የሚባሉ ሁለት ዓይነት ኒሻኖች ብቻ ነበሩ። አሁን ግን ለዚያው ለሰሎሞን ኒሻን የወርቅ ሰንሰለት እንዲሠራለት አድርገን ለንጉሠ ነገሥቱ ማዕርግ ላላቸው ለውጭ አገር ነገሥታት የሚሰጥ ሆኗል ።
ደግሞ ለእቴጌዬቱና ለውጭ አገር እቴጌዎች የሚሰጥ የንግሥተ ሳባ የተባለ ኒሻን ባለወርቅ ሰንሰለት እንዲሠራ አድርገናል ፡ ከዚህም በቀር የዳግማዊ ምኒልክና የሥላሴ ኒሻን የተባሉ ማዕርጋቸው በጣም ከፍ ያለ ኒሻኖችና የወታደር ሜዳይ የጥበብና የዕውቀትም ሜዳዮች በየማዕርጋቸው እንዲሠሩ አድርገን ብዙ ሰዎች ተሸልመዋል።

11ኛ. የትምህርት ቤት በአዲስ አበባ አንድ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ብቻ ነበር እንጂ ሌላ ስላልነበረ በውጭ አገር ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ጥቂቶች ነበሩ።
ከ1917 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን በአዲስ አበባና በሌሎችም በዋና በዋናዎቹ ከተሞች የውጭ አገር ቋንቋ መማሪያ ትምህርት ቤት ስለ አቆምን ፡ ከዚህ በፊት ከነበሩት ትምህርት ቤቶች በቀር ለልዩ ልዩ ሚሲዮኖችም ፈቃድና እርዳታ ሰጥተን የቋንቋ ትምህርት ቤት በያውራጃው ስለ ተከፈተ በዚህም ላይ ወደ ውጭ አገር ብዙ ልጆች እየሰደድን ስለ ተማሩ ብዙ ልጆች በየሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ለመሥራት ችለዋል።

12ኛ. በአዲስ አበባ የቆመው የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል የተባለ አንድ ሆስፒታል ብቻ ስለ ሆነ የሕዝቡን ሁሉ ጤና ለመጠበቅ አልበቃም ነበር።
ከ1915 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን በአዲስ አበባና በሌሎችም በዋና ዋና ከተሞች ብዙ ሆስፒታሎች እንዲቆሙ ስላደረግን ለልዩ ልዩ ሚሲዮኖችም ፈቃድና የገንዘብ እርዳታ እየሰጠን ሆስፒታሎች ስለ ተሠሩ የብዙ ሰዎች ጤናቸው እንዲጠበቅ ሆኖአል ። ዳግመኛም በልዩ ገንዘባችን አዲስ አበባ ላይ ባቆምነው ቤተ ሳይዳ ብለን በሰየምነው ሆስፒታል የስዊድን ተወላጅ የሆኑት ሐኪም ሙሴ ሐነር ተቀጥረው እንዲሠሩ አደረግን ፡ ሆስፒታሉም ስሙ የታወቀና የገነነ ሆኗል ።

13ኛ. በቀድሞ ዘመን ወታደር የሚሆን ሰው ሁሉ በልማድ ብቻ ነበር እንጂ የወታደር ትምህርት ቤት አልነበረም።
ከ1911 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን የወታደር ትምህርት ቤት አቁመን የወታደርነትን ሥራ ሁሉ በትምህርት ቤት እንዲማሩ አድርገናል ። ከዚህም በቀር ትንንሽ ልጆች (ወጣቶች) የቦይስካውትነትን ተግባር እንዲያከናውኑ መስፍን ሐረር በተባለው በልጃችን በመኰንን ጠባቂነት አቁመናል።

14ኛ. ቀድሞ ሰንደቅ ዓላማ የሚባለው ባለ አንበሳና ባለ ሦስት ቀለም ብቻ ነበር። ከ1920 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን ለንጉሠ ነገሥቱ የዘወትርና የበዓል ሰንደቅ ዓላማ ሦስቱ ቀለም ሳይለወጥ ፡ በአንበሳውና በወርቁ መርገፍ ብቻ እንዲለይ ሆኖ ለእቴጌዬቱና ለአልጋ ወራሹ ፡ ለጦር ሠራዊትና ለፖስታ ቤት ፡ ለመርከብም ሦስቱ ቀለም ሳይለወጥ በጌጡና በቅርጹ እየተለየ ሰንደቅ ዓላማ እንዲሠራ አድርገናል ።

15ኛ. በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በኢትዮጵያ በግራማፎን የውጭ አገር መንግሥቶች ሂም ናሲዮናል ይሰማ ነበር እንጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የተባለ አልነበረም።
አሁን ግን ከ1920 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ በተለየ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርና ማርሽ ተፈሪ ፡ ማርሽ ሚሊቴር የሚባል ወጥቶ በቤተ መንግሥትም በሌላም በሚያስፈልገው ስፍራ ሁሉ፡ የኢትዮጵያ መላክተኞችም ወደ ውጭ አገር በሔዱ ጊዜ የክብር አቀባበልና ግብዣ ሲደረግላቸው እንዲሰማ ሆኗል።
የውጭ አገር መንግሥቶች ብሔራዊ መዝሙርም መላክተኞቻቸው ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ በክብር አቀባበልና በግብዣ ጊዜ እንዲዘመር አድርገናል።

16ኛ. ከ1900 ዓመተ ምሕረትጀምሮ ናሽናል ባንክ ኦፍ ኢጅብት የሚባለው ማኅበርና በአዲስ አበባ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ተብሎ ከቆመው ካንድ ባንክ በቀር ሌላ ባንክ አልነበረም። ይህም ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ የተባለው ሲቆም በውሉ ከተጸፈው ጥቅም የሚበዛው የማኅበሩ ብቻ ስለሆነ ለመንግሥትና ለሕዝብ በጣም ችግር ሆኖ ይኖር ነበርና በ1920 ዓመተ ምሕረት የራሳችንን ልዩ ገንዘብ በአክሲዮን አግብተን መኳንንቱና ሕዝቡም እንደተቻለው አክሲዮን እንዲገባ አድርገን የባንክ ኦፍ አቢሲኒያን ኪሣራ ሁሉ ከፍለን ስለ ገዛነውና የኢትዮጵያ ባንክ ብለን ስለ ሰየምነው ትልቅ ጥቅም የሚገኝበት ሆኗል።

17ኛ. ከ1920 ዓመተ ምሕረት አስቀድሞ በኢትዮጵያ የአይሮፕላን ስሙ እምብዛም አይታወቅም ነበር። ከ1920 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን አይሮፕላኖች እየተገዙ እንዲመጡ ስለ አደረግን ለመንግሥቱም ለሕዝቡም ችግሩ ሁሉ እየቀለለ ሔዷል።

18ኛ. በውጭ አገር መንግሥታት የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ወይም ቆንስላ ስላልነበረ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ ለሚያገናኘው ገዳይ ሁሉ ልዩ መላክተኛ ይላክ ነበር። ወይም አንድ የውጭ አገር ሰው ተወክሎ መላክቱን ያደርስ ነበር።

ከ1921 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን በጎረቤቶቻችን መንግሥታት ሌጋሲዮን ፡ በሩቆቹ ግን ቆንስላ እንዲቆም ስለ አደረግን የመንግሥቱ ጉዳይ ሁሉ ያለችግር እንዲፈጸም ሆኗል ።

19ኛ. የጦር መሣርያ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ተከልክሎ ስለ ነበረ በያውራጃው ወስላታው በዝቶ ነበር። ከ1920 ዓመተ ምሕረት ጀ ግን ላገር መጠበቂያ የሚሆን መሣርያ እንድንገዛ በውል ስለ ተፈቀደ በያውራጃው ሁሉ ላሉት አገር ጠባቂዎች መሣርያ እየሰጠን ወስላታውን እንዲያጠፉ ስለ አደረግን ባገሩ ውስጥ ጸጥታና ሰላም ሆኗል። ይህም የጦር መሣርያ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ በተፈቀደ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር አይሮፕላን እንዳይፈቀድለት የኢጣልያ መልክተኛ ተከራክሮ ማስቀረቱን አንዘነጋውም። ይኸውም ሰላምን አጥፍቶ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለማድረግ ኢጣልያኖች ከብዙ ዘመን በፊት ማሰባቸውንና ማዘጋጀታቸውን የሚያስረዳ ነው።

20ኛ. የኢትዮጵያ ተወላጆች ከሆኑ መምህራን ወገን ተመርጠው ጳጳሳት እንዳይሾሙ በሕግ ተከልክሏል እየተባለ ሳይሾሙ ይኖሩ ነበር ።

ከ1920 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ግን የኢትዮጵያ አውራጆቿ ብዙ መሆናቸውንና በክርስቶስም ዘንድ ምእመናን ሁሉ በምግባር እንጂ በተፈጥሮ ልዩነት አለመኖሩን አጥብቀን ስለ ተነጋገርንና ስለ አስረዳን ከኢትዮጵያ ተወላጆች አምስት መምህራን ተመርጠው ጳጳስነት እንዲሾሙ አድርገን ሀገረ ስብከታቸውን እያካፈልን ሰጥተናቸዋል ።

21ኛ. ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ በሚጭንበት ጊዜ ከውጭ አገር መንግሥቶች ለዘውዱ በዓል ልዩ መላክተኛ ተልኮ እንዲመጣ ለማድረግ ልማድ አልነበረም ።

አሁን ግን ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ከፍ ከፍ እያለች እንድትሔድና ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ ያላትን ወዳጅነት እንድታጸና ስለ አደረግን በጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓመተ ምሕረት የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስንጭን የ12 መንግሥት እንደራሴዎች ወደ አዲስ አበባ መጥተው የዘውድ በዓላችንን አክብረው ተመልሰዋል። ይኸውም ኢትዮጵያ በዘመናችን ወደ ትልቅ ደረጃ መውጣቷን ያስረዳል ።

22ኛ. ማንኛውንም የሰላማዊውንና የወታደርነቱን ሥራ ፡ ያገሩንም አገዛዝ ሌላውንም ይህን የመሰለውን ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ወደደ እያደረገ ይሠራው ነበር።

አሁን ግን በሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓመተ ምሕረት ሕገ መንግሥት አቁመን ፡ የምክር ቤት ሠርተን ፡ የሕግ መወሰኛ አማካሪዎችን ሾመንና የሕግ መምሪያ አማካሪዎችን አስመርጠን ፡ ለነዚሁ ፕሬዚዳኖች ሾመን ፡ የመንግሥቱ ሥራ ሁሉ በምክር እንዲሠራ አድርገናል።

23ኛ. ንጉሠ ነገሥቱ ወይም መኳንንቱ ብዙ ሠራዊት እያስከተሉ ካንዱ አውራጃ ወደ አንዱ አውራጃ ሲሔዱ ምግብም ፡ ሣርና እንጨትም አለ ዋጋ መጥን እያወጣ እንዲሰጥ በግድ ይታዘዝ ነበር።

ከ1923 ዓ. ም. ጀምሮ ግን ባላገር በፈቃዱና በዋጋ ካልሆነ በቀር ማናቸውንም ገንዘቡን በግድ እየታዘዘ እንዳይሰጥ ባዋጅ አስቀርተናል ።

24ኛ. ስልክ የተዘረጋባቸው አገሮች ቁጥራቸው ጥቂት ስለነበረ ፡ በያውራጃው የመንግሥቱንም የንግዱንም የሕዝቡንም ችግር ለመጨረስ ብዙ ጊዜ ይወስድ ነበር።

በኋላ ግን በያውራጃው ሁሉ ስልክ እንዲዘረጋና ፖስታም እንዲመላለስ ስለ አደረግን የመንግሥቱና የሕዝቡ ችግር በጣም እየተቃለለ ሔዷል ።

25ኛ. ወንጀለኞች የሚታሠሩበት ቤት ለጤና የማይስማማ ንጹሕነት የሌለው ነበር። ከ1923 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን ለጤና የሚስማማ የመታጠቢያና የመታከሚያ ፡የንባብና የጽሕፈት ፡ የእጅ ሥራ ትምህርት ያለበት ቤት በልዩገንዘባችን አሠርተን ሰጥተናል። በእግር ብረትና በሰንሰለት መታሰራቸውም ቀርቶ በዘበኛ እንዲጠበቁ አድርገናል ።

26ኛ. መሬት ያለው ሰው ሁሉ ባመት ከሚከፍለው ከተወሰነው ግብር በቀር በየምክንያቱ ትርፍ ገንዘብ እንዲከፍል የጉልበትም ሥራ አለዋጋ እንዲሠራ በግድ ይታዘዝ ነበር።

አሁን ግን ባመት አንድ ጊዜ የሚከፍለው ግብር ተወስኖ ከዚያ በቀር ማናቸውንም የጉልበት ሥራ አለዋጋ እንዳይሠራ ሌላም ትርፍ ገንዘብ እንዳይከፍል በደንብና ባዋጅ አስቀርተንለታል ።

27ኛ. የነፋስ ስልክ በአውሮጳ ተገኝቷል ከማለት በቀር ፡ የነፋስ ስልክ አገልግሎት ጐልቶ በኢትዮጵያ አይታወቅም ነበር።

1924 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን በአዲስ አበባና በሌላውም በየትልልቁ አውራጃ የነፋስ ስልክ እንዲቆም ስለ አደረግን የመንግሥቱም የነ.ጋዴውም ፡ ሌላውም ባገር ውስጥና በውጭ አገር የሚገኘው ጉዳይ ሁሉ በቶሎ የሚፈጸም ሆነ። ይኸውም በ1928 ዓመተ ምሕረት ከኢጣልያ ጋር በተዋጋንበት ጊዜ አገልግሎቱን አበርክቷል።

28ኛ. የማዕርግ ልብስ ስላልተወሰነ ሁሉም አንድ ዓይነት የማዕርግ ልብስ ለብሰው ነበር።

በኋላ ግን የሰላማዊና የወታደር የማዕርግ ልብስ እንዲለይ ስለ አደረግን የሹመት ትልቅነትና ሲቢል ወይም ሚሊቴር መሆኑ በልብሱ እንዲታወቅ ሆኖአል።

29ኛ. ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት ጀምሮ ማናቸውም ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ከብትና ዕቃ የተሰረቀ እንደሆነ ፡ ዕድሜው ከ15 ዓመት በታች የሆነ ብላቴና መድኀኒት አጠጥተን ሌባውን ፈልገን ለማግኘት እንችላለን የሚሉ ሰዎች ነበሩና በትውልድም በጋብቻም የነዚህ ወገን የሆኑ ሰዎች ፡በአዲስ አበባና በሌላውም አውራጃ ሁሉ እየዞሩ ገንዘብ ጠፋኝ ከሚለው ሰው ዋጋ እየተቀበሉ መድኀኒቱን እያጠጡ ሌባውን እንዲፈልጉ መንግሥት ፈቅዶላቸው ይኖሩ ነበር። ሌባውንም አገኘነው የሚሉት መድኀኒቱን የሚአጠጡት ልጅ ሔዶ ባንድ ሰው ቤት ገብቶ በመኝታው ላይ የተኛ እንደሆነ ፡ ወይም ሰውዬውን ይዞ በጉልበት ጐሽሞ በላዩ የተኛ እንደሆነ ነው። እንደዚህም የተደረገ እንደሆነ ፡ ለመሰረቁ ምንም ምልክትና ምስክር ሳይገኝ በዚሁ ብቻ በግድ ተይዞ የጠፋውን ገንዘብ ለባለቤቱ እንዲከፍል ግዴታ ነበረበት። ይህን የመሰለውም ሥራ በሐሰትና በማታለል የሚሠራ ስለ ሆነ፣የማንንም ገንዘብ ባልሰረቀው በደኀናው ሰው ቤት ሌባሻዩን እያስገቡ እያስተኙ ፡ ወይም ሰውዬውን ጐሽሞ እንዲተኛበት እያደረጉ ሕዝቡን ሲያስሩና ሲያስጨንቁ ይኖሩ ነበር።

በኋላ ግን ይህን የመሰለው የሌብነት ነገር በዳኛ ምርምር ወይም በምልክትና በምስክር ካልሆነ በቀር ፣ መድኀኒት በማጠጣት ሌባውን ማግኘት የማይቻል ነገር መሆኑን ተመራምረን ስለ ተረዳነው ፡ የሌባሻይ ሥራ እንዲቀር አድርገን ሕዝቡን በዚህ ነገር ከሚመጣበት ጭንቀት ስለ ጠበቅነው በያውራጃው ትልቅ ደስታሆነ።

30ኛ. በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥቱ ምንም የበላይ ቢሆን የፊዎዳል ግዛት አልቀረም ነበር። ከ1910 ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን የትክለኛ ባላባት ግዛት ፣ መንግሥቱንም ሕዝቡንም የሚጐዳ መሆኑን ስለ ተረዳነው በወሎ ፡ በጎጃም ፡ በበጌምድር ፡ በየጁ ፡ በወለጋ ፡ በጅማ ፡ ትክለኛ ባላባቶችን አስቀርተን ሌሎችን-የመንግሥታችንን አገልጋዮች እየመረጥን እንዲሾሙ አድርገናል ።

31ኛ. በኢትዮጵያ እንደ ቆየውና እንደ ተለመደው አገረ ገዥዎች ሁሉ የጦር ሹሞች ናቸው እንጂ ፣ የሲቢል ሹሞች አልነበሩም። ስለዚህም ለወታደሮች በየአለቃቸው እየከፈሉ ከዚያው ከግዛታቸው ውስጥ ማደሪያ እያሉ ይሰጧቸዋል እንጂ አገሩ ሁሉ በመንግሥት እጅ ሆኖ ፣ በሲቢል ሹሞች ግብሩ እየተሰበሰበ ለወታደሮችም ለሌላም ለመንግሥት ጉዳይ ወጪ ማድረግ አልተለመደም ነበር።

ይህንንም ከብዙ ዘመን ጀምሮ የቆየውን ልማድ ባንድ ጊዜ ለማፍረስ ያገር ውስጥ ሁከት ያስነሣል በማለት ስለ ሠጋን አደራረጉን ለማሳየትና በየጥቂቱ ለማስለመድ ጅጅጋ ፡ ጨርጨር፡ ባሌ ፡ ወለጋ ፡ ሰዮ ፡ ጅማ የሚባሉትን አውራጆች በመንግሥት እጅ አድርገን ገቢው ገንዘብ ለወታደ ለሌላም ለመንግሥት ጉዳይ ወጪ እንዲሆን ማስለመጃ ምሳሌ አድርገናል።

32ኛ. ከዛሬ ዐሥር ዓመት በፊት በያውራጃው መንገድ ስላልተጠረገ ካንዱ አውራጃ ወዳንዱ አውራጃ ለመድረስ ብዙ ቀንና ብዙ ገንዘብ ማጥፋት ግድ ነበር።

ከ10 ዓመት ወዲህ ግን መንገድ ለመንግሥትም ለሕዝብም ጥቅም ያለው መሆኑን ስለ ተረዳነው ፡ ከአዲስ አበባ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ፡ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ የሚወስድ መንገድ እንዲጠረግ ስለ አደረግን በዐሥር ወይም በዐሥራ አምስት ቀን የሚደረሰው አገር አሁን በአውቶሞቢልና በካሚዮን በሁለትና በሦስት ቀን የሚደረስ ሆኗል ።

# ምዕራፍ 13

## ኢትዮጵያ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ ስለ ማድረጋችን ።

ትልቁ የዓለም ጦርነት ካለፈ በኋላ ወደ ፊት ይህን የመሰለ እጅግ የሚያሰቅቅ ጦርነት እንዳይነሣ ስለ ተፈራ ፣ የዓለም መንግሥታት ማኅበር የሚባል ቆሞ በሁለት መንግሥታት መካከል ጠብ የተነሣ እንደሆነ ፣ በፈቃዱ ጦርነት ማድረጉ ቀርቶ ጠቡ የተነሣበት ነገር ወደ ዓለም ማኅበር እየቀረበ ከተመረመረ በኋላ ፣ የእገሌ መንግሥት በድሏል የእገሌ መንግሥት ተበድሏል እየተባለ እንደ ጠቡ ትልቅነት እየታየ ፣ ፍርዱ በማኅበሩ ቃል እንዲቆረጥ ፡ ከማኅበሩ ፈቃድ የወጣ ግን የማኅበሩ ሁሉ ጠላት መሆኑ ነውና ሁሉም በጠላትነት ሊነሡበት እንጂ አንዱ ኃይለኛ መንግሥት በፈቃዱ ተነሡቶ ደካማውን መንግሥት እንዲወጋው ፡ ወይም ገንዘብ እንዲያስከፍለው አይገባውም ተባብለው 27 መንግሥታት ተስማምተው ሰኔ 28 ቀን ፡ 1911 ዓ.ም. ( እ.ኤ.አቄ. ሰኔ 21 ቀን 1919 ዓ.ም) ተፈራርመዋል። የማኅበሩም ዋና ስፍራ በስዊስ አገር ጀኔብ በሚባለው ከተማ ሆኗል እያሉ በአዲስ አበባ ካሉት የውጭ አገር ሰዎች አንዳንዶቹ በወዳጅነት እያስረዱ ስለ ነገሩን ብዙ ጽሑፎችም ስለ ተመለከትን ፣ ትልልቁን መኳንንቶችና ሚኒስትንን ሁሉ ሰብስበን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ነገርናቸው።

ኢትዮጵያ ወደ መንግሥታት ማኅበር ብትገባ ትልቅ ጥቅም ነው። ነገር ግን ወደ ፊት የመንግሥታችንን ሥራ ሁሉ እያሻሻልን ለመሔድ የሚያስፈልግ ነውና ወደ ማኅበሩ ከገባን በኋላ የመንግሥታችንን ሥራ ሳናሻሽል የቀረን እንደሆነ ፣ በማኅበሩ በኩል ችግር እንዳያገኘን ዛሬውኑ አሳባችሁን አስታውቁን አልናቸው። መኳንንቱና ሚኒስትሮቹም ባንድ ቃል ሆነው ባንድ ዓመት ውስጥ ከፍ ያለ መሻሻል ለማድረግ አይቻልም እንጂ በያመቱ በየጥቂቱ እየሠራን የመንግሥታችንን ሥራ ሁሉ ለማሻሻል ፈቃዳችን ነውና ወደ ማኅበሩ ብንገባ መልካም ነው ብለው ተናገሩና የመግባታችን ነገር የተቆረጠ ሆነ።

ከዚህም በኋላ የእኛን ደብዳቤ ይዘው ወደ ጄኔብ ሔደው ወደ ማኅበሩ እንድንገባ የተፈቀደልን እንደሆነ ፣ ወዲያው በእኛ ስም ሆነው እንዲፈርሙ ደጃዝማች ናደውን ዋና ፣ አቶ ኅሩይ ወልደ ሥላሴንና አቶ ፋሲካን ረዳቶች አድርገን በነሐሴ 1 ቀን 1914 ዓመተ ምሕረት ወደ ጄኔብ ላክናቸው።

መልከተኞቻችንም እንዳስታወቁን የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ ባቀረበችው ጥያቄ ፡ ለጊዜው ጥቂት ችግር ሆኖ ነበር። በኋላ ግን የፈረንሳይ መንግሥት መላክተኛ ሙሴ ዝብኤልና ቀድሞ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበሩት ሙሴ ላጋርድ በብዙ ስለ ረዱ ፡ የእንግሊዝና የኢጣልያ መልክተኞችም የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ማኅበሩ ብትገባ የእኛም መልካም ፈቃድ ነው ብለው ስለ ተናገሩ ፣ ማኅበሩ በሙሉ ፈቀዱና መላክተኞቻችን ስምምነቱን ፈርመው ተመለሱ። በአዲስ አበባም ትልቅ ደስታ ተደረገ። ደስታም መደረጉ ዛሬ ኢጣልያ እንዳደረገችብን ከመሰለው አደጋ የማኅበሩ ቃል ኪዳን የሚጠብቀን ስለ መሰለን ነበር እንጂ በሌላ ምክንያት አልነበረም። ፡

# ምዕራፍ 14

## ባሮች ነፃ እንዲወጡ ስለ ማድረጋችንና የነፃነታቸውም ነገር በያመቱ እየተሻሻለ ስለ መሔዱ ።

በቀድሞ ዘመን ባርያ መሸጥና መግዛት ፣ በእስያና በአውሮጳ በአሜሪካም ተለምዶ የሚኖር ስለ ነበረ ፣ በአፍሪቃ ክፍል በኢትዮጵያም ተለምዶ ይኖር ነበር። ቢሆንም ከባሮች የሚበዙት በምርኮ የመጡ ናቸው እንጂ ተሸጠውና ተገዝተው የመጡት ቀሩጥራቸው ጥቂት ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከ15ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ 18ኛው መቶ ዓመት ፣ የእስላሞችና የአረማውያን ኃይል በርትቶባት ነበርና በያመቱ ጥቂት በጥቂት እየሆነ ፣ ከአውራጆቿ ብዙዎቹ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እየሸፈቱ ለየራሳቸው አንዳንድ ባላባት እያበጁና አገር እየዘረፉ ኖረው ነበር። በኋላ ግን ከኛ በፊት የነበሩት ነገሥታትና ይልቁንም ዐፄ ምኒልክ እነዚህን አውራጆች እንደ ጥንቱ ወደ ኢትዮጵያ አንድነት ለመመለስ በጦርነት ሲያቀኑ ፣ ከጦርነቱ ላይ እየተማረኩ የመጡት ሁሉ እንደ ቀድሞው ልማድ ለማራኪው በባርነት እየተገዙ እንዲኖሩ ልማድ ሆኖ ነበር። ቢሆንም እነዚህ በምርኮ የሚመጡት ካንዳንዱ በቀር በመልክ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ብዙ ልዩነት የለባቸውምና ፡ ባሮች መሆናቸውን ለይቶ ለማወቅ ብዙ ያስቸግራል ። እንዲሁም ደግሞ አንዳንዶቹ ባርነታቸው በስም ብቻ ነው እንጂ በኑሮ ከማራኪያቸው ብዙ የሚለዩበት ኑሮ አልነበረም። ርስት ለመግዛትና ለመሸጥ ፡ ወይም እንደ ሌላው ሕዝብ ከመንግሥት ርስት ለመተከል ፡ በመንግሥት ሥራ ውስጥ የጦር አለቅነት የሚኒስትርነት ፡ በቤተ ክህነትም ሥራ ውስጥ የዲቁና ፡የቅስና ፡ የምንኩስና ፡ የገዳም ማኅበር አባትነት ፡ የደብር አለቅነት ማዕርግ ሊያገኙ ይችላሉ።

በመልክና በኑሮም ልዩነት ስለሌላቸው ከማራኪያቸው ወይም ከልጁ ወይም ከዘመዱ ለመጋባት ይችላሉ። አንዱም ማራኪያቸው በሚሞትበት ጊዜ እንደ ልጆቹ አድርጎ በኑዛዜ ርስትና ገንዘብ ይሰጣቸዋል ።

ደግሞ በዓለም ሁሉ እንደሚደረገው በደመወዝ እየተቀጠሩ የቀን ሥራ የሚሠሩ በያውራጃው ብዙ ሰዎች ይገኛሉ። ኢጣልያኖች ግን ይህን ሁሉ እያወቁ በየባለጠጋው ቤት በደመወዝ እየተቀጠሩ የሚሠሩትን እገሌ ይህን ያህል ባሮች አሉት እያሉ ያወራሉ። ለመወንጀል አጋነው ያወሩት ነበር።

ይህንንም የሚያስረዳ ነገር ትውልዱ ከጋሎች ወገን የሆነ በሐረር አውራጃ የሚኖር አንድ ባለጠጋ ነበረ። ይህም ሰው በደግነቱና በዕውቀቱ ብዛት ገንዘቡን ለባዕድ ሠሪ ከመስጠት ለዘመዶቹ መስጠት ትልቅ ጥቅም ነው እያለ የወንድሞቹንና የእኅቶቹን ልጆች የዘመዶቹንም ልጆች ሰብስቦ ደመወዝ እየሰጠ ሥራውን ያሠራቸው ነበር።

ሐረር ያለው የኢጣልያ ቆንሲል ግን ይህን ሁሉ ሳይመረምርና ሳያውቅ እገሌ ይህን ያህል ባሮች አሉት ብሎ ለመንግሥቱ ራፖር ጽፎ ኖሮ መንግሥቱ እውነት መስሎት እኛን መክሰሻ አድርጎ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አቅርቧል ።

ስለ ባሮች ነፃነት ባደረግነው ዐዋጅና ደንብ ነፃ ከሚወጡት ባሮች በቀር ሌላም አንዳንድ ምክንያት እየፈለግን ባሮችን ነፃ ለማውጣት የሚቻለንን ሁሉ እናደርግ ነበርና የቤኒሻንጉል ገዥ ሺሆጄሌ እንደ ዐዋጁና እንደ ደንቡ ባገሬ ብዙ ባሮች ነፃ ወጥተዋል ብሎ ስለ ነገረን ፣ በዐዋጅና በደንብ ነፃ ለወጡት አንተ ልትመሰገን አትችልምና በፈቃድህ ብትለቅ ያስመሰግንሃል ብንለው ፤ይህን ያህል ባሮች ነፃ እንዲወጡ ፈቅጄ ነው ስላለን ፣እንግዲያውስ ወደ አዲስ አበባ ላካቸውና እንዲማሩ እናደርጋለን አልነው። እነዚያም ባሮች ወደ አዲስ አበባ በተላኩ ጊዜ ለነፃነታቸው የምስክር ወረቀት እንዲቀበሉ አድርገን ፣ ወዲያው በወታደር ትምህርት ቤት ገብተው ይማሩ ጀመር። ከነዚሁም ብዙዎቹ ለሙዚቃ ትምህርት ተመርጠው ከስዋስ አገር ለማስተማር የቀጠርነው ሙሴ አንድሬኒኮ የሙዚቃ ትምህርት አስተምሮአቸው ነበርና ትምህርታቸውን ሲጨርሱ የወታደር ልብስ አልብሰን ንጹሕ የሆነ መኖርያ ቤት

አሥርተንላቸው ይኖሩ ነበር። ከመካከላቸውም በዕውቀት ለበለጠው ላንዱ የመቶ አለቅነት ማዕርግ ልብስ መስጠታችንንና ኒሻን መሸለማችንን ፣ ከርሱም ጋር ሌሎች የሙዚቀኝነት ሥራቸውን በትክክል እየሠሩ መኖራቸውን በአዲስ አበባ የሚኖሩ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና ቆንሲሎችም ሁሉ ያውቃሉ።

ይህንኑም የመቶ አለቅነት ማዕርግ የተቀበለውን ሻንቅላ ፡ ቁመቱ ሁለት ሜትር ከ10 ሳንቲ ሜትር ስለ ሆነ ፣ የሚያየውና የሚያውቀው ሁሉ ያደንቅ ነበር። አሁንም በግንቦት ወር 1928 ዓመተ ምሕረት ኢጣልያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ ይዘው እንደገደሉት ሰምተናል ።

ነገር ግን ከባርነት ነፃ አውጥተን ተምረው እንዲሠለጥኑ ባደረግን ፋንታ ኢጣልያኖች ሺሆጄሌ በተለየ ለንጉሠ ነገሥቱ የባሮች ግብር ላከላቸው ብለው ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ማቅረባቸው የሚያስገርም ነው።

ይህም የባርነት ነገር ከዚህ በላይ እንዳስረዳነው በልማድ ጸንቶ የቆየ ነበር እንጂ በፍጥረት ጌታና ባርያ ተብሎ የተለየ ነገር አለመኖሩ በሰው ልብ የታወቀ ስለመሆኑ፣ ከ1845ከ ፥ እስከ 1907 ዓ. ም. በኢትዮጵያ የነገሡት ዓፄ ቴዎድሮስ ፣ ዐፄ ዮሐንስና ዐፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ ባሮች እንዳይሸጡና እንዳይገዙ ዐዋጅ አድርገው ነበር። ነገር ግን በዚያ ዘመን ይህን ለመሰለው ሥራ ደንበኛ መሥሪያ ቤት አቁሞ መሥራት ስላልተለመደ ፡ አገሩም ሰፊ በመሆኑ ዐዋጁን ለመጠበቅና ለማስፈጸም የማይቻል ስለ ነበረ አሳባቸው ሳይፈጸም ቆይቶ ነበር።

አሁን ግን እኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነን የመንግሥቱን ሥራ አላፊነት ከተቀበልን በኋላ ስለ ባሮች ነፃነት ስማቸው ከዚህ በላይ የተጠራው ሦስቱ ነገሥታት የጀመሩትን መሠረት ተከትለን በኢትዮጵያ ባሮች እንዳይሸጡና እንዳይገዙ በ1917 ዓ.ም.መጋቀን ባዋጅ አስታወቅን። ከዐዋጁም አስቀድሞ በግዢም በምርኮም የመጡት ባሮች ነፃ የሚወጡበትን ፡ ወደ ፊትም ሲሸጡና ሲገዙ የሚገኙ ሰዎች የሚቀጡበትን ፡ደንብ አቁመን፡- ዐዋጁና ደንቡም የሚጠበቅበት በአዲስ አበባና በሌሎችም አውራጃች የጽሕፈትና የዳኝነት ቤቶች ተሠርተው ለዚሁ ሥራ አማካሪ ከእንግሊዝ አገር ሙሴ ደሐልቤርት የሚባል ተቀጥረን ዳኞችና ጸሐፊዎች እየተሾሙ የአስተዳደሩ ሥራ ሁሉ በጣም እየተሻሻለ ስለሔደ ብዙ ባሮች ነፃ ወጥተዋል። ቁሩጥራቸውም ከሙቶ ሺ በላይ ነው። ይኸውም ጄኔቭ በዓለም መንግሥታት ማኅበር መዝገብ ላይ በያመቱ ነፃ የወጣው ቁጥር ይገኛል ።

ደግሞ በእንግሊዝ አገር ከቆመው ከባሮች ነፃ ማኅበር የተላኩ ሰዎች ወደ አዲስ አበባ በ1923 ዓመተ ምሕረት በመጡ ጊዜ ፡ የዚሁኑ ነገር በብዙ ከተነጋገርን በኋላ ፣ ቢያንስ እስከ 15 ፡ ቢበዛም እስከ 20 ዓመት አሁን ያሉት ባሮች ሁሉ ነፃ እንዲወጡና የባርነት ነገር በጭራሽ ከኢትዮጵያ እንዲጠፋ እናደርጋለን ብለን በቃልም በጽሕፈትም አስታውቀናል። መቸም በማንም አገር ቢሆን አንዳንድ አጥፊ አይታጣምና ስለ ባርያ ነፃነት የተነገረውን ዐዋጅ ያፈረሱ አንዳንድ ሰዎች ቢገኙ እንኳን በሞት ቅጣት እንደቀጣናቸው የውጭ አገር ሚኒስትሮች ሁሉ ያውቃሉ። ስለዚህ በማናቸውም ቢሆን የባሮችን ነፃነት በሚቻለን ሁሉ ሳናቋርጥ ሠርተናልና ሕሊናችን አይወቅሰንም።

# ምዕራፍ 15

## አውሮጳን ለመጐብኘት ስለ ተደረገልን የክብር ጥሪ ።

ኢትዮጵያ ከሦስት ሺ የሚበልጥ ዘመን በነፃነቷ ጸንታ የኖረች መንግሥትናት። ነገር ግን በ16ኛው መቶ ዓመት መጀመርያ አሕመድ ግራኝ የሚባል ከኢትዮጵያ ምሥራቅ ከዘይላ ተነሡቶ ወደ መሃል ኢትዮጵያ ገብቶ ከዐፄ ልብነ ድንግል በተዋጋ ጊዜ እርሳቸው ወደ ኢትዮጵያ ሰሜን እያፈገፈጉ ይዋጉ ነበርና እርሱ ቤተ መንግሥቱንና ቤተ ክርስቲያኑን ሁሉ ሲያቃጥል ፡ በየዋሻውና በየደሴቱ ተደብቀው ከተረፉት ከጥቂቶች መጻሕፍት በቀር የሚበዙትን የታሪክና የጥበብ መጻሕፍት አቃጠላቸው።

ቢሆንም የኢትዮጵያን ጥንታዊነት ለማወቅ የሚፈልግ ሰው ቢኖር በግሪክና በላቲን በፖርቱጊዝና በዐረብ ቋንቋ የተጻፉ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚናገሩ ብዙ መጻሕፍት ይገኛሉና እነዚያን እያነበበ ጥንታዊነቷን ለመረዳት ይችላል። ከጌታችን ልደት በፊት ከኢየሩሳሌምና ከግሪክ ፡ ከዐረብና ከምስር አገሮች ብዙ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንደ ነበረ እርግጥ ነው። ከጌታችንም ልደት በኋላ ከ15ኛው መቶ ዓመት እስከ 18ኛው መቶ ዓመት አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች እየመጡ ኢትዮጵያን መጐብኘታቸው አልቀረም ነበር። ;

ኢጣልያኖችም በኢትዮጵያ ላይ ዓይናቸውን መጣል የጀመሩት በዚሁ በ19ኛው መቶ ዓመት ነው።

ከኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ወገን ወደ ውጭ አገር የሔዱ ብዙ ናቸው ። ከቤተ መንግሥት ወገን ግን አባቴ ልዑል ራስ መኰንን በ1881 ዓ. ም. ወደ ኢጣልያ ፣ በ1894 ዓ. ም. የእንግሊዝ ንጉሥ ግርማዊ ኤድዋርድ 7ኛ በነገሥ ጊዜ ወደ እንግሊዝ አገር ሔደው ነበር። በዚሁም ዓመት እግረ መንገዳቸውን ወደ ፈረንሳይ አገር መጥተው ጐብኝተዋል። ሌሎችም መኳንንቶች ወደ ጀርመንና ወደ መስኮብ ወደ ፈረንሳይና ወደ ቱርክ አገሮች እየተላኩ ሔደዋል።

በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በሙሉ አውሮጳ የታወቀች ስለሆነችና ዐፄ ምኒልክ ከየመንግሥታቱ ጋራ የወዳጅነትና የንግድ ውል ስለ ተዋዋሉ ብዙ የውጭ አገር ነጋዴዎችና መንገደኞች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣታቸው ምክንያት ከዚህ በላይ ስማቸው የተጠራው መንግሥታት በአዲስ አበባ ቆንስላና ሌጋሲዮን ማቆም ጀመሩ።

ከዚህም በኋላ በ1909 ዓመተ ምሕረት ንግሥት ዘውዲቱ በዙፋን በተቀመጡ ጊዜ እርሳቸው ወራሽ ልጅ ስለአልነበራቸው ፣ እኔ በእግዚአብሔር ፈቃድና በሕዝብ ውዴታ ተመርጬ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ስለ ሆንሁ ፣ በዐፄ ምኒልክ ጊዜ የተጀመረው የአውሮጳ መንግሥታት ወዳጅነት በጣም እንዲሰፋና እየጠና እንዲሔድ ሙሉ ፈቃድ አደረግሁ። ይህም አሳቤ እርግጠኛና እውነተኛ መሆኑን የአውሮጳ መንግሥታት አዲስ አበባ ባሉት ሚኒስትሮቻቸው በኩል ስለ ሰሙትና ስለ ተረዱት ፣ መጀመሪያ የፈረንሳይ ሬፐብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ሙሴ ፔዋንካሬ ፡ ቀጥሎ የቤልጅክ ንጉሥ ግርማዊ አልቤርት ፡ ቀጥሎ የኢጣልያ ንጉሥ ግርማዊ ቢክቶር አማኑኤል ፡ ቀጥሎ የእንግሊዝ ንጉሥና የህንድ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ጆርጅ 5ኛ ፡ ቀጥሎ የምስር ንጉሥ ግርማዊ ፉዓድ 1ኛ ፡ ቀጥሎ የግሪክ ሬፐብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን አሚራል ኮንቶሪዮቲስ ፡ ቀጥሎ የሉክሳምቡርግ ዱሼስ ሻርሎት በያገራቸው እየሔድን ያገራቸውን ልማት የሕዝባቸውን ሀብትና ብልጽግና የከተማቸውን ውበት የሊ.ቃውንቶቻቸውን ጥበብና ዕውቀት እንድናይ የክብር ጥሪ አደረጉልን ።

ነገር ግን ከዚህ በላይ እንዳስረዳነው አንዳንድ መኳንንት እየተላኩ ወደ አውሮጳ መጥተው ነበር እንጂ ፣ አልጋ ወራሽና የመንግሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የሆነ ወደ ውጭ አገር ወጥቶ ለመሔድ የተለመደ ነገር አልነበረምና ይህ የአውሮጳ መንግሥታት ያደረጉልን የክብር ጥሪ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለሠራዊቱም ሁሉ እንግዳ ነገር ስለ ሆነባቸው ፣ በነገሩ ተቸግረውበት ነበር። ይህንኑም በሰማን ጊዜ መሳፍንቱና መኳንንቱ በትልቅ ጉባኤ እንዲሰበሰቡ አድርገን ከአውሮጳ መንግሥታት ጋራ ወዳጅነታችንን እያሰፋን ለመሔድ በማሰባችን የወዳጅነትም ምልክቱ እርስ

በርሱ መገናኘትና መተዋወቅ በንግድና በሥራም ሕዝቡ እንዲገናኝ ማድረግ ፡ ለዚህም ሁሉ ዋናው ነገር ነገሥታቱና የነገሥታቱ ዘሮች ቃል ለቃል እየተነጋገሩ መቀራረብ ፡ እነርሱም መጥተው አገራችንን እንዲጐበኙ ማድረግ መሆኑን ስለ አስረዳናቸው ሁሉም ነገሩን በደስታ ተቀበሉት።

ይህም የአውሮጳ መንገዳችን ነገር በጉባኤው ቀርቦ ከተቆረጠ በኋላ ለመንገዳችን የሚያስፈልገው ሁሉ እንዲሰናዳ አዘዝን። ለመንግሥቱም ሥራ የጦር ሚኒስትራችን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዋና ሆነው ፡ ሚኒስትሮቹ ሁሉ ለየክፍላቸው ሥራ አላፊ እየሆኑ እንዲሠሩ ፣ የሠሩትንም ሁሉ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ እንዲያስታውቁ ደንቡን ሰጠናቸው።

የአውሮጳ መንገዴ ለእኔ ሦስት ጥቅም የሚሰጠኝ መሆኑን ተረድቼና ተስፋ አድርጌ ነበር። 1ኛው ጥቅም ቀድሞ በትምህርት ቤት ፣ ኋላም በሹመት ላይ ሳለሁ በመጽሐፍ ያነበብሁትን የአውሮጳን ሕዝብ ሥልጣኔ ፡ የፓሪስን ፡ የሎንዶንን ፡ የሮማን ፡ የብሩክሴልን ፡ የአቴናን ፡ የካይሮን ከተሞች ውበት በዓይኔ ለማየት ፡ 2ኛው ጥቅም አውሮጳን አይቼ ወደ ሀገሬ ስመለስ ምንም በቶሎ በሙሉ ለመሥራት ባይቻል እንኳ በዓይኔ ከማየው የሥልጣኔ ሥራ አንዳንዱን ለመጀመር ይቻላል በማለት ነው። 3ኛው አንድ የባሕር ጠረፍ ለማግኘት ነው። ስለ ባሕር ጠረፍ ከፈረንሳይና ከኢጣልያ ከመንገዳችን በፊት ተስፋ ተቀብለን ነበር።

ከዚህም በኋላ በሚያዝያ 8 ቀን 1916 ዓ. ም. ኀሙስ ከአዲስ አበባ ተነሥተን ወደ ጅቡቲ ወረድን። እኛንም ለመከተል የተፈቀደላቸው መሳፍንትና መኳንንት ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው። ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ፣ ራስ ሥዩም መንገሻ ፣ ደጃዝማች ናደው አባወሎ ፣ ደጃዝማች ገሠሠ ወልደ ሐና ፣ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር ፣ ደጃዝማች ሙሉጌታ ይገዙ ፣ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ ፣ ሊጋባ ወዳጄ ውቤ ፣ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፣ ልጅ መኰንን እንዳልካቸው ፣ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ፣ አቶ ሣህሌ ፀዳሉ ናቸው ።

ጅቡቲም ስንደርስ የጅቡቲ አገረ ገዥ ሙሴ ሊያ የክብር አቀባበል ካደረጉልን በኋላ በሚያዝያ 12 ቀን ፖርቶስ በሚባል በሜሳጅሪ ማሪቲም ኩምፓኒያ መርከብ ተሳፍረን ወደ ስዊዝ ካናል ተጓዝን ።

በስዊዝ ካናል ስንደርስ የግርማዊ ንጉሥ ፉዓድ መልክተኛ መጥቶ የንጉጮን ሰላምታ ነገረን። ፓትሪያርኩም አቡነ ቄርሎስ በኋላ ፓትሪያርክ የሆኑትን አቡነ ዮሐንስን ልከው በረከታቸውን ሰጡን ።

ገንጠራም ስንደርስ ግርማዊ ንጉሥ ፉዓድ ባዘጋጁልን ልዩ ባቡር ሆነን ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዝን። በኢየሩሳሌምም የእንግሊዝ መንግሥት ሐይ ኮሚሽነር ሰር ሔርቤርት ሳሙኤልና የየገዳማቱ ጳጳሳት ወደ ባቡር መቋሚያ መጥተው የክብር አቀባበል አደረጉልን ።

ደግሞ እንደ መልካም የዕድል አጋጣሚ ፡ የትንሣኤ በዓል ቀርቦ ነበርና ብርሃነ ትንሣኤውን ለማየት ስለ አበቃን እግዚአብሔርን አመሰገንን ። ከዚህም በኋላ በኢየሩሳሌምና በአውራጃዎቹ እየተዘዋወርን የተቀደሱትን ስፍራዎች ሁሉ ጌታችን የተወለደበትን ቤተ ልሔምን ፡ ያደገበትን ናዝሬትን ፡ የተጠመቀበትን ዮርዳኖስን ፡ ታምራት ያደረገበትን ቃና ዘገሊላን ፡ያስተማረበትን ባሕረ ጥብርያዶስንና በዙሪያው ያሉትን ቅፍርናሆምን ፡ ቤተ ሳይዳን ፡ መግደላን ፡ አብርሃምና ይስሐቅ ያዕቆብም የተቀበሩበትን ኬብሮንን ጐብኝተን ተሳልመን ተመለስን። በኢየሩሳሌምም ያለውን የገዳማችንን ነገር ከሃይማኖት አባቶቻችን ከግብጻውያን ጋራ ለመነጋገር ተጀምሮ ሳይጨረስ ቆይቶ ነበርና ከአውሮጳ ስንመለስ በወዳጅነት ተነጋግረን ነገሩን እንድንጨርስ ስለ አሰብን ይህንኑ አሳባችንን መክረውበት እንዲቆዩ በኢየሩሳሌም ላሉት ለግብጹ ሊቀ ጳጳስ ለአቡነ ጢሞቴዎስ በጽሕፈት አስታወቅናቸው። እርሳቸውም ይህንን አሳብዎን ለግብጽ ማኅበር አመልክቼ እቆያለሁ የሚል ምላሽ ጻፉልን።

ከዚህም በኋላ ግሪኮች በጎልጎታ ውስጥ ብዙ ክፍል ቦታ አላቸው ማለትን ስለ ሰማን ከዚሁ አንድ ክፍል ለኢትዮጵያ መነኩሳት መቀደሻ ርስት አድርገው እንዲሰጡልን አዲስ አበባ በሚኖረው በግሪክ ቆንሲል ጄኔራል በዶክቶር ዘርቦስ በኩል በኢየሩሳሌም ያሉትን የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ አቡነ ድምያኖስን ብንጠይቅ የአብርሃም

ገዳም ከሚባለው አንድ ክፍል ርስት አድርገን እንሰጣለን ስላሉ እኛም በበኩላችን ለግሪክ ገዳም ጥቅም የሚሆን ቦታ ኢትዮጵያ ላይ እንሰጣለን ብለን በአሳቡ ተስማምተንና ተዋደን ቀጥሎ ያለውን ውል ተጻጽፈን ተፈራረምን።


«የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ባንድ.ወገን በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ሆነው የኢየሩሳሌም ፓትሪያርክ ድምያኖስ በሁለተኛው ወገን በግሪክ ኦርቶዶክስ ማኀበር ስም ሆነው ከዚህ በሚከተለው ተስማምተው ተዋውለዋል ፡፡ ፡፡

## መጀመሪያ ፡

ብፁዕ ድምያኖስ የኢየሩሳሌምና የፓለስቲና ሁሉ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ እንደ መሆናቸው ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በመምጣታቸው ምክንያት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም የሆነ ታላቅ አሳባቸውንና ከቀድሞ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢየሩሳሌም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መካከል ጸንቶ የሚኖረውን ወዳጅነት ለመግለጥ ሲሉ በአብርሃም ቅዱስ ገዳም ውስጥ በቅዱስ መቃብር ቤተ ክርስቲያን አጠገብያለውን አንድ ክፍል ቤት በጭራሽ ርስት አድርገው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰጥተዋል ፡፡



የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ የንግሥ በዓል ጊዜ።



ንግሥት ዘውዲቱ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሲመለከቱ።

የቤቱ ክፍል ርዝመቱ 18 ሜትር ከ70 ሳንቲም ነው።

ወርዱ 8 ሜትር ከ 95 ሳንቲም ፣ ቁመቱ 4 ሜትር ከ 95 ሳንቲም ነው። ይኸው ከአባቶች የምግብ ቤት በታችና አጠገብ የምድር ቤት ወለል ሆኖ ጠንካራ ቅስት ያለው ፡ የቀድሞ በሩ ቅዱስ መስቀል ወደ ተገኘበት የሚወስድ ነው። ይህም የቤት ክፍል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለቤተ ክህነት ሥራ ለሚያስፈልጋቸው ማገልገያ እንዲሆን ተሰጥቷል ።

ሁለተኛ ፡

ይህም የቤት ክፍል ከዴር ኤል ሥልጣን ጋራ ባንድ በር ተገናኝቶ ሊያያዝ ነው። በሩንም የሚያስከፍቱየኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው፡ፓትረያርኩም ይህ በር እንዲከፈት እርዳታቸውን ያደርጋሉ ።

ሦስተኛ ፡

ወደ አብርሃም ገዳም የሚወስዱት የፊተኞቹ ሁለት በሮች ይዘጋሉ ፡ መስኮቶቹ ግን አይዘጉም።

አራተኛ ፡

ይህን የቤት ክፍል ለመሸጥና ለመለወጥ መያዣም አድርጎ ለመስጠት ወይም በላይ ከተነገረው ከቤተ ክህነት ሥራ በቀር ለማናቸውም ለሌላ ጉዳይ ለማድረግ አልተፈቀደም።

አምስተኛ ፡

ይህ የቤት ክፍል በሚታደስበት ጊዜ አስቀድሞ ለፓትረያርኩ ማስታወቅ ያስፈልጋል። ፓትረያርኩም ለዚሁ ሥራ ዐዋቂ የሆነ ይልካሉ።

ስድስተኛ ፡

ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተሰጠው የቤት ክፍል ተፋላሚ ሌላ ሰው የመጣ እንደሆነ ብፁዕ ፓትሪያርክ በነገሩ ገብተው ለመነጋገር አላፊነት አለባቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንን በኢትዮጵያ ሕዝብና በፓትሪያርክ መካከል ያለው ወዳጅነት እንዲጸና ስለፈለጉ የፓትሪያርክ ወኪል ዘወትር በኢትዮጵያ እንዲኖር ከዚህ የሚከተለውን ስጦታ ለመስጠትና ስጦታውም እንደ ሀገሩ ልማድ በፓትሪያርኩ ስም በመዝገብ እንዲጻፍ ፈቅደዋል።

የሚሰጠውም ስጦታ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

1ኛ፣ ለገዳሙና ለቤተ ክርስቲያኑ መኖሪያ የሚሆን የሚታረስ ምድር ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ ርቀቱ ከአንድ ቀን መንገድ በማይርቅ ስፍራ አምስት ጋሻ መሬት፣

2ኛ ፡ ለገዳሙና ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ በአዲስ አበባ ዙሪያ በጉለሌ ወይም በሸላ ወገን አንድ ጋሻ መሬት ይሰጣሉ። እነዚህም ስድስቱ ጋሻ መሬቶች በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ኦርቶዶክስ ላልሆነ ማኅበርና ኦርቶዶክስ ላልሆነች ቤተ ክርስቲያን ተላልፈው እንዳይሰጡ ተስማምተዋል።

ሰባተኛ ፡

እነዚህንም ስጦታዎች የተሰጣጡ ሁለቱም ወገኖች ይህን ውል ከሁለት ላይ በትክክል አስጽፈው ማኅተማቸውን አትመው የእጃቸውን ፊርማ አድርገውበታል። ሚያዝያ 16 ቀን 11916 ዓ. ም. በኢየሩሳሌም ሀገር ቅድስት ተጻፈ። »

ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሳይሆን ቀርቶ ይህ ውል ወደ ፍጻሜ አልደረሰም።

በኢየሩሳሌምም ያለውን ጉዳያችንን ከጨረስን በኋላ በሚያዝያ 23 ቀን በባቡር ተሳፍረን ወደ ካይሮ ወረድን ፡ በካይሮም ግርማዊ ንጉሥ ፉዓድ በቤተ መንግሥታቸው የክብር አቀባበል አደረጉልን። ከቀድሞ ጀምሮ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ጸንቶ የኖረውን ወዳጅነት ወደፊት እያሰፋን ለመሔድ ሁለታችንም እየገለጥን በመነጋገራችን ደስታችን ከልክ ያለፈ ሆነ።

በማግስቱም ፓትሪያርኩ አቡነ ቁርሎስ ስለ እኛ ክብር በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴና ጸሎት ለማድረግ ማሰባቸውን አስታውቀውን ነበርና ወዶ ቤተ ክርስቲያኑ ሔድን። ፓትሪያርኩም የሽምግልና ድካማቸውን ታግሠው በመንበሩ አጠገብ በዙፋናቸው ተቀምጠው ጸሎተ ቡራኬ አደረጉልን። ወዲያውም የግብጽና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እናትና ልጅ መሆናቸውን እርሳቸውም ከብዙ ዘመን ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሃይማኖት ልጆቻቸውን ለማየት ምኞትና አሳብ ስላላቸው ስለመንገዱ መራቅ ሳይችሉ በመቅረታቸው ማዘናቸውን ፡ ዛሬ ግን እኛ ወደ ካይር መጥተን በዓይናቸው በማየታቸው ምኞታቸውና አሳባቸው መፈጸሙን እየገለጡ በረጅሙ ተናገሩ።

ከዚህም በኋላ እኛ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዳለን እርሳቸው ባንድ ወገን ወደ እንግዳ መቀበያው ቤት ገብተው እኛ የሃይማኖት አባታችንን ለማክበር የወርቅ አክሊልና የወርቅ መስቀል ፡ የወርቅ መቋሚያ በወርቅ የተጠለፈ ግምጃ ቀሚስና ፡ካባ ላንቃ አምጥተንላቸው ነበርና በዕድሜ በመሸምገላቸውና በመድከማቸው ምንም እንኳ የማይችሉት ቢሆኑ እኛን ደስ ለማሰኘት ሲሉ አክሊሉን ደፍተው ካባ ላንቃውን ለብሰው ፡ የወርቁን መስቀል በቀኝ እጃቸው ፡ የወርቁን መቋሚያ በግራ እጃቸው ይዘው ፡ ይጠብቁን ነበርና ከቤተ ክርስቲያኑ ወደ አዳራሹ በገባን ጊዜ ቆመው ለመቀበል ቢሞክሩ የማይችሉ ሆኑ። እኛም ቅዱስነታቸውን ይህን በመሰለ ማዕርግ በማየታችን ምንም በልባችን ደስታ ብናደርግ መሸምገላቸውንና መድከማቸውን በማሰባችን ትልቅ ኀዘን ሆነብን።

በካይሮም በቆየንበት ጊዜ የጐበኘናቸውና ለልባችን መታሰቢያ ሆነው የሚኖሩት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው። ፒራሚዶችና እስፊንክስ ፡ ትልቁ የአንቲካ ቤት ፡ የመንግሥትና የግብፆች ትልልቅ የትምህርት ቤቶች ሆስፒታሎች ፡

የቀድሞ ዘመን አርጉ ገዳሞች ፡ የሉክሶር አንቲካና ባጠገቡ ተቆፍሮ የተገኘው የቱታንካሙን መቃብር ትልልቅ መስጊዶችና አልሐዛር የሚባለው ትልቁ የእስላሞች ትምህርት ቤት ናቸው። ቀጥሎም ከኢትዮጵያ የመጡ አራት ተማሪዎች ሲማሩ በማየታችንና እስከ ሁለት ዓመት ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ኢትዮጵያ ይመለሳሉ ብሎ አስተማሪያቸው ስለነገረን ደስ አለን ።

ከካይሮም ወደ እስክንድርያ ወርደን የቅዱስ ማርቆስን መቃብር ከተሳለምንና በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የመንበረ ማርቆስ ወኪል ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ዮሐንስ አሥርተው ከአራት ሺ የሚበልጡ ልጆች የሚያስተምሩበትን የትምህርት ቤቱን ካየን በኋላ ፣ በእስክንድርያ አጠገብ ራምሌ በሚባል ስፍራ የተሠራውን ፣ የኢትዮጵያ ልጆች እየመጡ የሚማሩበትን ቢክቶሪያ ኮሌጅ የሚባለውን የትምህርት ቤት ጐበኘን። የትምህርት ቤቱ አለቃ ምስተር ሪድ የሚባለው በተለየ ከኢትዮጵያ የሚመጡትን ልጆች እንደ አባት ሆኖ በርኅራኄ መጠበቁንና ማስተማሩን ስንሰማ ነበርና እነሚራክ ኅሩይን በዚያው አገኘናቸው። እነርሱንም በዓይናችን በማየታችን ልባችን በደስታ ተነካ። ወዲያውም የራስ ሙሉጉታ ልጅ ዐሥራተና ገብረ መድኅን ዐወቀ የሚባለው በዚሁ ትምህርት ቤት ለመማር ከእኛ ጋራ መጥተው ነበርና አደራ በማለት ሰጠነው።

# ምዕራፍ 16

## ከእስክንድርያ ወደ ፓሪስ ስለ መሔዳችን ።

በግንቦት 1 ቀን ኮርዲሊየር በሚባል መርከብ ተሳፍረን መርከቡ ጕዞ ሲጀምር የመሰናበቻ መድፍ ይተኰስ ጀመር።

በግንቦት 6 ቀን ኮርሲካን አልፈን ቱሎን በሚባለው ትልቅ ምሽግ ባለበት አኳያ ስንደርስ ፣ አንድ የጦር መርከብ መጥቶ ተቀበለን። ከዚያም ጀምሮ ወደ ማርሴይ እስከንጠጋ ድረስ ብዙ አይሮፕላኖች በአየሩ ላይ ያንጃብቡ ነበር። በመርከባችንም ቀኝና ግራ 5 የጦር መርከቦች እየተጓዙ መድፍ ይተኩሱ ነበር ።

ከመርከብም ስንወርድ የማርሴይ አውራጃ ገዥና የከተማው ከንቲባ ከብዙ መኳንንቶች ጋራ ሆነው ተቀበሉን። ከነዚሁም መካከል ከአባቴ ከልዑል ራስ መኰንን ጀምሮ የኢትዮጵያና የእኛም የራሳችን ወዳጅ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ልዩ መልክተኛ የነበሩትን ሙሴ ላጋርድን በማየታችንና በመገናኘታችን በጣምደስ አለን።

በማርሴይም ቤተ መንግሥት ጥቂት ካረፍን በኋላ የጦር መርከቦች አለቆች መጥተው የጦር መርከቦችን ለማሳየት እንደገና ወደ ባሕሩ ወስደውን ነበርና የሥራውን ጠንካራነት ፡ የመድፎቹን ትልልቅነት አይተን በታላቅ ማድነቅ ተመለስን።

በማግስቱ በግንቦት 8 ቀን ማታ በባቡር ተሳፍረን ወደ ፓሪስ ተጉዘን ነበርና ጧት በ4 ሰዓት ተኩል ፓሪስ በደረስን ጊዜ አዲሱ የሬፑብሊክ ፕሬዚዳን ክቡር ሙሴ ሚሌራና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሙሴ ፔዋንካሬ ሚኒስትሮቹም ሁሉ በሙሉ ማሬሻል ፎሽና ሌሎቹም ብዙ ጀኔራሎች በታላት ክብር ተቀበሉን። ለማደሪያም የተዘጋጀልን በውጭ ጉዳይ ሜኒስቴር ቤተ መንግሥት በኬደርሴ ነበርና ከፕሬዚዳኑ ጋራ ባንድ አውቶሞቢል ተቀምጠን በሰልፉ መካከል ሔድን።

በቤተ መንግሥቱም ጥቂት ዕረፍት ካደረግን በኋላ ለሬብሊክ ፕሬዚዳን ጕብኝት ለመመለስ ወደ ኤሊዜ ቤተ መንግሥት ሔደን ተመለስን ።

ከዚህም በኋላ የፓሪስን ማዘጋጃ ቤት እንድንጐበኝ ፕሮግራም ተደርጎ ነበርና በተወሰነው ሰዓት ወደ ማዘጋጃ ቤት ሔድን። በደረስንም ጊዘ የሬ" ብሊኩ ፕሬዚዳንና ሜኒስትሮቹ ሁሉ የጦር አለቆችና የከተማውም ትልልቅ ሰዎች ተሰብስበው አገኘናቸው። ወደ ትልቁም አዳራሽ በገባን ጊዘ የከተማው ከንቲባ ሙሴ ጭዊላርድና የማዘጋጃ ቤቱ አማካሪዎች ፕሬዚዳን በጣም ልባችንን የሚነካ የወዳጅነት ቃል እየተናገሩ ደስታቸውን ገለጡልን።

በፓሪስና በዙሪያዋ ያየነው የሚያስደንቀው ሥራ ሁሉ ብዙ ነው ። ግን በፓሪስ በቆየንበት ጊዜ ካየናቸው ከብዙዎቹ ዋነኞቹ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው። የናፖሊዎን መቃብር (አንቫሊድ )) የአይሮፕላን ማረፊያና የአይሮፕላን ሰልፍ፥የታንክ ሰልፍና አካሔድ ፡ኦፔራ፡ ኖትርዳም ደ ፓሪ፣ የፍርድ ቤት ፡ የብር መኪና ቤት ፡ (የዳግማዊ ምኒልክ መልክ ያለበት ብር የተሠራው በዚሁ ቤት ነው)። የሌጅዎን ደ ኦነር ኒሻን ጽሕፈት ቤት ፣ ቱር ኤፊል ፡ የቬርሳይ ቤተ መንግሥት ፡ የፎንቲኔብሎ ቤተ መንግሥት ፡ በሰንት ኤሊዜ ያለው የራዲዮ መሰብሰቢያ ቤት ፡ የመድፍ ተኩስ መማሪያና የመድፍ ዒላማ ነው።

የኦፊሴሉ ቀን እስኪጨረስ ከሬፐብሊኩ ፕሬዚዳን ከክቡር ሙሰ.ሚሜሌራ ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሙሴ ጥዋንካሬና ሌሎቹም የፈረንሳዊ ባለሥልጣኖች ባቀባበልና በግብዣ ጊዜ የሚናገሩትን የወዳጅነት ንግግር

በመስማታችንና ከዚህም በላይ የቆጠርናቸውን ልዩ ልዩ ቤተ መንግሥታት በማየታችን የልባችን ደስታ ስለ በዛ በቃል ሊነገር የማይቻል ሆነ።

የኦፊሴሉም እንግድነታችን ሲጨረስ በዚያው በፓሪስ ቆይተን ከፈረንሳዊ መንግሥትና ከፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩምፓኒያ ጋራ አንዳንድጉዳይ በወዳጅነት ለመነጋገር ስለ አሰብን ፤ሁለተኛም የክብርጥሪ ወደ አደረጉልን ወደ ሌሎቹ መንግሥቶች እየሔድን የኦፊሴሉ ቀን ሲጨረስ እየተመለስን የምናርፍበት በፓሪስ እንዲሆን ስለ ፈቀድን በኪራይ ማረፊያ ቤት ፈልገው እንዲያዘጋጁልን ለወዳጃችን ለሙሴ ላጋርድ አስታውተናቸው ነበርና በፓሪስ ከተማ ዳር ቢላ ካማስተራ የሚባል ቤት መዘጋጀቱን

ስላስታወቁንና አሁን የኦፊሴሉም ቀን ስለ ተጨረሰ ወደዚያው ሔደንገባን። የኦፊሴሉም ቀን መጨረሱ በተሰማ ጊዜ ፣ ለትምህርት ወደ ፈረንሳይ አገር የላክናቸው የኢትዮጵያ ልጆች ተሰብስበው መጥተው ተገናኙን ። ከመካከላቸውም አንዳርጌ መሳይ በሁሉም ስም ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የምስጋና ቃል ተናገረ

«ልዑል ሆይ ፣ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን በቀድሞ ዘመን በጥበብም በጉልበትም ከዓለም ሁሉ መብለጣቸውን፥ ከተማቸውንም በመርዊዌና በናፓታ አድርገው ኃይላቸውን እስከ ምድረ ግብጽ እያሰሙ ተከብረውና ተፈርተው መኖራቸውን የውጭ አገር ታሪክ ን ጽፈውት በማግኘታችንና በማንበባችን በልባችን ኩራት ይሰማናል

ባገራችን ግን መጻሕፍቶቻችን ሁሉ የተጻፉ ት በግእዝ ቋንቋ ስለ ሆነ፡ የማተሚያ ብልሃትም ስላልነበረ ካንዳንድ ሊቃውንቶች በቀር ሕዝቡ ሁሉ ያገሩን ታሪክ ባለማወቁ በጣም ያሳዝነናል

አሁን ደግሞ በደግነትዎና በትጋትዎ ኢትዮጵያ እንደ ጥንቷ በጥበብና በዕውቀት እንድትሠለጥንና ዓይንዋን እንድትከፍት አስበው እኛን ለትምህርት ወደ ውጭ አገር በመስደድዎ ፡ በአዲስ አበባና በሌላውም አውራጃ የትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ በማድረግምዎ፡። የመጽሐፍ ማተሚያ አቁመው በግእዝ ቋንቋ የተጻፉትን የቀድሞ መጻሕፍት ባማርኛ ቋንቋ እያስተረጐሙ በማሳተምዎና ለሕዝቡ እንዲታደል በማድረግዎ ዓለሙ ሁሉ ተደንቋል ።

እኛም ልጆቿ የአውሮጳን ሥልጣኔ እንድንከተል ፡ የኢትዮጵያንም ታሪክ እንድናውቅ በችግራችን ሁሉ እየረዱ እንድንማር ስለ አደረጉ ባለማቋረጥ ስናመሰግንዎ እንኖራለን። አሁን እንኳ የአውሮጳ መንግሥታት ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ነገሥታት ለማንም ያላደረጉትን የማክበር ጥሪ መጥራታቸው በመልካም መሪነትዎ ኢትዮጵያን እንዲያሠለጥኗት ስለ ዐወቁ ነውና መምጣትዎ የኢትዮጵያ ስም በዓለም ሁሉ እንዲሰማ አደረገ።

ኢትዮጵያ ያሁኑ ብቻ ደስታዋ ለልጅ ልጅ አልፎ ሲነገር የሚኖርነውና ልታመሰግንዎ ይገባታል። እኛም በፓሪስ ከተማ ሦስት ቀለም ሰንደቅ ዓላማችን ተሰቅሎ ሲውለበለብ በማየታችን በጣም የታደልን መሆናችንን ያስረዳናል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የሞቱት በሰማይ የቆሙት በምድር ሆነው ሊያመሰግኑም ይገባቸዋል » እያለ በረጅሙ ተናገረ።

ለዚህም ለተናገረው ቃል መደገፊያና ተስፋ እንዲሆናቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናግረን አረጋገጥንላቸው።

«እኛ አሳባችን በሚቻለን ሁሉ እየረዳን የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ትምህርትና ዕውቀት እንዲያገኙ ነው እንጂ ለናንተ ለጥቂቶቹ ብቻ አይደለም ። እናንተም በትምህርታችሁ ተግታችሁ ሙሉ ዕውቀት አግኝታችሁ ሀገራችሁን ኢትዮጵያን ለማገልገል እንዲያበቃችሁ እግዚአብሔርን እንለምናለን። ወደ ፊትም ትምህርታችሁን እስክትጨርሱ ማናቸውም የገንዘብ ችግር እንዳያገኛችሁ በሚቻለን ሁሉ እንረዳችኋለንና አይዚችሁ» ስላልናቸው ከልብየሆነ ደስታቸውን ገለጡልን ።

የኦፊሴሉም ቀን ስለ ተጨረሰና በልዩ ቤት ስለ ተቀመጥን የኢትዮጵያ መንግሥትና በተለየም የልዑል አባቴና የራሴም ወዳጆች የሆኑት ትልልቆች የፈረንሳይ ሰዎችእየመጡ ጒብኝት ያደርጉጀመር። ከዚህም በኋላ ከጠቅላይ

ሚኒስትሩ ከሙሴ ኾዋንካሬ ጋራ በወዳጅነት አንዳንድ ጉዳይ ለመነጋገር ቀጠሮ ጠይቀን ነበርና በቀጠሮው ቀን ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሔድን።

ለመነጋገርም ያሰብነው በጅቡቲ በኩል ነፃ የሆነ አንድ የባሕር በር እንዲሰጡን ካዲስ አበባ ከመነሣታችን በፊት ለዚህ በተለይ የምንነጋገርበት ጉዳይ መሆኑን በፈረንሳይ ምኒስትር በኩል አስታውቀን ተስፋ ተደርጎልን ነበርና ይህንም ለማድረግ የፈቀዱ እንደሆነ ከእኛም ወገን የፈረንሳይ መንግሥት ለዚህ ለውጥ የሚፈልገው ምን እንደ ሆነ እንዲያስታውቁን ነው።

ሁለተኛም የክሎቢኮቢስኪ ውል እየተባለ በሚጠቀሰው በኢትዮጵያና በፈረንሳይ መንግሥት መካከል በተደረገው የወዳጅነት ውል ይልቁንም በ7ኛው ክፍል የተጻፈው የዳኝነቱ ነገር በጣም አስቸጋሪ ሆኖብን ይኖራልና ውሉ ሳይፈርስ የሁለቱም መንግሥታት ጥቅም ተጠብቆ ጥቂት እንዲሻሻል ለማድረግ ነው።

ይህንም አሳባችንን ለሙሴ ኾዋንካሬ ባስታወቅናቸው ጊዜ ይህን አሳብዎን ለምክር ቤቱ አቅርቤ እንደተቻለ ያህል በወዳጅነት እናስብበታለን የሚል ቃላቸውን ሰጡን ።

# ምዕራፍ 17

## ከፓሪስ ወደ ብሩክሴል ስለ መሔዳችን ።

የቤልጅክ ንጉሥ ግርማዊ አልቤርት በኦፊሴል የሚቀበሉን በግንቦት 14 ቀን መሆኑን ፓሪስ ያለው የቤልጅክ አምባሳደር አስታውቆን ነበርና በዚሁ ቀን ወደ ማታ ከፓሪስ ተነሥተን ወደ ብሩክሴል ሔድን ።

በባቡር መቋሚያም ግርማዊ ንጉሥ አልቤርት ከሚኒስትሮቻቸውና ከጦር አለቆቻቸው ጋራ ሆነው ዘለዓለም የማይረሳ የክብር አቀባበል አደረጉልን።

ለማረፊያም የተዘጋጀልን ግርማዊነታቸው በሚኖሩበት በዋናው ቤተመንግሥት ባንድ ወገኑ ክፍል ነበርና ወደዚያ ገብተን ጥቂት ካረፍን በኋላ፣ ከንግሥቲቱ ከግርማዊት ኤልሳቤጥና በኋላ ንጉሥ ከሆኑት ከአልጋ ወራሻቸው ከልዑል ሊዮፖልድ ከሴቲቱ ልጃቸው ከልዕልት ማሪ - ፐሴ ጋራ አስተዋወቁን።

በራትም ግብዣ ላይ በቤልጅክና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ጸንቶ የቆየው ወዳጅነት ወደፊትም እየሰፋ እንዲሔድ ሙሉ ፈቃዳቸው መሆኑን እያረጋገጡ ገለጹልን ።

በብሩክሴልም በቆየንበት ጊዜ በብሩክሴልና በሌላውም በቤልጅክ አውራጃች ያየነውና መታሰቢያ ሆኖ በልባችን የሚኖረው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው። የብሩክሴል ማዘጋጃ ቤት ፡ የፈረስ እሽቅድድም ፡ የብሩክሴል ባንክ ፡ የኮንጎ አገር አንቲካ ቤት ፡ የእርሻ ማልሚያና የከብቶች ማርቢያ ስፍራ፣ናፖሊዎን ተዋግቶ ድል የሆነበት ወተርሉ፡ የጋን ከተማና የክብሪት ፋብሪካ ፡ የሊዩዥ ከተማና የጦር መሣሪያ ፋብሪካ ፡ የአንቬርስ ከተማ ፡ የሞራዥ ከተማ ፡ የደንጊያ ከሰል ማውጫ ፋብሪካ ፡ ሌላም ይህን የመሳሰለ መሥሪያ ቤት አይተናል።

## ከቡሩክሴል ወደ ሉክሳምቡርግ ።

የሉክሳምቡርግ መስፍኒት (ዱሼስ) ሻርሎት ገና ከአዲስ አበባ ስንነሣ የቤልጅክ ንጉሥ ግርማዊ አልቤርት ወደ ብሩክሴል መጥተን ጐብኝት እንድናደርግ መጥራታቸውን በሰሙ ጊዜ ፣ የእኔም አገር ለብሩክሴል በጣም ቅርብ ስለሆነ እግረ መንገድዎን አገሬን እንዲጐበኙልኝ ብለው ፡ አዲስ አበባ ባለው በቤልጅክ ሚኒስትር በሙሴ ፔራርድ በኩል አስታውቀውን ጥሪያቸውን ተቀብለን ነበርና ስለዚህ ከብሩክሴል ወደ ሉክሳምቡርግ ሔድን። በባቡር መቋሚያም የመስፍኒቱ ባል መስፍን (ዱክ) ፊልክስ በትልቅ ሰልፍና ክብር ከተቀበሉን በኋላ ወደ ቤተ መንግሥቱ ወሰዱን። ነገር ግን እንደ አጋጣሚ እኛ ሉክሳምቡርግ በደረስንበት ቀን መስፍኒቱ ወንድ ልጅ ስለ ወለዱ፣ በምሳ ግብዣ ጊዜ ከእኛ ጋራ ለመቀመጥ ባለመቻላቸው ኀዘናቸውን በመልእክት አስታወቁን። እኛም ሉክሳምቡርግ በደረስንበት በዚያ ቀን መስፍኒቱ ወንድ ልጅ መውለዳቸው በጣም የደስታ መታሰቢያ ሆኖ በልባችን የሚኖር መሆኑን እየገለጥን ለመስፍኑ ለልዑል ፊልክስ ነገርናቸው።

መስፍኑም እኛ ሉክሳምቡርግን በመጐብኘታችን ደስታቸውን እየመላለሱ ሲገልጡልን ከቆየን በኋላ ከመስፍኒቱ ጋራ በመልክት ተሰነባብተን ወደ ብሩክሴል ተመለስን።

በብሩክሴልም የኦፊሴል ቀን ስለ ተጨረሰ በግንቦት 23 ቀን ከንጉሥሥና ከንግሥቲቱ ተሰነባብተን ወደ ፓሪስ ተመለስን።

# ወደ ስዊድን ከተማ ወደ እስቶኮልም ፡ስለ መሔዳችን ።

ወደ አውሮጳ ከመጣን ዘንድ በአፊሴል ሳይሆን የአውሮጳን አገሮች በሙሉ ለመጐብኘት አሳብ ነበረን። ነገር ግን ወደ ሀገራችን የምንመለስበት ጊዜው ስለ ተቃረበ ፤ምንም እንኳ የአውሮጳን አገሮች በሙሉ ለመጐብኘት የማይቻል ቢሆን በአውሮጳ ሰሜን ያሉትን ባንድ ጊዜ አካሔድ ለመጐብኘት የሚመቹንን አገሮች ሆላንድን ፡ ጀርመንን ፡ ስዊድንን ፡ ለመጐብኘት ቁርጥ አሳብ አደረግን። በስዊድን ከተማ በእስቶኮልም ግን ሦስት ቀን ያህል ለመቆየት አሳብ ስለ ነበረን ፓሪስ ላለው ለስዊድን መንግሥት ሚኒስትር አስታውቀነው እርሱም ለመንግሥቱ ካመለከተና ካስፈቀደ በኋላ መንገዳችን ሁሉ እንዲቃና አደረገልን።

ከዚህም በኋላ በግንቦት 29 ቀን ከፓሪስ ተነሥተን በብሩክሴል አልፈን የሆላንድን ከተሞች ሮቱርዳምን ፡ላሄን እያየን አምስተርዳም ደረስን ። በአምስተርዳም ባቡራችን ሦስት ሰዓት ያህል ስለ ቆመ በአውቶሞቢል ከተማውን እየዞርን አየን። ከዚያም ሌሊቱን ሁሉ ስንሔድ አድረን ሲነጋ በጀርመን የወደብ ከተማ በሀምቡርግ ደርሰን አንድ ሰዓት ያህል ከተማውን እየዞርን ካየን በኋላ ወደ ስዊድን ተጓዝን። በጀርመንና በስዊድን መካከል ያለውን የሰሜን ባሕር የሚባለውን ተሻግረን በሰኔ 1 ቀን ከጧቱ በሦስት ሰዓት እስቶኮልም ከተማደረስን ።

እኛ እስቶኮልም በደረስንበት ቀን ንጉሥ ግርማዊ ጉስታፍ አዶልፍ ለዕረፍት ከሔዱበት ከባላገር ቤታቸው አልተመለሱም ነበር። ስለዚህም ግራንድ ሆቴል ሮያል በሚባል ሆቴል ገብተን ዐረፍን።

በዚሁም ቀን በዓለ ጳራቅሊጦስ ነበርና የኡፕሳላ ሊቀ ጳጳሳት ናታን ሳዲርብሎም መላክተኛ ልከው ስለ በዓለ ጳራቅሊጦስ ወደ ማታ ጸሎትና ስብከት እናደርጋለንና ለመምጣት ፈቃድዎ እንዲሆን እንለምናለን ስላሉን ከእስቶኮልም በ8 ሰዓት ተነሥተን በ10 ሰዓት ኡፕሳላ ደረስን። አገረ ገዥውና ሊቀ ጳጳሱም እስከ ባቡር መቋሚያ ወጥተው ተቀበሉን ፤ ጸሎትና ስብከት የሚጀምሩበት ሰዓት እስኪደርስ የኡፕሳላን ዩኒቨርሲቲና የመጻሕፍት ቤቱን አየን። በመጻሕፍት ቤቱም የግእዝና ያማርኛ መጻሕፍት በማየታችን በጣምደስ አለን ።

ጸሎትና ስብከት የሚጀመርበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሔድን። ሊቀ ጳጳሳቱም ከፍ ባለ ስፍራ ላይ ሆነው ስለ በዓለ ጳራቅሊጦስ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚያስፈልገውን እያወጡ ካነበቡና ረጅም ስብከት ካደረጉ በኋላ ስለ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ።

«ኢትዮጵያ ከእኛ አስቀድሞ ከብዙ ዘመን በፊት ክርስትናን መቀበሏ እርግጥ ነው። እኛም ስዊድኖች ክርስትናን ተቀብለን የክርስቶስ ቤተ ሰቦችና ማኅበሮች የሆንነው በዚያ በአፍሪቃ ከፍታ ላይ ከሚኖረው ከብርቱው ክርስቲያን በኋላ ነው። አሁንም ከዚያው ከከፍተኛው አፍሪቃ ለመጡት ለኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በፍቅር ሰላምታ ተቀባዮች መሆናችን የማይረሳ ዋና ነገር ነው» እያሉ በረጅሙ ተናግረው ሲጨርሱ በእውነት ተናጋሪነታቸው ልቤ በደስታ ስለ ተነካ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናገርሁ።

«ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ ሆይ ፤

በዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ምንም ባንዳንድ ትንንሽ ነገር ቢለያዩ መሠረታቸው አንድ ክርስቶስ መሆኑን የማያውቅ የለም። በቀድሞ ዘመን ስለሀገሩ ርቀት ስዊድንና ኢትዮጵያ በወሬ እንኳ አይተዋወቁም ነበር ። አሁን ግን አንዳንድ የስዊድን ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ከጀመሩ ወዲህ የሀገሩን መልካምነት የሰዎቹን ደግነት በቃላቸው ስለ ተናገሩ ፣ በሥራም ስለ አሳዩ ብዙ የኢትዮጵያ ሰዎች የስዊድንን አገር ለማየትና ከሕዝቡ ጋራ ለመገናኘት ይመኛሉ።

ኢትዮጵያ ከዛሬ ሺህ 600 ዓመት በፊት ክርስትና መቀበሏንና ታሪኳን የማያውቁ ብዙ ናቸው። እርስዎ ግን ታሪኳን ዐውቀው በደግነትዎና በእውነተኛነትዎ ኢትዮጵያ ከስዊድን አስቀድማ ክርስትና መቀበሏን ገልጠውና አስረድተው ስለ ተናገሩ ፡ በራሴና በኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ስም ሆኜ አመሰግንዎታለሁ። ዛሬም በዚህ በትልቁ በዓለ

ጳራቅሊጦስ ቀን ከስዊድን ሕዝብ መተዋወቄ የሁለቱ መንግሥታት ወዳጅነት እየጸናና እየሰፋ ለመሔዱ ዋና ምልክትይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» ብዬ ስጨርስ በዚያ የተሰበሰቡት ከሊቀ ጳጳሱ ጀምሮ ሕዝቡ ሁሉ ከልብ የሆነ ደስታቸውን ገለጡልን ።

ከዚህም በኋላ ወደ እስቶኮልም ተመለስን። ወደ እስቶኮልም የሔድነው በኦፊሴል ሳይሆን በግል ስለ ሆነ ከንጉሡ ጋራ ለመገናኘት አሳብ አላደረግንም ነበር። ንጉሥ ግን ወዲያው እስቶኮልም መግባታችንን ሲሰሙ እስከ እስቶኮልም መጥተው ብንገናኝ ደስ ይለኛል ብለው ልከው ነበርና ኦፊሴል ያልሆነ ጥሪያቸውን ተቀብለን ቶሊጋን ወደሚባለው የባሕር ዳር ቤተመንግሥት ሔድን። ንጉሥም ከባለሟሎቻቸው ጋራ በቤተ መንግሥቱ ደጃፍ ቆመው ሲጠብቁን ነበርና በሞቀ ፍቅርና በወዳጅነት ተገናኘን። በትልቁም አዳራሽ ጥቂት እንዳረፍን የምሳ ግብዣ ተደረገ ። ከምሳም በኋላ የሁለቱ መንግሥታት ወዳጅነት እየሰፋ የሚሔድበትን ፡ የሁለቱ መንግሥታትሕዝብ በጣም የሚቃረቡበትን ስንነጋገር ቆይተን ወደ ማታ በ11 ሰዓት ወደ እስቶኮልም ተመለስን ።

በእስቶኮልምና በዙሪያው ያየነው መታሰቢያም ሆኖ በልባችን የሚኖረው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው። ሰማኒያ ሺህ ማዞሪያ ያለበትን አዲሱን የስልክ ቤት የብረት ፋብሪካ ፡ የትምህርት ቤት ፡ ሆስፒታል ፡ የኡፕሳላ ዩኒቬርሲቲ የመጻሕፍት ቤት ነው።

ከዚህም በኋላ በሰኔ 8 ቀን ከእስቶኮልም ተነሥተን የሰሜን ባሕር የሚባለውን ተሻግረን በጀርመን አገር ሀምቡርግ ከሚባለው ከተማ ስንደርስ ፣ከባቡር ወርደን ሦስት ሰዓት ያህል በአውቶሞቢል ከተማውን እየዞርን አይተን በማግስቱ በሰኔ ቀን ፓሪስ ገባን።

# ምዕራፍ 18

## ከፓሪስ ወደ ሮማ ስለ መሔዳችን ።

በሰኔ9 ቀን ከፓሪስ ተነሡተን በ11 ቀን ሮማ ደረስን ።

የኢጣልያ ንጉሥ ግርማዊ ቪክቶሪዮ አማኑኤልና የመንግሥቱ መሪ ሲኞር ሙሶሊኒ የጦር አለቆችን አሰልፈው በባቡር መቋሚያ እጅግ ደስ የሚያሰኝ የክብር አቀባበል አደረጉልን። ለማረፊያም የተዘጋጀልን ግርማዊነታቸው በሚኖሩበት ቀድሞ የፓፓ ቤተ መንግሥት በነበረው ኩሪናል በሚባለው ነበርና ወደዚያው ገባን ።

በደርቡም በረንዳ ላይ ቆመን ሕዝቡን ለማሰናበት ከንጉሡ ጋራ ባንድነት ብቅ ባልን ጊዜ ባደባባዩ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ባንድ ቃል ኢጣልያ ለዘላለም ትኑር። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር። አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ ለዘላለም ይኑር እያሉ በደስታ ይጮሁ ጀመር። (ዛሬ ይህን ሲያስቡት እንዴት ይገርማቸው ይሆን ?)

በራት ግብዣም ላይ ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

«ልዑል ሆይ ፤

በሮማ ከተማ ልዑልነትዎን በፍቅር በመቀበሌ እጅግ ደስ ብሎኛል። ይህ የዛሬው አመጣጥዎ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ ያባትዎን የልዑል ራስ መኰንንን መምጣት ያሳስበኛል። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በእጅዎ የሰጠዎ መንግሥትእየለማ እንዲሔድ እርግጠኛ አሳቤ ነው።

የልዑልነትዎ ዕውቀት ከዚህ አስቀድሞ ለሀገሩ ልማትና ስፋት በብዙ ሥርቷል። አሁንም ወደ ኢጣልያ አገር መምጣትዎ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ያለውን ፍቅርና ጥቅም እያጸናው ይሔዳል ብዬ አምናለሁ።

በታላቁ ጦርነት ጊዜ ለኢጣልያ መንግሥት ያደረጋችሁለት የቸርነት ሥራ ለመቸውም አይረሳም። እኛም በበኩላችን ኢትዮጵያ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ በብዙ ረድተናል። ስለዚህም በሁለቱ መንግሥታት መካከል ያለው ፍቅር እየተረዳዳ ይኖራል ፡ በኢትዮጵያ ላይ የእግዚአብሔር በረከት እንዲወርድ እመኛለሁ» ብለው ጨረሱ።

እኔም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገርሁ ።

«ግርማዊ ሆይ ፣

ከኢትዮጵያ ድረስ መጥቼ ግርማዊነትዎንና መልካሚቱን አገርዎን የተወደደ ሕዝብዎን በማየቴ ደስታዬ ሙሉ ነው። ከብዙ ዘመን ጀምሮ ተመሥርቶ የቆየውን የሁለቱን መንግሥታት የፍቅር ማሰሪያ ለማጥበቅ ወደ ሮማ በመምጣቴ የታደልሁ ነኝ። ያባቱንም የልዑል ራስ መኰንንን ስም በማንሣትዎ እጅግ ደስ አለኝ። እርሳቸው በአባትዎ ፡ በንጉሥ ኡምቤርቶ ዘመን ወደ ኢጣልያ አገር በመጡ ጊዜ የተደረገላቸውን የክብር አቀባበል እያነሡ ሲናገሩ የሰሙ ሰዎች ሁሉ በጣም ያደንቃሉ። አሁንም እኔ መጥቼ ግርማዊነትዎ ያደረጉልኝን የክብር አቀባበል በማየቴ ደስ ብሎኛል። ወደ ፊትም አሳቤ ሁሉ ፍቅራችን እንዲጸና ወዳጅነታችን እንዲሰፋ ነውና ፡ የግርማዊነትዎም አሳብ እንደዚሁ እንዲሆን አምናለሁ። »

እኛ ኢትዮጵያውያን ያንድ ትልቅ አገር ንጉሥ የተናገረውን በመሐላ እንደ ተነገረ ቃል እንቆጥረዋለንና ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ቃል በመናገራቸው በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሰላምና ፍቅር ጸንቶ የሚኖር መስሎን ነበር እንጂ የመደለል ነገር አልመሰለንም።

በሰኔ 12 ቀን ለመንግሥቱ መሪ ለሲኞር ሙሶሊኒ ጐብኝት አድርገን ወዲያውም አንዳንድ ጉዳይ በወዳጅነት ለመነጋገር ስለ አሰብን ቀጠሮ ጠየቅን። ለመነጋገርም ፡ ያሰብነው ጉዳይ ቀድሞ የኢትዮጵያ ግዛት ዛሬ የኢጣልያ ቅኚ አገር ከሆነው ከአሰብ ወደብ ለሰሜኑ አገር በር ፡ በወዳጅነት ለኢትዮጵያእንዲሰጠው ነው።

በቀጠሮውም ሰዓት ሔደን ከተገናኘን በኋላ የኢጣልያ መንግሥት ከአሰብ ወደብ ነፃ የሆነ አንድ ክፍል በር በወዳጅነት እንዲሰጠን ለመነጋገር ፈቃድዎ ቢሆን ደስ ይለናል አልኋቸው።

ሲኞር ሙሶሊኒም ነገሩን በጥንቃቄ ከሰሙት በኋላ ይህን ነገር ለመነጋገር ፈቃዴ ነውና ከፖለቲካው ዲሬክተር ከኮንታሪኒ ጋር ተነጋግረው ምላሹን እርሱ ያስታውቅዎታል ብለው ወዲያው ኮንታሪኒ ተጠርቶ መጥቶ አገባጠሙን።

ከርሱም ጋራ በቀጠሮ ተገናኝተን በረጅሙ ከተነጋገርን በኋላ የተነጋገርነውን ሁሉ ለሲኞር ሙሶሊኒ አስታውቄ ምላሹ ነገ በኮንት ኮሊ እጅ ይመጣልዎታል ብሎኝ ተለያየን ።

በማግስቱም በኢትዮጵያ የኢጣልያ ልዩ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ኮንት ኮሊ መጥተው ስለ ጠየቁት ስለ አሰብ ወደብ ነገር የመንግሥቴ አሳብ ይህ ነው ብለው አንድ የውል አሳብ አቀረቡልን ።

የውሉም አሳብ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ፡

## አንደኛ ፣

የኢጣልያ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የሚኖረውን የፍቅር ማሰሪያ እያጠበቀ ለመሔድ ፍጹም ፈቃዱ ስለሆነ ፡ ስለ ኢትዮጵያም የገንዘብና የፖለቲካ ጥቅም ልማት እስካሁን በኢጣልያ መንግሥት እጅ ያለውን ከተማውን ፡ በከተማው ውስጥ ያሉትን የኢጣልያ መንግሥት ገንዘቦች የሆኑትን ቦታዎችና ቤቶች ሁሉ፣ ደግሞ የአሰብን ባሕር በርና ከባሕር በር አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ለምድር ባቡር የሚመች ቦታ እስከ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ድረስ ለኢትዮጵያ መንግሥት ሰጥቷል። ይህም የውሉ ዘመን እስኪፈጸም የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣልያ መንግሥት በተቀበለው በአሰብ የባሕር በርና እስከ ወሰኑ ባለው መንገድ ሙሉ ሥልጣን አለው።

## ሁለተኛ ፣

በባሕሩ በአሰብ ስፍራ ዙሪያ ወሰኑን ፡ የተሠሩትም ቤቶች ተጨምረው ፡ ደግሞ ከአሰብ የባሕር በር አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን የምድር ባቡር ለመሥራት የሚያስፈልገውን መሬት የኢጣልያና የኢትዮጵያ መንግሥት የሚመርጧቸው ዐዋቂዎች ከስፍራው ድረስ ሔደው ለባሕሩ በርና ለአሰብ ንግድ እንደሚያስፈልገው አድርገው ይወስናሉ።

## ሦስተኛ ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የፍቅር ማሰሪያ እያጠበቀ ለመሔድ ፍጹም ፈቃዱ ስለ ሆነ ፣ በዚህ በተባለው የባሕር በርና ቦታ በውሉ የተስማሙ እንደ ሆነ ፡ የገንዘብና የፖለቲካ ጥቅም ከኢጣልያ ዜጋ በቀር ለሌላ መንግሥት ዜጎች አይሰጥም። በመጨረሻም እኩል የሆኑ እንደ ሆነ ቀደምትነቱ ለኢጣልያ ዜጋ ይሆናል። ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ባገሩ ሕዝብ ለማሠራት ቢፈልግ የወደደውን ለማድረግ ይችላል።

## አራተኛ ፣

ከአሰብ የባሕር በር የኢጣልያ መንግሥት ምናልባት ዕቃ የሚያሳርፍበት ቦታ የቸገረው እንደ ሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት አንድ የተወሰነ ቦታ ይተውለታል።

## አምስተኛ ፣

የኢጣልያ ነጋዴዎች የንግድ ዕቃዎችን በአሰብ የባሕር በር በሚያሳልፉበት ጊዜ ቀረጡን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች በሚያስቀርጡበት ልክ ያስቀርጣሉ።

ስድስተኛ ፤

የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕሩን በርና የባቡሩን መንገድ ሥራ ከአሰብ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ለኢትዮጵያና ለኢጣልያ ኩምፓኒዮች ይሰጣል። እነዚህም ኩምፓኒዮች ሲቆሙ ሁለቱን እጅ ገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፡ አንዱን እጅ ገንዘብ የኢጣልያ ሕዝብ ያወጣሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት እጅ ገንዘብ ለማውጣት ያልቻሉ እንደ ሆነ ሌላ የውጪ ሰው ሳያስገቡ ሁለቱ ወገኖች ብቻ ገንዘቡን እኩል እኩል አዋጥተው ኩምፓኒያ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሰባተኛ ፤

የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ፊት ከሌላ መንግሥት ጋራ የባሕር በር ውል የተዋዋለ እንደ ሆነ ፡ ደግሞ በማናቸውም ሌላ የባሕር በር ነፃ የሆነ የቦታ ክፍል ፡ ወይም ስፍራ ያገኘ እንደ ሆነ ፡ በዚያውም መልካም ጥቅም የሚያገኝበት የሆነ እንደ ሆነ ፡ የኢጣልያ መንግሥት ያንኑ የባሕር በር ውል አድሶ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስፋት ተስማምቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር በር ውል ከሌላ መንግሥት ጋራ ተዋውሎ ሌላው መንግሥት በውሉ ጥቅም የሚያገኝ የሆነ እንደ ሆነ የኢጣልያ መንግሥትም ይህንኑ የባሕር በር ውል አድሶ ጥቅም ለማግኘት ይችላል።

ስምንተኛ ፤

ከዚህ ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢጣልያ መንግሥት የተዋዋሉት የወሰን ነገር ሁሉ ውሉ እየታየ ከሁለቱ ወገን ዐዋቂዎች ተመርጠው የወሰኑ ነገር እንዲጨረስ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተዋል። ደግሞ በእርሻም በንግድም በሥራም በማዕድንም ከዚህ ቀደም ውል የተቀበሉትን የኢጣልያ ኩምፓኒዮች ችግር እንዳያገኛቸው የኢትዮጵያ መንግሥት በሚቻለው ሁሉ ይረዳቸዋል።

ዘጠነኛ፤

ስለ ጁባና ስለ ዋቢ ሸበል ወንዝ ውሃ የኢትዮጵያ መንግሥት ለራሱ ጥቅም ከሚያስፈልገው በቀር ለሌሎች ለውጭ አገር ሰዎች ጥቅም ሰጥቶ ወደ ኢጣልያ ሱማሌ አገር እንዳይወርድ አድርጎ ውሃውን በጭራሽ እንዳይዘጋ ውል ገብቷል።

አሥረኛ ፤

የኢጣልያ መንግሥት የአሰብን የባሕር በርና በአሰብ ያሉትን ቦታዎችና ቤቶች ሁሉ ጨምሮ ለባቡሩም መንገድ መሥሪያ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን የሚበቃ ቦታ ስለሰጠ ከኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ገንዘብ እንዳይፈልግ ውል ገብቷል» የሚል ነው።

ይህንንም የውል አሳብ ከተመለከትነው በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰን ለምክር ቤቱ ማስታወቅ የሚያስፈልግ መሆኑን ስለ ተረዳነው ይህንኑ አሳባችንን ኮንት ኮሊ ለሲኞር ሙሶሊኒ እንዲያስታውቁ ነገርናቸው። የውሉ አሳብግን በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ፍጻሜ አልደረሰም።

በሰኔ 14 ቀን የሮማ ፓፓ ፒዮስ 11ኛውን ለመጐብኘት ቀጠሮ ተደርጎልን ነበርና በቀጠሮው ሰዓት ወደ ቫቲካን ቤተ መንግሥት ሔደን ተገናኘን። ፓፓውም በኢትዮጵያ የሚኖሩት የካቶሊክ ሚሲዮኖች በሰላምና በጸጥታ ስለ መኖራቸው የቀድሞውም ልማድ ቀርቶ አሁን በኢትዮጵያ የሃይማኖት ነፃነት ስለ መፈቀዱ ደስታቸውን እየገለጡ ተናገሩ። ተሰነባብተን በምንመጣበትም ጊዜ እግዚአብሔር የኢትዮጵያን አገርና ነገሥታቱንም ሕዝቡንምይባርክ ብለው ጸሎት አደረጉ።



ዓፄ ምኒልክ ባሉበት በቀኝ በኩል ደጃች ተፈሪ (ቀ.ኃ.ሥ)



ከግራ ወደቀኝ ግራዝማች ዮሴፍ፣ ከንቲባ ገብሩ፣ ሙሴ ላጋር፣ ልዑል ራስ መኰንን፣
ደጃዝማች አባ ታቦር፣ ሙሴ ቢሮ



የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ የንግስ በዓል።



ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ያኔ መስቀልን በዓል ሲያከብሩ ከተቀመጡበት ውስጥ ቆሞሩ ንጉሥ ተፈሪ [ቀ.ኃ.ሥ.] ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በቀኝ ራስ ጉግሳ አባተ ፊታውራሪ ወልዴ ገብርኤል፡

ከዚያም ስንወጣ ወደ ቅዱስ ሉጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ገብተን መቃብሩን ተሳልመን ፡የቤተ ክርስቲያኑን ውበት አይተን ከወጣን በኋላ ፡ በዚያው አጠገብ ያለውን ለኢትዮጵያ መናንያን የተሰጠውን የቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ለማየት ገባን። የኢትዮጵያ መነኩሳት ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የጌታችንን መቃብር ጎልጎታን ፡ የቅዱስ ጴጥሮስንና የቅዱስ ጳውሎስን መቃብር ሮማን ለማየትና ለመሳም ብዙ ናፍቆት አላቸውና ከኢትዮጵያ ድረስ ወደ ሮማ እየመጡ የማረፊያ ስፍራ እየቸገራቸው መጉላላታቸውን አይተው 1969 ዓ. ም. የነበሩት ፓፓ ይህ የቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ለኢትዮጵያ መናንያን ማረፊያ ይሁን ብለው ሰጡ ይባላል።

በዚህም ገዳም ያለውን ቤተ ክርስቲያን በየማዕፀኑ እየዞርን ስናይ የሰባት ኢትዮጵያውያን መነኩሳት ስም የተቀረጸባቸው ጥርብ ድንጋዮች አይተናል። በገዳሙም ባንድ ክፍል ቤት ገብተን በተቀመጥን ጊዜ ለትምህርት የመጡ ሰባት ኢትዮጵያውያን ቀርበው የኢትዮጵያን ቀደምትነት ፡ የነገሥታቱን ብርታትእየተናገሩ እኛንም እያመሰገኑ ደስታቸውን ገለጡልን ።

በሮማ በቆየንበት ጊዜ በሮማና በያውራጃቹም ያየነው ፡ መታሰቢያ ሆኖ በልባችን የሚኖረው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው። የኩሪናል ቤተ መንግሥት የነገሥታቱ መቃብር ፡ የኦቶቢስኪሊት እሽቅድድም ፣ የሮማ ማዘጋጃ ቤት ፡ ቫቲካንና የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ፡ የኢትዮጵያ ልጆች የሚማሩበት የእስጢፋኖስ ገዳም ፡ የቅዱስ ጳውሎስና የቅዱስ ዮሐንስ ፡ የእችን የድንግል ማርያምና የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኖች ፡ የቀድሞ ቄሣሮች ቤተ መንግሥት ፡ የቀድሞ ቄሣሮች ክርስቲያኖችን ከአራዊት ጋራ የሚያስታግሉበትና ባሮችን እርስበርሳቸውየሚያጋድሉበት፡የትያትርቦታ፡ የቪክቶር አማኑኤል 2ኛ ሐውልት ፡ በችንቶቸሌ የታየው የወታደር ሰልፍ የሮማ አንቲካ ቤት ፡ በብራቺያኖ የታየው የመድፍ ተኩስ ፡ ቼሊዮ የሚባለው የወታደር ሆስፒታል ፡፥ የእስፔዚያ መርከቦች የቶሪኖ ከተማ ፡ የፊያት አውቶሞቢል ፋብሪካ ፡ በቶሪኖ ያለው የነገሥታቱ መቃብር ቤት ነው ።

የኦፊሴሉም የጕብኝት ቀን ሲጨረስ ግርማዊ ንጉሥ ቪክቶሪዮ አማኑኤል ስለ አደረጉልን የወዳጅነት አቀባበል እያመሰገንን ተሰነባብተን በሰኔ 25 ቀን ወደ ፓሪስ ተመለስን።

በቀጠሮውም ሰዓት ሔደን ከተገናኘን በኋላ የኢጣልያ መንግሥት ከአሰብ ወደብ ነፃ የሆነ አንድ ክፍል በር በወዳጅነት እንዲሰጠን ለመነጋገር ፈቃድዎ ቢሆን ደስ ይለናል አልኋቸው።

ሲኞር ሙሶሊኒም ነገሩን በጥንቃቄ ከሰሙት በኋላ ይህን ነገር ለመነጋገር ፈቃዴ ነውና ከፖለቲካው ዲሬክተር ከኮንታሪኒ ጋር ተነጋግረው ምላሹን እርሱ ያስታውቅዎታል ብለው ወዲያው ኮንታሪኒ ተጠርቶ መጥቶ አገጣጠሙን።

ከርሱም ጋራ በቀጠሮ ተገናኝተን በረጅሙ ከተነጋገርን በኋላ የተነጋገርነውን ሁሉ ለሲኞር ሙሶሊኒ አስታውቄ ምላሹ ነገ በኮንት ኮሊ እጅ ይመጣልዎታል ብሎኝ ተለያየን ።

በማግስቱም በኢትዮጵያ የኢጣልያ ልዩ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ኮንት ኮሊ መጥተው ስለ ጠየቁት ስለ አሰብ ወደብ ነገር የመንግሥቴ አሳብ ይህ ነው ብለው አንድ የውል አሳብ አቀረቡልን ።

የውሉም አሳብ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ፡

አንደኛ

የኢጣልያ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የሚኖረውን የፍቅር ማሰሪያ እያጠበቀ ለመሔድ ፍጹም ፈቃዱ ስለሆነ ፡ ስለ ኢትዮጵያም የገንዘብና የፖለቲካ ጥቅም ልማት እስካሁን በኢጣልያ መንግሥት እጅ ያለውን ከተማውን ፡ በከተማው ውስጥ ያሉትን የኢጣልያ መንግሥት ገንዘቦች የሆኑትን ቦታዎችና ቤቶች ሁሉ፣ ደግሞ የአሰብን ባሕር በርና ከባሕር በር አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ለምድር ባቡር የሚመች ቦታ እስከ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ድረስ ለኢትዮጵያ መንግሥት ሰጥቷል። ይህም የውሉ ዘመን እስኪፈጸም የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣልያ መንግሥት በተቀበለው በአሰብ የባሕር በርና እስከ ወሰኑ ባለው መንገድ ሙሉ ሥልጣን አለው።

ሁለተኛ ፣

በባሕሩ በአሰብ ስፍራ ዙሪያ ወሰኑን ፡ የተሠሩትም ቤቶች ተጨምረው ፡ ደግሞ ከአሰብ የባሕር በር አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን የምድር ባቡር ለመሥራት የሚያስፈልገውን መሬት የኢጣልያና የኢትዮጵያ መንግሥት የሚመርጧቸው ዐዋቂዎች ከስፍራው ድረስ ሔደው ለባሕሩ በርና ለአሰብ ንግድ እንደሚያስፈልገው አድርገው ይወስናሉ።

ሦስተኛ ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የፍቅር ማሰሪያ እያጠበቀ ለመሔድ ፍጹም ፈቃዱ ስለ ሆነ ፣ በዚህ በተባለው የባሕር በርና ቦታ በውሉ የተስማሙ እንደ ሆነ ፡ የገንዘብና የፖለቲካ ጥቅም ከኢጣልያ ዜጋ በቀር ለሌላ መንግሥት ዜጎች አይሰጥም። በመጨረሻም እኩል የሆኑ እንደ ሆነ ቀደምትነቱ ለኢጣልያ ዜጋ ይሆናል። ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ባገሩ ሕዝብ ለማሠራት ቢፈልግ የወደደውን ለማድረግ ይችላል።

አራተኛ ፣

ከአሰብ የባሕር በር የኢጣልያ መንግሥት ምናልባት ዕቃ የሚያሳርፍበት ቦታ የቸገረው እንደ ሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት አንድ የተወሰነ ቦታ ይተውለታል።

አምስተኛ ፣

የኢጣልያ ነጋዴዎች የንግድ ዕቃዎችን በአሰብ የባሕር በር በሚያሳልፉበት ጊዜ ቀረጡን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች በሚያስቀርጡበት ልክ ያስቀርጣሉ።

ስድስተኛ ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕሩን በርና የባቡሩን መንገድ ሥራ ከአሰብ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ለኢትዮጵያና ለኢጣልያ ኩምፓኒዮች ይሰጣል። እነዚህም ኩምፓኒዮች ሲቆሙ ሁለቱን እጅ ገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፡ አንዱን እጅ ገንዘብ የኢጣልያ ሕዝብ ያወጣሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት እጅ ገንዘብ ለማውጣት ያልቻሉ እንደ ሆነ ሌላ የውጪ ሰው ሳያስገቡ ሁለቱ ወገኖች ብቻ ገንዘቡን እኩል እኩል አዋጥተው ኩምፓኒያ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሰባተኛ ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ፊት ከሌላ መንግሥት ጋራ የባሕር በር ውል የተዋዋለ እንደ ሆነ ፡ ደግሞ በማናቸውም ሌላ የባሕር በር ነፃ የሆነ የቦታ

# ምዕራፍ 19

## ከፓሪስ ወደ ሎንዶን ።

በሰኔ ወ ቀን ከፓሪስ ተነሥተን ወደ ሎንዶን ተጓዝን። ካሌ ላይ ደርሰን በእንግሊዝ መርከብ ገብተን ጉዞ ስንጀምር ሁለት የጦር መርከቦች በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሰንደቅ ዓላማ አጊጠው በመርከባችን ቀኝና ግራ ይጓዙ ነበር። ባሕሩንም አልፈን ዶቨር ስንደርስ 21 ጊዜ የሰላምታ መድፍ ተተኰሰ።

ከዶቨርም በባቡር ተሳፍረን ሎንዶን በቢክቶሪያ ባቡር መቋሚያ ስንደርስ የግርማዊ ጆርጅ ልጅ አሁን የነገሥት ያን ጊዜ ዱክ ኦፍ ዮርክ ሲባሉ የነበሩት በአባታቸው ስም ሆነው ከብዙ መኳንንትና ከክብር ዘበኞች ጋራ መጥተው የክብር አቀባበል አደረጉልን። ከዚያም ለማረፊያ በተሰናዳልን በሐይድ ፓርክና በናይትስብሪጅ አጠገብ አልቤርት ጌት በሚባል ቤት ገባን።

በማግስቱም በሐምሌ 1 ቀን ከግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ጋራ ለመገናኘት መፈቀዱን ልዑል ዱክ ኦፍ ዮርክ አስታውቀውን ነበርና በተወሰነው ሰዓት ሔደን ተገናኘን።

ከዚህም ቀጥሎ ያለውን ቃል ለግርማዊነታቸው ተናገርሁ ፡

«ግርማዊ ሆይ ፡

ከብዙ ዘመን አስቀድሞ በተመሠረተችው በታላቂቱ ከተማዎ በሎንዶን ግርማዊነትዎንና ግርማዊት ንግሥትን በማየቴ እጅግ ደስ ብሎኛል። በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል ጸንቶ የሚኖረው ወዳጅነት ከተመሠረተ ብዙ ዘመን መሆኑን ግርማዊነትዎ ያውቀዋል ።

ወደ ፊትም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና የኔም የራሴም የሁለቱ መንግሥታት ወዳጅነት እየሰፋና እየጸና እንዲሔድ ነውና የግርማዊነትዎም አሳብና ፈቃድ እንደዚሁ መሆኑን እናምናለን ።

ደግሞ ትልቁ አባቴ ልዑል ራስ መኰንን በትልቁ አባትዎ በንጉሥ ኤድዋርድ 7ኛ ዘመን ወደ ሎንዶን በመጡ ጊዜ የተደረገላቸውን የወዳጅነት ነገር ሁሉ ለየመኳንንቶቻቸው ሲነግሩ እየሰማሁ በጣም ያስደንቀኝ ነበር።

እኔም ልጃቸው ወደ ሎንዶን መጥቼ ግርማዊነትዎንና የከበረ ሕዝብዎን ፡ያማረች ከተማዎን በማየቱ እጅግ ደስ ብሎኛልና ይህ ደስታዬ ለእኔ መታሰቢያሆኖ በልቤ ውስጥ ይኖራል ፡

ግርማዊ ሆይ ፡ ለግርማዊነትዎና ለግርማዊት ንግሥት ለቤተ ዘመዶችዎም ሁሉ ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ ፡ ለሕዝብዎ ሰላምና በረከት ፡ ለሀገርዎ ልማትና ስፋት እንዲሆን የልቤ ምኞት መሆኑን ለግርማዊነትዎ እገልጣለሁ» ብዬ ስጨርስ ፡ ግርማዊነታቸውም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል መለሱ።

«ልዑል ሆይ ፡

አሁን ልዑልነትዎ የተናገረውን የወዳጅነት ቃል ስለ ሰማሁ እጅግ ደስ እያለኝ ከልቤ አመሰግንዎታለሁ። በእንግሊዝ መንግሥት ዋና ከተማ በደኅና በመግባትዎና ዓይን ላይን በመተያየታችን እኔና ንግሥት እጅግ ደስ ብሎናል።

የልዑልነትዎ አመጣጥ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ በሁለቱ መንግሥታት መካከል የሚኖረውን ወዳጅነት ወደ ፊት እያሰፋና እያጸና እንዲሔድ ተስፋ አደርጋለሁ።

ልዑል አባትዎ ራስ መኰንን ግርማዊ አባቴ ንጉሥ ኤድዋርድ ዘውድ በጫኑ ጊዜ ስለ ዐፄ ምኒልክ ሆነው መምጣታቸው ይታሰበኛል። ልዑል ራስ መኰንን ለሀገሬ ዘወትር የወዳጅነት አሳብ እንደነበራቸው በፍጹም አውቃለሁ። እንዲሁም ደግሞ ይኸው አሳብ በልጃቸው ዘንድ ለዘወትር እንዲኖር አልጠራጠርም።

ልዑልነትዎ በዚህ ሳሉ በሀገሬ ውስጥ ለማየት የሚያስፈልግዎን ነገር ሁሉ ያለችግር እንዲያዩ ተዘጋጅቶልዎታል። ደግሞ ከእኛ ጋራ ሳሉ ደስ የሚያሰኝና ጥቅም ያለው ነገር ሆኖልዎ ወደ ሀገርዎ በተመለሱ ጊዜ በእንግሊዝ አገር ያዩት ሁሉ ለልብዎ ደስ የሚያሰኝ መታሰቢያ እንዲሆንልዎ ተስፋ አደርጋለሁ።

አሁንም እንደገና ልዑልነትዎን እያመሰገንሁ ወዳጅነታችንን ለማጽናት አሳቤ መሆኑን አስረዳዎታለሁ። ወደ ሀገርዎም በተመለሱ ጊዜ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ከልብ የሆነ የማክበር ሰላምታዬን እንዲያቀርቡልኝ ልዑልነትዎን እለምናለሁ። ለኢትዮጵያም መንግሥት ደኅንነትና ልማት ፡ በረከትና ስፋት እንዲሆን ፍጹም አሳቤ መሆኑን እገልጥልዎታለሁ» ብለው ጨረሱ።

ከዚህም በኋላ ወደ አልቤርት ጉት ተመልሰን ሁለት ሰዓት ያህል እንደ ቆየን ግርማዊነታቸው ወደ አልቤርት ጌት መጥተው ጒብኝት መልሰው ሔዱ።

በሐምሌ 4 ቀን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምስተር ራምሴ ማክዶናልድ ጋራ አንዳንድ የመንግሥት ጉዳይ ለመነጋገር ቀጠሮ ተደርጎ ነበርና በቀጠሮው ሰዓት ወደ ውጭጉዳይ ሚኒስቴር ሔደን ተገናኘን።

ከዚህም በኋላ ምስተር ማክዶናልድ በሁለቱ መንግሥታት ዜጎች መካከል በወሰን ላይ ስለሚደረገው አምባጓሮ ነገሩን በረጅሙ አድርገው ከተናገሩ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለስንላቸው።

የወሰኑ ነገር በጽሕፈት ብቻ ሆኖ እንደ ውሉ ቃል ከሁለቱም መንግሥታት ወገን የተመረጡት መሐንዲሶች ከቦታው ላይ ሔደው ስላልወሰኑትና ምልክት ስላልተደረገበት የእኛም የእናንተም ዜጎች በወሰን ላይ የሚጣሉበት ምክንያቱ ይህ ነውና ወደ ፊት በቶሎ የሚያስፈልገውን አድርገን ወሰኑ ቢከለልና ምልክት ቢደረግበት ይሻላል። ይህ ከተደረገ በኋላ ሁለቱም ወገኖች ወሰናቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ አይጠረጠርም አልናቸው። ምስተር ማክዶናልድም በዚሁ አሳብ ተስማምተው የወሰኑ መካለል ነገር በቶሎ እንዲጀመር እናደርጋለን ብለው ተናገሩ። እንደ ተመለስንም የወሰኑ ክልል ሥራ እንዲሠራ አድርገናል ።

ሁለተኛው ጉዳይ የጣናን ባሕር ስለ መገደብ ነው። ምስተር ማክዶናልድ የእንግሊዝ መንግሥት የጣናን ባሕር እንዲገድብ የኢትዮጵያ መንግሥት ይፍቀድለት ብለው ጠየቁ። ለዚህም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለስንላቸው።

የጣናን ባሕር እኛው ራሳችን እናስገድባለን ፣ ስለ ኩባንያውም አቋቋም እንነጋገርበታለን። አስገድበን ውሃውን ለአንግሎ ኤዥብሲያን ሱዳን መንግሥትእናከራየዋለን አልናቸው።

በዚህም በዋናው አሳብ ተስማምተን ዝርዝሩን በጽሕፈት እንቀባበላለን በማለት ጨረስን።

ከዚህም በኋላ በእኛም ወገን ችግራችንን ለማመልከት ፈቃድ ጠይቀን ፡ ቀጥሎ ያለውን ጠየቅናቸው። ከዚህ ቀድሞ በዐፄ ምኒልክ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት ለራሱ የሚያስፈልገውን የጦር መሣሪያ እየገዛ ወደ ሀገሩ ሲወስድ እንዳይከለከል ውል ተደርጎ ነበር። አሁን ግን ከትልቁ የአውሮጳ ጦርነት ወዲህ የጦር መሣሪያ እየገዛን ለመውሰድ ተከልክለናልና እንደ ጥንቱ እየገዛን እንድንወስድ ይፈቀድልን አልናቸው። እርሳቸውም የዚህን የጦር መሣሪያውን ነገር ከፈረንሳዊና ከኢጣልያ መንግሥት ጋራ ባንድነት ሆነን ካልጨረስነው የእንግሊዝ መንግሥት ብቻውን ለመጨረስ አይችልምና ሦስቱም መንግሥታት ከመከሩበት በኋላ ምላሹን እናስታውቅዎታለን ብለው መለሱ።

ሁለተኛም ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ የሚያገናኝ የባሕር ወደብ ስለሌለው ብዙ ችግር ሆኖብናል። ዕውቀትና ብልጥግና የሚገኘው አንዱ መንግሥት ከሌላው መንግሥታት ጋራ በባሕርም በምድርም እየተገናኘና እየተጋጠመ ንግዱ ሲሰፋ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ፊት አሳቡ ሁሉ የሥልጣኔ ሥራ

እየሠራ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ በጣም ለመቃረብ ነው።  አሁን ባለፈው ዓመት እንኳ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር መግባታችን የሥልጣኔ ሥራ ለመሥራትና አገራችንን ለማልማት ማሰባችንን ያስረዳል። ስለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት አንድ የባሕር ወደብ ለኢትዮጵያ መንግሥት ርስት አድርጎ ቢሰጥ ለዘላለም የማይናወጥ ወዳጅነት ሆኖ ይኖራል። ስለዚህ ከሎንዶን ከመነሣቴ በፊት የዚህን ቁርጥ ምላሽ ቢያስታውቁኝ ደስ ይለኛል አልኋቸው።

ምስተር ማክዶናልድምይህን ነገርካሁን በቀር አልሰማሁትም ፡ ይኸውም በፓርላሜንት ተመክሮ ነገሩ ካልተቆረጠ እኔ ብቻዬን የምቆርጠው አይደለምና በቶሎ ምላሹን ልሰጥዎ አልችልም። ለፓርላሜንቱ ግን በተመቸ ጊዜ አቅርቤ እንዲመከርበት አደርጋለሁ ብለው ተመለሱ።

በዚሁም ቀን ማታ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ ጲጋዊ ራንደል ዳቢድሶን ለምሳ ጋብዘውን ነበርና ከአልቤርት ጌት በ7 ሰዓት ወደ ላምቤት ፓላስ ሔድን። እጅግ ያማረ ግብዣም ከተደረገልን በኋላም ሊቀ ጳጳሱ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

«ልዑል ሆይ ፡

ለእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ዋና ስፍራ በሆነው በላምቤት ፓላስ ልዑልነትዎን በመቀበሌ ከፍ ያለ ደስታ ሆኖልኛል። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አውራጆች ትልልቅ ወኪሎች የሆኑትን በየጊዜው እቀበላለሁ። ነገር ግን በጥንታዊነት ቤተ ክርስቲያናቸው ከዓለም ክርስቲያኖች መካከል በፊተኛው ስፍራ የቆመችው ላምቤትን ጐብኝቶ አያውቅም ።

ልዑል ሆይ ፡ ቤተ ክርስቲያንም የሺ600 ዓመት ያህል ጥንታዊ ታሪክ አላት። መጀመሪያም ከዚህ ወደሚቀድም ወደ ጉታችን ሐዋርያት ዘመን ይቃረብ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያንዎ ከአትናቱዎስና ከጓደኞቹ ዘመን የሚዘመድ ታሪክ አላት። ነገር ግን ልዑልነትዎ ከእንግዲህ ወዲህ የጥንት ወግ ብቻ የሚይዙ አይደሉምና ወደ ፊት በሕዝብዎ የክርስቲያንን ሥልጣኔ ማስፋትና የክርስቲያንን መጻሕፍት መዘርጋት ክብርዎ ነው።

ከማተሚያ ቤትዎ የቀድሞ ዘመንና አዲስ የሃይማኖት መጽሐፍ ብቻ አይወጡም። ነገር ግን እርስዎ ራስዎ የሥራው ተካፋይ ነዎ። ልዑልነትዎ ያሳተሟቸው የኢትዮጵያ መጻሕፍት የርስዎ መቅድም ያለበት ፣ የሊቁ የአፈወርቅና የመነኩሴው የማር ይስሐቅ መጻሕፍት ለሚመረምራቸው ሁሉ ጥቅሙ እጅግ ብዙ ነው።

የዛሬ መንገድዎ ዋና አዲስ ከሆነ ከምዕራብ ዓለም ጋራ የሚያስተዋውቅዎ መሆኑ የማይጠረጠር ነው። በመንፈሳዊ ነገርም ቢሆን ፡ በዓለም ነገርም ቢሆን መምጣትዎ ለሁላችን የዘለዓለም ደስታ ነው። የሀገርዎ መንፈሳዊና ሥጋዊ ደኅንነትም በእጅዎ የተያዘ እንዲሆንና ለመልካም ሥራ መጣጣርም የሚቻል እርዳታ ሁሉ እንዲገባዎ እርግጥ ሆኖ ይሰማኛል ።

ከልብ ፍቅርና ከፍ ካለ ተስፋ ጋራ የመጡበት ጉዳይ ሁሉ እንዲከናወንልዎ እንመኛለን» ብለው ጨረሱ።

በሐምሌ 5 ቀን የአፊሴሉ ቀን ስለ ተጨረሰ ወደ በኪንግሃም ቤተ መንግሥት ሔደን ከግርማዊ ንጉሥና ከግርማዊት ንግሥት ተሰነባበትን። በመሰነባበትም ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

«ልዑልነትዎ የሁለቱን መንግሥቶች ወዳጅነት ለማጽናትና ለማስፋት ወደ እንግሊዝ አገር በመምጣትዎ በጣም ደስ ብሎኛል። ስለዚህ ሎንዶንን ለማየትዎና ከእኛ ጋር ለመገናኘትዎ ለዘለዓለም መታሰቢያ እንዲሆንዎ በመቅደላ ጦርነት ጊዜ የእንግሊዝ የጦር አለቃ ያመጣውን የዐፄ ቴዎድሮስን ዘውድ መልሰንልዎታል» አሉ።

የዐፄ ቴዎድሮስ ዘውድ ተማርኮ ወደ እንግሊዝ አገር መምጣቱ ምንም የኢትዮጵያን ነፃነት የሚነካ ባይሆን እንኳ ፣ ይህ ዘውድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ነበር እየተባለ በውጭ አገር መታየቱ ደስ አያሰኝም ነበርና አሁን

ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ይህ የዐፄ ቴዎድሮስ ዘውድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ መፍቀዳቸው ትልቅ የወዳጅነት ምልክት መሆኑን ስለ ተረዳሁትና ትልቅ ደስታ ስለ ተሰማኝ ከጥልቅ ልቤ እውነተኛ ምስጋናዬን አቀረብሁላቸው ፡፡

በሐምሌ 11 ቀን የካምብሪጅን ዩኒቬርሲቲ ለመጐብኘት ከጧቱ በ4 ሰዓት ከሎንዶን ተነሣን፡፡ የዩኒቬርሲቲው ዋና አለቃ ወደ ሎንዶን ሳንመጣ ገና ሮማ ሳለን ዩኒቬርሲቲውን ለመጐብኘት ፈቃዳችን እንዲሆን በጽሕፈት ጠይቆን ነበር፡፡ ሎንዶንም ከደረስን በኋላ አሳቡን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ስለ አስታወቀን ፈቃዱን ለመፈጸም ሔድን ፡፡

የዩኒቬርሲቲውም ፕሮፌሰሮች ሁሉ በክብር ከተቀበሉን በኋላ የዩኒቬርሲቲው ዋና አለቃ ቀርበው«ልዑል ሆይ ፣ ሀገርዎን ኢትዮጵያን በጥበብና በዕውቀት ለመምራት መጀመርዎንና መትጋትዎን ሰምተናልና ዶክቶር ኦፍ ሎው የሚያሰኘውን የክብር ማዕርግ ሰጥተነዎታል» ብለው ለዚሁ የሚገባውን ልብስ ሰጡኝ ፡፡

ወዲያውም ትልቅ የምሳ ግብዣ አድርገውልን ነበርና ፡ በግብዣው ላይ ዋናው የዩኒቬርሲቲው አለቃ ዶክቶር ኤ ሲ ፒየርስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ

«ልዑል ሆይ ፡

ባለቅኔው ሆሜር ፡ የኢትዮጵያ ሰዎች ነውር የሌለባቸው ናቸው ብሏል ፡፡ ሄሮዶቱስም የኢትዮጵያ ሰዎች ፈጽሞ የወይን ጠጅ አይጠጡምና ዕድሜያቸው ረጅም ነው ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ሰዎች ለካምባይስስና ለፋርስ ንጉሥ ግብር አንገብርም ማለታቸው እርግጥ ነው፡፡ ከዚያም በኋላ ሀገራቸውን በኃይል ለመውሰድ የመጣውን ሁሉ እያሸነፉ መለሱት፡፡

የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ዝና ሰምታ ፣ ሽቱና ወርቅ ፡ አልማዝ ይዛሰሎሞንን በእንቆቅልሽ ለመፈተን በግመል እንደ መጣች የማያውቅ ማነው፡፡ የነገሥታትስ ሁሉእናት ትሆን ዘንድ ወደ ሀገርዋ እንደ ተመለሰች የማያውቅ ማነው፡፡ ምንስ ዘመኑ ቢበዛ ከዳዊት ዘር መሆናቸውን የማያስብ ማን ነበረ፡፡ የንግሥት ህንደኬ ወገንስ መሆናቸውን የማያውቅ ማን ነበረ፡፡ ይህ ሁሉ ክርስቲያንነታቸውን በሙሉ ኢትዮጵያ እንደ መሠረቱ ፣ የቀድሞ እምነት የብዙ ዘመን ታሪክ እንዳላቸው ያስረዳል ፡፡

የኢትዮጵያን መጻሕፍትና የሕግ መጻሕፍቶቻቸውን ባለፈው ዓመታት በካምብሪጅ ዩኒቬርሲቲ በክርስቶስ ኮሌጅ የተማረ አንድ ሰው ለእንግሊዞች ገለጠው፡፡

አሁንም ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በመካከላችን አሉ፡፡ እርሳቸውም የቀድሞ አባቶቻቸውን መንገድ ተከትለው ከምሥራቃውያንና ከግብጻውያን ይልቅ ዕውቀት ያላቸው ናቸው ፡፡

የቀድሞውንም የዛሬውንም ዕውቀት ይመረምራሉ፡፡ የቀድሞውን የክርስቲያን ትምህርት ሁሉ መርምረዋል፡፡ አዲሱንም ፅውቀት ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ ከኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሾች በመጀመሪያ ወደ አይሮፐላን ላይ የወጡ ልዑል ተፈሪ መኰንን ናቸው፡፡

ደግሞ የዮሐንስ አፈ ወርቅንና የማር ይስሐቅን መጻሕፍት ከግእዝ ወደ አማርኛ ቋንቋ አስተርጒመው በገዛ ማተሚያቸው አሳትመዋል፡፡ እነዚህም መጻሕፍቶች በካምብሪጅ ዩኒቬርሲቲ መጻሕፍት ቤት ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በቀር ለኢትዮጵያ ልጆች የትምህርት ቤት ሠርተዋል ፡፡

ስለዚህ ትልቁን የኢትዮጵያን መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ከጥንት ነገሥታት ዘር የመጡትን የኢትዮጵያ ተስፋ ልዑል ተፈሪ መኰንንን ፡ከዚህ ላላችሁት ለሁላችሁም እናስተዋውቃችኋለን» ብለው ጨረሱ፡፡

እኛም ዋናው የዩኒቬርሲቲው አለቃ ለተናገሩት ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል መለስን፡፡

«ለልዩ ልዩ ሕዝብ የዕውቀትና የጥበብ ምንጭ የሚመነጭበትን የካምብሪጅን ዩኒቬርሲቲ በማየቴ እጅግ ደስ ብሎኛል። እናንተም በታላቅ ደስታና በልብ ፍቅር ስለ ተቀበላችሁኝ አመሰግናችኋለሁ። ይልቁንም ደግሞ የኢትዮጵያ ነፃነትና የሕዝቡ ክርስቲያንነት ከብዙ ዘመናት አስቀድሞ መሆኑን አስረድታችሁ ታሪኩን በመናገራችሁ ደስታዬ ከልክ ያለፈሆነ።

የኢትዮጵያ መንግሥት በጣም ቀደምትነት እንዳለውና ከተመሠረተም ረጅም ዘመን እንደ ሆነ የማያውቁ ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ይኖራሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያን ታሪኳን በጣም ቢመለከቱ ፣ ከዮናናውያን ፡ ከሮማውያንም አስቀድሞ ጸንታ የኖረች መንግሥት መሆኗን ለመረዳት ይችሉ ነበር። በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን እንኳ በጣም የታወቀች መንግሥት ነበረች።

ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር ስለ ገባች ከአውሮጳ መንግሥታት ጋራ በጣም ለመቃረብ የተመቸ ሆኖላት። ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች በአውሮጳና በሌሎችም አገሮች ለትምህርት ስለሰደድና ቸው እነርሱም ለትምህርታቸው በጣም ስለ ተጉ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የዩኒቬርሲቲ ትምህርት ለመማር ወደ ካምብሪጅ እንዲመጡና እንዲማሩ ፡ ተምረውም ሲመለሱ መንግሥታቸውን እንዲያገለግሉ ተስፋ አደርጋለሁ» በማለት ከጨረስሁ በኋላ ተሰነባብተን ወደ ሎንዶን ተመለስን ።

በሎንዶን ከተማ ያየሁት ሁሉ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ይልቁንም በልቤ ውስጥ ተቀርጾው ለዘላለም መታሰቢያ ሆነው የሚኖሩት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው። የበኪንግሃም ቤተ መንግሥት ፣ታወር---አፍ --- ሎንዶን፡ የቅዱስ ቶማስ ሆስፒታል ፡ የፓርላሜንት ቤት ፡ ዙዎሎጂካል ጋርድን የሚባለው ልዩ ልዩ አራዊት የሚታዩበት ፡ ሐይ ኮርት የሚባለው የፍርድ ቤት ፡ የቅዱስ ጳውሎስ ካቴድራል (ቤተ ክርስቲያን) ፣ የዌምብሊ ኤግዚቢሽን ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቤት፣ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ መኖሪያ ቤት ላምቤት ፓላስ የሚባለው ፣ የእንግሊዝና የውጭ አገሮች የቅዱስ መጽሐፍ ማኅበር ቤት፣የእንግላንድ ባንክ ፡ የዊንድሶር ቤተ መንግሥት ነው።

ደግሞ በፖለቲካ ሳይሆን በተፈጥሮና በልማድ የሆነው የሕዝቡ ደግነት በጣም ሲያስደንቀኝ ይኖራል። ከዚህም በኋላ በሐምሌ 14 ቀን ከሎንዶን ወደ ፓሪስ ተመለስን።

ቀጥሎም አውሮጳ ድረስ መጥቼ የዓለም ሰላም የተመሠረተበትን ፡ የዓለም መንግሥታት ማኅበር የቆመበትንና እኛም ማኅበረተኛ የሆንበትን ጄኔቭን ሳላይ ወደ ሀገሬ አልመለስም በማለት ፣ በሐምሌ 21 ከፓሪስ ወደ ጄኔቭ ሔድሁ። ነገር ግን ወራቱ የዕረፍት ጊዜ ስለ ነበረ ፣ ዋናው ጸሐፊ አልነበሩምና ለጊዜው በዚያው የተገኙት ጸሐፊዎች በደስታ ተቀብለው የጽሕፈት ቤቱን ሁሉ በየክፍሉ አሳዩን። ከዚያም የስዊስን ዋና ከተማ ቤርንን አይተን ወደ ፓሪስ ተመለስን።

ደግሞ በኦፊሴልም ሳይሆን በግል የጀርመንን ከተማ ቤርሊንን ለማየት ፍጹም ፈቃዴ ሆኖ ሳለ ፣ ወደ ሀገሬ የምመለስበት ጊዜው በመቃረቡ ቤርሊንን ለማየት ባለመቻሌ እያዘንሁ ከኔ ጋራ ከነበሩት መኳንንቶች ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴና ሣህሌ ፀዳሉ ፣ ተስፋዬ ተገኝ የወዳጅነት ደብዳቤ ይዘው ወደ ቤርሊን ሔደው ከፕሬዚዳንቱ ከማርሻል ሂንደንቡርግ ጋራ ተገናኝተው እንዲመለሱ አደረግሁ።

ከፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩምፓኒያ ጋራ በውሉ ባንዳንድ ስፍራ በየጊዜው የሚያከራክር ነገር ነበረበትና በወዳጅነት ተነጋግረን ያለችግር በ4 ክፍሎች ተስማምተን ከኩምፓኒያው ፕሬዚዳን ከሙሴ ማክሲም ዤፔተን ጋራ በመፈራረማችን በጣምደስ አለን።

ደግሞ በጅቡቲ በኩል ነፃ የሆነ አንድ ክፍል የባሕር ወደብ ለማግኘት ወደ ፓሪስ በገባንበት ወራት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሙሴ ፒዋንካሬ አመልክተን ሳለን የፕሬዚዳኑና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሹም ሽር በድንገት ስለ ተደረገ ፣ ምላሹን በሌላ ጊዜ እናስታውቃችኋለን የሚል ተስፋ ሰጥተውን ነበርና አሁን ወደ ሀገራችን መመለሳችን ስለ ሆነ ፣ ምላሹን እንዲያስታውቁን ብንጠይቅ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቱር ከዚህ ቀጥሎ ያለው ደብዳቤ ተጻፈልን ።

ነሐሴ 13 ቀን 1924 ዓ.ም

ፓሪስ

ለኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ልዑል ተፈሪመኰንን።

«ልዑል ሆይ ፡፤

ልዑልነትዎ ፈቃዱ ሆኖ ለሀገርዎ ንግድ የሚሆን የባሕር ወደብ በር ስለጠየቁ፣፥ይህንኑም የጠየቁትን በር ለኢትዮጵያ መንግሥት ለመስጠት የፈረንሳይ ሬኾብሊክ መንግሥት ጽኑ በሆነ ምኞት ነገሩን መርምሮ ለመጨረስና የሁለቱ አገሮች መንግሥቶች የሚስማሙበትን ቃል ከዚህ ሳይሔዱ አስቀድሞ ለልዑልነትዎ መስጠት ደስ ባለኝ ነበር።

ነገር ግን የአማካሪዎቹ ፕሬዚዳን ከሔዱበት አገር ቶሎ ሳይመለሱ በመቅረታቸው ፡ ይኸው የሚደረገው ስምምነት ትልቅ ነገር ስለ ሆነ ፡ መላው የፈረንሳይ ሬፑብሊክ መንግሥት በግድ በነገሩ ሊመክርበት የሚያስፈልግ ነው። ስለዚህም ስምምነቱ ሳይጻፍ እስካሁን ቆየ። ከብዙ ዘመን ጀምሮ የፈረንሳይ መንግሥት በታሪክ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ባንድነት የሚያስተሳስረው የወዳጅነት ማሰሪያ እንደገና ደግሞ የሁለቱን መንግሥታት ፍቅር ጽኑ ለማድረግ የጠየቁት ነገር እንደገና መነሣቱ አይቀርም ። ይኸውም እንደገና በፍጥነት ተነሡቶ ጽኑ በሆነ ምኞት ስምምነቱ ተጽፎ ያልቃል ብዬ ለልዑልነትዎ አደላድዬ በማክበር አስታውቃለሁ ።

እነዚህ የሚዋደዱና ጐረቤቶች የሆኑ ሁለቱ መንግሥቶች በመካከላቸው እንዲኖር በሚያስቡት ጥቅም ነገር ላይ ሁሉ በፍጥነት ስምምነቱን ለመጨረስ ጊዜው እስካሁን ሳይመች ቀረ። ነገር ግን ወደ ፊት ያለ ጥርጥር በሚደረገው ስምምነት ልዑልነትዎ ወደ ፈረንሳይ አገር መጥተው ስለ ሰነበቱ ከልብ ጥልቅ የሆነ ፍቅር በሕዝቡ ልብ ማኖርዎን የሚመሰክር ብዙ መታሰቢያ ሆኖ ያገኙታል። የሁለቱም መንግሥታት የፍቅርና የጥቅም መታሰቢያ እንደ ገና እየለማ እንዲሔድ የሚያስፈልገውን ለማድረግ አንዳችም ነገር አይዘነጋም።

የፈረንሳይ ሬኾብሊክ መንግሥት ለኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት ዘውዲቱ የሚያስብላቸውን መልካም ምኞትና ተድላ ፡ የሕዝባቸውንም ልማት እንዲያስታውቁልን ልዑልነትዎን እለምንዎታለሁ።

(ፊርማ) ረኒ ረኑል ፡

ይህንንም ደብዳቤ ባነበብን ጊዜ የስምምነቱ አሳብ ምንም ለጊዜው ባይጻፍ እንኳ ፣ የደብዳቤው ቃል ወደ ፊት በቶሎ እንዲፈጸም ተስፋ የሚሰጥ በመሆኑ ደስ አለን። ወደ ሀገራችንም የምንመለስበት ጊዜው እንደ ተቃረበ ስለ ተረዳነው ፡ የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን የተባለ አዲስ ኒሻንና ደግሞ የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት እንዲሠራና ወደ አዲስ አበባ እንዲላክ ፡ በንግሥት ዘውዲቱና በእኛም መልክ አዲስ ቱምብር እንዲታተም ፡ ለሚኒስቴሮችም ክፍል የሚያስፈልጉት መጻሕፍት እንዲገዙ ትእዛዝ አደረግን ።

# ምዕራፍ 20

## ከፓሪስ ወደ ግሪክ ከተማ ወደ አቴና ።

ከአዲሱ የፈረንሳይ ሬፒብሊክ ፕሬዚዳን ከክቡር ሙሴ ዱሜርግ ጋራ ገና አልተዋወቅንም ነበርና በቀጠሮ ሻቶ ደ ራምቡዬ በሚባለው ቤተ መንግሥት ተገናኝተን ከተዋወቅን በኋላ ፣ ወዲያው ተሰነባብተን በነሐሴ 7 ቀን ለአቴና መንገዳችን ወደ ማርሴይ ተጓዝን። እስከ ማርሴይም የሚሸኙን የፈረንሳይ ባለሥልጣኖችና የቀድሞ ወዳጃችን ሙሴ ላጋርድ ከእኛው ጋራ ነበሩ።

ከማርሴይም በነሐሴ 9 አምፗዝ በሚባል አነስተኛ መርከብ ተሳፈርን። ባራተኛውም ቀን ፒሬ ከሚባለው ከግሪክ የባሕር ወደብ ከተማ ስንደርስ ፣ በአየር አይሮፕላኖች እያንዣበቡ ፡ በባሕርም የጦር መርከቦች መድፍ እየተኩሱ በታላቅ ክብር ተቀበሉን። ከዚያም አልፈን ፋሌሮን ከሚባለው ከተማ ስንደርስ የግሪክ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ሶፋሊስ ከሚኒስትሮችና ከጦር አለቆች ጋራ ሆነው ተቀበሉን። ከዚያም በባቡር ሆነን ወደ አቴና ተጓዝን። በባቡር መቋሚያም የሬፒብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ክቡር አድሚራል ኮንቶሪዮቲስ ካገሩ መኳንንቶችና ከውጭ አገር ዲፕሎማቲኮች ጋራሆነው ተቀበሉን። ወዲያውም በአቴና ወደ አለው ወደ ዋናው ቤተ ክርስቲያን ገብተን ሊቀ ጳጳሳቱ ክሪሶስቶሞስ ጸሎተ ቡራኬ ካደረጉ በኋላ ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀው ወደ ቤተ መንግሥቱገባን።

በራትም ግብዣ ላይ ፕሬዚዳኑ አድሚራል ኮንቶሪዮቲስ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ከቀድሞ ጀምሮ ጸንቶ የቆየውን ወዳጅነት ፡ የሁለቱ መንግሥታት ሕዝብ ታሪካቸው የተቃረበ መሆኑን እያስረዱ ተናገሩ ።

እኛም ከቀድሞ ጀምሮ አቴና የጥበብና የዕውቀት ምንጭ መሆኗን ፣ የሕዝቡንም ደግነት በታሪካችን ማግኘታችንንና ን ፣ወደፊትም በኢትዮጵያ ለሚኖሩት ግሪኮች ሁሉ እርዳታ ለማድረግ መፍቀዳችንን እየገለጥን ነገር ናቸው።

በማግስቱም አክሮፖሊስ የሚባለውን የቀድሞ ዘመን የአማልክት የጣዖታት ቤተ መቅደስ ሕንፃ አየን። ከዚያም ስንመለስ አካዳሚውንና ልዩ ልዩ ሙዜዬውም አየን ።

በነሐሴ 13 እስታዲውም በሚባል ስፍራ ልዩ ልዩ የሆነ የጅምናስቲክ ጨዋታና የወታደር ሰልፍ በያይነቱ አሳዩን ።

ወደ ማታም ዋናውን የአቴናን ዩኒቬርሲቲ ለማየት ሔደን ነበርና የዩኒቬርሲቲው አለቃ ሙሴ ዲሜትሪ ፓፓፒሌያስ ከፍ ባለ ስፍራ ቆሞ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናገረ ።

«ልዑል ሆይ ፡

የአቴና ዩኒቬርሲቲ በመካከሉ የግሪክ አገር ነፍስ የሚገለጥበት ነው። ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ታሪክ በተመሠረተ ፍቅርና በማይለያይ ማሰሪያ ከግሪክ አገር ጋራ የተሳሰረውን የሕዝብ እንደራሴ ዛሬ ማታ በመቀበላችን ደስ ብሎናል። ፡

አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት የሆናቸውን እነዚህን መታሰቢያዎች የልዑልነትዎ በእኛ መካከል መገኘት ሊያጠብቃቸውና ሊያድሳቸው ይችላል።

ሁለት ግሪኮች ፍሬምናጦስና ኤዲስዮስ የነጋዴው የሜሮፒዮስ ልጆች በኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ ተማርከው ወደ አገሩ ውስጥ ገቡ። የሃይማኖትም ሐዋርያ በመሆን ላገሩ ሰው በማስተማር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ።

ልዑል ሆይ ፡ ሁለቱን አገሮች የሚያስተሳስር ፍቅር በዚያን ጊዜ ተጀመረ። በ325 ዓ. ም. የክርስቲያኒቱ የግሪክ አገር ትልቁ ጳጳስ አትናቴዎስ እስክንድርያ ላይ በታላቅ ክብር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች ብሎ ለፍሬምናጦስ ስም ሰጠው። ደግሞ የዚህ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ አድርጎ ቀባው።

ደግሞ በልዩ አደራረግ ሄሊዮዶር ዲ. ኤሜሳ በጻፈው ሮማን በሚባለው መጽሐፍ እነዚህን የታሪክ መታሰቢያዎች ያነሣል። በዚሁም መጽሐፉ የኢትዮጵያን ንጉሥ ልጅ ቆንጆዩቱንና መልካሚቱን ያነሣል ።

ለሆሜርና ለሄሮዶቱስ በታሪኩ ስለ እርሱ ለሚናገረው ለስትራቦን በጀዎግራፊያው በብዙ ለሚያስብላቸው ኢትዮጵያውያን በጣምየታወቁ ነበሩ። በነዚህም ሲወርዱ ሲዋረዱ በመጡት ታሪኮች ምክንያት ያዲሲቱ ኢትዮጵያ ነገሥታት ሁል ጊዜ ከግሪክ አገር ጋራ የእውነተኛ ፍቅር መገናኛ አኑረዋል። ከሁሉም ይልቅ ዐፄ ዮሐንስና ዓፋ ምኒልክ ከግሪክ መንግሥት ጋራ በሚጻጻፉት ደብዳቤዎች ለሀገራችን እርግጠኛ ፍቅር ያለበት ቃል ተናግረዋል።

ልዑል ሆይ ፡ ባገርዎ ውስጥ የሚኖሩት ወንድሞቻችን ጥልቅ በሆነ ምስጋና በሕዝብዎ ዘንድ ያገኙትን መልካም አቀባበልና ፍቅር ዘወትር ይነግሩናል። ይኸውም እንደ ወንድማማች ለመሆን እስቲፈቀድላቸው ድረስ ነው። የዚህን ሕዝብ እንደራሴ ዛሬ በእኛ ዘንድ እንግዳ ሆነው በመቀበላችን እጅግ ደስ ብሎናል።

የግሪክ ጸሐፊዎች የመንገዳቸውን አኳኋን የጸፉና መጽሐፋቸውም ጥቅምሆኖ የሚነበብላቸው የኢትዮጵያን የፍጥረቱን ከፍ ያለ ማማር አጥብቀው አስረድተዋል። የነፋሱንና የዛፉን የቅጠሉንም ልዩነት የፀሐዩን ማማር በብርሃኑም የሀገሩን ማማር የሚገልጠውን ጽፈዋል።

ልዑል ሆይ ፡ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ግሪኮች ለሀገርዎ የሚሆነውን ሁሉ እንደ ራሳቸው ጥቅም ያዩታል። ምክንያትም ባገኙ ቀ፡ጥር በኢትዮጵያ ነገሥታትና በሕዝቡም ላይ ያላቸውን የፍቅር አሳብ ይመሰክራሉ።

ይህም አሳብ እናንተ ለእኛ ባላችሁ ወዳጅነት ብቻ የተነሣ አይደለም ። ባለፈው ታሪካችንና በጠባያችን እየተገፋፋን የአእምሮን ከፍታና ወደጀግንነት የሚያደርሰውን የነፃነት ፍቅር ሁሉ በማክበራችንም ነው። ስለዚህ ታሪካችን ባደረገልን ትምህርት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያለውን ፍቅራችንን ማጠንከራችን ምንም እንግዳ ነገር አይደለም ።

ከሌላው አፍሪቃ አገር ሁሉ በሚለይዋት ከፍጥረት በተሰጧት ተራሮችዋ የተነሣ ኢትዮጵያ ሁለጊዜ ነፃነቷን ጠብቃ መኖርዋን እናውቃለን ። በጨካኝና በአረመኔ ፡ በደረቅ በረሃ መካከል ኢትዮጵያ ከአንድ ሺ ዘመን ይበልጥ የክርስቲያንነት ጥግ ሆነች ለማለት የተገባ ነው። ሆሜር ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ይበልጣሉ ይላቸው ነበር። ዲዮዶርም ደግነታቸውን ይናገራል። ለነፃነታቸውም መዋጋታቸውን ያደንቃል ።

በታላቁ እስክንድርና በወራሾቹም ዘመን የግሪኮች ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ገብቶ አዲስ የሥልጣኔ መንገድ ከፍቶ ነበር። ማለፉንም የሚያስረዳ ማስታወሻ (ያገር ካርታ) ጻፈ። በጥሊሞሶችና የቢዛንስ ንጉሦች መሠረቱን ለማቆምና ግዛቱን እስከ ኤርትራ (ቀይ ባሕር) ለማስፋት የኢትዮጵያን ሕዝብ ይመኙ ነበር። ቢዛንስ ከፋርሶች ጋራ ሲዋጋ የኢትዮጵያውያንን ኃይል አጋፈጠላቸው። የልዑልነትዎ አገር በሜዲቴራኒና በህንድ ያሉት የሠለጠኑት ሕዝብ መንገድና መገናኛ ሆኖ ነበር። ግሪኮች በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ በጣም የሚከበሩ ስለ ነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት የግሪክ ቋንቋ ያውቁ ነበረ ተብሎ ተጽፏል ።

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመረመሩ ሰዎች ባራተኛው መቶ ዓመት ይኸው ቤተ ክርስቲያን ፣ በሃይማኖት ጸንቶ የክርስቲያን ሃይማኖት በአፍሪቃ ባሉት በሩቅ አገሮች ሁሉ እንዲሰፋ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደርግ ነበር። ነገር ግን የእስላም መነሣትና በየቀኑም እየበዛ መሔዱ በሰይፍ ኃይል በአፍሪቃ ሰሜን ያሉትን አገሮች ድል እያደረገ ፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃይል በብዙ አደከመው። በኋላ ግን ከፍጥረታቸው ባገኙት ጀግንነት ተከላክለው የእስላምን ኃይል አሸነፉ። እስላሞችም አቃጥለውት በነበረው ስፍራ ላይ እንደገና የአክሱምን ቤተ ክርስቲያን ሠሩ። የዚህም ቤተ ክርስቲያን እንደገና መሠራቱ ለኢትዮጵያ ትልቅ ዕጣና መታደል ነው ለማለት ይቻላል።

በነገሥታቱና በገዥዎቹም ብልህነት ካለፈው መቶ ዓመት ጀምሮ ፣ ይህ አገር እንደገና የመታደስን መንገድ ያዘ። ይኸውም የመታደስ መንገድ ይህን የተወደደና ጀግና ሕዝብ በትክክልነት ወደ ሕዝብ አንድነት የሚመራውነው።

የአቴና ዩኒቬርሲቲ በዚህ የግሪክ ሕዝብ አለቆች በተሰበሰቡበት ለጀግናው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ገዥ ፡ ለመኰንን ልጅ ሰላም ይላል። የግሪክ ሕዝብ ለሕዝብም ልማት የሚመኘውን ምኞትና በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን የፍቅር ማሰሪያ እያጠበቀ ለመሔድ ቁርጥ አሳብ ማድረጉን እንዲቀበሉት ይለምናል ብሎ ጨረሰ።

ይህንንም ከጥንታዊ ታሪክ የተለቀመ የወዳጅነት ቃል በመስማታችን ደስ ስላለን ከጥልቅ ልባችን የሆነ የምስጋና ቃል ተናግረን ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለስን።

በማግስቱም ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ ክሪሶስቶሞስና ከሌሎችም ታሪኩን በጣም ከሚያውቁ ሊቃውንቶች ጋራሆነን ቅዱስ ጳውሎስ የአቴናን ሰዎች ያስተማረበትን አርዩስፋጎስ የሚባለውን ለማየት ሔድን። ስፍራውም በአክሮፖሊስ አጠገብ ነው። ሊቀ ጳጳሱም የዚህን ስፍራ ታሪክ ከግብረ ሐዋርያትእየጠቀሱ በብዙ ተናገሩ።

አቴና የጥበብና የዕውቀት ምንጭ መሆኗን በታሪክ ስናነበው ቆይተን ነበርና አሁን በዓይናችን በማየታችን ደስ አለን ።

በአቴናም ካየነው ሁሉ ዋና መታሰቢያ አድርገን በልባችን የያዝነው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

የአክሮፖሊስ የአማልክት የጣዖታት ሕንፃ አርዩስፋጎስ ፣ አካዳሚና የልዩ ልዩ አንቲካ ቤት ፡ የመጻሕፍት ቤት ፡ ዩኒቬርሲቲው ፡ በእስታዲዎ የተደረገው የጅምናስቲክ ጨዋታና የወታደር ሰልፍ ፡ በአክሮፖሊስ ፍራሽ ውስጥ የታየው የሄሮዲስ አንቲኮስ ትያትር ፡ በፋሌሮን ባሕር ዳር የተደረገው ወደ አየር የተወረወረው የአርትፊሴል ተኩስ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እየመሰለ በአየሩ ላይ የተዘረጋው ነው።



በኅዳር በሽታ ጊዜ ከነ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አባይነህ ፡ ኢጋፋሪ ከልክሌ በጅሮንድ ሰብስቤ ፊታውራሪ ላንትይደሩ ደጃች ዘውዴ አየለ ሻለቃ በልሁና ቀኝዝማች ይነሱ አባይነህ



በስደት ሳለን

# ምዕራፍ 21

## ከአቴና ወደ አገራችን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ።

ስለ ኢየሩሳሌም ገዳማችን ቦታ ነገር በእኛና በሃይማኖት አባቶቻችን በግብጻውያን መካከል የተነሣው ነገር ፡ በወዳጅነት እንዲፈጸም የብዙ ዘመን አሳባችን ስለ ሆነ ኢየሩሳሌም በደረስንበት ወራት በጽሕፈት አድርገን ለሊቀ ጳጳሱ ብናስታውቃቸው በነገሩ እናስብበታለን የሚል ምላሽ ሰጥተውን ነበርና ምናልባት በነገሩ አስበውበት ቆይተው እንደሆነ የነገሩን ፍጻሜ ለመስማትና ለማወቅ ከአቴና ወደ ካይሮ ሔድን። ከፓትሪያርኩ ከአቡነ ቄርሎስ ጋራ ተገናኝተን የዚሁኑ የገዳማችንን ነገር ለመነጋገር ስለ አሰብን በነሐሴ 13 ቀን ከአቴና ተነሥተን እስፒሪያ በሚባል መርከብ ወደ እስክንድርያ ተጓዝን።

ከእስክንድርያም ወደ ካይሮ ወጥተን ከፓትሪያርኩ ከአቡነ ቄርሎስ ጋራ ከተገናኘን በኋላ የኢየሩሳሌም ገዳማችን ነገር በማኅበሩ አማካሪዎች ተመክሮ ገና አለመጨረሱን ስለ ነገሩን ትልቅ ኀዘን ሆነብን። ነገር ግን ወደ ሀገራችን የምንመለስበትጊዜ በጣም ቀርቦ ነበርና የነገሩን ፍጻሜ ሰምቶ የሚያመጣልን አንድ ሰው ትተን ለመሔድማሰባችንን ለፓትሪያርኩ አስታውቀን ከተሰነባበትን በኋላ ወደ ስዊዝ ተጓዝን። ከስዊዝም በነሐሴ 21 ቀን ሽሊ በሚባል በሜሳጀሪ ኩምፓኒያ መርከብ ተሳፍረን በ25 ነሐሴ ጅቡቲ ደረስን ።

በጅቡቲም ከግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ እኛን ለመቀበል ተልከው የመጡት አሁን ራስ የተባለው ደጃዝማች ጌታቸውና ደጃዝማች የተባለው ቀኛዝማች ዓምዴ ፡ በጅሮንድ ሣህለ ድንግል ወደ መርከቡ ውስጥ ገብተው ከተገናኙን በኋላ የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱን ደብዳቤ አስረከቡን ። ቃሉም ቀጥሎያለው ነው።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ሥይምተ እግዚአብሔር ዘውዲቱ

ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ፡

ይድረስ ከልጄ ከልዑል ተፈሪ መኰንን ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ። እንደምን ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ።

ስለ ሀገራችን ነፃነትና መታፈር ስለ ክብርዋም ስትል ፡ በማታውቀውና ሙቀት በሆነ አገር በመድከምህ ሳዝን ነበርና አሁን በደኅና በመመለስህ ብዙ ደስ አለኝ። ካሰብነው አገር ሁሉ ደርሰህ ርስትህ ወደምትሆን ወደ ኢትዮጵያ በሕይወት ስለ መመለስህ ፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል ። ይልቁንም ይህ ያሁኑ የአውሮጳ ጉዞህ መጀመሪያ ነገር ስለ ሆነ እጅግ ተጨንቀን ነበርና አሁን በደኅና ተመልሰህ በመምጣትህ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ ሊለው የተገባ ነው። አሁንም እንደዚሁ በሰላም መጥተህ በዓይነ ሥጋ ለመተያየትያብቃን። የሚቀበሉህም ደጃዝማች ጌታቸውና በጅሮንድ ሣህለ ድንግልን ፡ ቀኛዝማች ዓምዴን ልከናቸው መጥተዋል ።

ነሐሴ 19 ቀን 1916 ዓ. ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ።

ከጅቡቲ በነሐሴ 26 ተነሡተን ድሬዳዋ ላይ አንድ ቀን ውሎ አድርገን በ29 አዲስ አበባ ገባን ።

በባቡር መቋሚያ የውጭ አገር ዲፕሎማቲኮች በሙሉ ፡ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ከሊቃውንቱ ጋራ ፡ ሚኒስትሮችና የጦር አለቆችም የከተማውም ሕዝብ ስፍራ ጠቦት ሲጠባበቅ ነበርና መድረሳችንን የሚያመለክት መድፍ እየተተኰሰ በደስታ ተቀበሉን ።

ወደ ቤተ መንግሥትም በገባን ጊዜ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ የናፍቆትና የማክበር ሰላምታ ካቀረብን በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገርን።

ግርማዊት ንግሥት ሆይ ፡

የኢትዮጵያን ታሪክ ብንመረምር ፡ ከብዙ መንግሥታት ቀደምትነት እንዳላት ፡ በጥበብና በዕውቀትም የከበረች እንደ ነበረች ፡ ታላላቆች ታሪክ ጸሐፊዎች በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው በጣም ያስረዳናል ።

ንግሥተ ሳባም የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ወደ ኢየሩሳሌም በወረደች ጊዜ ለሰሎሞን ልዩ ልዩ የሆነ ገጸ በረከት ወስዳ እንደ ሰጠችው ክብረ ነገሥታችን ይመሰክራል። ይህም የኢትዮጵያን ቀደምትነትና ጥበቧንም ያስረዳናል ።

ደግሞ አባቶቻችን የኢትዮጵያ ነገሥታት ባሕርን ተሻግረው ፡ የመን የሚባለውን የዐረብ አገር ይገዙ እንደ ነበሩ ፡ በታሪክ ተጽፏልና ይህም ኃይለኛ መንግሥትእንደ ነበረች ያስረዳል ።

ነገር ግን በፊቷም በኋላዋም ከሚኖሩ አረማውያን ጋራ በየጊዜው ጦርነት ስለ ተነሣባት ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ በጣም ለመቃረብ የተመቸ ጊዜ ሳታገኝ ቀየች።

ግርማዊ አባትዎ ትልቁ ዳግማዊ ምኒልክ ዙፋናቸውን ከሚደግፉ ኃያላን ጋራ የጠፋውን አገር ሁሉ እንደ ገና አቅንተው እንደ ጥንቱ ኢትዮጵያን ሰፊ አደረጓት። ከውጭ አገርም መንግሥታት ጋራ ለመቃረብ የሚቻለውን ሁሉ አደረጉ።

ለዚሁም ሥራ በመጀመሪያ ወንድማቸውና አገልጋያቸው የሚሆኑ አባቴን ልዑል ራስ መኰንንን በመምረጣቸው በሁለቱም መካከል ትልቅ መተማመን እንደ ነበረ ያስረዳናል ።

አሁንም ግርማዊት ንግሥት የኢትዮጵያን ነፃነት ለዓለም ሁሉ ለመግለጽ ሲሉ እኔ ልጅዎ ወደ አውሮጳ ሔጄ ከነገሥታቱ ጋራ እንድገናኝና እንድቃረብ ፈቃድ በማድረግዎ ዓለም ሁሉ ተደንቋል። በዚሁም ምክንያት ኢትዮጵያ እንደ ከበረች የግርማዊትነትዎም ስም እንደ ተመሰገነ ወሬውን ሳይሰሙት አይቀሩም።

ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያ ልጆቿን በማስተማርና በማሠልጠን እንደ ጥንቷ ከትልቁ ደረጃ ትደርሳለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። የአውሮጳ ነገሥታትና ፕሬዚዳኖችም ሰላምታቸውን ከምስጋናቸው ጋራ ለግርማዊትነትዎ እንዳቀርብላቸው መለመናቸውን አስታውቃለሁ ።

ከዚህም በኋላ ጸሐፊ ትእዛዙ ስለ ግርማዊት ንግሥት ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አነበበ።

«ልጄ አልጋ ወራሽ ሆይ ፡

ስለ ሀገራችን ልማትና ስለ ሕዝባችን ጥቅም ከአውሮጳ ነገሥታት ጋራ ለመገናኘት ስትሔድ በልቅሶና በእንባ ተሰነባብተን ነበር። አሁን ግን በደኅና ተመልሰህ መጥተህ ዓይንህን ስለ አየሁት ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ። ይህችም ቀን የተባረከች ትሁን።

ደግሞ ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንም ጥንታዊት ብትሆን ፣ ብዙውን ዘመን በአረማውያን ስለ ተከበበች ከውጭ አገር ነገሥታት ርቃ መኖርዋ እርግጥ ነው።  ኋላ ግን አባቴ ዳግማዊ ምኒልክ አባቶቻቸው የጀመሩትን ዙሪያውን አገር አቅንተውና አደላድለው ሲጨርሱ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ ለመቃረብ ቢያስቡ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ መካከል አባትህን ራስ መኰንን»ንንን መርጠው በማያውቀው አገር ስለ ላኩት ከነገሥታቱ ጋራ ፍቅር አጽንቶ የዳግማዊ ምኒልክንም ፈቃድ ፈጽሞ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

አንተም የታመንህ ልጄ እንደ አባትህ በማታውቀው አገር ሐደህ የባሕሩን ሁከት ፣ የፀሐዩን ሙቀት ታግሠህ ፡ ለሀገራችን ልማትና ለሕዝባችን ሀብት ያሰብነውን አሳብ ፈጽመህ ፣ ጥንት የቆመውንም የነገሥታቱን ወዳጅነትና ፍቅር አስፍተህ ፈቃዴን ፈጽመህ ስለ መጣህ በጣም ደስ ብሎኛል።

ኢትዮጵያም የደስታ ምስጋናዋን ወደ እግዚአብሔር ታቀርባለች ። እናንተም አብራችሁ የሔዳችሁት መሳፍንትና መኳንንት ከቀ‘‘ጥር ሳትጐድሉ በደኅና ተመልሳችሁ ስለ መጣችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ። ወደ ፊትም እንደ አያችሁት አገር ለሕዝባችን ጥቅምና ለሀገራችን ልማት በሚሆነው ሁሉ እንድታስቡበትና እንድትተጉበት እንዲረዳችሁ ፈጣሪያችንን እለምናለሁ» ብሎ ጨረሰ።

ከዚህም በኋላ ወደ መኖሪያ ቤታችን ሔደን ቤተ ዘመዶቻችንን ሁሉ በደኅና ስለ ማግኘታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረብን ።

# ምዕራፍ 22

## የእንግሊዝ መንግሥት የጣናን ባሕር ሲገድብ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ከኤርትራ ወሰን ጀምሮ በኢትዮጵያ መሃል ለመሃል አቋርጦ እስከ ኢጣልያ ሱማሌ የምድር ባቡር ሲሠራ ለመረዳዳት ስለ መዋዋላቸው ።

የእንግሊዝ መንግሥት በ1895 (1902) ዓ. ም. ሌፍትናንት ኩሎኔል ጆንሌን ሐሪንግተን የሚባለውን ልዩ መልክተኛ አድርጎ ልኮ ፣ የኢትዮጵያመንግሥት ወደ ዐባይ ወንዝ የሚገቡትን ትንንሾች ወንዞችና የሶባትን ወንዝ በጭራሽ አቋርጦ እንዳያስቀር ፣ ከእንግሊዝ ሱዳን መንግሥትና ከዐፄ ምኒልክ ጋራ በስምምነት ተዋውሎ ነበር። ዐፄ ምኒልክም ይህንን ውል ስለፈቀዱ ፣ የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት በያመቱ ዐሥር ዐሥር ሺጊኒ ለኢትዮጵያ መንግሥት ይሰጣል ብሎ መላክተኛው በደብዳቤ ብቻ ጽፎ ሰጥቶ ነበር። በኋላ ደግሞ የዐባይ ውሃ በበጋ እየበዛ በክረምት ያንሳልና በጣና ባሕር ላይ ገድበን ውሃውን እየቀነስን እንድንወስድ ይፈቀድልን። ምናልባትም በጣና ባሕር ላይ ሲገድብ ውሃው በዝቶ በጣና ባሕር ውስጥ ያሉትን ደሴቶችና አብያተ ክርስቲያናት እንዳያሰጥም መሐንዲሶች ልከን አንድ ራፖር ለኢትዮጵያ መንግሥት እናቀርባለን ብለው ተፈቅዶላቸው በ1906 (1899) ዓ. ም. መሐንዲሶች ልከው ነበር ።

ከዚህ ቀጥሎ ከትልቁ ጦርነት በኋላ በ1912 (1919) ዓ. ም. የኢጣልያ መንግሥት ወደ ሎንዶን መላክተኞች ልኮ ፡ የእንግሊዝ መንግሥት የጣናን ባሕር እንዲገድብ የኢጣልያ መንግሥት ከኤርትራ ወሰን ጀምሮ በኢትዮጵያ መሃል ለመሃል አቋርጦ የምድር ባቡር እንዲሠራ እንረዳዳ የማለት አሳብ አቅርቦ ነበረ። ነገር ግን የእንግሊዝ መንግሥት በቀጥታ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ መነጋገር ስለ ጀመረ የኢጣልያ መንግሥት ያቀረበለትን አሳብ ለጊዜው ሳይቀበለው ቀረ።

ከዚህም በኋላ በ1916 ዓ. ም. እኛ የግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ 5ኛ እንግዶች ሆነን ወደ ሎንዶን በመጣን ጊዜ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ካሉት አንዳንድ ጉዳዮችን ለመነጋገርና ለመጨረስ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምስተር ማክዶናልድ ጋራ በቀጠሮ ተገናኝተን ስንነጋገር ፣ ከዚህ ቀደም የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት የጀመረው የጣና ባሕር መገደብ ነገር እንዲፈጸም ቢያደርጉልን ደስ ይለናል ብለው ጥያቄ ቢያቀርቡልን ፣ የጣናን ባሕር እኛ በጣም በታወቁ መሐነዲሶች አስገድበን የሁለቱ መንግሥታት ጥቅም ተጠብቆ የሚኖርበትን ውል ተዋውለን በኪራይ ብንሰጣችሁ መልካም ነገር ይመስለናል ብለን አሳባችንን ገለጥንላቸው።

ምስተር ማክዶናልድም መሐንዲሶቹን የምትቀጥሩት ከማንኛው መንግሥት መሆኑን አስቀድማችሁ ካስታወቃችሁንና ካስመረጣችሁን ፣ ይህንን አሳብዎን መቀበል ፈቃዳችን ነው ካሉ በኋላ ፣ ወዲያው ከአሜሪካ ዩናይትድ ስቴት መሐንዲሶች ለመቅጠር አትፈቅዱም ወይ ቢሉ በደስታ እንፈቅዳለን ብለን በዋናው ነገር በቃል ተስማምተን ከጥቂት ሳምንት በኋላ ፣ ይህንኑ በጽሕፈት አረጋገጥንላቸው። የኢጣልያ መንግሥት ግን ፣ የእንግሊዝ መንግሥትና እኛ በቀጥታ ተነጋግረን የጣናን ባሕር ለማስገደብ ነገሩ መቆረጡን በሰማ ጊዜ ፣ ከኤርትራ ወሰን ጀምሮ በኢትዮጵያ መሃል ለመሃል አቋርጦ እስከ ኢጣልያ ሱማሌ የምድር ባቡር ለመሥራት የእንግሊዝ መንግሥት እንዲረዳው ያሰበው አሳብ እንዳይቀርበት ፡ በ1918 (1925) ዓ.ም. እንደገና የእንግሊዝን መንግሥት እየጐተጐተ አነሣሥቶ ከዚህ ቀድሞ በ1912 (1919) ዓ. ም. የጀመረው አሳብ እንዲፈጸምለት ፡ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋራ ሮማ ላይ ተነጋግሮና ተስማምቶ የተስማሙበትን ቃል በደብዳቤ ተቀባበሉ። በደብዳቤም መቀባበል ብቻ ሳይሆን ጄኔቭ ላይ ከዓለም መንግሥታት ማኅበር መዝገብ እንዲገባ አደረጉ። ይህንንም ሲያደርጉ ለባለሥልጣኑ ለኢትዮጵያ

መንግሥት አንድም ቃል አላስታወቁትም ነበር ። ተስማምተው የተቀባበሉትም የደብዳቤው ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ሰር ሮለንድ ግራሃም ለሙሴ ሙሶሊኒ ።

ሮማ ታኅሣሥ 20 1925

ከነጭ ዐባይና ከጥቁር ዐባይ ወደነዚህም ወንዞች የሚገቡት የወንዞች ውሃ ለመስኖ የሚያስፈልግ ስለ ሆነ ውሃው እንዳያቋርጥ ፥ የሚቻልም ቢሆን እንዲበዛ ማድረግ ለምስርና ለሱዳን እጅግ ታላቅ የሆነ ጥቅም መሆኑን ክቡርነትዎ አይስተውም። እንደዚህም ለማድረግ ከዚህ ቀድሞ የተቀረጠው ልዩልዩ አሳብ ዛሬ አሁን ይሠራበታል። ሌሎቹም ይመከርባቸዋል ።

በዚህ ነገር ምስር ያላትን ጥቅም አስቦ በምስር ስምና በሱዳን ስም በባለአደራነት ሆኖ ፣ የእንግሊዝ መንግሥት አዲስ አበባ ላይ የጀመረው ንግግር ለክቡርነትዎ የታወቀ ነው። የንግግሩም መሠረት ከኢትዮጵያ መንግሥት ኮንሴሲዮን ተቀብሎ በጣና ባሕርና በዳሩ ግድብ ሠርቶ ውሃውን ለማጠራቀምና ለነጭ ዐባይ ወንዝ እንዲሆን ለማድረግ ነው። እስከ ዛሬም ድረስ ይህ ንግግር ምንም ፍሬ ያለው ነገር አላገኘም።

በኖቤምበር 1919 (ኅዳር 1912) ዓ. ም. የኢጣልያ መንግሥት መልክተኞች ሎንዶን በነበሩ ጊዜ ስለዚህ ነገር ኢጣልያ የምታደርገውን እርዳታ ቀጥሎ ባለው አኳኋን አቅርበው ነበር።

የእንግሊዝ መንግሥት ስለ ጣና ባሕር ውሃ ነገር ያለውን ታላቅ ጥቅም ተመልክቶ በባሕሩ ላይ ለኢጣልያ ጥቅም በተሰጠው ክፍል ግድብ እንዲሠራ ከኢትዮጵያ መንግሥት ኮንሲሲዮን ሲጠይቅ የኢጣልያ መንግሥት ይረዳዋል። ይህም ለእንግሊዝ ጥቅም የተሰጠው አውራጃ ወሰን እስቲከለልና በሦስቱ ስምምነት ውስጥ ኢጣልያ ያደረገችው ሬዘርብ በሙሉ እስቲመረመር ድረስ ነው።

የእንግሊዝ መንግሥት ከጣና ባሕር እስከ ሱዳን ድረስ የአውቶሞቢል መንገድ ለመሥራት ከኢትዮጵያ መንግሥት ኮንሴሲዮን ሲጠይቅ የኢጣልያ መንግሥት እንዲደግፈው ይጠይቃል። ይህም የምድር ባቡር እንደ ሦስቱ ስምምነት በአዲስ አበባ በስተምዕራብ በኩል ያልፋል። ለዚህም የምድር ባቡር ሥራ የሚያስፈልገው መሣሪያ ሁሉ ከዚህ በላይ በተመለከተው የአውቶሞቢል መንገድላይ በነፃ ያልፋል።

ኢጣልያ በኢትዮጵያ በስተምዕራብና ከዚህ በላይ የተነገረው የምድርባቡር በሚያልፍበት አገር በሙሉ የተለየ የገንዘብ ጥቅም አገባብ እንዲኖራት በኢጣልያ ክፍል በገንዘብ የሚጠቅም ኮንሴሲዮን ለማግኘት የምታቀርበውን ጥያቄ ሁሉ በኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ እንዲደግፍ እንግሊዝን ትጠይቃለች። ይህንንም ጥያቄ ለፈረንሳዊ ልታቀርብ ሬዘርብ አድርጋለች።

ከዚህ በላይ የቀረበውን አሳብ በዚያ ዘመን የሚቀበለው አልተገኘም ። ዋናውም ምክንያት ለምስርና ለሱዳን ልማት ፥እንዲያውም ለሕይወታቸው የሚያስፈልገውንና ዋና ነገር የሆነውን የወንዞቹን ምንጭ አንድ የውጭ መንግሥት በማናቸውም ብርቱ አሳብ ስለ ተነሣ ነው። ነገር ግን በመታደል በሁለታችን መንግሥቶች መካከል በነበረው የእምነት መገናኛ ምክንያት የግርማዊ መንግሥት በሌላው ጉዳይ ሊፈጽመው ፈቃዱ ሆነ። ስለዚህ የግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት ነገሩን እንደገና መረመረ ።

በዲሴምበር 13 1906 (ታኅሣሥ 4 1899) ዓ.ም. ሎንዶን ላይ የተደረገው ስምምነት በመጀመሪያው ክፍል የተመለከቱት የመንግሥታት ውሎች መሠረት ሆነው ኢትዮጵያ እንደ ነበረች እንድትኖር ውሉን የፈረሙት መንግሥቶች በየወገናቸው ጉዳት እንዳያገኛቸው ጥቅማቸውን ለመጠበቅ ስለ ሆነ ፥ ኢጣልያም ያቀረበችው አሳብ ከዚሁ ስምምነት ቃል ጋራ የማይቃወም መሆኑን የእንግሊዝ መንግሥት ተረዳው።

ከዚህ በኋላ የግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት ከዚህ ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ያወቀላትን ለምስርና ለሱዳን ጥቅም ያለባቸው ውሃዎች እንዳይነኩ ሬዘርብ አድርጎ ፣ ኢጣልያ ያቀረበለትን የመደገፍ እርዳታ በመልካም የሚቀበለውሆነ።

ስለዚህ በግርማዊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቱር ዋና ጸሐፊ ፡ ሥንቅና መሣሪያ ሠራተኛም ፣ ይህን የመሰለውን ሁሉ ከሱዳን ወሰን ጀምሮ እስከ ውሃ መገደቢያው የሚያመላልስበት የአውቶሞቢል መንገድ እንዲሠራና ይህንም መንገድ እያደሰ እንዲጠብቀው የኢትዮጵያ መንግሥት ለግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት ፈቅዶ ፣ ኮንሴሲዮን እንዲሰጠው በአዲስ አበባ ፡ ክቡርነትዎ ጥያቄውን እንዲደግፍለትና እንዲረዳው በማክበር እጠይቃለሁ።

በዚህም ምትክ የግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት የኢጣልያ መንግሥት ከኤርትራ እስከ ኢጣልያ ሱማሌ ወሰን የምድር ባቡር ለመሥራትና ለመዘርጋት ኮንሴሲዮን ለማግኘት ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚያቀርበውን ጥያቄ ለመደገፍ የተዘጋጀ ነው። ይህም የምድር ባቡር ባቡሩን ለመዘርጋትና በባቡሩም ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ሥራ ሁሉ ከዚህ በላይ የተባለውን የአውቶሞቢል መንገድ በሙሉ ነፃነት አቋርጦ ለመሔድ እንዲችል ይሆናል።

ስለዚህ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥት የሚፈልጉት ስለ ጣና ባሕርና ከኤርትራ እስከ ኢጣልያ ሱማሌ ስለሚዘረጋው የምድር ባቡር ኮንሴሲዮን ባንድ ጊዜ ሁለቱም እንዲያገኙ ፡ በኢትዮጵያ ያሉት የእንግሊዝና የኢጣልያ እንደራሴዎች አብረው ሆነው ተማክረው እንዲሠሩ የሚያስፈልገው አንድ ዓይነት የሆነ ትእዛዝ እንዲላክላቸው ያስፈልጋል። ከሁለቱ መንግሥ ታት አንደኛው የጠየቀውን ኮንሴሲዮን አግኝቶ ፡ ሁለተኛው ሳይሆንለት የቀረ እንደ ሆነ የጠየቀውና ያገኘው መንግሥት ደግሞ ሌላው ያላገኘው እንደዚሁ እርሱም እንዲሆንለት በብርታት እርዳታውን ሳያቋርጥ ይረዳዋል ።

የግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት በኢጣልያ መንግሥት ውድ በሆነ እርዳታ የሚያስፈልገውን የጣናን ባሕር ኮንሴሲዮን ያገኘ እንደሆነ በኢትዮጵያምዕራብና ከዚህ በላይ የተባለው ኢጣልያ በገንዘብ ተጠቃሚ እንድትሆንበት ሊያውቅላት የተዘጋጀ ነው። ደግሞ ከዚህ በቀር ከዚህ በላይ በተነገረው አገር ክፍል ውስጥ ኢጣልያ የምትጠይቀው የገንዘብ ጥቅም ፡ኮንሴሲዮን እንድታገኝ ጥያቄዋን ሁሉ ለመደገፍ የግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ ተቀበለ የኢጣልያ መንግሥት በበኩሉ ምስርና ሱዳን ስለ ውሃ ያላቸውን መብት ዐውቆ በነጭ ዐባይና በጥቁር ዐባይ ምንጮች ላይ ወይም በነዚሁ ምንጮች የሚገቡትንና የሚወጡትን ወንዞች እንዳይገድብ ፡ በዋናውም ወንዝ ውሃው እንዳይገባ የሚያስቸግርና ውሃውንም የሚያሳንስ ማናቸውንም ሥራ እንዳይሠራ ግዴታ ይገባል። ስለሆነም በዚያው አውራጃ ላሉት ነዋሪዎች ውሃው እንዲያገለግላቸው ለማድረግ የኤሌክትሪክ መኪና ለማስኬድ ፣ ውሃውን ለመገደብ ወይም ትንሽ ዘርፍ በሆኑ ወንዞች ላይ ለመጠጥ ለእርሻ በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ምግብ የሚሆን ነገር ለመቀበል ፡ የውሃ ማጠራቀሚያ ኩሬ ለመሥራት ይችላል።

የግርማዊ የእንግሊዝ መንግሥት ይህን ምክንያት አድርጎ የጣናን ባሕር ለመገደብና የውሃውንም ሥራ ለመሥራት የተቻለ ያህል ፡ በዚያው ካሉት ሰዎች እየተመረጡ እንዲሠሩ እስካሁን ድረስ በክረምት ወራት ከሚጠራቀመው ይበልጥ የሚያጠራቅም መገደቢያ እንዳይሠራ ለኢጣልያ መንግሥት ያረጋግጥለታል። ስለዚህ የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት የዚህ የውሃ መገደቢያ መሠራት ለምስርና ለሱዳን ከመጥቀም በቀር ያገሩን ልማት የሚያሳድግ ያገሩንም ሕዝብ በገንዘብ ጥቅም እያበለጠገ እንዲሔድ የሚረዳ መሆኑን ተረድቶታል ።

ፊርማ ግራሃም ፡

ሮማ ዲሴምበር 20 1925

(ታኅሣሥ 11 1918) ዓ.ም

ለክቡር ልዩ መልክተኛ በሰር ኤር ግራሃም ።

ክቡርነትዎ ከመንግሥትዎ እንደ ተቀበለው ትእዛዝ ስለ ምስርና ስለ ሱዳን ውሃ ስለ ማጠጣት ጉዳይና በጣና ባሕር ላይ ግድብ ሠርቶ ጥቁር ዐባይ እንዲሞላ ለማድረግ ፤ ከኢትዮጵያ መንግሥት እስካሁን ተደክሞበት ሳይፈጸም ስለ ቆየ ጉዳይ በታኅሣሥ 5 ቀን የጻፉልኝ ደብዳቤ ደርሶኝ በጥንቃቄ ተመልክቼዋለሁ።

ስለዚህም ጉዳይ በኖቤምበር 1919 (ኅዳር 1912) ዓ. ም. እንግሊዝና ኢጣልያ ተባብረው በወዳጅነት እንዲሠሩ የኢጣልያ መንግሥት መላክተኞች በሎንዶን ያቀረቡትን ድርድር ለምስርና ለሱዳን ልማት ለኑሮዋቸውም ጭምር በጣም አስፈላጊ በሆኑት ወንዞችና ምንጮች ላይ መቆጣጠር፡ ላንድ ለውጭ አገር ኃይለኛ መንግሥት የመፍቀዱን አሳብ ስለ አነሣ በዚያ ጊዜ ሳይቀበሉት መቅረቱን ክቡርነትዎ አይዘነጋውም ።

የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ይህን ጥያቄ አጥልቆ ከመረመረ በኋላ ፤ በዲሴምበር 13 1906 (ታኅሣሥ 4 1899) ዓ. ም. በሎንዶን የተደረገውን ስምምነት የሚቃወም ነገር እንደሌለበትና በስምምነቱ መጀመሪያ ክፍል እንደ ተመለከተው የዓለም መንግሥታትን ሕግ መሠረት ሳይለቅ በኢትዮጵያ ቀድሞ የነበረው እንደ ነበረ ሆኖ የፈረሙት መንግሥታት ባንድነት ተስማምተው ጥቅማቸውን ለመጠበቅ መሆኑን ክቡርነትዎ ደግሞ አስታውቆኛል። ስለዚሁ ምክንያት የእንግሊዝ መንግሥት የኢጣልያን አሳብ ተደግፎ የኢጣልያን ረዳትነት በደስታ ይቀበላል። ይኸውም እርዳታ የኢጣልያን መንግሥት ራሱ እንዳወቀው የምስርንና የሱዳንን ውሃ ዋና ጥቅም የማይነካ የሆነ እንደሆነ ነው። እንዲሁም ክቡርነትዎ ከመንግሥትም እንደ ተቀበሉት ትእዛዝ ፡ የእንግሊዝ መንግሥት በጣና ላይ የመገደብ ሥራ እንዲሠራ ለምግብ ለመሣሪያ ለሠራተኛ ፡ ይህንንም ለመሳሰለው ሁሉ ማመላለሻ እንዲሆን ከሱዳን ወሰን እስከ ግድቡ ድረስ የአውቶሞቢል መንገድ እንዲሠራ ፡ የኢትዮጵያን መንግሥት ለመጠየቅ የኢጣልያ መንግሥት እንዲረዳውና እንዲደግፈው ይጠይቃል። የኢጣልያ መንግሥት ይህን ስለአደረገለት የእንግሊዝ መንግሥት ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት ከኤርትራ ወሰን እስከ ኢጣልያ ሱማሌ ወሰን ፡ የባቡር መንገድ እንዲዘረጋና ጥቅሙም ለራሱ እንዲሆን ፡ ለዚህም የባቡር መንገድ ሥራና ፍሬ ለማግኘት የሚያስፈልገው ሁሉ ከዚህ በላይ በተነገረው የባቡር መንገድ በነፃ እንዲተላለፍ የሚያደርግ ውል የኢትዮጵያን መንግሥት በሚጠይቅበት ጊዜ ይረዳዋል ብሎ ክቡርነትዎ አስታወቀኝ። ደግሞ ስለዚሁ መጨረሻ ነገር በኢትዮጵያ ላሉት ለእንግሊዝና ለኢጣልያ እንደራሴዎች የሚያስፈልገው አንድ ዓይነት ትእዛዝ አልፎላቸዋል ።

ስለ ጣና ባሕርና ኤርትራንና የኢጣልያን ሱማሌ አገር ስለሚያገናኘው የባቡር መንገድ ፡ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥቶች ሁለቱም የተስማሙበትን የኢትዮጵያን መንግሥት እንዲጠይቁ ለማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ክቡርነትዎ አስታወቀኝ ።

ምናልባት አንዱ መንግሥት የጠየቀውን ውል አግኝቶ አንዱ ሳያገኝ ቢቀር ውል ያገኘው መንግሥት ላላገኘው መንግሥት እንደዚሁ እስቲያገኝ ድረስ እርዳታውን ሳያጎድልበት በሚቻለው መንገድ ይረዳዋል ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በኢጣልያ መንግሥት ረዳትነት የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ስለ ጣና ባሕር የጠየቀውን ውል ፡ ከኢትዮጵያ መንግሥት ለማግኘት የቻለ እንደ ሆነ የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ በስተምዕራብ ባለው ኢትዮጵያና ከዚህ በላይ በተነገረው የባቡር መንገድ በሚያቋርጠው አገር ሁሉ ፡ የኢጣልያን የተለየ የኤኮኖሚክ ሥልጣን ያውቅለታል ብሎ ክቡርነትዎ አስታውቆኛል። ከዚህም በቀር የእንግሊዝ መንግሥት ከዚህ በላይ በተመለከተው አገር ክፍል ስለ ኤኮኖሚክ ቦታ የኢጣልያ መንግሥት የሚያደርገውን ጥያቄ ሁሉ ይደግፋል። ስለ ሆነም ይህ ውልና ንግግር የሚጸናው የኢጣልያ መንግሥት ከዚህ በፊት እንደ ነበረው የሱዳንን የውሃ ደንብ ዐውቆ በጥቁር ዐባይና በነጭ ዐባይ ምንጮችና በመጋጠሚያ ወንዞችላይ ወደ ዋናው ጅረት እንዳይገቡ የሚከለክል

ማናቸውንም ዓይነት ሥራ እንዳይሠራ ግዴታ የገባ እንደ ሆነ ነው። ምንም ከዚህ በላይ እንደ ተጻፈው አኳኋን ቢሆን ያገሩ ነዋሪዎች ሕዝብ የሚጠጡትና ለቤት ጉዳይ ወይም ለእርሻ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ለማግኘት መቻላቸውን ለኤሌክትሪክ ኃይል አግዶ ማጠራቀም ፡ ይህንንም ለመሰለው አስፈላጊ ነገር እውነተኛ ግምት እያደረጉ ሊሠሩበት ይችላሉ ብሎ ክቡርነትዎ አስታውቆኛል ።

ከዚህም በቀር ክቡርነትዎ ከመንግሥቱ እንደ ተቀበለው ትእዛዝ ፡ ለግድቡ ሥራና ለመንገዱ የሚቀጠረው ሠራተኛ እስከሚቻል ድረስ ከዚያው ቦታ መሆኑን የባሕሩም ሙላት በዝናብ ወራት በሚሞላበት ጊዜ ካለው ልክ ይበልጥ እንዳያድግ መወሰኑን ለኢጣልያ መንግሥት አስታውቆአል። በመጨረሻም የዚህ የግድቡ ሥራ የሚጠቅመው ለምስርና ለሱዳን ብቻ መሆኑ ቀርቶ በዙሪያው ላሉ ሕዝቦች አገራቸውን የሚያለማና በኤኮኖሚክ ረገድ የሚያሰፋ መሆኑን የእንግሊዝ መንግሥት ተረድቶታል።

ክቡርነትዎ ከዚህ በላይ ላስታወቀኝና ላደረገልኝ ጥያቄ ምላሽ ፤ የእንግሊዝ መንግሥት በሌላው ክፍል ሁሉ በጣም ውድ የሆነውን በወዳጅነት ተስማምቶ የመሥራት መሠረት ፡ከዚህ በላይ ለተመለከተው ጥያቄ ማስፋፋት አሁን ጊዜው መሆኑን ስላወቀ ፡ የንጉሥ መንግሥት በጣም ደስ ብሎት አሳቡን መቀበሉን ይህ ስምምነት የተስፋፋ እንደ ሆነ በጣም ይጠቅማል ብዬ ለክቡርነትዎ አስታውቃለሁ።

በኖቬምበር 1919 (ኅዳር 1912) ዓ. ም. የቀረቡት ድርድሮች በሎንዶን ላይ ዲሴምበር 13 1906 (ታኅሣሥ 4 1899) ዓ. ም. በተደረገው ስምምነት ውስጥ ያሉትን ቃሎች ኢጣልያ ዘወትር እንደ ደገፋቸው ሁሉ ፡ የሚያፋርሱ አለመሆናቸውንና የዚህም ድርድር ዋናው ነገር እንደ ዓለም ሕዝብ ደንብ መሠረት የስምምነቱ መጀመሪያ ክፍል እንደሚለው ፡ ውሉን የፈረሙት ትልልቅ መንግሥቶች ጥቅማቸው እንዳይነካባቸው ተባብረው እየሠሩ ፡ ኢትዮጵያ እንደ ነበረች ሆና እንድትኖር ለማድረግ መሆኑን የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ስለ ተረዳው የንጉሥ መንግሥት ነገሩ እንደ ተፈጸመ ይቆጥረዋል ።

ይህ ከሆነ በኋላ ምንም ከዚህ በላይ የተጸፉት በኖቬምበር በሎንዶን ላይ የቀረቡት ድርድሮች በዲሴምበር 1919 ዓ. ም. በሎንዶን ከተፈረሙት ውሎች የወጡ ካንድ የቅፒ አኳኋን ካለው ሰፊ ስምምነት ውስጥ የሚቆጠሩ ስለሆኑና ፡ ከዚህ ስምምነት ውስጥ የተፈጸሙት ጥቂቶች ነገሮች ቢሆኑ፤የኢጣልያ ንጉሥ መንግሥት በተለየ የእንግሊዝ መንግሥት የወዳጅነትን ስምምነት መሠረት ስለ ፈቀደ ፡ የዚህ ፈቃድ ተካፋይ በመሆኑ ነገሩን እንደገና ለማንሣት ፈቃዱ ነው። ደግሞም ይህንን የስምምነት መሠረት ያለው ውል በዲሴምበር 1906 ዓ. ም. በሎንዶን የተደረገውን ውል ሳይተላለፍ በኢትዮጵያ ያለው የእንግሊዝና የኢጣልያ ጥቅም በጣም እንዲሰፋና እንዲጠበቅ ተስፋ እናደርጋለን። ለዚሁም ፍጻሜ በጣና ባሕር ላይ ግድብ እንዲሠራና ለምግብና ለመሣሪያ ማመላለሻ ከሱዳን ወሰን አንሥቶ እስከ ግድቡ የአውቶሞቢል መንገድ እንዲሠራ የእንግሊዝ መንግሥት ውል እንዲሰጠው በጠየቀ ጊዜ የኢጣልያ መንግሥት ይረዳዋል።

ከዚህም በቀር ከኤርትራ ወሰን አንሥቶ እስከ ኢጣልያ ሱማሌ አገር ድረስ የባቡር መንገድ ለመዘርጋትና ቦታውን ለመሥራት ለዚሁም የባቡር መንገድ መሥሪያ የሚያስፈልገው ነገር ከዚህ በላይ በተባለው የአውቶሞቢል መንገድ በነፃ እንዲያልፍ የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መንግሥት ለሚጠይቀው ጥያቄ የእንግሊዝ መንግሥት እረዳለሁ ያለውን እንደተፈጸመ ይቆጥረዋል ።

የዚህም መጨረሻ ነገር የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥቶች ስለ ጣና ባሕርና ኤርትራንና የኢጣልያን ሱማሌ አገር ስለሚያገናኘው የባቡር መንገድ ጉዳይ ፡ የሚጠይቁት ውል ለሁለቱም ባንድነት እንዲሰጣቸው የእንግሊዝ መንግሥት ለእንደራሴው እንደሚሰጠው ትእዛዝ የኢጣልያም መንግሥት አዲስ አበባ ላለው እንደራሴው የሚያስፈልገውን ትእዛዝ ያስተላልፍለታል። ምናልባት አንዱ መንግሥት የጠየቀውን ውል አግኝቶ አንዱ ሳያገኝ ቢቀር ሁለቱም የሚያገኙት እስከ ተቻለ ባንድነት እንዲሆን ወይም ያላገኘውደስ እስቲለው ውል ያገኘው እርዳታውን ሳያቋርጥ ይገፋበታል ።

በኢጣልያ መንግሥት ረዳትነት የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ስለ ጣና ባሕር የጠየቀውን ውል ከኢትዮጵያ መንግሥት ለማግኘት የቻለ እንደሆነ እንደዚሁም ለኢጣልያ መንግሥት በስተምዕራብ ባለው ኢትዮጵያና ከዚህ በላይ የተጠራው የባቡር መንገድ በሚያቋርጠው አገር የኤኮኖሚክ ሥልጣኑን ያውቅለታል። ደግሞ ከዚህ በላይ በተመለከተው አገር ክፍል ስለ ቦታ የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መንግሥት በሚጠይቀው ሁሉ ይደግፈዋል ።

የኢጣልያ መንግሥትም በበኩሉ ቀድሞ የነበረውን የምስርንና የሱዳንን ውሃ ደንብ ዐውቆ በነጭ ዐባይና በጥቁር ዐባይ ምንጭና መጋጠሚያ ወንዞች ላይ ወደ ዋናው ጅረት መፍሰስ የሚከለክል ምንም ሥራ እንዳይሠራ ውል ይገባል።

ስለ ውሃው ጥቅም የእንግሊዝ መንግሥት ግዛቱን በሚነኩ በተለየ የኢጣልያ ሥልጣን በሚገባቸው ውስጥ የሚቆጠሩት አገሮች የሚኖር ሕዝብ ፡ ቀድሞ የነበረውን አኳኋን እንዲያከብር የተረጋገጠ አሳብ እንዳለው አምናለሁ። ይህም አሳብ የሚቻለውን ያህልና በምስርና በሰዳን ዋና ጥቅም የሚስማማ እስከ ሆነ ድረስ ለነዚህ ነዋሪዎች ሕዝቦች ለሚያስፈልጋቸው ለኤኮኖሚሚክ ጉዳይ ደስ የሚያሰኘውን ለማድረግ እንዲቻል ሆኖ ተመሥርቶ ይፈጸማል።

የማክበር ሰላምታዬን ይቀበሉ ።

ፊርማ ሙሶሊኒ ።

በአዲስ አበባ ያሉት የእንግሊዝ መንግሥትና የኢጣልያ መንግሥት ሚሜኒስትሮች ስለዚሁ ጉዳይ ከየመንግሥታቸው እንደ መጣላቸው ትእዛዝ ሁለቱ መንግሥቶች የተስማሙበትን ውል ባንድነት ሆነው ባቀረቡልን ጊዜ በነገሩ እየተደነቅን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጻፍንላቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና

ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ

ተፈሪ መኰንን ።

ይድረስ ከክቡር ምስተር ቻርልስ ቤንቲክ

የእንግሊዝ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር

ሰላም ለርስዎ ይሁን ፡

በሰኔ 2 ቀን 1918 ዓ. ም. የጻፋችሁልኝ ደብዳቤ ደርሶኛል። ይህ ደብዳቤ የኢጣልያ ሚኒስትር ክቡር ኮንት ኮሊ ከላኩልኝ ደብዳቤ ጋራ በፍጹም የሚመሳሰል ነው። እንግሊዝ የጣናን ባሕር ለመገደብ ፡ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ውስጥ የባቡር መንገድ ለመሥራት ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ውል እንዲሰጣችሁ ፡ በሁለታችሁ መካከል ስምምነት መኖሩን ያስረዳኛል። ሁለታችሁ መስማማታችሁና ይህን ስምምነት ባንድነት ልታስታውቁን የሚገባችሁ የመሰላችሁ የሚያስቸግረን አሳብ ስለሚሰጥ ፡ አሁኑኑ ከሁሉ አስቀድሞ የምንመክርበት ነው። ስለዚህም ፍጻሜ ይህ ነገር ከሁሉ አስቀድሞ እንዲመረመር ስለሚያስፈልግ በመንግሥታት ማኅበር ፊት ማቅረብ የሚገባ ነው።

ሰኔ 8 ቀን 1918 ዓ.ም

ለኢጣልያ ሚኒስትርም በዚሁ ዓይነት ተጻፈላቸው ።

ከዚህም በኋላ ቀጥሎ ያለውን አቤቱታ ጽፈን ለመንግሥታት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ለሙሴ አቪኖል አቀረብን ።

እንግሊዝ የጣናን ባሕር ለመገደብ ፣ ኢጣልያ በኢትዮጵያ አቋርጦ የምድር ባቡር ለመሥራት መስማማታቸውን የሚያስረዳ ከሁለቱም የተጻፈ አንድ ዓይነት የሆነ ማስታወሻ አሁን በቅርቡ ጊዜ ለመንግሥታችን ደረሰው።

ይህ ስምምነት የተደረገው እኛ ሳንሰማው ለብቻቸው በመሆኑና እነዚህ ሁለቱ መንግሥታት ባንድነት ስለ አስታወቁን በጣም አዘንን ።

በመጀመሪያ እንኳ ወደ መንግሥታት ማኅበር ለመግባት በተፈቀደልን ጊዜ የዓለም መንግሥታት ሁሉ እንደ እኩል ይቆጠራሉ ፡ የሁሉም ነፃነት ይከበራል ፡ የማኅበሩም መጨረሻ አሳብ እግዚአብሔር እንደሚወደው ፣ በሰው መካከል ሰላም እንዲሰፋና እንዲጸና ነው ብለው ነግረውን ነበር።

አንዳንድ የመንግሥታት ማኅበረተኞች ለየብቻቸው ስምምነት አድርገው አንዱ ማኅበረተኛ የነሱን አሳብ እንዲቀበል ለማስገደድ ምንም ያገሩን ጥቅም የማይነካ ቢሆን እንኳ የሚፈቅድላቸው አይመስለንም ነበር።

ሁለተኛም ከተስማሙባቸው ጉዳዮች አንደኛው ጉዳይ ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ መንግሥትና የእንግሊዝ መንግሥት ተነጋግረውበት የነበረው ነው። ይኸውም የምንነጋገርበት ጉዳይ ሳይፈጸም ስለ ቆየና የምንመክርበት ስለሆነ የተቆረጠ ምላሽ አልተሰጠም ። ። ስለዚህም ጉዳይ እንዲነጋገሩ እርስ በርሳቸው ተስማምተው ይህንኑ ስምምነታቸውን ባንድነት ስለ አስታወቁን ፡እኛ ሳንመክርበትና ለሕዝባችን የሚስማማ መሆኑን ሳናውቅ የሚጠይቁንን ልንፈጽመው ስላልቻኩልን ከሚያስቸግር አሳብ መቁጠራችን አልቀረም።

ሕዝባችን መልካም ለመሥራት ፈቃደኛ ነው ፡ በሥልጣኔና በመሻሻል መንገድ እንዲመራ ሁለጊዜ ፈቃዳችን ነው። ነገር ግን በታሪኩ ውስጥ ከውጭ አገር ሰዎች መካከል ወሰኑን ሊደፍሩና ነፃነቱን ሊነኩበት የሚፈልጉትን ብቻ ነው ያወቀው። በእግዚአብሔር ቸርነት በወታደሮቻችን ጀግንነት ፡ በማናቸውም ምክንያት ዘወትር በነፃነታችን ኮርተን በተራሮቻችን ላይ ለመቀመጥ ችለናል ።

ስለዚህ ለኤኮኖሚክ ጉዳይ እያሉ በሀገራችን ወይም ግዛታቸውን በሚነካ የወሰን አገራችን ለመቀመጥ የሚፈቅዱት የውጭ አገር ሰዎች እንድንፈቅድላቸው ሲጠይቁ የፖለቲካ ነገር እንደ ሌላቸው መጠንቀቅ እንደሚያስፈልገን ፡ ይህ አሁን በድንገት ተስማምተው ያቀረቡት አሳብ ከሁሉ የተሻለ ማስረጃ መንገድ ይሆናል። እኛም ያዲሱን ዘመን ሥልጣኔ ለመከተል የጀመርነው በቅርቡ ጊዜ መሆኑን አለመዘንጋትና ምንም ያለፈው ታሪካችን ስመ ጥሩ ቢሆን ፣ ይህንን ከመሰሉ በፍጹም አዲስ ከሆኑ ነገሮች ጋራ በቶሎ እንድንላመድ ጊዜው አልፈቀደልንም። ፍጥረት እንኳ ባንድ ጊዜ አልተፈጠረም። ባንድ ዓመት ሥራውን ሁሉየለወጠ አገር ወዴት ይገኛል?

በእርግጥ ፈቃደኛ ከመሆናችን ጋራ ፣ ያገራቸው በጂዮግራፊያ አቀማመጥ እንዲቀድሙን የረዳቸው በወዳጅነት ምክር ካሳሰቡንና ጊዜ ከሰጡን ፡ኢትዮጵያ እስካሁን ዘወትር ትልቅ እንደ ነበረች ፡ አሁንም ወደ ፊት ከትልቅ ደረጃ እንድትደርስ ያለማቋረጥ እየተሻሻለች ትሔድ ነበር። ነገር ግን መቸኰል ያደጋ ጥፋት ያመጣል።

የዓለም መንግሥታት ማኅበር ማኅበረተኞች በነሱ ቢደረግባቸው ያለጥርጥር የማይወዱትን የማስጨነቅ መንገድ በእኛ እንዲደረግብን የሚፈቅዱ መሆናቸውን ለማወቅ እንፈልጋለን ።

እነዚህን የተቀበልናቸውን ማስታወሻዎች በተለየ የግዛታችን አንዱ ክፍል አገር ላንድ ለታወቀ ትልቅ መንግሥት ኤኮኖሚክ ሥልጣን ይለቀቃል ሲባል ፡ ካገራችን ነፃነት ጋራ የማይስማማ አሳብ መሆኑን እንድትረዱት ለክቡራን የዓለም መንግሥታት ማኅበረተኞች ለሆናችሁ መንግሥታት ሁሉ በማክበር አስታውቃለሁ።

የኤኮኖሚክ ሥልጣንና የፖለቲካ ሥልጣን በጣም የተጋጠሙ ወንድማማቾች መሆናቸውን ስለምናውቅ ይህ ስምምነት እንደ እኛ አሳብ ከዓለም መንግሥታት ማኅበር መሠረታዊ አሳብ ጋራ የሚስማማ ስላልሆነ ጥብቅ የሆነ አቤቱታችንን ልናቀርብ ይገባናል።

አዲስ አበባ ሰኔ 12 1918 ዓ.ም

ይህ የኛ አቤቱታ ደብዳቤ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ከደረሰና ነገሩ ከተመረመረ በኋላ ለሁለቱም መንግሥታት የጥያቄ ቃል ስለ ተጻፈላቸው የእንግሊዝ መንግሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለሰ።

ሎንዶን ኦገስት 3 1926

(ሐምሌ 25 1918)

ለዓለም መንግሥታት

ዋና ጸሐፊ ፡

በግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋና ጸሐፊ ስም ሆኜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሰር ኤሪክ ደ ሪሞንድ የጻፉት ደብዳቤ ግልባጭና ደግሞ በዲሴምበር 1925 (ታኅሣሥ 1918) ዓ. ም. የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ስለተስማሙበት ማስታወሻ ፡ በዚሁም ማስታወሻ ውስጥ እንደ ተመለከተው ዓይነት ሥራ የኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ እንዲሰጥ በሚጠይቁት ጊዜ ፡ ሁለቱ መንግሥታት ሊረዳዱ ስለ ተዋዋሉ ላቀረቡት አቤቱታ በሐምሌ 15 የጻፉልኝ ክቡር ደብዳቤዎ ደረሰኝ። ሁለተኛም ምንም በአዲስ አበባ ያሉት የእንግሊዝና የኢጣልያ ሚኒስትሮች እንግሊዝና ኢጣልያ የተስማሙበትን ማስታወሻ ባስታወቁ ጊዜ ለኢትዮጵያ መንግሥት ቢያረጋግጡለት ፣ በማስታወሻው ውስጥ ያለው እርግጠኛው ቃል በትክክል ስላልተተረጐመና በሁለቱ መንግሥታት ላይ ያላሰቡትን ስለ ላኩባቸው የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት አዝኗል። የኢትዮጵያ አቤቱታ እንደተጻፈው አኳኋን ፡ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ውል ተፈራርመው ምንም እንኳ አሳባቸው ለማኅበረተኛው የማይስማማው ቢሆን ፡ አስጨንቀው አሳባቸውን እንዲቀበል ለማድረግ ያሰቡ ይመስላል ፡ በራሳችሁ ላይ ቢደረግባችሁ ያለ ጥርጥር የማትቀበሉትን ይህን የማስጨነቅ ሥራ በኢትዮጵያ ላይ ሊሠራባት መገባቱን አስታውቀን ብለው የዓለም መንግሥታት ማኅበርን ለምነዋል ።

ሦስተኛ ፡ በእንግሊዝና በኢጣልያ ማስታወሻ ውስጥ የኢትዮጵያን መንግሥት ማስገደድን ወይም ማስጨነቅን የሚያሳስብ ምንም ነገር የለበትም። በእርግጥ የሆነ እንደ ሆነ ይህ ስምምነት በኢትዮጵያ ላይ የማስገደድ ሥራ ለመሥራት አልታሰበም ብለው ሰር ኦስተን ቻምቤርሊን በምክር ቤት አስታወቁ ።

እንደ አርሳቸው አሳብ የሆነ እንደ ሆነ ስምምነቱ ጥቅም ላላቸው ለሦስቱ መንግሥታት የሚጠቅም ነው። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ጥቅም ፈራጁ የኢትዮጵያ መንግሥት መሆን በፍጹም የሚገባው ነው ብለው ቀጥለው ተናገሩ።


የግርማዊ ንጉሥ ጉዳይ ፈጻሚ ይህንኑ ቃል ለአልጋ ወራሽ ተፈሪ እንዲያስታውቅ በሐምሌ ወር በቴሌግራም ትእዛዝ ተላልፎለታል ።

አራተኛ ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝቡ የሚጠቅም መሆኑን ለማሰብ ጊዜ ሳያገኝ ላደረጉለት ጥያቄ በፍጥነት ምላሽ እንዲሰጥ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ሊያስገድዱት ይፈልጋሉ በተባለው አሳብ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አመለክታለሁ።

በ18 ሜይ 1902 (8 ግንቦት 1894 ) ዓ. ም. አዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ ሚኒስትርና የኢትዮጵያ መንግሥት በተላላኩት ማስታወሻ ዐፄ ምኒልክ ከጥቂት ቀን በፊት በቃል ተነጋግረው የነበሩትን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በጽሕፈት አረጋግጠዋል።



ወ/ሮ ወለተ ዮሐንስ ፡ ባላምባራስ አድነው ፡ ልጅ ዘውዴ አየለ (ደጃዝማች) ፡ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ፡ ራስ እምሩ (ልዑል) አቶ ወልደ ማርያም አባይነህ ፡ ደጃች ተፈሪ (ቀ.ኃ.ሥ.) ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አባይነህ ።



በደጃዝማችነት ጊዜ

የጥቁር ዐባይን ውሃና የጣናን ባሕር አካሔድ የሚለውጥ ማናቸውንም ዓይነት ሥራ የእንግሊዝና የሱዳንን መንግሥት ሳይጠይቅ እንዳይሠራ፡ ይህንን የመሰለ ሥራ ለመሥራት የታሰበ እንደ ሆነ ግን ፡ የቀሩት ውሎች ሁሉ እንደዚያው ሆነው ብልጫው የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥትና የሱዳን መንግሥት ላቀረበው አሳብ ይሰጣል። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ምኒልክ ስለ ጥቁር ዐባይና ስለ ጣና ባሕር ለግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ወይም ከሁለቱ ላንዱ ለሚገባው ካልሆነ በቀር ለማንም ቢሆን ቦታ ለመስጠት አሳብ የላቸውም።

ይህ ውል ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ከዛሬ 24 ዓመት በፊት ጀምሮ የእንግሊዝ መንግሥት በጣና ላይ የግድብ ሥራ እንዲሠራ መፍቀዳቸውን ስለሚያስረዳ የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት በተመቸ ጊዜ ሁሉ ስለዚህ ሥራ የተቆረጠ ፍርድ ማቅረቡንና ፍጻሜውን አሁን በኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድና እርዳታ ለመመርመር ወደ ጣና ባሕር ተልከው ሔደው የነበሩት ዐዋቂዎች (መሐንዲሶች) አኳኋኑን በዝርዝር አጥንተው ከተመለሱ ወዲህ በፍጹም ለመገመት ይቻላል ።

ስለዚህ ስለ ጣና ባሕር ጉዳይ የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት በጣም በችኮላ ሠርቷል ብሎ መፍረድ ትክክለኛ ነገር አይመስልም።

አምስተኛ ፡ በቀረበው አቤቱታ መጨረሻ ክፍል የኢትዮጵያ መንግሥት ፡እንግሊዝና ኢጣልያ ያቀረቡት ማስታወሻ የኢትዮጵያ አንዱ ክፍል አገር ላንድ ትልቅ መንግሥት ኤኮኖሚክ ሥልጣን ይለቀቃል ሲባል ፡ የኢትዮጵያ ነፃነት የማይነካ ነወይ ? ብሎ ይጠይቃል። በተለየ ሰር ኦስተን ቻም ቤርሊን እንግሊዝና ኢጣልያ ያቀረቡት ማስታወሻ ለኢጣልያ ኤኮኖሚክ ሥልጣን ከኢትዮጵያ አንድም ክፍል አገር እናስቀራለን አይልም ብለው አጥብቆ ለማስታወቅ ይፈቅዳሉ። የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ስለራሱ ጥቅም ሲልና ኢጣልያ ውል ተዋውሎ በኢትዮጵያ ምዕራብና ከዚህ በላይ የተጠራው የባቡር መንገድ በሚያቋርጠው በጠቅላላው አገር (ኤርትራንና የኢጣልያን ሱማሌ የሚያገናኘው) የኢጣልያን የተለየ የኤኮኖሚክ ሥልጣን አውቃለሁ ማለቱ እርግጥ ነው። ነገር ግን ይህ ውለታ የሦስቱን መንግሥታት ክፍያ የሚነካ ወይም ስለ ጣና ባሕር ኢጣልያ ላረጋገጠችለት ለውጥ በተወሰነው አገር ክፍል የኢጣልያን ሥራ የሚወዳደር ሥራ ላይሠራና ይህንም ለመሰለ መወዳደር እንዳይደግፍ ስለ ተዋዋለ የእንግሊዝ መንግሥት ግዴታ አያገባውም።

ስድስተኛ ፡ ለሚመጣው ጊዜ ስብሰባ የምክር ቤቱ የኢትዮጵያ መንግሥት የላከልዎን ማስታወሻ ለመመርመር ሰር ኦስተን ቻምቤርሊን ለኢትዮጵያ የሰጡትን እምነትና ማስረጃ እንደገና ለማቅረብ ይቻላቸዋል ።

ፊርማ ጆን ሙሬይ

የእንግሊዝ መንግሥት ከዚህ በላይ ያለውን ቃል ለመንግሥታት ማኅበር በጻፈ በአራተኛው ቀን የኢጣልያ መንግሥትም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጻፈ።

ሮማ ኦገስት 7 1926

(ነሐሴ 1 1918)

ባለፈው ሐምሌ 15 ቀን የጻፉልኝ ደብዳቤ ፡ በዚሁም ደብዳቤ ውስጥ በኢትዮጵያ አገር ሥራዎችን ለመሥራት የኢትዮጵያን መንግሥት ለመጠየቅ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት እንዲተጋገዙ በዲሴምበር 1925 (ታኅሣሥ 1918) ዓ. ም. ስለ ተስማሙ ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኰንን የጻፉልዎ አቤቱታ ግልባጭና ተጨማሪ መድረሱን እንዳስታወቅዎ የመንግሥቱ አለቃና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዘውኛል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለዓለም መንግሥታት ማኅበረተኞች የላኩት ማስታወሻ ፍሬው ነገር እንደሚያሳየው ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በእንግሊዝና በኢጣልያ መካከል በተደረገው ስምምነት ውስጥ ያለው አሳብ በትክክል እንዳልገባቸው በማወቁ የንጉሥ መንግሥት በጣም ያዝናል። ይልቁንም የንጉሠ መንግሥት የገረመው ከጥቂት ጊዜ በፊት በአዲስ አበባ ያለው የኢጣልያ እንደራሴ ስለዚህ ስለ ተጠየቀው ጉዳይ መጨረሻ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥት አንዳንድ የኤኮኖሚክ ጥቅማቸው እንዲገናኝ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ያለ ትንሽ የንግግር ደንብ መሆኑን ከገለጠና ፡ ይኸውም ቢሆን የሚፈጸመው የኢትዮጵያ መንግሥት የሚፈቅድ የሆነ እንደ ሆነ ለኢትዮጵያ ኤኮኖሚክ መስፋፋት የሚረዳና ለጥቅሟ የሚስማማ የሆነ እንደ ሆነ መሆኑን ገልጦ በረጅሙ ለኢትዮጵያ መንግሥት ካመለከተ በኋላ በመሆኑ ነው።

ከዚህም ማመልከቻ ቀጥሎ ባሁኑ ሰኔ 12 ጀምሮ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አዲስ አበባ ላለው የኢጣልያ ሚኒስትር አንድ ደብዳቤ ጽፈውለት ፡ በዚሁ ደብዳቤ ውስጥ ስለ ተደረገላቸው እምነት የኢጣልያን መንግሥት አለቃ አመስግነው ኢጣልያ የወዳጅነት መስማማት እንዳላትና የኢትዮጵያን ነፃነት ለማክበር ፈቃደኛ መሆኗን አልጠረጥርም ብለው ጽፈዋል። በዚሁም በተጠየቀው ስምምነት ማስታወሻ ውስጥ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ የማስገደድና የማስቸኰል ሥራ ለመሥራት ያስባሉ ብሎ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያስፈራው ምንም እንደ ሌለ የኢጣልያ መንግሥትም ያውቃል። ደግሞ ከዚህ ቀድሞ ያደረገለት የወዳጅነትና የተረጋገጠ እምነት ለመፍራት የማያደርሰው መሆኑን ሊያስረዳው ይበቃ ነበር።

በተለየ ይልቁንም የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ አገር ክፍል በልዩ አድርጎ ለኢጣልያ ኤኮኖሚክ ሥልጣን ስለ መልቀቅ ነገር ይህ የተጠ የቀው ውል የእንግሊዝንና የኢጣልያን መንግሥታት የሚያስተሳስር ነው እንጂ ፡ የኢትዮጵያን ሥልጣን የሚነካ ወይም ለወደፊቱ የሦስቱን መንግሥታት ክፍያ ሥራ የሚወስን አይደለም።

ይህ ስምምነት የኢጣልያ ጐልማሶች የጀመሩት ሥራ በመልካም እንዲፈጸም ከኢትዮጵያ አገር ውስጥ የሚገኘው ጥቅም እንዲሰፋና እንዲታደል የእንግሊዝ ሥራ እንዳይወዳደረው የኤኮኖሚክ ዋስትና ዓይነት ነው።

ፊርማ ግራንዲ ፡

እነዚህም ሁለቱ መንግሥታት ለተጠየቁት የመለሱት ቃል በዓለም መንግሥታት ማኅበር በኩል ተልኮልን ካየነው በኋላ እንደገና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጻፍን ።

ይድረስ ለዓለም መንግሥታት

ማኅበር ዋና ጸሐፊ ።

ሰላም ለርስዎ ይሁን ፡

በታኅሣሥ 5ና 11 ቀን 1918 ዓ. ም. የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት በኢትዮጵያ ጥቅም ለማግኘት ስለ አደረጉት ስምምነት ፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አቤቱታ ለማቅረብ የሚገባ ስለ መሰለው በሰኔ 12 በጻፍሁልዎ ደብዳቤ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ማኅበረተኞች እንዲያስታውቁልን ለምኜዎ ነበር።

ሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት እንደነሱ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ማኅበረተኛ በሆነችው በወዳጅ መንግሥት ሳያስፈቅዱ እንደ ልባቸው ለመሥራት መስማማታቸውን የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሰምቶ በሚገባ አዘነ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህ ውል ለኢትዮጵያ የማይጠቅም መሆኑን ከመረመረ በኋላ ያልተቀበለው እንደ ሆነ እነዚህ ሁለቱ መንግሥታት የጠየቁትን የኤኮኖሚክ ውል ለማግኘት የማስጨነቅ ሥራ ሳይሠሩም አይቀሩ ብሎ ያስባል።

ይህ መሆኑ ከታወቀ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት እንደ ቀሩት ማኅበረተኞች ሁሉ ኢትዮጵያ ከሺ ዘመናት አስቀድሞ ያላት ነፃነቷ እንዳይነካ ወሰኗ እንዳይደፈር ቃል ገብተው የነበረውን አሁን የእንግሊዝና የኢጣልያ ስምምነት በቀጥታ እንኳ ባይሆን ከዓለም መንግሥታት ማኅበር ጋራ የሚስማማ አይደለም ለማለት ይቻላል ።

እንደ እኛ አሳብ እንደ ቃል ኪዳኑ 20ኛው ቃል እንዳይዋዋሉ ግዴታ ነበረባቸው። ነገር ግን ይህን ቃል ለማፍረስ ያሰቡ ስለ መሰለን የስምምነታቸው መጨረሻ በእኛ ዘንድ ዋጋ የሌለው ነውና እንደ ከንቱ ሆኖ ይቆጠራል። ሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት በየበኩላቸው በኦፊሴል በአንድ ቀን ባያስታውቁን ኖሮ አያሠጋንም ነበር። ይህ ባንድነት ያቀረቡት ማመልከቻ የማስጨነቅ መጀመሪያ ምልክት መሆኑን የሚገልጥልን ይመከላል። ከዚያም ወዲህ ለእኛ አቤቱታ ሲመልሱ ሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት የወዳጅነት አኳኋናቸውን እየገለጡ ፡ የኢትዮጵያን አቤቱታ ለማብረድ ይጣጣሩ ጀመር። ይልቁንም የእንግሊዝ መንግሥት ስለዚሁ ጉዳይ ጊዜ ኢጋጥሚቸው ክቡር ሰር ኦስተን ቻምቤርሊን በእንግሊዝ ምክር ቤት የተናገሩትን ማስረጃ ቃል አስታውቆናል። «ሁለቱ መንግሥታት አገሩን በኤኮኖሚክ ለመፈለግ አያስቡም ስምምነታቸው የኢትዮጵያን መንግሥት የሚያስር ነገር የለበትም የኢትዮጵያን መንግሥት ለማስጨነቅ የታሰበ አይደለም ፣ ደግሞ ለኢትዮጵያ ጥቅም ፈራጁ የኢትዮጵያ መንግሥት ነው» ብለው በግልጽ ተናገሩ። የኢጣልያ መንግሥትም ይህንኑ የመሰለ ቃል አስታወቀን ።

ከዚህም በቀር ሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት የተስማሙበት ውል በዓለም መንግሥታት ማኅበር ጽሕፈት ቤት እንዲቀመጥ ለማድረግ ማሰባቸውን የእንግሊዝ መንግሥት አስታውቆ የነበረውን በመዝገብ ማስገባታቸውን የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሰማ።

የቃል ኪዳኑ 18ኛው ክፍል የሚመጠነው ጽሕፈት ለማስታወቂያ ያህል መሆኑን እያወቅን ይህ ደንብ በመፈጸሙ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስፈልግ አይመስለውም። ነገር ግን የንጉሠ ነገሥት መንግሥት በቃል ኪዳኑ ውስጥ ያለውን ግዴታ ለመፈጸም ከዓለም ጋራ የዳኘነትና የክብር መሠረት ያለው መገናኛ ለማድረግ አሳባችን ስለሆነ ፡ይህን ደብዳቤ ከዚያ ከተባሉት ማስታወሻዎች ጋራ ተጽፎ አብሮ እንዲወጣ ፡ በስፍራውም የሚያስረዳውን ማንም ሰው እንዲያውቀውና ለአቤቱታዎቹ የተመለሱትም የተረጋገጡ ማስረጃዎች እንዲታወቁ ማስረጃዎን ስንለምን በደንብ የሚገባ ይመስለናል ።

እንደዚህ ሲሆን የዓለም መንግሥታት ማኅበር ማኅበረተኞች አስቀድሞ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ጥቅም ካላቸው ከሁለቱ መንግሥታት ጋራ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ውል እንደሌለውና ይልቁንም የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥታት ራሳቸው እንደ ተናገሩት የቀረቡለትን ጥያቄዎች ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና ለኢትዮጵያ ፈራጅ እሱ ለመሆኑ ጥርጣሪ እንዳይገባቸው ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ 30 1918 ዓ. ም.

ይኸም የኢትዮጵያ መንግሥት ሳይሰማ ሁለቱ መንግሥታት ለብቻቸው የተዋዋሉት ነገር በዓለም መንግሥታት ማኅበር አልቋል ብለን በ1916 (1924) ከምስተር ማክዶናልድ ጋራ የተነጋገርነው ሳይፈጸም እንዲቀር አላሰብንምና አሁን በሎንዶን የኢትዮጵያ ሚኒስትር አድርገን የሾምናቸውን አዛዥ ወርቅነህን በ1920 (1928) ልዩ መልክተኛ አድርገን ወደ አሜሪካን ዩናይትድ ስቴት ልከን በዓለም ላይ ከታወቀው ከዋይት እንጂኔሪንግ ኩባንያ ጋራ ስለ ጣና ባሕር መገደብ ተነጋግረው እንዲመለሱ አደረግን። ይህንኑም ለእንግሊዝ መንግሥት መልከተኞች አዲስ አበባ ላይ ተገናኝተው እንዲነጋገሩ አደረግን። እነሱም ተነጋግረው ከተመለሱ በኋላ የዋይት እንጂኔሪንግ ኩባንያ በ1923 (1930) እንደገና ብዙ መሐንዲሶች ልኮ የጣናን ባሕር መርምረው ተመለሱ።

ከዚህም በኋላ የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥትና የምስር መንግሥት መሐንዲሶች ባንድነት ወደ አዲስ አበባ መጥተው በብዙ ከተነጋገርንበት በኋላ ፡ የውሉን ዝርዝር ለመጻፍ በ1927 (1935) እንደገና አዲስ አበባ ላይ ለመገናኘት ተቃጥረው ተመለሱ። ነገር ግን በተቃጠሩበት ወራት የዋይት እንጂኔሪንግ ኩባንያ መላክተኞች

እንዲመጡ ቴሌግራም ለማሳለፍ ስንዘጋጅ ፡ አዲስ አበባ ያሉት የእንግሊዝ ሚኒስትርና የምስር ቆንስል የኛ መላከተኞች አሁን ለጊዜው ወደ አዲስ አበባ ከመምጣት ቆይተዋል ብለው አስታወቁን። እንደዚህም ያሉበትን ምክንያቱን ለጊዜው ገልጠው አላስታወቁንም። ነገር ግን የወልወል አደጋ ተጀምሮ ነበርና በግምት ምክንያቱ ይኸ ይመስለናል ። እኛም የዋይት እንጂኔሪንግ ኩባንያ መላከተኞች ወደ አዲስ አበባ እንዳይልክ አስታወቅን። ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ከእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት ጋራ ሳይስማማ ወደ ዐባይ የሚገቡትን ትንንሾች ወንዞችና የሶባትን ወንዝ አያቋርጥም የሚል ፈቃድ ስለ ሰጠ ፡ የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥትም በያመቱ ዐሥር ዐሥር ሺ ጊኒ ለኢትዮጵያ መንግሥት ይሰጣል የተባለው ውሉ ከተፈረመበትና ደብዳቤው ከተጻፈበት ከ1895 (1902) ጀምሮ እስከ 1924 (1931) ይህን ገንዘብ የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት አለመክፈሉን በመዝገባችን አይተን እንደ ደብዳቤው ቃል ይከፈል ብለን አዲስ አበባ ላሉት የእንግሊዝ መንግሥት ሚኒስትር ብንጽፍላቸው ፡ ይህ ገንዘብ የሚከፈለው የጣና ባሕር መገደብ ሥራ ሲፈቀድ ነው በማለትና ሌላም ልዩ ልዩ ምክንያት እያመጡ ስንጸጸጻፍ ቆይተን ሳለን በመካከሉ ኢጣልያ በግፍ ጦርነት ስላነሣችብን ነገሩ ሳይፈጸም ቀረ።

ደግሞ ስለ ጣና ባሕር መገደብ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋራ በቀጥታ መነጋገር ጀምረናል ብለን የኢጣልያን መንግሥት ጉዳይ ቸል አላልነውም ነበርና ከአሰብ እስከ ደሴ የአውቶሞቢል መንገድ ለመሥራትና ንግድ ለማስፋት ፈቃድ ቢጠይቅ በወዳጅነት ፈቀድንለት እንጂ ምንም ያስቸገርነው ነገር የለም።

የዚህ ሁሉ ዝርዝሩ ወደ ፊት ልዑል ዱክ ዴዛብሩዝ ለኛ ጐብኝት ለመመለስ ወደ አዲስ አበባ በመጡ ጊዜ ባደረግንላቸው የክብር አቀባበል ውስጥ ተጽፎ ይገኛል።

# ምዕራፍ 23

## ስለ አሰብ ባሕር ወደብና ስለ መንገድ ሥራ ፡ ስለወዳጅነትም ፣ ከኢጣልያ ጋራ ስለ መዋዋላችን ።

አገራችን ገንዘቧ የሆነውን የባሕር ጠረፍ አጥታ የሥልጣኔ መሰናከል ስለሆነባት ፡ ብዙ ጊዜ የምናዝንበት ፣ ይልቁንም ኢትዮጵያ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ከገባች በኋላ ከዓለም መንግሥታት ጋራ የመገናኛዋ ጉዳይ እየበዛ ስለ ሔደ አንድ የባሕር ወደብ ለማግኘት የሚያስፈልግ መሆኑን ተረድተነው ነበርና በአሰብ በኩል አንድ የባሕር ጠረፍ ለማግኘት የኢጣልያን መንግሥት ጠየቅን።

ዳግመኛም በጅቡቲ በኩል አንድ ወደብ ለማግኘት ምኞታችን መሆኑን አዲስ አበባ ላሉት ለፈረንሳይ ሚኒስትር በየጊዜው ስናሳስባቸው ነበር። በጅቡቲ በኩል አንድ የባሕር ወደብ ለማግኘት ያሰብንበት ምክንያቱ ባንድ ወገን ጥንቱንም የፈረንሳይ መንግሥት ጅቡቲን ሲይዝ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ተስማምቶ ስለ ሆነ ፡ በሁለተኛውም ወገን የፈረንሳይ ኩምፓኒያ ከኢትዮጵያ መንግሥት በውል ተቀብሎ የሠራው የምድር ባቡር የሚያገናኘን ስለሆነ ነው።

በኋላም በ1916 ዓ. ም. ፓሪስን ለመጐብኘት የፈረንሳይ መንግሥት ጥሪ አድርጎልን በመጣን ጊዜ ፡ በጅቡቲ በኩል አንድ የባሕር ጠረፍ ለማግኘት ምኞታችን መሆኑን በዚያ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ለነበሩት ለሙሴ ፒዋንካሬ ገልጠን ስላስታወቅናቸው ተስፋ ያለው ምላሽ ሰጥተውን ነበርና ወደ ሀገራችን ከተመለስን በኋላ የፈረንሳይ መንግሥት የሰጠንን ተስፋ እንዲፈጽምልን እየመላለስን ብንጠይቅ አንዳንድ ምክንያት እየሰጡ ቁርጥ ምላሽ ሳይሰጡ ሁለት ዓመት ያህል አቆዩን ።

የኢጣልያ መንግሥት ግን የባሕር ወደብ ስለ ማግኘት ከፈረንሳይ መንግሥት ጋራ መነጋገራችን ደስ አላሰኘውም ነበር ።

ከዚህም በኋላ በ1919 ዓ. ም. ግርማዊ ቪክቶር አማኑኤል 3ኛ ለእኛ ጉብኝት ለመመለስ አጎታቸውን ልዑል ዱክ ዴዛብሩዝን ወደ አዲስ አበባ ልከዋቸው ነበርና እርሳቸው እግረ መንገዳቸውን የባሕር ወደብና የመንገድ ሥራ ነገር ከእኛ ለመነጋገር መታዘዛቸውን እንደ ደረሱ አስታውቀውን የእንግድነታቸው ቀን እስቲጨረስ ድረስ አቆይተነው ነበር።

የልዑል ዱክ ዴዛብሩዝ ወደ አዲስ አበባ መምጣት ለእኛም ለሕዝባችንም ሁሉ ከኢጣልያ ጋራ ያለንን ወዳጅነት በጣም የሚያጸና መስሎ ታይቶን ነበር። ስለዚህ የመምጣታቸውን ነገር በኦፊሴል ከሰማንበት ቀን ጀምሮ ለአቀባበሉ የሚያስፈልገውን ትልቅ ፕሮግራም አሰናዳን። በተለየም የሚያርፉበት አዲስ ቤተ መንግሥት በእኛ ቤተ መንግሥት ግቢ እንዲጀመር አድርገን ባጭር ወራት ተጨረሰ። ቤቱም የዱክ ቤት ተብሎ ተሰይሞ እስካሁን እስከ ጦርነቱ መጨረሻ በስማቸው ይጠራ ነበር።

የእንግድነታቸውንም ቀን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለማስታወቅ ከመንግሥቴ ታዝዣለሁ ያልሁትን ጉዳይ ልነጋገር ብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ።

«የባሕር ጠረፍ ለማግኘት ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ንግግር ጀምራችሁ ሳይፈጸምላችሁ መቆየቱን መንግሥቱ ስለ ሰማ ፡ በአሰብ በኩል አንድ የባሕር ወደብ ለመስጠትና ከወደቡም ጀምሮ እስከ ደሴ የካሚዎን መንገድ ፡ ሁለቱ መንግሥታት እየተረዳዱ ማኅበር አቋመው ለመሥራት ፡ በዚህ ላይ እስከ 20 ዓመት ጸንቶ የሚቆይ የወዳጅነት ውል ለመዋዋል የመንግሥቴ ፈቃድ ነውና የኢትዮጵያም መንግሥት ፈቃድ እንዲሆን እጠይቅዎታለሁ። ከዚህም ቀድሞ

በ1916 ዓ. ም. ወደ ሮማ በመጡ ጊዜ ይህ ነገር ተጀምሮ ነበር» ብለው የመንግሥታቸውን አሳብ ገልጠው ቢነግሩን ፡ባንድ ወገን የባሕር ወደብ ካገኘን ፡ በሁለተኛውም ወገን ጦርነት ሳይደረግ ኢትዮጵያ ሥራ እየሠራች ወደ ትልቅ ደረጃ የምትደርስበት የ20 ዓመት ጊዜ ካገኘን መልካም ነው ብለን አሳባቸውን ተቀበልናቸው። ነገሩም በትልልቆቹ መሳፍንቶችና መኳንንቶች ፊት ቀርቦ ከተወደደ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተፈራረምን።

## ውል ፡

የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት ዘውዲቱና የኢጣልያ ንጉሥ ግርማዊ ቪክቶር አማኑኤል 3ኛው ፡ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ያለው ወዳጅነት ከዚህ የበለጠ እየጠበቀና እየጠነከረ እንዲሔድ ፡ በሁለቱም አገሮች መካከል ያለው የገንዘብ ጥቅም መገናኛ እየሰፋ እንዲሔድ ምኞታቸው ስለ ሆነ ፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በራሳቸው ፡ በወራሾቻቸውም ስም ሆነው ፡ የኢጣልያ ንጉሥ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ኮማንዳቶሬ ጁሊያኖ ኮራ በግርማዊ ቪክቶር አማኑኤል 3ኛና በወራሾቻቸው ስም ሆነው ቀጥሎ ያለውን ተስማምተው ተዋውለዋል ።

## አንደኛ ፡

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትና በኢጣልያን ንጉሥ መንግሥት መካከል ለዘለዓለም የጸና ወዳጅነት ይኖራል ።

## ሁለተኛ ፡

ሁለቱ መንግሥታት በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ያንደኛውን ነፃነት የሚነካ ወይም የሚጐዳ ነገር እንዳያደርጉና የየራሳቸውን ጥቅም እንዲጠብቁ በየበኩላቸው ግዴታ ገብተዋል ።

## ሦስተኛ ፡

ሁለቱ መንግሥታት በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ንግድ ለማስፋትና ለማልማት ግዴታ ገብተዋል።

## አራተኛ ፡

የኢጣልያ ተወላጆች ዜጎችና ጥገኞች በኢትዮጵያ በሚኖሩበት ዘመን ኢትዮጵያውያኖችም በኢጣልያ ቅ አገር በሚኖሩበት ዘመን ስለ ንግዳቸውና ስለ ሥራቸው ለኑሮዋቸውም ስለሚያስፈልጋቸው ነገርና ስለ አስተዳደራቸው ለማናቸውም ለሚያኖራቸው ሥራ አፈጻጸም ፡ ስለ ንግዳቸውም ስለሥራቸውም የሚኖሩበትን አገር መንግሥት ሕጎች መጠበቅና ማክበር አለባቸው።

ስለሆነም ከዚህ በላይ ለተባሉት የኢጣልያ ዜጎችና ጥገኞች በኢትዮጵያ በሚኖሩበት ዘመን በጥር 1 ቀን 1900 ዓ. ም. በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና በፈረንሳይ ሬፐብሊክ መንግሥት መካከል በተደረገው ውል በ7 ኛው ክፍል የተጻፈው ቃል ይህ ውል ጸንቶ በሚቆይበት ዘመን ሁሉ እንደ ጸናላቸው ይቆያል ።

## አምስተኛ ፡

ሁለቱ መንግሥታት በመካከላቸው የሚነሣውን የማይስማሙበትን ነገር በተለመደው በዲፕሎማቲክ መንገድ እንዲጨረስ ፡ የማይቻለውን ነገር በጦር ኃይል ሳይሆን ነገሩን ለፅርቅ ወይም ለሽምግልና ዳኞች ለማቅረብ ግዴታ ገብተዋል። የሽምግልና ዳኞች ስለሚመረጡበት አኳኋን ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው በደብዳቤ ይቀባበላሉ።

## ስድስተኛ ፡

ይህ ውል በዓለም መንግሥታት ማኅበር የውል መዝገብ ይገባል። ሁለቱ መንግሥታት አጽድቀው እንዲቀበሉት ያስፈልጋል። አደላድለውም የሚቀበሉበትን ደብዳቤ አዲስ አበባ ላይ እንደ ተቻለ መጠን በቶሎ ይቀባበላሉ።

## ሰባተኛ ፡

ይህ ውል አጽድቀው ከሚቀበሉበት ቀን ጀምሮ ለ20 ዓመት ይጸናል። ይህ ዘመን ሲፈጸም በያመቱ የሚታደስ ይሆናል ።

ይህ ውል በሁለቱ የኦፊሴል ቋንቋ ባማርኛና በኢጣልያ ከሁለት ላይ በትክክል ተጽፎ አንደኛው በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ፡ ሁለተኛው በኢጣልያ መንግሥት እጅ ይቀመጣል ።

ሐምሌ 16 ቀን 1920 ዓ. ም.

ይህ ከሆነ በኋላ በ1921 ዓ. ም. ልዑል ዱክ ዴዛብሩዝ እንደ ገና ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ መጡ። የመጡበትም ምክንያቱ የወዳጅነቱና የመንገዱ ሥራ ውል ከተፈረመ ትልቁን የአኖንሲያታ ኒሻን የሚባለውን ባለወርቅ ሰንሰለቱን ለእኛ ለመሸለምና ፡ እግረ መንገዳቸውን በአሩሲ አልፈው ከአሩሲና ከባሌ መገናኛ ተነሥቶ ወደ ኢጣልያ ሱማሌ አገር የሚወርደውን ዋቢ ሸበሌ የሚባለውን ትልቁን ወንዝ ከምንጩ፡ ላይ አይተው በዚያው ወደ ሞጋዲሾ ለመሔድ ነበር።

ምንጬንም ለማየት የፈለጉበትን ምክንያት በቃላቸው እንደ ነገሩን ፡ ትልቅ ማኅበር አቁሜ በሞጋዲሾ አጠገብ ትልቅ የእርሻ ሥራ ስለ አቆምሁ ያንን እርሻ የሚአጠጣው ውሃ ከዋቢ ሸበሌ የሚወርድ ስለ ሆነ ነው አሉን ።

በመንገዳቸውም ሁሉ ማናቸውም ችግር እንዳያገኛቸው መሪ የሚሆኑ ሰዎች ጨምረን ሰደድናቸው።

ልዑል ዱክ ዴዛብሩዝ ምንም እንኳ የኢጣልያ መስፍን ቢሆኑ የተፈረመው የወዳጅነቱ ውል ጸንቶ የሚኖር ነው እያሉ እየመላለሱ መናገራቸው አልቀረም ነበርና እንደ ቃላቸው ይሆናል የማለት ተስፋ አድርገን ነበር።

የወዳጅነቱንና የመንገዱን ሥራ ውል ከተዋዋልን በኋላ ውላችንን ለመጠበቅና ቃላችንን ለማክበር ስንል ፡ ብዙ ገንዘብ አውጥተን ከሆላንድ አገር መሐንዲሶች ቀጥረን አዲስ አበባም ካሉት ከእኛ መሐንዲሶችና ካገርሰዎች ጨምረን እስከ ደሴ ያለውን የመንገዱን አቅጣጫ አስመርምረን ፕላኑን አሠርተን ከጨረስን በኋላ ፡ የመንገዱ ሥራ እንዲጀመር ብንጠይቃቸው ጥንቱንም ለጠብ ማንሻ እንጂ ለሥራው አላሰቡበትምና ፡ የእኛ መሐንዲሶች የመረመሩትንና የቀየሱትን ነቅፈው የነሱ መሐንዲሶች በመረመሩትና በቀየሱት እንዲሠራ እየጠየቁና ነገሩን ወደ ኋላ እየጐተቱ አስቀሩት። በአውሮጳ ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ውሉን አፍርሶ ሥራውን እንዳስቀ ረው እያስመሰሉ ያስወሩ ጀመር። መቸም ቢሆን ለኢትዮጵያ ጉዳት የሆነባትእውነቱን እጠብቃለሁ እያለች እንደ ኢጣልያን ገንዘቧን ለጋዜጣ ሳታወጣና የሐሰት ወሬ ሳታወራ መቅረቷ ነው። ኢጣልያ ግን ይህን የመሰለ ወሬ ማውራቷ ኢትዮጵያ ውል አፍራሽ ናትና በጦርነት እወስዳታለሁ ለማለት እንዲመቻት መሆኑ የማይጠረጠር ነበር። በሥራዋም ተገልጦ እነሆ ይታያል ።

# ምዕራፍ 24

## አልጋ ወራሽነትንና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነትን ሳንለቅ የንጉሥነት ማዕርግ ስለ መቀበላችን ።

ልጅ ኢያሱ መንግሥትን ለመምራት ባለመቻላቸው ምክንያት፣ አልጋ ወራሽነታቸውን በተሻሩ ጊዜ ፡ ንግሥት ዘውዲቱ ሲነግሡ እኔም አልጋወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ስሆን ፡ ለመንግሥቱ ሥራ ሁሉ አላፊ ሆኘ እንድሠራ ነበርና በዚሁ በእንደራሴነቱ ሥልጣን የአዲሱን ሥልጣኔ መንገድ እየተከተልሁ ሥራ ስጀምር ፡ ባለመታደል ከመኳንንቱ የጥንት ልማድ ጠባቂዎች የሆኑት አንዳንዶቹ የተሾሙበትን አገር እንደ ፈቃዳቸው ለመግዛት ያሰቡትን አሳብ አስቀርተን ፡ የተበደለ ሲጮህ ፡ ጌትነታቸውን ሳንመለከት በትክክል ስንፈርድባቸው ፡ በግዛታቸው ከሚገኘው ገቢ ገንዘብ እንደቀረጥና የስልክ ዋጋ ፡ ይህንም የመሳሰለውን ወደ መንግሥት አግቡ ስንላቸው ፡ በሹም ሽርም ካንዱ አገር ወደ ሌላው አገር ስናዛውራቸው ኀዘን ይሰማቸው ጀመር። ይህንንም የሚያዝኑበትን ነገር ገልጠው እንዳይናገሩ ሥራው ሁሉ በትክክል መሠራቱን ልባቸው ያውቀዋልና መናገሩ የሚያሳፍራቸው ስለ ሆነ ፡ ይህን ትተው ለሥራቸው ሁሉ የቀና መሣሪያ ንግሥት ዘውዲቱን ለማድረግ ቆረጡ።

ለዚህም ሥራ በመጀመሪያ መሪ ያደረጉት ደጃዝማች ባልቻን ነው ። ደጃዝማች ባልቻ የተወለዱት ከአዲስ አበባ በጐዞ ያራት ቀን መንገድ በሚርቅ አገምጃ በሚባል አገር ነው። በአገምጃ ጦርነት በተደረገ ጊዜ እርሳቸው ገና ወጣት ልጅ ነበሩና በድሉ ውስጥ አንድ ወታደር አግኝቶና ማርኮ ለዐፄ ምኒልክ አመጣላቸውና በቤተ መንግሥት አደጉ። ክርስትናም ያነሷቸው አባቴ ልዑል ራስ መኰንን ናቸው።

ካደጉም በኋላ ዐፄ ምኒልክ ለመንግሥቱ ገንዘብ ሁሉ ጠባቂ አድርገው ሾሟቸው። በኋላ ግን በአድዋ ጦርነት ጊዜ ከኢጣልያኖች ጋራ ሲዋጉ የጀግንነት ሥራ ስለ ሠሩ ደጃዝማች ተብለው በክብር ይኖሩ ጀመር። አሁንም ኢጣልያኖች በግፍ ደብድበው የገደሏቸው ባርበኝነት በተዋጉበት ብቻ ሳይሆን በዚያው በአድዋ ጦርነት ቂም ጭምር ነው።

ደጃዝማች ባልቻ በዐፄ ምኒልክና በእኛም ዘመን በማዕርግና በክብር ሲኖሩ ፡ በ1912 ዓ. ም. የእኛን ሥራ ለማሰናከል የተነሡት ተራ ሰዎች መሪ ይሁኑን ብለው ስለ አታለሉዋቸው በነገሩ ገብተው ነበር። በኋላ ግን እነዚያ ተራ ሰዎች እየተያዙ ቅጣት ሲፈረድባቸው እርሳቸው በነገሩ አልገባሁም በማለት ተከራክረው ከቅጣት አምልጠው ወደ ግዛታቸው ወደ ሲዳሞ ሔደው ነበር።

ከቀድሞውም ባላገሩን ባገዛዝ ፡ ወታደሩን በማደሪያ ስለ በደሉት ወደ አዲስ አበባ እየመጣ በመጮሁ ምክንያት መጥተው እንዲፋረዱ ብለን ብንጠራቸው ፡ ነገ ፡ ሣልስት ፡ አሞኛል ደከሞኛል እያሉ ብዙ ወራት አሳልፈው መጡ።

ከመጡም በኋላ ከተበደሉት ሰዎች ጋራ በችሎት ቀርበው ይፋረዱ እንዳይባሉ አሞኛል በማለት በቤታቸው ተቀምጠው በእኛ ላይ ሁከት ለማድረግ መሞከራቸውን ስለ ሰማን ፡ ቤታቸውን በወታደር አስከብበን በግድ እንዲመጡ አድርገን ብናስመረምር ፡ በእኛ ላይ ሁከት ለማድረግ ማሰባቸውን በቃላቸው ስለ አመኑ ፡ የራሳቸው አሽከሮችም ስለ መሰከሩባቸው ከሹመታቸው ተሽረው በተወሰነ ስፍራ እንዲኖሩ በየካቲት ወር 1920 ዓ. ም. ተፈረደባቸው።

ከዚህም ቀጥሎ በነሐሴ ወር 1920 ዓ. ም. አንዳንድ የማይረቡ ተራ ሰዎች ደጃዝማች አባ ውቃውን መሪ አድርገው በእኛ ላይ ተነሡ ።

አባ ውቃው ቀድሞ የዐፄ ምኒልክ አሽከር ነበር። እኛ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆንን በኋላ ግን ደጃዝማች ብለን የዘበኞቻችን አለቃ አደረግነው። ነገር ግን ላገሩ ለኢትዮጵያና ለክብሩ አሳቢ ካለመሆኑ የተነሣ ፡ከማይረቡ ተራ ሰዎች ጋራ እየመከረ በእኛ ላይ ሁከት ለማስነሣት ስለፈለገ ፡ ወገን ለማብዛት ሲል ይህን ሁከት ለማስነሣት ያዘዙኝ

ንግሥት ዘውዲቱ ናቸው እያለ ማውራቱን ሰምተን ነገሩን በቃሉ እንዲነግረን ብንጠራው ፡ የቤተ መንግሥቱ ቅጥር ግቢ ሰፊ ነውና ካንዱ ወዳንዱ ስፍራ እየተዛወረ ቆይቶ ጊዜው ሲጨልም ፡ በቤተ መንግሥት አጠገብ ወደ አለው ወደ ዐፄ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ገብቶ ዐምዖ ተቀመጠ። በኋላ ግን በሞትም እንዳንቀጣው እጨጌውንና ካህናቱን አማላጅ ልኮ እጁን ስለ ሰጠ ፡ የሞቱን ቅጣት ተምሮ በልዩ ስፍራ በግዞት እንዲቀመጥ ተፈረደበት።

ከዚህም በኋላ በአዲስ አበባ የሚኖሩት ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ፡ የጦር አለቆችና በየሥራውም ላይ የተሾሙ ሰዎች ሁሉ ፡ ባንድነት ሆነው «በአልጋ ወራሻችን ላይ የማይረቡ ተራ ሰዎች በየጊዜው እየተነሡ ሁከት ያደርጋሉ ምናልባት ደግሞ ወደ ፊት ይህን የመሰለ ሁከት የተነሣ እንደሆነ እርስ በርሳችን ደም ሳንፋሰስ አንቀርምና ፡ ይህን ሁከት የሚያግድ ነገር ማሰብ ያስፈልገናል። ለዚህም የሚሻለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ማድረግ ነው ንግሥት ዘውዲቱ የመንግሥቱን ሥራ በሙሉ ለአልጋ ወራሽ ለቀው በፊት ሲነግሡ እንደ ተመሠረተው እርሳቸው የዘውዱንና የዙፋኑን ክብር ብቻ ይዘው እንዲኖሩ ፡ አልጋ ወራሽ ግን ከንግሥት ሳይማከሩና ሳያስፈቅዱ በመስከረም 17 ቀን 1909 ዓ. ም. እንደ ተወሰነውና እንደ ተጀመረው የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ በሥልጣናቸው ብቻ እንዲሠሩ ሥልጣናቸውም ኃይል ያለውና የተፈራ እንዲሆን የንጉሥነት ማዕርግ እንዲያገኙ ብናደርግ ነው›» በማለት ተስማምተው ነገራቸውን ከቆረጡ በኋላ በቤተ መንግሥት ግቢ ባለው በሰፊው አደባባይ ተሰብስበው ፡ አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ ንጉሥ እንዲባሉና ማናቸውንም የመንግሥቱን ሥራ ከማንም ሳይማከሩ በሥልጣናቸው ብቻ እንዲሠሩ ይፍቀዱልን የሚል ቃል ጽፈው ለንግሥት ዘውዲቱ አቀረቡ።

ንግሥት ዘውዲቱም ልዩ አማካሪዎቻቸውን ጠርተው ቢያማክሩዋቸው በጣም የሚያስቸግር ነገር መስሎ ታያቸው። በውነትም በጣም የሚያስቸግር መሆኑ ለእኔም ተሰምቶኝ ነበር። ከኢትዮጵያ ባንዱ በትልቁ ክፍል ንጉሥ ተብዬ እንዳልሔድ ሌላ እንደራሴ የሚያስፈልጋቸው ሆነ። ንጉሥ ተብዬ በአዲስ አበባ እንዳልቀመጥ ሁለት ንጉሥ ባንድ ከተማ መቀመጥ ያልተለመደ ሆነባቸው። ስለዚህ በነገሩ የማስብበት ቀን ስጡኝ የሚል ቃል ላኩባቸው።

ይህም የሕዝቡ አሳብ እንኳን ለንግሥት ዘውዲቱና ለእኔም ቢሆን ከብዶኝ ነበርና ከተሰበሰቡት መኳንንቶች መካከል ሦስት ሰዎች ጠርቼ የመንግሥቱ ሥራ ሳይከፋፈል ባንድ ሰው አሳብ ብቻ እንዲሠራ ያሰባችሁት አሳብ ቢፈጸም መልካም ነው እንጂ የንጉሥነቱ ነገር ባይነሣ መልካም ነው እንዲያውም እኔ በነገሩ አለመግባቴን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው እንጂ ሰው አያውቅምና እኔ ንጉሥ ለመሆን ጓጉቼ ያነሣሣኋችሁ ይመስላልና ይህ ነገር እንዲቀር አድርጉ ብዬ ወደ ሕዝቡ ዘንድ ብልክባቸው እኛ ለማንም ሳናደላ ለመንግሥታችን ክብር ፡ ለሕዝቡ ጥቅምና ሰላም እንዲሆን አስበን የተነሣንበት ነውና ወደ ኋላ ለመመለስ አንችልም የሚል ቃል ስለላኩብን ዝም አልን ።

ከዚህም በኋላ የማስብበት ቀን ስጡኝ የሚል ከንግሥት ዘውዲቱ የመጣላቸውን ምላሽ ባዩ ጊዜ ንግሥት ዘውዲቱ የማስብበት ቀን ስጡኝ ማለታቸው የርሳቸውን አሳብ ከሚከተሉ ፡ ያዲሱን ዘመን ኑሮ ከማይወዱ ወዳጆቻቸው ጋራ መክረው አይሆንም ለማለት ወይም በዚህ ምክንያት ሽብር እንዲነሣ ለማድረግና ለማፋጀት ጊዜ እንዲያገኙ ሳይሆን አይቀርምና ምንም ቢሆን ምላሹን ዛሬ ካልሰጡን ሳንለያይ እንደ ተሰበሰብን የሚያስፈልግ ነገር ለማድረግ ቆርጠናል የሚል ቃል ጽፈው ሁሉም እየፈረሙና እያተሙ እንደገና አቀረቡላቸው።

በዚህም ላይ ደግሞ የከተማው ሕዝብ ፣ ሚኒስትሮችና መኳንንቶች የጦር አለቆችም በግቢ የተሰበሰቡበትን እውነቱን ነገር አላወቁትም ነበርና ሽብር ሊያነሡ ጥቂት ቀርቷቸው ነበር።

ንግሥት ዘውዲቱም በፊርማና በማኅተም እየሆነ የቀረበላቸውን ቃል አስነብበው ከሰሙ በኋላ የሰው ደም እንዳይፋሰስ ነገሩን ብንቀበላቸው ይሻላል ብለው እናንተ መክራችሁ በወሰናችሁት ቀን አልጋ ወራሽ ዘውድ ጭኖ እንዲነግሥ ፈቅጃለሁ ፡ የሚል ቃል ተጽፎ እንዲነበብላቸው ስለ አደረጉ ጸጥታና እርጋታ ሆነ። ወዲያውም እርስ በርሳቸው እየተጋፉ እስከ እልፍኝ አደባባይ ድረስ ገብተው በደስታ እያጨበጨቡ የግርማዊት ንግሥትን ዕድሜዎን ያርዝምልን ፡ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር እያሉ ምስጋናቸውን አቅርበው በየቤታቸው ሔዱ።

በማግስቱም እንደ ገና ተሰብስበው መጥተው ፡ ይህ ነገር የዋለ ያደረ እንደ ሆነ ሌላ አሳብ ታስቦ እንዳይፈርስብን እስከ ሦስት ቀን የንጉሥነቱ ነገር እንዲፈጸም ቢሆን ይሻላል ብለው ቢጠይቁ ፡ ንጉሥነትን ያህል ነገር በሁለትና በሦስት ቀን ውስጥ ለመፈጸም የማይቻል መሆኑን ፡ በዚህም ላይ በዙሪያችን ያሉት የጎረቤቶቻችን እንደራሴዎች መጥተው የደስታችን ተካፋይ እንዲሆኑ ለየመንግሥታቸው ማስታወቅ የሚያስፈልግ መሆኑን አስረድተን ፡የዘውዱ በዓል ካንድ ወር በኋላ በመስከረም 27 ቀን 1921 ዓመተምሕረትእንዲሆን ነገሩ ተቆረጠ።

ንጉሥም እንድንባል ንግሥት ዘውዲቱ በመፍቀዳቸው ደስ ያላቸው ፡ በጎረቤታችን የቅኝ አገሮች ያላቸው እንግሊዝና ፈረንሳይ ኢጣልያም ደስ ስላላቸው የእንግሊዝ መንግሥት የበርበራውን ገዥ ምስተር ኪተርማስተርን ፡ የፈረንሳይ መንግሥት የጅቡቲውን ገዥ ሙሴ ሻፖን ቤሳክን ፡ የኢጣልያ መንግሥት የኤርትራውን ገዥ ሲኞር ኮራዶ ዞሊን ወደ አዲስ አበባ ላኳቸው።


ለዚሁም ለንጉሥነቱ በዓል የሚያስፈልገው ሁሉ ከተዘጋጀ በኋላ በመስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፣ንጉሥ ሲያነግሥ የሚደረገው ታላቅ ሥነ ሥርዓት ሁሉ ተደርጎ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እጅ ዘውድ ጭነን የበዓሉ ቀን በክብር ተፈጸመ ።



የደጃዝማችነታችንን የማዕርግ ልብስ እንደለበስን



በአልጋ ወራሽነታችን ዘመን።



ሐጂ በዳሶ (ፊታውራሪ) ልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ አቶ ኢብሳ በጅሮንድ ተምትሜ፣ ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል(ራስ) ግርማዊት እቴጌ መነን፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ልዑል መኰንን፣ ልጅ ከበደ ተሰማ (ደጃዝማች) ልዑል አልጋወራሽ ልጅ ፋንታዬ ጅማ አሁን (ፊትአውራሪ) መሐመድ ዓሊ ቀኛዝማች በልሁ ደገፉ።



በአልጋ ወራሽነትታችን ዘመን የነበረው መኖሪያ ቤታችን።

# ምፅራፍ 25

## ኢጣልያኖች ራስ ጉግሣ ወሌ እንዲሸፍቱ ስለማድረጋቸው ።

ኢትዮጵያ አንድነት የሌላት መንግሥት ናት እያሉ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ፊት ከሳሾች የሆኑት ኢጣልያኖች የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እንዲከፋፈል የፕሮፓጋንዳ ሥራ መሥራታቸውን መመልከት በጣም ያስደንቃል። እኛም በትጋት ፕሮፓጋንዳቸውን በማፍረሳችን ያስገርም ነበር ። ነገር ግን ሞከሩ እንጂ ለመለያየት አልቻሉም ።

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የአጥቂነት ጦርነት ለማድረግ ያሰበችው ከብዙ ዘመን አስቀድሞ መሆኑን አሁን በቅርቡ ዘመን የተደረጉት ነገሮች ይመሰክራሉ።

ውጭ ውጭውን ለሰው ይምሰል ኢጣልያ የኢትዮጵያ ወዳጅ ናት እያሉ እያወሩ በሕዝባችን መካከል ታላቅ ጉዳት የሚያመጣ ፕሮፓጋንዳ ይዘሩ ነበር። ይህንኑም በኢትዮጵያ የሚኖሩ የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ እንደሚያውቁት አንጠራጠርምና እንተወዋለን እንጂ ኢጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የሠሩት የተንኰል ፕሮፓጋንዳ ሁሉ ብንጽፈው ኖሮ ብዙ ገጽ በጨረሰ ነበር። ስለ ሆነም በራስ ጉግሣ ወሌና በራስ ኃይሉ በኩል የሠሩት የተንኰልና የፕሮፓጋንዳ ሥራ በሙሉ ኢትዮጵያ የታወቀ ነውና ሳንጽፍ ልንተወው አይገባም።

ራስ ጉግሣ የእቴጌ ጣይቱ ወንድም የራስ ወሌ ልጅ ናቸው። አባታቸው ራስ ወሌ ከግዛታቸው በአንዱ ክፍል ደጃዝማች ብለዋቸው ሲኖሩ በኋላ ወደ ሸዋ መጡ።

እቴጌ ጣይቱ ከዐፄ ምኒልክ ጋራ ከተጋቡ ወዲህ ዘመዶቻቸው የሆኑ የበጌምድርና የስሜን ፡ የየጁም ሰዎች ፡ ከሸዋ ሰዎች ጋራ በጣም እንዲቃረቡና ፡ እንዲያበጁ ይጥሩ ነበርና ፡ ሴቶቹን ዘመዶቻቸውን ከሸዋ መኳንንት ጋራ ፡ ወንዶቹን ዘመዶቻቸውን ከሸዋ ወይዛዝርት ጋራ ማጋባትን ዋና አድርገው ይዘውት ነበር። ስለዚህም በ1892 ዓ. ም. የወንድማቸው የራስ ወሌ ልጅ ደጃዝማች ጉግሣ የዐፄ ምኒልክን ልጅ ፡ (በኋላ የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት የሆኑትን) ወይዘሮ ዘውዲቱን እንዲያገቡ አደረጉ። በዚሁም ምክንያት በ1893 ዓ. ም. የራስነት ማዕርግ አግኝተው የበጌምድር ገዥ ሆነው ሲኖሩ ፡ ዐፄ ምኒልክ ታመው በቤት ከዋሉ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የነበሩት ራስ ቢትወደድ ተሰማ የበጌምድርን ግዛት ለራስ ወልደ ጊዮርጊስ ሰጥተው ፡ራስ ጉግሣ በግዞት እንዲኖሩ አደረገ -ራስ ጉግሣም 7 ዓመት ያህል በግዞት ከኖሩ በኋላ በመስከረም 17 ቀን 1909 ዓ. ም. ወይዘሮ ዘውዲቱ ለኢትዮጵያ ዘውድና ዙፋን ተመርጠው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ተብለው ሲነግሡ ፡ እግዚአብሔር እኔን ሴቲቱን መርጦ ለዚህ ለትልቁ ዘውድና ዙፋን ካበቃኝ ፡ ለብቻዬ ለመኖር ብፅዓት አደርጋለሁ እንጂ ከባል ጋራ አልኖርም ብለው ለብቻ መኖርን ስለ መረጡ ፡ ራስ ጉግሣም የንግሥትን አሳብ ቁርጡን ስላወቁት የመለያየታቸው ነገር በሁለቱም ፈቃድ ተጨረሰና ለራስ ጉግሣ የወሎጋ እምባቦንና የሳይንትን ግዛት ሰጠናቸው። ከአንድ ዓመት በኋላ ግን የበጌምድር ገዥ ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ስለ ዐረፉ ፡ የበጌምድርን ግዛት መልሰንላቸው ነበርና የቀድሞውን ግዛታቸውን በማግኘታቸው ለጊዜው ደስ ብሏቸው ሲኖሩ ፡ መቸም ኢጣልያኖች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅ ናቸውና ፡ አንዳንድ ኢጣልያኖች ለንግድ ወይም አገር ለማየት እያመካኙ መጥተው ከበጌምድር ወደ አሥመራ ሲመላለሱ ከራስ ጉግሣ ጋራ እየተገናኙ በልባቸው እንክርዳድ እየዘሩባቸው ይሔዱ ስለ ነበረ ደስታቸውን ወደ ኅዘን እስከ መለወጥ ደረሱ።

ከሁሉም የሚብሰው በጎንደር የኢጣልያ የንግድ ወኪል ሆኖ የተቀመጠው ፕሮፓጋንዳ ለማድረግ ዋና ሥራው ነበር።

የበጌምድር ገዥ መኖሪያው በደብረ ታቦር ከተማ ነው። ኢጣልያኖች ግን ፕሮፓጋንዳ ለመሥራት እንዲመቻቸው ካህናትና ነጋዴዎች በሚኖሩበት በጎንደር የንግድ ወኪል (አጃንሲያ) ለማስቀመጥ ከእኛ አስቀድሞ ከነበሩት ከዐፄ

ምኒልክና ከልጅ ኢያሱ ፈቃድ ተቀብለው ነበር። በኋላ ግን በጎንደር አጠገብ ባንድ ስፍራ ራስ ጉግሣ ወሌ የርስት ቦታ ነበራቸውና ይህን የርስት ቦታዎን በኪራይ ቢሰጡን ቦታዎን እናለማልዎታለን ፣ በኋላም በምንለቅበት ጊዜ በላዩ የሠራነውን ቤትና ሌላውንም ማናቸውንም ነገር ሁሉ አለዋጋ እንለቅልዎታለን የሚል ቃል ጽፈው ቢያቀርቡላቸው እውነት መስሏቸው ፈቀዱላቸው።

በዚህም ቦታ ለንግድ ወኪል አድርገው ያስቀመጡት ሙሴ ፖሌራ የሚባል ነበር። ሙሴ ፖሌራም ለዚሁ ለተንኰል ፕሮፓጋንዳ ሥራው እንዲመቸው ኢትዮጵያዊት ሴት በገንዘብ ቀጥሮ ሚስቱ ነሽ እያለ ልጆች ወለደላት።

በዚህም ላይ በዕድሜ ሽምግሎ ነበርና ኢትዮጵያውያን በዕድሜ የሸመገለ ሰው ማክበር ልማዳቸው ስለ ሆነ የጎንደር ሰዎች ሁሉ እንደ ውጭ አገር ሰው ሳያዩት ያከብሩት ነበር። እርሱም በበኩሉ ሴቶች ሲወልዱ ያራስጥሪ ፡ ሰው ሲሞት የተዝካር እያለ ገንዘብ ይሰጣል። እርሱ ካቶሊክ ሆኖ ሳለ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ካህናቱ እያዩት ይጸልያል። በዓመት በዓልም ቀን እንደ ኢትዮጵያውያን መኳንንት ልማድ ጠላ እያስጠመቀ ፡ ጠጅ እያስጣለ ፡ ሰንጋ እያሳረደ ካህናቱንና ነጋዴዎቹን ይጋብዛል። በዚሁም ሁሉ ምክንያት ከሕዝቡ ጋራ መልካም መገናኛ አበጀ ።

ደግሞ የበጌምድሩ ገዥ ራስ ጉግሣ ወሌ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የጸኑ የአውሮጳን ሃይማኖትና የሥልጣኔ ሥራ ተቃዋሚ መሆናቸውን ያውቃልና ወደ እርሳቸው እየሔደ ፡ «ለኢትዮጵያ የሚሻላት እንደ ጥንቱ እንደ አርጌው ልማድ ብትኖር ነው እንጂ የአውሮጳን ሥልጣኔ መከተል አይጠቅማትም። ያሁኑ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ግን አሳባቸው የአውሮጳን ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ለማግባት ነው ይባላል ፡ የአውርጳ ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ከገባ የሃይማኖት ነፃነት ይሆናል። የሃይማኖትም ነፃነት ከሆነ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እየደከመች ፡ የካቶሊክ ሃይማኖት እየበረታችና እየሰፋች እንድትሔድ ሊሆን ነው ፡ እንዲያውም ራሳቸው አልጋ ወራሹ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ሊገቡ ነው እየተባለ ይወራል። ደግሞ የባርነት ነገር ከኢትዮጵያ እንዲጠፋ በየጊዜው አዋጅ መንገራቸውን ሰምተናል። ነገር ግን አሁን ባሮች ሁሉ ነፃ ይውጡ ከተባለ ፡ እነዚህ የበጌምድር ጌቶችና ጨዋዎች ሁሉ እንደምን ሆነው ሊኖሩ ነው። ጌቶቹ በእጃቸው እያረሱ ፡ ወይዛዝርቱ በእጃቸው እየፈጩ ሊኖሩ ነውን ? በአውሮጳም ቢሆን ሥራው ሁሉ በመኪና ከሆነ ወዲህ የባርነት ነገር ቀረ እንጂ ቀድሞ እንደናንተ ሰው ሁሉ ለያንዳንዱ ባሮች ነበሩት። አሁንም በዚህ አገር እርስዎና እንደርስዎ ያሉት ትልልቆቹ መኳንንቶች ካላሰባችሁበት ትልቅ ጉዳት ያገኛችኋል ። » እያለ ፡ እርሳቸውም በበኩላቸው ለየትልልቆቹ መኳንንቶች እያስረዱ በእኛ ላይ በጦርነት ኃይል እንዲነሣ እያደረገ ይነግራቸው ነበር። እርሳቸውም መኳንንቶቻቸውን እየሰበሰቡ አንድ ወዳጄ የሆነ ሰው እንደዚህ ብሎ መከረኝ ምን ማድረግ ይሻላል እያሉ በምስጢር ስለ ነገርዋቸው ፡የተንኰል ምክር መሆኑን የተረዱት አንዳንዶች መኳንንቶች በምስጢር ወደ እኛ ይልኩ ነበር።

እኛ ግን ራስ ጉግሣ ወሌ የኢጣልያኖችን የተንኰል ምክር ሰምተው በመንግሥታችን ላይ ክፉ ነገር ያስባሉ ብለን አልጠረጠርንምና ነገሩን ለማጣራት ስንል በትዕግሥት ቆየን። በዚህ ጉዳይ ወደ ትዕግሥት የሚገፋን ስለ ንግሥት ዘውዲቱ በማሰብ ነበር።

በዚህም ላይ ደግሞ እንደ አጋጣሚ በዚያው ወራት በአዲስ አበባ የቆዳ ፋብሪካ እንዲቆም ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ላንድ ለውጭ አገር ሰው ኮንትራት ስለተሰጠ ፡ እርሱ ከበሬ ቆዳና ከፍየል ሌጦ በቀር የፈረስና የበቅሎ፣ የአህያና የውሻ ቆዳ እየገፈፈ ወደ ፋብሪካው እየወሰደ ይፍቅ ነበርና ፡ ኢጣልያኖች ይህን በሰሙ ጊዜ በአዲስ አበባ አህያና ውሻ እየታረደ ለመኳንንቱና ለወታደሩ በግብር ላይ ማብላት ተጀምሮዋል ፣ ወደ ፊት ግን የአህያና የውሻ ሥጋ ብሉ ተብሎ በሙሉ ኢትዮጵያ ዐዋጅ መነገሩ ይቀር አይመስልም እያሉ በያገሩ ስለ አወሩ የበጌምድር ሕዝብ በሙሉ ልቡ ተናወጠ ።

በኢትዮጵያ ጥንተ ክርስቲያኑ የበጌምድር ሕዝብ ይቅርና ክርስትናን አሁን በቅርቡ የተቀበለው ሕዝብ ቢሆን እንኳን ሥጋውን ሊበላውና የአህያና የውሻ ቆዳ እየተገፈፈ ይፋቃል ለሥራም ይሆናል ብለው ቢነግሩት ትልቅ ኀዘን እንደሚሰማው የታወቀ ነው። ምናልባት በአውሮጳም ይህን የመሰለውን የሚጸየፉ ሰዎች አይታጡም።

ራስ ጉግሣ ወሌ ከንግሥት ዘውዲቱ የተለያዩት ምንም እንኳ በፈቃዳቸው ቢሆን በዚህ በትልቁ የደስታ ዘመን ወደ አዲስ አበባ ሳይመጡ በበጌምድር ብቻ ተወስነው በመኖራቸው ማዘናቸውን ላንዳንድ ወዳጆቻቸው መናገር ጀምረው ነበርና ፡ ኢጣልያኖች ይህን ሲሰሙ ራስ ጉግሣን ለማታለል የተመቸ ጊዜ መሆኑን ዐውቀው ፡ የሚያስፈልግዎን ያህል መሣሪያ እንሰጥዎታለንና በኢጣልያ መንግሥት ረዳትነት ካሁኑ መንግሥት ሸፍተውና ተዋግተው በማዕርግም ንጉሥ ተብለው ከንግሥት ዘውዲቱ ጋራ የሙሉ ኢትዮጵያ ገዥ ይሆናሉ እያሉ በልባቸው ጠልቆ የሚገባ ነገር ስለ ነገርዋቸው ፡ አሁን ይህን የመሰለ ምክንያት ይዘው የአህያና የውሻ ሥጋ ለሚያበላ መንግሥት እየተገዛን ከመኖርና ባሮቻችንን ከመልቀቅ መሞት ይሻለናል እያሉ የበጌምድርን ሕዝብ በሙሉ ወገን ለማድረግና የጦርነት ኃይል ለማጠንከር ይሞክሩ ጀመር። ይኸንንም ቃል በሙሉ ባዋጅ መልክ ገልጸውታል።

ዳግም በደንከሌና በአውሳ አውራጃ ያለው ግዛታችን በረሃና የበሽታ ስፍራ በመሆኑ ወሰን ጠባቂዎች ወታደሮቻችን ስለ ተጎዱ ፣ አንዳንድ ጊዜ ወደ ደጋው እየወጡ እንዲያርፉ ይፈቀድላቸው ነበርና ኢጣልያኖች በሰላዮቻቸው ሲሰሙ ወታደሩ ብዛቱ ሲቀነስ ጊዜ እየጠበቁ የጦር መሐንዲሶች እየላኩ ተራራውንና ወንዙን ሜዳውንና ዳገቱን ካርታ እያነሡ ፡ ለራያ ፡ ለአዘቦ ጋሎች መሣሪያና ገንዘብ እየሰጡ ፡ ከእኛም መንግሥት እንዲሸፍቱ በሚቻላቸው ሁሉ የተንኰል ምክር ይመክሩዋቸው ነበርና ከነዚሁ ከዋጅራቶቹ አንዳንዶቹ እየመጡ ይነግሩን ነበር። እኛ ግን ኢጣልያ በ1920 ዓ. ም. ከእኛ ጋራ የተዋዋለችውን የወዳጅነት ውል ዘንግታ ይህን የመሰለ ሥራ መሥራቷን በማስመርመር ቆይተን ሳለን ፡ የዋጅራትና የራያ ፡የአዘቦ ጋሎች ከኢጣልያ በተቀበሉት መሣሪያና ገንዘብ ኰርተው ወደ ደጋው እየወጡ ሰው መግደላቸውን ፡ ከብት መዝረፋቸውን ስለሰማን ራስ ጉግሣ ወሌ የጁ ያደጉበት አገራቸው መሆኑንና ለበጌምድርም መቅረቡን ስለዐወቅን ፡ ባንድ ወገንም አሁን ወደ የጁ ሳይሔዱ የቀሩ እንደሆነ ከኢጣልያኖች ጋራ ምክር አላቸው ተብለው የታሙበት ሁሉ በዚህ እንዲገለጥ ስለ አሰብን ፡ እስከ የጁ የዋጅራትንና የአዘቦን ጋሎች በፍቅር እየጠሩ በወዳጅነት እየመከሩ ክፉ ሥራቸውን እንዲተዉ ያድርጓቸው ፡ እምቢ ቢሉ ግን በጦር ኃይል ይወጋሉ የሚል ትእዛዝ አሳለፍንላቸው።

ራስ ጉግሣም ትእዛዙ በደረሰላቸው ጊዜ ለጊዜው ፈቃድ ፈጻሚ ለመምሰል የበጌምድርን ሠራዊት ባዋጅ አስከትተው ወደ የጁ ሔዱ። የጁ ከደረሱ በኋላ ግን በዋጅራትና በራያ፡ በአዘቦ ጋሎች ላይ ለማድረግ የታዘዙትን በትክክል ሳይፈጽሙ ፡ እንዲያውም በኋላ ለርሳቸው ረዳቶች እንዲሆኑ ተስማምተው ወደ በጌምድር መመለሳቸውን ፡ ከተመለሱም በኋላ ወታደር መሰብሰብን የጦር መሣሪያ ማሰናዳትን ዋና ሥራ አድርገው መያዛቸውን ሰማን ። እኛም የወንድማማች ደም በከንቱ እንዳይፈስና የኢጣልያኖች ምኞት እንዳይ ፈጸም ለመጠንቀቅ ስንል ለማናቸውም ቢሆን ወረይሉ ላይ ተገናኝተን ከዘመቻው የተመለሱበትንና ሌላውንም ጉዳይ ሁሉ ቃል ለቃል ተነጋግረን ይመለሳሉ ብለን ብንልክባቸው እሺ ተነሣሁ መጣሁ እያሉ የማታለል ቃል ብቻ እየላኩ ለጦርነት እየተሰናዱ መቆየታቸውን ስለ ሰማን ወደ የጁ አልፈው ከዋጅራትና ከራያ ከአዘቦ ጋሎች ጋራ እንዳይገናኙ ለማገድ በዋድላና በደላንታ ሆነው የሚጠብቁ ወታደሮች በደጃዝማች ሙሉጌታ አበጋዝነት ላክን።

የኢጣልያ ፕሮፓጋንዳ ሠራተኞች በበጌምድር ያሉትን አንዳንድ ጠንቋዮችና ሕልም አላሚዎች እየፈለጉ ንጉሥ የምትሆንበት ዘመን ደርሷልና አይዞህ አትፍራ እያሉ እያደፋፈሩ እንዲነግሩዋቸው እያደረጉ ይልኩባቸው ነበር። ይህንንም ሁሉ የሚያስረዳ በጦርነቱ ውስጥ በተማረከው በራስ ጉግሣ የጽሕፈት ኮረጆ ውስጥ ተገኝቶ ታይቷል ።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳንዶቹ ከሃይማኖት ትምህርት በቀር ሌላ የዓለማዊ ፖለቲካ ትምህርት የሌላቸው ስለ ሆኑ መነኩሳት ወይም ባሕታውያን በዚህ ዘመን እንደዚህ ይሆናል ብለው ሲነግሩዋቸው ከእግዚአብሔር የተላኩ እየመሰላቸው እውነት አድርገው ይቀበላሉና በዚህም ለመጠቀም ኢጣልያኖች ይህን ስለዐወቁ ዋና መሣሪያ አድርገውት ነበር።

እኛም ኢጣልያኖች በዚህ ነገር መግባታቸውንና አለመግባታቸውን ለማወቅ ብለን ያገርን ውስጥ ጸጥታ ለመጠበቂያ አንድ አይሮፕላን በዋጋ ሸጡልን ፡ ነጂውንም ከናንተ ሰው እንቀጥራለን ብለን አዲስ አበባ ላለው

ለኢጣልያ ሚኒስትር ብንነግረው ለመንግሥቱ አስታውቄ ምላሹን በቶሎ አመጣለሁ ብሎን ነበር። ነገር ግን ምንም ምላሽ ሳይሰጠን ቆይቶ ራስ ጉግሣ በእኛ የጦር ሠራዊት ላይ አደጋ ጥለው ለመዋጋት አንድ ቀን ሲቀራቸው ፡ አይሮፕላኑን አሁን በፍጥነት ከአሥመራ ለመላክ አልደረሰልንም ብሎ ኣስታወቀን። ምላሹም እንደዚህ እንዲሆን ልባችን አውቆት የቆየ ስለ ሆነ ምንም አላስደነቀንም።

ራስ ጉግሣም ይህን በመሰለው በሐሰት ነገር ተታልለው ጦርነት ለማድረግ ስለቆረጡ የክተት ዐዋጅ አስነግረው በግስጋሴ መጥተው በመጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ.ም ቋራ ላይ በደጅዝማች ሙሉጌታ ላይ አደጋ ጥለው ሦስት ሰዓት ያህል እንደ ተዋጉ ድልሆኑ።

ኢጣልያኖች ብዙ ዓመት የደከሙበት የተንኰል ምክር በሦስት ሰዓት ፈረሰና ራስ ጉግሣ ከሞት አደጋ ደረሱ። በዚህም ጦርነት ውስጥ በራስ ጉግሣ ሠራዊት እጅ ተገኝቶ ከተማረከው መሣሪያ የሚበዛው ከአሥመራ የመጣ ወጨፎ በመሆኑ ራስ ጉግሣ እንዲሸፍቱ የረዱዋቸው ኢጣልያኖች መሆናቸውን አረጋገጠልን።

ራስ ጉግሣ በሞቱ በሁለተኛው ቀን በመጋቢት 24 ቀን 1922 ዓመተ ምሕረት ንግሥት ዘውዲቱ ዐረፉ።

ንግሥት ዘውዲቱ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ በስዊድኑ በዶክቶር ሐነርና በስዊሱ በዶክቶር ማይበርግ ተመርምሮ የታወቀ የሱካር በሽታ (ዲያቤት የሚባል በሽታ) ነበረባቸው። ይኸውም በሽታ በያመቱ እየባሰና እየጠነከረባቸው የሚሔድ ስለ ሆነ በዚህ ዓመት በጣም ታመው ነበር። ስለዚህ ለበሽታቸው መጨመሪያ እንዳይሆን ተብሎ የራስ ጉግሣን ሞት አልሰሙም ነበር። ይኸውም የሚያክሟቸው ሐኪሞች ዶክቶር ሐነርና ፡ ዶክቶር ማይበርግ ኀዘኑን አይስሙ ብለው ስለ አዘዙ ነው። ኢጣልያኖች ግን የተንኰላቸውን መስፈሪያ ለመሙላት ሲሉ ሰምተው በድንጋጤ ሞቱ ብለው አወሩ እንጂ ፡ በአዲስ አበባ ያሉት መሳፍንቱም መኳንንቱም ሚኒስትሮችም ንግሥት ዘውዲቱ የራስ ጉግሣን በጦርነት መሞት ሳይሰሙ ማረፋቸውን የማያውቅ የለም።

# ምዕራፍ 26

## የቤተ ክህነት ሥራ እየተሻሻለና እየታደሰ እንዲሔድ ስለማሰባችንና ስለ መጀመራችን ።

ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለመንግሥቱ ሥራ ሁሉ አላፊ እንደ መሆናቸው ለቤተ ክህነትም ሥራ አላፊነት አለባቸውና ከሊቃውንቱና ከመምህራኑ መካከል እየመረጡ በየአድባራቱና በየገዳማቱ ለመሾምና ለመሻር ሥራቸውንም ሁሉ ለመቆጣጠር ሥልጣን አላቸው።

ነገር ግን የመንግሥቱ ሥራ እየበዛ ከመሔዱና በዙሪያቸውም ካሉት አረማውያን ጋራ በየጊዜው ጦርነት ከማድረጋቸው የተነሣ ፡ የቤተ ክህነትን ሥራ በሙሉ ለመቆጣጠር ጊዜ አልነበራቸውም ነበርና በቤተ ክህነት ወገን በስሕተት እየገባ ልማድ ሆኖ የቀረና የቤተ ክርስቲያንንም ሥርዓት የሚያጐድል ብዙ ነገር ነበር።

አሁን ግን ሕገ መንግሥት አቁመን ፡ ለሚኒስቴር ቤቱ ሁሉ ደንብ ሰጥተን ሚኒስትሮች ለየሥራቸው ሁሉ አላፊ ሆነው እንዲሠሩ ስለ አደረግን ፡ከመንግሥት ሥራ በሚተርፈው ጊዜያችን ከሊቃውንቱና ከመምህራኑ ጋር እየተገናኘን የቤተ ክህነቱ ሥራ ጥቂት በጥቂት እየተሻሻለ እንዲሔድ አደረግን። ይኸውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1ኛ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቁም ትንሹም ወንዱም ሴቱም በክርስቲያንነቱ ጸንቶ የሚኖር ስለ መሆኑ ፡ በየሳምንቱ እሑድ እሑድና በየትልልቁ በዓላት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሔደ ቅዳሴ ይሰማል። የሚችልም ሥጋ ወደሙ ይቀበላል። ነገር ግን ቅዳሴው ሕዝቡ ሁሉ በማያውቁት በግእዝ ቋንቋ ስለ ነበረ ፡ ብዙዎቹ የዜማውን ድምጥ ከመስማት በቀር ምስጢሩን የሚያስረዳ ቃል ሳይሰሙ በየቤታቸው ይመለሱ ነበር። አሁን ግን ጸሎተ ቅዳሴው በአማርኛ ቋንቋ እንዲተረጐምና እንዲታተም አድርገን በየቤተ ክርስቲያኑ ስለ ታደለ ሕዝቡ መላውን እንኳ ባይሆን ዋና ዋናውን ቃል በቋንቋው ሲነበብ መስማት ጀምሯል። ወንጌልና የሐዋርያት መልክትም በአማርኛ ቋንቋ እንዲነበብላቸው ተደረገ።

2ኛ ፡ በየትልልቁ አድባራትና ገዳማት የሚኖሩት ፡ አለቃው ከካህናቱና ከገበዙ ፡ አበ ማኅበሩ ከመነኲሳቱና ከአርድእቱ ጋራ ስለ ኑሮአቸው በየጊዜው በመካከላቸው የሚነሣውን ሁከት ለማስቀረት ስንል ፡ ሊቃውንቱንና መምህራኑን እየሰበሰብን የቀድሞውን የየአድባራቱንና የየገዳማቱን የኑሮ ልማድና ደንብ እያስመጣን እየተሻሻለ አዲስ ደንብ እንዲቆም በመደረጉ ትልቅ ጥቅም ተገኝቶበታል። ተሻሽለው የቆሙትም አዲሶቹ ደንቦች በዝቋላ ፡ በደብረ ሊባኖስ ፡ በኢየሩሳሌምና በሌሎችም ገዳማት ሁሉ ይገኛሉ።

3ኛ፣ ባገራችን በኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን የተክሊል ጋብቻ ለመኖሩ መጽሐፈ ተክሊል በየአድባራቱ መገኘቱ ያስረዳል። ነገር ግን ግራኝ አሕመድ የሚባለው በተነሣበት ዘመን ወይም ዮዲት የምትባለው ከፈላሾች ወገን የሆነች ንግሣ ክርስቲያንን ባጠፋችበት ዘመን ይሁን አልታወቀም እንጂ ፡የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እየጐደለ ስለ ሔደ በሕዝቡ ይቅርና በካህናቱም ቢሆን በተክሊል መጋባት በጣም አልሰፋም ነበር። ዳሩ ግን ከቤተክህነትና ከሕዝቡም ወገን ብዙዎቹ ከሚስቶቻቸው ጋራ ሥጋ ወደሙ እየተቀበሉ ጋብቻቸውን አጽንተው ይኖሩ ነበር ።

አሁን ግን ሊቃውንቱና መምህራኑ የተክሊል ጋብቻን አጠንክረው እንዲሰብኩ አድርገን የተክሊል ጋብቻ የተለመደ ሆኗል ።

4ኛ ፡ በቀድሞ ዘመን ሰው ሲሞት ቤተ ዘመዶቹ ተዝካር እያሉ ጠላና ጠጅ ሌላም የሚያሰክር ነገር እየደገሱ ካህናቱን ወደ ሟቹ ቤት እየጠሩ ከልክ ያለፈ መብልና መጠጥ እየሰጡ ከትእዛዝ እንዲወጡ ያደርጓቸው ነበር። አሁን ግን ይህን የመሰለው አደራረግ ላዲሱ የሥልጣኔ ዘመን የማይስማማና በቅዱሳት መጻሕፍትም የተከለከለ መሆኑን ስለ ተረዳነው ፡ ተዝካር በሚያሰክር መጠጥና ከልክ ባለፈ መብል መሆኑ ቀርቶ ፡ ዘመዱ የሞተበት ሰው ሁሉ ፍታቱን

እያስፈታ እንደ አቅሙ ለካህናቱ የፍታት ገንዘብ እንዲሰጥ ፡ ለነዳያን ግን የመብልና የመጠጥ ድግስ እየደገሰ በመጠን ቢያበላና ቢያጠጣ እንዳይከለከል ፡ ጳጳሳቱና መምህራኑም ይህንኑ እንዲሰብኩ አደረግን።

ለሕዝቡም አርአያና ምሳሌ ለመሆን ስንል ፡ ልጃችን ልዕልት ዘነበ ወርቅ በሞተች ጊዜ ስለ ፍታቱ ለየአድባራቱና ለየገዳማቱ የገንዘብ ስጦታ እያካፈልን ሰጥተናል። ብዙ ሰዎችም እንደዚሁ ማድረግ ጀምረዋል።

5ኛ፣ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ባንዳንድ አውራጃ ሰው ሲሞት ዘመዶቹ አንዳንዶቹ ጠጉራቸውን እየቆረጡ ደረታቸውን እየመቱ እየጮሁ ያለቅሱ ነበር። አሁን ግን ሰው ሲሞት ዘመዱ ለኀዘኑ ምልክት በልብሱ ጫፍ ጥቁር ምልክት ከማድረግ በቀር ፡ ጠጒር መቁረጡን ፥ ደረት መምታቱን ፡ ከል መልበሱን ፡ እንዲተው በየቤተ ክርስቲያኑ እየዞራችሁ ስበኩ ብለን ለመምህራኑ ትእዛዝ ስለ ሰጠንና መምህራኑም በትጋት ስለ ሰበኩ ስለ ሞተው ሰው ተስፋ እስከ መቁረጥ ማዘን እየተቃለለ ሔዷል ።

6ኛ ፡ ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና ሃይማኖትዋ እንዳይናወጥ ፡ የተሰጣትም ሕግ እንዲጸና ለማድረግ አላፊነት እንዳለብን ስለ ተረዳነው በየሳምንቱ አንድ ቀን ሊቃውንቱና መምህራኑ ወደ እኛ እየቀረቡ የቤተ ክርስቲያንን ችግር ሁሉ በቃላቸው እንዲያመለክቱ ስለ ፈቀድንላቸው የቤተ ክርስቲያን ችግር እየተቃለለ ሔዷል።

ከዚህ በቀር ደንቡ እየተጻፈ ለጊዜው ሳይፈጸም ቆይቶ የነበረው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

7ኛ ፡ በኢትዮጵያ የካህናቱ ቀሩጥር እጅግ ብዙ ነው። ለነዚሁም ሁሉ መንግሥት ከያውራጃው ከግማሽ ጋሻ እስከ አንድ ጋሻ መሬት ለያንዳንዱ ካህን ርስት እያደረገ ሰጥቷቸዋል። ይኸውም ርስት እየሆነ የተሰጠው መሬት ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ስለመሆኑ ቤተክርስቲያን ልታዝዝበት አትችልም። በዚህም ላይ ከንጉሥ ነገሥቱ ጀምሮ መሳፍንቱም መኳንንቱም ሌላውም እነሱን የመሰለው ሁሉ ወይዛዝርቱ እንኳ ሳይቀሩ የቤተ ክርስቲያን ገበዞች እየሆኑ ከ200 እስከ 700 ጋሻ መሬት ንጉሠ ነገሥቱ ርስት እያደረገ ይሰጣቸዋል። የእኛ አሳብ ግን በግብዝና ምክንያት ለያንዳንዱ መሆኑ ቀርቶ ፡የቤተ ክርስቲያን ርስት ሆኖ ከገቢው ገንዘብ የቤተ ክርስቲያን አለቆች ለቀሳውስትና ለዲያቆናት ለመዘምራንና ለአንባብያን ለኑሮዋቸው የሚበቃ እየሰጡ በሚተርፈው የቤተ ክርስቲያን አለቆች እየተማከሩ በሚጐድለው መንግሥት እየረዳቸው የትምህርት ቤትና ሆስፒታል ፡ የሽሽማግሎች መጦሪያና የድኖች ልጆች ማሳደጊያ ቤት እንዲሠሩበት ለማድረግ ነው።

ይህንንም አሳባችንን በሙሉ ኢትዮጵያ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት እንዲፈጸም ለማድረግ ብዙዘመን የሚወስድብን ስለ ሆነ፡ጥቅሙንና አደራረጉን ለማሳየት ብቻ በዝቋላ ፡ በአዲስ ዓለም ፡ በአሰቦት ገዳማት በአዲስ አበባም አድባራት በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት እንዲጀመር አድርገናል።

# ምዕራፍ 27

## ከኢትዮጵያ መምህራን ተመርጠው ጳጳሳት እንዲሾሙ ስለ ማድረጋችን ።

ኢትዮጵያ እጅግ ሰፊ አገር ከመሆንዋ በላይ ካራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሺ 600 ዓመት ያህል በክርስትናዋ ጸንታ የምትኖር መሆንዋን የሚጠራጠር ማንም ሰው ያለ አይመስለንም። ቢኖርም ታሪኳን በማንበብ ብቻ ለመረዳት ይችላል ።

ነገር ግን ክርስትናዋን በተቀበለችበት ዘመን ቤተ መንግሥቱ ወይም የመንግሥቱ ዋና ከተማ አክሱም ላይ ስለ ነበረ ፡ ለዚያው ለአክሱም አውራጃ በእስክንድርያ በመንበረ ማርቆስ ከተቀመጠው ሊቀ ጳጳሳት እየተሾመ አንዳንድ ጳጳስ ብቻ እየመጣ ፣ የመጣውም ሲሞት ሌላ እየተተካ ይኖር ነበር እንጂ እንደ አውራጃው ስፋት ብዙ ጳጳሳት እየተሾሙ አይመጡም ነበር ።

በቅርቡም በ1864 ዓመተ ምሕረት በነገሡት በዐፄ ዮሐንስ ዘመን አራት ግብጻውያን ጳጳሳት ተሾመው በ1873 ዓ. ም. መጥተው ነበር ። ምክንያቱም ዐፄ ዮሐንስ ለሸዋው ለንጉሥ ምኒልክና በጐጃም ላነገሥዋቸው ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፡ ደግሞ ልጃቸውን ራስ አርአያን በበጌምድር ለማንገሥ አስበው ነበርና አንደኛውን ጳጳስ ለራሳቸው ለትግሬ አስቀርተው፥፡ምሦስቱን ጳጳሳት ለሦስቱ ነገሥታት ለማካፈል ነበር። ነገር ግን አራተኛው ጳጳስ ገና አክሱም ሳይደርሱ ስለ ሞቱ ፡ ራስ አርአያም ሳይነግሡ ስለሞቱ ፡ የኢትዮጵያን ሀገረ ስብከት ለሦስቱ ጳጳሳት ብቻ አካፍለው ሰጥተዋቸው ነበርና ካህናቱ የቅስናና የዲቁና ሹመት ለመቀበል አንደኛው ጳጳስ እስከሚኖርበት እስከ ሩቅ አገር ከመሔድና ከመድከም ዐርፈው ነበር ። ከነዚህም ከሦስቱ ጳጳሳት ሁለቱ ሲሞቱ ፡ ሌሎች ጳጳሳት ስላልተተኩ ፡ ለሙሉ ኢትዮጵያ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ብቻ ሆነው ስለ ነበሩ የርሳቸውም መኖሪያ በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ ስለ ሆነ ፡ ከኢትዮጵያ አውራጆች ለቅስናና ለዲቁና የሚመጡት የቤተ ክህነት ወገኖች ትልቅ ችግር እያገኛቸው በሁከት ይኖሩ ነበር።

እኛም የቤተ ክህነት ወገኖች በዚህ ነገር በጣም መቸገራቸውን ስለአወቅን ፡ ካገሩ ውስጥ መምህራን ተመርጠው ጳጳስነት ተሾመው በየሰበካቸው እየዞሩ እንዲሰብኩ ቅስናም ዲቁናም እንዲሰጡ በማለት ይህን አሳባችንን ከነማስረጃው ጽፈን በግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና በእኔ ማኅተም ታትሞ ለእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ለአቡነ ዮሐንስ ተላከላቸው።

አቡነ ዮሐንስም በመልካም አሳባቸው ነገሩን ከመረመሩት በኋላ የሚገባ ጥያቄ መሆኑን ስለ ተረዱት ፣ “ከኢትዮጵያ መምህራን አምስት መርጣችሁ ስትልኩልን ጳጳሳት አድርገን ለመሾም ፈቃዳችን ነው። ነገር ግን ለአምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቀዳሚ የሚሆን አንድ ግብጻዊ ጳጳስ ጨምረን እንልካለንና ይህንም እንድታውቁት ይሁን” የሚል ምላሽ ላኩልን ።

ይህንም ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለመምህራኑንና ለሊቃውንቱ ባስታወቅናቸው ጊዜ ብዙዎቹ ነገሩን በደስታ ተቀበሉት። ከቤተ ክህነት ወገኖችግን አንዳንድ ሰዎች አሳባችንን በግልጥ እንኳ ለመቃወም ባይቻላቸው መሞከራቸው አልቀረም ነበር። ይኸውም በልማድ ከመሸነፍ የተነሣ ነበር እንጂ ነገሩን እስከ ሥሩ መርምረውና ዐውቀውት አልነበረም። ቢሆንም ይህ አሳብ የተፈጸመ እንደ ሆነ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ክብር የሚሰጣት መሆኑን በቀን ብዛት ስለ አስረዳናቸው የቀድሞ አሳባቸውን እየለወጡ የኛን አሳብ መቀበላቸውን እያረጋገጡ አስታወቁ።

ከዚህም በኋላ መምህር ደስታ ፡ መምህር ኃይለ ማርያም ፡ መምህር ወልደ ኪዳን ፡ መምህር ኃይለ ሚካኤል ተመርጠው በግንቦት ወር 1921 ዓመተ ምሕረት ወደ ምድረ ግብጽ እንዲወርዱ አደረግን ።

ፓትረያርኩ አቡነ ዮሐንስም ለኢትዮጵያ ጳጳሳት አለቃ አድርገው የሚሰዷቸውን አቡነ ቄርሎስን ከገዳመ አስቄጥስ መነኩሳት መካከል መርጠው ይጠብቁ ነበርና የኢትዮጵያ መምህራን ካይሮ ሲደርሱ ወዲያው በፍጥነት ግንቦት 25 ቀን አምስቱንም ጳጳሳት አድርገው በአንድነት ሾሟቸው።

ስማቸውንም ፡ መምህር ደስታን አቡነ አብርሃም ፣ መምህር ኃይለ ማርያምን አቡነ ሴኤጥሮስ ፣ መምህር ወልደ ኪዳንን አቡነ ይስሐቅ ፣ መምህር ኃይለ ሚካኤልን አቡነ ሚካኤል ፡እያሉ ሰየሚቸው።

አቡነ ጴጥሮስ በሐምሌ ወር በ1928 ዓ. ም. ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ሲሰብኩ ተይዘው በኢጣልያኖች እጅ በሰማዕትነት ያረፉት ጳጳስ ናቸው ። አቡነ ሚካኤልም በጐሬ በጠላት እጅ በሰማዕትነት ተደብድበው ሞተዋል።

ጳጳሳቱ የጵጵስናውን ሹመት ከተሾሙ በኋላ ከሊቀ ጳጳሳቱ ከአቡነ ቄርሎስ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ በኢትዮጵያ ከዚህ ቀድሞ ያልተደረገ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከፍ የሚያደርግ ሥራ መሆኑን ስለ ተረዳነው መሳፍንቱና መኳንንቱ ፡ መምህራኑና ሊቃውንቱ የየአድባራቱም ካህናት በሙሉ እንዲሰበሰቡ አድርገን መድፍ እየተተኰሰ የክብር አቀባበል ተደረገላቸው።

ከዚህም በኋላ በየሀገረ ስብከታቸው እየዞሩ የትምህርት ሥራቸውን እንዲጀምሩ ስለ አሰብን ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው አካፈልናቸው።

ለሊቀ ጳጳሳቱ ለአቡነ ቁርሎስ ሀገረ ስብከት ሸዋ በሙሉ ፡ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለው አውራጃ፣ሐረርና አሩሲ ጭምር።

ለአቡነ አብርሃም ጎጃምና በጌምድር።

ለአቡነ ይስሐቅ ትግሬና ላስታ ፡ ዋግና በዙሪያውም ያለውን አውራጃ ሁሉ።

ለአቡነ ጴጥሮስ የወሎና የየጁ አውራጃ ሁሉ።

ለአቡነ ሚካኤል ከፋ ፡ ኢሉባቦር ፡ ወለጋ የሚባለውና የኢትዮጵያ

ምዕራብ በሙሉ።

ስድስተኛ ጳጳስ ለመሆንም የተመረጡት የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ገብረመንፈስ ቅዱስ ነበሩ። ነገር ግን ከመምህራኑ ጋራ ወደ ምድረ ግብጽ ለመውረድ ሳይመቻቸው ስለ ቀሩ ፡ በኋላ በዕድላቸው ፓትረያርኩ አቡነ ዮሐንስ የሃይማኖት ልጆቻቸውን ለመጐብኘት በ1922 ዓመተ ምሕረት በታኅሣሥ ወር አዲስ አበባ መጥተው ነበርና ወዲያው ለእጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የጳጳስነት ሹመት ሰጥተው ስማቸውንም አቡነ ሳዊሮስ ብለው ስለሰየሚቸው ለርሳቸውም ሀገረ ስብከት የኢትዮጵያን ደቡብ በሙሉ ሰጠናቸው ።

በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በቸርነቱ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ትልልቅ የዕድል ሥራ መሥራቱ በጣም የሚያስደንቅ ነው።

1ኛው ዕድል ፡ ክርስትናን ከተቀበለችበት ካራተኛው መቶ ዓመትጀምሮ እስካሁን አንድ ሺ 600 ዓመት ያህል ተደርጎ የማያውቅ ከመምህራንዋ መካከል ተመርጠው የጳጳስነት ሹመት መሾማቸው ነው።

2ኛው ዕድል፡ፓትረያርኩ አቡነ ዮሐንስ አዲስ አበባ ድረስ መጥተው በቤተ ክርስቲያንዋ ቀድሰው ለሕዝቡ ቡራኬ መስጠታቸው ወዲያውም የደብረ ሊባኖሱን እጨጌ ጳጳስነት መሾማቸው ነው።

# ምዕራፍ 28

## የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስለ መቀዳጀታችን ።

መስከረም 17 ቀን 1909 ዓመተ ምሕረት ንግሥት ዘውዲቱ ሲነግሥ እኔም ለአልጋ ወራሽነቱና ለእንደራሴነቱ ስለ ተመረጥሁ በባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነቴ የመንግሥቱን ሥራ እየሠራሁ 14 ዓመት ከቆየሁ በኋላ ፡ ንግሥት ዘውዲቱ በመጋቢት 24 ቀን 1922 ዓመተ ምሕረት ስለ ዐረፉ ፣ በማግስቱ የንጉሠ ነገሥቱ ዐዋጅ ተነግሮ በዙፋኑ ተቀመጥሁ።

ስለ ዙፋንና ስለ ዘውድ አወራረስ ኢትዮጵያ ከውጭ አገር መንግሥት ጋራ መገናኛ ሳታበጅ ብቻዋን በምትኖርበት ጊዜ ፡ የቆየው ልማድ በታሪክ እንዳነበብነው አንዳንድ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ሲሞት ፡ ሞቱ እንዳይሰማ በጥንቃቄ ቆይቶ ፡ ወራሹን ልጁን በዙፋኑ አስቀምጠው ፡ ዘውዱንም ወዲያው ዕለቱን ይጭኑለታል። የልጁ መንገሥና ዘውድ መጫን በዐዋጅ ከተነገረ በኋላ ሟቹን ንጉሥ በክብር ይቀብሩታል ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ሲሞት ፡ የቤት አዛገናች ማንም ሳይሰማ በስውር ወስደው ይቀብሩና በማግስቱ ወራሹን ልጁን በዙፋኑ አስቀምጠው ፡ሥርዓተ ንግሥ አድርሰው ዘውድ ከጫኑለት በኋላ ፡ ያባቱ መሞትና የልጁ መንገሥ ባንድነት ባዋጅ ይነገራል ።

አሁን ግን ከ12 የውጭ አገር መንግሥታት ጋራ የንግድና የወዳጅነት ውል ተዋውላ በዓለም መንግሥታት ማኅበርም ገብታ የበረታ መገናኛ ስለ አበጀች፣በሥልጣኔ ከፍ ከፍ ያሉት መንግሥታት ለዘውድ በዓላቸው እንደሚያደርጉት ፡ በኢትዮጵያ ሌጋሲዮንና ቆንስላት ያቆሙትን መንግሥታት ለዘውድ በዓላችን መጥራት የሚገባ መሆኑን ፡ የጥሪውንም ደብዳቤ ለመላክና መላክተኞቹ እስቲመጡ ለመጠበቅ ለዘውዱ በዓል የሚያስፈልገውን ለማሰናዳት ረጅም ጊዜ የሚያስፈልግ መሆኑን ስለ ተረዳነው የዘውዱ በዓል እስከ ሰባት ወር እንዲቆይ አደረግን ።

ከዚህም በኋላ ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ላለው ነገሥታትና ፕሬዚዳኖች

የጥሪ ደብዳቤ እየተጻፈ ተላከ ።

ለግርማዊ ጆርጅ 5ኛ የእንግሊዝ ንጉሥ ፣ የህንድ ንጉሠ ነገሥት።

ለግርማዊ ቪክቶር አማኑኤል 3ኛ ፡ የኢጣልያ ንጉሥ ።

ለግርማዊ ሂሮሂቶ ፡የጃፓን ንጉሠ ነገሥት ።

ለግርማዊ አልቤርት 2ኛ ፡ የቤልጅክ ንጉሥ።

ለግርማዊ ጉስታፍ 5ኛ ፡ የስዊድን ንጉሥ።

ለግርማዊት ዊልሔልሚና ፡የሆላንድ ንግሥት ።

ለግርማዊ ፉዓድ 1ኛ ፡ የምስር ንጉሥ።

ለክቡር ሙሴ ዱሜርግ ፡ የፈረንሳይ ሬፒብሊክ ፕሬዚዳን ።

ለክቡር ሚስተር ሑበር ፡ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴት ሬፒብሊክ ፕሬዚዳን።

ለክቡር ማርሻል ሂንደቡርግ የጀርመን ሬፔብሊክ ፕሬዚዳን ።

ለክቡር ሙስጠፋ ካማል ፓሻ፣የቱርክ ሬፔብሊክ ፕሬዚዳን ።

ለክቡር ሙሴ ኩንዱሪዮቲስ የግሪክ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳን ።

ደግሞ የፖሎኝ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ የንግድና የወዳጅነት ውል ለመዋዋል ንግግር ጀምሮ ሳይጨርስ የዘውድ በዓላችን ቀን ስለ ደረሰ ፡ ውሉ ባይፈረምም የወዳጅነት አሳባችንን ተገላልጠናልና ፡ ለዘውድ በዓልም መላክተኛ እንልካለን ብሎ መልካም ፈቃዱን ስለ አሳየን መልክተኛውን በታላቅ ደስታ ለመቀበል ፈቃዳችን መሆኑን ለፕሬዚዳኑ ለሙሴ ሞሴስኪ አስታወቅን።

ይህ የፖሎኝ መንግሥት ያን ጊዜ ያሳየን የወዳጅነት ምልክት ለዘወትር በልባችን ተቀርጾ ይኖራል ። ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳሳረዳነው በቀድሞ ዘመን የዘውድ በዓል የሚደረገው ወራሹ ልጅ በዙፋን ሲቀመጥ ዕለቱን ስለ ነበረ በያውራጃው ያሉትን መሳፍንትና መኳንንት ለመጥራት ጊዜው አያደርስም ነበር። አሁን ግን የዘውድ በዓላችን እስከ ሰባት ወርእንዲቆይ ስለ አደረግን ፤በሙሉ ኢትዮጵያ ያሉት መሳፍንቱና መኳንንቱ ባላባቶችም ሁሉ በየገዳማቱ ያሉ አባቶችና የያድባራቱ አለቆች መጥተው የደስታችን ተካፋዮች እንዲሆኑ የጥሪ ደብዳቤ ተላከላቸው። ምንም እንኳ ዛሬ የኢጣልያ ቅኘኙ አገር ቢሆን የኢትዮጵያ ነገሥታት የገደሙት ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ በትልቅነቱ ታውቆና ተከብሮ የሚኖረው የደብረ ቢዘን መምህር አባ ዓምደ ማርያም እንዲመጡ ተጻፈላቸው።

ወደ ፊትም ያለው ወራቱ ክረምት ስለ ነበረ ፡ ለመንገዳቸው እየተዘጋጁ ቆይተው የክረምቱ ወራት ሲያልፍ በመስከረም ወር መጨረሻ እየተነሡ እስከ ጥቅምት 20 ቀን አዲስ አበባ እንዲገቡ ትእዛዝ አለፈላቸው።

ይህም የጥሪው ቃል ለውጭ አገር መንግሥታትና ላገር ውስጥ ታላላቆች ከተላከ በኋላ ፡ የአዲስ አበባ ትልልቁ መንገድና በየመንገዱም ዳር ያሉት ቤቶች እንዲታዶሱ ፡ በየትልልቁ መንገድ ዳርና እንግዶቹ ሲመጡ በሚያርፉባቸው ቤቶች ሁሉ የኤሌክትሪክ መብራት እንዲበራ የሚያስፈልገው ሁሉ ተደረገ።

ልብሰ መንግሥቱ ፡ ዘውዱና ሉሉ ፡ በትረ መንግሥቱና ሰይፉ ፡ ቀለበቱ ይህንም የመሰለው ሁሉ በተለየ በወርቅና በአልማዝ እየሆነ ተሠራ።

የመሳፍንቱም የቀድሞ የክብር መለዮዋቸው የራስ ወርቅ ብቻ ነበር ። አሁን ግን የራስ ወርቁ በሥራና በአገልግሎት ለተሾሙት ራሶች እንዲሆን አድርገን ለአልጋ ወራሹና የዘር መስፍንነት ላላቸው ፡ በትልቅነቱና በሥራው ማማር ከራስ ወርቅ የበለጠ ፡ ከዘውድ ያነሰ የራስ ሉል ፡ ለሴቶች ቤተ ዘመዶቻችንና ለመሳፍንቱም ሚስቶች እንደማዕርጋቸው ከመሳፍንቱ አነስ አነስ የሚል ጌራ ወርቅ እንዲሠራላቸው አደረግን ።

ለጦር አለቆችም (ደጃዝማቾች) የአንበሳ ጋማ ጠጉር ከወርቅ ጋራ እየተሰባጠረ በከፈይ የተጠለፈ ልብስና ቆብ ተሠራላቸው።

ደግሞ ለዘውድ በዓላችን እየተጠሩና በፈቃዳቸውም ለሚመጡ ለውጭ አገር እንግዶች ፡ ላገር ውስጥ ባላባቶችና ለትልልቆች ሰዎች መታሰቢያ እየሆነ የሚሰጥ የእኔና የግርማዊት እቴጌ መነን መልክ ባንድነት የተሣለበት የወርቅ ሜዳይ በብዙ ተሠራ።

ከዚህም በኋላ ከጥቅምት ስምንት ቀን ጀምሮ እስከ ሃያ ቀን የተጠሩት የውጭ አገሮች መልክተኞች በየተራ ወደ አዲስ አበባ መግባት ጀመሩ።

የመልክተኞቹም ስም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መልክተኛ ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስስተር ፡

የግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ መልክተኛ ልዑል ዱክ ደኡዲኒ፡

የግርማዊ የቤልጅክ ንጉሥ መልክተኛ ክቡር ሙሴ ፔራርድ ፤

የግርማዊ የስዊድን ንጉሥ መልክተኛ ክቡር ባሮን ዳቤልሳ ፡

የግርማዊት የሆላንድ ንግሥት መልክተኛ ክቡር ሙሴ ዮንሐሪ ሔርስ ማድ፣

የግርማዊ የጃፓን ንጉሥ መልክተኛ ክቡር ሙሱ ኤዝቡር

የግርማዊ የግብጽ ንጉሥ መልክተኛ ክቡር ቶፊክ ነሲም ፓሻ ፡

የፈረንሳይ ሬፔብሊክ መንግሥት መልክተኛ ክቡር ማሬሻል ፍራንሼ ደስፔሬ

የአሜሪካ ዩናይትድ እስቴት መልክተኛ ክቡር ሙሴ ዣኮቢ፣

የጀርመን ሬፔብሊክ መንግሥት መልክተኛ ክቡር ባሮን ሾን በልተሐውዘን፡

የግሪክ ሬፔብሊክ መንግሥት መልክተኛ ክቡር ኮንት ፒ ሜታክሳስ ፡

የቱርክ ሬፒብሊክ መንግሥት መልክተኛ ክቡር ሙሂቲን ፓሻ፣

የፖሎኝ ሬፔብሊክ መንግሥት መልክተኛ ክቡር ኮንት ዲዚድ ባዚኪ

እነዚህም እንግዶች ሁሉ እንደ አመጣጣቸው ባደረግንላቸው የክብር አቀባበል ደስ እንዳላቸው ገለጡልን።

ደግሞ የትልቁ ንጉሠ ነገሥት የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት በመናገሻው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ እንዲቆም አድርገን ሥራው ተጨርሶ ነበርና በዘውዱ በዓል ዋዜማ እንዲመረቅ ስለ ተወሰነ ፡ ለዘውድ በዓላችን የመጡት እንግዶች ሁሉ በዚያው እንዲገኙ ሆኖ በታላቅ ክብር ከመጡ በኋላ ለዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት ያቆምንላቸው በሚገባ መሆኑን የሚያስረዳ ቃል በረዥሙ ተናግረን ስንጨርስ ፡ ሐውልቱ የተሸፈነበትን መጋረጃ የመግለጡን ክብር ለልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስስተር ሰጥተን ነበርና እርሳቸው ወደ ሐውልቱ ቀርበው መጋረጃውን ሲገልጡትና ሐውልቱ ሲታይ በኢትዮጵያውያን ልብ የተደረገው ደስታ ይኸን ያህል ነው ተብሎ ሊገመት አይቻልም።

በዚሁም ቀን ወደ ማታ በጅሮንዱ የንጉሠ ነገሥቱን ልብሰ መንግሥትና ዘውዱን ፡ ሉሉን ፡ በትረ መንግሥቱን ፡ ሰይፉን ፡ አልማዝ ቀለበቱን የእቴጌዩቱንም ልብሰ መንግሥትና ዘውድ ፡ የአልማዝ ቀለበት በሠረገላ አግብቶ በታላቅ ሰልፍ ወስዶ በመናገሻው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለሊቀ ጳጳሳቱ አስረከቦ ሌሊቱን ሙሉ ሲጸለይበት አደረ ።

እኛና እቴጌ ፡ ቤተ ዘመዶቻችንም መሳፍንቱና መኳንንቱ ከሌሊቱ በ6 ሰዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔድን።

የውጭ አገር እንግዶቻችን ግን ከጧቱ በ1 ሰዓት እንዲመጡ ተደርጎ ነበርና በዙፋኑ ቀኝና ግራ በተዘጋጀው ወንበር እንደ ማዕርጋቸው ተቀመጡ። የወንበሩም አቀማመጥ የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት በእንግዶቹ መካከል እየተሰባጠሩ ነበር።

ሥርዓተ ንግሥ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስ ገበታው የወርቅ የሆነ ወንጌል ይዘው ቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የመሐላ ቃል እንድንፈጽም ጠየቁን ።


«1ኛ ፡ ከቅዱሳን ነገሥታት ከአብርሃና ከአጽብሓ ጀምሮ በኢትዮጵያ ጸንቶ የኖረውን የኦርቶዶክስን ሃይማኖት አጽንተን ለመኖርና የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የወሰነችውን ሕግና ሥርዓት ሳናፈርስ እንድንጠብቅ ።

2ኛ፣ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በኢትዮጵያ ያለውን ሕዝብ በሥልጣናችንና በኃይላችን በምንሠራው ሥራ ሁሉ በርኅራኄና በትዕግሥት እንደ ሕጉ ለጥቅሙ እንድናስብለት ።

3ኛ ፡ ፈቅደን በምክር ቤት አስመክረን ያቆምነውን ሕግ ጠብቀን ለመኖር ፡ የኢትዮጵያን ግዛቱንም ሕዝቡንም ሁሉ እንደሚቆመው ሕግና እንደይ ምክር ቤቱ ሥርዓት አድርገን እንድንጠብቅ።

4ኛ ፡ በኢትዮጵያ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ትምህርት የሚስፋፋበትን ወንጌል የሚሰበክበትን የትምህርት ቤት አቁመን በቸርነታችንና በሥልጣናችን እንድንረዳ» ነው።





ከልዑላን ልጆቻችን ጋር

ይህንም ከዚህ በላይ የተጻፈውን ለመፈጸም ፈቃዳችን ለመሆኑ የመሐላውን ሥርዓት ከፈጸምን በኋላ በዚሁ ላይ ፊርማችንን ፈረምንበት።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ የሥርዓተ ንግሥን ሥራ ለስድስቱ ጳጳሳት አካፍለው ሰጥተው ጸሎቱ ተጀመረ። ከነዚሁ 5ቱ ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን ናቸው። ስድስተኛው ግን የእስክንድርያው ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ የዘውድ በዓላችንን ደስታቿ ለመካፈልና ቡራኬያቸውንም ለመስጠት ከምድረ ግብጽ ልከዋቸው የመጡት ጳጳስ አቡነ ዮሳብ ናቸው።

ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ የንባብና የጸሎት ሥራቸውን እየሠሩ መዘምራኑ እየዘመሩ ሥርዓቱን ከፈጸሙ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ቀርበው ቅብዐ መንግሥት ቀብተው የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ ጫኑልን። በዚህም ጊዜ አልጋ ወራሻችን ልዑል አስፋ ወሰን የራስ ሉሉን ከራሱ አውርዶ በፊታችን በተንበረከከ ጊዜ፡ ሊቀ ጳጳሳቱ ወንጌል ይዘው ቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በመሐላ እንዲናገር ጠየቁት።

1ኛ. አባቴን በፍጹም ልቡ እንዲያከብርና ታዛዥ እንዲሆን ።

2ኛ. በፈቃዳችን ያልሰጠነውን ከክፉ ሰዎች ጋራ በመተባበር እንዳይሻ።

3ኛ. ፈቅደንና በምክር ቤት አስመክረን ያቆምነውን ሕግ እንዲጠብቅ ነው። ይህንንም ለመፈጸም ከማለ በኋላ ፊርማውን ፈረመበት።

ከዚህም በኋላ የእቴጌዪቱ ሥርዓተ ንግሥ ተጀመረ። የእቴጌዪቱ አነጋገሥ የቀድሞና የዛሬው በጣም ልዩ ነው። የቀድሞውን በታሪክ እንዳነበብነው ፡ እቴጌዪቱ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋራ የገዥነት ተካፋይ አይደለችም ተብሎ ቅብዐ መንግሥት አትቀባም። ዘውዱም ለምልክት ያህል በጣም ትንሽ ነበር። ዘውዱንም የሚጭንላት ንጉሠ ነገሥቱ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ነው እንጂ በቤተ ክርስቲያን አልነበረም። ያውም በሦስተኛው ቀን ነው እንጂ ከንጉሥ ጋራ ባንድ ቀን ዘውድ እንድትጭን አይፈቀድላትም ነበር። አሁን ግን ከቅብዐ መንግሥቱ በቀር ዘውዱን ሊቀ ጳጳሳቱ እንዲጭኑላት ፡ የአልማዝ ቀለበቱንም በጣቷ እንዲያደርጉላት ፡ ቀኑም በዚሁ ንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ በሚጭንበት ቀን ባንድነት እንዲሆን ነገሩ በምክር ተጨርሶ ነበርና እንደዚሁ ተደርጎ ተፈጸመ።

# ምዕራፍ 29

## ሕገ መንግሥት ስለ ማቆማችን ።

በቀድሞ ዘመን በአውሮጳም በእስያም በአፍሪቃም ቢሆን ፣ ነገሥታቱ ሕዝቡን እንደፈቃዳቸው በሚገዙበት ጊዜ በነገሥታቱና በሕዝቡ ፡ በነገሥታቱም ቤተ ዘመዶች መካከል ብዙ ሁከትና መለያየት ነበር። ይህንንም የብዙ አገሮች አስተዳደር ታሪክ ያስረዳል ።

ባገራችን በኢትዮጵያም እንደዚህ ሲደረግ ይኖር ነበር። ስለዚህ ለአገዛዛችን ሕግ እንዲኖረው ለወራሾቻችንም በሕግ የተመሠረተ አገዛዝ ለማቆየት ፡ ሕዝባችንም የመንግሥቱን ሥራ ተካፋይ ሆኖ እንዲከታተል ለማድረግ አስበን ፣ገና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነን ሳለን ሕገ መንግሥት ቢቆም ለመንግሥቱም ለሕዝቡም ትልቅ ጥቅም የሚያመጣ መሆኑን ለንግሥት ዘውዲቱ አስታውቀን ነበር። ነገር ግን ያለሕገ መንግሥት አገርን መግዛት ጥቅማቸው የሆነ አንዳንድ ትልልቆች መኳንንቶች ፡ ሕገ መንግሥት የቆመ እንደ ሆነ የንግሥት ዘውዲቱን ማዕርግና ሥልጣን የሚያጐድል እያስመሰሉ ስለ ተናገሩ በዚህ ምክንያት አሳባችን ሳይፈጸም ቆየ።

በዚያ ጊዜ ምንም እንኳ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ብንሆን ፡በመካከሉ የሚያስቸግር ነገር ነበረበት። ትልልቁን ጉዳይ ሁሉ ከመፈጸሙ አስቀድሞ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ አስታውቃቸው ነበር። ጉዳዩንም እርሳቸው የሚቀበሉት ሲሆን በቶሎ እንዲፈጸም አደርጋለሁ ። የማይቀበሉት ሲሆን ግን እየመላለስሁ ከማስረዳት በቀር ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ነኝ ብዬ በኃይል ለመሥራትና እርሳቸውን ለማሳዘን አልፈቅድም ነበር። ምክንያቱም በዚህ የተነሣ ባገር ውስጥ ሁከት እንዳይሆንና የሰው ደም እንዳይፈስስ መጠንቀቅ የሚያስፈልግ ስለ ነበረ ነው። ስለዚህ ሕገ መንግሥት ማቆሙን በትዕግሥት አቆየሁት። ነገር ግን ንግሥት ዘውዲቱ በመጋቢት 24 ቀን 1922 ዓመተ ምሕረት ካረፉ በኋላ ዘውዱንና‹. ዙፋኑን በሚገባ በሕግ ስለ ወረስን ፡ ቀድሞ በእንደራሴነት ሳለን አስበነው የነበረውን ሕገ መንግሥትን ለማቆም ቆረጥን። ስለዚህ የልዩ ልዩ አገሮችን ሕገ መንግሥት መርምረን ፣ የውጭ አገር ልማድና ትምህርት ያላቸውን ፡ካገሩም ውስጥ ያውራጃውን ልማድና የቀድሞውን ታሪክ የሚያውቁ ሰዎች መርጠን ፣ከዚሁ ከውጭ አገሮች ሕገ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚስማማው ተመርጦ እየተዋጣ እንዲቀርብልን አዘዝን።

ተጽፎም ቀርቦ እኛ ከመረመርነው በኋላ ከመሳፍንቱ ወገን ፡ ራስ ካሣ ኃይሉ ፡ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ፡ ራስ ሥዩም መንገሻ ፡ራስ ጉግሣ አርአያ ፡ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ፡ ከሚኒስትሮችም ወገን የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል ፡ ያገር ግዛት ሚኒስትሩ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጐሹ ፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፡ የጽሕፈት ሚኒስትሩ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ታሪኩ ፡ ከመኳንንት ወገን ደጃዝማች ይገዙ በሀብቴ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ባንድነት እንዲመረምሩትና ለመፈረም የተዘጋጀ አድርገው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጠን ።

እነዚህም ነገሩን መርምረው ለመፈረም የተዘጋጀ አድርገው እንዲያቀርቡ የታዘዙት ሰዎች ፡ በአሳብ ሳይጋጠሙ ስለ ቀሩ ብዙ ጊዜ በእኛ ፊት ሲከራከሩበት ቆይተው ነበር። ከመሳፍንቱ ራስ እምሩ ብቻ አሳቡን ከሜኒስትሮችና ከመኳንንቱ ጋራ አድርጎ ነበር እንጂ የቀሩት አራቱ መሳፍንት በአሳብ አንድሆነው ነበር።

የመሳፍንቱ አሳብ ኢትዮጵያ በየትልልቁ አውራጃ ተከፍሎ ፡ ለመሳፍንቱ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት እየሆነ እንዲሰጥ ፡ በንጉሡ ነገሥቱና በመንግሥቱ ላይ ትልቅ የወንጀል ሥራ ሠርተው ካልተመሰከረባቸው በቀር ዘራቸው እንዳይነቀል ፡ በየውስጣቸውም ያለው የያውራጃው ባላባት የያዘው ግዛት ርስት ሆኖለት ለመሳፍንቱ እየገበረና እየታዘዘ እንዲኖር ነበር ። በጠቅላላም የፊዎዳል መንግሥት ማለት ነው።

የሚኒስትሮችና የመኳንንቱ አሳብ ግን «ኢትዮጵያ በየትልልቁ አውራጃ ተከፍሎ ለመሳፍንትና ለባላባቶች ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት ሆኖ ከተሰጠና ሹመት በዘር ይሁን ከተባለ ወደ ፊት የሚነሣው ትውልድ እንደምን ሊሆን ነው?። ቢማርስ ቢያገለግልስ ሹመትና ግዛት ካላገኘ ኢትዮጵያ አገሬ ናት ለማለት እንደምን ይችላል ?። ስለዚህ አሁን ያሉት መሳፍንትና ባላባቶች ጥፋት ካልተገኘባቸው ባገረ ገዥነት ብቻ ይቆዩ ፣ ጥፋት ተገኝቶባቸው ቢሻሩ ወይም ቢሞቱ ግን በግዛታቸው ዕውቀትና ችሎታ ያለው ማንም ኢትዮጵያዊ እንዲሾምበት ይሁን እንጂ ለዘር ማለፉ የሚገባ ነገር አይደለም። ዳሩ ግን ልጆቻቸው በዕውቀትና ባገልግሎት እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሆነው ቢገኙ ንጉሠ ነገሥቱ እንዳወቀ በአባቶቻቸው ግዛተ ወይም በሌላ ማዕርግ ስፍራ ይሹማቸው እንጂ ግዛታቸው ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት መሆኑ በሕገ መንግሥት ሲጻፍ አይታየንም» የሚል ነበር።

መሳፍንቱም ይህን ያቀረቡትን አሳብ ሚኒስትሮችና መኳንንቱ እንዳልተቀበሉዋቸው ባዩ ጊዜ ፡ ይህም ካልሆነ ከዚያው ከግዛታችን ከብዙ አውራጆች ውስጥ አንዳንዱ አውራጃ ብቻ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ነው ተብሎ በሕገ መንግሥት ይጻጸፍልን የሚል አሳብ አቀረቡ። ሚኒስትሮችና መኳንንቱ ግን ይህንም አሳብ አንቀበልም ብለው በፊተኛው አሳባቸው ጸኑ።

እኛም ለዚህ ሥራ የመረጥናቸው ሰዎች በአሳብ መለያየታቸውን በሰማን ጊዜ ሁለቱም ወገኖች አሳባቸውን ከነማስረጃው በጽሕፈት እንዲያቀርቡ አድርገን ከመረመርነው በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለመሳፍንቱም ቢሆን ፣ ለሌሎችም የመንግሥት አገልጋዮች ቢሆን ፣ ርስትና ጉልት ለመትከል ይችላል ፡ የሚል አንድ ክፍል በሕገ መንግሥቱ ይጻፍና ወደ ፊት አገልግሎታቸው እየታየ እንደሚያስፈልግ ይደረጋል እንጂ ፣ የፊዎዳል መንግሥት በዓለም ላይ መቅረቱን እያወቅን አሁን እንደ ገና ያንኑ አጽንተን በሕገ መንግሥት መጻፍ ወይም ያለ ሕገ መንግሥት መግዛት የማይገባ መሆኑን ለመሳፍንቱ አስረድተን ተጣርቶ ተጽፎ እንዲፈረም ይሁን በማለት ነገሩን ቆረጥን።

ከዚህም በኋላ መሳፍንትና ሚኒስትሮች ፣ የጦር አለቆችና አገረ ገዥዎች ሹማምንትና ጳጳሳት ሊቃውንትም ሁሉ በታላቅ ክብር እንዲሰበሰቡ አድርገን ለመፈረም የተዘጋጀው ሕገ መንግሥት ተነበበላቸውና ሁሉም ባንድ ቃል ወደነዋል ፣ይቁም የሚል አሳባቸውን ተናገሩ።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሦስት ሺ. ዘመን ያህል የተለመደው አገዛዝ ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ በሥልጣኑ እያዘዘ እንጂ የምክር ቤት አቁሞ በሕገ መንግሥት የገዛ ንጉሥ አልነበረምና ፡ በተለየ ወዳጆቻችን የሆኑ አንዳንድ ሰዎች ነገሩ ስላልገባቸው ፡ እንዴት በገዛ እጅዎ የመንግሥትዎን ሥልጣን ለሕዝብ ይለቃሉ ፡ እባክዎ እንዲቀር ያድር፣ በቅንነት ይመክሩኝ ነበርና እንደተቻለ መጠን ነገሩን እያስረዳኋቸው ነገሩን ተቀበሉት። ሕገ መንግሥቱም የሚፈረመውና ዐዋጅ የሚነገረው በሐምሌ 9 1923 ዓመተ ምሕረት እንዲሆን ስለ ተወሰነ ፣ ለየትልልቁ መኳንንት ጸሐፊ ትእዛዛችን ፣ ለውጭ አገር ዲፕሎማቲኮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን እንዲያስታውቁ ትእዛዝ ሰጠን ።

ከቀኑም 4 ሰዓት ሲሆን የውጭ አገር ዲፕሎማቲኮች በታላቅ ክብር መጥተው እንደ ማዕርጋቸው በየወንበራቸው አጠገብ በቆሙ ጊዜ ፡ ሕገመንግሥት ለማቆም ያሰብንበትን ምክንያት ለማስረዳት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናገርን።

«እኛ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ ከእግዚአብሔር ለተቀበልነው አደራና ለዚህ ለታላቁ ለንጉሠ ነገሥትነት ማዕርግ ላበቃን አምላካችን በአንደበት ብቻ ማመስገን ለራሳችን ጥቅም በሚሆንና በቀላል አደራረግ መደለል አይበቃንም በማለት ለዘለቄታ ቀዋሚ ፣ ለትውልድ ተሻጋሪ ፣ ለሰው ሁሉ የሚደርስ ጠቀሜታ የሚሆን ሕግ አቁመን ብንሠራ ምንም የአምላካችንን ወረታ ለመመለስ የበቃ ባይሆን ፣ እኛ ጀምረን መጨረሱን ለእግዚአብሔር እንድንሰጠው ማሰባችንን ልንገልጥላችሁ ስለ ወደድን በአሁን ሰዓት በዚህ በታላቅ ጉባኤ ሰበሰብናችሁ።

ሕግ ለሰው ሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም ።

መከበርም መጠቀምም የሚገኙት ከሕግ መተካከል የተነሣ ነው። መዋረድም መጐዳትም የሚመጡት ከሕግ መጓደል የተነሣ ነው። ግፍና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው።

እግዚአብሔር ከፍጥረት ሁሉ በላይ ሆኖ ፣ በቃሉ ብቻ ማዘዝ የማይቸግረው ሲሆን ፡ ሕግን መሥራቱ ሕግ ለዓለም ሁሉ የበላይ ገዥ እንዲሆን ስለዐወቀ ነው።

ከሰውም ትክክለኛ ለመባል የሚገባው በማናቸውም ረገድ ቢሆን ዋናውን አሳብ አዝልቆ ሲሆን ሰውን ሁሉ በሙሉ ፣ ሳይሆንም የሚበዛውን ለመጥቀም በተሰጠው ዕውቀት የሚጣጣርና የሚችል ሲሆን ነው።

አሳባችን ምንም በአንዳንድ ምክንያት ሳይፈጸም ቢቆይ ከብዙ ዘመን በፊት የጀመርነው ድካማችን ሁሉ ለመንግሥቱ ሕግእንዲቆምለት ነበርና ስለዚህ ለኢትዮጵያና ለተወደደው ሕዝባችን የምናስብለት በጽኑም የምንከተለው አሳባችን አሁን የምንገልጽላችሁ መጀመሪያ ሕግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መስጠታችንን ሁለተኛም ይህንኑ ሕግ አጠንክሮ ለመከተልና ለመጠበቅ መፍቀዳችንን ነው።

በዚህም ለኢትዮጵያ ሕዝብ በምንሰጠው ሕግ ውስጥ የሚዘረዘሩት ዋና ዋናዎቹ አሳቦች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. ኢትዮጵያ ወገን ያልተለያየባት አንድ ቤተሰብ ሆና ፣ ሕዝቡ ባንድ ሕግ ተወስኖ ፣ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ተገዝቶ በመተባበር እንዲኖር ይኸውም የመተባበር ኃይል ለዘለቃ በሚያስተሳስር ጥቅም ተጠብቆ እንዲኖር ለሰውም የግል ጥቅሙ ሳይቀርበት የመተባበር ኃይል እንዲመዘንና የበለጠ እንዲሆን ለማድረግ ነው። ይኸውም ለያንዳንዱ ለየራሱ የሚሆነው መጠቀም ሳይቀርበት የተለያየ ግለኝነት ፈላጊ እንዳይሆን ለማድረግ ነው።

2ኛ. የሕግ ጠቃሚነቱ ወይም ቀጭነቱ ለማንም ቢሆን የማያዳላ ትክክል እንዲሆን ለማድረግ ነው።

3ኛ. ባለፉት ዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌሎች አገር ተለይቶ በመኖሩ ታላቁ የዛሬው ሥልጣኔ የሚሰጠውን ጥቅም ለማግኘት ሳይችል በመቆየቱና የወትሮውን ሥልጣኔ በመከተሉ ምክንያት የኢትዮጵያ ነገሥታት ለሕዝቡ እንደ መልካም አባት ሆነው የማስተዳደር ሥራቸውን እየሠሩ ይኖሩ ነበር።
አሁን ግን ሕዝባችን በማናቸውም ረገድ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ እጅግ እየገፋ ስለሔደ የቀድሞ ነገሥታት ብቻቸውን ይደክሙበት የነበረውን ከባድ የሆነ የመንግሥቱን ሥራ ለማከናወን ፡ ሕዝቡ ከድካማችን እንዲካፈል ለማድረግ ሕገ መንግሥት ለማቆም ጊዜው ፈቀደልን ።
የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ዘመን ተባብሮ የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ እንዲሠራ የሚያስፈልግ ነው። ስለዚህ በዚሁ አሳብ የሚገባቸው ሰዎች ሁሉ ለሥራው ተካፋይ ለመሆን እንዲችሉ ሁለት የምክር ቤቶች አቁመናል።
በነዚሁም የምክር ቤቶች የሚመከሩ አማካሪዎች ፣ ሕዝቡ ተምሮና ዐውቆ ለመምረጥ እስኪችል ድረስ በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከያውራጃው እየተመረጡ ይመጣሉ። ምክሩም የሚቆረጠው በቃል ብዛት እየሆነ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወዶ ሲቀበለው የጸና ይሆናል።

4ኛ. በምክር ቤቱ የተመከረውንና ንጉሠ ነገሥቱ ወዶ የተቀበለውን ሚኒስትሮች በሙሉ ኢትዮጵያ እያከናወኑ አላፊም እየሆኑ የመንግሥቱንና የሕዝቡን ጉዳይ እንዲያስፈጽሙ ተደርጓል ።

5ኛ. ሁከት እንዳይነሣና ለኢትዮጵያ ጉዳት እንዳያመጣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መቸውንም ቢሆን በዚህ ሕገ መንግሥት ከተጻፈለት ትውልድ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኗል።

6ኛ. ሕግ ማስፈለጉ ማንኛውም የትዳር አኳኋን ተሻሽሎ በተደላደለና በታመነ መሠረት እንዲሆን ነውና ፣ ሁሉንም አሻሽሎ የሚያደላድል ዕውቀት ነው። የኢትዮጵያም አስተዳደር በማናቸውም ረገድ ወደ

ዕውቀት የተመራ እንዲሆን ፣ ዕውቀትን ሁሉ በያይነቱ እያማረጡ መቀበል መቻውንም የምንፈልገው እንዲሆን ለማድረግ ነው።

7ኛ. ይኸውም ያቆምነው ሕገ መንግሥት ልብ ወለድና ከአገርም ልማድ የተፋለሰ ሳይሆን ከሠለጠኑት መንግሥታት ሕዝቦች ትምህርት ጋራ የተያያዘና የተቃረበ ስለ ሆነ ከመሳፍንቶቻችንና ከመኳንንቶቻችን ከሌሎችም ዕውቀት ካላቸው ከኢትዮጵያ ተወላጆች መርጠን በአሳብ እየረዱን የተዘጋጀ ነው።

ሰው ይጀምራል እንጂ የመጨረስ ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻነውና ይህንን ያቆምነውን ሕገ መንግሥት ለመፈጸም እንዲያበቃን እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ እናደርገዋለን ።

እናንተም ከቡራን የውጭ አገር ሚኒስትሮችና ቆንሲሎች ፣ ሕገ መንግሥት ያቆምንበትንና የፈረምንበትን ይህን ዕድለኛውን ቀን ከኛ ጋራ ለማክበርና ደስታችንን ለመካፈል ስለ መጣችሁ እናመሰግናችኋለን ። »

ይህንም ተናግረን ስንጨርስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ያዋጁን ቃል ጸሐፊ ትእዛዛችን አነበበ።

«በእግዚአብሔር ቸርነት ፣ በሕዝብ ኅብረት ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ተመርጠን ዘውዱንና ዙፋኑን በሕግ አገባብ ተቀብለን ስንቀባ ፣ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን አደራ እኛም በሕግ ሠርተን ጠብቀን ፡ ተከታያችንም በሕግ እንዲቀበለንና በደንብ እንዲሠራ ፡ ለሀገራችንም በመልካም አስተዳደር በሕግ የሚጠብቅበትን ደንብ እንዲያቆም አድርገን ለኢትዮጵያ ልማትለመንግሥታችን ጽናትለምንወደው ሕዝባችንም ጥቅምና ሀብት ሆኖ ደስ እንዲያሰኝ ተስፋ ስለ አደረግን አሳባችንን ገልጠንና አስረድተን የመንግሥት ሕግ እንዲቆም መረጥን።

የመንግሥት ሕግ አቋቋም የሚያስረዳው የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ፊት የሚጸናበት መሠረት ፡ መሠረቱም የሚቆምበት ሕጉ ፡ ሕጉም የሚፈጸምበት ኃይሉ እንደምን እንደሚወሰን ታውቆ ፡ የመንግሥታችን አቋቋም ለዘለዓለም ቀዋሚና ጽኑ ሆኖ እንዲኖር የታመነ መጠበቂያ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው።

ስለዚሁም ሁሉ ነገር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ከተቀመጥን ጀምሮ ከእግዚአብሔር እጅ ታላቅ የሆነ አደራ ስለ ተቀበልን መንግሥታችን የሚጸናበትን የሕዝባችን ኑሮ የሚሻሻልበትንና ሕዝባችን ወደ ታላቅ የሥልጣኔና የደስታ መንገድ ተመርቶ ነፃ የሆኑና የሠለጠኑ ሕዝቦች ያገኙትን መልካም ነገር ሁሉ የሚያገኝበትን ማወጅና ማሠራት የሚገባ መሆኑን አስተውለን ።

ይህንም ለማድረግ የሚያስፈልገው ፍሬ ነገሩ ወደ ፊት ያለውን የመንግሥት ሕግ አቋቋም አጣርተን የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ እንዲከናወን ፡ የሕዝቡም የደስታ ኑሮ እንዲረጋገጥ ፡ ለልጅ ልጅም የሚያልፍ ክብር እንዲገኝበት ፡ መንግሥቱም በሰላምና በጸጥታ እንዲኖር ማድረግ መሆኑን አስተውለን።

ይህም እጅግ ከፍ ያለው አሳባችን መንግሥታችንን ከታላቁ ታሪክ ከፍተኛ ማዕርግ ለማድረስ ስለ ሆነ በንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ተቀምጠን በነገሥንበት በሁለተኛው ዓመት በ1923 ዓመተ ምሕረት ማንም ሳይጠይቀን በፈቃዳችን ይኸንን የመንግሥት ሕግ በዐዋጅ አቁመናል»።

ከዚህ ቀጥሎ በጽሕፈት የተዘጋጀው ሕገ መንግሥት ቀርቦና በመጀመሪያ እኛ ከፈረምንበት በኋላ ፣ ከአልጋ ወራሻችን ጀምሮ ፡ ጳጳሳቱና መሳፍንቱ፣ሚኒስትሮቹና ባላባቶቹ መኳንንቱም ሁሉ ፈረሙበት። የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ መልክተኞችም ለመታሰቢያ በተለይ በተሰናዳው ደብተር ላይ ስማቸውን እየጻፉ ለመታሰቢያ ፈረሙ።

# ምዕራፍ 30

## የሕገ መንግሥትን ትርጓሜ ስለ ማስረዳት ።

ከመኳንንቱና ከሕዝቡም ወገን ሕገ መንግሥት ማለት ምን እንደሆነ የሚያውቁት ጥቂቶች ነበሩና ሁሉም እንዲያውቁት አስፈላጊ መሆኑን ስለ ተመለከትን ሕገ መንግሥቱ በተፈረመበት ሰሞን መኳንንቱ በሙሉ፡ ከሕዝቡም ወገን ብዙዎች እንዲሰበሰቡ አድርገን የገንዘብ ሚኒስትራችን በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በስብከት እያስረዳ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ነገራቸው ።

## «ጃንሆይ ።

ዘንድሮ በኢትዮጵያ የተፈጸመው አሳብና የተወጠነው እቅድ በዓለም ላይ በማናቸውም አገር በማናቸውም ጊዜ ተደርጎ የማያውቅ ነው ።

ኢትዮጵያ በሁለትና በሦስት መቶ ዓመት የማትራመደውን ደረጃ ግርማዊነትዎ ባንድ ጊዜ አገሥግሠው ከፍ አድርገው ለታላቅ ማዕርግ አበቋት።

እስከ ዛሬ ድረስ ለያንዳንዳችን የሚያደርጉልን የችሮታዎ ብዛት ያስደንቀን ነበር። የዛሬው ግን ማንንም ሳይለይ ለሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድ ጊዜ የሚደርስ ነውና በእውነት ያስገርማል ።

ይህም በእኛ ዘመን በመፈጸሙና ለማየትም ለመስማትም ስለ አበቃን ዕድላችን በመልካም መታሰቡ አይቀርም። ስለዚህ እንኳንስ ለግርማዊነትዎ ለእኛም ቢሆን ጊዜያችን የሚያስመሰግን መሆኑ አይጠረጠርም። ወደፊትም የሚመጣውን ትውልዳችንን የሚያስከብር ነው።

መጠቅለያውን ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ ለመኖሪያዋ የሚያበቃትን የሕይወት ምንጭ አግኝታለችና ኃይልዋእየተጋነነ ፤እንደ ፀሐይ ለዘለዓለም እያበራች የማያቋርጥ ብርሃን ልትሰጥ ትችላለች። ስለዚህ ጃንሆይ ለኢትዮጵያ በድንገት ማንም ሳያስበው በፈቃድዎና በችሮታዎ ብቻ አስተዋይነትዎና ተመራማሪነትዎ ቅን ልቡናዎና ግልጽ አእምሮዎ እየመሩዎ ባደረጉላት ውለታ በዓለም ላይ ምሳሌ የማይገኝለት በመሆኑ ፡ የዓለም ተመራማሪዎች ሁሉ አሁንምያሉት ወደ ፊትም የሚነሡት በጣም መደነቃቸው የማይቀር ነው። ለታሪክዎም ከደጎቹ ከብልሆቹ ነገሥታት በላይ አድርጎ የሚያስፈርድልዎ ነው።

ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ከታወቀች ከሦስት ሺ ዘመን ይበልጣል ። ከዚያ ጀምሮ እስከ ዛሬ እጆቸዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ አንዳች ታላቅ ችሮታ በትዕግሥት ስትጠብቅ ቆይታ ነበርና ገና ዛሬ የእግዚአብሔርን ቡራኬ በግርማዊነትዎ እጅ ለመታደል አደረሳት ።

ፈጣሪ መኖሩንና የበላይ ገዥነቱን የሚያሳምነን ዓለምን በሙሉ በማይፈርስና በጽኑ ሕግ ለዘላለም ወስኖ በመፍጠሩ ነው።

የሰው ታላቅነቱ በልዩ የሚታወቀው የፈጣሪውን ሕግ እየተመራመረ በመግለጹና ያንኑ በመከተሉ ነው። ስለዚህም ራሱን ያስከብራል። ወገኖቹንም ይጠቅማል። ለኢትዮጵያ የሚበቃ ውለታ ለመሥራት ሕገ መንግሥት ከማቆም የበለጠ ሌላ ምንም ሊደረግ አይቻልም። ጃንሆይም መጀመሪያ በራስዎ ፈቃድ ለመንግሥትዎ አቋቋም መሠረት መትከልዎ ፡ ለሕዝብም አገዛዝ ሕገ መንግሥት መወሰንዎ ለኢትዮጵያ ውለታ ለመሆን የሚበቃ ሌላ የበለጠ ውለታ ምንም እንዳይገኝ ስለ ተረዱት ነው እንጂ በመታለል ወይም በሌላ ምክንያት አለ መሆኑን ማንም አይስተውም።

ይህም አሁን ላለነው ሰዎች ብቻ ሳይታሰብ ለመጭውም ትውልድ ለነፃነቱ መጠበቂያ ታስቦ የተደረገ መሆኑን አውቀነዋልና ምስጋናችን እውነተኛ ነው።

የመንግሥትን መሠረት መትከልና የሕግን ምሰሶ ማቆም ለትውልዳችን መጠቀሚያ የሚያስፈልግ ዋና አሳብ መሆኑን ግርማዊነትዎ ስለ ተረዱት ግን እኛም የኢትዮጵያ ተወላጆች ዜጎችዎ ሁሉ የዚህኑ ግምት አመዛዝነን ለመረዳትና የሥሩልንን ውለታ ለማወቅ ስለ ተቻለን ድካምዎ ሁሉ ከንቱ አይሆንም። ነገር ግን እኛ ዛሬ አብረንም ለምንኖር ሰዎች ለዚህ ላደረጉልን ወሮታ እንደሚበቃ ያህል አድርገን ውለታ መላሽ ለመሆን እናውቅበት ይሆንን ? ወይስ ውለታ አመላለስ እንደ ምን ሲሆን ነው በቂ የሚሆ ነው።

ለዚህ ላቀረብሁት ጥያቄ የሚያስፈልገውን አመላለስ ከመስጠት በፊት ግርማዊነትዎን መጀመሪያ የምለምንዎ በዚህ በታላቅ ጉባኤ ላይ የዚህን የትልቅ አሳብ አተረጓጐም ለኔ ለትንሹ አገልጋይዎ ስለ ፈቀዱልኝ የእውነተኛውን ምስጋናዬን ከዙፋንዎ ሥር ሳቀርብ ፈቃድዎ ሆኖ እንዲቀበሉኝ ነው።

ልዑላን መሳፍንት ፡ክቡራን ባላባቶችና መኳንንት አሁን የምለምናችሁ በሐምሌ 9 ቀን የተነገረውን ዐዋጅ የአሳቡን ትርጉም እንዳስረዳችሁ ፡የአሳቡ ጥልቅነት ምንኛ የረቀቀ መሆኑን እንድታውቁት ፡ በዚህስ መጀመሪያ ተጠቃሚማን እንደ ሆነ ፡ ለጃንሆይ ለታላቁ ውለታ ለመሆን የምንበቃው ምን ብናደርግ እንደ ሆነ እንዳስረዳችሁ ነው።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ለተናገርሁት ነገር ፡ አመላለሱንም ክርክሩንም ለእኔው አደርገዋለሁና እናንተ ብቻ በትዕግሥትና የሽልታ ነገር ብታገኙ ታዘቡኝ። ፍሬ ነገር ብታገኙ ግን የልባችሁ ገንዘብ አድርጉት።

## ስለ ሕገ መንግሥት ነገር ።

ጃንሆይ ከእንግዲህ ወዲህ የንጉሠ ነገሥት መንግሥትዎ አገዛዝ ለመቸውም ቢሆን በሕግ አወሳሰን እንዲሆን ፈቅደው አሳወጁ። ሕገ መንግሥት ማቋቋም ማበጀት ማለት ነው። ከሁለትና ከሦስት ነገሮች አማርጦ አንዱን ብቻ አዋሕዶ እንደ ማቆም ነው። እነሆ ለምሳሌ የግንብ ሕግ ካራት ነገር የተቋቋመ ነው። ከድንጋይ ፡ከኖራ ፡ ከአሸዋ ፡ ከቀጥታ ሚዛን። እንደዚሁም አገር ፡ ሕዝብ ፡ ንጉሥ ፡ ሕግ ፡ ባንድነት ተዋውደው ለመንግሥት አቋቋም መሠረት ይሆናሉና ባንድነት የመዋዋዳቸው አሳብ ሕገ መንግሥት ተብሎ ተሰይሟል። ነገር ግን ለመንግሥት አቋቋም መሠረት የሚሆነውን አሳብ አሳምሮ አጠንክሮ ለመደልደል ብዙዎች ታላላቆች ሰዎች በየጊዜያቸው ለያገራቸው እጅግ ደከመውበት ነበርና በዓለም ታሪክ ላይ ተጽፎ ይገኛል።

እንግዲህ ለዚሁ ለሕገ መንግሥት አቋቋም በዓለም ላይ የተደረገውን የመሠረት አኳኋን ሁሉ በትምህርት የሚሰበከውን በያይነቱ እናመለክታችኋለን

1ኛ. ንጉሥ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ በሀገሩ ምንም የተለየ ልማድ ወይም ደንብ ሳይኖርበት እብሪቱ ብቻ በየቀኑ የመራውን አሳብ እንደ ፈቀደ እንደ ባሕሪው ድንገተኛ መለዋወጥ እየለዋወጠ ያደርጋል። ያለ ፍርድ ይቀጣል ፡ ይገድላል ፡ ይሰቅላል። እንደዚህ የመሰለው መንግሥት ለአረምኔ ይስማማ እንደ ሆነ ነው እንጂ ለክርስቲያን ሕዝብ አይስማማም። የወንጌልም ቃል አይፈቅድለትም። ምሳሌውም ከሜዳ ላይ እንደ ተቆለለ ደንጊያ ውስጡ እንደ ዋሻ ሆኖ ሰው ቢኖርበት በድንገት እየተናደ ሊፈጠፍጠው ይችላል የማለት ያህል ነው። እርሱም የእብሪተኛ መንግሥት ተብሎ ተሰይሟል። የዘውዱም አወራረስ እንደ ጊዜው መመቸት ዓባይ ገነንነት ነውና ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣል ፡ በተለዋወጠም ቀጥር ሕዝቡን በወገን እየለያየ እርስ በርሱ እያፋጀ ዕድሉን ሁልጊዜ ደም ማፋሰስና መተላለቅ ያደርግበታል።

2ኛ. ንጉሥ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ በትክክል ተለይቶ የተጻፈ ሕግ ሳይኖረው ከትውልድ እየተሸጋገረ በቆየው ልማድ ይሠራል። ቅጣትም ምሕረትም ለማድረግ ፡ ለመሾም ለመሻርም ባደባባይ በጉባኤ እያስፈረደ በክብር እየሸለመ ፡ በገሃድ እያሳወጀ ነው። በድንገትም በደል ነገር ቢሠራ ማገጃ አልተደረገበትም። እንደዚህ ያለው መንግሥት አብዛኙ ሕገ መንግሥት ባልተቋቋመላቸው ሕዝቦች

መካከል ሲደረግ ቆይቶ ነበር። ምሳሌውም በጥሬ ካብ እንደ ተሠራ ቤት ነው። እርሱም ትዕግሥት ያለው በልማድ ነዋሪ መንግሥት ተብሎ ተሰይሚል። የዘውዱም አወራረስ ድንገተኛ ጊዜ ለሰጠው ወገን ነው።

3ኛ. ንጉሥ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ሕጉን የሚያሰናዱለት አማካሪዎች በተለይ ተደርገውለት ፡እነርሱም በተለይ ጉባኤ ፡ በተለይ ቀጠር እየተሰበሰቡ ይሠራሉ። ለመምከርምየተፈቀደላቸው ሰዎች ቀነጥራቸው የተወሰነ ሆኖ የሚመረጡትም ከያገሩ ክፍል ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ከሕዝቡም መካከል ነው ፡ የምክሩም ጉባኤ የሚደረገው በሁለትና በሦስት ክፍል የሆነ እንደ ሆነ የምክር ቤቱ እንደ ክፍሉ ተደላድሎ ይለያያል። በውስጡም አማካሪ የሚሆኑት ሰዎች እንደ ወገናቸው ማዕርግ ይመረጣሉ። የምክርቤታቸውም የመሳፍንት ፡ የመኳንንት ፡ የሕዝብ እየተባለ ይለያል። ነገር ግን ከሕዝብ ወገን የሚመረጡት ሰዎች እንደ ደንቡ የሚደረጉት በሕዝቡ መራጭነት ነውና ለተወሰነ ቀጠሮ ብቻ እየመከሩ እየተሻሩ ደግሞ ሌሎች እንደ ገና እየተመረጡና እየተተኩ እንደዚሁ ይሠራሉ። የሁሉም ምክራቸው የሚቆረጠው በቃል ብዛት ሆኖ በጽሕፈት እየተሰናዳ ለንጉሠ እየቀረበለት ንጉሥ ምክሩን የወደደውና የተቀበለው እንደ ሆነ ያጸድቀዋል። ቀጥሎም ያሳውጀዋል። ከዚህም በኋላ ሚኒስትሮቹ እንደ ሕጉ እየታዘዙ ያስፈጽማሉ-። ከሕግ የተላለፈውንም ሰው እያስፈረዱ ያስተጣሉ።

ሕጉን ለማደስ ወይም ጨርሶ ለመለወጥ እንደ ሕጉ ተመክሮበት ይደረጋል። እንደዚህም ያለው መንግሥት ራሱ ተባብሮ በሕግ ተወስኖ ገዥ ተብሎ ተሰይሟል። ያልጋውም አወራረስ ምንም ቢሆን ከዘሩ አይወጣም ።

ለዚሁም በንጉሡና በመሳፍንቱ በመኳንንቱና በሕዝቡ መካከል የመሐላና የውግዘት ቃል አለበትና ጸንቶ ይኖራል። ምሳሌውም በድንጋይና በኖራ በአሸዋም እንደ ተገነባ ቤት ያህል ነው።

4ኛ. ንጉሥ የሌለበት የማኅበር መንግሥት ሆኖ የማኅበሩ አለቃ ለተወሰነ ዘመን በሕዝቡ ፈቃድ የሚሾምበት ነው። እንደዚህ ያለው መንግሥትም በሕዝቡ ሥልጣን ብቻ ተገዝቶ የሚያድር የማኅበር መንግሥት ነው ።

የማኅበሩ አለቃ በተወሰነ ዘመን እየተሻረ ፡ ደግሞ በሕዝቡ ፈቃድ እየተመረጠ ይተካል። በማኅበር መንግሥት የማኅበሩ አለቃ ሚኒስትሮቹም አማካሪዎቹም የሚመረጡት ፈጽሞ በሕዝቡ መራጭነት ነው። ማንኛውም አሳብ የሚፈጸመው ሕዝቡ በቃል ብዛት ወደ ቆረጠበት ወገን ነው። መንግሥቱም የሕዝብ መንግሥት ተብሏል። እንደዚህ ያለው የመንግሥት አኳኋን በጣም ላልተማረና ላልሠለጠነ ሕዝብ የሚፈቀድ አይደለም። ለሠለጠኑትም ሕዝቦችእንኳ ደም እያፋሰሰ በጣም አስቸግሮ ይኖራል ።

ከነዚህ ከተቆጠሩት የመንግሥት አኳኋን ዓይነቶች የተላለፈ ሌላ እንኳ ቢኖርም ለዛሬው ጊዜ ለሰው ኑሮ ከነዚህ የሚሻል አይገኝም።

ለሰውም ምኞት ወሰን የለውምና ፡ ምኞትም ሲበዛ አሳብ ብቻ ሆኖ ይቀራል እንጂ ለኑሮ መጥቀሚያ አይሆንም። ስለዚህ ለሰው ኑሮ ጠቃሚ ለመሆን የሚችሉትን በዓለም ላይ የሚገኙትን የመንግሥት አገዛዝ ዓይነቶች አሳየሁ። እንግዲህ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ አሁን ላለችበት አኳኋን ይጠቅማል ብለው የፈቀዱላት የመንግሥት አገዛዝ ሦስተኛ ደረጃ ነው፤ማለት የኢትዮጵያ መንግሥት ለመቸውም የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሆኖ ንጉሠ ነገሥቱም ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ዋናው የሕግ አወሳሰን በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ እየሆነ ለዝርዝሩ ጉዳይ የሚያስፈልገው ለገ.ዜው በመሳፍንትና በመኳንንት ጉባኤ ላይ እየተመከረበት በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን እየተፈቀደ እንዲጸና ነው። ኋላም ሕዝቡ ሠልጥኖ ለዕውቀት የበቃ ሲሆን ለአማካሪነት የሚፈቀድላቸውን ሰዎች በየወገኑ መምረጥ እንዲፈቀድለት ነው።

እንደዚህም ማለት በዛሬው ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ መሳፍንቱንና ባላባቶቹን መኳንንቱንም ለሕዝቡ ሞግዚት አድርገውለት ወደ ማሻሻል ሊመሩት ነው።

እንግዲህ በጃንሆይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ የተሰጠ ሕገ መንግሥት ባጭሩ እንደዚህ ሆኖ ተወስኗል።

1ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት ለመቸውም የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ነው። ንጉሠ ነገሥቱም ባለሙሉ ሥልጣን ነው ገዢነቱ ግን በሕግ አወሳሰን ነው።

2ኛ. የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ቤቶች ለመቸውም የማይነቀሉ ትክለኞች ሆነው አማካሪዎቹ ብቻ በተለየ ዘመን ከየሀገሩ ክፍል ከመሳፍንቶችና ከባላባቶች ከመኳንንትና ከሕዝብ መካከል የሚመረጡይሆናሉ።

3ኛ. ዋናዎቹ ሕጎች በንጉሠ ነገሥቱ ዕውቀት ተመሥርተው ጸንተው እንዲኖሩ ሆኗል።

4ኛ. ለየዝርዝሩ ጉዳይ የሚሆኑት ሕጎች በምክር ቤቶች ጉባኤ ላይ እየተመረመሩ በቃል ብዛት እየተቆረጡ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን እያጸደቃቸው ይታወጃሉ።

5ኛ. ሚኒስትሮች ለየሥራቸው ክፍል አላፊ ሆነው ሥራቸውን በሙሉ ኢትዮጵያ ያስፈጽማሉ።

6ኛ. በኢትዮጵያ በጦር ኃይል በበላይ ሆኖ በሙሉ የሚያዝበት ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ነው።

7ኛ. ዋና ሥልጣንና ማዕርግ ፡ ሹመትና መብት ፡ ሽልማትና ክብር ፡ ርስትና ጉልት ፡ ትልቅ ማደሪያ ወይም መጧሪያ የሚሰጥ ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ነው።

8ኛ. ጦርነት ወይም ዕርቅ ለማሳወጅ የሚችል ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ነው።

9ኛ. ጥፋተኛ በሕግ ከተፈረደበት በኋላ ቅጣትን ለማቃለል ወይም ፈጽሞ ለመማር የሚችል ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ነው።

እንግዲህ ሕገ መንግሥት የተባለውን የመንግሥት መሠረት አቋቋም በያይነቱ ካስረዳሁ በኋላ ደግሞ ሕግ የተባለውን አሳብ እንዳስረዳ ፈቃዳችሁ ይሁንልኝ። ;

## ስለ ሕግ ፤

ሕግ ማለት በዓለም ላይ ለኑሮ ጸጥታና ሰላም እንዲገኝ በሰዎች መካከል የሚደረገውን ውል ሁሉ የሚወስን የመንግሥት ግዴታ ነው።

ደግሞም ሕግ ማለት ከውሉ የተላለፈውን ሰው ሁሉ አላፊ አድርጎ ፈርዶ አስገዳጅነት ላለው ኃይል አሳልፎ ለቅጣት የሚሰጥ ነው። እንደዚህ እየሆነ ሕግ ለሰው እንዲጠቀምበት የሚፈቅድለትን ለይቶ ወስኖ ያስጠነቅቀዋል። ደግሞም እንዲፈጽም ግዴታ የሚሆንበትን ምግባር እያስጠነቀቀ ያዘዋል። ሰው እንዲጠቀምበት የሚፈቀድለት ነገር ሁሉ የጥቅም መብት ተብሏል። ይኸውም የጥቅም መብት በሁለት ዋና ክፍል ይለያያል ።

1ኛ. የግል ጥቅም ለያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍነት ለየራሱ የሚሆን ነው።

2ኛ. የመተባበር ጥቅም ለሕዝቡ ሁሉ በሙሉ ለኢትዮጵያም ለአንድነትዋ የሚሆን ነው።

የግልም የመተባበርም አሳብ በሦስት ዓይነት ሊሆን ይችላል ።

1ኛ. የትዳር ጥቅም (ሀብት)

2ኛ. የአእምሮ ጥቅም (ዕውቀት)

3ኛ. የልቡና ጥቅም (ፍቅርና ሃይማኖት)

ለነዚህ ለተነገሩት በግልም በመተባበርም ለሚሆኑት ጥቅሞች ሁሉ ለደምሳሹ አሳብ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕግ ሰጥተዋል። ዝርዝር ለሚሆ ነው አሳብ ግን አማካሪዎች በምክር ቤት በጉባኤ እያሰናዱ እንዲያቀርቡላቸው ከላይ እንዳሳየነው የመንግሥት አቋቋም መሠረት ሕገ መንግሥት የተባለውን ተክለዋል ።

እስካሁን ድረስ ሕገ መንግሥት ምን እንደ ሆነ ፡ ደግሞ የሕግ አወሳሰን የሚደረገው እንደ ምን እንደ ሆነ ለማስረዳት ተናገርሁ። እንግዲህ ደግሞ ከላይ ያቀረብኋቸውን ጥያቄዎች እየዘረዘርሁ እናገራለሁ ።

## መረዳዳትንና መተባበርን እንድናውቅ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለእኛ ያደረጉልንን ሌሎችም ነገሥታት ለየሀገራቸው አድርገውታል። ነገር ግን በሌላው አገር እንደዚህ ያለው መሻሻል የተፈጸመው በችሮታ ሳይሆን ደም በመፋሰስና በግዴታ እየሆነ ለሁሉም አደጋ እየተረፋቸው ነበር።

በእኛ አገር ግን የሕዝቡ ዕውቀት ገና ለምንም ሳይበቃ ወደ ፊት የሚሆነውን ጉዳትና ጥቅም በማመዛዘንና በመገመት ዕድላችንን በመልካም አመራር ለማሻሻል ሲሉ ንጉሠ ነገሥታችን በዕውቀታቸውና በፈቃዳቸው ኢትዮጵያ እስካሁን በልማድ ብቻ ከምትኖርበት አኳኋን ተነሥታ ወደ ሥልጣኔ እንድትሸጋገር አደረጉ። ይኸውም እጅግ የሚያስደንቅ መሆኑ ኢትዮጵያ ከነበረችበት አኳኋን ባንድ ጊዜ ስትዛወርና ስትሸጋገር እንደዚህ በሰላምና በጸጥታ ከወገኖቻቸውና ከአገልጋዮቻቸው ጋራ በመስማማት ፡ በመተባበርና በመረዳዳትእየሆነ በደስታ በመፈጸሙ ነው።

ይህ እንደዚህ ያለው አደራረግ ብቻ ኢትዮጵያን ከሠለጠኑት ሕዝቦች ጋራእኩል አድርጎ ሊያስከብራት ይበቃል ።

እኛም እንግዲህ ውለታቸውን ለመመለስ ራሳችን ፈርደን በራሳችን ላይ ግዴታ የምናደርገው በእውነትና በቅንነት ተገኘ እንድንሆን ነው ። ጃንሆይ ወደውና ፈቅደው እንደዚህ የተከበረ አሳብ ሲመሠርቱልን ፡ እኛም ወደንና ፈቅደን ወሮታ መላሽ ካልሆንን የራሳችንን ጥቅም ብቻ ባጉል መንገድ ፈላጊዎች የሆንን እንደ ሆነ ፡ ከሕዝቡም ጋራ የሚያስተባብረንን ጥቅማችንን የናቅን እንደ ሆነ ፡ ባንድ ወገን ንጉሠ ነገሥታችንን ፡ በሌላውም ወገን ሕዝቡን ብዙዎቹን ማስቀየምና በሁሉም ወገን መጠላት ይሆንብናል ።

ሕግ ማለት በሰዎች መካከል በቅድስና ፡ በንጽሕና ተከብሮ ለመኖር የታዘዘ የማይደፈር ጽኑ ኃይል ነውና የተፈለገውም በሰዎች መካከል የሚሆ ነው ጥቅም በሚገባ ተደላድሎ ለመቸም እንዳይፈርስ መጠበቂያ ለመሆን የሰላማዊነት ፍላጎት ነው። ሕጉም ራሱ የሚጠብቀው በቃል ኪዳን በታሠረው ውል በልብ ቅንነቱና በእውነት ፈራጅነቱ ታማኝነት ነው።

ይህ በቃል ኪዳን የታሰረው ውል ሕግ ተብሎ ተሰይሞ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች የሚገናኙበት ፡ በትዳራቸው ሥራ ሁሉ ከመጠን እንዳይተላለፉ ማንኛውንም አኳኋን በልዩ እያስጠነቀቀ የሚወስንላቸውና የሚያስማማቸው ከጠብም የሚገላግላቸው ነው።

ስለዚህ ሕግ ከሁሉ የበለጠ የበላይ ኃይል ሆኖ ሊከበር የተገባ ነውና እኛም የኢትዮጵያ ተወላጆች ሁሉ ወደ ፊት ሕጉን አክብረን ለመኖር ግዴታችንም ውዴታችንም መሆኑን ዐውቀነው ወደን ቃል ኪዳን መግባታችንን ለመቸም እንዳንረሳው አጥብቀን ልንተጋበት ይገባናል ።

ለሰው ሁሉ በሕግ የተፈቀደለትን አኗኗር ለመከልከል ወይም ሁከት ለማድረግ የሚፈልግ ሰው በፈጣሪ ፊት በሕዝብም ጉባኤ ላይ መወቀስ በንጉሥም ፊት እንደ ዓመፀኛ መቀጣት የተገባው ነው። ደግሞም ሰው ሕግ ያዘዘውን ሳይፈጽም ቢቀር ፡ ወይም ሕግ የወሰነውን ተላልፎ ቢገኝ እንደዚሁ በሕግ መቀጣት የተገባው ነው ያሰኛል።

ሕግ በሚፈቅደው አኳኋን ሁሉ ሕዝቡ እንዲጠቀምበት በትጋት ለመጠበቅ በቃል ኪዳን ታስሮ ከውል የገባው ንጉሠ ነገሥቱ ነውና ይህ እንዲከናወንለት እናድርግ።

ደግሞ ሕግ የሚከለክለውን ሁሉ ማንም እንዳይተላለፍ ለማስገደድ በቃል ኪዳን ታስሮ ከውል የገባው ያው ንጉሠ ነገሥቱ ነውና ይህንም ለማከናወን እንዲመቸው እንደተቻለን እንጣጣርለት።





የቄ ልጆች የአርመን ሙዚቀኞች ተብለው የሚጠሩትን ስንቀበኝ ከቀኝ ወደግራ ካሣ ገብሬ ፤ ከንቲባ ወናጋሻው ፤ አቶ
... ልዑል ራስ ካሣ ፤ ፊታውራሪ በቀለ አየለ ፤

የ40 ልጆች የአርመን ሙዚቀኞች ተብለው የሚጠሩትን ስንጐበኝ ከቀኝ ወደ ግራ ካሣ ገብሬ፣ ከንቲባ ጠና ጋሻው፣ አቶ ካቻክ ፣ አቶ ዳባ ብሩ፣ ደጃች ነሲቡ፣ በለምባራስ ግርማ ያየህራድ፣ ልዑል ራስ ካሣ፣ ፊታውራሪ በቀለ አየለ።

በጃንሆይና በሕዝቡ መካከል የቃል ኪዳን ውል መታሰሩ ለመተባበራችንም ውዴታም ግዴታም ለሁለቱም ወገን ሲሆን ነው እንጂ ላንዱ ወገን ብቻ ሊሆን አይደለም።

ስለዚህ ለሁለቱም ወገኖች በያኳያችን ከሚሆነው ውዴታና ግዴታ በቀር ሌላ ምንም ከዚህ የሚበልጥ ጥቅም አይገኝልንም። ጃንሆይ ለኛ ሕግ በመስጠታቸው ፡ እኛም አክብረን በመቀበላችንና በመፈጸማችን የዚህን ዓለም ትዳራችንን ተስፋ ያለበት ታማኝ ልናደርገው እንችላለን። ስለዚህ አሳባችንም ሁሉ የተረጋጋ ይሆናልና ቁም ነገር ያለበትን የጥቅም ሥራ ሁሉ ለመወጠንና ለማከናወን እንድንተጋ ያደርገናል ።

ይህም ላገራችን ልማት ቅና አሳብ መሆኑን አንስተውም። ሕግ ባይኖር ግን ከግፍና ከበደል በቀር ምንም ታማኝ ለመሆን የሚበቃ ተስፋ አይገኝልንም ነበርና ልባችን ይሰንፍ ነበር። ትዳራችንም ስለማይከናወንልን አሳባችን ያልተረጋገጠና ያልተረጋጋ ይሆንብን ነበር ።

በዚህም አደራረግ ዓላማችን መሠረት የሌላት ከንቱ ምኞት ብቻ ሆና ትቀር ነበር። የዚህንም ሁሉ ጉዳቱን ስንገምተው ከባድነቱ በጣም ሳይታወቀን አይቀርም። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ሕግ በመስጠቱና በዚያው የሕዝቡን ጥቅሙንና ጉዳቱን ጠባቂ በመሆኑ በልዩ የሆነ ዕድል ፡ ከፍተኛ ሥልጣንና መብት ተሰጥቶታል። ይኸውም ለዘለዓለም የግል ገንዘቡ እንዲሆን ያስፈልጋልና ማንም ሌላ ሰው ሊፋለመው አይችልም። ከዕድሜውም በኋላ በውርስ በአገባብ ለልጆቹ እያለፈ እነሱም እንደ ቅድሚያቸው በተራ እየተተኩ የመንግሥቱን ሥራ እንደ ሕጉ ይፈጽሙታል እንጂ ወደ ሌላ ነገድ ሊዛወር አይችልም። ለዚህም ባለ አደራ ለመሆን በቃል ኪዳን ታስሮ ከውል የገባው የኢትዮጵያ ተወላጅ ሁሉ በሙሉ ነው።

ከዚህም የሚገኘው ዋናው ጥቅም በዘውድና ባልጋ አወራረስ ምክንያት በየጊዜው የሚነሣው ጠብና የሚሆነው ፍጅት ፡ ሕዝቡን ወገን እያስለየ የሚያመጣበት መተላለቅና የኢትዮጵያ መነጣጠል መለያየት እንዲቀር መደረጉ ነው።

የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን ፡ የሕዝቡንም ጥቅም ፡ የፍርድን ኃይል እቃወማለሁ ፣ ወይም አጓድላለሁ የሚል ሰው ቢገኝ በገዛ ፈቃዱ ከሕግ ውስጥ የተፋቀ መሆኑ ነውና ከቅጣት የሚያድነው ምንም መከታ አይገኝለትም።

ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያ በማናቸውም አኳኋን በሕግ የተጠበቀችና የተረጋጋች በመሆንዋ ባንድ ወገን ባገር ውስጥ በማናቸውም ዓይነት በትዳር አኳኋን እየደረጀች የህብት ዕድገት ትጨምራለች። ደግሞ በሌላው ወገን በውጭም በዓለም ላይ ዙሪያዋን ካሉት ሕዝቦች ጋራ በምትገናኝበት ነገር ሁሉ የዘለቃ ጥቅሟን እየተስማማች ለመዋዋልና ለመጠቀም ለመከበርም ትችላለች።

እንግዲህ ይህ ሁለቱ የመሻሻል ዘዴ ዋና ጥቅም ያለበት ገበያ መሆኑን ለመረዳት አያቅተንም። ለመንግሥት አቋቋም የሚሆነው መሠረት ሲተከል ፡ ሕግም ሲወሰን ፡ ለየዝርዝሩ ጉዳይ የሚሆነው ውሳኔ ሁሉ ባንድ ጊዜ ተጠንቅቆ ሊነገር ሊደረግም አይቻልም። ይኸውም የሕዝብ ትዳር ዓይነቱና መጠኑ ልዩነቱም እጅግ የበዛ ስለ ሆነ ነው። ነገር ግን እያደር እንደሚያስፈልገው እየሆነ በየጊዜው ለመፍቀድ ሳይደረግ አይቀርም የማለት ተስፋ በፍጹም አግኝተናልና ለወደ ፊቱ ልባችንን ያሳምንልናል ።

የጃንሆይም የችሮታቸው ሰፊነት በጉልህ የሚታየው ከዚህ ላይ ሲደርስ ነው። እንደ ጥንቶቹ ነገሥታት እንደ ፈቃዴ እገዛለሁ ለጊዜው እብሪቱ ያሰኘኝን አደርጋለሁ ለማለት ሲቻላቸው ይህን ትተው በፈቃዳቸውና በችሮርታቸው ለመንግሥታቸው አቋቋም መሠረት ተክለው በሕግ አወሳሰን ለሕዝባቸው ነፃነትን ሰጡ። ነገር ግን ይህን ሲያደርጉ የሕጉን ዓይነት ለመምረጥ ያንዱን የሠለጠነውን መንግሥት ሕግ አስተርጉመው እንድንተዳደርበት በግድ አላዘዙንም። እንደዚህ ተደርጎ በሆነ ጥቅማችን መሆኑ ቀርቶ ጉዳታችን ይሆን ነበር። ነገር ግን እንደ ሀገሩ

ልማድና እንደ ሕዝቡ ዕውቀት እንደ ትዳሩ ችግር እንደ ጊዜው ፈሊጥ እንዲሆንለት ብለው ራሱ ሕዝቡ ለጊዜው የሚስማማውን እየመከረ ፡ ሕገ መንግሥቱን እየጠበቀ ፡ አሳቡን እያመለከተ እንዲኖር ፈቀዱለት።

እንደዚህ አገባብ ባለው በልዩ በቆመ ምክር ቤት ውስጥ በልዩ በተመረጡት አማካሪዎች ጉባኤ ላይ እየተመረመረ በቃል ብዛት የተቆረጠው አሳብ እንደ ሕጉ ሕግ ለመሆን የበቃ ሲሆን ፡ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን እያጸደቀው ሲታወጅ ነውና ከዚህ የሚሻል አወሳሰን ላሁን ጊዜ አይገኝልንም። ያንኑ ንጉሠ ነገሥቱ ካጸደቀውና ካሳወጀው በኋላ ለፍጻሜው አላፊ የሚሆኑ ባለሥልጣኖች ሚኒስትሮች ሆነው ማንም ሰው ቢሆን ከትልቁ እስከ ትንሹ ድረስ ሕጉን ለመተላለፍ እንዳይችል ተደርጓል ።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ከታደሰችበትና ከተመራችበት ጐዳና ከጥከጥንቷ አኳኋን ልዩ የሆነበትን ምክንያት ፡ ልዩም ሆኖ ከእንግዲህ ወዲህ የኢ.ጵያ ሕግ በኢትዮጵያ ተወላጆች ፅውቀት እየተደራጀ ፡ በንጉሠ ነገሥቱ እየተፈቀደ እንጂ በውጭ አገር ሰዎች አሳብ ብቻ የተመራ ነገር አለመሆኑን አስረዳኋችሁ።

የሚኒስትሮች ሥልጣን የሚመለከተው የመንግሥቱንና የሕዝቡን ጉዳይ ሁሉ ነው። ከዚሁም ዋናው የእርሻ ፡ የከብት ማርባት ፡ የእጅ ሥራ ፡ የንግድ ፡ የዳኝነት ሥራ ፡ ይህንም የመሰለው ሌላው ሁሉ ነው።

ከእንግዲህ ወዲያ ማንም ሰው ለሕዝቡ የተፈቀደለትን በኃይልና በጉልበት ሊያጠፋበትና ጥቅሙን ሊከለክለው ወይም እንደ እብሪቱ መለዋወጥ ሁከት ሊያደርግበትና ግፍ በደል ሊሠራበት አይችልም። ከእንግዲህ ወዲያ ማንም ጉልበታምና ዘመናይ የሆነ ፡ ዐቅመ ቢሱን ድሀ እንዳያጠቃው ሕጉ ይጠብቀዋል። ለዚሁም የሕጉ መጽሐፍ ታትሞ በማናቸውም ሥፍራ እንዲገኝ ተደርጓልና ማንም ሰው ሕጉን እየተመለከተ በዚያው በሕጉ መካችነት ራሱን ከጥቃት ለማዳን ይችላል።

ከእንግዲህ ወዲያ ዳኞችም ፍርዳቸው የማያዳላ እንዲሆን በሕግ ተጠብቆ እንዲኖር ተደርጓልና በዚህም ሕዝቡ በጣም ሊጠቀምበት ይችላል።

እንግዲህ ለሕዝቡ የሚፈቀድለት የመረንነት ነፃነት ሳይሆን የሰውነቱ ነፃነትና የትዳሩ ጥቅም ነው እንጂ ከሕግ የወጣ ማናቸውንም ሥራ እንዲሠራ አይደለም። ይኸውም የሚታወቀው አእምሮው እንዲኮተኮትና እንዲቀና ፡ ሠርቶ መጠቀም እንዲችል ፡ ርስቱን እንዳይነቀል ተደርጎ በሕግ ስለተወሰነለት ነው። ነገር ግን ሕግ ተጽፎ ብቻ ቢቀመጥ እንደ ሞተ ሰው ይሆን ነበርና በቀጥታ እንዲፈጸም ተመልካችና አትጊ ተደርጎበታል። ከዚህም ሁሉ የሚገኝ ፍሬ የሰላም ፀጥታ ፡ የሥልጣኔ መሻሻል ፡ የትዳር መደርጀት ይሆናል።

የሰላም ፀጥታ ይገኛል ማለቱ ፣ በጉልበትና በእብሪት መኖር ክልክል ሆኖ በሕግ መኖር ብቻ ግዴታሆኖ ስለ ተፈቀደና በትጋት እንዲጠበቅ ሆኖ ሁሉም ባንድነት በጥንካሬ ስለ ተመሠረተ ነው።

ቀጥሎም በልዩ የቆሙት የሥራ መከናወኛ የሚሆኑ የሚኒስቱር ቤቶች ሥራቸውን በያይነቱ ተከፋፍለው የየድርሻቸውን አንዱ ላንዱ ሁከት ሳይሆኑ ለማስፈጸምና ለማስጠበቅ የሥልጣንና የሙብት ኃይል እንደሚበቃቸው እንዲያገኙ ስለ ተደረገላቸው ነው።

ማንም ሰው በበላይ የሕግ ኃይል አላፊ የሚያደርገው ከሌለበት ፡ያንዱ በደል ለሌላው ጥቅም እየሆነ በሰው ላይ ግፍ መደረጉ አይቀርምና ሕግ ከሁሉ በላይ እንዲሆን የተገባ ነው ተብሏል።

የሥልጣኔ መሻሻል ይገኛል ማለቱ ሰው ለራሱ ሠርቶ መጠቀም እንዲችል ተፈቅዷልና ርስቱን በማቅናትና በማልማት ፡ በእጅ ጥበብም ሠርቶ ጉዳዩን ፈጽሞ ትዳሩን በማደራጀት ፡ በዕውቀት በተደራጀ በአዲስ መሣሪያና በቀለጠፈ ዘዴ ጊዜውን እየቆጠበ በጥቂት ድካም በጥቂት ኪሣራ ብዙ ጥቅም ለማፍራት ይችላልና በእንደዚህ ያለው ሁሉ እየተቀናና ለመወዳደር መጣጣሩ የማይቀር ስለሆነ ነው።

የትዳር መደርጀት ይገኛል ማለቴም በዚህ በተፈቀደው ሁሉ መንገድ ሔዶ መበልጠግ እንዲቻል ሆኗልና ማንም ሰው በሥራ ለመበልጠግና ትዳሩንም ለማደርጀት ለመሠልጠንም መጣጣሩ የማይቀር ስለሆነ ነው። እንግዲህ የንጉሠ ነገሥቱንም የሕዝቡንም ጥቅምና ጉዳት እየለየሁ ከተናገርሁና ሁለቱም በቃል ኪዳን የተሳሰሩበትን የውል ውዴታና ግዴታ ሥልጣንና መብትንም እየለየሁ ካመለከትሁ በኋላ ፡ ለእኛም የሚገባንን ምግባር እንዳንረሳው ማስታወስ የተገባ ነው።

ንጉሥና ሕዝቡ ሕግ ባዘዘው ውዴታና ግዴታ ሊኖሩ በቃል ኪዳን ሲተሳሰሩ ከኛምእያንዳንዳችን በሚቻለን ሁሉ በእውነተኛው አገልግሎት በቅን ልቡና ልንረዳቸው ፡ ለኢትዮጵያም ላንድነቷ ለሚሆነው ጉዳይ ልንተባበርበት እንደዚሁ በቃል ኪዳን ተሳስረናልና ውዴታም ግዴታም የማይለቀን መሆኑን አሳስባችኋለሁ። ደግሞ ሕግ ለሁሉም ትክክል እንዲሆን ያስፈልጋልና ለኢትዮጵያ ተወላጆች ሁሉ ፡ ትንሽና ትልቅ ሀብታምና ድሀ ፡ የሠለጠነና ያልሠለጠነ ሳይባልና ሳይለይ ሁሉም እንደ ዕድላቸው መጠን እንዲጠቀሙ ያስፈልጋል። ሕግ ምንም በደኅና ንግግር የተጻፈ ቢሆን በውስጡ ያለው ፍሬው ነገር እንደዚሁ አሁን እንደ ተናገርነው በእውነት እንዲፈጸም ካልሆነ በቀር አንዳንድ ሰው በተለይ ሕጉን ለመተላለፍና እንደ ፈቃዱ ለመሆን ፡ ለማድረግም ከቻለ መደለያ ሆኖ ይቀራል እንጂ ለሠለጠነ ለክርስቲያን መንግሥትና ሕዝብ የበቃ እውነተኛ መተዳደሪያ ሊሆን አይችልም።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን የተከተሉትን የመንግሥት መሠረት በሕግ ወስነው በቸርነታቸው ሲፈቅዱልን ኢትዮጵያን ባንድ ጊዙ ከነበረችበት ስፍራ አንሥተው የሠለጠኑት ሕዝቦች ከደረሱበት ከከፍተኛው ማዕርግ ደረጃ ላይ ለማቆም አበቋት ብለናልና ንጉሠ ነገሥታችን እኛን ለማስከበር ሲሉ እንደዚህ ያለውን ከፍ ያለ አሳባቸውን ሲገልጹልን እኛም ሳንቀበላቸው ቀርተን ወይም ችላ በማለት አንረዳ ብለን ብናጋልጣቸው የውርደት ቦታችንን በገዛ እጃችን መፈለጋችንን መመስከር ይሆንብናል ።

ስለዚህ ነፃነት ተብሎ በከፍተኛ አሳብና በመልካም በቅንም ልቡና አስተያየት የተፈቀደውን ነፃነት አንዳንድ ሰዎች ትርጓሜው ሳይገባቸው ቀርቶ መረንነት የተፈቀደላቸው መስሏቸው እንዳይታለሉ ሁላችንም በየበኩላችን ለየወገናችን ማስጠንቀቅ የተገባ ሥራችን ነው። ምንም ነፃነት ቢፈቀድ የመረንነት ሥራ እንዳይፈቀድ ማንም ሰው እንዲያውቀው ያስፈልጋል።

እንደዚህ ያለውም እንዳይደረግ ለማስገደጃ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ኃይል በጣም የበቃ መሆኑን መናገር የማያስፈልግ ትርፍ ነገር ይመስለኛል።

ሕግ ያዘዘውን ሁሉ በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ያው ሕጉ በመታደስ ሊሽረው ይችላል እንጂ ሌላ ማንም ሰው ሊሽረው አይችልም። ደግሞ ትልቅ አሳብ ለማከናወን መቸም ብዙ ጊዜ ይወስዳልና ትዕግሥት እንዲኖረን ያስፈልጋል። እንደዚህም ማለት ይህ በሰፊው የታቀደው አሳብ ሁሉ ዕለቱን ለመከናወን አይችልምና ለፍጻሜው የሚበቃ ዘመን የሚያስፈልግ መሆኑን ማወቅ አለብን ማለት ነው። ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች ጊዜ ለመጠበቅ ትዕግሥት እያጡ ሕጉ ተጻፈ እንጂ አይሠራበትም እያሉ ሕዝቡን እንዳያበሳጩትና ተስፋ እንዳያስቆርጡት በየበኩላችን በየወገናችን ማስረዳት የተገባ ሥራችን ነው። ከተማሪ ቤት ባንድ ቀን አውቆ የሚወጣ የለም። ይህ የተነገረው ሁሉ መንግሥቱንና ንጉሥን ለሚወድ ልብ ምንም ቅርታ ሊያስገባበት የሚችል አይመስለኝም።

እንደዚህ ያለው ሰፊ አሳብ በቀላል መሠረት ላይ አይወጠንምና ውጥኑ የሚከናወንበትን ዋናውን ብልሃት አስቀድሞ በጥንቃቄ እየመረመሩ ማወቅ ዋና ዘዴ ነው።

በድንገተኛና በቀላል አሳብ እየተነሣን ለሕዝቡ የሚያመጣውን ጥቅምና ጉዳት ሳንገምትና ሳናመዛዝን የሠራን እንደ ሆነ ወደ ከፍተኛው የሥልጣኔ ደረጃ መድረሳችን ቀርቶ ይልቁን ወደታች ወደ አላዋቂነት እየተመለስን መዋረዳችን አይቀርም። ይህንም ሁሉ እናንተ ከዚህ ያላችሁት ጌቶች ትስቱታላችሁ ብዬ አልጠራጠርም። ነገር ግን በውጭ ያለውን ሕዝብ ምናልባት ያብዛኙን የዕውቀቱን ደረጃ ሳትገምቱት አትቀሩምና በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ እናንተ መሪ ሞግዚት እየሆናችሁ ጥቅሙንና ጉዳቱን ለመለየት እስቲችል እያስታገሣችሁ እንድታቆዩት ያስፈልጋል ።

የነፃነትን የእውነተኛውን ትርጉምና ጥቅሙን ለማወቅ መጀመሪያ መማርና መርማሪ መሆን ያስፈልጋል። የተማረም ሰው ራሱ ከመረንነት ሥራ የታገሠ እንዲሆን ዐውቆ ይጠነቀቃል። ላልተማረ ሰው ግን ዕውቀትና ቅንነት ያላቸው ሰዎች መሪ እየሆኑት ከጥፋት እንዲድንና ተጠቃሚ ጠቃሚም እንዲሆን ያስፈልጋል።

ከዚህም በቀር የበታች ለበላዩ በፍጹም ታዛዥመሆኑን ፡ የበላይም የበታቹን የሚያዝበትን አገባቡን እንዲያውቅበት እናንተው እራሳችሁ ምሳሌ እየሆናችሁ እንደሚቻላችሁ ለሀገራችንና ለንጉሠ ነገሥታችን ማገልገል የተገባ ምግባራችሁና ጥቅማችሁ ነው።

እንደዚህ እየሆነ ፡ ሁላችንም ስንረዳ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ብቻ የወደቀው ትልቅ ሸክም እየተከፈለ ለሁላችንም እየተዳረሰ ይቀልለታልና ሥራውም በፍጥነት እየተከናወነ ለሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ መጠቀሚያ ይሆናል።

እንግዲህ ያለ ይሉኝታና ያለ ፍራቻ ለእውነተኛው ለትልቁ አሳብ ብቻ ሲል ሕዝቡ የሚጠቅመውን ችሮታ ከመንሣት ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን ምግባር ከማስቀረት ፡ በእውነትና በሕግ ለመግዛት ከሚጣጣረው ከንጉሠ ነገሥታችን ጋራ በመተባበር በየሥራችን እየተጋን አገራችን ኢትዮጵያ ለከፍተኛው ማዕርግ እንድትበቃ በዚሁም ትውልዳችን ሁሉ የተባረከ እንዲሆን ከሁሉ የበለጠ ምኞታችንና ጥረታችን ይሁን።

እንግዲህ ጌቶቹ ሆይ ፡እስካሁን እንደ ተቻለኝ አድርጉ ተናግሬአለሁና ደስ አሰኝቷችሁ እንደ ሆነ ወደ ፊትም ጃንሆይ በፈቀዱበት ጊዜ የሕግን አገባብ በጣም ለማስረዳት በእኔ ወገን መቸውንም በፍጹም ልቡናዬ የተሰናዳሁነኝ ።

ከዚህም በኃላ ሁለት የምክር ቤቶች ተዘጋጅተው ነበርና አንደኛው የሕግ መወሰኛ ፡ ሁለተኛው የሕግ መምሪያ ተብለው ተሰየሙ።

ከአራት ወር በኋላም ከያውራጃው የተመረጡት አማካሪዎች እንዲመጡ አድርገን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ የጫንበት ሁለተኛው ዓመት በሚጀመርበት በጥቅምት 23 ቀን 1924 ዓ. ም. ትልቅ በዓል ተደርጎ የምክርቤቱ ተከፈተ።

ይህም አደራረግ የጠላትን ልብ ስለ አናወጠው በልቡ ብቻ ማዘኑ ሳይበቃው ፡ ያሁኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ሥራ አጀማመር ወደ ፊት በጣም የሚያሠጋ ነውና እኛ ኢጣልያኖች ዛሬውኑ በጣም ልናስብበት ያስፈልጋል ብሎ በቃሉ መናገሩን የሰማ የሁላችንም ወዳጅ የሆነ ሰው ነገረን ።

# ምዕራፍ 31

## ኢጣልያኖች በራስ ኃይሉ በኩል የተንኰል ፕሮፓጋንዳ ሠርተው ልጅ ኢያሱ ከሚጠበቁበት ከፍቼ አምልጠው እንዲወጡ ስለ ማድረጋቸው ።

ራስ ኃይሉ የጎጃሙ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ናቸው። ንጉሥ ተክለሃይማኖት ገና ልጅ አዳል ሲባሉ በ 1861 ዓመተ ምሕረት የነገሡትን የዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ዘመድ ወይዘሮ ላቀችን አግብተው ራስ ተብለው ነበር። በኋላ ደግሞ በ1864 ዓመተ ምሕረት የነገሡት ዐፄ ዮሐንስ ዘውድ ሰጥተው በ1873 ዓመተ ምሕረት በጎጃም ንጉሥ አሰኙዋቸው።

ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ራስ በዛብህና ደጃች በለው የሚባሉ ሌሎች ልጆች ነበርዋቸው። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሞቱ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ የጎጃምን ግዛት ለራስ ኃይሉ ሰጥዋቸው። ያን ጊዜ ግን ደጃዝማች ሥዩም ይባሉ ነበር።

ነገር ግን ከቀድሞ ጀምሮ ሥራቸው ሁሉ የተንኰል ሥራ ነበርና፣ያባታቸውን መኳንንቶች ለማጥፋት ስለ አሰቡ ማጎተማቸውን እያስመሰሉ አስቀርጸው ከዐፄ ምኒልክ እንከዳ የሚል ቃል እየጻፉ ለዐፄ ምኒልክ ቢያቀርቡ መኳንንቱ ይህን የመሰለ ሥራ አልሠራንም ብለው ስለ ተቃወሙ ነገሩ ቢመረመር እርሳቸው በተንኰል ማጎተማቸውን አስመስለው ማስቀረጻቸው ስለ ተገለጠባቸው እስራት ተፈርዶባቸው ፪ ዓመት በአፍቀራ ከቆዩ በኋላ ዐፄ ምኒልክ በቸርነታቸው ከግዞት አውጥተው እንደ ገና የጎጃምን ግዛት መለሱላቸው። ከዚህም በኋላ የእቴጌ ጣይቱን የእኅት ልጅ ወይዘሮ አሰለፈችን ስለ አገቡ ጋብቻውን ለማክበር በ1901 ዓ. ም. የራስነት ማዕርግ አገኙ። ስማቸውም ሥዩም መሆኑ ቀርቶ ኃይሉ ተባሉ። ልጅ ኢያሱም ባባታቸው በንጉሥ ሚካኤል ፈቃድ ብቻ የራስ ኃይሉን ልጅ ወይዘሮ ሰብለ ወንጌልን አግብተው ነበር።

ራስ ኃይሉ በጎጃም የሚያልፉትን ኢጣልያኖች ሁሉ በመልካም አቀባበል እየተቀበሉ ይሸኙዋቸው ነበር። ከዚህም በቀር ታምሜአለሁ እያሉ በደሴ ወይም በጎንደር ወደሚቀመጡት የኢጣልያ የንግድ ወኪልና ሐኪም ይመላለሱ ነበር ።

በጎንደር ፡ በደሴ፥ በመጋሎ ፡ የንግድ ወኪል እየተሾሙ የሚቀመጡት ኢጣልያኖች ሐኪምነት ያላቸው እየተመረጡ ነበር። ምክንያቱም ካገሩ ገዥና ከሕዝቡ ጋራ በሕክምና ሥራ እየተገናኙ የተንኰል ፕሮፓጋንዳ ለማድረግ እንዲመቻቸው ነው።

እኛም የኢጣልያንን አደራረግ ሁሉ መጠርጠራችን አልቀረም ነበር። ነገር ግን ባንድ ወገን የወዳጅነት ውል መዋዋላችንን ስለ አሰብን ፣ በሁለተኛውም ወገን ወኪል በሚኖርበት አገር የሚኖሩትን ሕዝብ ወደ ወኪሉ ቤት እየሔዳችሁ አትታከሙ ብለን ብንከለክል የሥልጣኔ ሥራ አይሠሩም ብለው በዓለም ፊት ያሳጡናል በማለት ለዚሁም ዋና ማስረጃ እስትናገኝ በትዕግሥት ቆይተን ነበር።

በኋላ ደግሞ በጎጃም የቆንሲል ቤት ለማቆም ኢጣልያ አጥብቃ ብትጠይቅ የወዳጅነቱን ውል ያከበርን መስሎን ፈቀድንላትና የቆንስላ ቤት አቆመች።

ለልማዱ ቆንሲል መሾም የሚፈለግበት ምክንያት ዜጎቹ የሚኖሩበት ንግድ የሚነግዱበት አገር ሲሆን ነበር። ኢጣልያ ግን ነጭም ጥቁርም ቢሆን አንድ እንኳ ዜጋና ነጋዴ ደብረ ማርቆስ ላይ አልነበራትምና ለፕሮፓጋንዳ ብቻ መሆኑን ሰው ሁሉ ያውቀው ነበር። በዚሁም በቆንስላው ግቢ አንድ የሕክምና ቤት አቁሞ ነበርና የጎጃም መኳንንቱም ሕዝቡም ወደዚያው እየሔዱ ይታከሙ ነበር።

ራስ ኃይሉ የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲጠፋና ለኢጣልያ እንዲሆን አሳብ አላቸው ብለን አንጠረጥርም ነበር። ነገር ግን ጊዜው ካለፈ በኋላ በመጨረሻ እንደ ሰማነው ኢጣልያኖች የሚነግርዋቸው ልጅ ኢያሱ ከሚጠበቁበት አምልጠው እንዲወጡ ያደረጉ እንደ ሆነ እርሳቸው የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት ሲሆኑ እርስዎም ቢሆን በጎጃምና በበጌምድር ፣ ባይሆንም ባባትዎ ግዛት በጎጃም ንጉሥ ይባላሉ። ልጅዎም እቴጌ ትባላለች። ይህንም በማድረግ በሚያስፈልግዎና በሚቸግርዎ ሁሉ የኢጣልያ መንግሥት ትረዳዎታለች እያሉ ነበር። ይህም የኢጣልያኖች ምክር በልባቸው ጠልቆ ስለ ገባ ራስ ኃይሉ ይህንኑ ነገር ለመሞከር ምቹ ጊዜ ይጠብቁ ስለ ነበረ ፡ ለዘውድ በዓላችን ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሁለት ዓመት ያህል ቆይተው ነበርና ልጅ ኢያሱ ከሚጠበቁበት ከፍቼ አምልጠው እንዲወጡ፣ በገንዘብም በነገርም የሚቻላቸውን ሁሉ በምስጢር ይሠሩ ጀመር። ለዚሁ የታሰበው የተንኰል አሳብ ልጅ ኢያሱ ከሚጠበቁበት ከፍቼ አምልጠው ሲወጡ ፣ በሙገር ተሻግረው ሜጫ ላይ ከራስ ኃይሉ ጋራ ተገናኝተው በግንደበረት ወይም በሌላ በሚመች ስፍራ ዐባይን ተሻግረው ደብረ ማርቆስ ሲደርሱ የንጉሠ ነገሥትነት ዐዋጅ አስነግረው ወዲያው ራስ ኃይሉን በጎጃም አንግሠው ከዚያም በበጌምድር አልፈው ወደ ወሎ ተሻግረው ደሴ ላይ ሆነው የጎጃምን ፡ የበጌምድርን ፡ የስሜንን ፡ የትግሬን ፡ የየጁን ጦር ባዋጅ በክተት ሰብስበው ወደ ሸዋ መጥተው ከእኛ ጋራ ተዋግተው አዲስ አበባ እንዲገቡ ነበር።

ምናልባትም ይህ አቅዳቸው የተሰናከለ እንደ ሆነ ፣ በአይሮፕላን ሆነው በፍጥነት ወደ ጎጃም ለመሻገር እንዲመቻቸው፣ ስለ አይሮፕላኑ ከኢጣልያኖች ጋራ ተነጋግረው ኖሮ ፣ ባሮን ፍራንኬቲ የሚባለው ባለ አራት ሞተር አይሮፕላን ይዤ እመጣለሁና ስለ ትልቅነቱ በአዲስ አበባ ሰፊ ስፍራ ስለ ሌለ በአዲስ ዓለምና በገነት ከተማ መካከል ባለው ሰፊ ሜዳ እንዲያርፍ ይፈቀድልኝ ብሎ ፣ ገና ከአሥመራ ሳይነሣ በሌጋሲዮኑ በኩል ፈቃድ ቢጠይቅ ፣ ለልጅ ኢያሱ ወይም ለራስ ኃይሉ ጉዳይ መሆኑን አልጠረጠርንም ነበርና በአዲስ ዓለም አጠገብ እንዲያርፍ ፈቀድንለት። ምስጢሩ ግን ልጅ ኢያሱ እንዲያመልጡ ያደረጉት አቅድ ለአዲስ ዓለም በሚቀርብ በሜጫ ስለ ሆነ ኖሮአል ።

አይሮፕላኑም በመጣ ጊዜ አንድ መትረየስ ከጠመንጃዎችና ከብዙ ጥይት ጋራ በውስጡ መኖሩን ሊቀበሉት የሔዱት ብዙ ሰዎች አይተዋል ። ዐሥር ቀን ያህል በዚያው በአዲስ ዓለም አጠገብ ከቆየ በኋላ ደግሞ እንደገና አሁን የራዲዮ መኪና በቆመበት በአዲስ አበባ አጠገብ ባለው ሜዳ ለመዛወር ቢጠይቅ ይህንም ፈቀድንለት። ይህም አሳብ ራስ ኃይሉን ከአዲስ አበባ ወስዶ ከልጅ ኢያሱ ጋራ ለማገናኘት እንዲመቸው መሆኑ በኋላ ተገልጧል።

ነገር ግን ከሰው አሳብ የእግዚአብሔር አሳብ ይበልጣልና ልጅ ኢያሱከፍቼ ወጥተው የሚያመልጡበት አቅድ ስለ ተሳሳተባቸው ልጅ ኢያሱ ሳይወጡና የመውጣታቸውን ምልክት ሳያስታውቁ ስለ ቆዩ ፣ ባሮን ፍራንኬቲ አንድ ወር ሙሉ ሲጠባበቅ ቆይቶ የልጅ ኢያሱ ወሬ ስለ ጠፋበት ፣ በግንቦት 8 ቀን 1924 ዓመተ ምሕረት አይሮፕላኑን ይዞ ወደ አሥመራ ተመለሰ።

እርሱ በተመለሰ በአራተኛው ቀን ልጅ ኢያሱ ከፍቼ አምልጠው መጥተው ያያ ጉለሌ ሲደርሱ አምልጩ ወጥቼአለሁና ሜጫ ላይ እንድንገናኝ የሚል ደብዳቤ ለራስ ኃይሉ ልከውላቸው ኖሮ ፣ ራስ ኃይሉ በፊት ያሰናዱት አቅድ ሁሉ ስለ ፈረሰባቸው አልተሰናዱም ነበርና አምሳ ያህል ፈረሶች ለማስገዛት የግንደበረትን ባላባት በፍጥነት ላኩት ።

ልጅ ኢያሱም ወደ ራስ ኃይሉ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎችም መኳንንቶች ደብዳቤ ልከው ነበርና ፣ ራስ ኃይሉ በነገሩ ያልገቡ ለመምሰልና አታልለው ለማምለጥ ስለ አሰቡ ልጅ ኢያሱ እኔን በተንኰል ለማታለል ደብዳቤ ጽፈውልኛል ፡ እኔ ግን ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ በቀር ሌላ ጌታና ንጉሥ የለኝምና ለመንግሥትዎ የታመንሁ መሆኔን እንዲያውቁልኝ ብለው ከልጅ ኢያሱ የመጣላቸውን ደብዳቤ አቅርበው አሳዩን ።

ነገር ግን የልጅ ኢያሱ ማምለጥና ራስ ኃይሉም በነገሩ ሁሉ መግባታቸው በአዲስ አበባ እየሰፋ ተወርቶ ነበርና ፣ በጉዳዩ መግባታቸውን የሚያስረዳ ብዙ ምልክት ተገኘባቸው። በአሽከራቸውም እጅ የነበረው ኮረጆ ተገኝቶ

በውስጡ ያለው ሲመረመር ከልጅ ኢያሱ ጋራ የሚላላኩበት የቁጥር ቃልና ሌላም ሁለቱ ብቻ የሚተዋወቁበት ምልክት ተገኘባቸው።

ፈረሶችም ለመግዛት የላኩት ሰው ተይዞ ቢመረመር ፣ ፈረሶቹን ገዝተህ ከልጅ ኢያሱም ተገናኝተህ የሚሉህን ሰምተህ ና ብለውኝ ነበር ብሎ መሰከረባቸው። በመጨረሻው ግን በደግነትዎ ምሕረት ከሚያደርጉልኝ በቀር ሰይጣን አስቶኝ ይህን ሁሉ ማድረጉ እውነት ነው ብለው በቃላቸው አመኑ። ከስምንት ቀንም በኋላ በችሎት ቀርበው እንዲፈረድ ተደርጎ ነበርና ዳኞቹ በሙሉ የሞት ፍርድ ፈረዱባቸው ።

እኛ ግን የሞት ቅጣቱን ለውጠን ገንዘባቸውን ተወርሰው በተወሰነ ስፍራ በግዞት እንዲቆዩ አደረግን። ልጅ ኢያሱም በሜጫና በግንደበረት አውራጃ ራስ ኃይሉን ሲጠብቁ ሰንብተው ተይዘው መታሰራቸውን ከሰሙ በኋላ ፣ ዐባይን ተሻግረው ወደ ደብረ ማርቆስ ለመግባት የሁለት ቀን መንገድ ሲቀራቸው የጎጃም ሕዝብ ይዞ እኛ ለላክነው ለደጃች ደስታ ዳምጠው አሳልፎ ሰጣቸው።

ኢጣልያኖች በ1909 ዓመተ ምሕረት ልጅ ኢያሱ በተሻሩ ጊዜ የልጅ ኢያሱ ተቃዋሚ መሆናቸውን እየገለጡ ለእኛ ይናገሩ ነበር። አሁን ግን ወዳጅ መስለው ከፍቹ እንዲያመልጡ እርዳታ ማድረጋቸው እነሱ በጦርነት አንድ ወታደር እንኳ ሳይሞትባቸው እኛን እርስ በርሳችን አዋግተው ኢትዮጵያን ለመውሰድ አቅድ ማድረጋቸውን ያስረዳል።

# ምዕራፍ 32

## የስዊድን አልጋ ወራሽ ልዑል ጉስታፍ አዶልፍ ሊጐበኙን ስለ መምጣታቸውና በክብር ስለ መቀበላችን ።

እኛ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከመሆናችን አስቀድሞ የስዊድን ሚሲዮኖች በአዲስ አበባ ትምህርት ቤት አቁመው ለኢትዮጵያ ልጆች የእንግሊዝ ቋንቋና የወንጌል ትምህርት ማስተማር ጀምረው ነበር። እነዚህም ሚሲዮኖች ባገር ውስጥም በውጭ አገርም በማናቸውም የፖለቲካ ጉዳይ ሳይገቡ ፣ በደግነትና በርኅራኅ ብቻ ያስተምሩ ነበር። እኛም ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነቱን ከያዝን በኋላ ሥራቸውን ሁሉ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል አስመርምረን ቋንቋና መንፈሳዊ ትምህርት ከማስተማር በቀር ሌላ አሳብ እንደ ሌላቸው በተረዳነው ጊዜ ሥራቸውን እያሰፉ እንዲሔዱ የሚቻለንን እርዳታ ሁሉ አደረግንላቸው። ይልቁንም በአዲስ አበባ ካደረግንላቸው እርዳታ በቀር በሐረርና በነቀምቴ የትምህርት ቤትና ሆስፒታል እንዲሠሩ ፣ የገንዘብና የመሬት እርዳታ እየሰጠናቸው በነዚሁ አገሮች ያለውን ሕዝብ በትምህርትም በሕክምናም እንዲረዱ አደረግን። እነዚህም ሚሲዮኖች በአዲስ አበባና በሐረር ፡ በነቀምቱ ከሕዝቡ ጋራ በመስማማት ይኖሩ ነበር።

ኋላም በ1916 ዓመተ ምሕረት አውሮጳን በጐበኘን ጊዜ ወደ ስዊድን ዋና ከተማ ወደ እስቶኮልም ሔደን ከግርማዊ ጉስታፍ ጋራ በወዳጅነት ስንነጋገር የኢትዮጵያና የስዊድን ሕዝብ በጣም ለመቀራረብ የሚችሉ መሆናቸውን ገለጥንላቸው።

ከአውሮጳም ወደ አዲስ አበባ ስንመለስ ፣ ቤተ ሳይዳ የሚባለውን ሆስፒታል በልዩ ገንዘባችን ሠርተን ባቆምን ጊዜ ከስዊድን ዶክቶር ሐነር የሚባለውን በኦፔራሲዮን ሥራ ስመ ጥሩ የሆነውን ቀጥረን ስለ ወሰድን ብዙ በሽተኞች እየታከሙ ድነዋል። ይልቁንም ከዚያ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቀውን ኤክስሬ የሚባለውን የበሽታ መመርመሪያ ገዝቶ እንዲያመጣና እንዲያቆም ስላደረግን የቤተ ሳይዳ ሆስፒታል የሕክምና ሥራ በጣም እየሰፋና እየተቃና ሔደ።

ከዚያም ቀጥሎ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥራ አማካሪ የሚሆን ትልቁን ሊቅ ዶክቶር ኮልሞዲን ከስዊድን ቀጥረን ስለ አመጣነው ፡እርሱ በብዙ እየረዳን ቆይቶ በአዲስ አበባ ዐረፈና ከጥቂት ጊዙ በኋላ ዐፅሙ ወደ ስዊድን እንዲሔድ አደረግን። ቀጥሎም በዶክቶር ኮልሞዲን ምትክ ጀኔራል ቢርጂን ጠይቀን እንዲመጣ አድርገን ነበርና እርሱም ብዙ ረድቶናል። እነዚህም ሁለቱ የስዊድን አማካሪዎች እንደ ኢትዮጵያውያን ሆነው ስለ አገለገሉ በየክፍሉ ያሉት ሚኒስትሮቻችን ደስታቸውን ይገልጡልን ነበር።

ደግሞ ካፒቴን ደታም የሚባልና ሌሎችም አራት የጦር መኰንኖች አስመጥተን በገነት ከተማችን ካዜርን አሠርተን የጦርነት ትምህርት እያስተማሩ ብዙ ልጆች አሠለጠኑልን ።

በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ የሚኖሩት ስዊድኖች ስለ በዙ በግርማዊ ጉስታፍ አዶልፍ ጥያቄ በአዲስ አበባ የስዊድን መንግሥት ቆንስላ ቤት እንዲቆም ፈቀድን። በመጨረሻውም እኛ በ1916 ዓመተ ምሕረት ያደረግንላቸውን ጐብኝት ምክንያት አድርገው አልጋ ወራሻቸው ጉስታፍ አዶልፍ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ጐብኝት እንዲመልሱ መፍቀዳቸውን በ1927 ዓመተ ምሕረት በኦፊሴል አስታወቁን። ይህንም ትልቅ የሆነ የወዳጅ መንግሥት እንግዳ የምንቀበልበት ቤተ መንግሥት በአውሮጳ መሐንዲሶች ፕላኑን አሥለን ባንድ ዓመት ውስጥ ተሠርቶ ተጨረሰ።

ነገር ግን ኢጣልያ መቸም ቢሆን ኢትዮጵያ በምትሠራው የሥልጣኔ ሥራ ሁሉ መቅናቷ አልቀረም ነበርና ፣ የእንግዳችንን አቀባበል ያሰናከለች መስሏት እንግዳችን አዲስ አበባ ለመግባት 20 ቀን ያህል ሲቀራቸው ፣ በኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ. ም. በግዛታችን በወልወል ውስጥ ገብታና አደጋ ጥላ ብዙ ሰው ገደለችብን። ወዲያውም በአሁኑ

የሁከት ጊዜ የስዊድን አልጋወራሽ ከመንገድ ይመለሳሉ እንጂ ወደ ኢትዮጵያ አይመጡም ፡ ጦርነቱም ከአዲሱ ዓመት በፊት ሳይጀመር አይቀርም እያሉ በከተማ የሚያወሩ ኢጣልያኖች ብዙ ነበሩና ምናልባት ይህ ወሬ እውነት የሆነ እንደሆነ ለትልቁ እንግዳችንና ለእኛም ትልቅ ኀዘን ይሆናል በማለት በጣም ሠግተን ነበር።

ኢጣልያ እኛ የሥልጣኔ ሥራ ነው እያልን የምንሠራውን ሁሉ በሌላ አሳብ እየተረጐመች በዓለም ፊት ማውራቷን አልዘነጋነውም። ይህንም የሚያስረዳ ነገር በ1927 ዓ. ም. ስለ ተደረገው የዘውድ በዓላችን ፣ መልክተኞቻቸውን ለላኩት መንግሥታት ሁሉ ጐዱብኝት ለመመለስ ፣ ለእንግሊዝና ለፈረንሳይ ፡ ለኢጣልያ አልጋ ወራሻችንን ፣ ለሌሎቹም መንግሥታት መልክተኛ ስንልክ ከነዚሁ መንግሥታት ለአንደኛው ለጃፓን መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችንን ብላቴን ጌታ ኅሩይን ፣ ወደ ቶኪዮ ልከን ነበርና መልክቱን ፈጽሞ ሲመለስ ፣ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያና ጃፓን ልዩ የምስጢር ውል ተዋዋሉ ፣ ከዚህም በቀር 3 ሚሊዮን ኤክታር መሬት ኢትዮጵያ ለጃፓን ኩምፓኒያ ኮንሴሲዮን ሰጠች እያሉ በጋዜጣ ያወሩ ጀመር። እንደዚህም ማውራታቸው ጐረቤቶቻችን የሆኑት እንግሊዝና ፈረንሳይ እንደነሱ በእኛ ላይ የሚቀኑ ስለ መሰላቸው ይሆናል እንጂ ፣ይህን የመሰለ ምስጢርና የኮንሴሲዮን ውል አለመዋዋላችንን ሳያውቁት ቀርተው አልነበረም። ኢትዮጵያና ጃፓን ከዚህ አስቀድሞ እንደ ሌሎቹ መንግሥታት የንግድ ውል ከመዋዋል በቀር ፡ ለምስጢርና ለኮንሴሲዮን ውል ይቅርና መነጋገር እንኳ የላቸውም። ከዚህም የባሰ ነገር የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ-ከጃፓን መስፍኒት ጋራ ሊጋባ ነው ብለው በጋዜጣ አወጡ። በዚሁም ምክንያት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን የኢጣልያን ሚኒስትር ኮንት ቤንችን ጠርቶ በአልጋ ወራሻችን ላይ ይህን የመሰለ የሐሰት ወሬ በኢጣልያ ጋዜጣ መውጣቱ ስለ ምን ነው አልጋ ወራሻችን ከዚሁ ካገራቸው ሚስት ማግባታቸውን እርስዎ ራስዎ ያውቁ የለምን ብሎ ቢጠይቀው በስሕተት የሆነ ነገርነውና ስሕተት እንዲታረም አደርጋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ አንድ ሳምንት ቆይቶ ስሕተቱ መታረሙን አስታወቀ።

ይኸን ማንሣታችን ነገሩ ስለ አጋጠመን ነው እንጂ ኢጣልያኖች በእኛ ላይ የሚሠሩትን የሐሰት ወሬ ጽፈን እንጨርሳለን ብለን አይደለምና ለስዊድን እንግዳችን የተደረገውን አቀባበል ወደ መጻፍ እንመለሳለን ።

የስዊድን መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ጉስታፍ አዶልፍ ምንም ኢጣልያ በወልወል ግዛታችን ላይ አደጋ ጥላ ሁከት ማንሣቷን ቢሰሙ ከመንገድ ለመመለስ አላሰቡምና በዚያው በተወሰነው ቀን በታኅሣሥ ወር በኢትዮጵያ የልደት በዓል አዲስ አበባ ደረሱ ።

ከርሳቸውም ጋራ ባለቤታቸው ልዕልት ሉይስና ሴቲቱ ልጃቸው ልዕልት እንግሪድ ወንዱ ልጃቸው ልዑል ቤርቷል ሌሎችም ተከታዮች ነበሩ።

የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንቶች እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ በኢትዮጵያና በስዊድን መንግሥታት መካከል በጣም የጠበቀ ወዳጅነት መኖሩን ያውቃሉና አልጋ ወራሹን ከነቤተ ዘመዶቻቸው በማየታቸው ትልቅ ደስታ ተደረገ። ይህንም የመሰለ ከጥልቅ ልብ የሆነ የወዳጅነት አቀባበል 7 ቀን ያህል ከተከበረ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

# ምዕራፍ 33

## የቀይ መስቀል ማኅበር ስለ ማቆማችን ።

ኢጣልያ በዓለም መንግሥታት ማኅበር የገባችውን ግዴታና የፈረመችውን የኬሎግን ውል ጥሳ ፡ ከእኛም እስከ 20 ዓመት ጦርነት ሳታደርግ በሰላም ለመኖር በ1920 ዓ. ም. (በአውሮጳውያን አቆጣጠር በ1928 ዓ. ም.) የተዋዋለችውን የወዳጅነት ውል አፍርሳ ፣ ኢትዮጵያን ትወጋለች ብለን አላሰብንም ነበር። በወልወል ላይ አደጋ ጥላ ወታደሮቻችንን ብትገድልም ፣ ወደ ፊት ትልቅ ጦርነት እንዳታደርግ የሚያግዳት ስለ መሰለን ፣ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አስታወቅን። ነገር ግን ኢጣልያ ኀፍረትን ከምንም ሳትቆጥረው ከዘለዓለም የስም ክብር የዕለት ጥቅምን መርጣ ፡ የተዋዋለቻቸውን ውሎች ሁሉ በእግሯ ረግጣ ፣ ብዙ መሣሪያና ብዙ ወታደሮች ወደ ሁለቱ ቅኚ አገሮችዋ ለመስደድ አለማቋረጧን በሮማ ያለው ጉዳይ ፈጻሚያችን ነጋድራስ አፈ ወርቅ ገብረ ኢየሱስ ስለ አስታወቀን ፤እንደ ተቻለ የወታደሮ ቻችንን ሕይወት ለመጠበቅ ስንል በሐምሌ 8 ቀን ናጸ ዓ. ም. በአዲስ አበባ የቀይ መስቀል እንዲቆም አደረግን። ወዲያው ቀጥሎ ከዓለም የቀይመስቀል ማኅበር ገባን። ነገር ግን ማኅበሩ የቆመበት ጊዜ ቅርብ ስለ ሆነ ፣ የቀይ መስቀልንጥቅምነት ሕዝቡገና አላወቀውምነበርና ከአንዳንድ ትልልቆች ሰዎች በቀር ፣ የእርዳታ ገንዘብ ለመስጠት የቻለ ስላልተገኘ ፣ ነገሩን ለሕዝብ እስክናስረዳው ጊዜው ያልፋል በማለት ለጊዜው ለደመወዝና ለመድኀኒት መግዣ ይህንም ለመሰለው ሁሉ እስከ ሁለት መቶሺ ብር ከግምጃ ቤታችን አውጥተን ለእርዳታ ሰጠን። ቢሆንም ኢጣልያኖች ጦርነት ለማድረግ የመጡት ባንድ ወገን ብቻ ሳይሆን በምሥራቅና በሰሜን በደቡብም ስለሆነ፣ ብዙ ሐኪሞችና ብዙ መድኀኒት የሚያስፈልግ መሆኑ ታውቆ ነበርና በዓለም ያሉት የቀይ መስቀል ማኅበሮች እንደሚቻላቸው ያህል እንዲረዱ የኢትዮጵያ የቀይ መስቀል ማኅበራችን ጀኔብ ላይ ባለው በዋናው የቀይመስቀል አማካይነት ልመናውን አቀረበ። በየመንግሥቱም ያሉት የቀይመስቀል ማኅበሮች ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ በሚቻላቸው ሁሉ ለመርዳት መፍቀዳቸውን ገለጡልን።

ከዚህም በኋላ የእንግሊዝና የስዊድን ፣ የሆላንድና የኖርዊ የምስር የቀይ መስቀል ማኅበሮች ፣ ሐኪሞችንም መድኀኒቱንም የሕክምና መሣሪያውን ፡ ሌላውንም ለዚሁ የሚያስፈልገውን ሁሉ ሙሉ አምቡላንስ እያደረጉ ላኩልን።

የፈረንሳይና የጀርመን ፣ የጃፓንና የቱርክ ፣ የአሜሪካና የመስኮብ የግሪክና የአውስትራሊያ የሌሎችም የትንንሽ መንግሥታት የቀይ መስቀል ማኅበሮች እንደተቻላቸው መጠን ገንዘብም መድኀኒትም የሕክምና መሣሪያም እየላኩ ትልቅ እርዳታ አደረጉልን ።

ይልቁንም ዋናው የጀኔብ የቀይ መስቀል ማኅበር የገንዘብ እርዳታ ከመላኩ በቀር ወዲያው የኢትዮጵያን የቀይ መስቀል ማኅበር ሥራ እንዲያቃኑ ብሎ ሙሴ ብራውንና ዶክቶር ዢኖ የተባሉትን ሁለት ሰዎች ጨምሮ ልኮ ነበርና የኢትዮጵያ የቀይ መስቀል ሥራ እየሰፋና እየተቃና ይሔድ ጀመር ።

በአዲስ አበባም ከሚኖሩት የውጭ አገር ሰዎች አንዳንዱ ኢጣልያ የምትሠራብንን የግፍ ጦርነት እያዩ ከማዘናቸው የተነሣ የየራሳቸውን ሥራ እየተወ የቀይ መስቀል ሥራ ይሠሩ ነበርና እነዚህን ሁሉ አጥብቀን እናመሰግናለን። .

የኢትዮጵያም የቀይ መስቀል ማኅበር ጦርነቱ የበረታበትን ስፍራ እያጠያየቀ ሐኪሞቹ በየመንገዱ ችግር እንዳያገኛቸው ፣ ያገር ሰዎች እየተጨመሩእንዲሔዱ አደረገ። ፡

የስዊድን አምቡላንስ በሲዳሞና በባሌ በኩል ፡ የእንግሊዝና የሆላንድ አምቡላንስ የእኛ ጠቅላይ የጦር ሠፈር ባለበት በሰሜን በኩል ፡ የኖርዌና የምስር አምቡላንስ በውጋዴን በኩል እየሔዱ እንዲያክሙ ተደረገ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀይ መስቀል ማኅበር የቀጠራቸው ሐኪሞችም በትግሬ፣በውጋዴን ፤በሲዳሞ በሌላም ባስፈላጊው ስና፡ራ ረዳት እየሆኑ እንዲሔዱ ተደረገና ሥራው ለጊዜው በመልካም ይሠራ ጀመር።

ሐኪሞቹም ሥራቸውን ሲሠሩ የጀኔብን የቀይ መስቀል ማኅበር ደንብ እየጠበቁ ከወታደሮች ሰፈር በጣም እየራቁ ነበር። ነገር ግን የኢጣልያ ወታደሮች በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት ጦርነት የድፍረትና የግፈኝነት ስለሆነ ፣ የዓለምን ሕግ ጥሰው በቦምብ እየደበደቡ የቀይ መስቀሎችን ሰፈር እንዳጠፉት ወደ ፊት በስፍራው እንናገረዋለን ።



የንጉሥነት ዘውድ በጫንን ጊዜ ።



አውሮፓን በጐበኘንበት ሰዓት ከግራ ወደ ቀኝ ልዑል ራስ ሥዩም፣ ልዑል ራስ ተፈሪ(ቀ.ኃ.ሥ) ልዑል ራስ ኃይሉ



ከግራ ወደቀኝ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ኃይሌ ወልደ ሩፌ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል፣ ደጃች ነሲቡ ዛማኔል፣ ቢትወደድ መኰንን ደምሰው፣ ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል፣ ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ጉግሣ አርአያ፣ ራስ አደፍርሰው፣ ልዑል ራስ ካሣ፣ ልዑል መኰንን(በህጻንነት) ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ በቀለ አየለ፣ ደጃች በዛብህ፣ ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ፣ ራስ ከበደ፣ ራስ ጌታቸው አባተ፣ ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል



ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ኃይሌ ወልደ ሩፌ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል፣ ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል፣ ራስ ሙሉጌታ፣ ልዑል ራስ ካሣ፣ ልዑል መኰንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ራስ አደፍርስው፣ ራስ ደስታ፣ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ፣ አፈንጉሥ አጥናፍ ሰገድ፣ ደጃች ሀብተ ሚካኤል፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ፣ በጅሮንድ ዘለቀ

# ምዕራፍ 34

## ኢጣልያ በግፍ መነሣትዋን በየጊዜው ስለ ማስታወቃችን ።

በወልወል የተደረገውን ግጭት በዕርቅ ለመጨረስ እንዲቻል በ1920 ዓ.ም በተዋዋልነው ውል በ5ኛው አንቀጽ በተጸፈው መሠረት ሽማግሌ እንምረጥ እያልን በየጊዜው በመጠየቅ ደከመን ነበር። ነገር ግን የኢጣልያ ፍላጎት ወደ ጠብ ያዘነበለ ስለ ሆነ የዕርቁን ነገር ችላ ብላ በወሰናችን አቅራቢያ የጦር መሣሪያ ማከማቸትዋን ሰማን። ስለዚህም በግንቦት 8 ቀን 1927 ዓ. ም. ከዚህ ቀጥሎያለውን ቃል ወደ ጀኔብ አስተላለፍን። ፡

«ለዓለም መንግሥታት ማኅበር

አማካሪዎች ፕሬዚዳን

ጀኔብ ።

እኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፡ የኢትዮጵያ ጥያቄ በሚመረመርበት ባሁኑ ጉባኤ ፡ ይህን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መልክት ክቡርነትዎ መልካም ፈቃዱሆኖ እንዲነበብ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን ።

ከኛ በኩል እስከ ዛሬ ድረስ ወታደርም መሣሪያም ሳናስከትት ፡ ነገርም ሳናነሣ ኢጣልያ ካለፈው መስከረም በፊት ጀምራ በወሰናችን አቅራቢያ ወታደር ፡የጦር አቢዬን ፡ ታንክ ፡ ሌላም በያይነቱ የጦር መሣሪያ ትሰበስባለች። ይኸንንም ማድረጓን በኢትዮጵያ የሚኖር ማንኛውም ሰው፡የማንኛውም አገር ተወላጅ የሆነ ያውቀዋል። ወልወል ላይ አደጋ ከሆነበት ጊዜ ወዲህ ፡ በፊት ከገባችው ከእንተርናሲዮናል ግዴታዋ ሁሉ ለመሰወር በሁለታችን መካከል የተነሡት ጠቦች ሁሉ በትክክለኛው መንገድ እንዳይመረመሩ ለማድረግ በታወቀው በዲፕሎማቲክ መሣሪያ እየፈለገች በማይገባ መንገድ ሰፊ አገር ከግዛታችን መያዚ የታወቀ ሆኖ ሳለ ፡ ኢትዮጵያ ላላጠፋችው ጥፋት ካሣ እንድትሰጣት ትጠይቅ ጀመረች። ከኢትዮጵያም ግዛት አንድ ክፍል መያዚ ኢትዮጵያንም ማጥቃቷና ሕዝቡንም ለማግኘት መመኘቷ በሚገባ ለማሠልጠን ነው ፡ በአረመኔም ሕዝብ ላይ ለማድረግ የሚገባ ነው ለማሰኘት አሁን በቅርብ ፕሮፓጋንድ አቆመች። ኢጣልያ በኢትዮጵያ ወይም በመንግሥቱላይ የምታቀርበው ክስ ቢኖር ፡ በሚያስፈልገው ጊዜና ስፍራ ላይ የሚገባውን ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀን ነን። አሁንም ደግሞ ለሽምግልናውና ለዕርቁ ዳኝነት የመንግሥቷ ሠራተኞች የሆኑ ሁለት ያገሯን ሰዎች መረጠች። የነሱም መመረጥ ነገራችንን በትክክል መንገድ መመርመሩን የሚከለክል ባይሆን እንኳ ምርምሩ እንዲያስቸግር የሚያደርግ ነው። ከዚህም በቀር ለሽማግሌዎቹ እንዲመረምሩት የሚቀርበውን ነገር ኢጣሊያ መወሰኗ በሽምግልና ለመታየት የሚገባውን ዋና የሆነውን በግንቦት 20 ቀን 1900 ዓ. ም. የውል ትርጉም ነገር ሳይጨረስ እንዲቀር ለማድረግ ነው። እውነተኛና ትክክለኛ የሽምግልና ዳኝነት ተስማምቶ ለማቆም ባሁኑ በኢጣልያ አሳብ በዲፕሎማቲክ መንገድ አልተቻለም። ወደፊትም አይቻልም።

ኢትዮጵያ የሽምግልናውን ዳኝነት አልቀበልም አለች ብላ ኢጣልያ አመካኝታ በመንግሥታት ውል የተቀበለችውን ግዴታ ለማስወገድ የሚፈቅድላት መንገድ እንዳታገኝ በማለት ነገራችን በትክክልና በፍጥነት ማለቁ እንዲረጋገጥልን ፡ ችላ ሳንል በማሰብ የኢትዮጵያ ተወላጅ ያልሆኑ ሁለት ሽማግሌዎች መምረጣችንን ለኢጣልያ አስታውቀናል። ምንም ይህ ጎረቤታችን የሆነ መንግሥት ጦር ማዘጋጀቱም ባያቋርጥና በየወሰናችን ላይ መጣ ቆሱ ባይቀር በወሰን ላይ ግጭት እንዳይሆን ተጠንቅቀንበት በሙሉ በግዛታችን ላይ የሆነ ነፃ ቦታ ለማቆም ፈቃዳችን ሆኖ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ውል ቃል እንዲፈጸምና በውነት ለመከላከያ ያልሆነው የኢጣልያ የጦርማዘጋጀት እንዲቆም እንዲያደርጉ አማካሪዎቹን አጥብቀን እንጠይቃለን። ካለፈው ወር ታኅሣሥ ጀምሮ በሱማሌና በኢትዮጵያ ወሰን አቅራቢያ የተደረገውም አደጋ ሁሉና በግንቦት 20 ቀን 1900 ዓ. ም. የተደረገውን የውል ትርጒም ሽማግሌዎቹ መርምረው እንዲፈርዱ ኢጣልያ አልቀበልም የምትል የሆነ እንደ ሆነ ግን አማካሪዎቹ ነገሩን ራሳቸው በጃቸው

አድርገው መርማሪ እንዲያደርጉበትና የመንግሥታት ውል 15ኛውን ክፍል መሠረት አድርገው በሙሉ መርምረው እንዲጨርሱት እንጠይቃለን።

ይህን ጥያቄ ኢትዮጵያ የምታቀርብበት ምክንያቱ ነገሩ በሕግ በሙሉ በፍጥነትና በሰላም እንዲያልቅ በመፈለግ ብቻ ነው ። »

ከዚህም በኋላ በሐምሌ 11 ቀን ለምክር ቤታችን ባደረግነው ንግግር የነገሩን ሁናቴ ለሕዝባችን አስታወቅነው። ቃሉም ከዚህ በታች ያለው ነው።

«ከአርባ ዘመናት ይበልጥ ጀምሮ ፡ ኢጣልያ አገራችንን ለመውሰድ ያላትን ምኞት ምን ጊዜም ቢሆን አላቋረጠችም ነበር። በነዚሁ ዘመናት ሁሉ በልዩ ልዩ አኳኋን ዘወትር ይታይ የነበረው ይኸው ምኞቷ ባለፈው በ1926 ዓ. ም. በክረምቱ ውስጥ በሥራዋ እየተገለጸ መታየት ጀመረ ። ይኸውም ርግጥ ይሆን ዘንድ ባለፈው ዓመት በነሐሴ ወር ውስጥ አላንዳች ምክንያት የኢጣልያ መንግሥት በወሰኖቻችን አቅራቢያ የጦር መሣሪያ በብዙ ማከማቸት ጀመረ።

ይህንኑ ነገር ሰምተን ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ ጠይቅ ብለን ፡ ሮማ ላለው ጉዳይ ፈጻሚያችን ትእዛዝ እንዲያልፍለት አደረግን ፣ ይህን የጦር መዘጋጀት ያደረግነው ኢትዮጵያ የኤርትራንና የሱማሌ ቅኚ አገሮቻችንን ለመውጋት አሳብ ስላላት ነው የሚል መሠረት የሌለው ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ሐሰት የሆነ ምክንያት ምላሽ አድርገው ሰጡ። ምንም ይህ የተሰጠው ምላሽ ጨርሶ ሐሰት መሆኑን ብንገልጽ ፡ ኢጣልያ ከዚያን ጊዜ ጀምራ የምትከተለው አሳቧ በረጅሙ መርምራ በቁረጠችው ፕላን ነበርና ምንም በፍጹም የወሰነችው አሳቧ እኛን በማጥቃት ለመውጋት ቢሆን ለመከላከያ ነው እያሰኘች የጦር መዘጋጀቷን እየገፋች ከመሔዷ አላቋረጠችም።

ይህን የመሰለውን ግፈኛ የሆነ አሳብ በዓለም ሕዝብ ፊት የሚገባ ነገር አስመስሎ ለማሳየት ለዚሁ የሚጠቅም ምክንያት ማግኘት ለኢጣልያ የሚያስፈልጋት ነበረ።

ግማሾቹ የኢትዮጵያ አገር የመሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች በሆኑና ፡ ግማሾቹ የኢጣልያ የንግድ ወኪል (አጃንሲያ) አሽከሮች በሆኑ በኢትዮጵያ ተወላጆች መካከል ባለፈው በኅዳር ወር ውስጥ ጐንደር ላይ ፡ በሴት ምክንያት አምባጓሮ ተነሣ። በነዚህ ሰዎች መካከል በራሳቸው ጉዳይ ይህ ጠብ ተነሥቶ ደም ቢፈስ ፣ አዲስ አበባ ያለው የኢጣልያ ሌጋሲዮን በዲፕሎማቲክ መንገድ በብርቱበነገሩገብቶበት፣መንግሥታችን ሰላም ፈላጊ በመሆኑ የከረረ ጠብእንዳይነሣ ሲል ኢጣልያኖች የጠየቁት እንዲፈጸምላቸው አደረገ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ላሁኑ ጠባችን መሠረት የሆነው የወልወል አደጋ ወደቀ።

ኢጣልያ የኛን ግዛት ቀንሳና የአገራችንን ነፃ ተገዥነትን እንደ ማክበር ሁሉ ጥሳ በ1900 ዓመተ ምሕረት በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተደረገው ውል የወሰነውን ወሰን መቶ ኪሎ ሜትር ያህል አልፋ ወልወል በሚባለው ቦታላይ ወታደርና ብዙ መሣሪያ አስቀመጠች።

በእንግሊዝ ሱማሌና በእኛ መካከል ያለው ወሰን በመወሰኑ ምክንያት በውል እንደ ተፈቀደላቸው የእንግሊዝ ሱማሌ ጐሣዎች ከብት የሚያግጡበትን ቦታ ሔደው አይተው ለመወሰን ከኢትዮጵያም መንግሥት ፣ ከእንግሊዝም መንግሥት ሰዎች ታዘው ነበር።

እነዚህ መንግሥታት ለሥራ የላኳቸው መልክተኞች የታዘዙትን ሥራ በግዛታችን ላይ ሲሠሩ የሚጠብቃቸው መንግሥታችን ስለ ነበረ ተከታዮች ወታደሮች ተሰጥተዋቸው ነበረ። በነዚህም በኢትዮጵያ ወታደሮች እንደምታውቁት ሁሉ በኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ. ም. አደጋ በድንገት ተጥሎባቸው አርበኞቹ ወታደሮቻችን በኢጣልያ መትረየስ በታንኩና በአቪዮኑ እየተመቱ መውደቃቸው የኢጣልያ አጥቂዎች ቀድሞ አስበው የፈጸሙት ግፍ መሆኑን እንደሚበቃ የሚመሰክር ነው።

እንደዚህ አድርገው በገዛ ግዛታችን ላይ ወታደሮቻችንን ወግተው ኢጣልያ የገዛ ሰዎቿ የሠሩትን ግፍ አዛውራ በእኛ ላይ ለማድረግና እኛን ለመውቀሥ አሰበች። ወታደሮቻችንን መግደሏ የማይበቃት ሆነና መንግሥታችን ይቅርታ እንዲጠይቃትና ካሣ እንዲከፍል ከመጠየቅ ደረሰች ።

ኢትዮጵያም የሚገባትን መብት ሕሊናዋ ያውቅላታልና ኢጣልያ ለዘለዓለም በመካከላችን ሰላምና ወዳጅነት ጸንቶ እንዲኖር በመካከላችንም ጠብ ቢነሣ ይኸው ጠብ በሽማግሌ ሥልጣን በሰላም እንዲያልቅ ቃል የገባችበትን በ1920 ዓ. ም. የተደረገውን ውል ጠቅሰን ነገሩን በውሉ ቃል መሠረት ለመጨረስ ጥያቄያችንን ወዲያው አቀረብንላት። ለዚህም ላቀረብነው ጥያቄያችን ምላሹ ፍጹም እምቢታ ሆኖ ኢጣልያ ሳይመረመርና በሚገባው መንገድ ሳይፈረድ ያቀረበችውን ጥያቄ በሙሉ ለማስፈጸም ጥብቅ አሳቧን ገለጸች።

እኛም ፡ክብር ምንም ቢሆን እንዳይነካ ቁርጠን ነበርና ፡ አንድ መንግሥት በሙሉ ፈቃዱ ይህን የመሰለውን ጠብ ለተገባው አለመድሎ ለሚፈርድ ለመንግሥታት ዳኛ አቅርቦ ቢፈረድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ይህንኑ መንግሥት ከፍ አድርጎ የሚያሳየው እንጂ የሚያዋርደው አለመሆኑን ስለተረዳነው በዚህ ነገር ውስጥ ኢትዮጵያ ጥፋተኛ ሁና የተገኘች እንደ ሆነ የተፈረደባትን ፍርድ በሙሉ ወዲያው የምትፈጽም መሆንዋን በግልጽ አስታወቅን።

ኢጣልያ ነገሩ በሽማግሌ እንዲያልቅ የማትፈልግ ከመሆንዋ የተነሣ ነገሩ በሕግና በሰላም መንገድ እንዲያልቅ ፈቃዳችን ስለ ነበረ ይህንኑ ሰላማዊ መንገድ በመፈለግ ነገሩን ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች ለማድረስ የሚያስፈልግ ሆነ። ይኸንኑ ነገር ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር ያደረስንበትን ምክንያት በዝርዝሩ በጽሕፈት አድርገን ለኢጣልያ ንጉሥና ለኢጣልያ መንግሥት ሹም ለሙሴ ሙሶሊኒ አስታወቅን ።

ባለፈው ጥር ወር የዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች በተሰበሰቡበት ጉባኤ ላይ ነገሩ ታይቶ በሽማግሌ እንዲያልቅ አሳቡን ኢጣልያ ሲቀፋት ተቀበለች።

ነገር ግን በዚሁ በጥር ወር 11 ቀን የዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች የቈረጡትን ቃል ተከትለን ሽማግሌዎቹን ለመምረጥ ተጀምሮ የነበረው የዲፕሎማቲክ ንግግር ያላደረግነውን ጥፋት ለማሳመን እየተጣጣረ የኢጣልያ መንግሥት ሚኒስትር ነገሩን እየጐተተው ስለ ሔደ በመጋቢት ወር ውስጥ እንደ ገና ነገሩን ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች ማድረስ የሚያስፈልገን ሆነ ።

በውነትም ኢጣልያ በዲፕሎማቲክ መንገድ መንግሥታችንን በማይገባ ለመጫን ስትጣጣር ፡ ደግሞ ባንድ ፊት በየቀኑ በራዲዮ የሚመጣው ወሬ በየቀኑ ወታደር የጦር መሣሪያ ጥይት ወደ ኤርትራና ወደ ኢጣልያ ሱማሌ ወሰኖቻችን ባለማቋረጥ መላኳን እየሰማን ጦር ይሆናል የማለትን አሳብ በየጊዜው የሚያረጋግጥልን ሆነ ።

ነገሩን ሁለተኛ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር ከማድረሳችን የተነሣ በኀቦት 17 ቀን 1927 ዓ.ም በርግጡ ሽማግሌዎቹ እንዲመረጡ ተቈረጠ።

ኢትዮጵያ የሚፈረደው ፍርድ በፍጹም በሕግ-መሠረት አለመድሎ እንዲሆን ምኞቷ ስለ ነበረ ከሷ ወገን ሽማግሌ የሚሆኑትን በመንግሥታት ሕግ በዕውቀታቸውና በሥልጣናቸው እጅጉን የታወቁ አንድ የፈረንሳይ የሕግ ሊቅና አንድ የአሜሪካ ሕግ ዐዋቂ ሁለት ሰዎች መረጠች።

ኢጣልያም በበኩሏ ከኢጣልያ መንግሥት ሹማምንት ውስጥ ሁለት የኢጣልያ ሰዎች መረጠች።

በዚህም ምክንያት ምንም የምንቃወመው ነገር ባይኖር ፡ የኢጣልያ መንግሥት ያገሩን ሰዎች በመምረጡ ክርክሩ በሕግና አድልዎ በሌለበት መንገድ እንዲያልቅ አለመፍቀዱን ማሳሰብ የሚገባ መስሎ ታየን። ምክንያቱም ማንም ሰው ቢሆን እንዲከራከርላት በመረጠችው በአገሩ ላይ አድልዎ የሌለበት ፍርድ ይፈርዳል ተብሎ የማይጠረጠር ስለሆነ ነው።

የኢጣልያ መንግሥት የመረጣቸው ጨዋዎች የታያቸውን እንዲፈርዱ ነፃነት የሌላቸው በመሆናቸው ምክንያት ክርክሩ በሽምግልና ዳኝነት እንደማያልቅ የሚያሠጋ ስለ ሆነ ፡ የእንግሊዝም መንግሥት የዓለም መንግሥታት ሕግ ዋና መሠረቱ የዓለም ሰላም መሆኑን ተመልክቶ ፡ደግሞ ዋና ምኞቱ በዓለም ላይ ሰላም እንዲጸድቅ ስለ ሆነ የመታረቂያ መንገድ ይገኝ እንደ ሆነ በማለት በበኩሉ መሞከር ጀመረ። ምንም የውጋዴ አውራጃ የኢትዮጵያ መሆኑ በሕግ ረገድ የማያጠራጥር ቢሆን ፡ምንም ኢጣልያ ተጋፍታ መጥታ በርስታችን ላይ ክፉ አደጋ ብትጥልብን ፡ የእንግሊዝ መንግሥት ያቀረበው የዕርቅ ሐሳብ እኛ ከውጋዴ ግዛታችን አንድ ክፍል ቈርሰን ለኢጣልያ እንድንሰጥና ለዚህም ለውጥ እንግሊዝ የዘይላን በርና አንድ ክፍል ከግዛቱ ቈርሶ ለኛ እንዲሰጥ ነበር። እኛም ሰላም ለመፈለጋችን ወሰን የለውምና ፡ ይህን የቀረበውን የዕርቅ አሳብ ለመመርመር ተዘጋጅተን ነበር ። ነገር ግን ይህ የዕርቅ አሳብ ገና ከመቅረቡ ሙሴ ሙሶሊኒ በፍጹም አልቀበለውም ስላሉ በነገሩ እንድናስብበት የማያስፈልግሆነ ።

አሁን ጨዋዎቹ የተመረጡበትን ጉዳይ ለመፈጸም አልተቻላቸውም ። የእንግሊዝ መንግሥት ያቀረበውን የዕርቅ አሳብ የኢጣልያ መንግሥት ዋና ሹም ባጭሩ ቈረጠው።

ኢጣልያኖችም መሰናዳታቸውን አላቋረጡም። የኢጣልያ መንግሥትም ታላላቁ ሹማምንት በልባቸው ያለው ዋናው አሳባቸው አገራችንን ለመውሰድ መሆኑን በግልጥ ይናገራሉ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ የጦርነት ሰዓት እየቀረበ መሔዱ ነው።

ባለፈው ሰኔ 1 ቀን የኢጣልያ መንግሥት ዋና ሹም የአፍሪቃ ምሥራቅ ተብሎ አዲስ ወደ ተሰየመው ወደ ኤርትራና ወደ ሱማሊያ በታዘዘው አምስት ሺ. ወታደር ፊት ቆሞ እንደ ልማዱ ለኢጣልያ ሕዝብ ሲሰብክ የጦር ፈላጊነት መንፈሳቸውን ለማነቃቃት ብሎ እናንተ የምትሔዱት ለታሪካችን በጣም ከፍ ያለ የጀግንነት ነገር ልትጽፉ ነው ብሎ ተናገረ።

ሙሴ ሙሶሊኒ እንደሚሉት ኢጣልያ የምትፈልገው የእኛን ሕዝብ ለማሠልጠን ነው።

ነገሩ በሰላማዊ መንገድ እንዳያልቅ ለማድረግ ኢጣልያ ካሁኑ ቈቁርጣለች። አሳቧ ብዙ ደም ፈሶ የቀድሞውን የአድዋን ብድር ለመመለስ ነው።

አረመኔ ሕዝብ እያለች ስሙን የምታጠፋው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠውን ቃል የሚያከብርና የፈረመውን ውል የሚያጸድቅ ሕዝብ ነው።

ኢትዮጵያ ጦርነት እንዲሆን አትፈልግም። የመጣውን ግን መከላከሏ አይቀርም። በአድዋ ጊዜም ቢሆን ጠብ አንሺ ኢትዮጵያ አልነበረችም። ጦርነትም የሆነበት ምክንያቱ ኢጣልያኖች ወሰን አልፈው በግዛቷ ውስጥ ስለ ተገኙ ነው። ምናልባት ደግሞ ነገ እንደዚሁ ያደርጉ ይሆናል ።

በእግዚአብሔር ቸርነት በአርበኞቿ ጀግንነት የመጣባትን መከታ ምንም በ1888 ዓ. ም. ኢትዮጵያ ድል ብትነሣ (ብታደርግ) የሚገባትን ሁሉ አልጠየቀችም ፤የግዛቷ ማስፋፊያ ምክንያት አላደረገችውም።

ከቀን እስከ ቀን የማይቀር መስሎ የሚታየው ጦርነት በደረሰ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ሕሊናው አይወቅሠውም ፤ ሰላም እንዲጠበቅ የተቻለውን ሁሉ አድርጓል።

ኢትዮጵያ በሌሎች አገሮች ላይ ሥልጣን ይኑረኝ የማለት አሳብ የላትም በግዛቷ ውስጥ ባለቤት ሁና ሥልጣንዋና ወሰንዋ ሳይደፈር ለነፃነቷ ስትል እስከ መጨረሻው ድረስ ለመከላከል የተዘጋጀች ነች።

ተጋፊ የሆነው የኢጣልያ ሕዝብ ዘመኑ ያወጣውን የአጥቂነት መሣሪያ ይዞ ሥልጣኔ ላስተምራችሁ ነው ብሎ ሲመጣ ለንጉሥ ነገሥቱና ላገሩ ለመሞት የተዘጋጀ አንድነት ያደረበት ሕዝብ ተሰልፎ ይጠብቀዋል።

ወታደር ሆይ ፣ በጦርነት ውስጥ አንድ የተከበረና የተወደደ አለቃ ለነፃነታችን ብሎ ሞተ ሲባል አትዘን ፣ ተስፋ አትቁረጥ። ላገሩ የሚሞት ሁሉ ዕድለኛ ሰው መሆኑን ተመልከት እንጂ ሞት ሳያማርጥ በሰላም ጊዜ ሆነ በጦርነት የፈቀደውን ይወስዳል። ያለ ነፃነት ከመሞት ነፃነትን ይዞ መሞት ይሻላል።

አባቶቻችን አገራችንን በነፃነት ያቆዩልን ሕይወታቸውን እየሠዉ ነው። እነሱ አብነት ይሁኑዋችሁ ።

ወታደር ፡ ነጋዴ ፡ገበሬ ፡ ልጅም ፡ ሽማግሌም ፡ ወንድም ፡ ሴትም አንድነት ይደርባችሁ። እየተረዳዳችሁ ላገራችሁ ተከላከሉ። እንደ ጥንት ጊዜ ልማድ ሴቶችም ወታደሩን በማደፋፈር ቀ*ስለኛ በማስታመም ላገራቸው ይከላከላሉ። እርስ በርሳችን እንድንለያይ ምንም ኢጣልያ የተቻላትን ሁሉ ብታደርግ ክርስቲያን ሆነ ወይም እስላም አንድ ሆኖ ይመከታል።

ምሽጋችንና ጋሻችን እግዚአብሔር ነው። የአጥቂዎቻችን አዲስ መሣሪያ ለኢትዮጵያ ነፃነት ከመከላከላችሁ ከተቀደሰ አሳባችሁ አያዘንብላችሁ።

ዛሬ የሚፍገር ንጉሣችሁ በዚያ ጊዜ በመካከላችሁ ይገኛል ፣ ለኢትዮጵያ ነፃነት ደሙን ለማፍሰስ ተዘጋጅቷል ።

ሳንጨርስ ዳግመኛ አንድ የምንነግራችሁ ነገር አለ። ይኸውም ለሰላም አጥብቀን መጣጣራችንን ነው። እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም መድከሙን እናሳስባችኋለን። በዲፕሎማቲክ መንገድ ሰላማዊ የሆነና ለሁለታችንም ክብር ያለበት የመስማሚያ መንገድ መፈለጉን አላቋረጠም። የኢጣልያ መንግሥት በፈቃዱ የፈረመውን የወዳጅነትና የሽምግልና ዳኝነት ውል እንዲያከብር እንዲያደርግ የዓለም መንግሥታትን ማኅበር ሁለት ጊዜ ጠይቋል ።

ዳግም ጦርነት በፍጹም እንዲቀር ተብሎ የቀረበውን ውል ኢትዮጵያም ኢጣልያም ከሌሎች መንግሥታት ጋራ ስለ ፈረሙ የውሉም መሥራች አሜሪካ ስለ ሆነ አሁን በቅርቡ ለአሜሪካ መንግሥት አስታውቀናል ።

ደግሞ አሁን ሆላንድ አገር የሁለታችንም ጨዋዎች ክርክራችንን ሲመረምሩ የኢጣልያ ጨዋዎች ስላስቸገሩ ፓሪስ ያለው ሚኒስትራችን ሦስተኛ ጊዜ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር እንዲያመለክት አዘነዋል።

እስከ መጨረሻው ድረስ ሰላም እንዲሆን እንጣጣራለን። ነገር ግን ድካማችንና መልካም አሳባችን ፍሬ ያላገኘ እንደ ሆነ ሕሊናችን አይወቅሠንም። የኢትዮጵያ ሕዝብም በእምነት ተባብሮ ላገራችን ነፃነት በእውነተኛው ነገር ለመከላከል እግዚአብሔር የአርበኞቻችንን ኀይል እንዲያጸና እጁን ወደ እግዚአብሔር ይዘረጋል ።

ሐምሌ 11 ቀን 1927 ዓ. ም.»

ከዚህ በኋላ ደግሞ በጳጉሜ 6 ቀን ድምፃችንን በራዲዮ በማሰማት ለዓለም ሕዝብ አስታወቅን። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

«እንደ ኢትዮጵያ ቁጥር 1918 ዓ.ም. በሚጀመርበት ጊዜ ፡ ይህ አዲሱ ዘመን ሕዝባችንና ዓለም በጋለ ልብ የሚመኘውን አስፈላጊ የሆነውን ሰላም እንዲያመጣ እየተመኘን ባለፈው ዘመን ቀኖች የተደረጉባቸውን ዋና ዋና ነገሮች መመልከትና ማሳሰብ የተገባ መስሎ ይታየናል።

በውጋዴ ግዛታችን ውስጥ በኢትዮጵያ መሬት ላይ በወልወል በኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ. ም. ብዙ መሣሪያ የያዙ በማይገባ በኢትዮጵያ ግዛት ገብተው በተገኙ እስካሁንም በዚያው ባሉ በኢጣልያ ወታደሮችና የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ሱማሌ ግዛት ለመወሰን የታዘዙትን ሰዎች እንዲከተሏቸው በታዘዙት ወታደሮች መካከል የተደረገው ግጭት ፡ ይህ ግጭት ተርታ ነገር ስለ ሆነ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ውል እንደ ተመለከተው መሠረታዊ ነገርና ኢትዮጵያ በነሐሴ 20 ቀን 1920 ዓመተ ምሕረት ከኢጣልያ ጋራ በተዋዋለችው በተለየ ውል እንደ ተጻፈው ቃል በቶሎ ሊጨረስ የሚገባው ነበር።

አደጋው እንደ ተደረገ ፡ መንግሥታችን በሽምግልና ዳኞች እንዲጨረስ የጠየቀው ይህ የወልወል ግጭት በነሐሴ 28 ቀን አሁን በቅርቡ ፍርድ ተሰጠ። ነገሩንም እስከዚህ ፍጻሜ ለማድረስ ኢትዮጵያ የወልወልን ግጭት ጉዳይ በሰላምና በሕግ መንገድ ለመጨረስ ስትጣጣር ፡ ኢጣልያ በብርቱ ስለ ተቃወመች ፡ በጥር 11 ቀን ፡ በግንቦት 17 በመጨረሻውም በነሐሴ 28ቿ ቀን የዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች ጉባኤ ተሰብስቦ እንዲመረምር ለማድረግ ግድ ሆነበት። የወልወልን ነገር እንዲመረምሩ የታዘዙት ሁለቱ የኢጣልያ መንግሥት ሰዎች ከሌሎቹ ከሦስት የሽምግልና ዳኞች ጋራ ሆነው አምስቱም ሰዎች ባንድ ቃል ኢትዮጵያም ኢጣልያም በወልወል በተደረገው አደጋ አላፊ ሊሆኑ አይችሉም ብለው ፈረዱ። የወልወል ነገር በዚህ ስለ ተፈጸመ ኢጣልያ መንግሥታችንን ለማዋረድ ካሣ ክፈሉ ለባንዲራ ሰላምታ ስጡ ብላ ኢትዮጵያን በዓለም ፊት አጥቂ አስመስላ ለማስፈረድ የጠየቀችው እንዲቀር ተደረገ። ኢጣልያም በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለማድረግ ምክንያት ያደረገችው የወልወል ግጭት ስለ ሆነ ይህ ምክንያት ዛሬ በፍርድ ተወገደ።

የዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተነሣውን ነገር የሽምግልና ዳኞች በሚገባ እንዲጨርሱ የሚያስፈልገውንና የተቻላቸውን ነገር አደረጉ። ስለሆነ የኢጣልያ መንግሥት በብርቱ ይቃወም ነበር።

በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ላለው ግጭት ምክንያት የሆነው አንደኛው በግንቦት 20 ቀን 1900 ዓ. ም. በሁለቱ መንግሥታት መካከል ስለሱማሌ ግዛት ወሰን የተደረገው ውል ትርጒም ሳይጨረስ ቈይቷል። የዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች በጥር ወር በተሰበሰቡ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት የዚሁ የወሰን ውል ትርጉም እንዲመረመር ጠይቆ በተለየም ወልወል የሚገኘው በኢትዮጵያ ወይም በኢጣልያ ግዛት ውስጥ መሆኑ እንዲመረመርና እንዲቈረጥ ጠየቀ። የኢጣልያ መንግሥት ግን ይህን ነገር የሽምግልና ዳኞች አይመረምሩብኝም ብሎ ተቃወመ። ወልወል የሚገኘው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መሆኑን በኢጣልያ በቅኝ አገር ሚኒስቴር በኦፊሲዬል የወጣው ካርታ አይበቃም ቢባል እንኳ ይህ የኢጣልያ መንግሥት አደራረግ ለማስረዳት የሚበቃ ነበር።

በዓለም መንግሥታት ማኅበር ብርታትና በሕግ የሚገባና የሰላምን መንገድ ተከትሎ ፍጻሜ እንዲያገኝ መንግሥታችን ጠንክሮ በመያዙ በወልወል የተደረገው ግጭት በሽምግልና ዳኞች ፍርድ ተቈርጦ ስለ ኢጣልያ ባለፈው ዓመት በነሐሴ ወር የወልወል ግጭት ሳይደረግ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለማድረግ ስላሰበች ፣ ይህን ጦርነት ለማድረግ ከ5 ወር በኋላ በወልወል ላይ የተደረገውን ግጭት ምክንያት አገኘሁ ብላ የያዘችውን አሳብ ዛሬም እያረጋገጠች ትሔዳለች። ከነሐሴ ወር 1925 ዓ. ም. ጀምሮ ኢጣልያ በኤርትራና በሱማሌ ቅኝ አገሯ መሣሪያ መላክ ስለ ጀመረች ፡ ወታደር መሣሪያ ልዩ ልዩ የጦር መኪና ጥይት ሳታቋርጥ እየላከች ስታጠነክር ቆየች። የዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎችና የሽምግልናም ዳኞች በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተነሣውን ነገር በሰላም ለመጨረስ ሲሠሩ ኢጣልያ መሣሪያና ወታደር መላኳን አላቋረጠችም።

ዛሬ የወልወል ነገር ስለ ተጨረሰና ጦርነት ለማድረግ ለኢጣልያ ምክንያት ስላጠረባት ኢትዮጵያ ለመከላከያ የሚያስፈልጋትን መሣሪያ እንዳታገኝና ሌሎቹ መንግሥታት እንዳይሸጡላት ካደረገች በኋላ ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አውሬ ስለ ሆነ አሠልጣኝ ያስፈልገዋል እያለች ለዓለም ሕዝብ ለማሳመንና ኢትዮጵያን ለማስጠላት ትሠራለች።

የኢጣልያን አኳኋን ታሪክ ይፈርደዋል። ኢጣልያ ሥልጣኔ የተወሐደኝ ነኝ እያለች ስትናገር ፡ ሰላማዊ በሆነ ፡ አስቀድሞ መሣሪያ እንዳያገኝ በተደረገበት ፡በነሐሴ 20 ቀን 1920 ዓ. ም. ኢጣልያ በግልጥ ሰላምና ወዳጅነት ጸንቶ እንዲኖር የፈረመችውን ውል ተማምኖ በሚኖር ሕዝብ ላይ በማይገባ ጦርነት ታደርጋለች። ኢጣልያ ወታደሮቿ ድል እንዲያደርጉላት ብዙም ጉዳት እንዳያገኛቸው ወደ ፊት ጦርነት አነሣበታለሁ ብላ ያሰበችበትና ኢትዮጵያን መሣሪያ እንዳታገኝና እንድትደክም አድርጋ በሕዝባችን ላይ ለመፈጸም የምታዘጋጀውን የማይረባ ሥራ የተገባ አስመስላ ለማስረዳት ትፈልጋለች።

ስለዚህም የኢጣልያ ወታደሮች በማይገባ ወሰን ተላልፈው አገራችንን ያዙብን ብለን ላቀረብነው በሕግ ለተመሠረተው ማስረጃችን የሮማ መንግሥት ምላሽ ሳይሰጥ በእኛ ዘንድ የተሾሙት እንደራሴዎቹ ኢጣልያ ስለ ኢትዮጵያ ከልብ የሆነና የማይጠፋ ወዳጅነት አላት እያሉ ብዙ ጊዜ በግልጥ እንዲያረጋግጡ አድርጎ በግዛታችን ውስጥ የነዛቸው ቀሩጥራቸው የበዛ ደመወዝ የሚሰጣቸው ሠራተ የሚያመጡጠለትን ወሬ ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ እየሰበሰበ ሲያጠራቅም ኖሮ ፡ አሁን በመጨረሻው ሰዓት ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች አቀረበ።

የኢጣልያ መንግሥት በብልግናና በሐሰት ላቀረበው ክስ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች በነሐሴ 29 ቀን ክስ ያቀረበበት ማስታወሻ ገና ስላልቀረበልን ይህነን ክስ የምናውቀው ለጊዜው ባጭሩ ነውና አሁን ምላሹን በዝርዝር የምንሰጥበት ጊዜያት አይደለም። ነገር ግን መንግሥታችን ምክንያቱ ለዓለም ሕዝብ የተገለጠ የሆነውን በመጨረሻ ሰዓት የቀረበውን የዚህን ክስ ምላሽ አንድ ባንድ ለመመለስና ማስረጃውን ለመስጠት የተዘጋጀ ነው። ላሁኑ ግን በጀኔብ ያሉን መልክተኞቻችን ፡ ነገሩን የሚመረምር የእንተርናሲዮናል ኮሚሲዮን እንዲቆም ከዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች እንዲጠይቁ የተጣራ ትእዛዝ ማሳለፋችንን ብቻ ማስታወቅ ይበቃል።

የኢጣልያ መንግሥት ያቀረበውን ክስ የሁለቱንም ነገር መርምሮ ለመቁረጥ የሚችል ይህ የጠየቅነው የእንተርናሲዮናል ኮሚሲዮን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥብቆ ሰላምን ይፈልጋል። ከዚህም በቀር አገሩን በልቡ ይወዳል። ምንም የሚበቃ መሣሪያ ባይኖረውና በኢጣልያ ፖለቲካ ምክንያት እንዳያገኝም ቢደረግ ባገር ፍቅር የተቃጠለና የኲራ ልብ ያለበት ደረቱን መክቶ ከጠላቱ በመከላከል ይቃወማል።

በሰላም እርሻቸውን እያረሱ የሚኖሩ ክንዳቸው የጠነከረ ፡ ለነፃነታቸው ቀናተኞች የሆኑ ገበሬዎቻችን እርሻቸው በጠላት እጅ እንዳይገባ ለመከልከል ማረሻቸውን በቅልጥፍና የሚያገላብጡትን ያህል ፡ ጐራዴና ጦራቸውንም በቅልጥፍና ሊሠሩበት ይዘው ይነሣሉ። ጦርነት እንዲደረግ አንፈቅድም። ነገር ግን በጦርነት ስንጠቃ ሳንከላከልና ጠላታችንን ሳንቋቋም አናሳልፍም። ኢትዮጵያ እምነቷ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፍርድ ከሰው ፍርድ እንዲበልጥ ታውቃለች። ሰውም ወገኑን ለማጥፋት ያወጣው አዲስ መሣሪያና መድፍ የሥልጣኔ ምልክት አይደለም።

ያሁኑ ዓለም በደረሰበት ችግር ውስጥ ምንም ሥራቸው ከልክ ያለፈና የበዛ ቢሆን ከብዙ ወራት ጀምረው ኢጣልያ ለራሷ በማሰብ ብቻ ሰላምን ለማጥፋት ስለ ተነሣች ሰላም እንዳይጠፋ ለማጠንከር የሚጥሩ የመንግሥታት ሰዎች ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ሕዝቧም ፡ የመንግሥት ሰዎች የሆኑ ሁሉም ሰላምን ለመጠበቅ የሚደከሙት ድካም መልካም ፍሬ እንዲያፈራ መሪያቸው እንዲሆን ጸሎታቸውን ሳያቋርጡ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባሉ።

ኢትዮጵያ በውል የገባችውን ማናቸውንም የእንተርናሲዮናል ግዴታ ሁሉ አክብራ ዘወትር መፈጸምዋን ፡ ደግሞ አሁን በርሷና በኢጣልያ መካከል የተነሣው ግጭት በሰላም እንዲጨረስ ክብርዋና ማዕርጓ በሚፈቅድላት መጠን መስማሚያ መንገድ መፈለጓን ታውቃለችና ፣ ሕሊናዋ አይወቅሣትም። ታላቅመንግሥትየተባለችው ኢጣልያ በማይገባ የምታደርገው ይህ የአጥቂነት ሥራ ለሰው ልጅ ሁሉ ሥልጣኔ የሚሰጥና ኑሮውን የሚያሻሽልለት ሰላም መሆኑን ተረድተው አሳባቸውን በዚሁ ላይ ለሚያኖሩ ለትልቅም ለትንሽም ለዓለም መንግሥታት ሁሉ የሚያሠጋ ስለ ሆነ በዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካሪዎች ርዳታ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተነሣው ጠብ በሕግና በሚገባ ፍርድ ከዓለም መንግሥታት ማኅበር ውል ጋራ የተስማማ ሆኖ እንዲጨረስ እየተመኘች ኢትዮጵያ ተስፋ ታደርጋለች ። »

# ምዕራፍ 35

## <u>የክተት ዐዋጅ ስለ መንገራችን ።</u>

የሠለጠነው ዓለም ሁሉ አንዱ መንግሥት ከሌላው መንግሥት ጋራ ጦርነት ለማድረግ የፈለገ እንደ ሆነ ጦርነት ለማድረግ መፈለጉን ያስታውቃል ። ካስታወቀም በኋላ የሁለቱም ወገኖች እንደራሴዎች ወደ መንግሥታቸው ይመለሳሉ። ዜጎቻቸውም ቢፈልጉ ሊወጡ ይችላሉ።

ኢጣልያ ግን በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለማድረግ ካሰበች ብዙ ዘመን ፡ ለማድረግም ከተሰናዳችና ከቆረጠች ሦስት ዓመት ሆኖ ሳለ ጦርነት ለማድረግ አላሰብሁም እያለች ታወራ ነበር። ነገር ግን ማናቸውም ጊዜ ጊዜው ሲደርስ መገለጡ አይቀርምና ፣ አሁን ጀኔራል ዲ ቦኖ ስለ ጦርነቱ ባወጣው መጽሐፉ ተናግሮታል። ይኸውም በሙሴ ሙሶሊኒ ፊርማ የተፈረመ ስለሆነ ሐሰት ነው ለማለት አይቻልም።

ጦርነቱንም ለመጀመር የወሰነችው አቅድ እስቲደርስ የጦር መሣሪያና ብዙ ወታደሮች ወደ ቅኚ አገሮቿ ወደ ኤርትራና ወደ ሱማሌ አገር መላኳን በሰማን ጊዜ ፡ ሮማ ባለው በጉዳይ ፈጸሚያችን በኩል ምክንያቱን ብንጠይቅ ንጉሥ ነገሥቱ በቅኚ አገሮቻችን ላይ አደጋ ጥለው እንዳይወጉን ለመጠበቅ ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም የሚል ማንም ሰው እውነት ነው ብሎ ሊቀበለው የማይችል ምላሽ ሰጠ ።

ምክንያቱ ይህ ከሆነ በማለት በእኛ በኩል ይህን የመሰለ አሳብ አለመ ታሰቡን ለኢጣልያና ለዓለም ሁሉ በራዲዮ አስታወቅን።

ይህንም ብናስታውቅ የጦር መሣሪያና ወታደሮች መላኳን አላቋረጠችም ነበር። እኛም በበኩላችን እንዳንሰናዳ ባገ ውስጥ የጦር መሣሪያ ለማሠራት ፋብሪካ አልነበረም። ከውጭ አገርም እንዳንገዛ የሚበቃ ገንዘብ አልነበረንም። ብድርም ብንጠይቅ ኢጣልያ ጦርነት ለማድረግ መቁረጧ ታውቆ ነበርና የሚያበድረን አላገኘንም ነበር። ይልቁንም ደግሞ የዓለም መንግሥታት በጄኔብ ላይ ባቆሙት ማኅበር በቃል ኪዳኑ የተጻፈውን ኢትዮጵያና ኢጣልያ ወደው ስለ ፈረሙ ፣ በመካከላችን ማናቸውም ዓይነት ጠብ ቢነሣ እንደ ውሉ ቃል ነገሩ በማኅበሩ ታይቶ በሰላም የሚጨረስ ስለ መሰለን ፡ በዚህም ላይ ደግሞ ሁለቱ መንግሥታት በተለየ በሐምሌ 21 ቀን 1920 ዓ. ም. ባደረጉት በወዳጅነቱ ውል በ5ና በ7 ቁጥር በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተነሣውን ጠብ በዲፕሎማቲክ መንገድ ተነጋግረው የማይጨረስ የሆነ እንደ ሆነ ፣ ነገሩ በሽማግሎች ይጨረሳል እንጂ እስከ 20 ዓመት በመካከላቸው ጦርነት አይደረግም ስለሚል ፡ ኢጣልያም ከሠለጠኑት ከትልልቁ መንግሥታት አንደኛው እኔ ነኝ ብላለችና የማኅበሩን ቃል ኪዳን የማታፈርስ ስለ መሰለን ፡ ይልቁንም ደግሞ የቀድሞ ዘመን አረማውያን እንደሚያደርጉት ጦርነት ለማድረግ መቁረጧን ሳታስታውቅ ጦርነት ትጀምራለች ብለን ባለመጠርጠራችን ፣ የወልወል አደጋ ከተደረገበት ከኅዳር 26 ቀን ጀምሮ በአድዋ አደጋ ጥላ ጦርነት እስከ ጀመረችበት እስከ መስከረም 22 ቀን ድረስ እኛ የክተት ዐዋጅ አላደረግንም ነበር ።

ነገር ግን ኢጣልያኖች የእኛ ወታደሮች ያሉበት በየዳር አገሩ በሩቅ ስፍራ መሆኑን ያውቃሉና ማንም መንገደኛ ሊጓዝበት የማይችልበትን ክረምቱን ጠብቀው አደጋ የጣለብን እንደ ሆነ የማለት ጥርጣሬ ስለ ገባን ለመጠባበቂያ የሚሆኑ ወታደሮች ከየደንቡ በቁጥር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አድርገን ነበር።

የነዚህም መኖሪያቸው በኢትዮጵያ ምዕራብና ደቡብ በሩቅ ስለ ሆነ ለመንገዳቸውም እስቲሰናዱ ክረምቱ ገብቶ ነበርና ዝናብና ጭቃ ስላስቸገራቸው በሐምሌ ወር እየተነሡ በመስከረም እኩሌታ አዲስ አበባ መድረስ ጀመሩ ።

ኢጣልያኖች ግን ባንድ ወገን ዕርቅ የሚፈልጉ እየመሰሉ ለዓለም መገግሥታት ማኅበር ወዝ እየሰጡ ፡ በሁለተኛውም ወገን የጦር መሣሪያና ወታደሮች እየላኩ ሙሉ መሰናዳት ካደረጉ በኋላ ፣ ጦርነት ለመጀመር

መቁረጣቸውን ለእኛ ወይም ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ሳያስታውቁ በመስከረም 21 ቀን 1928 ዓመተ ምሕረት በአይሮፕላን ወሰን አልፈው መጥተው በአድዋ ከተማ ቦምብ እየጣሉ ሽማግሌውንና ሕፃናቱን ፡ ሴቱን ካህናቱን ደበደቧቸው፣ዋና ዋናውንም ቤት አቃጠሉት።

ምናልባትም ለመጠባበቂያ ብለን የቀይ መስቀል ማኅበር ቤት በአድዋ እንዲቆም አዝዘን ነበርና ያንንም አቃጠሉት።

ባሁኑ በሠለጠነውም ዓለም ጊዜ አንዱ መንግሥት ሌላውን መንግሥት ለመውጋት ሲያስብ ሳያስታውቅ አያደርግም። ኢጣልያ ግን ከዕለት ጥቅሟ በቀር ክብርዋንና ስምዋን ሳትጠብቅ ምንም ማስታወቂያ ሳታደርግ ጦርነት ስለ ጀመረች ለታሪኳ የሚያሳፍራት መሆኑ አይጠረጠርም።

ከዚህም በቀር አዲስ አበባ የነበረው የኢጣልያ ሚኒስትር ኮንት ቤንች ትልቅ ችግር አድርጎብን ነበር ። እንደ ሠለጠነው ዓለም መንግሥት ቢሆን ኢጣልያ ጦርነት ለማድረግ መቁረጥዋን ሚኒስትርዋ እንዲያስታውቅ ማድረግ ሚኒስትሩንም መጥራት ይገባት ነበር። ዜጎቻችን ሁሉ ከኢጣልያ ግዛት እንዲወጡ በኢጣልያ ጉዳይ ፈጻሚያችንና አሥመራ ባለው ቆንስላችን በኩል እናስታውቅ ነበር። ምናልባት ኢጣልያ የጦር ማስታወቂያ ሳታደርግ ሚኒስትርዋን የጠራች እንደ ሆነ ለጦርነት መሆኑን ዐውቀን እኛ እንዳንሰናዳ ፡ የከተትም ዐዋጅ እንዳንነግር ለማድረግ ሳይሆን አይቀርም። ወይም ደግሞ ሚኒስትርዋን በኃይል ሳናስወጣ አንድ ትልቅ አደጋ የደረሰበት እንደ ሆነ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ሚኒስትር ላይ እንደዚህ የመሰለ የግፍ ሥራ ሠራች ብለው በዓለም ፊት እንዲፈረድብን ለማድረግ አስባ ይሆናል ።

እኛ ግን የዓለምን የሥልጣኔ መንገድ ለመከተል ጀምረን ሳለን እንደ ኢጣልያ ወደ ኋላ ተመልሰን የሕገወጥነት ሥራ መሥራት የማይገባ መሆኑን ስለ ተረዳነው ሚኒስትሩና ቆንሲሎቹ ፡ ወኪሎቻቸው ፡ ሌሎችም ዜጎቻቸው ሁሉ ማናቸውም ዓይነት ችግር ሳያገኛቸው በ ሚቀርባቸው መንገድ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ አስታወቅናቸው። ስለዚህ በሚቀርባቸው መንገድ በምሥራቅ ያሉት በጅቡቲ ፡ በደቡብ ያሉት በሞጋዲሾና በኬንያ ፡ በምዕራብ ያሉት በሱዳን ፡ በሰሜን ያሉት በአሥመራ እንዲሔዱ ተደረገ።

ማስታወቂያ ሳያደርግ ፡ የዓለም መንግሥታት ማኅበርን ቃል ኪዳን አፍርሶ የጦርነት አደጋ የጣለ መንግሥት ዜጎቹን ጦርነቱ እስቲጨረስ እንደ እስረኞች አድርገን ብናቆያቸው እንኳ ፡ እንደ ክፉ አድራጊ ባልተቆጠርንም ነበር። ግን ሰላምን ለመፈለግ ስንል ይህንም ለማድረግ አልፈቀድንም። ነገር ግን እኛ ምንም እንኳ የሰላምን መንገድ ብንከተል ፣ ሚኒስትሩ ከምንም ሳይቆጥረው ቀርቶ በያውራጃው ያሉት ቆንሲሎቹና ወኪሎችም ዜጎቹም በሙሉ ሳይወጡ እኔ አልወጣም ብሎ እምቢ አለ። እንዲያውም በጣም ለማስቸገር ሲል በዚያው በኩል ወደ ሞጋዲሾ ቢሔድ የሚቀርበውን የመጋሎን ወኪል ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ጠራው።

ከዚህም ሁሉ የባሰ ነገር ከዚህ አስቀድሞ በአዲስ አበባ በአውቶሞቢል ሲሔድ የነበረውን ትቶ አሁን በፈረስ እየሆነ ፣ ባንዲራ የያዘና ሽጉጥ የታጠቀ አሽከር በፈረስ እያስከተለ ፣ እንኳን የውጭ አገር ሚኒስትሮችና ያገርም ትልልቅ ሰዎች በማይሔዱበት በተራ መንገድ ይሔድ ጀመረ። ለመጠባበቅም እንዲመጡ የታዘዙት ወታደሮች አዲስ አበባ መግባት ጀምረው ነበርና ፡ ያንድ ጠላት ሚኒስትር ይኸን በመሰለው አካሔድ በከተማውስጥ ሲሔድ ባዩት ጊዜ ፡ ደማቸው እየፈላ በክፉ ዓይን ማየት ጀምረዋል ማለትን ስለ ሰማን ፣ ምናልባት አንድ አደጋ ያገኘው እንደ ሆነ ለሰላም ስንል እስካሁን የታገሥነው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ይቀራል በማለት የተጠሩት ወኪሎች እስቲመጡ ባንድ በተወሰነ ስፍራ ዐርፎ እንዲቀመጥ አማካይ በሆነ ባንድ ስፍራ እንዲቆይ ተደረገ። ነገር ግን እኛ ለሰላምና ለጸጥታ ያደረግነውን እነሱ ወደ ክፉ ተርኩመው ሚኒስትራችንን አስረው አስቀመጡት ብለው አወሩ ።

ከዚህም በኋላ ኢጣልያኖች በሰሜንም ፡ በደቡብም ወሰን እያለፉ በየከተሞቻችን ላይ ቦምብ እየጣሉ ፣ ሰዎች መግደላቸውን ፡ ቤቶች ማቃጠላቸውን አረጋግጠን ስለ ዐወቅን ፣ ምንም ለመከላከያ የሚሆንና የሚበቃ አዲስ

መሣሪያ ባይኖረን እንኳ ላገራችን ነፃነት እንደ ተቻለ መከላከል ይገባናል በማለት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክተት ዐዋጅ በመስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም.እንዲነገር አደረግን።

«ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ያገሬ የኢትዮጵያ ሰው ፣ ኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሲያያዝ መምጣቱንና በነፃነቱም ታውቆና ተከብሮ መኖሩን ታውቀዋለህ።

ካሁን ቀደም ኢጣልያ የዛሬ 40 ዓመት በብልሃቱና በጉልበቱ ተመክቶ የኢትዮጵያን ነፃነት አጥፍቶ ፣ ሕዝቡን እንደ ባሪያ አድርጎ ለመግዛት ተመኝቶ ፣ አገራችን መካከል መጥቶ ቢወጋን ግፍ የማይወደው አምላካችን ረድቶን ድል ማድረጉን ለኛ ቢሰጠን የሔደውን አገራችንን አልፈለግንም። በሐማሴንና በሱማሌም በኩል ወሰን እየገፉ ርስታችንን ወስዶ በዚያው በወሰደው አገር ላይ ያሉት ወንድሞቻችን የተሸከሙትን የባርነት ቀንበር ዓይንህ የሚያየው ጆሮህ የሚሰማው ነው።

በእነሱ ላይ በሚሠራው ግፍ ስናዝን የሔደውን አገራችንን ሳንፈልግ ፣ አሁን ደግሞ በሞላው አገራችን በሚኖረው ሕዝብ ላይ የባርነት ቀንበር ለማሸከም አስቦ በውጋዴ በኩል በድብቅ ጦር አምጥቶ ጠብ ያልፈለጉትን የኛን ሰዎች ቢገድልብን ፡ የተዋዋልነውንም ውል ቢያፈርስብን ፡ ለዓለም ሰላም ተብሎ ወደ ቆመው የዓለም መንግሥታት ማኅበር እኛም ገብተናልና እንደ ሕጉ የወልወል ጠብ በሽማግሎች ታይቶ በደለኛው እንዲታወቅ ብለን ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አመለከትን።

ነገሩም ገና በሽማግሎች ሳይታይና ሳይፈረድ ኢጣልያ ጦሩን በትግሬና በውጋዴን ወሰን ስላቀረበ እንደገና ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ብናመለክት ማኅበሩ ነገሩ በሽማግሎች ይታይ ብሎ ፈረደልን። ሽማግሎቹም ነገሩን መርምረው ወልወል ላይ በተደረገው አደጋ የኢትዮጵያ መንግሥት አልበደለምና አላፊነት የለበትም ብለው ፈረዱልን። ይህም ሁሉ ሲሆን ኢጣልያ ወደ ወሰናችን በየጊዜው ጦር እያመጣ መጨመሩን አልተወም። እኛም ነገሩ በሽማግሌ ታይቶ በሰላም ይፈጸም የምንለውን ሁሉ ኢጣልያ ከመለማመጥ ቁጥሮት ከየሺ ዘመን ይበልጥ በነፃነት የኖረችውን በጥንታዊነቷ የታወቀችውን ሽማግሌዋን አገራችንን ነፃነቷን አጥፍቼ እወስዳለሁ በማለት ስለ ተመኘ ፣ ለመጠቃት በመታሰባችን እጅግ አዝኛለሁና ያገሬ የኢትዮጵያ ሰው ጉልበት ያለህ በጉልበትህ ፣ ጉልበት የሌለህ በኀዘንህ ርዳኝ። በጉልበትም በኀዘንም የምትረዳበት ምክንያቱ ለሃይማኖትህና ለነፃነትህ እንደ አባትና እንደ ልጅ እየተሳሰበ ሲረዳዳ ለኖረው ለንጉሠ ነገሥትህ ኩርቶ ነፃነቱን ለሚያሳየው ባንዲራህ ስትል ነው።

ነፃነትም የሌለው ሕዝብ በጠላት እጅ እንደ ከብት እየተነዳ ካገሩ የሚሰደድ ፡ በገዛ ምድሩ ርስቱን በሌላ ሰው እጅ እያየ ጭሰኛ ሆኖ በውርደትና በመረረ ኀዘን የሚኖር ፡ በከብቱና በንብረቱ በመቃብሩ መሬት እንኳ የማያዝበት ፣ ለዘሩ የሚተላለፍ ባርነትን ወርሶ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው። ስለዚህ ስንኳን ሌላው ሰው ንጉሥም ጳጳስም ቢሞት ሰው ነውና ዘሩ ይተካበታል። ያገር ነፃነት ሲጠፋ ግን ምትክ የሌለው፣ባርነቱም ከዘር ሲተላለፍ ከማይሞት ስም ጋራ የሚኖር የዘላለም እስር ነውና ኢጣልያ ምንም በመሣሪያው ቢኩራ ሞት የጋራ መሆኑ የታወቀ ነው።

1ኛ. በሳል በጉንፋን የምትሞተውን ሞት ከሩቅ አገር እኛን ለማጥቃት ለመጣው ጠላታችን ባገርህና በርስትህ በቤትህ ላይ ሆነህ መመከት አቅቶህ ላገርህ ለኢትዮጵያ ሞት ብትነፍጋት ፡ ደምህንም ሳታፈስ ብትቀር በፈጣሪህ የምትወቀስበት በዘርህ የምትረገምበት ነውና ፣ የተለመደ የጀግንነት ልብህን ሳታበርድ ወደ ፊት የሚቆይህን ታሪክህን እያሰብህ ጠንክረህ ለመዋጋት ቁርጠህ ተነሣ።

2ኛ. አነሣሥህም ጭፍራ ካለቃህ፣ሎሌ ከጉታህ ሳትለይ በጥቅምት 12 ቀን ለሚካኤል ደሴ ላይ ክተት። ስትጓዝም ከሣርና ከገለባ ከኩበት በቀር እንኳን ከቤት ያለውን ገንዘቡን ከውጭም ያለውን ከብቱንና አዝመራውን የነካህ አብሮህ የሚሞተውን ወንድምህን መግደልህ ነውና ገንዘቡን በጥፍ ከፍለህ ትቀጣለህ ።

3ኛ. በየመንገዱ ላይ ያለህ ባላገር ለኢትዮጵያ ነፃነት የሚዘምተው ወታደር እንዳይቸገር አገረ ገዥህ በሚነግርህ ቀን በሚሰፍርበት ቦታ እያወጣህ ገቢያ አቁምለት። እሰፈርም እያመጣህ ለምትገበያየው ነገር የዘመቻው ጊዜ እስቲያልቅ ድረስ ቀረጥ አትነካም ምሬሃለሁ ።

4ኛ. ባላባትም የሆንክ ሁሉ ለዘመቻ የደረሱትን ልጆችህን ይዘህ ላገር ጥበቃ አላፊ የሚሆን እንደራሴህን ላገረ ገዥው እንደራሴ እየሰጠህ ካገረ ገዥህ ጋራ እንድትነሣ። በሽምግልና ዘመቻ የማትችል ግን አንተ አገር ጠብቅ ልጆችህ ካገረ ገዥው ጋራ ይነሡ።

5ኛ. የሹማምንትና የወታደርም ልጅ ለዘመቻ የደረስህ ከዚህ ቀደም ከደንብ ያልገባህና ለጌታ ያላደርክ ባገር ውስጥ ሥራ ሳትይዝ የተቀመጥክ ጠበንጃ ያለህ ጥይትና ሥንቅህን ፡ ጠበንጃም የሌለህ ጠበንጃ ጥይት ሥንቅህንም ዳርጌሃለሁና አገረ ገዥህን ተከትለህ እንድትዘምት።

6ኛ. ከደንብ ከገባህ በኋላ ደንብህን ለቀህ የያን የምትኖር ወታደር ሁሉ እየተመለስክ በያለቃህ ከደንብህ እየገባህ ዝመት። የመኳንንትና የወታደር አሽከርም በያገሩ የተቀመጥህ የተጣላህም ፥ ብትኖ( ታርቀህ ከጌታህ ጋራ ዝመት። በብርቱ ተበድያለሁና ከጉታዬ ጋራ ታርቄ ለመኖር አልችልም የምትል ግን መሣሪያውንና በደንብ የተቀበልከውን ማናቸውንም ገንዘብ በጦር ሚኒስቴር ዳኛ ለጌታህ አስረክበህ ከጦር ሚኒስቱር ባልደረባና ጠበንጃ እየተቀበልክ እንድትዘምት በፍጥነት አዲስ አበባ እንድትመጣ ይሁን።

7ኛ. ገበሬና ነጋዴም የሆንህ ያለህን ብረት ባገረ ገዥህ ሹም አስቈጥረህ በመዝገብ አጽፈህ አገር ጠባቂው እንደራሴ የሚያዝህን ትእዛዝ እንድትሰማና በሚቸግርበት ሁሉ እንድትረዳ ይሁን ።

8ኛ. በያገሩም ያለህ ነጋዴና ባላገር ካህንም ብትሆን ኪራዩን እከፍልሃለሁና ከዐሥራቱ እህል ላይ እየጫንክ ክተት እተባለበት ቦታ ድረስ እየወሰድህ አግባልኝ።

9ኛ. ለዘመቻ ከታዘዝህ በኋላ ወስልተህ ከዘመቻው የቀረህ ግን ባገሩ ሹም ወይም በከሳሽ እየተያዝህ በርስትህና በገንዘብህ ባካልህም ትቀጣለህ ለከሳሹም ከገንዘብህ ሚሶውን መርቄለታለሁ።

10ኛ. ካሁን ቀደም ነፍስ ገድለህ ባለደምህን ፈርተህ ወንበዴም ሆነህ ቤት አቃጥለህ የሰው ገንዘብ ቀምተህ ሸሽተህ በዱር በገደል የምትኖር ምሬሃለሁና በጥቅምት 5 ቀን በየሻለቃህ ግባ። ስትገባም በሻለቃህ ከየአገረ ገዥው መዝገብ እየተጻፍክ ባልደረባም ሊጋባውን ሰጥቼሃለሁና ከሱ ጋራ ወይም ከሻለቃህ ጋራ ዝመት። በተወሰነልህ ቀን ሳትገባ የቀረህ ግን በተያዝክበት አገር ትሰቀላለህ። የሟቹ ወገን የሆንህ ባለደምም ጉማውን እኔ እከፍልሃለሁና ባለደምህን ማርልኝ።

11ኛ. የዘመቻ ዐዋጅ ከተነገረ በኋላ የወንበዴነት ሥራ ስትሠራ ለጠላት ሥንቅም ነገርም ስታቀብል የተገኘህ ርስትህንና ገንዘብህን ትወረሳለህ። ያለ ምሕረትም በሞት ፍርድ ትቀጣለህ ። »

የጦርነቱንም ድርጅት ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው አደረግን። በሰሜን በትግሬ በኩል ለመጣው ጠላት ተከላካይ ዋናው ጠቅላይ አዝማች ራስ ካሣ ሆኖ በውስጡ የሙሉ ትግሬ ጦር አዛዥ ራስ ሥዩም መንገሻ፣ ራስ ሙሉጌታ ይገዙ፣ ራስ ከበደ መንገሻ፣ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ ራስ ጌታቸው አባተ፣ ደጃች አያሌው ብሩ፣ ደጃች መሸሻ ወልዴ፣ ደጃች በየነ ወንድማገኘሁ፣ ደጃች መንገሻ ይልማ፣ ቢትወደድ መኰንን ደምሰው፣ ደጃች አድማሱ ብሩ፣ ደጃች አበራ ተድላ፣ ደጃች አውራሪስ ዱሉ፣ ደጃች ወልደ ማርያም በዳዳ፣ ደጃች በላይነህ ደባልቀው ፡ ያልጋ ወራሽ ጦር አዛዥ ደጃች ወዳጄ ውቤ፣ ደጃች አምባቸው ገሠሠ ፡ የዋግ ጦር አዛዥ ደጃች ኃይሉ ከበደ፣ ደጃች ወንድ በወሰን ካሣ፣ ደጃች አበራ ካሣ፣ ደጃች ኃይሉ ተስፋዬ፣ ጸሐፊ ትእዛዝ አፈ ወርቅ ወልደ ማርያም፣ በጅሮንድ ለጥይበሉ ገብሬ፣ ቀኛዝማች ደጎኔ ወልደ ማርያም ናቸው።


NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ልዑል ራስ ጉግሣ አርያ፣ ደጃች አቻሜለህ፣ ልዑል ራስ ካሣ፣ ደጃዝማች አደፍርሰው(ራስ)፣ ፊታውራሪ በቀለ አየለ ልዑል መኰንን፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ደጃች ለጥይበሉ፣ ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ልዑል ራስ ስዩም፣ ራስ ጌታቸው አባተ፣ አቶ ተስፋዬ ተገኘ፣ ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል።



ራስ ካሣም ከክረምቱ በፊት ወደ ግዛቱ ወደ በጌምድር ሔዶ ከርሞ ነበርና በቶሎ ተነሥቶ ሔዶ ለራስ ሥዩም እንዲደርስላቸው ትእዛዝ አሳለፍንለት። ከሸዋም የጦር ሚኒስትራችን ራስ ሙሉጌታ ከዚህ በላይ የተቆጠሩትን የጦር አለቆች ይዞ እንዲቀድም አደረግን ።

በጥቅምት 8 ቀን የጦር ሠራዊቱን አሰልፎ ከፊታችን ቀርቦ ሲሰናበተንም ሊከተለው ስለሚገባው ጥንቃቄ ለርሱና በዙሪያችን ተሰልፎ ላለው የጦር ሠራዊት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ትእዛዝ ሰጠነው።

«ላገርህ ነፃነትና ለኛ ለንጉሠ ነገሥትህ ክብር ደምህን ለማፍሰስ ቆርጠህ መነሣትህን ማየታችን ደስ የሚያሰኝ ነው።

ጌታ ገንዘቡን የሚያስጠብቀው ላመነው አሽከሩ ስለ ሆነ ፡ አንተም እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ አድርገህ ፡ የጦር ሠራዊታችንን እየጠበቅህ ፣ በማናቸውም ችግራቸው ሁሉ እየረዳህ ፡ ለጠላት እንድትመክት አዝዘንሃል።

አሁን የመጣብን ጠላት ደም የተቃባነው ፡ ከጥንት የቆየ ነው እንጂ አዲስ ድንገተኛ ጠላት አይደለም። ሰላም ፈላጊ የሆነውን የዓለም መንግሥታትን ማኅበር አምነን ፡ ጦራችንን ወደ ግምባር ባለ ማስቀደማችን አሁን ያገኘውን ሁሉ በጭካኔ ከመግደል በቀር እንኳን ለወታደር ለሽማግሌና ለሴት ፡ ለሕፃንም ይራራል ተብሎ አይጠረጠርም። ለሴቶችና ለሕፃናትም አለመራራቱን ባጀማመሩ ሰምተነዋል ።

በማናቸውም ቢሆን ሞት አይቀርምና እገሌ በሳልና በጉንፋን ፡ በተሰቦ ሞተ ከመባል ላገሩ ነፃነት ፡ ለንጉሠ ክብር ፡ ለትውልድ ስም ደሙን አፍስሶ ሞተ መባል ትልቅ ጥቅም ያለው መሆኑን መዘንጋት አይገባም ። በጦርነት ላይ አንዱ ቢሞት ተራውን ተወጣ ይባላል እንጂ እገሌ ሞቷል ብሎ መደናገጥ የጀግንነትን ክብር የሚያዋርድ መሆኑን ማወቅ ነው።

ለወታደርም ፡ ለባላገርም ፡ ለነጋዴም ቢሆን ትልቁ ኩራቱ ያገሩ ነፃነት መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ስለዚህ ከመካከላችሁ ጠብና ተንኩል እንዲጠፋ ፡ ፍቅርና አንድነት እንዲሰፋ ፡ ሎሌ ለጌታው ፡ ጭፍራ ላለቃው መታዘዝን እንዲያውቅ በሚቻላችሁ ሁሉ ማስረዳት ነው። ኢጣልያኖች በመሣሪያቸው ቢኩሩብን እኛም ትልቁ መሣሪያችን የእግዚአብሔር እርዳታ በመሆኑ እንኩራባቸዋለን።

ቀይና ብጫ አረንጓዴ ባንዲራችን ፡ «ሞዓ አንበሳ» የሚለው ማኅተማችን የነፃነታችን ምልክት ነውና ፣ ይህ የነፃነታችን ምልክት እንዳይጠፋ እስከ መጨረሻዋ ጠብታ ደማችንን እያፈሰስን ብንሞትም ለስማችንና ለታሪካችን ትልቅ ክብር ነው።

ይህነንም ስላልናችሁ እንደ ዘመኑ ዓይነት ጦርነት እየተዋጋችሁ ኢትዮጵያን ከጠላት እጅ ለማዳን ነው እንጂ ባለመጠባበቅና በንዴት እንደ እሳት እራት በጦርነት ውስጥ እየገባችሁ ለመሞት ብቻ የሆነ እንደ ሆነ ለጠላት የተመቸይሆናል።

የምታደርጉትም ጥንቃቄ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

1ኛ. ድንኳን ስትተክሉ በየሻምበሉ እየተለየ ስፍራ ቢያጋጥም በጐድጓዳና በዛፍ ፣ በዱር ውስጥ መትከል ነው። አተካከሉም ካንዱ ድንኳን እስከ 30.ክንድ እንዲራራቅ ማድረግ ነው።

2ኛ. አይሮፕላን ሲበር በታየ ጊዜ ገላጣውንና ትልቁን መንገድ ሰፊውንም ሜዳ ትቶ በዘብጥና በጐድጓዳ በዘወርዋራ መንገድ ፡ ዛፍና ዱር ባለበት ስፍራ መጓዝ ነው ።

አይሮፕላን በምብ ለመጣል ሲመጣ 100 ሜትር ያህል ዝቅ ካላለ አይመቸውምና ፡ ለዚሁ ሥራው ዝቅ ባለ ጊዜ በመልካም በረጃጅም ጠበንጃ እሮምታ ተኩሶ በፍጥነት መበታተን ነው። ሦስት ወይም አራት ጥይት ከመታው አይሮፕላኑ መውደቁ አይቀርም። ለዚህም ተኩስ የተመረጠውን መሣሪያ ይዘው ለመተኰስ የታዘዙት ብቻ ይተኩሱ እንጂ ጠበንጃ ያለው ሁሉ ቢተኩስ ጥይት ከማባከንና ያሉበትን ስፍራ ከማሳየት በቀር ጥቅም የለውም።

3ኛ. አይሮፕላኑ ገና ብቅ ሲል የተበታተናችሁ እንደ ሆነ የምትበታተኑበትን አቅጣጫ እንዳያየው ጥቁት ቀረብ እስቲል በጥንቃቄ ቂይቶ መበታተን ነው። ጦርነት በሚደረግበት ጊዜ ጣፋ ጋሻ ፡ጉሜ፡ ብርና ወርቅ ለምድ ፡ ግምጃ ቀሚስ ፡ይህን የመሰለ ሁሉ ለጠላት ጠበንጃ ማነጣጠር ይመቻልና ፣ ኮት ያለው ኮቱን ፡ የሌለው ደበስ ያለ እጀጠባብ ብቻ መልበስ ነው። ይህንንም የወርቅና የብር ሽልማታችሁን እግዚአብሔር ረድቶን ስንመለስ ታደርጉታላችሁ። አሁን እየተዋችሁት መሔድ ነው። ይህንንም ሁሉ የምክር ቃል ማስታወቃችን ባለመጠንቀቅ ትልቅ ጉዳት እንዳያገኛችሁ ብለን ነው እንጂ በሐምሌ 11 ቀን በተናገርነው ዲስኩር እንዳስረዳናችሁ ፡ በጦርነቱ ጊዜ በመካከላችሁ ሆነን ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ደማችንን ለማፍሰስ የተዘጋጀን መሆናችንን ስናረጋግጥላችሁ ደስ ይለናል ። »

# ምዕራፍ 36

## የደቡብን የጦር ሠራዊት ስለ ማደራጀት ።

የደቡቡን የጦር ሠራዊታችንን በቀኝና በግራ በመሃል አድርገን በሦስት ክፍል አደራጀነው።

ለቀኙ ደቡብ ክፍል የጦር ሠራዊት ዋናው አዝማች የሐረርን መስፍን እንደራሴ ደጃዝማች ነሲቡን አድርገን ፣ ለርሱ ረዳቶች ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤልንና ደጃዝማች ዓምዴን ፡ ደጃዝማች አበበ ዳምጠውንና ደጃዝማች መኰንን እንዳልካቸውን ጨመርንለት። ደግሞ ጄኔራል ውሂብ ፓሻ የተባለ የቱርክ ተወላጅ የሆነ ሰው ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የግፍ ጦርነት ለማድረግ መነሣቷን ስለ ዐወቀ እኛ ሳንጠይቀው በፈቃዱ ለመርዳት መጥቶ ነበርና ፣ ለማናቸውም ለጦርነቱ አኳኋን ለደጃዝማች ነሲቡ አማካሪ አድርገን ሰጠነው። ስለ ሕክምናው ሥራ አዲስ አበባ በተፈሪ መኰንን ስም በቆመው በአሜሪካ ሚሲዮን ሆስፒታል ይሠራ የነበረው ዶክቶር ሆክ ማን ቈስለኞችን ለማከም ወደደጋህቡር ለመውረድ ፈቃዱመሆኑን በኢትዮጵያ ሕዝብ የቀይ መስቀል ማኅበር በኩል ስለ አስታወቀ ፣ ለጊዜው እርሱ ብቻ ወረደ። በኋላ ግን ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ እርዳታ በምስር ከተማ በካይሮ የቀይ መስቀል ማኅበር ቆሞ ነበርና ፣ ፕሪንስ እስማኤል ዳውድ የተባለው ከቤተ መንግሥት ትውልድ ያለው ሰው ከማኅበሩ ተልኮ ከ20 የሚበዙ ሐኪሞችና ረዳቶች ይዞ ከሙሉ አምቡላንስ ጋራ መጥቶ ነበርና እርሱ በቀኝ ደቡብያለውን የጦር ሠራዊት በማከምእንዲረዳ ተደረገ።

ለግራው ደቡብ ክፍል የጦር ሠራዊት ዋና አዝማች ራስ ደስታን አድርገን ፣ ለርሱ ረዳቶች ደጃዝማች ገብረ ማርያምንና ደጃዝማች መኰንን ወሰኔን ፡ ደጃዝማች ደባይ ወልደ አማኔልን ፡ ፊታውራሪ ታደሰ ገነሜን አደረግን። ለሕክምናውም ሥራ ለጊዜው ከሱዳን ማኅበር ተልኮ የወረደው ዶክቶር ሆክማን የቦምቡን አኳኋን ለመመርመር መዘውሩን እያወላለቀ ሲያይ እንደገና ፈንድቶ ስለ መታው ፣ ወዲያው ሞተና በአይሮፕላን አስመጥተነው አዲስ አበባ ተቀበረ።

በቆራሔ ያስቀመጥነው የጦር አለቃ ጀግናው ግራዝማች አፈ ወርቅ ለመታኰሻና ለአይሮፕላን ቦምብ መከላከያ እንዲመች መሬቱን እያስቆፈረ ደኅና አድርጎ መሽጎት ነበር። ስለዚህ የኢጣልያ ወታደሮች ሁለት ጊዜ ቢመጡ ሁለት ጊዜም ድል እያደረገ መለሳቸው። ኢጣልያኖችም በቆራሔ ከግራዝማች አፈ ወርቅ ጋራ ፊት ለፊት ተጋጥመው የእግር ጦርነት ለማድረግ የማይችሉ መሆናቸውን ከተረዱት በኋላ በአይሮፕላን እየተመላለሱ የቦምብ ዝናብ ያዘንቡበት ጀመር። አንድ ጊዜ 300 ቦምብ ጣሉበት። ግን የጥንቃቄውን ትእዛዝ ያልጠበቁትን 5 ሰዎች ከመግደልና 15 ሰዎች ከማቁሰል በቀር ብዙ ጉዳት አላደረገም ።

በጥቅምት 23 ቀን 20 አይሮፕላኖች እንደ ገና ተመልሰው መጥተው ቦምብ ሲጥሉ ጀግናው ግራዝማች አፈ ወርቅ በኦርሊኮን ተኩሶ አይሮፕላንለማውረድ ሲያነጣጥር ባጠገቡ የወደቀው የቦምብ ፍንጣሪ እግሩን መትቶ አቈሰለው። ከቈሰለም በኋላ ጀግንነቱ እያበረታታው የቀኑስሉን ሕመም ታግሦ ሥራውን ይሠራ ጀመር ።

ነገር ግን ጥቂት ከቆየ በኋላ ኃይሉ መድከሙንና ለመተጕኩስ አለመቻሉን ስለ ዐወቀ አንሥኝ ብሎ ወደ ማረፊያው ስፍራ ወሰዱት። ሐኪምም ያለበት 220 ኪሎ ሜትር ያህል በሚርቅ በደጋህቡር ነበርና ወደዚያ እንዳይሔድ ወታደሮቹ ይበተናሉ ብሎ ስለ ሠጋ ፣ በዚያው እንደ ሆነ እኔ በብርቱ ቈስያለሁና ምናልባት የሞትሁ እንደ ሆነ በእኔ ምትክ ቆራሔ ላይ የጦር አለቃ በፍጥነት ይላኩ ብሎ ወደ ዋናው የጦር አዝማች ወደ ደጃዝማች ነሲቡ በራዲዮ ቴሌግራም አስታወቀ ።

ደጃዝማች ነሲቡም ለቆራሔ የጦር አለቃ ፊታውራሪ ዻንጉል ኩላሴ የሚባለውን ላከው። ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕትንም ለማሳከም ወደ ደጋህቡር ሲወስዱት በመንገድ ዐረፈና ደጋህቡር ባለው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ቀበሩት።

በዚህም ጊዜ አንድ ኢንቴርዬር ሚሲዮናዊ ሐኪም በፈቃዱ ለመርዳት እሔዳለሁ ብሎ ወደ ሲዳሞ ሔደ በኋላ ግን የስዊድን የቀይ መስቀል ማኅበር ዶክቶር ሂላንደርን ዋና አድርጎ ሐኪሞችና ረዳቶች ከሙሉ አምቡላንስ ጋራ ስለላከ እነርሱ ወደ ግራ ደቡብ እንዲሔዱ ተደረገ።

ለመሃል ደቡብ ክፍል የጦር ሠራዊት ፣ ደጃዝማች በየነ መርድን ዋና አዝማች አድርገን ለርሱ ረዳቶች በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማን ፡ ፊታውራሪ አጥናፍ ሰገድ ወልደ ጊዮርጊስን ፡ ቀኛዝማች አስፋው ወልደ ጊዮርጊስን ፡ እንደዚሁም ከጠላት ጋር ሆነን አገራችንን አንወጋም ብለው ኢጣልያንን ከድተው የመጡትን ቀኛዝማች ሰላባንና ቀኛዝማች አንዶምን ጭምር አደረግንለት። ለሕክምና ሥራ ግን ለጊዜው ሐኪም አልተገኘም ነበርና ለቀስል ማሰር ብቻ ዕውቀት ያላቸው ያገር ልጆች ሔደው ነበር። በኋላም ወደ ራስ ደስታ ከሔዱት ከስዊድን ሐኪሞች ተከፍለው ወደ ደጃዝማች በየነ መርድ እንዲሔዱ ተደረገ ።

ከዚህም በቀር ጦርነቱ ሳይጀመር በቀኝ ደቡብ አውራጆች በደጋህቡርና በቡላሌ ፡በሳሰበኔና በደጋሐመዶ ፡ በቡርቆት ፡ በቆራሔና በሐራዲጌት፣ በቀብሪደሐርና በፋፈን ፡ በጭቆ እና በዋቢ ሸበሌ ፡ በቡርደዴና በተፈሪ ከተማ እነዚህንም በመሰሉት በግራ ደቡብና በመሃል ደቡብ ባሉት ትንንሾች ከተሞች ሁሉ ጥቂት ጥቂት ወታደሮች እየያዙ የሚጠባበቁት የጦር አለቆቹ ሁሉ በየታዘዙበት ስፍራ ሆነው ኢጣልያኖች እየገፉ ሲመጡባቸው እስከሚቻላቸው እየተከላከሉ ሲበረቱባቸው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ትእዛዝ ሰጠናቸው።

ኢጣልያኖች ግን በአይሮፕላን እየበረሩ ከዚህ በላይ በተቆጠሩት በትንንሾቹ ከተሞች ሁሉ የቦምብ ዝናብ ያዘንቡባቸው ጀመር። ነገር ግን የውጋዴን አውራጃ መሬት ድቡሽትና አሻዋማ ስለ ሆነ ከቦምቡ የሚበዛው ሳይፈነዳ በአሸዋ ውስጥ እየተቀበረ ይገኝ ነበር። እንደዚሁም አንድ ጊዜ በደጋህቡር አጠገብ የወደቀው ቦምብ ሳይፈነዳ ተገኘ።

ኢጣልያኖችም እንደ ገና በጥቅምት 24ና 25 ቀን ሃያ ሃያ አይሮፕላን አምጥተው ቦምብ እየጣሉ ቆራሔን በጭራሽ አጠፉት።

በቆራሔም ዙሪያ ከብቶቻቸውን ውሃ ለማጠጣት የመጡትን ሱማሌዎች ከነከብቶቻቸው ገድለው በቆራሔገቡ።

በግራዝማች አፈወርቅ ስፍራ የተተካው ፊታውራሪ ጓንጉል ኰላሴ ኢጣልያኖች ቆራሔ መግባታቸውን ሳይሰማ 500 ያህል ወታደሮች ይዞ ሲገሠግሥ ከሳሰበኔ በስተምሥራቅ ሐነሌይ በሚባል ስፍራ ሲደርስ ፣ የጠመንጃ ተኩስ ስለ ሰማ ወታደሮቹን በፍጥነት በየቁጥቋጦውና በየፈረፈሩ በየሣሩ ውስጥ እየተራራቁ እንዲበተኑ አዘዛቸው ።

ጥቂትም እንደ ቆዩ የኢጣልያ ወታደሮች በካሚዮን እየሆኑ ብዙ ታንክም እያስከተሉ ሲመጡ ባዩዋቸው ጊዜ ወደ ፊት እስቲቀድሙ ዝም ብለው ተኙ። በኋላ ግን በየታንኩ ውስጥ ያሉት ከታንኩ እየወጡ የላላ መኪና ሲያጠባብቁ ፣ በየካሚዮኑም ያሉት እየወረዱ ቀኝና ግራ ፡ ፊትና ኋላ ሲመለከቱ ጓንጉል ምልክት ባሳየ ጊዜ ወታደሮቹ በሮምታ ተኩሰው ሁሉንም ፈጅዋቸው። በዚሁም በጣም በሚያስደንቀው ጦርነት ከጓንጉል ወታደሮች የሞቱት ጥቂት ናቸው። ነገር ግን ጓንጉል ራሱ ቈስሎ ነበርና ወታደሮቹ ወደፊት ለመግፋት ስለአልተቻላቸው በዚያው ቆይተው የድሉን ነገር ለደጃዝማች ነሲቡ አስታወቀ።

ደጃዝማች ነሲቡም ይህን የጀግንነት ሥራቸውን በሰማ ጊዜ ሁለት ካሚዮን ልኮ ቁስለኞቹን ወደ ደጋህቡር አስወስዶ እንዲታከሙ አደረገ ።

በዚህም ድል ውስጥ ከተበላሹት መትረየሶች በቀር አራት ማለፊያ ማለፊያ መትረየሶችና ብዙ ጠመንጃና ጥይቶች ተማርከው ወደ ደጋህቡር ተወሰዱ።

እኛም የግራዝማች አፈወርቅን መሞትና ቆራሔሑም በኢጣልያኖች መያዙን ከሰማን በኋላ ፣ ደግሞ በሰሜን በኩል የመጡት ኢጣልያኖች ከአድዋ ወደ መቀሌ መግፋታቸውን ፣ የመቀሌ ገዥ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣም እናት አገሩን ኢትዮጵያን ፣ንጉሠ ነገሥቱን እኛን ከድቶ ወደ ኢጣልያኖች መግባቱን ስለ ሰማን ፣ የጠቅላይ ጦር

ሰፈራችንን በደሴ አድርገን በሰሜንና በደቡብ ያለውን የጦር ሠራዊት አኳኋን እያዳመጥን ለመቆየት ስለ አሰብን ፣ ወደ ደሴ ከመሔዳችን አስቀድሞ በኅዳር 9 ቀን በአይሮፕላን ወደጅጅጋ ወረድን።

በማግስቱም ስለ ሀገሩ ነፃነትና ስለ ንጉሥ ነገሥቱ ክብር በጀግንነት ሕይወቱን አሳልፎ ለሰጠው ለግራዝማች አፈወርቅ ፣ የደጃዝማችነት ማዕርግ ሰጠነው። ይኸውም ለትውልዱና ለታሪኩ መታሰቢያ ሆኖ እንዲኖር ነው። ወዲያውም ላንዳንድ ሰዎች የጦር አለቅነት ሹመት ሰጠን። በሦስተኛውም ቀን የጦር አለቆችን በሙሉ ሰብስበን ከአይሮፕላን ቦምብና ከሌላውም አደጋ የሚጠበቁበትን ምክር በቃል ነግረን ፣ ወዲያውም ስለዚሁ ቀጥሎ የተጻፈውን የምክር ቃል እንዲታደል አደረግን ።

«የዛሬ ሣ ዓመት የኢጣልያ መንግሥት በግፍ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማጥፋት ስለ ተነሣ በዚያ ጊዜ የነበራችሁት አሁንም በሕይወት ያላቻሁት አርበኞች በአድዋም ያልነበራችሁት በዚያው የነበሩ አባቶቻችሁ ደማቸውን በማፍሰስ አርበኝነታቸውን አሳይተው ያገራቸውንና የርስታቸውን ነፃነት ከጠላታቸው ከኢጣልያ አዳኑ። አሁን የኢጣልያ መንግሥት ያንኑ የዛሬ ፺ ዓመት ድል የሆነበትን ጦርነት ብድር ለመመለስ በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊቱ አልቋልና አለችግር እንዋጋቸዋለን ብሎ ለሕዝቡ ሰብኮ ያልሞታችሁትን እንደ ሞታችሁ አድርጎ ፡ የታወቀውን በዓለም ታሪክ ተጽፎ የሚገኘውን የኢትዮጵያን ልጆች ጀግንነት አዋርዶ ነፃነታችሁን ለማጥፋት ፡ርስታችሁንና ቤታችሁን ለመውረር፣አሮጌ አባትእናታችሁን በባርነት ለመግዛት ፡ ልጆቻችሁን ስደተኞች ለማድረግ ፡ የኢትዮጵያን ጀግኖች እንደሌሉ አድርጎ ለማስቈጠር ፡ በሰሜንም በደቡብም ጦር አምጥቶ ለማጥቃት ጦርነት ጀመረ። የዓለም መንግሥታት ሁሉ ኢጣልያ በኢትዮጵያላይ በግፍ መነሣቷን ዐውቀውሁሉምለኛረዳቶች ሁነዋል ። ኢጣልያየኢትዮጵያአርበኞች ምንም ያለቁ ቢመስላትና ያሉትንም ከምንም ሳትቈጥራቸው ብትቀር በዘራችሁና በኢትዮጵያ ላይ የተደረገባትን ግፍ ጠላታችንን በማሸነፍና በግፍ ከያዙት ግዛታችን በማባረር ጀግንነታችሁን ማደስ የተገባችሁ ዋና ነገር ነው። ሰው ለዘላለም ነዋሪ ሊሆን አልተፈጠረም። መጨረሻውም ከዓለም የሚለየው ሞት ነው። ይህ ሞት ይቀድማል ይከተላል እንጂ ለሰው ልጅ ሁሉ አይቀርለትም። ከመቃብር በላይ እየሰፈፈ የሚታይ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ መታሰቢያ ሁኖ የሚኖር ስም ነው።

የዛሬ ጣሻ ዓመት በአድዋ ይህ ጠላታችን በተዋጋን ጊዜ የኢትዮጵያ ጀግኖች ድል ስለ መቱት እንኳንስ በሕይወት ያላችሁት በዚያውም የቀሩት ቢሆኑ ስማቸው ሳይረሳ ለዘላለም ሲጠራ ይኖራል። አሁንም ላለው ትውልድ ዋና የሚያኮራ ነው። ደግሞ ለወንድ ልጅ እንኳንስ አገሩንና ርስቱን "የሚቀማ ፡ ወገኑን ወደ ስደት የሚያደርስ ጠላት ተነሥቶበት እንዲያውም ቢሆን ዋና ምኞቱና የሚያኰራው ሞት በጦርነት የሚደርስበት ነው።

ዶሮ እንኳን ጫጩቶቿን ከአሞራ ለማዳን ትተናነቃለች። ይህ ከሆነ በአእምሮም በጉልበትም ብዙ ሺ ጊዜ የሚበልጠው ሰው ምን ያህል ከጠላቱ ጋራ መታገል እንደሚገባው ዕወቁ።

እንግዴህ ለሰው ልጅ ሞት በመጨረሻው የማይቀርለት ከሆነ የማይጠፋ ስሙን ለመትከል አሮጌ አባትና እናቱ፡ ሚስቱ፡ልጆቹ እንዳይሰደዱበትና ዛሬ በነፃ አገራቸው በኢትዮጵያ ተከብረው ሲኖሩ ነፃነት የጠፋ እንደሆነ ይህ ክብራቸው ቀርቶ በውርደት እንዳይወድቁ ለማድረግ የመጣውን ጠላት በመውጋት ሕይወታችሁን ብታሳልፉ ክብራችሁ የቱን ያህል ይሆናል። የከበረ ስማችሁም በልጆቻችሁና በወገኖቻችሁ ዘንድ ሲመሰገንና በዓለም ታሪክ ሲጠራ ይኖራል። ከዚህም ቀደም ጠላታችን ይህነኑ ያጥቂነት አሳቡን ለመፈጸም ማሰቡን ዐውቀን በሰላም ጊዜ የምንገዛችሁ ንጉሥ ነገሥታችሁ በጦርነትም ጊዜ ከመካከላችሁ ሆነን ደማችንን ለማፍሰስ መቁረጣችንን ነግረናችሁ ነበር። ይኸው አሁንም ከናንተ ጋራ አለን።

ኢጣልያኖች ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ቢያበዙ ካወቃችሁበት ምንም ሊጐዷችሁ አይችሉም። አይሮፕላንም የተባለው በሚጥለው ቦምብ ጩኸት ለማስደንገጫና ልብ ለማስነፍ ነው እንጂ ሌላ የሚጠቅም ሥራ አይሠራም። ስለ ዛሬው ዘመን የጦርነት አኳኋን ብዙ ጉዳት ሳያገኛችሁ ጠላታችሁን ለማጥቃት እንድትችሉ በያለቃችሁ በኩል የሰጠናችሁን ምክር መከተል ነው። ላገራችሁ ነፃነት ለመከላከል ፡ በዚህም ባላችሁበት ስፍራበችግራችሁ ሁሉ

በገንዘብም በሥንቅም ችግራችሁን ለማቅለል እርዳታችንን አናጐድልባችሁም። አሁንም ለሀገራቸውና ለወገኖቻቸው ክብር የተገባ ሥራቸውን ሲሠሩ ሕይወታቸውን ላሳለፉ አርበኞች ለወገኖቻቸውና ለቤተ ዘመዶቻቸው ሁሉ ችግር እንዳያገኛቸው ንጉሠ ነገሥትም አባትም ሆነን እንጠብቃቸዋለን። ስለዚህም በያሉቃቸው ስማቸው ተጽፎ እንዲቀርብልን የጦር እንደራሴዎቻችንን አዘናል። እኛም ሕይወታችን እስኪያልፍ ድረስ ዘወትር ከናንተ ጋራ ነን። ኅዳር 10 ቀን 1928 ዓ. ም.»

ስለ ጦርነቱም አደራረግ ወደ መሃል ውጋዴን የወረዱ እንደ ሆነ አገሩ ለሠራዊት የሚበቃ ውሃና ምግብ ፤ለከብትም ሣርና እህል የማይገኝበት ጽኑ በረሃ ስለሆነ ፣ ከጅጅጋ እስከ ደጋሀቡር ባለው አውራጃ እየተዛወሩ ቆይተው የኢጣልያ የጦር ሠራዊት በረሃውን አልፎ መጥቶ ወደነሱ ሲጠጋ ጦርነት እንዲጀምሩ በየጊዜውም የሚሆነውን ሁሉ ጠቅላይ ሠፈራችን ወደ አለበት እየላኩ እንዲያስታውቁን ትእዛዝ ሰጠናቸው ።

ከዚህም በኋላ በአውቶሞቢል ከጅጅጋ ወደ ሐረር ወጥተን በሐረር ከተማ ለተከታዮቻችን የምሳ ግብዣ አድርገን ወደ ድሬዳዋ ወረድን። በማግስቱም በኅዳር 11 ቀን በአይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

# ምዕራፍ 37

## ስለ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ክዳት ።

ኢጣልያኖች በጀግንነት ጦርነት ሳይሆን በአይሮፕላን ቦምብ እየጣሉ አድዋ ከገቡ በኋላ ብዙ የኢትዮጵያ መኳንንቶች ፣ ከንጉሥ ነገሥቱ እየከዱ ወደ እኛ ገቡ እያሉ በዕለት ወሬ ገልጠው ነበር። ይህም ወሬ ሙሉ እውነት አይደለም። እንደ ሀገራችን እንደ ኢትዮጵያ ልማድ የጦር አለቆች ወይም አገረገዥዎች የነበሩ መኳንንቶች ፣ በዕድሜ ሸምግለው ወይም በደዌ ምክንያት ሥራ ለመሥራት የማይችሉሆነው ሹመታቸውን ሲለቁ፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ጥፋት እየተገኘባቸው ከሹመታቸው ሲሻሩ በየርስታቸው ላይ ሆነው እያሳረሱና እያስነገዱ ፣ ወይም እየተጦሩ የሚኖሩ ብዙ ናቸው። እንደዚህ ሆነው ሲኖሩም በቀድሞ የማዕርግ ስማቸው መጠራታቸው አይቀርም።

ኢጣልያኖች ግን እነዚህን የመንግሥት ሥራቸውን ለቀው የሚኖሩትን መኳንንቶች በኃይልም በማስፈራራትም ወደነርሱ እንዲገቡ 'አድርገው ደጃዝማች እገሌ ፡ ፊታውራሪ እገሌ ፡ ቀኛዝማች እገሌ ፡ ከንጉሥ ነገሥታቸው እየከዱ ወደ እኛ ገቡ ፡ አገር ተቀብሎናል ፡ ሕዝቡ ወዶናል እያሉ በራዲዮ መግለጥ ጀመሩ።

ነገር ግን ከትግሬ መኳንንቶች መካከል የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ መክዳት ሐሰት ነው ተብሎ ሊካድ የማይቻል ነው።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ የትግሬው መስፍን የራስ ጉግሣ አርአያ ልጅ ነው። የመስፍንም ልጅ ስለ መሆኑ ልጃችንን ዘነበ ወርቅን አግብቶ ነበር ። ነገር ግን እርስዋን አግብቶ አንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ባለመታደል ሚስቱና አባቴ ተከታትለው ስለ ሞቱ በትልቅ ኀዘን ወድቆ ነበር። እኛ ግን ምንም ሚስቱና አባቱ ቢሞቱ ከማዕርጉ እንዲዋረድ አሳብ አልነበረንምና ያባቱን ግዛት እንደርታን ፣ አጋሜን ፣ ቦራ ሰለዋን ፣ የዕዳ መሆኔንና የሁለት አውላሎን የበላይነት ሰጥተን በዋናው ከተማ በመቀሌ እንዲቀመጥ አደረግን።

አባቴ ራስ ጉግሣና ራስ ሥዩም በትግሬ ባላባትነት እየተቃኑና እየተፎካከሩ ይኖሩ ነበርና ፡ አሁን አባቴ በሰፊው ይዘውት ከነበረው ግዛታቸው እርሱ ገና ልጅ ስለ መሆኑ ሁለት ትንንሾች አውራጃዎች ወደ ራስ ሥዩም ተጨምረውላቸው ነበርና ይህን ምክንያት አድርጎ በአባቴ የተጀመረውን ጠብ ለመፈጸም ሲል ከራስ ሥዩም ጋራ ጠቡን እያጎላው ሔደ።

ኢጣልያኖችም ኢትዮጵያን ለመውሰድ የሚችሉት በጦርነት ኃይል ሳይሆን ትልልቆቹን ሰዎች እርስ በርሳቸው በማጣላት ፣ ከንጉሥ ነገሥቱም በማስከዳት መሆኑን በእቅዳቸው አሰናድተው ያስቀመጡት ነበርና በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴና በራስ ሥዩም መካከል የተጀመረውን ጠብ በሰሙ ጊዜ ከርሱ ጋራ መላላክ ጀምረው ኖሮ ፣ አንዳንድ ሰዎች ይህን ወሬ ቢነግሩን ዐፄ ዮሐንስ የኢጣልያኖች ተቃዋሚ ነበሩና ምንም ቢሆን የዐፄ ዮሐንስ ዘር ነኝ የሚል ሰው ኢትዮጵያን ይከዳል ብለን ባለመጠርጠራችን የተወራበትን ወሬ በመናቅ ተውነው።

እርሱም ይህ የታማበት ነገር እንዳይገለጥበት ምናልባት ኢጣልያኖች በጦር ኃይል የመጠብን እንደ ሆነ በግዛቱ በአጋሜ ላይ ሆኜ እስከ ሞቱ የሚቻለኝን እየሠራሁ እከላከላለሁ እያለ ይልክብን ነበር። ይልቁንም ከሐማሴን ወታደሮች ጋራ ተላልኬ ወደ እኛ እየከዱ እንዲመጡ አድርጉአለሁ እያለ ይልክ ነበር። በኋላም እነዚሁ የተላላክኋቸው ወታደሮች ገቡልኝ ብሎ ስለ ላከ ፣ ሁለተኛም ለታማኝነቱ ምስክር ያደረገው ያባቱን ወንድም ደጃዝማች ከበደ አራጋውን ስለ መከሰሱ ነው። የክሱም ቃል እንደዚህ የሚል ነበር።

«ደጃዝማች ከበደ አራጋው የመንግሥታችን ታማኝ አይደለም። ይህንም የሚያስረዳ ነገር ከኢጣልያኖች ጋራ ይላላካል። የሚላላክበትንም ደብዳቤ አግኝቼ በእጄ አግብቼዋለሁ። ደግሞ ሁለቱን ልጆቹን ወደ አሥመራ ልኮ ከኢጣልያኖች እንዲማሩ አድርጓል። ስለዚህ አይሮፕላን ይላኩልኝና ወደ ግርማዊነትዎ እንዲመጣ ቢሆን ይሻላል።

ይህ ካልሆነ እዚህ ለኢጣልያኖች ፕሮፓጋንዳ እያደረገ አስቸግሮኛል። ደብዳቤውንም ያገኘሁት ከታማኙእጅ በገንዘብ ገዝቼ ነው ። »

እኛም የነገሩን እርግጥነት ለማወቅ ስንል ደብዳቤውን ላክልን ብለን ከላከልን በኋላ ደጃዝማች ከበደን በአይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ አስመጣ ነው። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ይህን ሁሉ በማድረጉ የተጠረጠረበት ሁሉ የሐሰት መስሎን ነገሩን ችላ አልነው።

ነገር ግን ኢጣልያኖች በአድዋና በአጋሜ በኩል መግባታቸው በተሰማ ጊዜ ከሐማሴን ወደ እኛ ወገን እየከዱ የመጡትን ሰዎች መሣሪያቸውን እየቀማ አሰራቸው ማለትን ሰማን ።

ቀጥሎም ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ረዳቶች እንዲሆኑ በማለት ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን ዋና አድርገን ደጃዝማች ቦጋለ ብሩ፣ ደጃዝማች ደስታ ዳንጉል፣ ደጃዝማች ዓለማየሁ ደስታ፣ ደጃዝማች ተፈሪ ወልዱ፣ ደጃዝማች በላይ ማሩ፣ ደጃዝማች ዳምጠው ወልደ ተክሌ፣ ደጃዝማች እጅጉ ከበደ፣ ፊታውራሪ መስፍን ዘለቀ፣ ፊታውራሪ ተበጀ ተክሌ የተባሉትን ወደ መቀሌ ልከናቸው ነበርና እነሱ በመቀሌ አጠገብ ሰፍረው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌግራም አሳለፉልን።

«ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ያመኗቸው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ እናታቸውን ኢትዮጵያን አባታቸውን ጃንሆይን ከድተው ወደ ኢጣልያ መግባታቸውን በዐዋጅ አስታወቁ። ስለዚህ መላ ኢትዮጵያን እይዛለሁ ብሎ የመጣውን ኢጣልያን የዋግ ጦር ብቻ መቀሌ ላይ ተዋግቶ አይመልሰውምና እንደ ተቻለ አንጋች ጦር ቢመጣልን መልካም ነው። »

ወዲያውም ከርሱ መኳንንቶች ብዙዎቹ ለሃይማኖታቸውና ለታሪካቸው ሲሉ ከኢጣልያ ጋራ ሆነን ንጉሠ ነገሥታችንን አንወጋም ኢትዮጵያንም ለባዕድ አሳልፈን አንሰጥም እያሉ እየተዉት ወደ እኛ በመምጣታቸው የመከዳቱን ነገር እርግጥ መሆኑን ተረዳነው። ቢሆንም ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አገሩን ከድቶ ወደ ኢጣልያኖች የገባበትን ምክንያት ከእርሱ ከድቶ ወደ እኛ የመጣው ታማኙ የነበረ አሽከሩ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ነግሮናል።

«ጌታዬ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ለመታከም ወይም ወደ አዲስ አበባ በመርከብ ለመሔድ አሥመራ ሲገቡ ፡ ኢጣልያኖቹ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት አንሥተን ራስ ሥዩምን አጥፍተን አንተን ባባትህ አልጋ አስቀምጠን የሙሉ ትግሬ ንጉሥ እናደርግሃለን እያሉ ይነግሩዋቸው ስለ ነበረ ፡ የመድፋቸውን የመትረየሳቸውን የአውሮፕላናቸውን ብዛት ፡ የጠመንጃውን አዲስነት ያሳይዋቸው ስለ ነበረ ፡ ባንድ ወገን ሙሉ ትግሬን ለማግኘት ተስፋ ስለ ሰጧቸው ፡ በሁለተኛውም ወገን በዕድሜ ልጅ ናቸውና የኢጣልያኖችን የጦር መሣሪያ ብዛት በማየታቸው ስለ ፈሩ ነው ። » እያለ ይነግረን ነበር።

ይህም እላይ ካልነው ጋራ እርግጥ መሆኑን የሚያስረዳ ነገር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ከድቶ ከነርሱ ጋራ ሲቀላቀል ጀኔራል ዲቦኖ በግርማዊ ንጉሥ ቪክቶርና በመሪው በሙሴ ሙሶሊኒ ፈቃድ ከአላውሃ በመለስ ትግሬን በሙሉ ሰጥተን ራስ ብለንሃል ብሎ ዐዋጅ ነግሮለት ነበር። ጉዳያቸው ከተፈጸመላቸው በኋላ ግን ሙሉ ትግሬ ይቅርና ያባቱን ቤት መቀሌን እንኳ አልሰጡትም።

ኢጣልያኖች ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴን ካስከዱ በኋላ ሌሎችም መኳንንቶች እየከዱ የሚገቡላቸው፣ የወታደሮቻችንም ልብ በዚህ ምክንያት የሚሸበር መስሏቸው ነበር። ነገር ግን መኳንንቱም ወታደሩም ፡ ይህ ያስቆሮቱ የይሁዳ ወንድም እያሉ እርሱን ከመስደብና ከመጥላት በቀር በርሱ መከዳት የደነገጠና የፈራ የለም ።

እርሱም መከዳቱን ባስታወቀ ጊዜ የእኛ የጦር አለቆች ወደ መቀሌ ተቃርበው ነበርና የርሱ መኳንንትና አሽከሮች ከእኛ የጦር አለቆች ጋራ እየተላላኩ እጁን ሊያሲዙት ቆርጠው ነበርና እርሱ ይህን በሰማ ጊዜ በመስከረም 30 ቀን ከሌሊቱ በ7 ሰዓት ከመቀሌ ወጥቶ እስከ አምሳ የሚሆኑ አሽከሮች ብቻ አስከትሎ በፅዳጋ ሐሙስ በኩል ሔዶ

ከኢጣልያኖች ጋራ ተቀላቀለ። እነዚያንም ከኢጣልያ እየከዱ የመጡ ሐማሴኖች በመቀለ እያሰረ አስቀምጧቸው ነበርና እርሱ ሸሽቶ ካመለጠ በኋላ ከእስር ቤት እየወጡ ከእኛ ሰዎች ጋራ ተቀላቀሉ።

ከኢጣልያኖችም ጋራ ከተደባለቀ በኋላ የገዛ አሽከሮቹንና ባላገሮቹን ስለ ፈራ አንድ ጊዜ መቀሌ ፡ አንድ ጊዜ አጋሜ ፡ አንድ ጊዜ ዕዳጋ ሐሙስ ፡ አንድ ጊዜ አድዋ እየተዛወረ እንደ ነፍሰ ገዳይ ፡ እየተገላመጠና ነፍሱን እየጠበቀ ፣ ጦርነቱ እስቲጨረስ ቆየ እንጂ ባንድ ስፍራ እንኳ ከእኛ ወታደሮች ጋራ ጦርነት ገጥሞ አልተዋጋም። የከዳተኛነቱንም ታሪክ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ይቅርና የውጭ አገርም ታሪክ ጸሐፊ ይዘነጋዋል ብለን አንጠረጥርም። እናቱንም የሚከዳ ለሞግዚቱ ይጠቅማል ተብሎ አይታሰብም።

# ምዕራፍ 38

## ወደ ደሴ ስለ መሔዳችን ።

የሰሜኑንና የደቡቡን የጦር ሠራዊት ካደራጀን በኋላ ፣ እኛም ስለ ሀገራችን ነፃነት በጦር ሠራዊታችን መካከል ተገኝተን መከላከል የሚገባ ሥራችን ስለ ሆነ የክብር ዘበኞቻችንን ባለቃቸው በቀኛዝማች መዙሪያ ባንቲርጉ አዛዥነት ፡ የመሃል ሰፋሪ የሚባለውን ጦር በለጋባ ጣሰው አዛዥነት እንዲቀድሙ አድርገን ፡ እኛ በኅዳር 18 ቀን 1928 ዓመተ ምሕረት ከአዲስ አበባ ተነሥተን ወደ ደሴ ተጓዝን። ዋና አሳባችንም የከተት ዐዋጅ አስነግረን ነበርና የሩቅ የዳር አገሩ እስቲከት ለቀደመው ጦር ደጀን ሆነን ደሴ ላይ ለመቆየት ነው።

ከእኛም ጋራ የነበሩ የጦር አለቆች ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል፣ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ፣ ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል ሐዋስ፣ ደጃዝማች አደፍርሰው ይናዱ፣ ደጃዝማች ወንዲራድ ድፋባቸው፣ ቀኛዝማች በልሁ ደገፉ፣ ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ወልደ ገብርኤል ናቸው።

ደሴም ከደረስን በኋላ ኢጣልያኖች እኛን ለማዘንጋት ስለ አሰቡ ፡ ስምንት ቀን ያህል በአይሮፕላን ሳይመጡ ቆይተው ነበር። የጦር ሠራዊቶቻችን ገና ከአዲስ አበባ ሳንነሣ ስለ አይሮፕላን ጥንቃቄ የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዲያደርጉ ስለ አስታወቅናቸው ሁሉም በየሰፈራቸው መሬቱን እየቆፈሩ ዋሻ እየሠሩ በጥንቃቄ ይጠብቁ ጀመር። ከዚህም በኋላ በኅዳር 26 ቀን ዓርብ ጧት በድንገት 21 አይሮፕላኖች መጥተው ቦምብ ያዘንቡብን ጀመር። ወዲያውም የጦር ሠራዊቶቻችን መከላከያ ስለሌላቸው እንዳያልቁ ብለን በፍጥነት በየዋሻው ውስጥ እንዲገቡ ትእዛዝ አሳልፈን እኛ ኦርሊኮን የሚባለውን የአውሮፕላን ማውረጃ መድፍ ጠምደን ተኩስ ጀመርን። ዳሩ ግን አይሮፕላኖቹ የሚበሩት በጣም ከፍ ብለው ስለ ሆነ በዚያ ቀን ለመምታት አልተቻለም።

እንደሚጥሉት ቦምብ ትልቅነትና ብዛት በደሴ ከተማ የሰው ዘር የሚተርፍ አይመስልም ነበር። ነገር ግን ከጣሏቸው ቦምቦች የሚበዙት ሳይፈነዱ ስለ ቀሩ የሞቱት 20 ሰዎች ፣ የቆሰሉ 100 ይሆናሉ። ደግሞ 50 ያህል የሣር ቤቶች ተቃጠሉ እንጂ በዚህ ቀን ሌላ ትልቅ ጉዳት አላደረጉም። ይልቁንም በየቤተ ክርስቲያኑ ላይ የወደቁት ቦምቦች እየተንከባለሉ ከመውረድ በቀር ትንሽም ጉዳት ሳያደርጉ ስለ ቀሩ ሕዝቡ ሁሉ አደነቀ። ከዚህም በኋላ አንዳንድ ጊዜ ተራውን ፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እያሠለሰ ይመጣ ጀመር።


አንድ ቀን ግን በጥር 7 አንድ ትልቅ የጦር አይሮፕላን መጣና ቦምብ ይጥላል ብለን ስንጠባበቀው መጀመሪያ ጭስ ሲወጣ ታየ ፡ ቀጥሎ አይሮፕላኑ ተቃጥሎ ኖሮ በውስጡ ያሉት በፓራሹት ሲወርዱ በገደል ውስጥ ስላረፉ ሁሉም ሞተው ተገኙ አይሮፕላኑም ተቃጠለ።

በደሴም ሳለን ላቫልና ሖር ስለ ዕርቅ ብለው ያቀረቡትን አሳብ አዲስ አበባ ያሉት የእንግሊዝ ሚኒስትር ሰር ሲድኒ ባርቶንና የፈረንሳይ ሚኒስትር ሙሴ ቦዳር «ለኢትዮጵያ መንግሥት አቅርበን እንድናሳይ ከመንግሥታችን ታዘናል ፣ ይህንም የኢትዮጵያ መንግሥት ቢፈቅድ ይቀበለዋል እንጂ የግዴታ ነገር የለበትም» ብለው ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ለብላቴን ጌታ ኅሩይ ስለ አቀረቡለት እርሱ ዕለቱን በቴሌግራም አሳለፈልን ።


የምስተር ሖርና የሙሴ ላቫልም አሳብ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

«ሀ/ ትግሬ ፡ ከምሥራቅ ትግሬ አገር ለኢጣልያ የሚለቀቀው ፡ በደቡብ በኩል በግባ ወንዝ አጠገብ ቀረብ ብሎ ተወስኖ ፡ በምዕራብ በኩል ከሰሜን ወደ ደቡብ በሚወስደው መስመር በአክሱምና (ይህ ማለት አክሱም ወደ ኢትዮጵያ ሆኖ) በአድዋ መካከል (አድዋ ወደ ኢጣልያ ወገን ሆና) የሚያልፈውን ተከትሎ ነው።

ለ/ በደንከል አገርና በኤርትራ መካከል ያለውን ወሰን ስለ ማቃናት። የአውሳ ወሰን መስመር ወደ ደቡብ ወደ ኤርትራ መሬት ዝቅ ብሎ ተከፍሎ ለኢትዮጵያ ወደ ባሕር መውጫ መንገድ መስጠት አስፈላጊ ነው።




ለመዠመሪያ ጊዜ ወዳገራችን የመጣውን አውሮፕላን ስንጐበኝ



ቢትወደድ መኰንን ደምሰው ወደዘመቻው ለመሄድ በፉከራ ሲሰናበተን።

NIGUSS DIGITAL LIBRARY

ሐ/ በውጋዴንና በኢጣልያ ሱማሌ መካከል ያለውን ወሰን ስለ ማቃናት። - ኢትዮጵያ ኬንያና የኢጣልያ ሱማሊያ የነዚህ የሦስቱ አገሮች ወሰኖች ከሚገናኙበት ማዕዘን ላይ አንሥቶ የኢጣልያና የኢትዮጵያ አዲሱ ወሰን እንደሚከተለው ይሆናል። ጠቅላላውን የሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ይዞ ዋቢ ሸበሌን ቆርጦ ወደ ኢዲዶሌ ያልፋል። ቆራሔን ወደ ምሥራቅ ፣ ወራንደብን ወደ ምዕራብ ትቶ ከብሪታንያ ሱማሌ አገር ወሰን ጋራ በ45ኛው ሜሪዲያን መገናኛ ይጋጠማል።

በዚህ አወሳሰን ለኢጣልያ በሚሰጡት መሬቶች ውስጥ በሚገኙት የግጦሽ ስፍራዎችና ውሃዎች እንዲገለገሉበት ለእንግሊዝ ሱማሌ አገር ነገዶች ያላቸው መብት ተጠብቆ ይኖራል ።

መ/ ኢትዮጵያ ወደ ባሕር መውጫ ጠረፍ ከሙሉ የገዥነት መብት ጋራ ታገኛለች። ይህም የባሕር መውጫ ኢጣልያ በምትስማማበት ስፍራ በፈረንሳይ ሱማሌ አገር ወሰን በኩል በቀጭኑ ከሚወርድ ለወደብ መድረሻ ከሚስማማ መሬት ጋራ በአሰብ ጠረፍ ላይ ይደረጋል ።

ዩናይትድ ኪንግደምና የፈረንሳይ መንግሥት ኢትዮጵያ በምታገኘው መሬት ውስጥ በነርሱ ላይ የተባለውን በባርያና በመሣሪያ ማስተላለፍ ነገር ግዴታዋን ስለ መፈጸምዋ መያዣ ያለው ነገርን ለማግኘት ይደክማሉ።

የዚህ ክፍል መሬት ወሰኖችም እንዲህ መሆን አለባቸው። በምሥራቅ በኩል በኢትዮጵያና በኢጣልያ ሱማሌ አገር መካከል የተቃናው ወሰን ፡ በሰሜን 8ኛው ፓራሌል ፡ በምዕራብ 45ኛው ሜሪዲያን ፡ በስተደቡብ በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል ያለው ወሰን ነው።

የኢትዮጵያን አብዛኛውን ክፍል በያዘ በዚህ በተከለለው መሬት ውስጥ ኢጣልያ በአንድ ኩምፓንያ ፡ ወይም በሌላ በማናቸውም ዝግጅት ዓይነት መተዳደር ያለበትን የተገለለ የኤኮኖሚክ መብት ታገኛለች። ወደዚሁም የሚቆጠረው የተገኘው የአገር ተወላጆችና የውጭ አገር ዜጎች ተገዢ ፡ ባልተያዙት መሬቶች ላይ የባለቤትነት መብት ፡ የማዕድን ማውጣት ሞኖፖል፡የደኖች ፤ይህን የመሰለውም ነው። ይህ ኦርጋኒዛሲዮን ለአገሩ ኤኮኖሚክ መደርጀት እርዳታ ለመክፈል የተገደደ መሆን አለበት። ከገቢውም አንዱ ክፍል የኅብረት ጠባይ ባለው አኳኋን ለተወላጁ ሕዝብ በበጎ አድራጎት ይሰጣል።

በተከለለው ክፍል አገር ውስጥ የኢትዮጵያው አስተዳደር መቈጣጠር ከሕዝቦች ማኅበር እንደተሰጡት የእርዳታ ሥራዎች አቅድ በንጉሠ ነገሥቱ ገዥነት ሥር የለመደ (የተገራ) መሆን አለበት። ንጉሠ ነገሥቱም በመላው የሐበሻ አገር ላይ የተስፋፋ እንዲሆን ቀደም ብለው ተቀብለውታል። በነዚህ ሥራዎች ውስጥ ግን በዋና አማካሪ በሚደረግ ቀጥታ ተቈጣጣሪነት ሥር ላይ ኢጣልያ ያመዘነ ችሎታ ያላት ትሆናለች። የተባለውም ዋና አማካሪ የኢጣልያ ተወላጅነት ያለው ሆኖ ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ለመርዳት ከሕዝቦች ማኅበር ተመርጦ ለሚሰጠው የበላይ አማካሪ ስለ ተነገሩት ጉዳዮችረዳት ይሆናል። የበላይ አማካሪው ለኢትዮጵያ ጕረቤት (አዋሳኝ) ከሆኑት ከኃያላኑ ዜጋ እንዲሆንም ፣ የእርዳታቸው እቅድ ሠራተኞች በዋናው ከተማም እንደ ተከለለው መሬት ሁሉ ፡ የኢጣልያ ዜጎች ኑሮና ነፃ የሆነው የውጥናቸው መስፋፋት እንዲጠበቅ አስፈላጊ ጉዳይ አድርገው መመልከት አለባቸው።

የዩናይትድ ኪንግደም መንግሥትና የፈረንሳይ መንግሥት የሐተታው ዝርዝር በሕዝቦች ማኅበር የሚደራጀው ይህ ድርጅት የኢጣልያንን ጥቅሞች በዚህ ወረዳ በሙሉ እንደሚጠብቁ ለማረጋገጥ በመፍቀድ ይደክማሉ።

ይህንንም የምስተር ሖርንና የሙሴ ላቫልን አሳብ ከመረመርን በኋላ የዓለም መንግሥታት ማኅበር በፍርድ ተቀበሉ ቢል ከሦስት ሺ ዘመን የሚበልጥ በነፃነቷ ጸንታ የቆየችውን አገራችንን በፈቃዳችን ለኢጣልያ አንለቅም በማለት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መቃወሚያ ፓሪስ ባለው ሚኒስትራችን አማካይነት ለዓለም መንግሥታት ማኅበር እንዲያስታውቅ አደረግን ።

«ቃል ኪዳን አፍራሹ መንግሥት ካጠቃው አገር ከፍተኛውን ክፍልና በዓለም ማኅበር ሽፋን ሥር ሆኖ የቀረውን አገር ፣ አስፈጻሚነት ካለው መቈጣጠር ጋራ እባክህ ተቀበል ተብሎ በማኅበሩ መለመኑ ፣ ከቃል ኪዳኑ ጋራ የሚስማማ ነውን? የጠላት ምኞቱ የተጠቃውን ወገን ፈጽሞ ለማጥፋት መሆኑ የማይናወጥ እውነት ሆኖ ሳለ ፡-- ጠቅላላው ጉባኤ እንዳወቀው ሁሉ፡-- የኪዳኑን ሥርዓት የፈጸመችው የተበዳይነት መሥዋዕት የሆነችው አገር፣ አጥቂውን እሺ ብላ እንድትቀበልና ለዓለም ሰላም ሲባል ነፃነትዋን ፡ የግዛትዋንም መብት የሚቃወመውን ኃይለኛ ጠላትዋን መከላከልን እንድ ትለቅ በማኅበሩ ልትጠየቅ ነውን ? ተጠቂዋ አገር ማኅበሩ ሊከዳኝ ነው ብላ የማኅበሩ መክዳት ሥጋት እንዲያድርባትና አዳኝ የማግኘት ተስፋ እንድታጣ ሊደረግ ነውን ? መልካቸው ዘራቸው ኃይላቸው ማናቸውም ዓይነት ቢሆን፣በሕዝብ መካከል ላለው ለወደ ፊቱየኢ ንተርናሲዮናል ዝምድና ዋና ጉዳይ የሆነው ይህ ነገር ፣ ከሁሉ አስቀድሞ በማኅበሩ ፊት እንዲቀርብና በሙሉ ነፃነት በመላው ዓለም ዓይን ፊት በግልጽ ሊመረመር አይገባውምን?»

# ምዕራፍ 39

## በደሴ ሳለን ጀኔራል ዲቦኖ ተሽሮ ማሬሻል ባዶሊዮ መሾሙን ስለ መስማታችን ።

ዋናው የጦር መምሪያችን ገና በደሴ ሳለ ፣ የኢጣሊያ የጦር አበጋዝ የነበረው ጀኔራል ዲቦኖ ተሽሮ ማሬሻል ባዶሊዮ መሾሙን ሰማን። ምክንያቱም ከኛ ጋራ በደሴ የነበሩ አንዳንድ ባለጋዜጦች እንደነገሩን ፣ ጀኔራል ዲቦኖ ኢጣሊያ ተከላካይ እንድትሆን እንጂ ጦርነት ጀማሪ እ ንድት ሆን ሳይፈቅድ ጦርነቱን ጀምር የሚል ትእዛዝ ስለ መጣበትና ስለ ጀመረደስ አላለውም ነበርና ጦርነቱን ችላ ስለ ማለቱ ነው ይባላል ።

ይህም እውነት መሆኑን የሚያስረዳ ጀኔራል ዲቦኖ የጦር አበጋዝነቱን ተሽሮ ከተመለሰ ወዲህ በጻፈው መጽሐፉ ፣ «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጦርነት ጀማሪ ለመሆን ስላልፈለጉ ፣ በጸሎትና በጾም ቆይተዋል ይባላል እንደምን ላድርግ ብዬ ብጠይቅ ንጉሠ ጦርነት ለመጀመር ባይፈልጉም አንተ አደጋ ጥለህ ውጋቸው የሚል ትእዛዝ መጣልኝና ጦርነቱን ጀመርሁ» ይላል።

ሁለተኛም ጀኔራል ዲቦኖ ጦርነቱ በቶሎ እንዳይጀመር ስላሰበ ጦርነቱን ለመጀመር የሚበቃ ገንዘብ የለኝም ብሎ ቢያመለክት ፣ የሚያስፈልገው ገንዘብና ወታደር ይላክልሃል የሚል ምላሽ መጣለት ይላል። ይኸውም ጀኔራል ዲቦኖ በጻፈው በጦርነቱ መጽሐፍ በመቅድሙ ላይ ሙሶሊኒ ስለፈረመበት የኢጣሊያ ወገን የሆነ ሁሉ ሐሰት ነው ብሎ ሊክደው አይችልም።

ደግሞ አንዳንድ ሰዎች እንደ ነገሩን ጀኔራል ዲቦኖ ሐበሾችን በተለመደው ጦርነት በመድፍና በመትረየስ ፡ በጠመንጃ ተዋግቸድል ለማድረግ እችላለሁና ፣ መከላከያ የሌላቸውን ሕዝቦች በጋዝ ጪስና በሰናፍጭ መርዝ ተዋግተን ድል ብናደርጋቸው የፋሺስትን ታሪክና ክብር የሚያጠፋ ይሆናልና ባናደርግ ይሻላል የማለት አሳብ ስለ ነበረውና ስለ ተናገረም የተሻረው በዚህ ምክንያት ነው ይባላል ።

ከዚህም በኋላ ከሰሜኑ የጦር ሠራዊታችን ጋራ መገናኛው ሁሉ ፡ ስልኩም ራዲዮኑም በቦምብ ስለ ተበላሸ በተምቤን በኩል የራስ ካሣና የራስ ሥዩም ፡ በሽሬም በኩል የራስ እምሩና የደጃዝማች አያሌው ፡ በአላጉም በኩል የራስ ሙሉጌታ ወሬና አኳኋን ስለ ጠፋብን ፣ ወደ ፊት ለመግፋት ቁርጥ አሳብ አደረግን። ነገር ግን ከዚህ ቀድሞ መላልሰን እንዳስረዳን እኛ ባንድ ወገን የዓለምን ሰላም እንጠብቃለን በማለት ፡ በሁለተኛውም ወገን የዓለም መንግሥታት ማኅበርን ቃል ኪዳን በመተማመን ፡ በሦስተኛውም ወገን ያዲሱን ዘመን የጦር መሣሪያ ለመግዛት የሚበቃ ገንዘብ ስለሌለን ብድርም ብንጠይቅ ስለ ተከለከልን በመሣሪያ ነገር በጣም ተቸግረን ነበር ።

ከሕዝባችንም ላይ በእርዳታ በተገኘው በጥቂቱ ገንዘብ መሣሪያ ለመግዛት ብንጠይቅ በዓለም መንግሥታት ማኅበር የገቡት መንግሥታት ሁሉ ለኢትዮጵያም ለኢጣልያም የጦር መሣሪያ ካገራችን እንዲሸጥላቸው አንፈቅድም ብለው ከለከሉን ።

ይህም ነገር ለሰሚው ሁሉ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ኢጣልያ ልዩ ልዩ መሣሪያ የፈቀደችውን ያህል የምትሠራበት ፋብሪካ አላት። ኢትዮጵያ ግን የጦር መሣሪያ ፋብሪካ አልነበራትም። ስለዚህ ኢትዮጵያንና ኢጣልያን አወዳድሮ ሁለታችሁም ካገራችን የጦር መሣሪያ አትገዙም ማለት ትክክለኛ ነገር አልነበረም።

ደግሞ ከጦርነቱ አስቀድሞ ያገርን ጸጥታ ለመጠበቂያ መሣሪያ እንድንገዛ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ከኢጣልያም ጋራ በፓሪስ ላይ ተዋውለን በዚህ ምክንያት ተገዝቶ የቆየ መሣሪያ ነበርና ላሁኑ ችግራችን እንዲደርስልን አስመጥተነው ጅቡቲ ሲደርስ የፈረንሳይ ሱማሌ ገዥ በባቡር እንዳይጫን ስለ ከለከለ ወደ ፓሪስ አስታውቅልን ብለነው ነበርና ከመንግሥቱ ምላሹ አልመጣልኝም እያለ በማቆየቱ ምክንያት ላሁኑ ችግራችን የማይደርስ መሆኑን ስለ ተረዳነው ፣ ይመጣል ብለን መጠባበቃችንን ትተን ወደ ኮረም ለመጓዝ ግዴታ ሆነብን። በኋላ ግን ጦርነቱ

ሊጨረስ ጥቂት ሲቀረው በባቡር ለመጫን ተፈቅዶላችኋል ተባለና ግማሹ ገና ድሬዳዋ ፡ ግማሹ አዲስ አበባ ሲደርስ በኢጣልያኖች እጅ ስለ ገባ ለእኛ ሳያገለግለን ቀረ ።

# ምዕራፍ 40

## የጦር ሠፈራችን ገና በደሴ ሳለ በራስ ደስታ ግምባር የጦሩን መፈታት ስለ መስማታችን ።

በስተግራ ደቡብ የጦር አዝማች ያደረግነው አማቻችን ራስ ደስታ ዳምጠው፣ የኢጣልያ ሱማሌ አገር ወሰን ወደሚሆን ወደ ዶሎ ተቃርቦ ነበርና የኢጣልያ ሱማሌ አገር ዋና አዝማች ጀኔራል ግራሲያኒ ፡ ራስ ደስታ ወደ ወሰኑ መቃረቡን በሰማ ጊዜ በውጋዴን በኩል ያቀረበውን የጦር ሠራዊትና ታንኩንም ፡ አይሮፕላኑንም ወደ ራስ ደስታ አዙሮ በሙሉ ኃይል መጥቶ አደጋ ጣለበት። ራስ ደስታም ለቦምብ የተመቸ፣ ለእግረኛ ግን ያልተመቸ ስፍራ ነበርና የጦር ሠራዊቱ የታንኩንና የቦምቡን አደጋ ለመከላከል የማይችል ስለ ሆነ ድል ሆነ። ይልቁንም ደግሞ የራስ ደስታ ሠራዊት የተደናገጠበት ምክንያት ፣ የስዊድን የቀይ መስቀል ሐኪሞች እንደ ደንቡ ከጦርነቱ ስፍራ በጣም ርቀው ሰፍረው ቁስለኛውን ሲያክሙ ኢጣልያኖች የቁስለኛ ማከማቻው ያለበትን ባወቁ ጊዜ በአይሮፕላን እየመጡ በላያቸውም ቦምብ እየጣሉ ድንኳናቸውንና መድኀኒታቸውን የማከሚያ መሣሪያቸውን ሁሉ ምግባቸውም ሳይቀር ማቃጠላቸውን በማየት ነው።

ከሐኪሞቹም አንዱ በዚያው ሞተ። የሐኪሞቹም ዋና መሪ የነበረው ዶክቶር ፍላንዳር በብርቱ ቈቈሰለ። የሚታከሙትም ቀስለኞች በዚያው በድንኳኑ ውስጥ ሲታከሙ በቦምብ እየተመቱ ያለቁ ብዙ ናቸው። የዶክቶር ፍላንደርም መቁሰል በተሰማ ጊዜ አዲስ አበባ በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ያለው የስዊድኑ ሐኪም ዶክቶር ሐነር በአይሮፕላን ሔዶ አምጥቶ አክሞ አዳነው። የቀሩትም ሐኪሞች ባንድ ወገን የጦር አደጋ ስለ ደረሰባቸው በሁለተኛውም ወገን መድኀኒታቸውና የማከሚያ መሣሪያቸው ስለ ተቃጠለባቸው እንደገና መድኀኒትና ማከሚያ መሣሪያም ፡ ድንኳንም ፣ምግብም ለማሰናዳት ወደ አዲስ አበባ መመለስ ግድ ሆኖባቸው ነበርና ቁስለኞቹን ሁሉ እየተዉ ተመለሱ። ይህንንም ሁሉ ለማሰናዳት ጊዜ የሚያስፈልግ ስለሆነ አሰናድተው እስቲመለሱ ኢጣልያኖች ጦርነቱን እያጣደፉ ወታደሩንና ባላገሩን በቦምብና በጋዝ መርዝ እየፈጁ ወደ ፊት ለመግፋት የተመቸ ጊዜ ሆነላቸው። ራስ ደስታም ለአውቶሞቢልና ለካሚዮን ያሠራውን መንገድ ኢጣልያኖች እንደ ያዙት ባወቀ ጊዜ ከሞት የተረፉትን ወታደሮች ይዞ በረሃ ለበረሃ ባቋራጭ መንገድ ገሥግሦ ወደ ነገሌ ደረሰ። በዚያም ያጠራቀመውን ምግብና ሌላም የሥንቅ ነገር ሁሉ ኢጣልያኖች እንዳያገኙት በእሳትእንዲቃጠል አድርጎ ወደ ዋዳራ ወጣ።

ኢጣልያኖች የነገሌን መንደሩንና ቤተ ክርስቲያኑን በቦምብ ካቃጠሉ በኋላ ራስ ደስታ ወዳለበት ወደ ዋዳራ መጥተው ጦርነት አደረጉ። ነገር ግን ስፍራው ዱር ስለ ሆነ ለቦምብ ስላልተመቻቸው ምንም ለማድረግ አልቻሉም ነበርና የስዊድን የቀይ መስቀል ካሚዮን በዚያው ባንድ ስፍራ ቆሞ ስላገኙ የራሳቸውን ጥይት በዚያ ሞልተው የቀይ መስቀል ካሚዮን ጥይት ተጭኖበት አገኘን ብለው ለዓለም ሁሉ የሐሰት ወሬ ያወሩ ጀመር።

ራስ ደስታም በሲዳሞና በባሌ አውራጆች እየተዛወረ ሲከላከል አንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ወደ አሩሲ አውራጃ ገብቶ ነበርና ፣ ጀኔራል ግራሲያኒ ይኸን ሰምቶ በብዙ የጦር ሠራዊት አስከብቦ በአሩሲና በማረቆ ላይ ትልቅ ጦርነት ካደረገ በኋላ ራስ ደስታ በጦርነቱ ውስጥ ተማረከና በየካቲት 16 ቀን 1929 ዓ. ም. ስለ ሀገሩ ነፃነትና ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ክብር በኢጣልያኖች እጅ ተገደለ። ከርሱም ጋራ የነበሩ የጦር አለቆች እነ ደጃዝማች ገብረ ማርያም የሚገባቸውን የጦር አለቅነታቸውን ሥራ እየሠሩ መሞታቸውን ኢጣልያኖች ራሳቸው ይናገሩላቸዋል ።

# ምዕራፍ 41

## <u>ተጨማሪ ጦር ለማደርጀት ዐዋጅ ስለ ማድረጋችን ።</u>

በሲዳሞ የጦር ግንባር ፡ ጠላት ኃይሉን አበርትቶ በታንኩ እየተረዳ በነገሌ በኩል ወዳገር ውስጥ ለመግባት እርምጃ መጀመሩን ስለ ሰማን ተጨማሪ ጦር ተደራጅቶ እንዲሔድ ፡ በደሴ ሳለን ለሕዝባችን የሚከተለውን ቃል በዐዋጅ አስታወቅነው።

«ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት

ዘኢትዮጵያ ።

የሀገራችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣ ኢጣልያ ጠብ ቀስቅሳ ፣ ውል አፍርሳ ወሰን አፋልሳ የዓለም መንግሥታትም የተቀበሉትንና እርሷም ወዳ የፈረመችውን ውል ከምንም ሳትቈጥር የሰላምን ከተማ በመደብደብ ፣ ሕፃናትን ሴትንና ሽማግሎችን በማጥፋት ፡ ቤተ ክርስቲያንን በማቃጠል ፡ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ሕዝብ ብለው ሳይለዩ የሚረዱትን የዓለምን የቀይ መስቀል ማኅበር ፡ የማንንም ሕዝብ ሳትለይ በቦምብ በመግደል በሕግ የተከለከለውንም የጋዝ ጢስ በመጣል ማጥፋት ጀመረች። ይህም አልበቃም ቢላት ባገር ውስጥ ሰላም እንዲጠፋ ፡ እርስ በርሳችን ሁከት እንዲነሣ የሐሰትና የማታለል ቃል ባልታረመ ንግግር እየጻፈችና እየበተነች ታግላ ለመጣል በሚቻላት መንገድ ሁሉ መፈተንዋን ያየኸውና የሰማኸው ነው። በዚህም ነገር እንኳን ያገራችንና የውጭም ሕዝብ ያላዘነና በነገሩ ያልተቈጨ የለም።

በትግሬም ሠራዊታችን በኩል መከላከያ በሌለው ከተማ የምትኖረውን ሴት ለማርከስ ይዞ ቢወስዳት በገዛ ጩቤው ልቡን ወግታ ፡ መሣሪያውን ገፋ በመምጣቷ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ወንዱ ሴቱም ቢሆን ኢጣልያ በሚሠራው ግፍ በንዴት መቃጠሉ ታውቋል ።

ሽማግሌም ፡ ወንድም ፡ ሴትም ለዘመቻ የምትችል በኀዘንና በገንዘብህ እስካሁን እንደ ረዳኸው እርዳኝ። አጥቂና ግፈኛ ከሆነ ጠላታችን ስንከላከል የመጣብን አደጋና ሞትም ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት ለታሪክ በሚዛን የማይገመት ዋጋ የምናገኝበት ነው።

አምላካችንም እስከ ዛሬ ድረስ በወጣው የጦር ሠራዊታችን በገለጠው ኃይል ከኛ ጋራ መሆኑን ያስረዳል። ጠላቶቻችንም ምንም በጉልበት የማይሆንላቸው ቢሆን ብረት በተሸፈነ መሣሪያ በማስፈራራት ፡ የጋዝ ጢስ በመጣል ቢሞክሩም የአርበኛው ጦራችንን ልቡን ለማናወጥ አሳቡን ለመለወጥ አልሆነላቸውም። እስካሁንም በብርታት ከጠላታችን እንደ ተከላከለና እንደገፋ ነው።

ጦርነቱም እንደ ተጀመረ እንዳስታወቅናችሁ ቃል የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ባንድነት ሆኖ የመጨረሻው ጠብታ ደም እስኪፈስ ለመመከት እኛም ከጦር ሠራዊታችን መካከል ለመገኘትና ፈተናውን ለመካፈል ቈርጠን ስለተነሣን ይህነኑ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ መላው ዓለም ተረድቶታል።

አሁንም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆንክ ሥንቅ ለሌለህ ሥንቅ ፡ መሣሪያ ለሌለህ መሣሪያ እሰጥሃለሁና ባውራጃ ባውራጃው በግንባር እየተቈጠርህና እየተጻፍህ ቆይተህ እኔ በማስታውቅህ የጦር አበጋዝ ትዘምታለህና ተሰናድተህ ተቀመጥ። ጥር 12ቀን 1928 ዓ. ም.»

እንደዚሁም በጠላት ኃይል ተጠቅቶ የተጐዳው የሲዳሞ ጦር ሠራዊታችን እንዲበረታና ወታደር ያልሆነውም ሁሉ እንዲረዳ የሚከተለውን ምክርና ትእዛዝ አሳለፍንለት ።

«ይህ ዓለም ኀዘንና ደስታ የተቀላቀለበት ስለ ሆነ ፣ ሰው አንድ ቀን ሲበረታ ፡ አንድ ቀንም ሲደክም ነው። እስከ ዛሬም እበረሃ ወርደህ ለጦር ፡ ለበሽታ ፡ ለቦምብ መመከትህን በየጊዜው ራስ ደስታ አስታውቆኛል። እንኳን ለግዛትህ ለሌላው አገር ተርፈህ ሥራ የምትሠራውን እንዴት ጠላት ሲዳሞን ፡ ወንድ እንደሌለበት አድርጎ ይግባበት ? አሁንም ወደ ፊት እንኳን ወታደር ፣ ወንድ ልጅ ለብረት የደረስህ ፣ ራስ ደስታ አስታወቀህ ድረስ ከትተህ እርዳ። ጥር 19 ቀን 1928 ዓ.ም.»

በባሌ በኩል ላለውም የጦር ሠራዊታችን ይኸው ቃል እንዲተላለፍለት አደረግን። ፡

# ምዕራፍ 42

## ከደሴ ወደ ኮረም ስለ መጓዛችን ።

ከደሴ ተነሥተን ወደ ኮረም ስንጓዝ በየመንገዱ ሁሉ ቦምብ ይዘንምብን ነበር። ይልቁንም በሌሊት ለመጓዝ መንገዱ ወጣ ገባ ስለ ሆነ የጨረቃ ብርሃንም ስላልነበረ በጣም ተቸግረን ነበር።

የጦር ሠራዊታችን ገና ከአዲስ አበባ ሳይነሣ ስለ ቦምብ አደጋ ነገር እንደ ተቻለ ያህል ማስጠንቀቂያ እየታተመ እንዲታደለው አድርገን ነበርና ፣እንደ ማስጠንቀቂያው ቃል በየዱሩ ውስጥ እየተበታተነና እየተደበቀ ስለ ተጓዘ ፣ የቦምቡ አደጋ ሊያገኘው አልቻለም። ኢጣልያኖችም ይህንኑ ዐውቀው በየዱሩና በየጥጋጥጉም ሁሉ ቦምብ መጣል ጀመሩ። ይሁን እንጂ ይህንንም ቢያደርጉ የጦር ሠራዊታችንን ለማግኘትና በብዙ ለመጉዳት አልቻሉም። ስለዚህ አሳባቸውን ለውጠው በየባላገሩ መንደርና በየተሰማራው ከብት ላይ ቦምብ እየጣሉ የባላገሩን ልብ ሰበሩት። ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ በክርስቲያንነቱ የጸና መሆኑን ያውቃሉና ፣ እሑድ እሑድ ካህናቱና መነኩሳቱ ፡ ወንዱና ሴቱ ፡ ሽማግሌውና ሕፃኑ ቅዳሴ ለመስማት ወደ ቤተክርስቲያን ሲሰበሰቡ እየጠበቁ በቦምብ ይፈጁዋቸው ጀመር። በዚህ ምክንያት ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ተቃጠሉ።

ማርሻል ባዶሊዮም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖታዊ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኑ ሲቃጠል ጥልቅ ኀዘን እንዲሰማው ስለ ዐወቀ ፣ ኢጣልያኖች የአረመኔ ሥራ መሥራታቸው እንዳይገለጥ ለማድረግ ሲል የፈረሰውንና የተቃጠለውን ቤተ ክርስቲያን መልሼ እሠራለሁና አይዞህ አትዘን የሚል ቃል ጽፎ በአይሮፕላን መበተን ጀመረ።

ሕዝበ ክርስቲያኑን ከመግደልና ቤተ ክርስቲያኑንም ከማቃጠል በቀር በየቤተ ክርስቲያኑ ብዙ ዘመን የኖሩትን በብራና የተጻፉትን የዕውቀትና የጥበብ ምንጮች የሆኑትን አሮጌዎች የግእዝ መጻሕፍት ማቃጠላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርና ጥበብንና ዕውቀትን መርማሪዎች የሆኑትን የዓለምን ሊቃውንት ሁሉ እጅግ ያሳዝናል።

ኢጣልያ የክርስቲያን መንግሥት ነኝ እያለች የጦር ሠራዊቷ ቤተ ክርስቲያንን መጻሕፍትን ማቃጠላቸው በኋላ ዘመን ክብርዋን የሚያዋርድ ታሪኳን የሚያጠፋ መሆኑን አልተመለከተችውም ይሆናል።

ይህንንም በመሰለው ችግር በየጁ ውስጥ ወልድያ የሚባለውን ከተማ አልፈን ኮረም ደረስን። ኢጣልያኖች ግን ከደሴ ተነሥተን ኮረም እስክንደርስ በአይሮፕላን በጣሉት ቦምብ ብዙ ጉዳት እንዳላገኘን በተረዱት ጊዜ ኤፒሪት የሚባለውን የጋዝ መርዝ በቤርሜል እያደረጉ መጣል ጀመሩ። አንዳንዱ ቤርሜል ቁመቱ ከአንድ ሜትር ይበልጣል። ጎኑም ትልቅ ነው ። ሲወድቅም እንደ ቦምብ ይፈነዳና መርዙ እየተረጨ ባጠገቡ የተገኘውን ሁሉ ይገድላል። ኢጣልያኖች' መከላከያ የሌለውን ጀግናውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በጭራሽ ለማጥፋት አዲስ የወጣውን የፈሪ መሣሪያ ይዘው መቅረባቸው በጣም ያሳዝናል ።

በዚህም የመርዝ መሣሪያ ምንም የኢትዮጵያን የጦር ሠራዊት ቢያጠፉበት መከላከያ የሌለውን ሕዝብ በመርዝ አጠፉት ተብሎ በኋላ ዘመን በታሪክ ሲነገር የኢጣልያን ፋሺስት ለዘለዓለም ኃፍረትንና ውርደትን አሸክሚቸው የሚኖር መሆኑ የማይጠረጠር ነው።

ከዚህም ቀጥለው በአይሮፕላን ላይ ሆኖ መርዝ እንደ ዝናብ የሚረጭ መኪና አበጅተው በጦር ሠራዊታችንና በባላገሩ ፣ በከብቱና በውሃውም በሣሩና በቅጠሉም ፡ በመሬቱም ላይ እንደ ዝናብ ያወርዱበት ጀመር። አወራረዱም በጣም ረቂቅ ስለ ሆነ ለዓይን ጎልቶ አይታይም። ይህንም የመሰለ መርዝ መርጨት ባንድዛፍ ወይም ተክል ውስጥየዛፍ ወይም የተክል በሽታ የገባ እንደ ሆነ የበሽታውን ሚክሮብ ለመግደል ይደረጋል ሲሉ እንሰማ ነበር እንጂ በጦር ሠራዊትና በባላገር ላይ ይፈጸማል ብለን አልጠረጠርንም ነበር።

ኢጣልያኖች ግን በተራራውም በሜዳውም የሚኖሩትን የኢትዮጵያን ሕዝብና እንስሳት ለማጥፋት ሲሉ የመርዝ ጭጋግ የሚበትኑ አይሮፕላኖች ከጧት እስከ ማታ እያመላለሱ ሰውንም እንስሳውንም ፈጁት። አገሩም በሙሉ በእሳት የተቃጠለ ይመስል ነበር። በአየሩም ጥሩ ነፋስ ለማግኘት አልተቻለምና ሰዉም እንስሳውም መተንፈስ እያቃተው ያልቅ ጀመር።

የሚድን እየመሰለው በየዛፉ ሥርና በየፈረፈሩ የተጠጋው ሰው ሁሉ ከዚያው ሸሽቶ ለማምለጥ ስለ አልቻለ ፣ በዚያው እያለቀ ስፍራው ሁሉ ሬሳ ብቻ ስለ ሆነ ሽታው የባሰ ችግር አመጣብን። ሬሳውንም ለመቅበር የሞተው ብዙ ስለሆነ አልተቻለም።

በኮረም ሳለን የራስ ሙሉጌታን አኳኋን የሚያረጋግጥ መልክተኛ ስለመጣና ስለ ነገረን ፣ ትልቅ ኀዘን ተሰማን። ራስ ሙሉጌታ የጦር ሚኒስትራችን ስለ ሆነ አምሳ ሺ ያህል የጦር ሠራዊት ይዞ ወደ መቀሌ ገሥግሦ ከመቀሌ ከተማ ኢጣልያኖችን ለማስወጣት ቁርጥ አሳብ አድርጎ ነበር። ነገር ግን ኢጣልያኖች ይህንኑ አሳቡን በሰላዮቻቸው ስለ ዐወቁት ፣ ራስ ሙሉጌታ ገና አምባ አራዶም ሳለ በግንባር ደረሱበት። ደግሞ ለራያና በዚያው ዙሪያ ላለው ጋላ መሣሪያና ገንዘብ እየሰጡ ከእኛ አስከድተውት ነበርና በስተጀርባ ራስ ሙሉጌታን እንዲከብና ሥንቅ አቀባይንም እንዲከላከል አድርገውት ነበር።

ራስ ሙሉጌታም የታወቀ ስመ ጥሩ ጀግና ስለ ሆነ ፣ በየካቲት 4 ቀን ረቡዕ ጦርነት ገጥሞ ሦስት ቀን ሙሉ በብርቱ ከተዋጋ በኋላ ፣ ምንም በእግር ለመጣው ጠላት ቢመከት በአየር ለመጣው ቦምብና መትረየስ መመከት ስላልቻለ ሌላ የተሻለ ስፍራ ይዞ ለመዋጋት ወደ ኋላው ማፈግፈግ ግዴታ ሆነበት። ነገር ግን ሠራዊቱ በየስፍራው ስለተበታተኑና የራያም ጋሎች በስተጀርባው ስለ ከበቡት ፡ እንደገና ጦርነት ለማድረግ አልተመቸውምና ወደ እኛ መጥቶ ለመቀላቀል ጉዞ ጀምሮ ነበር። የካቲት ቀን አህዮ በሚባል ስፍራ ላይ ድንገት በጥይት ተመትቶ ሞተና ከእርሱ ጋራ ያሉት ጥቂቶቹ አሽከሮቹ ቀብረውት መምጣታቸውን ሰማን ።

የወሎጋ የጦር አዝማች ቢትወደድ መኰንን ደምሰውም ፣ ራስ ሙሉጌታ በፊትም በኋላም መከበቡን ሰምቶ ለእርዳታ ሲገሠግሥ ከኢጣልያ የጦር ሠራዊት ጋራ ተጋጥሞ በጀግንነት ተዋግቶ ቀይሐታ በሚባል ስፍራ ሁለት ምሽግ አስለቅቆ ፣በሁለተኛው ቀን ውጊያ በቦምብ ቆስሎ የካቲት ፰ ቀን ስለሞተ ፣ለራስ ሙሉጌታ እርዳታ አለመድረሱን ሰማን። በዚህም ሁሉ ምክንያት ወደ ፊት እየገፋን ሔደን እኛው ራሳችን የጦር አበጋዝ ሆነን ለማዋጋትና ለመዋጋት ቀቆርጥ አሳብ አደረግን ።

# ምዕራፍ 43

## በሽሬና በተምቤን የነበረው የጦር ሠራዊታችን እየቀናው ስለ መሔዱ ።

የኢጣልያ ወታደሮች መጀመሪያ ጦርነት የተጋጠሙት ከራስ ሥዩም ወታደሮች ጋራ ነው። የራስ ሥዩም ወታደሮች እስከ ሠላሳ ሺ ይሆናሉ። እነዚሁም በየስፍራው ተበታትነው ይዋጉ ነበር እንጂ ፣ ባንድ ስፍራ ብቻ አልነበረም። ራስ ሥዩም ግን ወደ ኋላ እያፈገፈጉ ከመቆየት በቀር ፊት ለፊት ጦርነት እንዳይገጥሙ ትእዛዝ አሳልፈንላቸው ነበር። ምክንያቱም የሰሜኑ የጦር አበጋዝ ራስ ካሣ ሳይደርስ የተጋጠሙ እንደ ሆነ ብቻቸውን በመሆናቸው ጉዳት እንዳያገኛቸው ፡ ሁለተኛም የኢጣልያን ወታደሮች ወደ መሃል አግብተው ለመክበብ እንዲመቻቸው ለማድረግ ነበር።

ራስ ሥዩም እንደ ተቀበሉት ትእዛዝ ወደ ኋላ እያፈገፈጉና እየተከላከሉ ሁለት ወር ከቆዩ በኋላ ፣ በኅዳር ወር መጨረሻ ራስ ካሣ ደረሰላቸውና እርሳቸው በስተግራ ፡ደጃች አያሌው በግንባር ፡ ራስ ካሣ በጀርባ (ደጀን) ሆነው ሲጠባበቁ የጎጃሙ ገዥ ራስ እምሩ 10ሺ የጦር ሠራዊት ይዞ ደረሰላቸው ። እርሱም በሺሬ በኩል የሚመጣውን ጠላት እንዲጠባበቅ ተደረገ። እንደዚህም መደረጉ መቸም ኢጣልያኖች ግንባር ለግንባር ፡ እግር በእግር ሆነው በመትረየስና በጠመንጃ ጦርነት ይገጥሙናል ከማለት በቀር ፣ በጋዝ ጢስና በኤፒሪት መርዝ የጦር ሠራዊታችንን ይፈጁታል ብለን አላሰብንም ነበርና ወደ መሃል ሲገቡ በቀኝና በግራ በፊትና በኋላ ያለው የጦር ሠራዊታችን ለመከበብና ለመቁረጥ እንዲመቸው ለማድረግ ነበር። ምናልባትም ደግሞ በራስ ካሣ በኩል የጦር ሠራዊት እንዳያንስና እንዳይጠቁ ስለ አሰብን ፣ከጦር ሚኒስትራችን ከራስ ሙሉጌታ ጋራ ካለው ሠራዊት ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ፡ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ፡ደጃዝማች በየነ ወንድማገኘሁፊታውራሪ ዘውዱ አባ ኮራን እንዲሔዱ ትእዛዝ አሳለፍን። በዚህም በተሰናዳው እቅድ በሺሬና በተምቤን ያለው የጦር ሠራዊታችን እየቀናው ይሔድ ነበር። ከነርሱ መካከል ደጃዝማች በየነ ወንድማገኘሁ በጀግንነት ተዋግቶ ሞተ።

በዚያም በኩል ከእኛ ሠራዊት ጋራ በርትተው የሚዋጉ የኤርትራ ወታ ደሮች ነበሩ እንጂ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾቹ ኢጣልያኖች ጥቂቶች ነበሩ ።

ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች ኢጣልያኖች ግን የሚሰለፉት በጣም ርቀው በስተኋላ ስለ ሆነ ፣እነሱን ለማግኘት ብዙ ችግር ነበር። የእኛ ሠራዊት ጐራዴ እየመዘዘ ፊት ለፊት እየዘለቀ ሲገባ ሲያዩት አስቀድመው ይሸሻሉ። እንዲያውም በጠቅላላው ለመሸሻ ስፍራ ሳያዘጋጁ ጦርነት አይገጥሙም ነበር ።

በሺሬና በተምቤን በኩል ከሚከላከሉት ወታደሮቻችን መውዜር ጠበንጃ የያዙት በመቶው ዐሥር ይሆናሉ። ከመቶው ዘጠናው ግን ከ40 ዓመት አስቀድሞ የነበረ ውኸግራ ፡ ሰናድር ፡ ሌላም ይህን የመሰለ አሮጉ ጠመንጃ ነው። መትረየስም ከ125 የሚበልጥ አልነበራቸውም። መድፍ ግን ከጠላት ከተማረከው በቀር አንድ እንኳ የላቸውም ነበር። ከጠላትም የተማረከው አንዳንድ ነገር እየጐደለው ስለ ተገኘ ምንም አይሠራም ነበር።

የውኸግራ ጥይት እርሳሱ ጥቁርና ልስልስ ስለ ሆነ በአጥንት ላይ ያረፈ እንደሆነ ይታጠፍና ይጠፈጠፋል። ሥጋ ለሥጋም የወጣ እንደሆነ እርሳሱ በወጣበት በኩል ቀኑስሉ ትልቅና ሰፊ ይሆናል። ስለዚህ ኢጣልያኖች ይህን አይተው በዱምዱም ጥይት ወጉን ብለው አወሩ። በዓቢያዲና በእርባ ወይኔ የእኛ ሠራዊት በራስ ካሣ አበጋዝነት በብርቱ ተዋግቶ ድል አድርጓል። በሺሬም በኩል በራስ እምሩ የተላከው ሠራዊት በጀግንነት ተዋግቶ ከመቶ የሚበልጥመትረየስና ብዙም የዘመቻሥንቅ ማርኳል። ነገር ግን የእኛ ወታደሮች እንደ ቆየው ልማዳቸው ጠበንጃቸውን እየወረወሩ ግንባር ለግንባር ተቃርበው በጐራዴ ካልተማቱ በሩቅ ሆኖ ጠበንጃ ተኩሶ መግደልን ከጀግንነት አይቁጥሩትም ነበርና ይህን በማድረጋቸው ብዙ ጉዳት እንዳገኛቸው እርግጥ ነው።

በዓቢያዲና በእርባ ወይኔ ከተደረገውም ጦርነት በቀር በሹም አውሬ ላይ ትልቅ ጦርነት ተደርጎ ነበር። በዚህ ጦርነት ጊዜ ኢጣልያኖች ከእርዳቸው ውስጥ ወጥተው ነበርና ጦርነቱ ግንባር ለግንባር ነበር። በአየርም አይሮፕላን አልነበረምና የአርበኝነት ውጊያ ሆኖ ነበር። በእኛ ወታደሮችና በኢጣልያ ወታደሮች መካከል የነበረው ልዩነት የእኛ ወታደሮች የያዙት አሮጌ መሣሪያ ፡ የኢጣልያ ወታደሮች የያዙት አዲስ መሣሪያ መሆኑ ብቻ ነበር። ቢሆንም የእኛ ወታደሮች በተለመደው ፈጣንነታቸው እንደ ነብር እየተወረወሩ በጦርነቱ መካከል ስለ ገቡ የኢጣልያ ወታደሮች መትረየሳቸውንና ጠመንጃቸውን ከነጥይቱ ፡ ቴሌፎናቸውንና የራዲዮ መኪናቸውን እየተዉ መሸሽ ጀምረው ነበርና የወታደሮቻችን ልብ እየበረታ ይሔድ ነበር።

የተማረከውን መሣሪያውንና የዕቃውን ብዛት ለመገመት ብዙ መቶ ወታደሮች ከጦርነቱ ስፍራ ወደ ሰፈር ለማመላለስ አራት ቀን ሙሉ የፈጀባቸው መሆኑን መናገር ብቻ ይበቃል። ወታደሮቻችን መሣሪያውንና ዕቃውን ካመላለሱ በኋላ በሰፈራቸው የተቅማጥ በሽታ ገብቶ ብዙ ጉዳት ስለአገኛቸው ኢጣልያኖች ድል ሆነው ሲሸሹ ምናልባት በዕቃቸው ላይ አንድ መርዝ አድርገውበት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳድሮ ነበር።

ኢጣልያኖች ምንም ባዲሱ መሣሪያ ቢበልጡን የእኛም ወታደሮች በልብ ጀግንነት ብልጫ ስለ ነበራቸው በየጊዜው ኢጣልያኖችን ብዙ ጉዳት እንዳገኛቸው አይጠረጠርም።

በተምቤንና በሺሬ አውራጃዎች በተደረገው ጦርነት የእኛ ወታደሮች ድል እያደረጉ ከ300 የሚበልጥ መትረየስ ብዙ መድፍና ታንክም የማረኩት እንደ ውጅግራ ባለ ባሮጌ ጠመንጃ እየተዋጉ ነው።

ከእኛ የጦር ሠራዊት መካከል ታንክ የሚባለውን የጦር መሣሪያ የሚያውቀው ጥቂት ነበር። ከአዲስ አበባም ሲነሣ ከታንክ አደጋ የሚጠበቁበትን ምክር በጽሕፈት ስንሰጣቸው አንዳንዶቹ ታንክ ማለት ምንድን ነው? ይሉ ነበር። በኋላ ግን በጦርነቱ ስፍራ ሦስት አራት ጊዜ አካሔዱንና አመጣጡን ስለ አዩት የጥንቃቄውን ምክር እየተከተሉ ለመዱትና በታንኩ ምንም ጉዳት አላገኛቸውም። እንዲያውም በየፈረፈሩና በየቁጥቋጦው ሥር ተደብቀው እየቆዩ አልፎ ከሔደ በኋላ እየተከታተሉ እንደ ነብር እየዘለሉ በላዩ እየወጡ በየቀዳዳው እየተኩሱ በውስጡ ያሉትን ይገድሏቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜም በሙቀቱ ምክንያት ኢጣልያኖቹ ከታንኩ ውስጥ እየወጡ በየዛፉ ሥር ሲቀመጡ የእኛ ወታደሮች ከተደበቁበት እየወጡ ሰዎቹን እየገደሉ ታንኩን ይማርኩ ነበር። በደጃች አያሌው ግንባር ፊታውራሪ ሽፈራ የሚባለው ባንድ ቀን ብቻ አምስት ታንክ ማርኳል ።

በተምቤንና በሺሬ በኩል የሚዋጋው የጦር ሠራዊታችን በታኅሣሥና በጥር ወር እየቀናው ስለ ሔደ አክሱምንና አድዋን ከኢጣልያኖች እጅ ለማስለቀቅ ፡ ወደ መቀሌም ለመቃረብና ለማቋረጥ ጥቂት ቀርቶት ነበር። ራስ እምሩ በሺሬ ወረዳ በአክሱም ምሥራቅና ደቡብ ሆኖ በትጋት ይጠባበቅ ነበር። ለወታደሩም ሥንቁን እንደታዘዘለት እያደረገ ጊዜው ሳይተላለፍ ይሰጠው ነበርና ልቡን የረጋ አድርጎ ይዋጋ ነበር። በርሱ ግንባር የነበረው የኢጣልያ የጦር ሠራዊት እስከ 25ሺ ተገምቷል። በየካቲት 11 ቀን ከጦርሠራዊቱ ከፍሎ ወደ መረብ ልኮ ነበር። ከአሥመራና ከአድዋ መንገድ መገናኛ ላይ ሲደርሱ በራማ ምሽግ ያሉት ኢጣልያኖች ሙብራት አበሩባቸው ። ወዲያውም ተኩስጀምረው ነበርና 5 ሰዎችገደሉ፤ጥቁቶችም ቆሰሉ። ኢጣልያኖች ግን 45 ሰዎች ገደልን ፣ የቆሰሉትም ከመቶ ይበልጣሉ ብለው አውርተዋል። ፡

የራስ እምሩ ወታደሮች ግን በጥንቃቄና በድፍረት ቀርበው አደጋ ስለጣሉባቸው በራማ ያሉት ኢጣልያኖች ከሞቱትና ከቆሰሉት በቀር በፍጥነት እየሸሹ ስለ ሔዱ አመለጡ።

በዚያም የተገኘው የጦር መኰንንኖች ልብስና ጠመንጃ ፣ ብዙ መትረየስ ከብዙ ጥይት ጋራ ለብዙ ቀን የሚበቃ ሥንቅ ነው። በማግስቱም የሞቱትን የኢጣልያ ወታደሮች ሬሳ እስከ አራት መቶ ከቆጠሩ በኋላ የኢጣልያ ወታደሮች እንደገና መጥተው አደጋ እንዳይጥሉባቸው ስለ ሠጉ ትተውት ወደ ሺሬ ተመለሱ። ራስ እምሩ ይህንኑ በቴሌግራም ስላስታወቀን በማስታወቂያ እንዲወጣ አደረግን። ከዚህ በኋላ ግን ከአድዋ ወደ አሥመራ የሚወስደውን መንገድ

ኢጣልያኖች በጥንቃቄ ስለ አስጠበቁት የራስ እምሩ የጦር ሠራዊት አንዳንድ ጊዜ ትንንሽ አደጋ እየጣሉ ጉዳት ከማድረግ በቀር ትልቅ ጦርነት ለማድረግ አልተመቻቸውም። ፡









በስደት ወደ እንግሊዝ አገር ስንገባ በቀኝ በኩል አቶ ሎሬንሶ ታአዛግ(ብላቴን ጌታ) አዛዥ ወርቅነሕ

ኢጣልያኖችም የራስ እምሩን አኳኋንና ብርታት ባዩ ጊዜ በአክሱም ካለው የጦር ሠራዊታቸው ከፍለው ወደ ሰለቅለቃ ሒደው ምሽግ እንዲሠሩ አድርገው ነበርና ራስ እምሩም በበኩሉ ወታደሮቹ ከቦምብ የሚጠበቁበት ዋሻ አስቆፍሮ ይጠባበቅ ጀመረ። ከዚህም በኋላ ኢጣልያኖች በሰለቅለቃ አጠገብ ከራስ እምሩ ጋራ ተጋጥመው ቀኑን ሙሉ ብርቱ ጦርነት ሆኖ ነበር።

ነገር ግን ኢጣልያኖች በሩቅ የሚመታ መድፍ ነበራቸውና በሩቅ እየሆኑ ስለ ተኩሱባቸው በዚህም ላይ በአይሮፕላን ቦምብ ስለ ጣሉባቸውና የሰናፍጭ መርዝ ስለ አፈሰሱባቸው ራስ እምሩ ጦሩን ይዞ ወደ ኋላው ለማፈግፈግ ግዴታሆነበት።

ደግሞ በመጋቢት 2 ቀን ተከታትለው መጥተው እንደገና ብርቱ ጦርነት ከተደረገ በኋላ እንደዚያው እንደ ተለመደው ብዙ አይሮፕላኖች መጥተው የሰናፍጭና የኤፒሪት መርዝ እያፈሰሱ ስለ ፈጁዋቸው ራስ እምሩ ጥቂት ራሱን ሆኖ ወደ ኋላው አፈገፈገ ።

ይልቁንም ደግሞ ኢጣልያኖች በየሳምንቱ ብዙ ብዙ አይሮፕላኖች እየላኩ ከስሜን አውራጃች ከተሞች ዳባትን ፥ ከበጌምድር ከተሞች ጎንደርን ፥ ከጎጃም ከተሞች ደብረ ማርቆስን በቦምብ ማቃጠል ጀምረው ነበርና በጦርነቱ ያሉት የነዚህ አገሮች ወቃደሮች ይህን በመስማታቸው ልባቸው ስለ ተሸበረ በጦርነቱ ስፍራ ለመቆየት አልቻሉምና በየጥቂቱ እየሆኑ መመለስ ጀምረው ነበር።

ቢሆንም ራስ እምሩ በተምቤን በነራስ ካሣ በኩል ፥ በአምባ ራዶምና በአላጌ በራስ ሙሉጌታ በኩል ፥ በማይጨው በእኛ በኩል ጦርነት መደረጉን እስቲሰማ እየተከላከለ ቆይቶ ነበር። ይህን ከሰማ በኋላ ግን ከቦምብና ከጋዝ ከሰናፍጭም የተረፉትን ወታደሮች ይዞ ወደ ጎጃም ተመለሰ። ደጃዝማች አያሌውም በስሜን ግዛቱ ኢጣልያኖች መግባታቸውን በሰማ ጊዜ ወደ በጌምድር ከተማ ወደደብረ ታቦር ሔደ።

በሰሜን በኩል በኮረምና በአሸንጌ ባሕር መካከል የቀይ መስቀል ሐኪሞች በሚቻላቸው ሁሉ በትጋትና በብርታት ሠርተዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀይ መስቀል ማኅበር የላከው ዶክቶር ዳሲዮስም ከእኛ አልተለየም። ከኮረም ወዲያ እስከ ማይጨው ግን የራሳችን ልዩ ሐኪም ሆኖ ከኛ ጋራ ከሚጓዘው ከዶክቶር መልአኩ በያን በቀር ሌላ ሐኪም አልነበረም ። በኮረምና በአሸንጉ ዙሪያ የእንግሊዝ የቀይ መስቀል ማኅበር የላካቸው ሐኪሞች የቀይ መስቀልን ሕግ እየጠበቁ በብዙ ትጋት እንደ ረዱን ልንዘነጋው አንችልም። ሰፈራቸውንም ከጦር ሠራዊት ሰፈር በጣም በሚርቅ ስፍራ አድርገው የቀይ መስቀል ምልክትና የእንግሊዝን ባንዲራ በሰፋፊው እያደረጉ በመሬት ላይ እየዘረጉ በድንኳናቸውም ላይ እየሰፉ የኢጣልያ አይሮፕላን በሩቅ እንዲያየውና የቀይ መስቀል ማኅበር ሰፈር መሆኑን እንዲያውቀው አድርገው ነበር ። ኢጣልያኖች ግን ይኸንኑ የቀይ መስቀል ምልክት በአይሮፕላን ሆነው እያዩ የቀይ መስቀል ማኅበርን ደንብና ሕግ ብናፈርስ ጠያቂ የለብንም በማለትና በድፍረት በላያቸው ቦምብ እየጣሉ የማከሚያ መሣሪያቸውን ሁሉ ተሰባብሮ የተቆለለ አሮጉ ብረት አደረጉት። ድንኳናቸውንም ብል የበላው አሮጌ ጨርቅ አስመሰሉባቸው። ሐኪሞቹም የሚያክሟቸው ቁስለኞችና በሽተኞች የተኙበትም መሬት በቦምብ ሲገለበጥ በዚያው እየተቀበሩ ቀሩ። ይህን የመሰለ የጭካኔ ሥራ ባሁኑ በሥልጣኔ ዘመን በሚደረገው የጦርነት መዝገብ ተጽፎ የሚገኝ አይመስለንም። እነዚህንም መስመሮች የሚያነቡ ሁሉ ይህን የመሰለው ሥራ ከሕግ የወጣ መሆኑን ሲያዩ በኢጣልያ አገር የሥልጣኔ ሥራ ከንቱ ሆኖ እንደ ተቆጠረ ሳይመለከቱት አይቀሩም ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ይህንንም እየመላለስን ለመናገር አንሰለችም።

ኢጣልያኖች በሽተኞችና ሦስለኞች ታክመን እንድንበታለን ብለው በተስፋ የተኙበትን ቤት በማቃጠላቸውና ቀአስለኞቹንእንደገና አጥንታቸውን እያደቀቁ ከመፍጀታቸው በቀር በሰው ፊት እጅግ የሚያዋርዳቸውና የሚያሳፍራቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው የግፍ ሥራቸው ነው።

የእንግሊዝን የቀይ መስቀል በቦምብ ካጠፉት በኋላ ሐኪሞቹ በኮረም አቅራቢያ ባለው አገር ዋሻ ፈልገውና አግኝተው ኢጣልያኖች ሊደርሱበት የማይችሉበት ብርቱ መጠጊያ የሚሆን መስሏቸው በሽተኞቹንና ቁስለኞቹን

ሁሉ በዋሻው እያስገቡ አስተኝተዋቸው ነበር። ነገር ግን የኢጣልያ አይሮፕላኖች እንደ አዳኝ ውሻ እያነፈነፉ ያንን ዋሻ ስለ ተከታተሉት ወደ ዋሻው ሌላ ቁስለኛ ለማስገባት የገቡትንም ለማውጣት የማይቻል ሆነ። ቁስለኞች ተሸካሚዎችም ለመተላለፍ አቃታቸው። ስለዚህ የእንግሊዝ የቀይ መስቀል ሐኪሞች ቀኑስለኞቹን በጣም ጎልቶ በሚታየው በካሚዮን ከማመላለስ እየተበታተነ በሚሔድ በበቅሎ እየጫነ ማመላለስ የሚሻል መስሎ ስለታያቸው ፣ በቅሎችና ሌላም የሕክምና መሣሪያ ለመግዛት አለቃቸው ዶክቶር ሚሌ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ግድ ሆነበት። በዚህም ላይ ደግሞ ሐኪሞቹ ለራሳቸውና ለረዳቶቻቸው ሕይወት መጠንቀቅ ነበረባቸውና ሕዝባችን ያከሙናል ይረዱናል ብሎ ተስፋ ያደረገባቸው የቀይ መስቀል ሐኪሞች ይህን የመሰለ አደጋ ሲወርድባቸው ፡ በሰውም ልጅ ላይ ሊደረግበት የማይገባ ይህን የመሰለ የጭካኔ ሥራ ሲሠራባቸው በማየቱ ከሰይጣን ጋራ የሚታገል እየመሰለው ተስፋ መቀረጡና የድካም አሳቡ ከልክ ያለፈ ሆነ ።

# ምዕራፍ 44

## ከኮረም ወደ ማይጨው የጦር ግንባር ስለ መሔዳችን ።

በኮረም ሳለን የጠላት አይሮፐላን በየቀኑ ከ2 እስከ 9 ሰዓት ተራ በተራ እየተመላለሰ ብዙ ቦምብና የመርዝ ጋዝ ጥሎ በሠራዊታችን ላይ ጉዳት አደረሰ ። በተምቤን በኩል የዘመቱትም የጦር አለቆች ተምቤን ላይ በጀግንነት ተዋግተውና ተግባራቸውን ፈጽመው በቦምብና በመሣሪያ ብልጫ ድል ስለሆኑ ተበታትነው ነበርና ወደ እኛ እንዲሰበሰቡ ላክንባቸው። እነርሱም መጋቢት 10 ቀን ከሌሊቱ በ8 ሰዓት ኮረም ደርሰው ከእኛ ተገናኙ። ዋነኞቹ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉና ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ ሲሆኑ ከእነርሱ ጋራ ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ፡ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ፡ ደጃዝማች አበራ ካሣ ፡ ጸሐፊ ትእዛዝ አፈወርቅ ፡ በጅሮንድ ለጥይበሉ ገብሬ ፡ ቀኛዝማች ደጎኔ ወልደ ማርያም ፡ ፊታውራሪ ዘውዱ አባ ኮራንና ሌሎችም መኳንንቶች ነበሩ።

መጋቢት 11 ቀን ሐሙስ ኢጣልያኖች አምባላጉን አልፈውማይጨው ላይ መስፈራቸውን ስለ ሰማን ፡ ከእኛ ጋራ ደጀን ሆኖ ቆይቶ የነበረውን የክብር ዘበኞችንና ከየጦሩ ግንባር የተመለሰውን ሠራዊት ይዘን ፡ እኛ ራሳችን መሪሆነን ለመዋጋት ቆረጥንና ከማታው በሁለት ሰዓት ከኮረም ተነሥተን ወደ ጦሩ ግንባር ወደ ሐዮ ስንሔድ ሌሊቱ ስለ ጨለመ ሠራዊቱ ችቦ እንዲያሰናዳ አድርገን ነበርና በችቦ መብራት ተጓዝን። መንገዱ ጠባብ በመሆኑም ምክንያት ጉዞው ብዙ ሰዓት ፈጀ።

በዚህ ዓይነት ተጕዘን መጋቢት 12 ቀን ከአሸንጌ ባሕር ጥቂት አለፍ ብለን ለአይሮፐላን መጠባበቂያ ከሚመች ቦታ ላይ ዋልንና ሌሊቱን ተጉዘን ሐዮ ከሚባል አገር ደረስን። በዚህ ዕለት የጠላት አይሮፐላን ብዙ ቦምብ ስለ ጣለና እንደ ውሃ የሚርከፈከፍ መርዝ (ኤፒሪት) ስላርከፈከፈ በሰውና በከብት ላይ የደረሰው እልቂት የሚያሳዝን ነበር።

መጋቢት 13 ቀን ሐዮ ውስጥ ደረቅ አምባ ላይ ለአኤሮፕላን መጠባበቂያ ምቹ በሆነ ቦታ ሰፍረን ዋልን። ከማታው በ2 ሰዓት የጦር አለቆችንና ሹማምንትን ሁሉ ሰብስበን ስለ ውጊያው አቅድና ስለ አሰላለፉ ተራ የእኛን አሳብ ካስረዳናቸው በኋላ ፡ በእነርሱም በኩል ጦርነቱን በምን አኳኋን መግጠም እንደሚሻል አስተያየታቸውን እንዲገልጹ አደረግን። በዚህ ጊዜ የነበሩት ታላላቅ መኳንንቶች ልዑል ራስ ካሣ ፡ ልዑል ራስ ሥዩም ፡ ራስ ጌታቸው ፡ ደጃዝማች ወንዲራድ ፡ ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል ፡ደጃዝማች አደፍርሰው ፡ ሊጋባ ጣሰው ፡ ፊታውራሪ አሸናፊ ሲሆኑ ሌሎች የሻለቆችና ከነዚያም በታች የሆኑ የጦር አለቆችም ነበሩ። መኳንንቱ መክረው በአንድ ቃል ያቀረቡልንም አሳብ፦

> «ሞት ለሁላችንም የማይቀር ርስት ነው እግዚአብሔር ቀኙን ሰጥቶን ድል ብናደርግ ነፃነታችንን አዳንን ማለት ነው ፡ ብንሞትም ለሀገራችን ነውና ሞታችን ከሰማዕትነት ይቆጠራል። ከጠላት ጋራ ተጠቃቅቶ መሞት ታላቅ ዕድል ነው። ለውጊያውም ሌሊት ተቃርበን ሲነጋጋ እንግጠመው»

የሚል ነው። እኛም የእነርሱን ንግግር ከአዳመጥን በኋላ «ብንሞትም ብንኖርም ለሀገራችን ነው እኛ የምናስበው ሀገራችን እንዳትሞት ብቻ ነው» አልናቸውና ወደ ጦርነቱ ግንባር ወደ ባዕታዋዮ የምንጓዝ መሆናችንን አስረዳናቸው።

መጋቢት 14 ቀን እዚያው ሐዮ ደረቅ አምባ ላይ ዋልን። በዚህም ቀን የጨርጨር ባላባቶች ከኢጣልያ የተቀበሉትን ጠበንጃና ጥይት ይዘው መጥተው «እስከ ዛሬ ድረስ ልባችን የተከፈለው ንጉሣችሁ የሉም እያሉ ኢጣልያኖች ስለ አወሩልን ነበር አሁን ግን በዓይናችን ስለ አየንዎ ከጠላት በተቀበልነው መሣሪያ ስለ ሀገራችን ነፃነት እየተዋጋን እንሞታለን » እያሉ የታማኝነት ቃላቸውን ገለጡልን። እኛም ጠላት የሚያወራላችሁ የሐሰት ስብከት እናንተንና ሀገራችሁን የሚያጠፋ መሆኑን ዕወቁት ብለን አስጠነቀቅናቸው።

በዚሁ ቀን 12 ሰዓት ሲሆን ከደረቅ አምባ ተነሣንና ሌሊቱን ተጉዘን ባዕታዋዮ ዋሻ ላይ ሰፈርን። ይህ ስፍራ ከኢጣልያኖች ሰፈር ጋራ ግንባር ለግንባር የሚያስተያይ ነው።

መጋቢት 15 ቀን በባዕታዋዮ ሳለን የጠላት አይሮፕላን እየተመላለሰ ብዙ ቦምብ ሲጥል ዋለ። ስድስት ሰዓት ሲሆንም አንድ ትልቅ አይሮፕላን መጥቶ እኛ ባለንበት ስፍራ ዝቅ ብሎ ቦምብ ሲጥል ከኛ በኩል መትረየስ በእሮምታ ተተኩሶ ስለ ተመታ ተቃጠለና እየጨሰ በደባር በኩል አልፎ ወደቀ። የኢጣልያ ራዲዮም አይሮፕላኑ አራት ሰዎችን እንደያዘ መቃጠሉን አረጋገጠ።

ከመጋቢት 16 እስከ 19 ቀን የጦር አቅድ እያሰናዳን ባዕታዋዮ ላይ ቆየን። በእነዚህ ዕለታት አይሮፕላን በብዛት እየተመላለሰ ቦምብና የመርዝ ጋዝ ሲጥል ነበርና በየቀኑ በወታደሮቻችን ተኩስ እየተቃጠለና እየጨሰ ወደ ጨርጨር ቆላ ሲሔድ ይታይ ነበር። ። በተለይም መጋቢት 19 ቀን ከመጡት አይሮፕላኖች አንዱ በኦርሊኮን ተመትቶ እዚያው በቅርቡ ስለ ወደቀ ከዚህ በኋላ ብዙ አይሮፕላኖች መጥተው ቦምብና መርዝ እየጣሉ ብዙ ሰው ሞተ፣ብዙ ሰውም ቆሰለ።

መጋቢት 19 ቀን ቅዳሜ የጦር አለቆችን ጠርተን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መሪ ትእዛዝ ሰጠን።

«ስንኳን ይህ ያሁኑ የመጨረሻው የታላቁ ጠላታችን ጦርነትና አውሬ ለማደን እንኳን ሲኬድ ቆራጥ ለመሆን ከቂም መራቅ የሚያስፈልግ ነው። ለጦር የቀረበ ወንድ ልጅ ባለፈው ሁለት ልብ በሆነው ወታደር ሁሉ እግዚአብሔር የፈረደበትን አይታችኋልና እግዚአብሔር ይፈርድብኛል ብሎ ፡ ልቡን ታዛቢ አድርጎ ሥራ ካልሠራ በነጇና በትእዛዝ ብቻ የሚሠራው ዋጋ የሌለው ነው።

ቆርጦ ካልሠሩ ቢሸሹም ሞት አለ። እግዚአብሔርም የሚረዳው ለቆረጠና ጨክኖ ለሠራ ነውና የሀገራችሁ የኢትዮጵያ ነፃነት ፡ ሰንደቅ ዓላማ እንዳይደመሰስና እንዳይቀደድ ጠንክራችሁ ተዋጉ። ግዝቱን ጥሳችሁ ሞት ላይቀር የነፍሳችሁንም የሥጋችሁንም ክብር አበላሽታችሁ አትሙቱ።

አለቃዬ ሸሸ ወይም ሞተ ፡ ሬሳ ቁስለኛ አነሣለሁ ማለት ለሚፈራው ልቡ መሸሻ ለማበጀት ነው እንጂ እውነት ለቁስለኛው አዝኖ አይደለም ። አለቃው ሲሞት ጠንክሮ የተዋጋው አንድ ወታደር አለቃ ይሆን የለምን ።

እግዚአብሔር ቀኙን ቢሰጠን ገንዘባችንና ሀብታችን የኢትዮጵያ መቆም ነውና ለገንዘብ መሻማት አትቸኩሉ። የቆሰለም ምርኮኛ ፈረንጅ ብታገኙ ፡ ምርኮ መገኘቱ የጠላትን ምስጢር ለማወቅ ይረዳልና ፡ በእጁ ጨቤ ሽጉጥ ወይም የሚፈነዳ ነገር ይዞ የሚያበላሻችሁ ካልሆነ በቀር አትጨርሱት።

ሎሌ ከጌታው ፡ ጭፍራ ከአለቃው ከተለየ ሽሽት መጀመሩ ነውና የኔም የኢትዮጵያም ጠላት መሆኑን ዕወቁት ። »

ከዚህም ሌላ የጦር ሠራዊታችን የጥንቃቄ ጉድለት ጉዳት እንዳይደርስበት አስበን ከዚህ በታች ያለውን በስምንት አንቀጾች የተከፈለ ትእዛዝ አስተላለፍንለት።”

1ኛ. ከሰፈርህ ወደ ታዘዝክበት ቦታ የምትነሣው ከማታው በ2 ሰዓት ነው።

2ኛ. ወደ ጦርነቱ ለመሔድ ሌሊት በምትጓዝበት ጊዜ አለቃህ የሚያሳይህን መንገድ ተከትለህ መሔድ ነው እንጂ ባልንጀራህን እንዳትጣራ እንዳታቅራራ ፡ መብራት እንዳታበራ ፡ ጡሩምባ እንዳትነፋ ይሁን። የዚህም ምክንያቱ ጠላት ድምፅህን የሰማ እንደ ሆነ ተዘጋጅቶ በመጠበቁ ይጐዳኻል ፡ ሳይሰማና ሳያውቅ ድንገተኛ አደጋ የጣልክበት እንደ ሆነ ግን ጠላታችን ብዙ ይጐዳል።

3ኛ. ጠላታችን የሸሸ መስሎ ግራና ቀኝ መትረየስ በተጠመደበት በእሳት መካከል እንዳያገባህ ተጠንቀቀህ ፡ የጠላትንም ማታለል ፈርተህ ወደ ኋላ ሳትመለስ እሱ የሚመራህን ትተህ ዳሩን ሔደህ በጠላትህ ውደቅበት።

4ኛ. አሁን የመጣብን ጠላት ኢትዮጵያን ከነሕዝቧ በሙሉ ለማጥፋት የተነሣ ስለ ሆነ እኛም በሙሉ ካላጠፋነው አንድ ሰው በመግደል ገና ጦርነቱ ሳያልቅ ፡ ጠላት ድል መሆኑ ሳይታወቅ ወደ ኋላ ተመልሶ ግዳይ መጣል የጦር ኃይላችንን የሚቀንስ ነውና ለኔ ብቻ ቀናኝ ብለህ በመመለስህ ባልንጀራህን ጠላት እንዲያጠቃው አጋልጠህ ብቻውን መተውህ ስለ ሆነ በጧት ቀናኝ ብለህ ብትመለስ ግዳዩ አይቆጠርልህም።

5ኛ. ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ገንዘቡ ነፃነት ስለ ሆነ ፡ ነፃነትን ለማጥፋት የመጣውን የቀረበውን ጠላት ድል አድርገህ ሳታባርርና ቦታውን ሳታስለቅቅ ዕቃ ለመዝረፍ አትጣደፍ። ብትዘርፈውስ መልሶ ከወሰደው ምን ተጠቀምህ። የጠላትን ገንዘብ የሚወስድ ሰው የወሰደው ገንዘቡ እንዲረጋለት ጠላትን አስቀድሞ እንዳይመለስና እንዳይነጥቀው አድርጎ ማጥፋት ነው።

6ኛ. ስትዋጋ ውለህ ምናልባት ጠላት ጠንክሮብህ አንድ ቀን ድል ማድረግ ቢያቅትህ ረዳት ወታደር እየላክንልህ ጠንክረህ መዋጋት ነውእንጂ ተመለስ ሳትባል ፊትህን እንዳትመልስ።

7ኛ. ተኩስ ጀምሩ ለማለት አዲሞሻሽ ላይ የርችት ምልክት ይሰጣል።

8ኛ. በሽጉጥ በእጅ በሚወረወር ቦምብ በጩቤ የሚያበላሽ ካልሆነ በቀር የጠላት ምስጢርና ኃይል የሚታወቀው በምርኮኛ ቃል ነውና የተቻለህን ፡ ይልቁንም ባለ ማዕርግ ሰው ሲገኝ መማረክ ነው። መጋቢት 19 ቀን 1928 ዓ. ም.። »

ከዚህም በኋላ ወደ ጦርነቱ የምንቀርብበትን አቅድ በአራት ክፍሎች መደብንና ከየቤተ ደንቡ ተመልሶ የተጠራቀመውን ጦር ጨምረን አንዱ ክፍል በቀጥታ በእኛ የሚታዘዝና የሚመራ ሆኖ የቀረው ሦስቱ ክፍል በሦስቱ አበጋዞች በልዑል ራስ ካሣና በልዑል ራስ ሥዩም በራስ ጌታቸው እንዲመራ አደረግን። በእኛም በቀጥታ የሚታዘዘውና የሚመራው እንደሚከተለው ሆኖ ተመደበ።

በግንባር የቀኛዝማች መኩሪያ ባንት ይርጉና የምክትሉ የግራዝማች ክፍሌ ዕርገቱ ጭፍራ የክብር ዘበኛ ጦር።

በግራ የግራዝማች አበራ ግዛው ጭፍራ የክብር ዘበኛ ጦር።

በቀኝ የቀኛዝማች በልሁ ደገፉ ጭፍራ የእልፍኝ አስከልካይ ፡ የባለሚል ጦር። ፡

በጀርባ ደጀን ሆኖ የደጃዝማች አደፍርሰው ጭፍራ የእልፍኝ ዘበኛ ጦር።

እንዲሰለፍ አደረግን ።

በየአበጋዞቹ የሚመራውም ሦስቱ ክፍል እንደሚከተለው ሆኖ ተመደበ ።

## በመሃል ግንባር ፡

ለመሃል ግንባር አበጋዝ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ሆኖ ሰልፈኛውን በሚከተለው አኳኋን መደብንለት ።

ራስ ከበደ መንገሻ ከሰዎቹ ጋር።

* በሊጋባ ጣሰው ዋለሉ የሚታዘዝ የመሃል ሰፋሪ ጦር።
* በፊታውራሪ አሸናፊ የሚታዘዝ የግቢ ሚኒስቴር ጦር።
* በደጃዝማች ግዛው ጅማ የሚታዘዝ የባሶና የጎላ ጦር።
* የእርሻ ሚኒስቴር ጦር።
* ደጃዝማች አበራ ተድላ (የማይጨው ገዥና አገሩ ስለ ሆነ የአቅጣጫው መሪ በመሆን ጭምር)



ሎንዶን በስደት ሳለን በግራና በቀኝ አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኃኅን (ብላቴን ጌታ) አቶ ሎሬንሶ ታአዛህ (ብላቴን ጌታ)



በስደት ሳለን።



በስደት ሎንዶን ስንገባ በግራችን በኩል የሚታዩት ኢትዮጵያውያን ልዑል ራስ ካሣ፣ አዛዥ ወርቅነህ፣ ልዑል አስፋ ወሰን፣ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ (ጸሐፊ ትእዛዝ)



በስደት ጊዜ በቀኝ በኩል አባ ሐና፣ አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ በግራ ፊታውራሪ አስፋው ከበደ አቶ ለገሠ ገብረማርያም፣ አዛዥ ወርቅነህ፣ አቶ ሥዩም

## በቀኝ ግንባር ፡

ለቀኝ ግንባር አበጋዝ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ ሆነው ሰልፈኛውን በሚከተለው አኳኋን መደብንላቸው።

* የሰናድር ያዥ ጦር።
* የወለጋ አርጀና የወለጋ ጉድሩ ጦር።
* የፈረስ ዘበኛ ጦር።
* የሊቀ መኳስ ኃይለ ማርያም ወልደ ገብርኤል ጭፍራ።
* በቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ ወልደ አብ የሚታዘዝ የመድፈኞች ጦር።
* ፊታውራሪ ተፈሪ ተድላ ፡ (አገሩ ስለ ሆነ የአቅጣጫው መሪ በመሆን ጭምር። )

## በግራ ግንባር ፡

ለግራ ግንባር አበጋዝ ራስ ጉታቸው አባተ ሆኖ ሰልፈኛውን በሚከተለው እኳኋን መደብንለት።

* የከምባታ ጦር።
* የዕቃ ቤት ጦር።
* የገንዘብ ሚኒስቱር ጦር።
* በቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ወልደ ገብርኤል የሚታዘዝ የፖስታና የቱሌፎን ሚኒስቱር ጦር ።
* በቀኛዝማች አበበ ረዴ የሚታዘዝ የማለፊያ ጠመንጃ ያዥ ጦር።
* በቀኛዝማች በየነ በላይነህ የሚታዘዝ የባልደራስ ጦር ።
* ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ (የአቅጣጫው መሪ በመሆን ጭምር። )

ከእነዚህም ሌላ በጸሎትና በምህላ ለመርዳት የተከተሉን መንፈሳውያን አባቶች ፡ አቡነ ጴጥሮስ የወሎ ጳጳስ ፣ እጨጉ ገብረ ጊዮርጊስ ፣ ሊቀ ገብረ ክርስቶስና ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ ፡ ካስከተሉዋቸው ካህናት ጋራ እኛ ባለንበት ክፍል አብረው እንዲሰለፉ አደረግን። ከመሳፍንትና ከመኳንንትም ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉና ልዑል ራስ ሥዩም ፣ ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል ፣ ደጃዝማች ወንዲራድ ፣ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ፣ ደጃዝማች አበራ ካሣ ፣ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ለምክርና አስፈላጊ ለሆነ ዋና ጉዳይ ከእኛ ዘንድ በቅርብ የሚገኙ ሆነው ተመደቡ።

የሰልፉ ድርጅትና የአቀራረቡ አቅድ በዚህ አኳኋን እንዲመራ ከአደረ ግን በኋላ ፡ በጦርነትና በመልእክት ጊዜ የወገንን ወታደር ከጠላት ወታደር ለይቶ ለማወቂያ የሚያገለግል ምልክት ለሠራዊታችን ተሰጠ። ምልክቱም አንተ የማን ነህ ? ሲለው ተጠያቂው «የአባ ጠቅል» ብሎ ይመልስለታል። «ጠቅል ምን አለ?» ብሎ ሲጠይቀውም

በጦሬ አልታመንም

ኃይል የእግዚአብሔር ነው» አለ ይለዋል ።

ተጠያቂው ይህን ምልክት የመለሰለት እንደ ሆነ ፡ የወገን ጦር ነው ብሎ ያምነዋል። ይህን ለመመለስ ሲያቅተው ግን የጠላት ጦር መሆኑን ያውቃልና በጠላትነት ይመለከተዋል ማለት ነው።

ከዚህም በቀር በባዕታዋዮ ዋሻ የተቀመጠውን የጦር መሣሪያና ጥይት፣ ዕቃና ገንዘብ እንዲጠብቁ ለታዘዙት የዘበኞች አለቆች «ምናልባት ጦራችን ድል የሆነ እንደ ሆነ መሣሪያውና ዕቃው በጠላት እጅ እንዳይገባ ምልክት

ስንልክላችሁ እንዲቃጠል አድርጉ» ብለን አስጠንቅቀን ምልክት ሰጠናቸው። ቃሉም «አምላካችን ከእኛ ጋራ አልወጣም» የሚል ነው።

# ምዕራፍ 45

## የማይጨው ጦርነት ።

መጋቢት 20 ቀን 1928 ዓ. ም. እሑድ በባዕታዋዮ ሰፈር ሳለን የጠላት አይሮፕላን በየጊዜው እየተመላለሰ ቦምብና መርዝ ሲጥል ዋለ። እኛም ጦርነቱ በማግስቱ ሰኞ እንዲጀመር ትእዛዝ ሰጠንና ወደ ጦርነቱ ቦታ ለመጠጋት እሑድ በ11 ሰዓት ከባዕታዋዮ ተነሥተን መሐን ላይ አደርን። መጋቢት 21 ቀን ሰኞ ለየክፍሉ የተመደበው ጦር ሳይከት ስለ ቀረ የጦርነቱ ግጥሚያ ለሰኞ መሆኑ ቀርቶ እዚያው መሐን ላይ ውሎ አደረግን። በዚህ ስፍራ ከአይሮፕላን አደጋ የሚከልል በቂ ዋሻ አልነበረም። ትንሽ ዋሻ አግኝተው ወደ ዋሻው እንድንሔድ ቢነግሩንም ዋሻው ለሠራዊቱ ሁሉ የማይበቃ ነበርና «እኔስ ዓለሙን ከሕዝቤ ጋራ እንደ ተካፈልሁ መከራውንም ሳልለይ እካፈላለሁ እንጂ ሕዝቤን ትቼ አልሔድም» ብያቸው እዚያው ዋልሁ።

መጋቢት 21 ቀን ማክሰኞ ጦርነቱ እንዲደረግ ስለ ወሰንን ፣ ባለፈው ቀን በተዘጋጀው አቅድ መሠረት ሰልፈኛው በየክፍሉ ሌሊቱን ተጕዞ ተጠግቶ ፡ ሲነጋ ውጊያው እንዲጀመር አዘዝን። ወታደሩ እንደ ታዘዘው በየክፍሉ ሲጓዝና ሲጠጋ አደረ። እኛም ከሌሊቱ በ10 ሰዓት ከመሐን ተነሥተን ወደ ጦርነቱ ቦታ ተጓዝን።

ግንባር ቀዳሚው ጦራችን በጨለማው ሰዓት ተጕዞ ወደ ጠላት ምሽግ ሊቃረብ ሲል የጠላት ቃፊር ወገኑን ለማንቃት የተኩስ ድምፅ ቢያሰማ የእኛም ጦር በጕዞ ላይ እንዳለ የተዙስ ድምፅ በተሰማበት በኩል ይተኩስ ጀመር። የኢጣልያ ወታደሮችም ምሽግ መሽገው በተቀመጡበት በማይጨው ውስጥ ባለው መሐን በሚባለው ቦታ ይተኩስ ጀመር እንግዲህ በፊት እንዳሰብነው ሳይሆን በድንገተኛ ተኩስ ውጊያው ስለ ተከፈተ ደንበኛው ጦርነት እንዲጀመር ትእዛዝ ሰጠንና ውጊያው ይካሔድ ጀመር።

የእኛ ጦር እየተፏከረ ሒዶ ከጠላት ምሽግ ላይ ስለ ደረሰ የጠላት ወታደር አንደኛውን ምሽግ ለቆ ወደ ሌላው ምሽግ እየተደረበ ሲከላከል ይታይ ጀመር ።

በአራትና በአምስት ሰዓት ላይ የጠላት አይሮፕላን ደርሶ ቦምብ እየጣለ ከወደ ኋላ ያለው የእኛ ጦር ፡ ወደ ግንባር ለቀደመው ወታደር ለእርዳታ እንዳይደርስለት አድርጎ አቋረጠው። በዚህ ጊዜ የጠላት ጦር እንደገና አንሰራራና ለቆት ወደ ነበረው ምሽግ ተመልሶ ለመግባት በብርቱ ይዋጋ ጀመር።

ጦራችን በጋለ መንፈስና በድፍረት ሲዋጋ ዋለ። ጦርነቱም ከሌሊቱ እስከ 5 ሰዓት ድረስ አላቋረጠም። በዚህ ቀን ውጊያ ብዙ መኳንንትና የጦር አለቆች ላገራቸው ሕይወታቸውን በመሠዋት ሞተዋል።

እኛም በዚህ ዓይነት ውጊያ እንዳለን ቀኑ ስለ መሸ ትናንት አድረንበት ወደ ነበረው ወደ መሐን ተመለስን። ሠራዊታችን በውጊያው ተጐድቶ ስለነበረ አብዛኛው ሌሊቱን ወደ ባዕታዋዮ ሲጓዝ አደረ። አንዳንድ ወታደርም በጠላት ምሽግ አጠገብ አድሮ ሌሊቱን ይታኩስ ነበረ።

መጋቢት 23 ረቡዕ መሐን ላይ ውሎ አድርገን ቁስለኛ እንዲነሣ የሞተም እንዲቀበር ትእዛዝ ሰጠን። ከወታደርም አንዳንዱ ወኔው እየቀሰቀሰው ወደ ጠላት ምሽግ ሔዶ ሲዋጋ ዋለ።

መጋቢት 24 ቀን ሐሙስ መሐን ላይ ውሎ አደረግን። በዚህ ቀን ውጊያው እንዲደገም ማሰባችንን ለጦር አለቆች ብናስታውቃቸው ሁናቴውን የገመቱት ሁሉ እንዲህ እያሉ አመለከቱን። «ሠራዊታችን ከማክሰኞ ማታ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ባዕታዋዮ ሰፈር ስለ ተጓዘ አሁን በዚህ ያለነው ጥቂቶች ነን ለውጊያው የሚበቃም ወታደር የለንም። አሁን ያለንበትም ቦታ ከአይሮፕላን ለመጠበቅ ከለላ የሚሆን አንዳች ነገር ስለሌለበት አደገኛ ቦታ ነው። ስለዚህም

ወደ ባዕታዋዮ ሔደን ፡ ጦሩን እንደ ገና ሰብስበንና አስከትተን ብንዋጋ ይሻላል» አሉን። እኛም «እግራችንን ከዚህ ከነቀልን የጦርነቱ መደገም ይቀራልና እኛው ያለነው ብንዋጋ ይሻላል» ብለን መለስንላቸው።

በዚህ ጊዙ ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም በእኛ ውሳኔ ተቸግረው «ለጦርነት የሚበቃ ወታደር ሳይኖር መዋጋት በከንቱ መሞትና መጥፋት ነው» እያሉ ምክንያቱን ሁሉ በመዘርዘር ስላስረዱንና የጦር አለቆች ያቀረቡልንን አሳብ በመከተል ከሌሊቱ በ6 ሰዓት ወደ ባዕታዋዮ ሔድን።

መጋቢት 25 ቀን ዓርብ ባዕታዋዮ ከዋሻው ዋልን። በዚያው ሳለን ኢጣልያኖች ባለፈው ማክሰኞ ለቀውት የነበረውን ምሽግ እንደ ገና መያዛቸው ተሰማ። ስለዚህም ተከታትሎ የሚመጣውን ጠላት ለመከላከል እንድንችል በማለት በባዕታዋዮ አካባቢ ለመከላከያ ያመቻሉ በተባሉት ቦታዎች ላይ በር ጠባቂ ጦር እንዲቀመጥባቸው አደረግንና ለወደፊቱ የጦር አቅድ ከጦር አለቆች ጋራ እየተመካከርን መሥራት ጀመርን።

እኛ ያለንበት ባዕታዋዮ መሃል ሰፈር ሆኖ ሌሎቹ በር ናቸው የተባሉት ለጥበቃ የታዘዙት የጦር አለቆች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. በቦክራ ተራራና በመሐን ተራራ መካከል ባለው በር ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ የሰቆጣን ጦር ይዞ
2ኛ. ከከሣድ ሐዮ አንሥቶ እስከ አድባማዙ ድረስ ባለው ኮ በር ራስ ጉታቸው
3ኛ. ከከሣድ ሐዮ ጀርባ ከዋሻው አንሥቶ እስከ መሐን ድረስ ራስ ከበደ መንገሻ
4ኛ. ሐዮ ሚካኤል አጠገብ ባለው በር የግቢ ሚኒስቴር ጭፍራ እንዲሰፍር ተደሪ

ለበር ጥበቃ የመደብናቸው የጦር አለቆች ወደ ስፍራው ከመድረሳቸውና በሩን ከመያዛቸው በፊት የጠላት ጦር ከምሽጉ እየመጣ ባለፈው ዕለት ዐርፈንበት ወደ ነበረው ወደ መሐን ሲገባ ይታይ ጀመር። መሐን የተባለው ስፍራ እኛ ላለንበት ለባዕታዋዮ ቅርብ ነው ።

እኛም ጠላት ጉዞ መጀመሩን ከተመለከትን በኋላ እንግዲህ ከምሽጉ ከወጣ በሜዳ ላይ ልንጋጠም ስለሚቻል ደግሞም ወደ እኛ ጉዞ መጀመሩ ስለማይቀር ቦታ ይዘን እንድንዋጋ በቶሎ ለመታኰሻ የሚሆን ቦታ ያዙ ብለን ለየሹማምንቱ ትእዛዝ አስተላለፍን። አይሮፕላኖችም እየተመላለሱ ሰፈራችንን ከመደብደብ አላቋረጡም ነበርና እኛም ራሳችን ሳንቀር ኦርሊኮን እየተኩስን ተከላከልን ።

መሐን የገባው የጠላት ጦር በሜዳ ላይ ውጊያ መግጠሙንና ወደ እኛ መምጣቱን ትቶ እዚያው መሽገና መድፍ እየተኰሰ በአሽጋጋሪ የወታደሮቻችንን ሰፈር ይደበድብ ጀመር። በዚህ ጊዜ የእኛ ጦር ከላይ አይሮፕላኖች በሚያዘንቡበት ቦምብና መርዝ ፣ ከታችም በመድፍ ተኩስ ብዙ ጉዳት ደርሶበት ስለ ተሰቀቀ ጦሩ ተፈታና ፊቱን አዙሮ ወደ ኮረም መጓዝ ጀመረ።

ባዕታዋዮ ላይ ለመዋጋት ያሰብነው አቅዳችን ሁሉ በዚህ አኳኋን ስለፈረሰ መኳንንትና የጦር አለቆች ወደ እኛ ቀረቡና ፣ «ወደ ኮረም ተመልሰን ወታደሩን ሰብስበን አሸንጌ ላይ ብንዋጋ ይሻላል። እዚያም ሳይቀናን ቢቀር በላስታ ፡ በየጁ ፡ በወሎ ስፍራ እየያዝን ብንዋጋ ይሻላል ። » የሚል ሐሳብ አቀረቡልን። ከዚያም በኋላ የጦር አለቆች ሁሉ ተሰብስበው እንዲመክሩበት ስለ ፈቀድን ሁሉም በእኛ ፊት ተሰብስበው የምክር አሳባቸውን በዝርዝር እየገለጹ ተናገሩ። ያቀረቡትም ምክር ከእውነተኛ ሕሊና የመነጨ መሆኑን እየተናገሩ በመሓላ አረጋገጡልን ።

እኛም «ሰው የእግዚአብሔር መሣሪያ ስለ ሆነና አሁንም የነገራችሁኝ የመደለል ነው እንዳልል ቁርጠኛ መሆኑን በመሐላ ስለ አረጋገጣችሁልኝ አላማጣ ድረስ እሔዳለሁ ነገር ግን እግዚአብሔርን እየለመናችሁ ቂም በቀል አጥፍታችሁ ኃጢአታችንን እያሰባችሁ አሸከርና ጭፍራችሁንም እያነቃቃችሁ መቆምን ሳታስቡ የምትሞቱበትን አስቡ» ብለን አስጠነቀቅናቸው።

ከዚህም በኋላ ባዕታዋዮ ላይ ያለውን ሥንቅና መሣሪያ ለየጦር አለቆቹ እንዲታደል አደረግንና የተረፈውም መሣሪያና ሥንቅ ለጠላት እንዳያገለግል እንዲቃጠል ትእዛዝ ሰጠንና ከሌሊቱ በ3 ሰዓት ተኩል ወደ ኮረም ተጓዝን።

መጋቢት 26 ቀን ቅዳሜ ጧት አሸንጌ ስንደርስ የጠላት አይሮፕላኖች ብዙ ሆነው መጥተው በአሸንጌ ላይ የሚጓዘውን ሠራዊታችንን በቦምብ ደበደቡት። እኛም የአሸንጌን ባሕር ወደ ግራ ትተን በስተቀኝ በኩል ባለው በአሸንጌ ማርያም አጠገብ ውሎ አደረግንና ማታውኑ ተጉዘን እዳ አጋፋሪ አደርን።

መጋቢት 27 ቀን እሑድ እዳ አጋፋሪ ውሎ አደረግን። በዚህም ቀን ኢጣልያኖች እኛ ያደርንበትን የአሸንጌን ቀበሌ ለመከበብ ታቹን በጨርጨር ቆላ ቆርባታ ላይ የነበራቸውን ጦር ልከው ኖሮ የእነርሱ ጦር ከእኛ ቀድሞ ኮረምና አላማጣ ደርሶ ስፍራ መያዙን ሰማን። የሚጓዘውም ሠራዊታችን በኢጣልያኖች አይሮፕላን እየተደበደበና የባላገር ወስላታ አደጋ እየጣለበት ብዙ ሰው አለቀ። የተረፈውም ተበታትኖ በላስታ መንገድ ስለተጓዘ ለመዋጋት ያቀድነውን ለመፈጸም የማይቻል ሆነ ።

# ምዕራፍ 46

## ወደ አዲስ አበባ ስለ መመለስ ።

ኮረም ላይ እንዋጋለን ብሎ የመከረውና የተማማለው የእኛ ጦር ተበታትኖ በላስታ መንገድ ሒድ ብለውሃል እያለ እርስ በርሱ እየለፈፈ ይጓዝ ጀመር። ከእኛ ጋራ የቀሩትም ሹማምንት የሠራዊቱን ሁናቴ ተመልክተው ወደ ኋላችን ተመልሰን ላስታ ወይም የጁ ላይ ሆነን ብንዋጋ ይሻላል ብለው አመለከቱን። እኛም ያለ ሠራዊት ብቻችንን የምንሠራው ጠቃሚ ሥራ አለመኖሩን ስለ ተረዳን መጋቢት 27 ቀን እሑድ በ12 ሰዓት ከእዳ አጋፋሪ ተነሥተን ሌሊቱን ተጓዝንና ላት ጊዮርጊስ ላይ ጉሬዛ ከሚባል ዋሻ አደርን ።

መጋቢት 28 ቀን ሰኞ ላት ጊዮርጊስ ላይ ውሎ አደረኝና በ12 ሰዓት ተጉዘን ጉራ ማርያም ፡ በመጋቢት 29 ቀን በጉራ ማርያም ውለን በ11 ሰዓት ተጓዝንና መረዋ ማርያም ማኅደር በተባለ ስፍራ ፡ በመጋቢት 30 ረቡዕ ማኅደር ላይ ውለን በ10 ሰዓት ተነሣንና አዘዝጌ ደረስን። በዚያም ጥቂት ቆይተን በ6 ሰዓት ተኩል ጉዞውን ቀጠልንና ላስታ ግራርች ደርሰን አደርን።

ሚያዝያ 3 ቀን ቅዳሜ ተከዜን ተሻግረን ተጓዝንና ጥላስፈሬ ሥላሴ ከደረስን በኋላ የትንሣኤን በዓል ለማክበር ከቤተ ክርስቲያን አደርን ።

ሚያዝያ 4 ቀን እሑድ ስለ ትንሣኤ በዓል በጥላስፈሬ ሥላሰ ውሎ አድርገን እዚያው አደርን። ከዚህ ቀን በፊት የተጓዘው ጦር የሦስትና ያራት ቀን መንገድ ተጉዞ ስለ ነበረ ወደ ፊት በቀደሙትና ወደ ኋላ በቀሩት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በማሰብ ቀጥሎ ያለውን ትእዛዝ አስተላለፍን ።

> «ይድረስ ወደ ፊት ከቀደማችሁ የጦር አለቆችና ሠራዊት እናንተ ወደ ፊት ሔዳችሁ ከእኛ መለየታችሁ ጉዳት የሚያመጣ ሆኖአልና ይህ ወረቀት እንደ ደረሰላችሁ በየሰፈራችሁበት ቆማችሁ እንድትቆዩን ይሁን። ይህ ቃል ከደረሰላችሁ በኋላ አልፋችሁ ብትሔዱ ግን ለእኔም ለመንግሥቴም ጠላት መሆናችሁ ነው። »

ይህም ቃል ከደረሰ በኋላ ራስ ጌታቸውና ሊጋባ ጣሰው ግምዋሻ በተባለ አገር ሲጠብቁ ቈዩ። ሌላው ሹማምንትና ወታደር ግን ቀድሞ ሔዶ ባላገር እየወጋው ብዙ ሰው አለቀ።

ሚያዝያ 5 ቀን በ9 ሰዓት ከጥላስፈሬ ተነስተን ወደ ቅዱስ ላሊበላ ቤተ ክርስቲያን ለመሔድ ተጓዝን። ከተከተሉን ሰዎች ታላላቆቹ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፣ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ፣ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ፣ ደጃዝማች አበራ ካሣ ፣ ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል ሐዋስ ፣ ደጃዝማች አደፍርሰው ይናዱ ናቸው።

በዚሁ ቀን ከማታው በ4 ሰዓት ላሊበላ ደርሰን በልዑል ራስ ካሣ ቤት አደርን። ከሌሊቱም በ10 ሰዓት ወደ ቤተ ማርያም ሔደን አስቀደስን ።

ሚያዝያ 6 ቀን ማክሰኞ የቅዱስ ላሊበላን ቤተ ክርስቲያን ሁሉ እየተዘዋወርን ጐበኘን። በዚህም ቀን ላሊበላ ላይ ያሉት የአሜሪካ ሚሲዮናውያን ተቀብለው አስተናገዱን። ቀጥሎም ወደ አሸተን ማርያም ወጥተን ጐብኝተን ተመለስንና በራስ ካሣ ቤት አደርን ።

ሚያዝያ 7 ቀን ከሌሊቱ በ8 ሰዓት ተነሥተን ጉዞ ጀመርንና ጧት የቅዱስ ነአኵቶ ለአብን ቤተ ክርስቲያን በሩቅ ተሳለምንና ወደ ገነተ ማርያም አለፍን። እዚያም ስንደርስ የገነተ ማርያም ካህናት ንሴብሖ እያሉ በዝማሬ ተቀበሉን። ከዚህ በኋላ ወደ ጥላስፈሬ ተመልሰን በ6 ሰዓት ደርሰን እዚያው አደርን።

በተዳገርው ወታደርና በባላገር መካከል አንዳንድ ግጭት መፈጠሩን ካሁን በፊት ሰምተን ስለ ነበረ ወታደሩም ሆነ ባላገሩ የእርስ በርሱን ግጭት ትቶ ጠላቱን ብቻ እንዲከላከል ቀጥሎ ያለውን የዐዋጅ ቃል አስነገርን።

## ዐዋጅ

«ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ያገሬ የኢትዮጵያ ሰው ጠላታችን በአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን በስምንት በኩል ተከፍሎ ስለ መጣብን የጦር ሠራዊታችንን ይዘን በአንድ ቦታ ብቻ ስንቀመጥ ባላገርና ወታደር እየተጣላ መጋደሉ ለአገራችንና ለሕዝባችን ጉዳት ስለ ሆነ እኛም የተነሣብን የኢትዮጵያን ነፃነት የሚያጠፋ ቤተ ክርስቲያንን የሚያቃጥል ርስት የሚነቅል ሃይማኖት የሚያረክስ ስለሆነ ተምቤንና መቀሌ ጦር ልከን ማይጨው ላይ እኛው ራሳችን እግዚአብሔር ያስቻለንን ያህል እርዱ ውስጥ ገብተን ሠራን። ነገር ግን የጠላታችንን ኃይል ለመግፋት የምንችለው ብዙ ቀን በመዋጋት ስለ ሆነ ብዙ ቀን በአንድ ቦታ በመቆየትም ወታደርና ባላገር በዘረፋ ምክንያት እየተጣላ እርስ በርሱ መጋደሉ ለሕዝባችን ጉዳት የሚያመጣ መሆኑን ስለ ተረዳነው ሥንቅ በሚገኝበት አገር ታላቁን ጦርነት ለማድረግ ወደ ሸዋ ተጕዘናል ።

አሁንም የመጣብን ጠላት አንዳንድ ወረቀት እየጻፈ ቃሉን እያሳመረ ቢበትንልህ እውነት እንዳይመስልህ። አሁን እንኳ በቤተ ክርስቲያናችን በካህናቶችና በመነኰሳት በሴቶችም ላይ የሚያደርገውን ግፍና ርኩሰት በጆሮህ የሰማኸው ባይንህ ያየኸው ነው። ዘራችንን አጥፍቶ ፣ ርስታችንን ለልጁ ለማውረስ ቆርጦ ስለ መጣብን ባለ አእምሮ የሆነ ሰው ይቅርና እሾህ እንኳ በስፍራው የመጣበትን እየወጋ ማስቸገሩ የታወቀ ነውና ባገርህ ሲገባ የምትችል ባለ አቅምህ በሰፈረበትና በሚጓዝበት ላይ አደጋ እየጣልህ ባገርህ ላይ እየተዘዋወርህ አገርህ ምድርህ እንዳይደፈር ባለህበት ተዋጋ። አገርህ ላይ ሆነህ መሥራት የሚያስቸግርህ ግን ላንተም ለጓዝህም ቀለብህን እኛ እንሰጣለንና አለንበት ድረስ መጥተህ ላገርህ ፣ ለርስትህ ፣ ለሃይማኖትህ ከኛ ጋራ ሆነህ እንድትዋጋ ይሁን። ጠላታችን ባላባትና ድኃ ሳይል የኢትዮጵያን ዘር ለማጥፋት ስለ ተነሣ በገባበት አገር እየሰበሰበ በመትረየስ መፍጀቱን ተምቤንና አድዋ ላይ የተደረገውን ብትጠይቅ ትረዳዋለህ። በፈቃዱ የገቡለትን ባላባቶች እንኳ ምንም ጥፋት ሳይገኝባቸው እያሰረ ወሰዳቸው። ስለዚህ ብትዋጋም ባትዋጋም ሞቱ የማይቀርልህ ነው። ይህንንም የምነግርህ ለመደለል ወይም ለኔ ጥቅም አይደለም ላንተው ለራስህ ነው። በኋላ የማይረሳ ጸጸት የማይመለስ ጥፋት የሚያገኝህ መሆኑን እርግጡን ስላወቅሁት የማውቀውን የማስታውቅህ እግዚአብሔርን ምስክር አድርጌ ነውና ሳትጠራጠር የምነግርህን እመን።

ሚያዝያ 5 ቀን 1928 ዓ. ም. ላስታ ጥላስፈሬ ተጻፈ። »

ከዚህም በኋላ በተለይ አብሮን ለሚጓዘው ጦር ቀጥሎ የተጻፈውን ትእዛዝ አስተላለፍን ።

«የእንግዲህ መንገዳችን ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ስለ ሆነ ፡ አለቃ ለሌለህም አለቃ አድርጌልሃለሁና ከሱ ሳትለይ አለቃ ያለህም ካለቃህ ሳትለይ ተጓዝ። ስትጓዝም ሁለት እጁ ሰው ወደ አጀብ አንዱ እጅ ሰው ወደ ጓዙ ይሁን። ከጓዝም ስትውል ጭነትህን እመሃል ፡ አንተ ፊትና ኋላ ግራና ቀኝ ሆነህ ተጠንቅቀህ ጕራህን ሳትለቅ መጓዝ ነው። ከደጀን የተረፍከና ከፊታውራሪ ያለፍክ ትቀጣለህ። የጉዞ አበጋዝ የሆንከም በተራ ወረቀትህን ተቀብለህ ወደፊትም ሳትቀድም ወደ ኋላም ሳትቀር የተሰጠህን ተራ ጠብቀህ ሒድ። ጥይትም መዋጊያህ ነው እንጂ መገበያየህ አይደለምና እንዳትሸጥ ይሁን ።

ሚያዝያ 5 ቀን 1928 ዓ. ም. ጥላስፈሬ ተጻፈ። »

ሠራዊታችን ተበታትና ወደ ኋላው ስለ ተመለሰ እኛ ከጥቂቶች ሰዎቻችን ጋር ሆነን ብቻችንን የምንሠራው ሥራ ዋጋ ሊኖረው እንደማይችል የታወቀ ነገር ሆነ። ወደ የጁ ቀድመን ስፍራ ይዘን እንድንዋጋ ያሰብነውም ሳይሳካ ቀረ። እንዲያውም ለመዋጊያ ይሆናሉ ብለን ያሰብናቸውን ቦታዎች ሁሉ ጠላት እየቀደመ ስለ ያዛቸው ባላሰብነው አቅጣጫና መንገድ ተመርተን እንጓዝ ጀመር። በተጓዝንባቸውም አገሮች ላይ ለጉዞአችን ችግር የሚሆኑ ነገሮች ሳይገጥሙን አልቀሩም።

ከማይጨው እስከ አዲስ አበባ የተላለፍንባቸው አገሮች ሰቆጣ ፣ ላስታ ፣ ዋድላ ፣ ደላንታ ፣ ወረሂመኑ ፣ ተንታ ፣ አሊ ቤት ፣ አበይ ቤት ፣ ለጋምቦ ፣ ለገሂዳ ፣ ጅማሚዳ ፣ መርሐቤቴ ፣ ሰላሌ ፣ ፍቼ ናቸው። እነዚህን ሁሉ አልፈን ሚያዝያ 22 ቀን 1928 ዓ. ም. ኀሙስ በ3 ሰዓት አዲስ አበባ ገባን።

# ምዕራፍ 47

## ከአዲስ አበባ ወደ ውጭ አገር ለመሔድ በምክር ስለ መቆረጡና ስለ መሔዳችን ።

ሚያዝያ 22 ቀን ኀሙስ ወደ ዋና ከተማችን ወደ አዲስ አበባ ከገባን በኋላ ሚኒስትሮቹና መኳንንቱ ፣ ታላላቆቹም ሰዎች ሁሉ በቤተ መንግሥታችን ተሰብስበው ታላቅ ምክር ተደረገ። በምክሩም ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮጳ ሔደው ኢጣልያ የሠራችብንን ግፍ ሁሉ በቃላቸው ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ቢያመለክቱ መልካም ነው ተብሎ በምክር ከተቆረጠ በኋላ ለእኛ የሚያስፈልገን ከሁለቱ አንዱን መምረጥና መቁረጥ ብቻሆነ።

አንደኛው መዋጋትን ትቶ በምክር እንደ ተቆረጠው ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ለማስታወቅ ወደ ጄኔብ መሔድ ሁለተኛውም በከተማ የተገኙትን ጥቂቶች ወታደሮች ይዘን የሽማግሌውን ፣ የሴቱንና የሕፃኑን ሞት የከተማውን መቃጠል ሳናስብ መዋጋት ነው።

በዚህም ብርቱ አሳብ ውስጥ ሳለን በየሰዓቱ የሚመጣልን ወሬ ኢጣልያኖች ንጉሠ ነገሥቱ በአዲስ አበባ ከተማ መግባታቸውን ምክንያት አድርገው ከተማውን በቦምብ ሊያቃጥሉት ነው የሚል ነበር።

ደግሞ ኢጣልያኖች የአዲስ አበባን ከተማ በቦምብ አያጠፉትም ብለን እንዳናምን የጦር ሠራዊትና መከላከያ መሣሪያ የሌለበትን የሐረርን ከተማ በቦምብ መምታታቸውንና በግምቡም ውስጥ በጣም ተከብረው በሚኖሩ በአባ ዣሩሶ እንድርያስ ላይ ትልቅ ጉዳት ማድረጋቸውን ሰምተናል ።

እኛም ከልጅነታችን ጀምሮ የሚበልጠውን ዘመናችንን ያሳለፍነው በዚሁ በሐረር ከተማ ስለ ሆነ በቦምብ መመታቱና መቃጠሉ በተለየ ልባችንን አሳዝኖታል። እንግዲህ የሐረርን ከተማ ያቃጠለ ጠላት አዲስ አበባን ለማቃጠል ምንም የሚከለክለው ነገር አለመኖሩን ተረድተነው ነበር። ደግሞ ይህንኑ ለማረጋገጥ ሲሉ ከተማውን እናጠፋዋለን የሚል ቃል ጽፈው ከጥቁር ባንዲራ ጋራ በአይሮፕላን ጥለው ነበር። ይልቁንም በአዲስ አበባ ላይ መዋጋትን ብናስብ በሰሜን በኩል በብዙ ሺ የሚቈጠሩት በየተራራውና በየሜዳው ላይ በመርዝ እየተቃጠሉ በጭንቅ የሞቱትና የቆሰሉት ወታደሮቻችን ከዚህም በቀር በመርዝ እየተቃጠሉ የሞቱት የባላገሮች ሴቶችና ሕፃናት ጭንቀታቸው በዓይናችን ፊት እየተሣለ ይታየን ነበርና አሁን ደግሞ በእኛ ምክንያት በአዲስ አበባ ይህን የመሰለ የሚያስጨንቅ የመከራ አደጋ እንዲደረግ ለመቁረጥ በጣም የሚያስቸግር ነገር ሆነብን። በምክሩም የነበሩት ሰዎች አገራቸውን የሚወዱ ለእኛም ታማኞች ነበሩና አሁን በአዲስ አበባ ውስጥ ወይም በውጭ ከኢጣልያኖች ጋራ ተዋግተን ድል ለማድረግ የማንችል መሆናችንን እያወቅን ሰላማዊ ሕዝባችንን ለምን እናስፈጀዋለን ከተማውስ ለምን በቦምብ ይቃጠላል። ስለዚህ ቀድሞ እንደታሰበው መንግሥቱ ወደ ጎሬ ይዛወርና ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ በእንደራሴነት እየሠሩ ይቆዩ። ንጉሠ ነገሥቱ ግን የሚያስፈልጉትን ረዳቶች አስከትለው አቤቱታቸውን ቢያቀርቡ ይሻላል ብለው ነገሩን ስለቆረጡ አሳባቸውን ተቀበልነው።

ከዚህም በኋላ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጎሬ ላይ ሆነው የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ እንዲያስሔዱ ትእዛዝ አሳለፍን። ከንቲባውም የከተማውን ዘበኞች እያዘዘ የሕዝቡ ጸጥታ እንዲጠበቅ ፣ ኢጣልያኖችም በአዲስ አበባ ዳር ሲደርሱ እንደ ደንቡ ነጭ ባንዲራ ይዞ በሰላም እንዲቀበላቸው ትእዛዝ ሰጠነው።

ከዚህም በኋላ በባቡር ተሣፍረን ዓርብ ለቅዳሜ አጥቢያ ወደ ድሬዳዋ ወረድን። ድሬዳዋም ሚያዝያ 24 ቀን ቅዳሜ ማታ በደረስን ጊዜ በአዲስ አበባ ሽብር ተነሥቶ ብዙ ሰዎች መሞታቸውንና ብዙ ዕቃም መዘረፉን ብዙ ቤትም መቃጠሉን ሰማን።

በዚሁም በተደረገው ሽብር ምክንያት ኢጣልያኖች ከተማው እንዲቃጠልና ዕቃውም እንዲዘረፍ አዝዘው የሔዱት ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው የሚል እጅግ የተነወረና የተጠየፈ የሐሰት ወሬ ማውራታቸውን ጅቡቲን ካለፍን በኋላ በጋዜጣ

ሰማነው። በጠላት እጅ እንዳይሞት ስናስብለት የነበረው ሕዝባችን በእኛ ምክር እርስ በርሱ እንዲተላለቅና እንዲዘራረፍ እንደምን እናስባለን ? ደግሞስ ይህን የመሰለ አሳብ ካለብን ብዙ ገንዘብ አውጥተን የሠራነውን አዲሱን ቤተ መንግሥት ሳናቃጥል እንደምን ለኢጣልያኖች ትተንላቸው እንሔድ ነበር።

ይህንንም ጉዞዋችንን ስንጀምር ቀድሞ በ1924 ዓ. ም. ዛሬ ነፃነታችንን ለማጥፋት ከመጣው ጠላት ጋራ በተንከኰል ተመሳጥረው በኢትዮጵያ ሁከት ለማድረግ ሲሞክሩ ተገኝተው በዚሁም ተመስክሮባቸው እስከ ዕድሜ ልካቸው እንዲታሰሩ የተፈረደባቸውንና የታሰሩትን ራስ ኃይሉን እስከ ድሬዳዋ አውርደናቸው ነበርና አገራቸውን ኢትዮጵያን የከዱ በመሆናቸው ሞት የሚገባቸው ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር የከዳታቸውን ብድራት ይከፈላቸው ብለን ፈትተን ለቀቅናቸው።

እርሳቸውም ባለፈው ጊዜ የሠሩት ሥራ ሁሉ በደል መሆኑን አምነው ወደ ፊት በሚቻላቸው ሁሉ እየሠሩ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ የመሐላ ቃል ተናግረው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

ከድሬዳዋም በባቡር ተሳፍረን ሚያዝያ 25 ቀን እሑድ ከጧቱ በ4 ሰዓት ተኩል ጅቡቲ በደረስን ጊዜ ፤ አገረ ገዥውና ሌሎችም የፈረንሳይ መንግሥት ባለሥልጣኖች ሕዝቡም ሁሉ ያደረጉልንን የወዳጅነት አቀባበል ለመቸውም አንረሳውም። ለማረፊያም የተዘጋጀልን በቤተ መንግሥቱ ነበርና ከቤተ ዘመዶቻችን ጋራ ወደዚያ ገባን ።

በዚህ ኀዘን በመላበት ሰዓት ቀድሞ በአንዳንድ ምክንያት ወደ ጅቡቲ በምንወርድበት ጊዜ ከተደረገልን አንዳችም ሳይጐድል የተደረገውን የወዳጅነት አቀባበል ስናይ ልባችን መጽናናቱን ለመናገር እንችላለን ።

# ምዕራፍ 48

## ከጅቡቲ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መሔዳችን ።

ከአዲስ አበባ ስንነሣ የቀረጥነው አሳብ ወደ ጀኔብ ሔደን ከግፈኛው ከኢጣልያ የደረሰብንን የመከራ ችግር ለመንግሥታት ማኅበር በቃላችን አመልክተን ፍርድ እናገኛለን በማለት ነበር። ነገር ግን አስቀድሞ ለእቴጌና ለቤተ ዘመዶቻችን ከእኛም ጋራ እየተሰደዱ ለወጡት ለብዙዎች የጦር አለቆች የሚቀዩበት ስፍራ ማዘጋጀት የሚያስፈልግ መሆኑን ስለ ተረዳነው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሔድ ቆረጥን ።

ከዚህም በኋላ በሚያዝያ 25 ቀን እንተርፕሪዝ የሚባለው የእንግሊዝ መንግሥት የጦር መርከብ ጅቡቲ ደረሰና ለመሳፈሩ እንድንዘጋጅ ካፒታኑ አስታወቀን ።

ይኸውም የጦር መርከብ በቶሎ ወደ ጅቡቲ የደረሰበት ምክንያት እኛ በማይጨው ላይ ከኢጣልያኖች ጋራ ከተዋጋን በኋላ ከአዲስ አበባ ጋራ መገናኛችንን ስልኩንም ራዲዮኑንም በአይሮፕላን ቦምብ እየጣሉ ስለ አጠፉት አንድ ወር ያህል ሚኒስትሮቻችን ከእኛ ጋራ ለመገናኘት አልቻሉም ነበርና ወሬያችን ስለ ጠፋባቸውና ስለ ተቸገሩ እቴጌንና ቤተ ዘመዶቻችንን ወደ ኢየሩሳሌም ሰደው እነሱ ወደ ኢትዮጵያ ምዕራብ ሔደው ጎሬ ላይ መንግሥቱን ለማቆም አስበው የእንግሊዝ መንግሥት ለእቴጌ የጦር መርከብ እንዲልክ አዲስ አበባ ካለው ከእንግሊዝ ሚኒስትር ጋራ ተነጋግረው የእንግሊዝ መንግሥት መፍቀዱን አስታውቀ ስለ ቆየ ነው።


አንዳንድ ሰዎች ግን በእንግሊዝ የጦር መርከብ ስለ መጓዛችን ምክንያት እኛ ወደ አውሮጳ ለመምጣት የቆረጥነው አንድ ወዳጅ የሆነ መንግሥት በነገሩ ገብቶ ስለ መከረ ነው ብለው እስከ ማውራት ደረሱ። ይህም በጭራሽ ሐሰት የሆነ ልብ ወለድ ነው እንጂ እውነት ነገር የለበትም። ዋናው ምክንያት ግን ከዚህ በላይ እንዳስረዳነው ነው። ደግሞም የምንሔደው ወደ እንግሊዝ የማንዴት ግዛት ወደ ኢየሩሳሌም ስለ ሆነ በእንግሊዝ የጦር መርከብ መሔድ የሚገባ መሆኑን ማንም አይስተውም። ይህንንም አስበው የተናገሩ ሰዎች የእንግሊዝን የእንግዳ ተቀባይነት ባሕርይ ባለማወቃቸው ይሆናል።

በማግስቱ ሰኞ ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ. ም. ከእኩለ ቀን በኋላ 10 ሰዓት ያህል ሲሆን ወደ ጦር መርከብ ገባን። መርከቡም ጉዞ ሊጀምር ጥቂት ሲቀረው በውጋዴን በኩል ሲከላከሉ የቆዩት የጦር አለቆች ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል ፣ ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ይናዱ ፣ ደጃዝማች ዓምዴ ሀብተ ሥላሴ ፣ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ፣ ደጃዝማች መኰንን እንዳልካቸው ባለፈው የሠሩትን ራፖር ለማስረከብና ወደ ፊትም ለሚሠሩት ትእዛዝ ለመቀበል ወደ እኛ መጥተው ነበርና ራፖራቸውን አስረክበው ለወደ ፊትም ትእዛዝ ተቀብለው በታላቅ ኀዘን እየተሰናበቱ ወጡ። በኋላ ግን ከደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ይናዱ በቀር የቀሩት በሌላ መርከብ እንዲመጡ ሆነ።

መርከቡም ጉዞ ሲጀምር የፈረንሳይ ሱማሌ ቅኝ አገር መንግሥት መድፍ እያስተኰሰ አይሮፕላኖችም በምንጓዝበት መርከብ ዙሪያ እንዲያንዣብቡ አድርጎ የመሰናበት ሰላምታ ስለ አደረገልን ልባችን በደስታ ተነካ።

ሌሎችም አምስት የእንግሊዝ የጦር መርከቦች (ቶርፔዶዎች) እኛ ያለንበትን የጦር መርከብ በሩቅ ይከተሉ ነበር ።

የስዊዝን ካናል አልፈን ፖርት ሳይድ ስንደርስ በፖርት ሳይድ ያለው ቆንስላችንና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ባንዲት ጀልባ ውስጥ ሆነው እጅግ የተከበረውን ሦስት ቀለም ሰንደቅ ዓላማችንን ይዘው ጀልባቸውን በመርከቡ አጠገብ እየቀዘፉ እንባቸውን በመሐረማቸው ሲጠርጉ በማየታችን ያ ትልቁ ኀዘናችን ተቀስቅሶ ያውከን ነበር። ይልቁንም መርከቡ በዚያ አልቆመም ነበርና ሳንገናኛቸው በማለፋችን በሁላችንም ልብ ታላቅ ኀዘን ሆነ። በ5ኛው ቀን በሐይፋ ወደብ ደረስንና መርከባችን ቆመ። በዚያም ሌሎች የእንግሊዝ የጦር መርከቦች ተሰልፈው ይጠብቁን ነበር።





እኛም ከነበርንበት መርከብ ጥቂት ራቅ ብሎ ካርኔሮ የሚባል የኢጣልያ መርከብ በባንዲራ አጊጦ ቆሞ ነበር። ይኸውም እኛ ከአገራችን ወጥተን በመምጣታችን ላይ አሁን ደግሞ የኢጣልያን መርከብ በማየታችን የምናዝን መስሏቸው በተንኰል ያደረጉት መሆኑ አይጠረጠርም።

ከመርከብም ስንወርድ የእንተርፕሪዝ መርከብ ሙዚቀኞች የኢትዮጵያን የሕዝብ መዝሙር ድምፅ እየነፉልን ወረድን። ከመሬትም ወርደን የክብር ሰላምታ ለመስጠት በተሰለፉት ወታደሮች መካከል ስናልፍ እንደዚሁ የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር ድምፅ ያሰሙን ነበር። እርስ በርሳቸውም ጠብ አንሥተው የነበሩት እስራኤላውያንና ዐረቦች እንኳ ጠባቸውን ረስተው ባንድነት ቆመው በደስታና በአክብሮት ይመለከቱን ነበር።

ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተን በባቡር ማቆሚያ ስንደርስ የእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣኖች በክብር ተቀበሉን። በመጀመሪያ ወደ ጎልጎታ ገብተን የጌታችንን መቃብር ከተሳለምን በኋላ ወደ ኪንግ ዳዊት ሆቴል ገባን።

በማግስቱም ደብረ ገነት ወደሚባለው ገዳማችን ወጣን። በኢየሩሳሌም ከብዙ ዘመን ጀምሮ ጸንቶ የሚኖር ሰፊ ገዳም አለና በዚያ ከኢትዮጵያ እየመነኑ የሚመጡ ወንዶች መነኩሳትና ሴቶች መነኩሳይያት ተማጥነው ይኖሩበታል። በዚህም ገዳም በአማርኛ ቋንቋ እየተነጋገሩ ፣ በግእዝ ቋንቋ እየቀደሱ የሚኖሩበት ስለ ሆነ ደስታቸው ትልቅ ነው።

አሁን ግን አጥቂው ጠላታችን በዋናው ከተማችን በአዲስ አበባ መግባቱን በመስማታቸውና እኛም ከአገራችን ወጥተን ወደ ባዕድ አገር መምጣታችንን በማየታቸው ይልቁንም በኢጣልያ ጦርነት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ብዙ መጻሕፍት መቃጠላቸውን ብዙ መነኲሳትና ካህናት ሴቶችና ሕፃናት ፣ ሽማግሎችም በጋዝ መርዝና በቦምብ ማለቃቸውን ስለ ነገርናቸው በእንባ ይራጩ ጀመር።

ከዚህ በኋላ ከአዲስ አበባ ስንነሣ እንዳሰብነው ከአገራችን ወጥተን የመጣንበትን ምክንያቱን ለማስረዳት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ለመንግሥታት ማኅበር ወደ ጄኔብ አሳለፍን ።

የመንግሥት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ፡

ጄኔብ ።

ማኅበረተኞች ለሆኑት መንግሥቶች ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እንዲያስታውቁልን እንለምናለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጽሞ እንዳያልቅ ስንል ወደ ውጭ አገር በመውጣታችን ባዲሱ ዘመን ታይቶ ተሰምቶ የማያውቅና የማይመዛዘን ከሰው የተፈጥሮ ባሕርይ የተላለፈ የግፍ ጦርነት እንዲያልቅ ለማድረግና ጥንታዊ የሆ ነው የኢትዮጵያ ነፃነትና የዓለም መንግሥቶች ሰላም መሠረት የዓለምም መንግሥቶች የውጭ ግዴታ መከበር ከኢጣልያ ጠንቅ እንዲጠበቅ ለማድረግ ራሳችንን በሰላምና በነፃነት እንድንሰጥላት ቆርጠናል።

ከመጀመሪያው አንሥተን ሰላም እንዳይናወጥ የሚቻለንን ሁሉ አድርገናል። ኢጣልያ እንደ ዝናብ አድርጋ በጋዝ መርዝ መውጋት እስከትጀምር ድረስ መከላከላችን ሊቀጥል አለመቻሉ ባንከላከልም ፍሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለቅ ብቻ እንደሚሆን ግልጥ እስቲሆን ለአገራችን በመታመን ተከላክለንላታል።

አሁንም የመንግሥታት ማኅበር ውል እንዲከበር ለማድረግ የሚደክመውን ድካም እንዳያቋርጥ በማይገባ በሠራዊት ጉልበት የውል ግዴታዎቿን ጥላ ገዥ ነኝ የምትለውንና ግዛት ማስፋቷን እንዳያውቁላት እንጠይቃለን።

ግንቦት 11 ቀን 1928 ዓ. ም. ኢየሩሳሌም ፡
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ።





በዠኔቭ ጉባኤ የኢትዮጵያን ጉዳይ ላማመልከት ንግግር በምናደርበት ሰዓት

# ምዕራፍ 49

## ከኢየሩሳሌም ወደ ሎንዶን ስለ መሔዳችን ።

ከኢየሩሳሌም ወደ ሎንዶን ለመሔድ ፈቃድ ጠይቀን ከተፈቀደልን በኋላ እቴጌንና ቤተ ዘመዶቻችንን ከእኛም ጋራ የመጡትን የጦር አለቆች በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አድርገን ከልጆቻችን አልጋ ወራሻችንን መርድ አዝማች አስፋ ወሰንንና ፣ የሐረር መስፍን መኰንንን ፣ ሴቲቱ ልጃችንን ፀሐይን ፣ ለሰሜኑ ጦር ጠቅላይ አድርገነው የነበረውን ራስ ካሣን አስከትለን በግንቦት 15 ቀን ከኢየሩሳሌም ወደ ሐይፋ ወረድን። ከዚያም ኬፐታውን በሚባል በእንግሊዝ የጦር መርከብ ተሳፍረን ወደ ጅብራልታር ተጓዝን ።

ከጅብራልታርም አሪያን ላይን በሚባል በመንገደኞች መርከብ ተዛውረን ሳውትሔምቶን በሚባል በእንግሊዝ የወደብ ከተማ ከመርከብ ወርደን ከዚያ በባቡር ወደ ሎንዶን ተጓዝን ።

በሎንዶንም የባቡር ማቆሚያ የእንግሊዝ ሕዝብ የክብር አቀባበል ካደረገልን በኋላ ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀልን ስፍራ ሔድን። በዚያም የተሰባሰበው ሕዝብ የኀዘናችን ተካፋይ መሆኑን ስለ ገለጠልን የእንግሊዞችን ርኅሩኀነታቸውንና ደግነታቸውን አደነቅን ።

ከጥቂት ቀን በኋላ እኛ ብዙ ሕዝብ በሚሰበሰቡበት ልጃችን ፀሐይም ብዙ ሴቶች በሚሰበሰቡበት ስፍራ እየሔድን ኢጣልያ በክርስቲያኑና በየዋሁ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሠራችውን የጭካኔ ሥራ እየገለጥን ስላስረዳናቸው የእንግሊዝ ሕዝቦች ግፍን የማይወዱ ፣ የእውነት ፍርድን የሚፈልጉ በመሆናቸው ቀድሞ በወሬ የሰሙትን የመከራችንን ነገር አሁን ደግሞ በቃላችን ስላስረዳናቸው ሁሉም የኀዘናችን ተካፋዮች መሆናቸውን ገለጡ።

ነገር ግን ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የሠራችውን የግፍ ሥራ ለመንግሥታት ማኅበር አመልክተን ነበርና ማኅበሩ መክሮ ያቀረበውን የዕርቅ አሳብ እኛ ተቀብለን ኢጣልያ ሳትቀበል ስለ ቀረችና ወሰን አልፋ አደጋ ስለጣለች በማኅበሩ ቃል ኪዳን በ16ኛው ክፍል እንደ ተጻፈ ጭቆና አድርገውባት ጭቆናው ዐሥር ወር ያህል ከቆየ በኋላ ነገሩ በእንግሊዝ ፓርላሜንት ተነሥቶ ኢጣልያ ምንም ጭቆና (ሳክሲዮን) ቢደረግባት በኢትዮጵያ ላይ የግፍ ሥራዋን እያበዛች ከመሔድ በቀር ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነገር አልተገኘምና በከንቱ የዓለምን ንግድ ከማሰናከል ጭቆናው ቢቀር ይሻላል በማለት ብዙ ቀን ተከራከሩበት። ከዚያም በኋላ ከሕዝቡ ወገን ብዙዎቹ ኢጣልያ የግፍ ሥራዋን እያበዛችና እየጨመረች ከሔደች ሌላ ጭቆና እንዲጨመርባት ያስፈልጋል ብለው ነበር። ነገር ግን መቼም ቢሆን ከሕዝብ አሳብ የመንግሥት አሳብ እንዲያሸንፍ የታወቀ ነውና ጭቆናው እንዲቀር መቆረጡን ሰማን።


OR
Nº33-36

# ምዕራፍ 50

## ከሎንዶን ወደ ጄኔብ ሔደን ከመንግሥታት ማኅበር ፍርድ ስለ መጠየቃችን ።

እኛ ከወልወል አደጋ በፊት ከዚያም በኋላ ቢሆን እምነታችንን በመንግሥታት ማኅበር እያጸናን መሔዳችንን አልተውንም ነበርና ይህን የሚያዩ አንዳንድ ሰዎች በፊትም ቢሆን በመንግሥታት ማኅበር ላይ መታመናችሁን ትታችሁ ለጦርነት ተዘጋጅታችሁ ቆይታችሁ በነበረ ይህ ሁሉ አደጋ አይደርስባችሁም ነበር አሁንም ወደ ፊት በመንግሥታት ማኅበር ላይ መታመናችሁ ከንቱ ነው እያሉ በልባችን ጥርጣሬ ለማግባት ይሞክሩ ነበር። እኛ ግን እንኳን የ52 መንግሥታት ቃል ኪዳንና የሁለት ሰዎችም ቃል ኪዳን ቢሆን ተከብሮ መኖር የሚገባ መሆኑን እናውቃለንና እስከ መጨረሻው ቀን እምነታችንን ከመንግሥታት ማኅበር ላይ አናጐድልም በማለታችን ከመጽናት በቀር አሳባችንን አለወጥነውም። ከአገራችንም ወጥተን የመጣነው ማኅበሩ ትክክለኛ ፍርድ እያሳጣንም በማለት ችግራችንን ለማኅበሩ በቃል ለማስረዳት ነው።

በሎንዶንም ሳለን የመንግሥታት ማኅበር 1936 ዓ. ም. በጁን 26 (ሰኔ 19 ቀን 1928) በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተነሣውን ጠብና የሌላውንም ትንንሽ ጉዳይ ለመነጋገር ቀጠሮ ማድረጉን ስለ ሰማን ወደ ጄኔብ ለመሔድ ቁርጥ አሳብ አደረግን። ለቀጠሮውም ስምንት ቀን ሲቀረው ከወዳጆቻችን አንዳንዶቹ እየመጡ ጃንሆይ ወደ ጄኔብ ባይሔዱ ይሻላል ምክንያቱም ራስዎ ሔደው በጉባኤው ፊት ቀርበው ከተነጋገሩ በኋላ ትክክለኛ ፍርድ ሳያገኙ የቀሩ እንደ ሆነ የባሰ ኀዘን ይሆንብዎታልና መላክተኞች ቢልኩ ይሻላል በማለት ነው ይሉን ነበር። አንዳንዶቹ ደግሞ በአሁኑ በትልቁ ችግርዎ ጊዜ ራስዎ በጉባኤው ፊት ቀርበው ማናቸውንም ነገር በቃልዎ እያስረዱ ካልተናገሩ መላክተኞች ብቻ ልከው ቢቀሩ ነገሩ ለጉባኤው ከብዶ አይታይምና ባይቀሩ ይሻላል እያሉ የወዳጅነት ምክር ይመክሩን ነበር።

እኛም ከአገራችን ከኢትዮጵያ ወጥተን የመጣንበት ምክንያቱ ራሳችን በመንግሥታት ማኅበር ፊት ቀርበን ግፋችንን በቃላችን ለማመልከት እንጂ መልክተኛ ለመላክ አልነበረምና በሰኔ 18 ቀን ልዑል ራስ ካሣን ፣ ደጃዝማች ነሲቡን ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይን ፣ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስን ፣ አቶ ሎሬንሶ ታእዛዝን ፣ አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅንን አስከትለን ከሎንዶን ተነሥተን በፓሪስ ላይ አልፈን በማግስቱ ጧት በባቡር ጄኔብ ደረስን። ከዚያም በኋላ በሰኔ 23 ቀን 1928 ዓ. ም. የ52 መንግሥታት እንደራሴዎች በተሰበሰቡበት ቤት ገብተን አሳባችንን ለመናገር ቀጠሮ ተደርጎልን ነበርና በቀጠሮው ቀን ሔደን በማንበቢያው ስፍራ ስንቆም ለወሬ የመጡት ኢጣልያኖች ንግግራችንን ለማሰናከልና እንዳይሰማ ለማድረግ ሲሉ እያከታተሉ ያፏጩ ጀመር። በዚህ ጊዜ የሩማንያ መልእክተኛ ሙሴ ቲቱሌስኪ «ስለ ፍርድ ስትል እነዚህን አውሬዎች ዝም አሰኝ» ብሎ ለጉባኤው ፕሬዚዳንት ለሙሴ ቫን ዚላንድ አመለከተ።

የጉባኤውም ፕሬዚዳን ኢጣልያኖቹ በብዙ መንግሥታት እንደራሴዎች ፊት የብልግና ሥራ መሥራታቸውን አይቶ ዘበኞች በግድ እንዲያስወጧቸው ስለ አዘዘ እየያዙ አስወጧቸው።

ከዚህም በኋላ እኛ በአማርኛ ቋንቋ አነበብንና ወዲያው በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ እየተተረጐመ ጉባኤው ሁሉ እንዲሰሙት ተደረገ። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

ክቡር ፕሬዚዳን

ክቡራን የመንግሥታት መልክተኞች ።

በፈረንሳይ ቋንቋ ብነግራችሁ እወድ ነበር። ነገር ግን አሳቤን በመንፈሴ ኃይል ሁሉ ከልቤ ለመናገር የሚቻለኝ በአማርኛ ቋንቋ ስለ ሆነ በፈረንሳይ ቋንቋ ባለመናገሬ የመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ ይቅርታ እንዲያደርግልኝ እለምናለሁ።

እኔ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፡

የዛሬ ስምንት ወር አምሳ ሁለት መንግሥታት የዓለምን መንግሥታት ሕግ የተላለፈ የአጥቂነት ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ መደረጉን አረጋግጠው ካስታወቁ በኋላ ለሕዝቤ ይደረግለታል ብለው ቃል የገቡለትን እርዳታና የሚገባውንም ትክክለኛ ፍርድ ለመጠየቅ ዛሬ ከዚህ ቀርቤአለሁ ።

ለነዚህም ለአምሳ ሁለት መንግሥታት የኢትዮጵያን ሕዝብ አቤቱታ ለማቅረብ ከንጉሠ ነገሥቱ የሚበልጥ ሌላ ሰው አይገኝም።

በዚህ ጉባኤ ያንድ መንግሥት ንጉሠ ነገሥት ወይም ፕሬዚዳን ቀርቦ ሲናገር ምናልባት ገና ዛሬ መጀመሩ ነው። ደግሞ ያንድ አገር ሕዝብ ይህን የመሰለ ግፍ ሲሠራበትና አሁንም በአጥቂው እጅ ለመውደቅ ሲደርስ የታየው በእርግጥ ዛሬ ብቻ ነው።

ደግሞ አንዱ መንግሥት የሌላውን መንግሥት አገር በጦርነት እንዳይወስድበትና ንጹሓን የሆኑትንም የሰው ወገኖች ኃይለኛ በሆነው በጋዝ ቶክሲክ መርዝ እንዳይፈጃቸው ተብሎ በዓለም ካሉ መንግሥቶች ጋራ በተዋዋለው ውል በክብርና በግልጥ የሰጠውን ቃል ኪዳን ተላልፎ በጨካኝነት መሣሪያ ያንዱን ሕዝብ ዘር በቁርጥ ለማጥፋት ከዚህ ቀድሞ የተነሣና ምሳሌ የሆነ መንግሥት አልታየም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነቴ ወደ ጄኔብ የመጣሁበት ምክንያት ለጦር ሠራዊቱ ዋና መሪ ሆኘ ራሴ ከተዋጋሁ በኋላ ከብዙ ሺ ዘመናት በፊት ጀምሮ የቆየውን ነፃነቱን ለመጠባበቅ ስለሚታገለው ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ለመከላከልና ይህንም ከፍ ያለ የተገባኝን ሥራ ለመፈጸም ነው። እነዚህም የተከተሉኝ ሹማምንቶች ራሳቸው ከደረሰባቸውና ምስክር ከሆኑት ከሚያሰቅቅ ነገር በሕዝቤም ላይ ከተደረገው ስቃይ የዓለምን መንግሥታት እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው እለምናለሁ።

በጄኔብ የተሰበሰቡትና ለብዙ ሚሊዮን ሰዎች ሴቶችና ሕፃናት ሕይወት አላፊ ለሆኑት መንግሥታት እንደራሴዎች በእነዚህ ፍጥረቶች የደረሰባቸውን የሞት አደጋ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰባትን ዕድል በዝርዝር አስረዳለሁ ።

የኢጣልያ መንግሥት ጦርነት ያደረገው በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ከጦርነቱ ስፍራ በራቁት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ በድንጋጤ ለመግደልና ዘራቸውንም ለማጥፋት አደጋ እየጣለ ወጋቸው።

ጦርነቱ እንደ ተጀመረ በ1928 ዓ. ም. የኢጣልያ አይሮፕላኖች በጦር ሠራዊቶቹ ላይ ጋዝ ላክሪሞገን ያለበት ቦምብ ጣሉባቸው። ይህም ቦምብ እጅግ አልጐዳቸውም ነበር። ምክንያቱም ወታደሮቹ ቦምብ በወደቀ ጊዜ ጋዙን ነፋስ እስኪወስደው ድረስ መበታተኑን ስለ ዐወቁበት ነው ።

ከዚህ በኋላ የኢጣልያ አይሮፕላኖች ኤፒሪት የተባለውን ጋዝ መጣል ጀመሩ። በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ላይ ኤፒሪት ያለበት በርሜል ወደቀባቸው ይኸውም ሆኖ የኤፒሪቱ ጋዝ ያደረገው ጉዳት የለም። ምክንያቱም የኤፒሪቱ ውሃ የሚያገኛቸው ወታደሮች ጥቂቶች ስለ ነበሩና በርሜሉ በመሬት ላይ ሲወድቅ ወታደሮቹ ሕዝቡም መርዝ ያለበት መሆኑን ስለ ዐወቁት ነው።

የኢጣልያ የጦር ጠቅላይ ሹም መቀሌን የኢትዮጵያ ወታደሮች በከበቡ ጊዜ የኢጣልያ የጦር ሠራዊት መፈታቱን ስለ ተረዳውና ስለ ሥጋ ሌላ ዓይነት የኤፒሪት አጣጣል አደረገ። ይህንም አደራረግ አሁን ለዓለም ገልጦ ማስታወቅ የተገባኝ ነው።

በአይሮፕላኖቹ ላይ የኤፒሪቱን ውሃ የሚረጭ መኪና ተዘጋጅቶ ሰፊ በሆነው አገር ላይ ሞትን የሚያመጣ ረቂቅ ዝናብ እንዲወርድበት ተደረገ ። የኢጣልያም አይሮፕላኖች አንድ ጊዜ 9 ፡ 15ም እየሆኑና እየተመላለሱ የኤፒሪት

ዝናብ ሳያቋርጥ እንዲወርድ አደረጉ። በጥር መጨረሻ 1928 ዓ. ም. ጀምሮ በወታደሮቻችን፣ በሴቶችና በልጆች፣ በከብቶችና በፈሳሽ ወንዞች በኩሬዎችና በከብት መሰማሪያዎች ቦታዎች ላይ ሳያቋርጥ ሞት የሚያመጣ ይህ ዝናብ ዘነበባቸው። ፍጡር የሆኑትን ሁሉ በፍጹም ለማጥፋት ውሃውንና ለከብት የሚሆነውንም ሣር መርዝ ብቻ ለማድረግ የኢጣልያ የጦር ሹም አይሮፕላኖቹ ይህንኑ ሥራቸውን እየተመላለሱ እንዲሠሩ አደረገ። ዋና የጦርነት መሣሪያ ያደረገው ይህንኑ ነው።

ይኸም በረቂቅነት የሚሠራ የጭካኔ ሥራ ጦርነት ከሚደረግበት ቦታ በራቁት ቦታዎች የሚገኙትን ሕዝብ አጠፋቸው። አገራቸውንም ምድረበዳ አደረገው። አሳቡም በሚበዛው በኢትዮጵያ ግዛት ክፍል ላይ ድንጋጤንና ሞትን ለመዝራት ነበር።

እጅግ የሚያሳዝን ነገር የሚያመጣ ይህ ብልሃት ተፈጸመበት። ሰዉም ከብቱም በፍጹም አለቀ። ከአይሮፕላንም የሚወርደው የሞት ዝናብ የሚነካውን ሁሉ እያሰቃየ ያባርር ነበር። ይህም የመርዝ ዝናብ የዘነበበትን ውሃ የሚጠጡ መርዙም የሚነካውን ምግብ የሚመገቡ በታላቅ ሥቃይ አለቁ። በኢጣልያ ኤፒሪት ምክንያት በብዙ ሺ የሚገመቱ ሰዎች ሞቱ። እኔም ወደ ጄኔብ ለመምጣት የቆረጥሁት የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበትን ሥቃይ ለሠለጠነው ዓለም ለማስታወቅ ነው።

ይህንንም የማያከራክር ምስክርነት ከእኔና ከነዚህ ከተከተሉኝ በጦርነቱ ላይ ከነበሩት ሰዎች የተሻለ ለመንግሥታት ማኅበር የሚያስረዳ አይገኝም።

አውሮጳም ይህን ነገር እንዳለቀ አድርጎ ቢቆጥረው በራሱ የሚደርስበትን የሚጠብቀውን ይህን ዕድል ማሰብ ይገባዋል ።

ይህ ሁሉ መከራ በጦር ሠራዊቴና በሕዝቤ ላይ ሲወርድበት መላክተኞቼ ለመንግሥታት ማኅበር የሚያቀርቡት አቤቱታ ምላሽ ሳያገኝ ቀረ ። መላክተኞቹም በጦርነቱ ውስጥ አልነበሩምና በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን መከራ እነሱ ያላዩት ስለ ሆኑ በሕዝቤ ላይ የተፈጸመበትን የወንጀል ሥራ ለማስረዳት ራሴ ለመምጣት ቆረጥሁ።

በኢትዮጵያ ላይ በየጊዜው የደረሰውን ዛሬ ለተሰበሰበው ለመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ ማሳሰብ የሚያስፈልግ አይደለምን?

ከሃያ ዓመት በፊት ጀምሮ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ሆኜ ፡ በኋላም ንጉሠ ነገሥት ተብዬ የሕዝቤ መሪ ሆኜ ስሠራ ላገሬ ያዲሱ ሥልጣኔ ጥቅም እንዲደርሰው በተለየም ጎረቤት ከሆኑት መንግሥቶች መልካም የጉርብትና መገናኛ ለማቆም መድከሜን አላቋረጥሁም። በተለየም ከኢጣልያ መንግሥት ጋራ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጦርነት እንዳይነሣ የሚከለክል በሁለቱ መንግሥቶች መካከል የሚነሣው ክርክር በወዳጅነትና በሽምግልና ዳኞች እንዲጨረስ የሚያደርግ የሠለጠኑት የዓለም መንግሥታት ለሕዝብ ሰላም እንዲሆን መሠረት ያደረጉትን የወዳጅነት ውል በ1920 ዓ. ም. ተዋዋልሁ።

የ0ሥራ ሦስቱ መንግሥታት ጉባኤ በመስከረም 25 ቀን 1928ዓ. ም. ባቀረበው ማስታወቂያ የደከምሁበትን ሥራ ዐውቆ በግልጥ ተናግሮልኛል። የተናገረውም ቃል ይህ ነው።

«ኢትዮጵያ ወደ መንግሥታት ማኅበር በመግባትዋ ግዛትዋ እንዳይነካባትና ነፃነትዋ እንዳይጠፋ አዲስ መተማመኛ በመስጠት አሁን ካለችበት የሥልጣኔ ደረጃ ከፍ ወዳለው እንድትደርስ መንግሥታት አስበው ነበር ። አሁን ባለችው በኢትዮጵያ ውስጥ በ1915 ዓ. ም. ይታይ የነበረው የጸጥታ ማጣትና የሽብር ኑሮ አይታይባትም። ይልቁንም አገሩ ከፊተኛው ይበልጥ አንድ ሆኖአል። የዋናውም መንግሥት ሥልጣን ከቀድሞው ይበልጥ ይከበራል» ይላል።

የኢጣልያ መንግሥት በኢትዮጵያ ሽብር ለማንሣት አንዳንድ ሰው በመግፋት ለዐመፀኞችም መሣሪያ በመስጠት ይህንም የመሰለ ብዙ ዓይነት ችግር ባያደርግብኝ ለሕዝቤ የሠራሁት ሥራ ከዚህ የበለጠ ፍሬ አፍርቶ ይጠቅም ነበር።

የሮማ መንግሥት ዛሬ በግልጥ ማድረግ እችላለሁ ብሎ የተነሣበትን ኢትዮጵያን በጦርነት ለመውሰድ ያሰበውን አሳብ ባለማቋረጥ ሲያዘጋጅ ኖረ። እንዲሁም ከእኔ ጋራ የፈረመው ውል ሁሉ ከልቡ አልነበረም። ይህንም የወዳጅነት ውል የፈረመው አሳቡን ለመሸፈኛ እንዲያገለግለው ኖርዋል ።

የኢጣልያ መንግሥት ዛሬ በጉልበት ያገኘውን ለመሥራት ከ14 ዓመት ጀምሮ መዘጋጀቱን አረጋግጦ አስታውቋል። ስለዚህ በ1915 ዓ. ም. ኢትዮጵያ በመንግሥታት ማኅበር እንድትገባ በነገሩ መደገፉና መርዳቱ በ1920 ዓ. ም. የወዳጅነት ውል መዋዋሉ ጦርነት ከሕግ የወጣ ነገር ለመሆኑ በፓሪስ ላይ የተደረገውን ውል መፈረሙ የዓለምን እምነት የሚነዳ ሥራ ለመሥራት ነው ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያ መንግሥት ግን በዚህ በታላቅ ክብር በተደረገው ውል ሁሉ ይታየው የነበረው በሰላም መንገድ ላይ ሆኖ አገሩን ወደ ሥልጣኔ ለመምራት በሙሉ ልቡና በሙሉ ኃይሉ ለመሥራት የጀመረውን ሥራ ለመፈጸም እንዲቻለው እንደገና መተማመኛ የሚሆነው ነገር ማግኘቱ መስሎት ነበር።

በህዳር ወር 1927 ዓ.ም የተደረገው የወልወል ጠብ ለእኔ በድንገት ከሰማይ እንደ ወረደ መብረቅ ቁጣ ሆኖ ተሰማኝ። ። ኢጣልያ ጠብ እንዲነሣ መፈለጓ ግልጥ ነበር። እኔም ይህንኑ ለመንግሥታት ማኅበር ማሰማቱን አልተውሁም። ስለዚህም በ1920 ዓመተ ምሕረት በተደረገው ውል በተጻፈው ቃል የመንግሥታት ማኅበርም በቆመበት መሠረት በሽማግሌም ዳኝነት በዚህ ሁሉ መንገድ ነገሩ እንዲታይ ጠየቅሁ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ መጥፎ ዕድልዋ ሆኖ አንዳንድ መንግሥቶች በአውሮጳ አኳኋን ምክንያት በማናቸውም ረገድ ቢሆን የኢጣልያን ወዳጅነት ማግኘት በግድ የሚያስፈልግ መስሎ ታያቸው የኢጣልያም መንግሥት በኃይል ለጠየቀው ጥያቄ የተሰጠው ዋጋ የኢትዮጵያን ነፃነት አሳልፎ መስጠት ሆነ። በመንግሥታት ማኅበር ውል የዓለም መንግሥታት የገቡት ግዴታ ቀርቶ ይህ በስውር የተደረገው ውል በዚያ ጊዜ ለተነሣው ለኢትዮጵያ ጉዳይ ሁሉ እጅግ የተጫነው ሆነ። በዚሁም ምክንያት በተደረገው ጥፋት ኢትዮጵያና ዓለም ሁሉ እጅግ ተቸገሩበት እስካሁንም ድረስ ይህ ችግር አላቋረጠም።

ይኸውም በመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው የመንግሥታት ማኅበር ውል መሻር አንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ አልቀረም። የሮማ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርገውን ፖለቲካ የሚያበረታታለት ስለ ሆነ በኢትዮጵያ ላይ በመጫን የተጀመረው ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢጣልያን ገዥነት እንዲቀበል ለማድረግ የማይበቃ የሆነ እንደ ሆነ በጦርነት አደርጋለሁ ብሎ ይዘጋጅ ጀመረ። ለዚሁም ፡ ጊዜ ማግኘት የማያስፈልግ ሆነበት። ለዕርቅ የተመረጡት የሽምግልና ዳኞች ሥራቸውን ለመጀመር እንዳይችሉ በብዙ ዓይነት ተንኰል እየተደረገ በልዩ ልዩ ረገድ ነገሩ እንዲጐተት ሆነ። ይኸውም የሽምግልና ዳኞች ሥራ እንዳይፈጸም ብዙ ዓይነት መሰናከል ተደረገበት። አንዳንዶቹም መንግሥቶች ለዚህ ለሽምግልና ዳኝነት የሚሆን ሰው ከዜጎቻቸው ውስጥ እንዳይመረጥ ለመከልከል ፈለጉ። የሽምግልናውም ዳኝነት ሥራ ከተቋቋመ በኋላ ነገሩ ለኢጣልያ በመልካም መንገድ እንዲፈረድ ዳኞቹን ተጭነዋቸው ነበር። ነገር ግን ይህ ሁሉ በከንቱ ተደከመበት። ሁለት የኢጣልያ ሰዎች የነበሩትም የሽምግልና ዳኞች ባንድ ቃል ሆነው በወልወልም ነገር ቢሆን ከዚያም በኋላ በተደረገው ነገር ቢሆን ኢትዮጵያን በዓለም መንግሥታትፊት አላፊ የሚያደርጋት ነገር የለም ብለው ፈረዱ።

ይህም ፍርድ ከተፈረደ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣልያ ጋራ አዲስ የወዳጅነት ዘመን ይጀምራል በማለት በእርግጥ ተማምኖ ነበር። ለሮማም መንግሥት በእውነተኛ መንገድ ለማግኘት እጄን ዘረጋሁ።

ከኅዳር ወር 1926 ዓ. ም. ጀምሮ እስከ መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ. ም. በየጊዜያቱ የሆነውን ነገር ሁሉ በዝርዝሩ በመስከረም 25 ቀን 1928 ዓ. ም. የተሰበሰበው የ13 መንግሥቶች ኮሚቴ ባደረገው ራፖር ለዋናው ማኅበር ጉባኤ አስታወቀ።

በዚሁም ራፖር ከተጻፈው ከተቆረጠው ነገር በቁጥር 24 25ና 26 ብቻ የተጻፈውን ቃል አሁን አስታውሳለሁ።

የኢጣልያ ማስታወሻ ለምክሩ ጉባኤ የተሰጠው በነሐሴ 29 ቀን 1927 ዓ. ም. ነው። የኢትዮጵያ ማስታወሻ የተሰጠው ግን የመጀመርያው አቤቱታ በታኅሣሥ 5 ቀን 1926 ዓ. ም. ነው። በነዚህ በሁለቱ ጊዜያቶች መካከል የኢጣልያ መንግሥት ነገሩ በምክሩ ጉባኤ ፊት ቀርቦ እንዳይታይ ሲል 1920 ዓ.ም በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል በተደረገው ውል በተጻፈው ቃል ብቻ ነገሩ ይፈጸማል እያለ እንዲቆይ አደረገ። በዚህም ጊዜ ሁሉ በምሥራቅ አፍሪቃ በኩል የኢጣልያ ወታደር እየተከታተለ ይላክ ነበር። የኢጣልያ መንግሥት ወታደር የላከበት ምክንያት የኢትዮጵያ መንግሥት ለጦርነት የሜዘጋጅ በመሆኑ ለቅኝ አገሩ የሚያሠጋው ስለሆነ ለመከላከል የሚያስፈልገው በመሆኑ ነው ብሎ ነገሩን ለምክሩ ጉባኤ ምስጢሩን ሰውሮ አመለከተ። የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ይልቁንም በኢጣልያ አገር በኦፊሲዬል በተነገረው የዲስኩር ቃል እንደሚታየው የኢጣልያ መንግሥት ለጠብ ማሰቡ ምንም የማያጠራጥር ነው ሲል በየጊዜያቱ አስታወሰ።

ጠቡ ከተነሣ ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት ነገሩን በሰላም ለመጨረስ ፈለገ። በመንግሥታት ማኅበር ውል በተጻፈው ቃል ነገሩ እንዲታይ ጠየቀ። የኢጣልያ መንግሥት ግን በ1920 ዓ. ም. በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል በተደረገው ውል ቃል ብቻ ነገሩ እንዲታይ ስለ ፈቀደ የኢትዮጵያም መንግሥት ይህንኑ ተቀበለ። የሽምግልና ዳኞችም ነገሩን በመልካም ሳይፈርዱለት ቢቀሩ እንኳ ፍርዱን በመልካም ፈቃድ እፈጽማለሁ ብሎ አስታወቀ የሽምግልና ዳኞቹም ወልወል የማን ግዛት እንደ ሆነ ነገሩን እንዲያዩ ኢጣልያ ሳትፈቅድ ስለ ቀረች ኢትዮጵያ ይህንም ተቀበለች። ይህንም ነገር የሚመረምሩ ነፃ የሆኑ ሰዎች በአገሩ እንዲላኩ የምክሩ ጉባኤ ጠየቀ ። የምክሩ ጉባኤ በፈቀደው ዓይነት የቆረጠውን ምርመራ ለመቀበል የተዘጋጀ መሆኑን አስታወቀ። የኢጣልያ መንግሥት በበኩሉ የወልወል ነገር በሽማግሌዎች ታይቶ ካለቀ በኋላ የፈቀደውን ሥራ ለመሥራት እንዲችል ነፃነቱን ለመጠየቅ የማመልከቻውን ዝርዝር ለምክሩ ጉባኤ አቀረበ። ከኢትዮጵያ ጋራ ያለውን ነገር ሁሉ ለመጨረስ በማኅበሩ ውል የተጻፈውን ቃል ለማስፈጸም ብቻ የሚበጅ ነገር የለበትም ብሎ አስረገጠ። ደግሞ ለኢጣልያ ይህ ነገር ዋና የሕይወቱ ጥቅም ያለበት ስለሆነና ራሱን ለመጠበቅ ዋና መጀመሪያ የሚያስፈልገው ስለ ሆነ ተስፋውን በጭራሽ ከኢትዮጵያ ላይ ካላነሣና የራሱን ጥቅምና ቅኚ አገሩንም ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን ነገር ለማድረግ ሙሉ ነፃነቱን ካላገኘ በቀር ኢጣልያ ከሁሉ ያነሰ መጀመሪያ ማድረግ የሚገባውን ሥራ ማጉደል ይሆንበታል ብሎ አደላድሎ አስታወቀ።

የዐሥራ ሦስቱ መንግሥቶች ምክር ቤት ያቀረበው ራፖር ቃል ይህ ነው። የምክሩና ዋናውም የማኅበሩ ጉባኤ በአንድነት ሆነው «የኢጣልያ መንግሥት የማኅበሩን ውል ቃል ማፍረሱንና አጥቂ መሆኑን» በግልጥ አስታወቀ።

እኔም በግድ የመጣብኝን ጦርነት ለማድረግ አለመፈለጌን በየጊዜው ከማስታወቅ አላቋረጥሁም። የምዋጋውም የሕዝቤ ነፃነቱና የኢትዮጵያም ሙሉ ግዛት እንዳይነካባቸው በማለት ብቻ መሆኑንና በዚሁም ጦርነት የምከላከለው የታላቅ መንግሥቶች ጎረቤት የሆኑ ትንንሽ መንግሥቶች ሁሉ በኃይል አገራቸውን ለመውሰድ እንዳይችል የነርሱን ጉዳይ ጭምር ነው።

በ1928 ዓ. ም. በጥቅምት ወር ዛሬ የሚሰሙኝ 52ቱ መንግሥቶች «አጥቂው አያሸንፍም የሕግ መንግሥት እንዲኖርና እንዲጸና ከሕግ ተላልፎ በኃይል የሚሠራ ሥራ እንዲፈርስ በማኅበሩ ውል የተጻፈው ቃል ሁሉ እንዲፈጸም እናደርጋለን» ብለው ቃል ሰጥተውኝ ነበር።

በዓለም ሁሉ አጥቂነቱ ከተፈረደበት መንግሥት ሕዝቤ እንዲከላከል ያደረግሁት ፡ እምነቴን የገለጥሁት የዛሬ ስምንት ወር 52ቱ መንግሥቶች የተከተሉትን ፖለቲካ እኔም ተከትዬ ነውና ይህንኑ ፖለቲካቸውን እንዳይዘነጉት አሳስባለሁ።

ምንም የጦር መሣሪያዬ ከአጥቂው ያነሰ ቢሆን አይሮፕላን ፡ መድፍ ሌላም መሣሪያ የቀነሰለኛ ማሳከሚያ በጭራሽ ባይኖረኝ ተስፋዬ በመንግሥታት ማኅበር ውል ላይ ነበር። 52ቱ መንግሥቶች ከነዚሁም በዓለም የበለጡ ያሉባቸው በአንድ አጥቂ በሆነ መንግሥት ብቻ ሊሸነፉ የማይቻል ነው ብዬ አስብ ነበር። በውል ኃይል ተማም በአውሮጳ አንዳንድ ትንንሽ መንግሥቶች እንደ ደረሰባቸው ሁሉ ለጦርነት አልተዘጋጀሁም ነበር። አደጋው የሚያጣድፍ በሆነ ጊዜና በሕዝቤም ፊት ያለብኝ አላፊነት ሕሊናዬን የሚነካ ስለሆነ በ1928 ዓ.ም መሣሪያ ላማግኘት ሞከርሁ፤። ብዙ መንግሥቶችም እኔን ለመከልከል ሲሉ መሣሪያ ካገር እንዳይወጣ ከለከሉ። የኢጣልያ መንግሥት ግን በካናል ስዊስ በኩል መሣሪያና ጥይት ወታደርም ሳያቋርጥና ማንም ሳይከለክለው ለማስተላለፍ ችሎ ነበር። በመስከረም 23 ቀን የኢጣልያ ወታደር ግዛቱን አገሬን ወረረው ከጥቂት ሰዓት በኋላ ብቻ ወታደር እንዲሰበሰብ የክተት ዐዋጅ አደረግሁ። ሰላምን ጠብቆ ለመኖር በመፈለግ አሳብ በታላቁ ጦርነት ጊዜ ጦርነቱ ሊደርስ አቅራቢያ አንድታላቅ መንግሥት እንደ አደረገው ሁሉ በማናቸውም ምክንያት ጠብ ፈላጊነት እንዳይነሣ በማለት ወታደሮቹ 30 ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ኋላ እንዲመለሱ አደረግሁ። ከዚህም በኋላ ጦርነቱ ለምክሩ ጉባኤ እንዳመለከትሁት ሁሉ በታላቅ ግፍ ይቀጥል ጀመር።

በዚህ በማይወዳደር ጦርነት አርባ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ የሚገዛ የሚያስፈልገውንም መሣሪያና ገንዘብ ለማግኘት የሚችል የሰውን ሕይወት ለማጥፋት በያይነቱ የሆነ መሣሪያ ለመሥራት የቴክኒክ ጥበብ ሁሉ ያለው መንግሥት ያለ መሣሪያ ያለ ገንዘብ ትክክል ፍርድንና የነገሥታትን ማኅበር ቃል ብቻ ተማምኖ ከተቀመጠው ትንሽ ከሆነ ከ12 ሚሊዮን ሕዝብ ጋራ በተደረገው በዚህ በማይወዳደር ጦርነት የሮማ መንግሥት የማኅበሩን ውል አፍርሷል ተብሎ ከተፈረደና አጥቂውም እንዳያሸንፍ እንከላከላለን ከተባለ በኋላ ለኢትዮጵያ መንግሥት የተደረገው ያገኘውም እርዳታ እንደ ሌለ እናንተ ልትገምቱት ትችላላችሁ ።

በማኅበሩ ያለው አንዳንዱ መንግሥት ሁሉ በማኅበሩ ውል በ17ኛው ክፍል ተጽፎ የፈረመው ፊርማ እንደሚያዘው ሁሉ አጥቂው ያደረገው ጦርነት በያንዳንዱ ማኅበረተኛ ላይ በራሱ እንደተደረገበት ሁሉ ቆጥሮት የለምን?

ይህ ውል የተገባበት ቃል ይፈጸማል ብዬ ሙሉ ተስፋዬን በርሱ ላይ አድርጌ ነበር። ተስፋዬም ደግሞ አጥቂው ዋጋ አያገኝም ኃይልም በሕግ ፊት እንዲሸነፍ ይደረጋል ተብሎ በማኅበሩ ጉባኤ የተነገረው ቃል የሚያደላድል ተስፋ አግኝቶ ነበር።

በታኅሣሥ ወር 1928 ዓ. ም. ኢትዮጵያ እንድትከፋፈል ተብሎ የቀረበውን ድርድር በዓለም ሁሉ ያለው ብዙ መቶ ሚሊዮን የሚሆን ሰው እንደ ተቃወመው ሁሉ የምክሩም ጉባኤ አሳቡ ይህ ነው ሲል በግልጥ አስታውቆ ነበር። ብዙም ጊዜ «ይህ የተነሣው ጠብ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጠብ ብቻ አይደለም ጠቡ የኢጣልያ መንግሥትና የመንግሥታት ማኅበር ጠብ ነው» ተብሎ ተነግሮ ነበር።

እኔም ራሴ ሕዝቤም የመንግሥታት ማኅበርን ውል የሚያስወግድ ለራሴ ጥቅም የሚሆን ያቀረቡልኝን ድርድር ሁሉ አልቀበልም ብዬ መመለሴ ስለዚህ ነበር። እኔም የተከላከልሁት ለጥቃት የሚያሠጋውን የትንንሾች መንግሥቶች ጉዳይ ጨምሬ ነበር። እናደርግልሃለን ተብለው የተሰጡኝ ቃሎች ሁሉ ወዴት ደረሱ?

ከታኅሣሥ ወር 1928 ዓ. ም. ጀምሮ ሦስት መንግሥቶች በማኅበሩ ውል የገቡበትን ግዴታ ዋጋ እንደሌለው ሁሉ አድርገው በማየታቸው በታላቅ ኀዘን ተመለከትሁ። ከኢጣልያ ጋራ ያላቸው አገባብ ኢጣልያ በአጥቂነት ያደረገችውን ሥራ ለማቆም ማናቸውንም ነገር እንዳይቀበሉ አደረጋቸው።

ይልቁንም ደግሞ ለእኔ የተስፋዬን አሳብ የቆረጠብኝ ያንዳንዶቹ መንግሥቶች ሥራ ነው። እነዚሁም መንግሥቶች በመንግሥታት ማኅበር ላይ ያላቸውን እምነት ሳያቋርጡ እየተናገሩ የመንግሥታት ማኅበር ሕግ እንዳይፈጸም ደግሞ ሳያቋርጡ ይደክማሉ። አንዳንድ መንግሥቶች የአጥቂውን ሥራ በቶሎ የሚያስቀር ደኅና ነገር በቀረበ ጊዜ እንኳንስ ነገሩ እንዲፈጸምና ነገሩ ለክርክር እንዳይቀርብ በብዙ ምክንያት ያቆዩታል። በጥር ወር 1928 ዓ. ም. የተደረገው የምስጢር ውል ይህን የመሰናከል ሥራ አስቀድሞ ያመለከተ ኖሯልን?

የኢትዮጵያ መንግሥት በቀጥታ ጥቅማቸው ያልተነካባቸው ሌሎች መንግሥቶች የመንግሥታትን ማኅበር ውል ለመከላከል የወታደሮቻቸውን ደም ያፍስሱ ብሎ አልጠበቀም። የኢትዮጵያ ጦረኞች ጠይቀው የነበሩት ለመከላከያ የሚሆናቸውን ነገር ብቻ ነበር። ስለዚህም ብዙ ጊዜ መሣሪያ ለመግዣ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ጠይቄ ነበር። ይህንም እርዳታ ተከለከልሁ። በመንግሥታት ማኅበር ውል በ16ኛው ክፍል የተጻፈው ቃልና መንግሥቶች እየተባበሩ በመረዳዳት ጸጥታ እንዳይጠፋ ያደርጋሉ የተባለው የአፈጻጸሙ ትርጓሜ ምን ይሆን?

ከጅቡቲእስከ አዲስ አበባ ያለው የምድር ባቡር ለኢትዮጵያ የሚሆን መሣሪያ እንዲተላለፍበትና ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያገለግል በተጠየቀ ጊዜ መሣሪያው በዚያ በኩል እንዳይገባ ብዙ ችግር ተደረገ። ላሁኑ ሰዓት ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላገባብ ለገባው ለኢጣልያ ሠራዊት ዋና የሥንቅና የመሣሪያ ማመላለሻ ሆኗል። የገለልተኝነት (የነትራሊቴ) ደንብ እንኳ የኢጣልያ ወታደሮች እስካሉበት ድረስ ይህን የመሰለው ነገርእንዳይጫን ይከለክላል። ይህ ከሆነ የመንግሥታት ማኅበር ውል በ16ኛው ክፍል በተጻፈው ቃል ማኅበረተኞች የሆኑት መንግሥቶች ሁሉ አንድ መንግሥት ሌላውን በአጥቂነት የወጋው እንደ ሆነ ሌሎች ገለልተኛ መሆናቸው ቀርቶ መርዳት የሚገባቸው ለአጥቂው ሳይሆን ለተጠቂው ስለ ሆነ የነትራሊቴ ደንብ እዚህ መነሣት አይገባውም። በዚህ አኳኋን የመንግሥታት ማኅበር ውል ከዚህ ቀድሞ ተጠብቋልን ? ዛሬም እንደ ተጠበቀ ነው ለማለት ይቻላልን?

አሁን በመጨረሻው በመንግሥታት ማኅበር ታላቅ አገባብ ያላቸው ታላላቅ መንግሥቶች በምክር ቤታቸው አጥቂው የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መሬት አንዱን ክፍል ከያዘ በገንዘብ ጥቅም ረገድ ይህ እንዳይሆን ያቆምነውን መከላከያ መቀጠል አያስፈልግም ብለው አስታወቁ።

በአርጀንቲን መንግሥት ጥያቄ በአጥቂው በኢጣልያ ምክንያት የሆነውን ነገር ለመመርመር የተሰበሰበው የመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ ዛሬ በፊቱ የሚገኘው አኳኋን ይህ ሆነ።

ዛሬ የመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ በፊቱ ያለው ጉዳይ ኢጣልያ በአጥቂነት የሠራችውን ለመጨረስ ብቻ አይደለም። በሙሉ የዓለምን መንግሥታት የሚነካ መሆኑን አረጋግጬ አስታውቃለሁ። ይህም ጉዳይ ለዓለም ጸጥታ እንዲሆን መንግሥታት ለመረዳዳት የሚገባቸው የጋራ ጸጥታ (ሴኩሪቲ ኮሌክቲቭ) የተባለው የመንግሥታት ማኅበር ሕይወት የዓለም መንግሥቶች ለተዋዋሉት ውል መስጠት የሚገባቸው እምነት ትንንሾቹም መንግሥቶች አገራቸውና ነፃነታቸው እንዳይነካ የተቀበሉት ቃል ኪዳን የሚከበርበትና ዋጋው የሚገመትበት የመንግሥቶች ትክክልነት የተመሠረተበት መሠረት ይህን ለማጽናት ወይም ትንንሾች መንግሥቶች የኃይለኞች መንግሥቶች ተገዥ ለመሆን መቀበል ይገባቸውእንደ ሆነ ለመፍረድ ነው። በአጭር ቃል የተነካውና የተበደለው የዓለም ሕዝብ የተገባ አንዋወር ነው እንጂ ኢትዮጵያ ብቻ አይደለችም። በአንድ ውል ላይ የተፈረሙ ፊርማዎች ዋጋቸውን የሚያገኙት አንዱ በሌላው ላይ የግል ጥቅሙን በቀጥታና በፍጥነት ለማግኘት ለመፈጸምም እንዲችል እንዲረዱት ሲሆኑ ነውን?

በረቂቅ መንገድ መበላለጥ ዋናውን ነገር ሊለውጠው ወይም የክርክሩን መንገድ በሌላ በኩል ሊመራው አይገባም። ይህንም ማመልከቻ ለመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ የማቀርበው በእውነተኛነት ከልቤ ነው።

ከእግዚአብሔር መንግሥት በተቀር የፍጡር መንግሥት ሁሉ አንዱ ካንዱ የሚያበላልጥ ሥራ የለውም። ነገር ግን በምድር ላይ ኃይለኛ የሆነው መንግሥት ምንም በደል የሌለበትን የሌላውን መንግሥት ሕዝብ ለማጥፋት

የሚገባው መስሎት በተነሣበት ጊዜ ተጠቂው ወገን ለመንግሥታት ማኅበር የተበደለውን የሚቀርብበት ሰዓት ነው። እግዚአብሔርና ታሪክ ፡ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ።

ሕዝቤ ዘሩ ሊጠፋ በደረሰበት ፡ የመንግሥታት ማኅበርም እርዳታ ከጥፋት ለማዳን በሚችልበት ጊዜ ማናቸውንም ሳላስቀርና ሳላቆይ በተዛዋሪ ቃል ሳይሆን እውነቱን አውጥቼእንድናገር ሊፈቀድልኝ የተገባ ነው።

ከዚህ ቀድሞ የተደረገው ሳይበቃ የቀረው ሳንክሲዮን የታሰበውን ፍሬ አላፈራም ተብሎ በማረጋገጥ ቃል ሲነገር እሰማለሁ። በማናቸውም ጊዜ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን በፈቃድ እንደማይበቃ የተደረገና ደግሞ አፈጻጸሙ እንደሚገባ ያልሆነ ሳንክሲዮን አጥቂውን ለማቆም እንደማይችል የታወቀ ነው። አጥቂውን ሳናቆመው ቀረን ያሰኛል እንጂ የማይቻል ስለሆነ ነው ለማለት አይቻልም። ኢትዮጵያ በገንዘብ እርዳታ እንዲደረግላት ከዚህ ቀድሞ ጠየቀች። አሁንም ትጠይቃለች። ይኸስ ሊፈጸም የማይቻል ነውን?

የመንግሥታት ማኅበር ግን በሰላም ጊዜ እንኳ በአጥቂው ላይ ሳንክሲዮን አናደርግበትም ላሉ ለሌሎች መንግሥቶች በገንዘብ እርዳታ አድርጎላቸው ነበር። የኢጣልያ መንግሥት የጨካኝነት መሣሪያ እንዲያገለግለው በማድረጉ ብዙ ጊዜ እየደጋገመ የዓለምን መንግሥታት ሕግ ሁሉ በመተላለፉ ምክንያት ዛሬ ሳንክሲዮን ይነሣለት የሚል አሳብመታሰቡን ልቤ እጅግ እያዘነ ተመለከትሁ። ይህስ አደራረግና አሳብ ኢትዮጵያን አጥቂው መንግሥት የፈቀደውን ይፈጽምባት ብሎ መተው አይደለምን ? በመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ ፊት ለሕዝቤ በታላቅ ብርታት ለመከላከል ባቀረብሁበት ጊዜ ጥቂት ቀደም ብሎ ይህ አሳብ መታሰቡ የመንግሥታት ማኅበር ማኅበረተኞች ከሆኑት መንግሥቶች ኢትዮጵያ እርዳታንና መተማመኛን እንዳታገኝ አንደኛውን መጨረሻውን ዕድሏን የሚቆርጥባት አይደለምን ? የመንግሥታት ማኅበር ሥራ መሪ ለመሆን ሥልጣን ባላችሁ በታላላቅ መንግሥቶች እርዳታ የሚገኘው የመንግሥታት ማኅበርና ማኅበረተኞች በሚገባ ተስፋ አድርገው የሚጠብቁት ይህን የመሰለውን ፍጻሜ ነውን?

ኢጣልያ በአጥቂነት በሠራችው ሥራ ነገሩ እዚህ ቢደርስ የመንግሥታት ማኅበረተኞች የሆኑት መንግሥቶች የኃይለኛውን ፈቃድ በመፈጸም ምሳሌ ለመተው ፈቃዳቸው ይሆናልን?

የመንግሥታት ማኅበር ውል እንዲሻሻልና የመንግሥታት መረዳዳት የሚሰጠው መተማመኛ የተፈተነ እንዲሆን ለማድረግ ተብሎ በእርግጥ ለመንግሥታት ማኅበር ዋና ጉባኤ አሳብ መቅረቡ ነው። መለወጥ የሚገባው ውሉን ኖርዋልን ? ውሉን የፈረሙት በሙሉ የተጻፈውን ቃል ለመጠበቅ ፈቃዳቸው ካልሆነ ውሉ ቢለወጥስ እንዲጠበቅ ምን መተማመኛ ይገኛል ? የጐደለው ከዓለም መንግሥታት አሳብ ነው እንጂ ከመንግሥታት ማኅበር ውል አይደለም።

የመንግሥታት ማኅበረተኛ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ሆኜ የመንግሥታት ማኅበር ውል እንዲከበር የሚያስፈልገው ነገር እንዲፈጸም ጉባኤውን እጠይቃለሁ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከውል የተላለፈ ነገር ስለ ተደረገበት በዚሁ በተደረገበት ግፍ ምክንያት ከዚህ ቀድሞ ያቀረብሁትን መቃወም አሁንም እንደ ገና እቃወማለሁ። በዓለም ፊት ሆጄ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በኃይል የተደረገባቸውን ነገር አይቀበሉም ። ሥርዓት እንዲያሸንፍ የመንግሥታት ማኅበር ውል እንዲከበር የሚገባቸውም ሥልጣንና ግዛት እንዲመለስላቸው የሚቻላቸውን ነገር ሁሉ ማድረጋ .ቸውን እገልጣለሁ።

በተጠቃችሁ ጊዜ አጥቂ እንዳያሸንፋችሁ እንረዳችኋለን ብለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃልኪዳን የገቡት 52 መንግሥቶች ቃል ኪዳናቸውን አጽንተው እንዲረዱ እርዳታቸውን እጠይቃለሁ። ለኢትዮጵያ ምን ልታደርጉላት ትፈቅዳላችሁ?

ታናናሽ መንግሥቶች እንዳይጠፉ ፡ በኢትዮጵያ የደረሰባት ዕድል እንዳይደርስባቸው መንግሥቶች እንዲረዳዱ መተማመኛ ለማድረግ ቃል ኪዳን የገቡትም ታላላቅ መንግሥቶች የኢትዮጵያ ነፃነት እንዳይጠፋ ግዛቷም እንዲከበር ምን ዓይነት እርዳታ ለማድረግ አስባችኋል?

እዚህ የተሰበሰባችሁ የዓለም እንደራሴዎች ሆይ ፣ አንድ ንጉሠ ነገሥት በደረሰበት ኀዘን ማድረግ የሚገባውን ሥራውን ለመፈጸም ጄኔብ ወደ እናንተ መጥቻለሁ።

ለሕዝቤ ምን ምላሽ ልውሰድለት ?



በ1929 ዓ.ም አዘጋጅተነው የነበረው የሕይወት ታሪካችን በ1965 ዓ.ም በኅትመት ላይ እንዳለ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል በ1964 ዓ.ም አዘጋጅቶ ያቀረበልንን የንጉሥ ሣህለ ሥላሴን የዘር ሐረግ ተመልክተን ሕዝባችን እንዲያውቀ ውና የታሪክ ማስታወሻ እንዲሆነው በማሰብ ከዚህ መጽሐፍ ጋር እንዲወጣ ተደርጓል።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY